እሺ ከ1998 እስከ 2001 የኦነግ አባል ሆነው ሲንቀሳቀሱ ነበር ብለከናል

አዎ

እስቲ እንዴት አወቅህ ምንድነው እስቲ አንድ በአንድ ማለት ነው እከሌ እንዲህ እንዲህ አድርጓል እከሌ እንዲህ እንዲህ አድርጓል እያልክ ለይልን በጥቅሉ ---

አሁን አብዱራህማን ባሌ ለምሳሌ

እሹ እ

ተማሪዎችን በመቀስቀስ

እሺ

በትምህርት ቤት ውስጥ ቅስቀሳ ያካሂድ ነበር

የምን ቅስቀሳ ነውስ ያካሂድ የነበረው

ተማሪዎችን መቀስቀስ ነው መንግስት ላይ ማስነሳት ነው

እሺ እሺ አባል ሆኖ እሺ ጥሩ ሌሎቹስ እነ ሌንጂሳ ያልካቸውስ ሌንጂሳ ማለት ቅጥል ስሙ ነው 11ኛ ተከሣሽ ዙቤር ሁሴንን ነው

እሱ ዙቤር የኦነግ ሰራዊት ነበር

እሺ

መንግስት አስተምሮ ወደ እሱ ካመጣው በኋላ አሁንም ተመልሶ በእዛው እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጠለ ነው ከተማ ውስጥ ቁጭ ብሎ መንግስት ምህረት አድርጐ ካስተማረው በኋላም እንደገና ወደ እዛው እንቅስቃሴው ገባ ከተማ ውስጥ በመቀመጥ ነው

እሺ እሱን ሰራዊት ነው ብለከናል እሱ ሰራዊት ነው ብለከናል እስቲ እንዴት እንደሆነ ሰራዊት እንደሆነ ንገረን

እሱ መጀመሪያ ነው የኦነግ ሰራዊት የነበረው

እሺ ከእዛስ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

ወደ መንግስት ከተመለሰ በኋላ የኦነግ ሰራዊቶችን ወደ ከተማ ውስጥ ሰው እንዲገድሉ አስገብቶ ከሽጉጥ ጋር እሱ እቤት አገኘን

እቤቱ ምን አገኛችሁ

ሽጉጥ እሱ እቤት የኦነግ ሰራዊት የሆኑ ሰዎችን አስቀምጦ እያለ አሳርፎ እሱ እቤት እያሉ የመንግስትን አካል የሆኑ ሰዎችን ለመግደል ተዘጋጅተው እያሉ እዛ ነው የያዝናቸው እሱ የተያዘ ነው እነሱም ከተያዘ በኋላ ለእራሱም ሽጉጥ ገዝቶ ደብቆ አስቀምጦ እያለ ከእሱም ላይ ተገኝቷል ከእዛ በኋላ

እሺ ከማልሳ ከማል አልይ

እሱም ከማልም በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች በመንግስት ላይ ተቃውሞ እንዲያነሱ ያደርግ ነበረ ነው አንድ አንድ በከተማ ውስጥም የሚፈፅማቸው ተግባሮች ነበሩ ለምሳሌ ያህል ልጆችን በመሰብሰብ ይቀሰቅስ ነበረ ተቃውሞ እንዲወጡ ከእዛ በኋላ ሲታወቅበት ሲደረስበት ጠፍቶ ወደ ሰራዊት ተቀላቀለ የኦነግ ሰራዊት ውስጥ ተቀላቀለ ተኩስም ተከፍቶ ነው ይሄ ሰው በቁጥጥር ስር ሊውል የቻለው

መቼ ነው በቁጥጥር ስር የዋለው

የማስታውሰው 2001 ይመስለኛል ነው

እሺ ጥሩ ኢብራሂም ደረሳስ ያልከው 14ኛ ተከሣሽ

አብዱራህማን ባሌ እና ኢብራሂም ሁሴን ሚኒሻውን ተከትለው በድንጋይ መተው መሳሪያውን ለመንጠቅ ሲሉ እሱም በኦነግ ሰራዊት አባልነት ተደራጅቶ ነበረ የሚንቀሳቀስ የነበረው ነው እሱም ከእዛ በኋላ ወደ ኦነግ ሰራዊት ውስጥ ተቀላቅሎ መከላከያ ሰራዊት በተረገ እንትን ነው የተያዘው

በስንት ዓ/ም ነው የተያዘው

2001 ጥር ውስጥ ይመስለኛል

በቃን

አበቃችሁ

አዎ

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እሺ ምስክር ጊዜው ከ1998 እስከ 2001 ዓ/ም ነው ብለዋል ይሄ በሁሉም ተከሣሾች ላይ ነው

እነሱ በተለያየ ጊዜ ነው በዛን ወቅት በተለያየ ጊዜ ነው

ይሄ ጊዜ ከ1998 እስከ 2001 ዓ/ም ድረስ ያሉትን በእርግጠኝነት እንዴት ሊያውቁት ቻሉ

እኔ በከተማው አስተዳደር ነበርኩ በዛን ጊዜ የከተማው አስተዳደር ነበርኩኝ

የከተማው አስተዳደር በመሆንዎት ባለዎት የስራ ሀላፊነት ምክንያት እያንዳንዲ የከተማው ነዋሪ ከመቼ ጀምሮ እዛ ውስጥ አባል እንደሚሆን ማወቅ ይችላሉ እንዴ

እነሱ የእነሱን በእዚህ ጊዜ ውስጥ እንደሆነ እንቅስቃሴያቸውን አውቃለሁ

እሺ አውቃለሁ ብለዋል ሌላ ጥያቄ ካለ አማክሯቸውና

እኮ በምን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ ነው እያንዳንዱን እዛ ከተማ ውስጥ የሚኖርን ሰው ---- እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ ነው

ሁሉንም ሳይሆን እነሱን አውቃቸዋለሁ ነው የመንግስት ስራ እንደምሰራ በሰላም ጉዳይም ስለምንሰራ ስራችን ስለሆነ በዚህ አውቃቸዋለሁ

እሺ ሌላ ጥያቄ ካለ በመንግስት ስራ የሰላም ስራም ጨምሬ ስለምሰራ በዚህ ምክንያት አወኩ ብለዋል ሌላ ጥያቄ ካለ

እሺ ሌላ ጥያቄ በምስክርነት ውስጥ ሲናገሩ ት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች በመንግስት ላይ እንዲያምፁ ቅስቀሳ ሲያደርግ ነበር ያሉት ተከሣሽ አለ እርሶ ሲቀሰቅስ ሰምተዋል አይተዋል

አዎ

ምን ሰምቻለሁ አይቻለሁ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

629

ሰምቻለሁ ነው

እንደዛ እንደሚያደርጉ ሰምተዋል

አዎ

እሺ ሌንጂሳን በተመለከተ ትጥቅ ነበረው

ዙቤር ነው

አዎ ዙቤር

ከእሱ እቤት ሽጉጥ ተገኝቶ ተወስዷል ነው

እና ሽጉጥ ተገኝቶ ተወስዷል ---

ከእሱ እቤት ሽጉጥ ተገኝቶ ተወስዷል

እሺ ከማልን በተመለከተ ከማል በወቅቱ በ2001 ዓ/ም ሲያዝ የት ነው የተያዘው ያስታውሳሉ

ሊደጋል ሉላ ወረዳ ውስጥ ነው

ከተማ ውስጥ ነው ጫካ

በጦርነት ላይ ነው የተያዘው ነው

አብዱራህማንስ

እሱ ወደ ጫካ አልገባም ነበረ

ከተማ ውስጥ ነበረ የሚኖረው እዛ እረበሽ ከተባለበትስ በኋላ የት ነበር ያውቃሉ ወይ

እሱም እዛው ከተማ ውስጥ ሆኖ ሳይታወቅ እንቅስቃሴዎችን ያደርግ ነበረ ነው

ጥሩ አሁን አብዱራህማን የተባለው አብዱራህማን ባሌ ነው ወይ

አዎ

እሺ ጥያቄ ይቀጥል

628

ስለዚህ እርሶ የኦነግ አባላት ወይንም ታጣቂዎች የነበሩትን ሰዎች ያረጋገጡበት መንገድ ለምሳሌ አብዱራህማንን ስናይ በውስጥ ለውስጥ ይንቀሳቀስ ነበር እንጂ የተመዘገበ ሰነድ ወይንስ በእጁ ገንዘብ ሲቀበል ሲቀሰቅስ ሲያደራጅ እርሶ በቀጥታ አይተዋል ወይ የከተማ አስተዳደር በነበሩበት

እንዴ መናገር የያዝኩትን ነገር እየተናገርኩ ያለሁት ነገር እኔ ሁሉንም ከአፋቸው ነው የሰማሁት ምርመራ ስላደረኩላቸው እኔ ስለመረመርኳቸው

እሺ እንጂ ሲንቀሳቀሱ አላይዋቸውም እርሶ

እነሱም አይገኙም በእዛን ሰአት በድብቅ ነው የሚንቀሳቀሱት ነው የሚለው

ስለዚህ በግልፅ የሚያውቁት ነገር የለም ማለት ነው

በአይኔ አላየሁም እንጂ ይሄንን ነገር እንደሚፈፅሙ አውቃለሁ

ጨርሻለሁ ጨርሻለሁ

እሺ ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ አለ ጥያቄ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

ሰምቻለሁ ነው ያሉን አብዛኛውን ነገር አሁን ለምሳሌ ቅድም ሌንጂሳ የሚባለው ወይም ዙቤር ሽጉጥ ተገኝቶበታል ብለዋል ይሄንን በአይንዎት መገኘቱን አይተዋል ያውቃሉ ወይንስ በመስማት ብቻ ነው

እኛን ደብቆን ሰራዊት አብሮት ሄዶ ከደበቀበት በኋላ ውስጥ ነው ያስወጡት ነው

እ

ያንን ካስቀመጠበት ቦታ ነው ያስወጡት ፖሊሶች ሄደው ነው

እሺ እርሶ ነበሩ ወይንስ ፖሊሶች ብቻ ናቸው ሄደው ያወጡት

የለሁም ሰማሁ እንጂ እኔ

እሺ በቃ ጨርሻለሁ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

የለሁም እኔ ሰማሁ እንጂ

አበቃችሁ የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ እሺ እርሶ እናመሰግንዎታለን መሄድ ይችላሉ ጨርሰዋል ማን ይጠራ ዐ/ሕግ

ኢብራሂም አሜ 58ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

በስንተኛ ላይ ነው 58ኛው ምስክር

በ1ኛ በ11ኛ በ5ኛ በ14ኛ እና በ -----

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ኢብራሂም አሜ

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ

ለምስክርነት ነው የቀረብከው

አዎ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ሌንጂሳ

እ

ሌንጂሳ ቦኬ

ስንተኛ ማለት ነው

11ኛ ተከሣሽ ዙቤር

እሺ ሌላስ

ከማል አልይ

እሺ ሌላ

630

ደረሳ

ደረሳ 14ኛ ነው

ሌላ

ባሌ ነው የሚለው

እሺ በእነሱ ላይ ነው የምትመሰክረው

አዎ በእነዚህ ላይ ነው

ፀብ ዝምድና አለህ ከእነሱ ጋር

የለኝም

እስቲ ካለ እዚህ ውስጥ አሳየን ተነሳ እና ከዚህ ወዲያ ለይ የለውን እሺ 1ኛ የዐ/ሕግ ተከሣሽን አሳይቷል እሺ 14ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል 5ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ማነው ስምህ ዙቤር 11ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ና ተቀመጥ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ ኢብራሂም እነዚህ 4ቱ የለየካቸው ሰዎች እስቲ ምን ልታስረዳ ነው የመጣከው እስቲ ንገረን ከጊዜው ጀምረህ ምን እንዳደረጉ ንገረን

በሌንጂሳ ላይ ምስክርነት ቃሉን የማውቀው እሱ ቀብሮ የነበረውን ሽጉጥ ፖሊስ አውጥቶ ይዞ ሲሄድ አይቻለሁ

ምንድነው ሌንጂሳ ምንድነው የሚሰራው ምን ነበረ መቼ ነው ጊዜውስ

የኦነግ አባል መሆኑን አውቃለሁ

እሺ

የኦነግ አባል መሆኑን ታውቃለህ ከመቼ እስከ መቼ

98 ከእዛ በፊት የኦነግ ሰራዊት ሆኖ እንደነበረ አውቃለሁ ግን 98 ያየሁት ይሄንን ነገር ነው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቂጥር

631

እሺ የት አካባቢ ነው

ጉሎዳ ነው

ጉሎዳ ማለት የት ነው ያለው

አረዳ ጀቤል የሚባለው ቀበሌ ውስጥ ነው ሽጉጡን እንዲያወጣ የደረጉት ፖሊሶች ሄደው እዛ ድረስ ነው ያስወጡት

እሺ ሽጉጡ እሺ ይሄ ሴንጂሳ የተባለው ላይ ሽጉጥ መያዙን አውቃለሁ የአባዎ ወይንም የኦነግ አባል ነበረ ብለከናል መቼ ነው በቁጥጥር ስር የዋለው መቼ እንደሆነ ታውቃለህ

የዛኑ ጊዜ ነው የተያዘው ነው እሱን ይዘውት ነው ሽጉጡን ለማስወጣት

ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል ከተያዘ

እኔ ያየሁት ይሄንን ቀን ነው የዛን ቀን የሆነውን ነገር ከእዛን በፊት ያለውን ግን በጆሮዬ ሰማሁ እንጂ አላውቅም ነው አላየሁም

ምንድነው የሰማከው በጆሮህ

እሱ እና ሌላ ሰው ሆነው እያለ ከእሱ ጓደኛ ጋር ሽጉጥ መያዙን ነው የማውቀው የሰማሁት ይሄንን ሰማሁ ይሄንን

እሺ ሌሎቹስ ላይ ሌሎቹ ላይ ማለት አብዱራህማን ባሴ ላይ ከማል አልይ ላይ እና ኢብራሂም ደረሳ ላይ የምታውቀው

ማለት እነሱ በትምህርት ቤት ውስጥ እንቅስቃሴ እያደረጉ እያለ ከሰው ጋር ተጣልተው ከእሱም ተከትለው ለመደብደብ በሚሄዱበት ሰአት ጥይት ተተኩሶ ከጠፋ በኋላ መጣን እኛ ሰምተን ስንመጣም አጣናቸው ከእዛን በኋላ ጠንከር ያለ ፍለጋ አሰሳ አድርገን አገኘናቸው እና እንዲያዙ ከፖሊስ ጋር ይዘን እስር ቤት ወስደናቸዋል ነው

እሺ ኢብራሂም ሁሴን ወይንም ደግሞ ኢብራሂም ደረሳ የት ነው የተያዘው

እዛው ከተማ ውስጥ ነው

የዛን ጊዜ ከእዛ ከተማ ተይዞ ነው ወደ እዚህ ያመጣው ከእዛ በኋላ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

632

ከእዛ በፊት ፍ/ቤት ቀርቦ ፍርድ አጊኝቶ ከእዛ በኂላ እንደገና ወጥቶ ነው ወደ ኦነግ ሰራዊት የሄደው

እሺ ከእዛ ወደ ኦነግ ሰራዊት ሄደ ወደ ኦነግ ሰራዊት ከሄደ በኂላ መቼ እንደተያዘ ታውቃለህ ወይ

ከእዛ በኂላ ከኦነግ ሰራዊት ከተያዘም በኂላ ታስሮ ተለቆ እንደገና ወደ መንደር ገባ ነው እኔ ይሄንን ነው የማውቀው

እሺ እ ከማል አልይሳ

በእዛ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ ተነስቶ ያ ሰራዊት የኦነግ ሰራዊት ውስጥ ገብቶ ሲንቀሳቀስ ተይዞ መያዙን አውቃለሁ ነው

እሺ አብዱራህማን ባሌስ

አብዱራህማን ባሌም ታስሮ ተፈቷል ከእዛ በኂላ 2ኛ ምን አድርጐ እንደገባ እኔ የማውቀው ነገር የለም ይሄንን ነው የማውቀው እኔ

በቃ እሺ ጨርሻለሁ

አበቃችሁ

አዎ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ለተከላካይ ጠበቃው

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ማንን ነበረ ፍርድ ተፈርዶበታል ያሉኝ

ደረሳ እና ባሌ ፍ/ቤት ቀርበው አውቃለሁ ነው

ዐ/ሕግ ስንት ይቀራል ከአሁን በኂላ

ከአሁን በኂላ ---

ምን አሉኝ አልሰማዎትም

633

ደረሳ እና ባሌ ፍ/ቤት ቀርበው አውቃለሁ

ደረሳ ከእዛ ምን ሆነ ፍ/ቤት ከቀረበ

አዎ ተቀጣ

አሁን በሚሉን በ1998 ዓ/ም አስነሱት በሚሉት ጉዳይ ነው እንዴ የተቀጡት

በእዛ ነው የተቀጣው በእዛ ጉዳይ

በ1998 -----

አዎ

እርሶ መስክረው -----

አዎ

እሺ አብዱራህማን ሲያዝ እንዴት ነው ያውቃሉ የት እንደተያዘ

አዎ አውቃለሁ እዛው ከተማ ውስጥ ነው

እዛው ከተማው ውስጥ ነው

አዎ

ከማልስ

ከማል በእዛን ወቅት ፈልገን አጣነው እሱን ፈልገው አጣነው አለ

በኋላ ----- ነው እንዴ ይሄ ---

እኔ ሰማሁ እንጂ በጆሮዬ ከሰው ያመዩ የሚባል ቦታ ተያዘ ሲባል ሰምቻለሁ

እንጂ የት እንደተያዘ አያውቁም

አላውቅም

ዙቤርን በተመለከተ በእዛን ወቅት ሽጉጥ እንደነበረው ያውቃሉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

እሺ እኔ በእሱ ከእዛ በፊት ሽጉጥ ይኑረው አይኑረው የማውቀው ነገር የለም ነበር ግን ከእዛ በፊት ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ተይዘው ከአንድ ሰው ጋር ሽጉጥ ተገኝቶባቸው 2ቱም ታስረው እሱም ተፈቶ ወደ እቤት እንደገባ አውቃለሁ ከእዛ በኋላ ደግሞ ኢንፎርሜሽን ደርሷቸው ይሁን አላውቅም ከዚህ ጀምሮ የመጣ ፌደራል ፖሊስ የተላከ እዛ ድረስ መጥቶ ይዞት እሱን ሽጉጡን አስወጥቶታል ነው የሚለው

ስለዚህ አሁን እርሶ በሚመሰክሩበት ጉዳይ ላይ እዛው ፍ/ቤት ላይ ጉዳያቸው ሲታይ እርሶም ምስክር ነበሩ ወይ ነው

እኔ ፍ/ቤት አልቀረብኩም ፖሊስ ጋር ነው ቃሌን የሰጠሁት

ፖሊስ ጋር ኦኬ

በዚሁ ጉዳይ አዎ

ከእዛ በኋላ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ እነ አብዱራህማንን ሌሎቹንም እዛው ከተማ ውስጥ ያገኝዋቸው ነበር

አዎ እዛው ነበሩ ከተማ ውስጥ

ስለዚህ እዛው ከተማ ውስጥ ሲኖሩ ታዲያ ችግር ይፈጥሩ ነበር እንዴ እነሱ እዛ ከተማ ውስጥ

በትምህርት ቤቱ የተደረገው ቅስቀሳ ምክንያት ነው ተይዘው ፍ/ቤት የቀረቡት

እንጂ ከእዛ ውጪ ምንም አይነት ችግር እዛ ከተማ ውስጥ --- ነበር ወይ

በቃ ከዚህ ውጪ የማውቀው ነገር የለም

ከእዛ ውጪ በሰላማዊ በመንግስት ላይ ሲያነሳሱም አይተው አያውቁም

ከዚህ ውጪ ምንም ነገር እኔ ሲፈፅሙ አላየሁም ነው

እሹ ጨርሻለሁ

ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ አላችሁ

የለንም

635

ድጋሜ ጥያቄ የለም እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግንሀለን መሄድ ይችላሉ ቀጣይ ምስክር ማን ይጠራላችሁ

70ኛ የዐ/ሕግ ምስክር መሀመድ ኢብራሂም

መሀመድ ኢብራሂምን ጥሩ በስንተኛው ላይ ነው

በ26ኛ ተከሣሽ ላይ ነው

በ25ኛ

በ26ኛ

ምስክሩ መሀሳ ፊፅመዋል እሺ ወደ ፊት ይምጡ እና ይቀመጡ እስቲ እጅህን አውርድ ባክህ ምን ሆነህ ነው እስቲ ፖሊሶች አስተናግዱዋ ይሄ እኮ ለፍ/ቤቱም መቅረብ የለበትም እያያችሁ እንትን ማድረግ ትችላላችሁ

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - መሀመድ አብራሂም

አድራሻ - ከወተር

ለምስክርነት ነው የቀረቡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

አብዲ አመኑር

አብዲ

አመኑር

አህመድ ኑር ጥረ ፀብ ዝምድና አለዎት ከእርሱ ጋር

የለኝም

636

ቢያዩት ያውቁታል እስቲ ይለያሉ እዚህ ውስጥ ተነሱ እና እዩት አብዲን አሳዩን ማነው ስምህ በለው አብዲ አህመድ ኑር እሺ 26ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ መሀመድ አማርኛ አይችሉም እንዴ

እችላለሁ ትንሽ ትንሽ

ትንሽ ትንሽ ስላሉ በአስተርጓሚ

እሺ ቀጥል ዛሬ ምንድነው በ

ቆይ እስቲ ዐ/ሕግ አንዴ

አማርኛ በደንብ ትችላለህ

አይ ትንሽ ትንሽ ነው

አዎ ትንሽ ትንሽ አሉ ስለዚህ በቋንቋው ይሻላል በሚያውቀው

እሺ እሺ በአስተርጓሚ እንቀጥላለን

በአስተርጓሚ

26ኛ ተከሣሽን ለይተውልናል እና እስቲ ምን አድርጐ ነው የተከሰሰው በምንድነው የሚያቁት እስቲ ያስረዱልን ለፍ/ቤቱ

እኔ በእዛ ቀበሌ በሀገራችን ውስጥ ተጠሪ ነበርኩኝ በ98 ዓ/ም እሱ ተከሣሹ ጠፍቷል ብለን ወረቀት ፅፈን ለአስተዳደር አቅርበን ነበረ ከእዛ በፊት እንቅስቃሴ ውስጥ ነበረ ነው

በምን እንቅስቃሴ ውስጥ ነበረ ከእዛ በፊት

ተቃዋሚ ነበረ የመንግስት

ምንድነው ተቃዋሚ ማለት ምንድነው ተቃዋሚ ዓለፀው

837

ይሄ መንግስት ልክ አይደለም ይሄንን መንግስት አንደግፍም ይል ነበረ

እሺ እያለ በምን እንቅስቃሴ ውስጥ ነበር ያለው ይሄንን መንግስት አንደግፍም እያለ

በ97 ዓ/ም እንደ እሱ አይነት ወጣቶችን በመሰብሰብ አንድ ላይ እንቅስቃሴ ያደርግ ነበረ ነው

አንድ ላይ 97 ላይ እንደ-- ወጣቶችን በማሰባሰብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የምን እንቅስቃሴ ነበረ

ሰይፍ ይዞ ነበረ

እ

ሚኒሻዎች ሰይፍ ታጥቆ ነበረ ነው እንግዲህ

እሺ

እና ሚኒሻዎችን አንዳንድ የመንግስት አካላቶችን ይቃወም ነበረ ያጠቃ ነበረ እና እሱንም ለ

በምንድነው የሚያጠቃው

በእጅ ምንም የፈፀመ ነገር የለም በሀሳብ በሀሳብ በሀሳብ ይንቀሳቀስ ነበረ ይሄንን መንግስትን ይቃወም ነበረ

እኮ ይሄንን መንግስት የሚቃወመው በምን አይነት መልኩ ነው በዚህ በዚህ መልኩ ይሄንን መንግስት ይቃወም ብለህ ---

እሱ ሰዎችን ሰብስቦ አንድ እቤት ውስጥ በመቃም መነጋገር ነው በየሀገሩ

እሺ ቆይ ኤው መንግስትን ይቃወማል ብለከናል ምን እያደረገ ነው ምን እያለ ነው የሚቃወመው ንገረን

የኦነግን ሰራዊት ሀሳብ ይደግፍ ነበረ ነው

እሺ የኦነግን ሰራዊት ሀሳብ ይደግፍ ነበረ

አዎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

638

የቱ የእናንተ አካባቢ እሱ የነበረበት ቦታ የት ነው ምን ይባላል ስሙ እ ወተር

ወተር ይባላል ነው

የት አካባቢ ነው ይሄ ወተር ያልነው የት በምን ዞን ስር ነው ያለው

በዚሁ በሀረርጌ ውስጥ ነው

እሺ በሀረርጌ ዞን ምን ምስራቅ ምእራብ

ምስራቅ ሀረርጌ

እሺ ምስራቅ ሀረርጌ ውስጥ ያለነው ብለከናል ይሄ ወተር እዛ ነበረ የሚኖረው ብለካል እሺ ከእዛ ለአስተዳደር ጠፋ ብለን ፃፍን ያልከው ነገር አለ ወዴት ሄዶ ነው የጠፋው

ወደ ኦነግ ገባ ተቀላቀለ

ወደ ኦነግ ምንድነው የገባው

የኦነግረ ሰራዊት ነው የሆነው

የኦነግ ሰራዊት ሆነ

አዎ

ከእዛስ

ከእዛ በኋላ ከእዛ ወጥቶ በፊት ወፍጮ ይፈጭ ነበረ እዛ ለሚፈጭለት ሰውዬ ጋር ሄዶ ተቀመጠ ያንን መረጃ ደረሰን እና ሄደን መረጃ ሲደርሰን እኔ እና አንድ ፖሊስ ሆነን ይዘን ለ ወረዳው አስተላለፍነው

መቼ ነው የያዛችሁት

98 99 መሀል ነው ቀኑን በትክክል አላስታውሰውም

አሁን ስንት አመተ ምህረት ላይ እንዳለን ታውቃለህ ወይ

2002 ነው

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ከእዛ በኂላ እንዳስረከብነው መንግስትም ተቀበለና ተሀድሶ ሰጥቶት ካስተማረው በኂላ መልሶ እንደገና ለቀቀው ተመለሰ ገባ

ወዴት ገባ

ወደ ሀገር ገባ

እሺ ከእዛስ

ያው ያርስ ነበረ ነው ከእዛ በኂላ

እ

በእርሻ ስራ ይሰማራ ነበር

ከመቼ ጀምሮ ነው በእርሻ ስራ ሲሰማራ የምታውቀው

መሬት ሲቆፍር ነበረ ያርስ ነበረ ቀኑን ደግሞ አላስታውሰውም

መቼ ነው ተሀድሶ የወሰደበትን ጊዜ ታውቃለህ ወይ

2000 ይሁን እኔ ቀኑን አላስታውሰውም ተሀድሶ የወሰደበትን

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እርሶ በምን ሀላፊነትዎት ነው ሪፖርት ያደረጉት

እኔ የእዛ ሰራዊት አባል ነኝ ሚኒሻ ነኝ

እሺ እርሱ በሀሳብ የኦነግን ሰራዊት እንደሚደግፍ አውቅ ነበረ ጫት እየቃመ ያወሩ ነበረ ብለዋል እርሶ ነበሩ እንዴ እዛ ሲቅሙ አብረንው

አዎ እዛ ሄጄ ልቹን መክሬያቸው ምንድነው እናንተ የምትፈልጉት እንዲህ አይነት ነገር ጥሩ አይደለም ተው ብዬ የያዘውን ቢላዋ የያዙትን ቢላዋ ተቀብዬ መጥቻለሁ ነው መክሬያቸው

እሺ በወቅቱ በሚያዝ ሰአት እርሶ ነበሩ እንዴ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

640

እኔ ነኝ የያዝኩት

ምን እየሰራ ነበር

ሰው እቤት ነበረ ሰው ጋር ቁጭ ብሎ የነበረው ከእሱ ሰውዬ ጋር በፊት ይተዋወቁ ነበረ ወፍጮ ይፈጭለት ነበረ

ስለዚህ በሰላማዊ ሁኔታ ሆኖ ነው ያገኙት ስራ ላይ ሆኖ

አዎ ከእዛ ከሰራዊት ከተመለሰ በኋላ እዛ ፈዲስ እሱ ጋር ነው ተደብቆ ነው ያለው

ተደብቆ ማለት ምን ማለት ነው

ተደብቆ ነው ያለው

እኮ ይደበቅ አይደበቅ በምን አወቁ እርሶ ሰው እቤት አይደለ እንዴ ቁጭ ያለው ተመልሶ ወፍጮ የሚፈጭበት የሚያውቀው ሰው እቤት ነበረ ብለዋል ያ ደግሞ ማለት ሰው እቤት ቁጭ ማለት መደበቅ ነው ማለት አይደለም እንዴት አወቁ

መጀመሪያም ጋራ ስለገባ ጫካ ከእዛም ጠፍቶ ስለመጣ እሱም ስለሚያውቅ ነው ጫካ መግባቱን እና ለእዛ ነው እዛ የሄደው

በምን አወቁ እርሶ ጫካ መግባት አለመግባቱን

አውቃለሁ አውቃለሁ ብለዋል

ሌላ ጥያቄ

አራት ልጆች ናቸው ከእርሱ ጋር አብረውት ተነጋግረው ብቻውን አይደለም ተነጋግረው ነው ጫካ የገቡት

መንግስት ተሀድሶ ከሰጣቸው በኋላ ሌሎች ሰዎች ምንድነው የሚያደርጉት በእናንተ እናነተ ጋር አሁን ባለው በስራዎት በሀሪ መንግስት ጫካ የሚገቡትን ልጆች መልሶ ተሀድሶ ያስገባል ከእዛ በኋላ ምንድነው የሚሆነው

በሰላም ይሰራሉ

ስለዚህ እርሶም ሲያገኙት ጫካ ገብቶ ተሀድሶ ገብቶ ከወጣ በኋላ በሰላማዊ ህይወት ይኖር ነበረ ሌላ የሰራው -- አለ

አዎ

የሰራው ነገር የለም ከእዛ በኋላ

ምንም የማውቀው ነገር የለም

ጨርሰናል

እሺ ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ

የለንም

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ

የታሀድሶ ጊዜ እና ዓ/ምቱን ታስታውሳለህ አታስታውሰውም

2000 ሳይሆን አይቀርም

ታስታውሳለህ አታስታውስም

አላስታውስም

በግምትስ በግምት እሺ

ከዛ በኋላ አሁን የማውቀው ነገር የለም

እሺ እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ ቀሪ ማን ነው ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር ማን እንመዝግብ

ቀጣይ 29ኛ ምስክር ኡስማን አደም

ኡስማን አደምን ጥሩ በስንተኛው ላይ ነው

የሚመሰክረው በ9ኛ፣ በ15ኛ፣ በ22ኛ፣ በ25ኛ፣ በ29ኛ፣ እና በ30ኛ ተከሳሾች ላይ

መሀላ አስፈጽሙ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ብዝ

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ፡፡

አማርኛ ይችላሉ እንዴ

አዎ

በደንብ

አዎ

በደንብ ይችላሉ

አዎ

እሺ ጥሩ

29ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ኡስማን አደም

አድራሻ- አወዳይ

ለምስክርነት ነው የቀረቡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

በእነ ጀማል

ሌላ

እና ኪሚያ

እሺ ሌላ

ሌላ ስማቸውን ጠፋብኝ እንጂ አውቃቸዋለሁ ሳይ

ሁለቱን ግን ስም ያስታውሳሉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ጀማል ሁለት ጀማል አለ

ጥሩ እስኪ ይነሱና መጀመሪያ የሚያውቁትን ይለዩልናል ለምስክርነት የመጡበትን ጉዳይ ካሉት መሀል ረጋ ብለው እሺ ብድግ በሉ ብድግ በይ ጥሩ አሁን መለየት ከቻላችሁት ጋር ፀብ ዝምድና አሎት እንዴ

የለኝም

የሎትም እስቲ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ ኡስማን ከእነዚህ ከሁለቱ ሌላ የሚያውቋቸው የሉም እዚህ ውስጥ ከወንዶችም ከሴቶችም

አሁን ጊዜው እንትን ስለሆነ ጠፉብኝ እንጂ እዚህ ውስጥ ሳያቸው አሁን አላየሁም

በደንብ እዩዋቸው እስቲ ስማቸውን ያስታወሷቸውን ሰዎች አወጧቸው አነሷቸው

ጀማልም ይኸው

የት አለ ጀማል እሺ እሷስ ማን ናት

እሷ ስሟ ነው እኮ የጠፋብኝ የአባቷን ስም አውቃለሁ

ጥሩ ቅድም በስም የለዩልንን ሰዎች ከዚህ ውስጥ ያውጧቸው ቅድም ስማቸውን የጠሯቸውን ሰዎች

ቆይ ቆይ ዐ/ህግ በስም ለማስታወስ ይቸግረኛል ባያቸው የተወሰኑትን አስታውሳለሁ ብለው የሚያውቁትን ለይተዋል ከዚህ መሀል ሌሎቹን መለየት አልቻሉም እንዴ የሚያውቁትን ሰው ተቸግረዋል

ትንሽ

ማየት ችግር አለበት

አዎ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

6114

እሺ. ስለዚህ

ቅድም በስም ብለው ሁለት ሰው ሁለት ጀማል አለ ብለው ከዛ ደግሞ ሌላም ስም ጠርተውልናል እነዛን ሁለት ጀማል ስላሉ እሳቸው ቅድም ሁለት ጀማሎች አሉ ስላሉን እንዲለዩልን ለማድረግ ነው

መለየት ይችላሉ ጀማሎችን

አይቼ ነው እኮ መለየት አቃተኝ

መለየት አቃቶት

አዎ

ጥሩ

እሺ. በስምስ ሁለት ጀማል አሉ ብለውናል ስማቸውን እስከነአባታቸው ጥሩልን

ጀማል ከድር ጀማል ሀምዛ

ጀማል ከድርና ጀማል ሀምዛ

አዎ

እሺ. ጀማል ከድር ጀማል ሀምዛ

ጀማል ከድር ጀማል ሀምዛ ነው ያሉት

አዎ

ጀማል ከድርና ጀማል ሀምዛ አሉ

እሺ. ሌላ

ሌላ በስም የሚያስታውሱት

ስራቸውን ነው እንጂ ከዛ ላይ ካለ ስም ብትጠራቸው እኔ ምንም ችግር የለም መጀመሪያ የሰጣቸው ቃል ምንም------------ የለም

የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ቁጥር 4 ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

645

እሺ ይቀጥሉ ጥያቄ

እሺ አሁን ሁለቱ ያስቆሟቸው አሉ ከዛ ደግሞ ሁለት ጀማሎች አሉ ብለውናል እስቲ በእሱ ላይ የሚያውቁትን ይንገሩን ምንድን ነው ያደረጉት

እነሱ የኦነግ ደጋፊ መሆናቸውን አውቃለሁ

ከመቼ ጀምሮ

ከ1999 እስከ 2000 አውቃቸዋለሁ

ከ1999 እስከ 2000 ድረስ አውቃቸዋለሁ ብለዋል

አዎ

የት አካባቢ ነው የሚያውቋቸው

አወዳይ

እስቲ የኦነግ አባል ናቸው ብለውናል ምን ነበር የሚያደርጉት

እዛ እኛ -------- ቅስቀሳ ምናምን ነገር ያደርጋሉ

ምን እያሉ ነበር የሚቀሰቅሱት

እነዚህ እኛ ኦፒዲዮ ጀሌዎች ናቸው

የኦፒዲዮ

ጀሎዎች

እሺ ማንን ነው እንደዚህ የሚሉት የኦፒዲዮ ጀሌዎች ናቸው ብለው የሚሉት እነማንን ነው

የኢሃዲግን አባሎች ስለዚህ ከዛ በኋላ ችግር አለባቸው ብዙ ናቸው እንደውም እነሱ ብቻ ሳይሆኑ የእኛ አካባቢን እኛ እናውቃለን ስለዚህ የዛን ጊዜ በጣም እዛ ተረብሸዋል

እስቲ አሁን የእነሱ አባል ናቸው ብለውናል አደም

አዎ

646

አባል ናቸው ካሉን ደግሞ እነዚህ የኦፒዲዮ ጆሌዎች ናቸው ይላሉ ብዋል የኢህዲግ አባላትን ከዚህ ሌላ

አሁንም እንደገና እንደውም እዚህ ምስክርነት ስንት ጊዜ መጥተን ስንመለስ ቀጠሮ ተይዞ ገና ፍ/ቤት አልቀረብንም ስንመለስ እዛ ከተማ ውስጥ የተናገረች ሰው አለች

ማን

እቺ

ስሟ ማን ነው

ስሟ የአባቷ መሀመድ ነው

ስሟን አላስታውስም ብለዋል እኮ

ስሟን ትንገረንና እኛ እንድንይዘው ነው

ማን ነው ስምሽ ጀና መሀመድ ነች

አሁንም እየተናገረች ነው እንደውም

ምን እያለች ነው የምትናገራችሁ

አሁንም ምንም ነገር እንደማታመጡ እዛ ሄዳች ስትመሰክሩ ለራሳችሁ እየታሰራችሁ ነው እንደውም ከዚህ በኋላ እስቲ አንድ ነገር ብትናገሩ እናያችኋለን ብላ ረብሻ እያደረገች ነው

እሺ ይሄንን ያው ፍ/ቤቱ ሰምቶሎታል

ጀና 22ኛ ተከሳሽ ማለት ነው እሺ ሌላ

እስቲ ከዚህ ሌላ ያኔ በወቅቱ ማለት ነው የዛን ጊዜ

በወቅቱም ልጆቹን ቅስቀሳ አድርጋ

ምን እያለች ነበር ቅስቀሳ የምታደርገው

ቅስቀሳ በጆሌዎች ላይ ምንድን ነው በአማረኛ ይከብደኛል ትንሽ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

6417

ይናገሩት በሚችሉት ቋንቋ ቆይ አንዴ ምንዳ ለምንድን ነው ከዚህ የምትርቀው እስቲ ና አሁን ቁጭ በል እስቲ አሁን ድገሙት ኦሮምኛውን ይተረጉምልናል አሁን ያሉትን ምን ማለት ነው

ጀሌ ማለት ተከታይ ይሄ ሰው የሚከተል ማለት ነው አንተ ጀሌ በአማርኛውም ጀሌ ይባላል ጀሌ ማለት ተከታይ እንደማለት ነው ሰው የሚከተል ማለት ነው

እና

አንተ ተከታይ ተመለስ ለምን አትመለስም ወደእኛ አትመለስም

ወደማን አትመለስም

መሳሪያውን ይዘህ እነሱ የኦነግ እንትን ለመሆን ለማድረግ ነው እንደገና ተመልሳ ይሄንን ሰሞን ነው ያለችኝ እንደውም እስከ ቤቴ ድረስ ተከትላኝ

እሺ ይሄንን ብላለች ብለውናል ያኔ ማለት ነው የዛን ጊዜ ከ1999 እስከ 2000 ባለው ጊዜ ተማሪዎችን ይቀሰቅሱ ነበር ብለዋል

ተማሪዎቹን እየቀሰቀሱ ልጆቹን

ምን አድርጉ እያሉ ነው የሚቀሰቅሷቸው ተማሪዎቹን ምን አድርጉ ምን ያሉ ነው የሚቀሰቅሷቸው

የኦፒዲዮ እንትን አትሁኑ እኛ የኦነግ አባል ነን ኦነግ ነች አገሪቷ የኦነግ ነች እያለች እየቀሰቀሰች ችግር እየፈጠረች

እሷ ይሄንን ታደርጋለች ብውናል እሱስ ይሄንኛው ማን ነው ስሙ

እሱ የኦነግ ደጋፊ ነው

ስሙ ማን ነው

ጀማል

ጀማል እሺ

አዎ ደጋፊ ነው

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

6118

ምን ያደርግ ነበር ያኔ ከ1999 እስከ 2000 ባሉት ጊዜ እናንተ አካባቢ ምን ያደርግ ነበር

እነሱም እንደዛው ናቸው ይቀሰቅሳሉ እኛ አካባቢ አጠቃላያቸው እንደውም የቅስቀሳ የኦነግ ደጋፊዎች ስለሆኑ

እሺ ስለዚህ እሱም -------------- ነበር ነው ያሉን

ያው ነው ልጆቹንም እየቀሰቀሱ ነው ሰፈር ውስጥ

እሱ ምን ነበር በዛን ጊዜ

እሱ እንደዚህ ከተማ ውስጥ አንድ ፀጉር ቤት ይቀመጥ ነበር መደብር የሰው ቤት ይሰራ ነበር

እሺ ምን ነበር ጀና ኦነግ ነች አሉን እሱ ይቀሰቅሳል ብለውናል ምን እያለ ነው የሚቀሰቅሰው ምን ሁኑ እያለ ነው የሚቀሰቅሰው

ያው የኦዴድን እንትን አትከተሉ

እና ምን ሁኑ ነው የሚለው

ረብሻ እንዲፈጥሩ ልጆቹ

ምን ብለው ረብሻ እንዲፈጥሩ ምን እንዲያደርጉ

የኦነግ አባል እንዲሆኑ አጠቃላይ

እሺ ሁለቱ ጀማል ያሏቸውስ ጀማል ከድር እና ጀማል ሀምዛ ብለው የነገሩንስ እነሱስ ምን ነበር የሚያደርጉት

እነሱ ጀማል አንድ ጀማል ደግሞ የኦነግ አባል ነበር ከዛ ታሀድሶ ወስዶ ተመልሶ እንደገና ሰፈር ውስጥም ቅስቀሳ እያደረጉ

የትኛው ጀማል ጀማል ሀምዛ ነው ጀማል ከድር

ጀማል ሀምዛ

ጀማል ሀምዛ እሺ ምን ያደርግ ነበር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እንደዛው ቅስቀሳ እያደረጉ ነው

ታሀድሶ ከወሰደም በኋላ

ታሀድሶ ከወሰደም በኋላ

ምን እያለ ነበር የሚቀሰቅሰው

የኦነግን አባል ሁኑ ብሎ

እሺ ያንኛውስ ጀማል ከድርስ

ጀማል ከድር አሁን እየተናገርኩ አይደለም

ጀማል ከድር እዚህ የቆመው ነው እያለ ነው

እሺ በቃ ከነዚህ አሁን ከነገሩን ከሁለቱ ጀማሎች እና ከጀና ውጪ የሚያስታውሱት በስምም ይሁን ወይም ቢያዩት የ ሚያስታውሱት

አንድ እኔ የማስታውሳት አንዷ ባሏ ኦነግ ነበር ባሏ ሞቷል በኦነግ

ማን ነው እሱ

ኪሚያ ነች ኦነግ ውስጥ ነበር ባሏ እዛው ሰፈር ውስጥ ኑ ብለው ሲጠሩት ሲሮጥ ተመቶ መቷል እሷ እዚህ እስረኛ ነች

አለች እዚህ

እስረኛ ነች እሷ አለች

የት አለች

እኔ እሷን አላየኋትም አሁን

ኪሚያ የምትባል

እሷ ግን አባል ነች እንጂ እንደዛ ስታደርግ አልነበረም

እሺ እቺ ኪሚያ ባሏ

650

ኦነግ ነበር

የዐ/ህግ ምስክር ሆነው የመጡት ምስክር ስለ ስሟ ስለሁኔታዋ አላውቅም እያሉ ነው ሁላችንም እዚህ የተገኘነው ፍትህ ለማስገኘት ነው ስለዚህ ስም እያስታወሱ ተገቢ የህግም አካሄድ አደለም ስለዚህ አሁን ዐ/ህጉ እያነሱት ያሉትን ስም ያልጠቀሱትን ነው እያነሱ ያሉት የራሳቸው ምስክር ናቸው ማስታወስ ከቻሉ የሚችሉትን ይመስክሩ በዚህ ላይ ተቃውሞ የለንም ግን ስም እየጠቀሱ ማስመስከር

እሺ ጥሩ ዐ/ህግ

እኔ ከራሴ አላወጣሁትም የክሳችን ይሄ ምስክር የሚያስረዳው ብለን በቁጥር 9ኛ፣ 15ኛ፣ 22ኛ ብለን ጭብጥ አስይዘናል የክስ ቻርጃችንም ላይ አለ አሁን 15ኛ ተከሳሽ ብለን የገለጽናትን ባሏ የሞተባት ኪሚያ የምትባል አለች እዚህ ብሎ ራሱ መግለጽ ጀመረ እሱ ሲናገር ኪሚያ አለች ወይ የታለች ብዬ እኔ እሱን ተከትዬ ቀጠልኩኝ ቀጥታ ሰውየው ሳያነሳ ግን ኪሚያ ብዬ አንስቼ አልመራሁም ስለዚህ ከመሪ ጥያቄም ጋር የሚያያዝም አይደለም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥም ግድ ይለናል ሰውየው አለች ባሏ የኦነግ አባል ሆኖ ሞቷል በጦርነት እያለ ተከሳሿንም በእሷ ላይም ያስረዳል ብለን ቆጥረነውም እያለ ዝም የምንልበት ምንም የህግ አግባብ የለም

እሺ ፍ/ቤቱም እየተከታተለ ነው ያለው ምስክሩ አሁን ብቻ አይደለም ገና ሲጀምሩ መጀመሪያ ላይ ይሄንን ስም አንስተውታል ስለዚህ እየተከታተላችሁት ችሎቱን እየተከታተላችሁት አሁን ጥያቄው ይቀጥል አግባብ ነው

እሺ ኪሚያ ባሏ የሞተባት አለች ብለውናል እስቲ እሷስ ምን ነበር የምታደርገው ባሏስ በምንድን ነው ሞተ ያሉን እስቲ ዘርዝረው ይንገሩን

ባሏ ኦነግ አባል ነበር ከዛ ሰራዊት እቤት ድረስ ሄደው ሲጠሩት ከሰራዊት አባል በዛው ተመቶ መቶ

ስንት አመተ ምህረት ላይ ነው የሞተው

በ1986 እና በ1985 ዓ/ም መካከል ነው በዚህ መካከል ነው

አሁን ስንት አመተ ምህረት ላይ ነው ያለነው

2002

2002

አዎ

ስለዚህ 86 ማለት የዛሬ 18 አመት ማለት ተመቶ የሞተው

አዎ

የዛሬ 18 አመት እሺ ያኔ የእሷ ባል በሰራዊቱ ተመቶ ሞቷል አሉኝ እሷ ምንድን ነበር ስታደርግ የነበረው

ባሏን ነው እንጂ የእንትን አባል እሷ ከዛ በኋላ ምንም ስታደርግ አላየሁም እኔ

ምንም የሚያውቁት ነገር የለም በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ

ምንም ነገር እኔ የማውቀው ነገር የለም

ቅድም ባሏ ሞቷል እሷ ግን አባል ነበረች ሲሉ ነበር

የኦነግ አባል መሆኗ አልካድኩም እኮ አሁንም

ነበረች የኦነግ አባል

አዎ

እስከ ስንት አመተ ምህረት ድረስ ነበረች

እስከ አሁንም ድረስ ያው ናቸው እዛ አካባቢ

በስንት አመተ ምህረት ላይ ነው በቁጥጥር ስር የዋለችው

አሁን ከምርጫው በኋላ ነው

ስንት አመት ይሆናል በግምት

በግምት አንድ ሁለት አመት ከምናምን ይሆናል

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ... የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

652

ሁለት አመት ከምናምን ይሆነዋል የዛን ጊዜ በቁጥጥር እስከዋለች ድረስ በምንድን ነው ስትንቀሳቀስ የሚያውቋት

ምንም ስትንቀሳቀስ አደለም አባል መሆኗን ነው እንጂ

እሺ ጨርሻለሁ

አበቃችሁ

አዎ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ አሁን ይቀጥል አማክሯቸው ግን ሁለቱን ሰዎች

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ዛሬ ሊመሰክሩባቸው የመጡት ወደ 6 ሰዎች ናቸው ከነዚህ ውስጥ ሁለቱን ብቻ ነው መለየት የቻሉት ሌሎቹን እዚህ ላለመኖራቸው

አንዴ ቆይ ይመዝገብ

አንደኛ ምስክራችን ጀማል ሁለት ጀማሎች አሉ ብለዋል 9ኛ እና 29ኛ ጀማል ከድርና ጀማል ሀምዛ ለይተዋል ኪሚያ የምትባለዋን

15ኛን እሺ

የምትባለዋን 15ኛን ለይቷል ባሏ የኦነግ አባል ሆኖ ሞቷል እንደገና ደግሞ ጀና የምትባለውን ደግሞ

22ኛ እሺ

አሁን ድረስ እየዛተችብኝ ነው ብሎ 4 ምስክር ለይቶ መስክሯል እኛ ስድስት ብለን ብንጠቅስም ስድስት ላይ ነበር የመጣከው ተብሎ ሊጠየቅ አይገባም ያስታወሰውን አራቱን አስታውሳለሁ ብሎ አራቱ ላይ መስክሯል ሁለት ላይ እንደመሰከረ ተደግሮ በዛ መልኩ መያዝ የለበትም ተስተካክሎ ጠርቶ በመሰከራቸው በአራቱ ላይ መስቀለኛ ጥያቄ ቢጠይቅ ሁለቱ ግን አላስታውስም ባላቸውና ባልመሰከረው ሊጠየቅም አይገባም መጠየቅም የለበትም

653

እሺ እዚህ ላይ በአጭሩ

አንደኛዋን አሁን አስታወሷትን የተባሏትን ተከሳሽ ምናልባት ዐ/ህጉ እንዳሉት ከ18 አመት በፊት በኦነግ አባልነቱ ተገሏል እየተባለ ባለው ባለቤቷ ነው እኛ ጥያቄአችንን ያነሳነው ከ18 አመት በፊት ስለተገደሉ የኦነግ አባል ማስታወስ የቻሉ ምስክር ስለሆኑ ሊመሰክሩባቸው የመጡዋቸውን ምስክሮች ሌላው ቢቀር በስም ማስታወስ ያልቻሉበትን ምክንያት ከምስክሩ ታማኝነት አንፃር ለፍ/ቤቱ ግንዛቤ ለመፍጠር ያነሳሁት ጥያቄ ነው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል።

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል በተመሰከረው እና በተመሰከረባቸው በተነሳባቸው ላይ ነው መስቀለኛ ጥያቄ መቀጠል ያለበት በተጨማሪ ግን በምን አስታወስክ እንዴት ልታስታውስ ቻልክ ብሎ ጥያቄውም በራሱ ፕሮፐር አይደለም ዞሮ ዞሮ ግን በተነሳው በተመሰከረው ነገር ብቻ መስቀለኛ ጥያቄ አንሱ

ብይኑን እንቀበላለን ምስክር አሁን ጀማል ከድርና ጀማል ሀምዛን ሁለት ጀማሎች እንዳሉ ነግረውናል ጀማል ከድርን

ስራ ነው ወይስ

አዎ ስራው መደበኛ ስራው ምንድን ነው

መደበኛ ስራው ጫት

ጫት ምን ማድረግ

የጫት ፀሐፊም ነበር አስተማሪም ነበር ድሮ

ስለዚህ መደበኛ ስራውን ሲሰራ ነው እዛ ከተማ የሚያውቁት

እኔ እንደዛ ነው የማውቀው

ታዲያ ደጋፊ ይሁን አይሁን በምን አወቁ

እንደዛው በእኛ አካባቢ በእያንዳንዳችን እንተዋወቃለን

የት ቦታ ነው ይሄ ድጋፍ ሲሰጥ ያዩት እርሶ

ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ችሎት 4

654

እዛ አወዳይ አወዳይ መጀመሪያ ኢህዲግ ሳይገባ በፊት ኦነግና ጃራ ነበሩ የተቆጣጠረው የዛን ጊዜ ነው የምንተዋወቀው መጀመሪያ ኢ.ህዲግ እዛ ሳይገባ ኦነግና ጃራ ነው የተቆጣጠረ

እዩሎት ምን መሰሎት እኔ እየጠየኮት ያለሁትኝ ደጋሚ መሆኑን አሁን ባለን ጊዜ እዚህ ለምስክርነት በመጡበት ጊዜ በምን አወቁ ነው ካወቁ ደግሞ በምን ይገለፃል ያ ምስክርነት ደጋፊ መሆኑ ማለት ነው

ታሀድሶ ወስዶ መምጣቱ ራሱ ወረቀት አለው

ስለዚህ ታሀድሶ ወስዶ ከመጣ በኋላ ታዲያ የሰራውን ነገር ያውቃሉ ምን አድርጓል ከዛ በኋላ

ከዛ በኋላ አላልኩም እኔ

ከዛ በፊት ያለውን ነው እየተናገሩ ያሉት

ከዛ በፊት ያለውን እንትን ነው ያልኩት

ስለዚህ ታሀድሶ ወስዶ ከመጣ በኋላ ሰላማዊ ስራውን እየሰራ የሚገኝ ሰው ነው ይሄንን ነው የሚያውቁት

እኔ ዘጋቢ መሆኑን ከዛ በኋላ ስራቸውን ሲሰሩ ነው የማውቀው ብዬ ነው ቃሌን መጀመሪያ

እሺ ታሀድሶ ወስዶ ከመጣ በኋላ ሰላማዊ ነዋሪ መሆኑን ያውቃሉ ወይ ነው ጥያቄው አዎ ወይም አይደለም ነው እኔ የምፈልገው

ሲሰራ ነው የማውቀው ስራውን

ሰላማዊ ሰው ሆኖ ማለት ነው

አዎ

ከታሀድሶ በኋላ

አዎ

ጨረስኩ ጀማል ሀምዛ

ጀማል ሀምዛ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አዎ አሁን ስለ ጀማል ከድር ነው ያወራነው

ጀማል ከድር ነው እንዴ አይደለም ጀማል ሀምዛን ነው ያወራነው

ሰላማዊ ሰው መሆኑን የሚያውቁት

አዎ

እሺ ጀማል ከድርስ

ጀማል ከድር እንደገና ተመልሶ ስራውን ድሮ መደብር ይሰራል እንደገና ሰፈር ውስጥ ቅስቀሳ እያደረገ እያለ አውቃለሁ

መቼ ነው ይሄ አሁን የሚሉት

1999 እና እስከ 2000 መሀከል ያለው አውቃለሁ

ሲያዝ ያውቃሉ እንዴ

አዎ

የት ነው የተያዘው

አወዳይ ነው

ከተማ ውስጥ

አዎ

ምን እያደረገ

እዛ ከተማ ውስጥ ይዞራል እሱ ምንጊዜም

አዋ እሱማ አንድ ከተማ ውስጥ ያው መንቀሳቀሱ አይቀርም እሱ ሳይሆን

ሲያዝ አውቃለሁ ምን ሲያደርግ ሳይሆን የያዘው ፖሊስ ነው ከተያዘ በኋላ ነው እኛ የተጠራነው

ምን ሲያደርግ እንደተያዘ ያውቃሉ

ምን ሲያደርግ እንደተያዘ አላውቅም

አያውቁም ጨርሻለሁ ሌላዋን አውቃታለሁ ያሉት ጀና መሀመድ ነው ----------- በዜማ ታስፈራራኝ ነበር ብለው ነው ሰው ነበር እንዴ

መቃወሚያ አለ እስቲ ቆይ

ምስክሩ ስለጉዳዩ በዛን ጊዜ አባል ስለመሆኗ የሚያውቅ መሆኑን መስክረዋል ከዛን በኋላ ሰፈር ውስጥ አሁን ድረስ ዛቻ ታደርግብኛለች ብሏል እኛ ቀጥታ በዛ ላይ ለተፈፀመው ዛቻ ወንጀል አልከሰስንም ማስረጃ አልቆጠርንም የዚህን ጊዜ ነው ማን አለ ተብሎ ሊጠየቅ የሚገባው አለበለዛ የምስክሮቻችንም ዊትነስ ፕሮቴክሽን የማንሰጥ ከሆነ ማንም ምስክር አይመሰክርልንም ስለዚህ ክቡር ፍ/ቤት ከፐፕሊክ ኢንተረስትም አንፃር እንዲህ አይነት ጥያቄ ሊጠየቁ አይገባም

እሺ እዚህ ላይ

የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ላይ ያነሱት ጥያቄ ነው የመስቀለኛ ጥያቄ አግባብም ተከሳሹ ዋና ጥያቄ የተነሳባቸውን ወይም ደግሞ ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ ማድረግ ነው ዋና ጥያቄ ዐ/ህግ ያስመሰከረው ስለዚህ ባስመሰከረው ላይ እኛ ደግሞ መስቀለኛ ጥያቄውን መጠየቅ ተገቢነት አለው ነው።

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ጥያቄው በአብላጫ ድምጽ ይቀጥል ተብሏል ጥያቄውን ቀጥሉ

በወቅቱ ---------- ሰው ነበር ወይ ነው ጥያቄው

ሰው ነበር ወይ እኔን አሁን ገና ለወደፊት እሷም እኔም በዛ መንገድ ነው የማልፈው እሷ

ሰው በዛን ጊዜ ነበር ወይ

የዛን ጊዜ ሰው አልነበረም

አልነበረም ሌላው በፊት ትቀሰቅስ ነበር ብለዋል ምን እያለች ነበር የምትቀሰቅሰው

ይመልሱ ግድ የለም

ጀላ ጀሌ ብሎ ስታደርግ ነበረች

ቅድም ያሉትን ነው

667

አዎ

እሷ እንደዛ በማለቷ ምክንያት የመጣ ችግር አለ እንዴ ታዲያ

ተቃውሞ አላችሁ ቆይ ተቃውሞ አለ እዛ

የኦፒዲዮ ጀሌ ናችሁ ይሄንን አገር ኦፒዲዮ አያስተዳድረውም በኦነግ ስር ተደራጁ ኦነግ ነው ለእኛ የሚጠቅመን ብሎ የሚቀሰቅስን ሰው ማድረጉ ብቻ ወንጀል መሆኑ ተደንግጓል የደረሰ ውጤት ምን አለ ማን ተከተለ ማን አልተከተለም ምንስ ውጤት መጣ የሚል ጥያቄ አግባብ አይደለም ይህንን ያለ በራሱ ህጉ ማነሳሳት ወንጀል መሆኑ ተደንግጓል በቃ አለቀ፡፡

እሺ እዚህ ላይ የምትሉት ክርክር አዳምጣችኋል አልሰማችሁም አሁን የተባለውን ድገሙላቸው እስቲ በአጭሩ

ምስክሩ ማለት ነው እንደ ክስ አቀራረባችን በዛን ጊዜ ከ1999 እስከ 2000 ባለው ጊዜ ውስጥ ጀና የምትባለው የመንግስት አባላትን በተለይ የኢህዲግ ደጋፊዎችና ኢህዲጎችን የኦፒዲዮ ደጋፊ ናችሁ ጀሌዎች ናችሁ እያለች የተለያየ ስድቦችን ከመሳደብ ባሻገር በኦፒዲዮ ስር ተደራጁ ኦፒዲዮ ነው የሚጠቅመን እያለች ስትቀሰቅስ እንደነበረ መስክረዋል ያንን ማለቷ ብቻውን ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ስለሆነ ያንን በማለቷ ምን ውጤት ተገኘ ምን ውጤት መጣ ተብሎ ሊጠየቁ አይገባም ምስክሩ በዚህ መልኩ የቀረበውን ጥያቄ ምን ውጤት ምን ለውጥ መጣ የግድ መንግስት መገልበጥ ያለባትና ኦነግ መንገስ ያለበት አይመስለንም ህጉ አይልም ስለዚህ ይሄንን ጥያቄ ተቃውሞ አለን ነው

እሺ ክርክር

ኦፒዲዮ ምናልባት ዐ/ህጉ ይገባኛል ያው በአንፃራዊ ቃል ሲጠቀሙ ኦፒዲዮ ማለት ኦሄዲድ ነው የኢህዲግ አባል ነው እሱን ደግፉ ማለቷ አይደለም ወንጀል እየሆነባት ያለው ለነገሩ ግን ------------በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ቀስቅሳለች ካሉ እነማንን ነው የቀሰቀሱት ምን ምን በመቀስቀሷስ ብቻዋን ነው ያወራችሁ እነማን ነበሩ ወደሚለው ለመምጣት ስለፈለኩ ነው ጥያቄውንም ማስተካከልም እችላለሁ ፍ/ቤቱ

ጥሩ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ጥያቄው የሚስተካከል ከሆነ ይስተካከልና ከዛ በኋላ ክርክሩ የሚያስነሳ ከሆነ እናያለን እስቲ የተስተካከለው ጥያቄ ምንድን ነው የምታነሱት

ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ጥያቄውን አስተካክለነዋል በወቅቱ ጀና መሀመድ ቅስቀሳ ታደር ነበር

ቆይ የተስተካከለውን ጥያቄ እንስማ

ቅስቀሳ ታደርግበት በነበረ ወቅት የዛሬው ምስክር በወቅቱ ፖሊስ ነበሩ በወቅቱ የፖሊስ አባል ነበሩ

ነበርክ አልነበርክም ነው

አደለም የፖሊስ አባል ነበሩ እና እውነትም ቀስቅሳ ከነበረ ይዘው ለምን ወደህግ አላቀረቧትም ወደሚል አሻሽዬዋለሁ

እሺ እዚህ ላይ ተቃውሞ አለ የምታነሱት ወይስ ጥያቄው ይቀጥል እሺ እዚህ ላይ መልስ

እኔ የፖሊስ አባል አልነበርኩም

እሺ ሌላ ጥያቄ

አባል አልነበርኩም የኦሄዲድ እንትን ነበርኩ እንጂ የፖሊስ አባል አልነበርኩም

እሺ ጥሩ ይበቃል ሌላ ጥያቄ

ምን ብላ እንደቀሰቀሰች ሰምተዋል

ቅድም የተናገርኩት ነው

ድጋሚ

የስሚ ስሚ ነው ወይስ ቀጥታ ራሳቸው ሰምተዋል ወይ ለማለት ፈልጌ

እኔ ሰምቻለሁ ምስክር ማድረግ በዛን መሀከል አልቻልኩም እኔ

ሰምቻለሁ አሉ የሰሙትን ነው

የት ቦታ ነው የሰሙት

የዛ አወዳይ ከተማ

አወዳይ ምኑ ጋ ምን ቦታ ማለቴ ነው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምን ቦታ ወደ እኔ ቤት መሄጃ የእሷን ቤት አልፌ ነው የምሄደው እኔ

ምን ያህል ሰው ነበር እሷ ስትቀሰቅስ

ሰው ነበረ አልነበረም በአጭሩ

አልነበረም

አልነበረም እሺ ጨርሻለሁ

ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ህግ አስመዝግቡ ድጋሚ ጥያቄ ከሌለ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

እስቲ ኪሚያ ሻም ኢብራሂም ጀማል ከድር ሳኒ፣ ራህማ መሀመድ አብዱረህማን

እስቲ እነዚህን ትለያቸዋለህ

አሁን የተነሱትን

እሷን ታውቃታለህ

እሷን አውቃታለሁ

ሌላስ ሌላ አዲስ የተነሱትን

ሻሚ አብዲ

እሺ ሻምን ሌላ አዲስ ሰው እሷስ

ኪሚያ

ኪሚያ ነች

ኪሚያ

ምን አይነት ረብሻ

እዛ ተማሪዎች የዛን ጊዜ ከተማሪዎች ጋራ ድንጋይ ፖሊስ ሲወረውሩ ልጆች ጋራ ሮጣ እንትን ስታደርግ አይቻለሁ እኔ በአይኔ ነው ያየሁት

ስትወራወር

ልጆቹ ጋር አዎ

ሌላስ ያዩት ነገር አለ

ሌላ የለም

የለም ቅድም ታሀድሶ ተሰጥቶት የነበረ ሰው ያለ መሆኑን ተናግረዋል የትኛው ነው ታሀድሶ የተሰጠው እስኪ ጀማል ሀምዛ ተነስ

እሱ ነው

ለእሱ ነው የተሰጠው

አዎ

ከታሀድሶ በኋላ ምን ሲያደርግ አዩ ረብሻ ውስጥ አይተውታል ወይ ሲቀሰቅስ ወይ ሽብር ተግባር ውስጥ ሲሳተፍ

ረብሻ ውስጥ እንጂ እዛ ሲቀሰቅስ አላየሁም

ከታሀድሶ በኋላ

ከታሀድሶ በኋላ እዛ እኛ ዞን ነበር እኛ ዞን ውስጥ ስንዞር እንደገና እሱም እንደዚህ ነው ብለው ወደእኛ ሲያመጡ እኛ መክረነው ስንት ጊዜ እሱ ታሀድሶ ወስዷል ብለን ትተነዋል

ከታሀድሶ በኋላ በምንም አይነት ተግባር አልተሳተፈም

አልተሳተፈም እኔ አላየሁትም

ጀማል ከድርን በተመለከተ እሱስ ምን ሲያደርግ ነው ያዩት በተግባር ያዩት ምንድን ነው ምን ሲያደርግ ነው ያዩት

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

672

እሷ ናት ወይ ነው ጥያቄው

ኪሚያ እሷ ነች ወይ

እሷ ነች አዎ

እየተቀረፀ አይደለም ኪሚያ እሷ ናት

አዎ

እስቲ ኪሚያን አስመልክቶ ቅድም የተናገሩት ነገር አለ

ኪሚያ ባሏ የኦነግ አባል ነበር

አንዴ ጥያቄውን አስጨርሱንና ከዛ መልስ ስጡ መጀመሪያ ጥያቄአችንን ጨርሱ ባሏ የኦነግ ሰራዊት ሆኖ ከመሞቱ ባለፈ እሷ የኦነግ አባል ነች ወይ

እሷ ደጋፊዎች ናቸው እንጂ የኦነግ አባል ሆና እነሱን ስትከተል አላየሁም

ስትከተል አላዩም

አዎ

በሽብር ተግባር ወይ በመቀስቀስ ተግባር ተሳትፋስ አይተዋል

አላየኋትም

ጀናን በተመለከተ አሁን ለምስክርነት ከመጡ ወዲህ የኦፒዲዮ ጀሌ ብላ ስለመሳደቧ ተናግረዋል ከዛ በፊት ስትቀሰቅስ ወይ ህዝብ ስታነሳሳ አይተዋል እርሶ

የዛን ጊዜ አይቻለሁ

መቼ

በ1999 አካባቢ

ምንድን ነው ያዩት

እዛ አንድ የሆነ ረብሽ ተነስቶ ነበር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ጀማል ከድርን እንደዛ ቅስቀሳ ሲያደርግ አይቻለሁ እኔ

ምን ብሎ ሲቀሰቅስ ነው ያዩት

ከተማሪዎች ጋር ረብሻ ሲፈጥሩ ከእነሱ ጋር ሲሄዱ ተማሪዎች ፖሊስ ላይ ድንጋይ ሲወረውሩ ምናምን ከልጆች ጋር ተሳትፎ ሲሄድ አይቻለሁ

ከልጆች ጋር ሲሄድ ነው ያዩት ወይስ ሲናገር ድንጋይ ሲወረውር ምን ሲያደርግ ነው ያዩት

ከልጆች ጋር እንደዛ ድንጋይ ከሚወረውሩት ጋር ግሩፕ ሆነው ሲሄዱ ነው ያየሁት እኔ

እሱስ ወርውሯል እንዴ ሲወረውር አይተውታል

ሲወረውር በአይኔ አላየሁም

ሲቀሰቅስስ አይተዋል

ሲቀሰቅስ የዛን ጊዜ

አዎ

ከረብሻ ፈጣሪዎች ጋር ሲሄድ እኛ እንደዛ ነው ያየነው

ሲሄድ እንጂ ሲቀሰቅስ አላዩም

አዎ በአይኔ አላየሁም በጆሮዬ አልሰማሁም

ሲቀሰቅስ በጆሮ አልሰሙም

ከረብሻ ፈጣሪዎች ጋር የሚሄድ ሰው እንደዛው ነው ብዬ ይገፎ ነው እኔ

ነው የሚገምቱት

አዎ

ኪሚያ ባለቤቷ ካረፈ በኋላ ምን ስታደርግ ነው እንቷ የምታውቀው በአጭሩ

እኔ ምንም ስታደርግ አላውቅም ባሏ የኦነግ አባል መሆኑን

673

መሆኑን ነው የምታውቀው እሺ ይበቃል ሻምስ ሻም ኢብራሂም

ሻም የእንትን ደጋፊ መሆኑን ነው እንጂ የማውቀው ምንም ነገር አላውቅም እኔ

ጀማል ሀምዛስ

እንደዛው ነው

ራሀማስ ራሀማ መሀመድስ

እኔ እንደዛው ናቸው የማውቃቸው

እሺ እርሶ ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ ዐ/ህግ ቀሪዎቹን 8:00 ሰዓት ላይ እንስማ ብዙ አልቀረም 6 ሰው ነው

6 ሰው ነው የቀረን

በአንድ በሁለት ነው በዛ ያሉ እንትን አላቸው

የተወሰኑት ነው በዛ የሚለው

አሁን አንድ እንስማና ከቀትር በኋላ ያለውን ደግሞ እንደዚሁ እንቀጥላለን ማን ይጠራላችሁ

69ኛ የዐ/ህግ ምስክር አህመድ አሊዪ

9ኛ ነው አደለ

69ኛ አህመድ አሊዪ

በስንተኛ ላይ ነው

በ26ኛ ተከሳሽ ላይ

እሺ ምስክሩን ጥሩት

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ።

አማርኛ ይችላሉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

674

እችላለሁ

69ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አህመድ አሊዩ አህመድ

አድራሻ- ምስራቅ ሐረርጌ ቀርሳ ወረዳ ወተር

የት አካባቢ ማለት ነው

እዚህ ቀርሳ ወደ ቁልቢ መሄጃ መንገድ

ሐረር ነው

አዎ ምስራቅ ሐረርጌ ነው

ለምስክርነት ነው የመጡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

አብዲ አህመድ ኑር

ከእሱ ጋር ፀብ ዝምድና አሎት

እኔ ምንም ፀብ የለኝም ከእሱ ጋር

ጥሩ ያውቁታል እንዴ

አዎ እዛ እኛ ጋ ነው ወተር ነው አውቀዋለሁ

እስቲ ከዚህ ውስጥ አሳዩን

አለ

እሱ ነው

አብዲ አህመድ እሱ ነው

675

አብዲ አህመድ ኑር

ጥሩ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አህመድ አሊዪ ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለህ ተከሳሽን ለይተሃል እስቲ ምንድን ነው በእሱ ላይ የምታስረዳው ምንድን ነው የምታውቀው ከጊዜው ጀምረህ የምታውቀውን ነገር ንገረን

ከእሱ ጋር የማውቀው ልጁ በፊት ሰራዊት ሆኖ ሲንቀሳቀስ ነበር

ስንት አመተ ምህረት ላይ

አመተ ምህረቱን አላስታውስም ከዛ በኋላ ግን

የምን ሰራዊት ሆኖ ነበር የሚንቀሳቀሰው

የኦነግ

የኦነግ ሰራዊት ሆኖ

አዎ

የት አካባቢ ነበር ሲንቀሳቀስ የነበረው

እኔ እንጃ ሲንቀሳቀስ ነበር ከእኛ ጋር ሄዷል

እናንተ የት ነው ያላችሁት

እኛ ወተር ነው ያለነው

በፊት የት ነበር እሱ የሚኖረው

ወተር ከእኛ ጋር ነበር

ወተር ከእናንተ ጋር ነበር የሚኖረው

አዎ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ከዛ ከወተር ወጴት ሄደ

ሄደ ያው ወደ ታች ሄደ

ወጴት ወደታች ሄደ

ወደታች ሄደ እንግዲህ እኔ አላውቅም ገባ ከዛ በኋላ መያዙን ሰማሁ

ከእናንተ አካባቢ ወተር ነው የእኛ አካባቢ ብለከኛል አደለ

አዎ

ከእናንተ አካባቢ ወጴት ሄደ ሲባል ሰማህ

ወደጫካ ሄደ

ወደጫካ

አዎ

ማን ጋ

ማን -----------

ኦነግ

አዎ

እሺ ወደ ጫካ ሄደ ሲባል ሰማህ

አዎ

ስንት አመተ ምህረት ነው ይሄንን ያሰማከው

ሰማው ያው

በግምት ምን ያህል አመት ይሆነዋል

1999 ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ቁጥር 4

6ሃ8

1999 ላይ ሰማህ

አዎ

እሺ ከዛስ

ከዛ በኋላ ተያዘ ታሀድሶ ----------

መቼ ተያዘ

በ2001 መሰለኝ እኔ ቀኑን በትክክል አላስታውስም

እሺ ቀኑን በትክክል የማታውቀው 2001 የሚመስልህ ጊዜ ተያዘ

አዎ ተያዘ ------------- ገባ እኛ ጋ ከዛ በኋላ ድንች እርሻ ቆፈረ ድንች ተከለ ድንች እንደተከለ ደግሞ ሲያጠጣ ሲያድር ነበር አሁን -------------------- እርሻ ድረስ አባቱን ስንጠይቀው እርሻ ሲያጠጣ ነበር አሉ ሄድን እዛ እርሻ እርሻ አጠጥቶ ሌላ ቦታ ሄዶ ተኛ እኛ ከዛ አጣንና ተመልሰን ----------------------- መጣ እኛ ጋ

መቼ ነው የመጣው

የዛኑ ቀን ማታ

የዛኑ ጊዜ በተፈለገ ጊዜ በዛ በ2001 ማለት ነው ታሀድሶ ወስዶ ከጨረሰ በኋላ ማለት ነው

አዎ መጣ ለምንድን ነው የምትፈልጉኝ አለ አይ እኔ አይደለሁም የፈለኩህ የክፍለሀገሩ ፀጥታ ዘርፎች ነው አልኩት እኔ እኮ ታሀድሶ አለኝ ሲል ወረቀትም አለኝ አለ እሺ እንደዛ ከሆንክ ቀርሳ ነው ያሉት እና ሂድ ብዬ -------------- ራሱ ሄደ ------------- ይሄንን ነው የማውቀው እኔ

በቃ ጨርሻለሁ

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ እስቲ ፈጠን ፈጠን እያላችሁ በአጭሩ

መስቀለኛ ጥያቄ የለንም

የላችሁም ድጋሚ ጥያቄም አይኖርም

679

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ምን ሲያደርግ ነው እሱን በደንብ የምታውቀው አንተ

ከገባ በኂላ መሬት ቆፍሮ ድንች ሲተክል ነው የማውቀው ድንች ተክሎ ውሃ ሲያጠጣ

ከታሀድሶ በኂላ ማለት ነው

አዎ

እሺ እናመሰግናለን ጨርሰሃል መሄድ ትችላለህ ማን ይጠራ ዐ/ህግ ሌላ ምስክር

48ኛ ምስክር ዩሱፍ በየነ አነስ የሚለውን

ጥሩ ነው አዎ በአንዳንድ ሰው ላይ ያሉትን እየለያችሁ አቶ ዩሱፍ በየነን ጥሩ

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ፡፡

48ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ዩሱፍ በያን

አድራሻ-

ልትመሰክር ነው የመጣከው በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

አብዱረሃማን ሁሴን ጀብሪል

ከእሱ ጋር ዝምድና ፀብ አለህ ወይ

የለኝም

ጥሩ እስቲ አብዱረህማንን አሳየን አብዱረህማን ዩሱፍ ሁሴን 12ኛ ተከሳሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል እስቲ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ዩሱፍ እስቲ በተከሳሹ ላይ ምንድን ነው የምታውቀው ምንድን ነው የምታስረዳው

እኔ ስለ እሱ ስለተከሳሹ የማውቀው ነገር ኦነግ ውስጥ ሆኖ እኛን በኦነግ ውስጥ---------------- መጣ እኛ ጋ

መቼ ነው የመጣው

አመተ ምህረትና ቀን አላውታውስም

በግምት ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል

በግምትም ሶስት ይሁን ሁለት አራት ይሁን የማውቀው የለም አመቱን

አሁን ባልከን ጊዜ እስቲ በኦነግ ውስጥ ሆኖ ሲያደራጀን መጣ ብለሃል ምን አላችሁ ምን አድርጉ አላችሁ

አዎ ከእኔ ጋር እንድትሰሩ አደርጋለሁ አደራጃችኋለሁ ብሎ አለን

ምንድን ነኝ ብሎ አላችሁ

እኔ የእነሱ አባል ነኝ

የማን አባል ነኝ አለ

የኦነግ

እሺ ከዛስ

ይሄንን እያለ እያለ መንግስት ነው የደረሰበት በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ መንግስት ነው የደረሰበት

በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ መንግስት ደርሶበት ምን ሆነ

ተያዘ

እሺ ከዛስ

ያዙት ከዛ እሱም ራሱን ገለጸ

ምን ብሎ ገለጸ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

681

ከእነሱ ጋር ይሄንን ያህል ሰራቻለሁ እንዲ እንዲህ ነው ብሎ ተንትኖ

እሺ ከዛስ

ከዛ በኋላ እንደዛ ብሎ ከገለጸ በኋላ ራሱን በሰላም ወደቤቱ ገብቶ ስራውን ይሰራ ነበር

መቼ ነው ስራውን ይሰራ የነበረው

አስቤ አልያዝኩትም አመተ ምህረቱን ቀኑን

ከዚህ ሌላ የምታወቀው ነገር አለ ወይ

እኔ ምንም ነገር አላውቅም

እሺ በወቅቱ እንደዚህ በኦነግ ስር ተደራጅ ብሎ ሲልህ ተደራጀህ እንዴ አንተ

አለን እንጂ እንደዛ ያዘዘን ነገር ምንም ነገር የተፈጸመ ነገር የለም

እሺ እንደዛ ያላችሁ ጊዜውና ለመንግስት ራሱን የገለጸበት ጊዜው ምን ያህል ይሆናል በግምት

ምንም አይራራቅም እዛው አካባቢ ነው

ጊዜ መገመት አልችልም ብሏል

አይራራቅም በዛ ወቅት አካባቢ ነው

እስቲ እሱ በማን ስር እንደተደራጀ የነገራችሁ ነገር አለ ወይ ማን ነው ያደራጀው

አልነገረኝም አባዎ ከማለት ውጪ ኦነግ ከማለት ውጪ ምንም ያለኝ ነገር የለም

ጨርሰናል

ይበቃችኋል እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አለ የለም መስቀለኛ ጥያቄ የለም ድጋሚ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግናለን መሄድ ትችላለህ ቀጣዩ ምስክር ማን ነው

ቀጣይ ምስክር 47ኛ በድሪ ሼክ ኡመር

በድሪ ሼክ ኡመር በስንተኛው ላይ ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

682

በ12ኛ እና በ20ኛ እንዲሁም በ21ኛ

በ12ኛ፣ 20ኛ 21ኛ

አዎ

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ።

እሺ ይቀመጡ አባባ

47ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - በድሪ ሼክ ኡመር

አድራሻ- ሚደጋ ቶላ ወረዳ

ለምስክርነት ነው የመጡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

አብዲ ኡስማን

ሌላስ

ሌላ አላውቅም አብዲ ኡስማን ላይ ብቻ ነው የመጣሁት

እሺ አብዲ ኡስማን ላይ ብቻ ከእሱ ጋር ፀብ ዝምድና አሎት

የለኝም

እሺ አብዲ ኡስማንን ያሳዩናል እስቲ እሺ ይቀመጡ ፀብ ዝምድና አለህ ከእሱ ጋር

የለኝም

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ በድሪ ሼክ ኡመር ዛሬ ለምስክር ነው የመጡት እና ምን አድርጎ ነው የተከሰሰው እስቲ ምንድን ነው የሚያውቁት በእሱ ላይ

እኔ በዛን ሰዓት በፀጥታና ፍትህ ዘርፍ እሰራ ነበር

መቼ ነው የዛን ቀን ጊዜው መቼ ነው

ሶስት አመት ይሆነዋል

እሺ የዛሬ ሶስት አመት እሰራ ነበር በዚህ ጊዜ በሚሰሩ ጊዜ

በእሱ ላይ ምንም -----------------

ምንም የሚመሰክሩት የለም በእሱ ላይ

እሱ ተማሪ ነበር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነበር እና ከዛ በፊት እንደዚህ ሆነን ተደራጅተን ነበር ብሎ

ምን ተደራጅተን ነበር

ከዛ ተመልሶ ሲመጣ ወደ መንግስት ስራ ነው የገባው

ተደራጀን ብሎ ያለውና የተደራጀውን የሚያውቁት ነገር ካለ ይንገሩን ስለዛ ነው የፈለግነው

ከእነሱ ጋር ከተደራጁት ሰዎች ጋርም ይሄንን ሃይማኖት እናጠፋለን

ምንድን ነው የተደራጁት የተደራጁትን ነገር ይንገሩን ምንድን ነው የተደራጀው

አልገባኝም ይሄ ቋንቋ የተከበረው ፍ/ቤት አልገባኝም

አሁንም አልገባህም

አዎ

እስቲ ድገሙት እንደገና

ይሄንን አባዎ የሚባል ነገር እዚህ ህብረተሰቡ ውስጥ የገባን ደብቀው ይዘው እዛው ህብረተሰቡ ውስጥ አድርገዋል ተብሎ ነው

እሺ እሱስ የዛን ጊዜ ምን አለ ታዲያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አሁን እኔ በኦፒዲዮ ውስጥ ከተደራጀው ተደራጅቻለሁና ያንን የነበረውን ከዛ በፊት ያለውን እናፈርሳለን እናጠፋለን ብሎ ነው ሲል ያለው

መቼ ነው እንደዛ ብሎ ያለው

ያው በተመረመረ ወቅት ነው በምርመራ ወቅት

የተመረመረ ወቅት ጊዜው መቼ ነው

ሶስት አመት ይሆነዋል ብያለሁ

እሺ የዛሬ ሶስት አመት ሲገመገም ወይ ሲመረመር እንደዚህ አለ እስቲ ምን ምን እያደረጉ ነበር የተደራጁት ምን ምን አድርገን ነው የተደራጀነው ብሎ አለ

እኔ እንግዲህ እዛ አካባቢ ነበርኩኝ ከዞን የመጡ ናቸው የመረመሩት አንዳንዱን ነገር ነው የሰማሁት

እኮ ምንድን ነው የሰማከው በምን ውስጥ ነው ተደራጀሁ ያለው

እሱ ራሱ በዛን ሰዓት የመንግስት ሰራተኛ ነው

እሺ ይሁን የመንግስት ሰራተኛ ይሁን ምን ተደራጀሁ አለ ነው እየተባልክ ያለከው

በፊት ተደብቀን ነበር ብሎ ነው ያለው

ምኑን ነው ተደብቀን ብሎ ያለው

ይሄንን ነው አባዎ የሚባለውን

እሺ ተደብቀን አደረግን ከነማን ጋር ነበር ይሄንን

እነሱ የሉም እዚህ ብዙ ሰዎች ናቸው

እስቲ ጥራቸው ስማቸውን

አብዱሰላም፣

እሺ ሌላ ማን አለ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አብዱሰላም አለ ሌላ

አህመድ ከሊፍ

አህመድ ከሊፍ እሺ ሌላ

እኔ እነዚህን እነዚህን ነው የማውቃቸው ብዙ ሰዎች ስለሆኑ ስማቸውን መጥራት አልችልም ነው

እሺ ተደራጅተን ነበር ብሏል ብለከናል በአባዎ ስር ተደራጅተናል ብሎ ነግሮናል ብለሃል እስቲ ምን ምን እያደረግን ነበር ስንደራጅ የነበረው ለአባዎ ምን ምን አደረግን ብሎ አለህ የተደራጁትስ ምን እያደረጉ ነበር

እኛ ከበፊት በድብቅ ነበር ስናደርግ የነበረው እንጂ አሁን እናጥፋ ይሄንን ብሎ ነው እንጂ የተናገረው

በድብቅ ምን ስናደርግ ነበር ምንድን ነበር ድርጊቱ በድብቅ ሲደረግ የነበረውን ግለጸው

ቆይ አንዴ እስቲ አንዴ ትርጉሙ ነው መሰለኝ እስቲ ሌላም ደግሞ በተጨማሪ ኦሮሞኛ ያስቸግራል እንዴ ቋንቋው አያስቸግርም

አንዳንድ ቃሉ ነው የሚያስቸግረኝ

እስቲ ሌላም ደግሞ ሁለት እየተጋገዛችሁ የት አለ የማረሚያ ቤቱ ልጅ

እስቲ በጋራ አንድ ላይ ድጋሜ ምስክርነቱን ስጡ በሉት አሁን የሚጨርሰውን ጠይቋቸውና ጠይቋቸው ጥያቄውን

እሺ በድብቅ ይዘነው ተደራጅተን ነበር ብሏል ብለሀል በድብቅ ተደራጅተው ምን ነበረ ሲያደርጉ የነበረው በአባዎ ስር በድብቅ ተደራጅተው ምን ነበር ስናደርግ ነበር ብሎ የነገረህ

እኔ በተጨባጭ የማውቀው ነገር የለም

እሺ የዛን ቀን በአባዎ ስር ተደራጅተን ነበር ብሎ ሲናገር ሰምተካል አይደለም ወይ ብለህ ጠይቀው

አዎ ሰምቻለሁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

በዛኑ ቀን በአባዎ ስር በድብቅ በህብረተሰቡ ውስጥ ይዘነው ተደራጅተን ነበር ያለው ተደራጅተው ምን ሲያደርጉ እንደነበር ነው የገለፀላችሁ

ተቃውሞ አላችሁ እሺ ተቃውሞ

የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ከአንድም ወደ 6 ጊዜ ነው ፖይንት ያደረኩት ተደራጅተን ነበር በድብቅ ብሎ ሲናገር ሰማሁት ብለው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ከእዛ በኋላ ስለ አደረጃጀቱ የማውቀው ነገር የለም እያሉ በተደጋጋሚ 6 ጊዜ ምስክሩ እየተናገሩ ነው ስለዚህ ዐ/ሕግ በማስጨነቅ ሊያስመሰክሩ አይገባም ምስክራቸውን ምስክሩ ተናግረዋል አንዴ

እሺ እሺ

እዚህ ላይ አላችሁ ክርክር

እዚህ ላይ ያለን ክርክር ምንድነው በአባዎ ስር በድብቅ ተደራጅተን በመሀበረሰቡ ውስጥ ይዘነው ነበረ ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ አለ ሰውዬው የተናገረው ነገር የዛን ጊዜ በአባዎ ስር ተደራጅተው ምን ሲያደርጉ እንደነበር የነገራቸውን ንገረን ነው ያልኩት ምንም አልነገረንም ብሎ አልገደበኝም እሱ ምስክሩ ነው ይሄንን ሊል የሚገባው ተከላካይ ጠበቃው አይደለም ስለዚህ በዚህ

ሌላ የተናገረው ነገር አለ ነው አጭሩ ጥያቄ

አዎ ከእዚህ ሌላ በአባዎ ስር ተደራጅተው ምን ሲያደርጉ እንደነበረ የነገራችሁን ካለ ንገረኝ ነው ከሌለ የለም ብሎ ሊያስቆመኝ የሚገባው ምስክሩ አልነገረንም ብሎ ሊል የሚገባው

እስቲ ጥያቄው ይቀጥል ጥያቄው መልሱም ይቀጥል ምንድነው በተጨማሪ ያኔ ሲናገር ምን በተጨማሪ ተናገረ ትርጉሙም ሊሆን ይችላል እስቲ

ሌላ የማውቀው ነገር የለኝም

ከዚህ አሁን ከመሰከርክበት ከእሱ ከእዚኛው ተከሣሽ ውጪ ማለት ነው ፖሊስ ጣቢያ ላይ ያኔ የመሰከርክበት ሰው የለም ወይ በሌላ ሰው ላይ የምስክርነት ቃል አልሰጠክም ወይ ወይንስ ሰጥተሀል

የለም

687

እስቲ አስታውስ በዚህ ላይ ብቻ ነው የሰጠከው እርግጠኛ ነህ

እሱ ብቻ ላይ ነው እኔ የመሰከርኩት መጀመሪያም የተጠራሁት ለእሱ ብቻ ነው የተጠራሁት

ከዚህ አሁን ከእዚህ ከተከሣሽ ውጪ በፖሊስ ጣቢያ ላይ የሰጠከው የምስክርነት ቃል ታስታውሳለህ በደንብ አድርገህ እሱ ላይ ብቻ ነው ወይ የመሰከርከው ፖሊስ ጣቢያ ቀርበህ የምስክርነት ቃል

አዎ እሱ ብቻ ላይ ነው እኔ ቃሌን የሰጠሁት

ክቡር ፍ/ቤት ሌሎች ሰዎች ላይ የተሰጠበት ሁኔታ እና የተፈረመበት ስላለ እንዲጠየቅልንና

እስቲ

ሌሎቹም ሰዎች ተነግረውት አልሰጠሁም ብሎ እንዲያረጋግጥልን ነው አሁን አልሰጠሁም እያለ ነው

አሳይዋቸው ፊርማውን አሳይዋቸው

ነገሩ ፊርማ አይደለም እኔ አማርኛ መፅሀፍም አልችልም

ጥሩ ከ2ቱ ውጪ ከዚህ ውጪ ሌላ አልመሰከሩም ጣቢያ ላይ

ሌላ ላይ እኔ ምስክርነት አልሰጠሁም

እሺ

አብዱራህማን ሁሴን የሚባል ላይ አልሰጠክም የምስክርነት ቃል

እኔ አልወጣሁም

እሺ መሀመድ አልይ የሚባልስ ላይ ምንም የምስክርነት ቃል አልሰጠክም

አልወጣሁም

እሺ በቃን ጨርሰናል

አበቃችሁ

688

መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ይሄኛው ተከሣሽ በወቅቱ መደራጀቱን በኦነግ ስር የት ቦታ ነው የተናገረው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ አይደለም ወይ ኦነግን ከዚህ በኋላ ማጥፋት አለብን ብሎ የተናገረው እርሶም የሰሙት ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ነው አይደለም ብለህ ጠይቃቸው

ህዝቡ ላይ ነው

ህዝቡ ላይ ምን ብሎ ነው የተናገረው እሱን ያስታውሱታል ኦነግን እናጥፋው ብሎ አይደለም የተናረው

አዎ

ለህዝቡ በተሰበሰበበት

አዎ

ጨርሻለሁ

ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

በድሪ ተከሣሹ ይሄንን ኦነግን -------- ነበረ አድራጅተን ነበረ ከአሁን በኋላ ማጥፋት አለብን ብሎ ያለው ፖሊስ የለም ነበረ እንጴ እንደዚህ ብሎ ቃል ሲሰጥ

ነበሩ

እሺ ፖሊሶቹ ሲጠይቁት ታዲያ ለምንድነው ይሄንን የመለሰው

ከዞን የመጡ አስገምጋሚዎች የተው ነበሩ በዛን ሰአት ነው ይሄንን ነገር የተናገረው

እሺ አስገምጋሚዎቹ ውስጥ ፖሊስ አለ ወይንስ ፖሊስ የለም

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

በህዝቡ ላይ እራሱን ያጋለጠ ይቅርታ እናደርግላቹሀለን በሚል አብሮኝ ነበረ ግን እንደ ፖሊስነት ቃል ሲቀበሉ አይደለም

እሺ ጨርሻለሁ

አበቃችሁ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እሺ ቀሪ ምስክሩን 0/ሕግ 3 ምስክር ነው የሚቀረን

አዎ

3 ምስክሮችን ከቀትር በኋላ እንሰማለን

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰዒድ ሀሰን

- ዩሱፍ መሀመድ

ከሣሽ - 0/ሕግ ሀረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሣሾች - እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ሰዎች ከማረሚ ቤት 68 ሰው ከማረሚያ ቤት ቀርበዋ

ከተከላካይ ጠበቃ ጋር ተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ ሳሙኤል አባቴ ቀርቤያለሁ

ዛሬ መዝገቡ ያደረው ቀሪ የ0/ሕግ 3 ምስክሮችን ለመስማት ነው ምስክሮቹ ቀርበዋል 0/ሕግ

ከፖሊስ ጋር ያደሩ ስለሆነ ፖሊስ ያቀርብልናል ቀርበዋል

ቀርበዋል

አንድ ምስክር ጥሩ እሺ ማን ይጠራላችሁ

ኡመር አብዱላሂ 46ኛ የ0/ሕግ ምስክር ነው

ኡመር አብዱላሂን ጥሩ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምናልባት ኦሮምኛ ወደ አማርኛ

አስተርጓሚ

የሚተረጉም ከሆነ ደንበኞቼ እንደሚሉኝ ያው እኔ ኦሮምኛ ቋንቋ አልችልም ግን አተረጓጎም ላይ ትክክል አይደለም እና --- ይቀየርልን ነው

እሱ ፍ/ቤቱ የራሱ የፍ/ቤቱ አስተርጓሚ አለ መስፈርቱን አሟልቶ የተቀጠረ ሰራተኛ አለ ሌላ ችግር ካለ ፍ/ቤቱ የሚከታተለው ነገር ስላለ የዚህን ያህል የጎላ ችግር እስካሁን ስላልደረሰ በዚሁ ነው የምንቀጥለው ችግር ካለ እኛ እያየን ነው የምንሄደው እሺ አስተርሚውን ጥሩት ኡመር በማን ላይ ነው የቆጠራችሁት

በ12ኛ በ13ኛ በ16 በ17 እና በ18ኛ ተከሣሾች ላይ

መሀላ አስፈፅሟቸው ምንዳ የለም ከማረሚያ ቤት የመጣው አስተርጓሚ እስቲ ፈልጉ ሌላ ኦሮምኛ ቋንቋ የሚችል

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ኡመር አብዱላሂ

አድራሻ - ሚደጋ ቶላ የሚባል ወረዳ ነው

ጥሩ ለምስክርነት ነው የመጣከው

አዎ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

አብዱራህማን ሀሰን ጅብሪል

አብዱራህማን ሀሰን

ሁሴን ጅብሪል

ሁሴን ጅብሪል

አዎ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ...

ሴላስ ስማቸውን አታስታውስም

መሀመድ አሊይ አለ

እሺ መሀመድ ሴላ

ሴላ አላውቅም

2ቱ ላይ ብቻ ነው

በ2ቱ ላይ ብቻ ነው

እሺ ጥሩ

ኡመር አብዱላሂ ነው ያለው ማነው

ኡመር አብዱላሂ አብዱመሊክ ነው

አብዱመሊክ

ይሄ 41ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ነው በአያት ስም ስለ---

ሌላ ኡመር አለ

ሌላ ኡመር አብዱላሂ ዩኒስ የሚባል አለ

ጥሩ አሁን ኡመር አብዱላሂ ማን ይመስክርላችሁ

ኡመር አብዱላሂ ዩኒክን ነበር ያልነው እሱ ቃለ መሀላ ከፈፀመ ምናልባት ጭብጣችንን እሱ ላይ

ካልቸገራችሁ መቀየር ይቻላል ችግርኮ የለውም ይሄ ይቀጥል

ይቀጥል ይችላል

እሺ --- እንትኑን አስይዙ በስንተኛ ላይ ነው

እና ይሄንኛው ግን ይሄንኛው የሚያስረዳው ግን 41ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ነው እሱ

692

እሺ በማን ላይ ነው የሚመሰክረው

ኡመር አብዱላሂ አብዱልመሊክ 41ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ነው የሚያስረዳውም በ2 ተከሣሾች በ12ኛ እና በ21 ነው እሱ የጠራቸው ነው

በ12ህ እና

21ኛ ተከሣሾች ላይ

እሺ ጥሩ በዚሁ ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

የለኝም

እስቲ ተነሳ እና ታሳየናለህ እዚህ ውስጥ ካሉ ማነው ስምህ

እነዚህ ብቻ ናቸው የማውቃቸው

መሀመድ አልይ ስንተኛ ነህ 21 ማነው ስምህ ስንተኛ ነህ 12 አብዱራህማን ሁሴን ነህ ሁሴን ጅብሪል እሺ ጥሩ እሺ ዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ኡመር እነዚህን ተከሣሾች ለይተካል እስቲ ምንድነው የምታስረዳው በእነሱ ላይ ምንድነው የምታውቀው

የማውቀው በአብዱራህማን ሁሴን ጅብሪል ላይ

እሺ

የአባም አባል አደርግሀለሁ ብሎ ወደ እኔ መጥቶ ነበረ

መቼ ነው የመጣው

በ98 ዓ/ም

እሺ፡ ከእዛስ

693

እሱ ወደ እኔ እንደመጣ እኔ አባዎን አልፈልግም ብዬ እንቢ ብዬ እንቢ ማለቴን ነው የማውቀው

ከዚህ ሌላስ ያለህ ነገር አለ

እሱ እነዚህን ሰዎች እነዚህን ሰዎቹን አሳይሀለሁ ብሎኝ

የቶቹን ሰዎች

የአባዎ ሰዎች ማለት ነው አሳይካለሁ ብሎኝ በኋላ እኔ እንቢ ስለው እኔን መሸሽ ጀመረ

እሺ በመሀመድ አልይ ላይ ምንድነው የምታውቀው

መሀመድ አልይ እራሱን ማጋለጡን ነው የማውቀው

ምን በሎ አጋለጠ

የአባዎ አባል ሆኜ በመቆየቴ ብሎ በሰፊው ህዝብ ላይ ይቅርታ መጠየቁን ነው የማውቀው

መቼ ነው እንዲህ ያለው

ይሄንን አመተ ምህረቱን አላውቅም

በግምት ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል

2ቱም በአቆጣጠር አንድ ናቸው ጊዜውን አላውቀውም ነው የሚለው

የቅድሙን 1998 ብለከናል

አዎ በዛው ላይ ነው

በዛው አመት

አዎ በእዛ ላይ ነው

ጨርሰናል

አበቃችሁ ጥያቄ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

--መሀመድ አሊይ በሰፊው ህዝብ በፊት ሲናገር ነበረ ብለሀል የት ነው የተናገረው በለው

በአና ሚደጋ ወረዳ ነው

ከእዛስ በኂላ ምን ሆነ ከተናገረ በኂላ

ትንሽ ከቆየ በኂላ መወሰዱን ነው የማውቀው

በሰላም ይኖር ነበረ ከተናገረ በኂላ

ከተናገረ በኂላ በሰላም መኖሩን አውቃለሁ ከእዛ በኂላ መወሰዱን አውቃለሁ ነው የሚለው

ሲያዝ በሰላማዊ ህይወት ውስጥ እያለ ነው ወይ ታውቃለህ ወይ

እኔ የሰውን ሆድ ውስጡን ማወቅ አልችልም

አይ እዛው አካባቢ ላይ ምን እየሰራ ነበር የምታውቀው

ከእዛ በኂላ ተማሪ መሆኑን ነው የማውቀው

ይሄንን በተመለከተ ሁሴን የአባዎ አባል ይሁን አይሁን ታውቃለህ ወይ በለው

እኔ መጥቶ ያው እኔን ሲያነጋግረኝ ነው የማውቀው

እንጂ እዛ አባል ይሁን አይሁን የምታውቀው ነገር የለም

እኔ አላውቅም

እዛ አካባቢ አብዱራህማን ሁሴን ችግር ይፈጥር ነበር እንዴ

እሱ ተይዞ ሲሄድ እና እሱም ደግሞ እኔን ያለኝን ብቻ ነው እንጂ የማውቀው ሌላ የማውቀው ነገር የለም

ጨርሻለሁ

ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

የለንም

ድጋሜ ጥያቄ የለም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግንሀለን ከኂላ ቁጭ በል ቀጣይ ምስክር ማን ይጠራላችሁ

40ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ጫላ ከማል

ጫላ

ጫላ ከማል ከዲር

40ኛ ነው

40ኛ ነው አዎ

በስንተኛ ላይ ነው

እሱም የሚያስረዳው በ12ኛ እና በ21ኛ ተከሣሾች ላይ ነው

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

እሺ -----

ምንም ነገር የለኝም

ተነሳ እና አሳየን እሺ ዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ጫላ እነዚህን ሰዎች ለይተሀልናል እና እስቲ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቃቸው እስቲ ለፍ/ቤቱ አስረዳ አንድ በአንድ ንገረን በለው እሺ አብዱራሀማን

አብዱራሀማን ጅብሪል አባዎን ለማጠናከር ማለት ነው ለእዛ ነው ወደ እኛ የመጣው

መቼ ነው ወደ እናንተ የመጣው

ቆይቷል እኔ ቀኑን አላውቅም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

696

ምን ያህል ይሆናል በግምት

1998 መሆኑን አስታውሳለሁ ነው የሚለው

እሺ 1998 ላይ የት ነው የመጣው የት አካባቢ ነው

እኛ ለጫት ስራ ከተማ ውስጥ ነበርን

የት ከተማ ምን ይባላል ያላችሁበት

ሚደጋ የሚባል ከተማ ነው

እሺ ሚደጋ የት ዞን ነው ያለው በለው

ከተማ ውስጥ 01 የሚባል ቦታ ነው

እኮ በምን ዞን ውስጥ ነው ያለው የት አካባቢ ነው

ያው ከተማው ነው ያዉ ዞኑ ከተማው ነው ነው የሚለው

የት ነው ሚደጋ ያለው አሁን የምትለን ቦታው አካባቢውን መለየት አትችልም ወይ እዚህ አካባቢ ነው ብለህ

ሚደጋ ከፈዲስ በታች ነው ግን ወደ ክልል 5 ይጠጋል

እሺ እዛ ቦታ ማለት ነው መጣ ብለህል ምንድነው ያደረገው መጥቶ ምንድነው ያደረገው

እናንተን ማደራጀት እፈልጋለሁ

በምንድነው ያ ማደራጀት እፈልጋለሁ ያለው

እሱ ለማደራጀት መምጣቱን ብቻ ነው የነገረን

በምን ሊያደራጃችሁ መምጣቱን ነው የነገራችሁ

አደራጃቹሀለሁ ማለቱን ነው እንጂ

በምን ላይ አደራጃቹሀለሁ ብሎ ነው የመጣው

697

በአባዎ አባልነት

እሺ ብሎ መጣ ከእዛስ አደራጃችሁ ወይስ ምን ተፈጠረ ምን ተደረገ

እኛን አላደራጀንም ከእዛ በኋላ ተይዞ ሄደ በመንግስት እጅ ተይዞ ነው የሄደው

እሺ አብዱራህማንን ይሄን ነው የሆነው አልከን መሀመድሳ

መሀመድም በእዛው በአባዎ ጉዳይ ነው

እሺ እሱን ምን ሲያደርግ ነው የምታውቀው

ምንም ሲሰራ አላውቅም ያው መማር ተማሪ መሆኑን ነው የማውቀው

አባዎ እያልከን ነበረ በእሱም ላይ

የዛኑ እለት ነው እንጂ የማውቀው ከእዛ በፊት አላውቅም

ምኑን አወቅህ የዛን እለት

በእዛን እለት ለአባልነት አደራጃቹሀለሁ ብሎ ሰበሰበን እንጂ ከእዛ በፊት ያለውን አላውቅም

እሺ እሱን መቼ ነው የሰበሰባችሁ

1995 ነው

እሺ

ቀኑን በትክክል አላውቀውም ነው

እሺ እና አደራጃችሁ

እዛ መጥቶ እዛ መጥቶ ያው 5 ብር ከላዩ ላይ ወሰደ

ለምንድነው የወሰደው 5 ብሩን

ለማደራጀት ገንዘብ አዋጡ ተብሎ ለእሱ ነው

እሺ ጨርሻለሁ

ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ
የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

698

እሺ በተመሳሳይ መስቀለኛ ጥያቄ ይኖራል ይቀጥል

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እሺ ምስክር የምስክርነት ቃልዎን ሲሰጡ ወደ እዛ ከተማ መጥቷል ብለዋል 3ታችሁም የእዛ ከተማ ነዋሪ ናችሁ ወይንስ አይደላችሁም

3ታችን እነማን ነን እነማንን ነው የሚለው

አሁን የመሰከርክባቸው 2ቱ እና አንተ

አዎ እዛ ነው የምንኖረው

ታዲያ እዛው ከሆነ የሚኖሩት ከየት መጥተው ነው የሚያደራጁት እዛው ከተማ ውስጥ እየኖሩ ከየት ነው መጡ የምትለው ከሌላ ከውጪ ከየት ነው የሚመጡት

ሁላችንም የተለያየ ስራ ነው የምንሰራው

ግን እዛው ከተማ አንድ ላይ ነው የሚኖሩት

እዛ ከተማ ነው የምኖረው ብሏል

ስለዚህ

እና የተለያየ ስራ ስለምንሰራ እዛ መምጣቱን ነው እንጂ ከየት እንደመጣ አላውቅም ነው የሚለው

እኮ እዛው ከተማ ነዋሪዎች ናቸው

አዎ ከተማው አንድ ነው ትልቅ ነው ግን መንደር መንደር ነው

እሺ ታዲያ ከእዛ በኂላ ስብሰባ ላይ አልተገናኛችሁም እንዴ

ከእዛ በኂላ አልተገናኘንም

ስብሰባ ላይ አልነበርክም ወይ

እኔ ያው በመንግስት መያዛቸውን ነው እንጂ እኔ በዛን ሰአት እኔ አላውቅም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቋጥር

ስነ ስርአት አድርጉ ቆይ ቆይ ቆይ ቆይ አንዴ

አዎ እንትን እዚህ ጋር

ቆይ አንዴ ቆይ ስርአት አድርጉ ለሁላችሁም ነው ይሄ ማስጠንቀቂያ

የሚለው በመንደሩ ላይ

--- ችግር ካለ በማስተካከያ አድርጉ እና

ይቅርታ መጠየቃቸውን ነው የማውቀው

እኮ እሱን ነው እየጠየኩህ ያለሁት በለው ስለ እሱ እንድትነግረን ነው ለፍ/ቤቱ እንድታስረዳ

አብዱራህማንም ያው ይቅርታ ጠይቆ ወደ ሚኒሻ መመለሱን ነው የማውቀው መሀመድ አሊም ያው እንደዛው በህብረተሰቡ ላይ ይቅርታ ጠይቆ ወደ ትምህርቱ መመለሱን ነው የማውቀው

ጨርሰናል

አበቃችሁ እሺ ድጋሜ ጥያቄ ይኖራል ዐ/ሕግ

የለንም

ድጋሜ ጥያቄ የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ የሰሩትን ታውቃለህ ወይ

ከእዛ በኋላ አላውቅም

እሺ እናመሰግንሀለን መሄድ ትችላለህ ጨርሰሀል ማን ይጠራላችሁ ስንተኛ ነው

46ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ነው የሚመሰክረውም በ12ኛ በ13ኛ በ16ኛ በ17 እና በ18 ተከሣሾች ላይ ነው

ምስክሩ ይጠሩ

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

700

ስም - ኡመር አብዱላሂ

አድራሻ - ከሚደጋ አና ቶላ ከእዛ ወረዳ ነው የመጣሁት

ጥሩ ለምስክርነት ነው የቀረብከው

አዎ

በማነ ላይ ነው የምትመሰክረው

አብዱራህማን ሁሴን ሸሪፍ ኡመር ረብላ ሸሪፍ ሰይኖ መታን እነዚህ ናቸው

ጥሩ ታውቃቸዋለህ

አውቃቸዋለሁ

ፀብ ዝምድና አለህ

የለንም

እስቲ አሳየን ተነሳና እሺ ጥሩ ምስክሩ ከተከሣሾች መሀል 5ቱን 6 ሰው ለይቶ አሳይቷል ስምሽ ማነው የአንቺ ስም ማነው ጠይቃት እስቲ ስምሽ ማነው በላት ስንተኛ ቁጥር ላይ ነው ያለሽው ረበላ ሸሪፍ ነሽ

13 ላይ ነው

13ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ማነው ስምሽ

ረብላ ሸሪፍ

ስንተኛ ቁጥር ነሽ ዐ/ሕግ ስንት ላይ ናት

13 ነኝ

ረብላ ሸሪፍ ያንቺ ስንት ቁጥር ነው

---- ያቺኛዋም 13 እያለች ነው እቺኛዋም 13 እያለች ነው

ማነው ስምሽ የእሷ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ገ01

ዘይኔባ

ዘይኔባ ---- 16ኛ ነች

16ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል 12 አብዱራህማን ሁሴንን አሳይቷል 12ኛ ተከሣሽን ስንተኛ ቁጥር ነህ 17 ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል አንተ ነህ እሺ 18ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ማነው ያኛው አብዲሽኩር ነህ አንተ አብዲሽኩ ኡመር 17ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቱል ሽሪፋ ስንተኛ ነህ ጀማል ከድር ሳኒ ስንት ነህ ተራ ቁጥርህ ማነው ስምህ በለው እስቲ ስምህ አህ ሽሪፍ ኡመር ኤሌሞ አንተ 19ኛ ነህ እሺ 19ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ጥሩ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ኡመር እስቲ እነዚህ የለየካቸውን ማለት ነው አንድ በአንድ ምን ሲያደርጉ እንደነበር በምን እንደምታቃቸው ታስረዳልናለህ

ከማን ልጀምር

እስቲ ከአብዱራህማን ሁሴን ጀምር አብዱራህማን ሁሼን ጅብሪል

አብዱራህማን ሁሴን እንትን መጀመሪያ ተደራጅቶ ነበረ

በምነድን ነበረ የተደራጀው

እራሱ ተደራጅቶ በኋላ የአባዎን አባሎች አስይዟል ታምኖ ቀበሌ ወደ ቀበሌ ተመልሶ ከእዛ አባሎቹን አስይዟል ነው

እሱ ከምንድነው የተመለሰው ከየት ነው የተመለሰው

ከአባዎ አባልነት ተመልሶ

መቼ ነው

እኔ ቁጥሩን አላውቅም ግን እረጅም ጊዜ ነው

ምን ያህል ይሆነዋል በግምት

Ⴖ02

ያ ቆይቷል ከተመለሰ በኂላ ነው የማውቀው በ2002 ወደ እኛ ተመልሶ ሚኒሻ መሆኑን ነው የማውቀው

አሁን ስንት አመተ ምህረት ላይ ነው ያለነው ብለህ እስቲ ጠይቀው

2002 ነው

እና በዚህ አመት ተመልሶ ሚኒሻ ሆኖ ነበር

ከታሰረ አንድ አመቱ ነው ነው የሚለው

ስለዚህ አሁን አንተ በዛን ጊዜ ማለት ነው ከመታሰሩ በፊት የምታውቀውን ነገር ስለ እሱ እንድትነግረን ነው የተፈለገው

እኔ በምን እንደተደራጀ አላውቅም ያው መያዙን ነው የማውቀው

ቅድም በአባዎ ተደራጅቶ ነበረ ተመለሰ ያልከውስ ከየት አምጥተህ ነው ታዲያ

አባል ሆኖ ተይዟል ማለትን ነው የሰማሁት

አንድ አካባቢ ነው የምትኖሩት

አንድ ሀገር ነው ያለነው

የት ነው የምትኖሩት

ሁሉም አርሶ አደር ነው ያው

የት ነው የምትኖሩት ሀገሩ ስሙ እሺ እዚህ ሚደጋ ውስጥ ነው

ነጋያ ሚደጋ ------- ኒደጋ የሚባል ወረዳ ነው

እሺ የአባዎ አባል መሆኑን ሰማሁ ብለህል እ እስቲ እነዴት ነው ልታውቅ የቻልከው ይሄንን ልትሰማ የቻልከው በምን ምክንያት ነው

እኔ የሰማሁት ተይዘው ወደ ቀበሌ መምጣታቸውን ነው

ከየት ነው የተያዙት

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ቁጥር 4

ከከተማ ውስጥ ተይዘው መጥተው ቀበሌ ላይ ይቅርት መጠየቃቸውን ነው የማውቀው

እስቲ ይቅርታ ሲጠይቅ ምን አለ ምን ብሎ ይቅርታ ጠየቀ

ከእንግዲህ በኋላ አልመለስበትም ከእዚህ በኋላ

ቆይ ለምንድነው አልመለስም ያለው

ምን አልከኝ

ወደ ምንድነው ከእንግደህ በኋላ አልመለስም እያለ

ከእንግዲህ በኋላ ያን እንትን ያደራጀውን ክፍል ወደ እዛ ወደ አደራጀዉ ክፍል አልመለስም አለ

ወደ ምኑ ነው ያደራጀው ክፍል አልመለስም ያለው

እኔ ይሄንን ነው የሰማሁት ምን እንደሆነ አላውቅም

እኮ ይቅርታ ጠየቀ 2ኛ ወደ እዚህ አልመለስም እያለ ነበር ብለካል አይደለም

ከእንግዲህ በኋላ ወደ እነሱ አልመለስም

ወደ እነማነው አልመለስም ያለው

ከዚህ በኋላ ወደ አባዎ አልመለስም ከእነሱ ጋርም አልደራጅም ነው ያለው

እሺ ረብላንስ ረብላ ሽሪፍን በሚመለከት እስቲ ምንድነው የምታውቀው በእሷ ላይ

ያው ያኔ ረብላም አብራ ነው የተደራጀችው

ከማን ጋር ነው አብራ የተደራጀችው

አብዱራህማንም ረብላም ሰይብሎም አንድ ጋር ነው የተደራጁት

ቆይ አብዱራህማን ረብላም እና ማን

ሰይኖ አንድ ጋ ነው የተደራጁት

ሰይኖ ሰይኖ ሰይኖ የትኛዋ ነች ቆይ

ልጅ ያላት

እሺ ዘይነባን 16ኛን እሺ አብዱራህማን ረብላም ዘይነባም አንድ ላይ ናቸው በለሀል እስቲ

10 10 ብር ጫት ግዙልን ብለውን መጡ የ10 10 ጫት ግዙልን ብለው እዛ ውስጥ ተይዘው ጫቱም እላያቸው ላይ ተይዟል ነው የሚለው እዛ ላይ ነው ቀበሌው ይቅርታ ጠይቀው እዛ ላይ ነው እንትን ቀበሌው ይቅርታ ያደረገላቸው

የ10 10 ብር ጫት ግዙልን ብለው የተያዘው በለው ምን ስለሆኑ ነው የገዛችሁላቸው ለምንድነው የገዛችሁላቸው በለው

እንደ መልክተኛ ነው ያደረጉት

ምን ማለት ነው አልገባኝም የምን መልክተኛ

ከከተማ ጫት ግዙ እና አምጡልን ብለው በእዛ ላይ ነው የተያዙት

ማነው ከከተማ ጫት ገዝታችሁ አምጡልን ያላቸው እነማን ናቸውስ በምን የተደራጁ ሰዎች ናቸው

አባዎ ነው

አባዎ ናቸው

አባዎ ናቸው

ኦኬ አንተ አዋጥተካል ወይ

እኔ ያዋጣሁት ነገር የለም እነሱ ይቅርታ ሲጠይቁ ብቻ ነው የሰማሁት

እሺ ይሄንን ብለሀል ከዚህ በተያያዘ እስቲ ዘይነባ ዘይነባ ላይ ከዚህ ሌላ የምታውቀው ነገር አለ ወይ

የቅርታ ከጠየቁ በኋላ ቤታቸው መጥተው ምክላከያ ሲፈትሽ ነው የማውቀው

ከማን እቤት

ከዜይነባ አባት እቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምን ተገኘ ታዲያ ሲፈተሽ

አንድ ቀያይ ትንንሽ ነገር --------- መገኘታቸውን ነው የማውቀው

ምንድነው የተገኙት ቀያይ ትንንሽ ነገሮች ግለፀው

ባንዲራ ነው ሲባል ነው

የምን ባንዲራ ነው

የአባዎ ባንዲራ ነው

ምን ያህል ነው ብዛቱ

2 ፍሬ ነው

ከእሱ ሌላስ የተገኘ ነገር አለ ወይ

ጥይት ተገኝቷል ግን ወንድሟ ሚኒሻ ስለነበረ እሱም ሞቷል የእሱ ነው

ምን ያህል ነው

እኔ አንድ ካዝና እና ግማሽ ይሆናል 50 50 ፍሬ ያክላል ወደ 53 አካባቢ ይሆናል

ይሄንን ብቻ ነው ያገኛችሁት ከዚህ ሌላስ ያገኛችሁት ነገር አለ ወይ

ከዚህ ሌላ ምንም እዛ እቤት ውስጥ ያየነው ያገኘነው ነገር የለም

እሺ ጥይቱ የምን ጥይት ነው የምን መሳሪያ ነው

የክላሽ እና 3 አባ የሚንቶብ ነው

እሺ የክላሽ እና 3ቱ ፍሬ ደግሞ

የሚንቶብ ነው

የሚንቶብ መሳሪያ ነው

እሺ አብዱሽክሩስ ላይ የምታውቀው ምንድነው አብዱሽኩር ኡመር ላይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት

706

ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል እና አብዱሽኩር ፌደራል መጥቶ ሲወስዳቸው ነው እንጂ በእነሱ ላይ ምንም የማውቀው ነገር የለም

ምን ብሎ ነው የወሰዳቸው

ፌደራል ወሰዳቸው ነው መባሉን ነው እንጂ እኔ ስለ እነሱ ከእነሱ ጋር ምንም ንግግር የለኝም ነው የሚለው

ስለ እነሱስ የሰማከው ነገር የለም

ምንም አልሰማሁም አላውቅም

እሺ ሽሪፍ ኡመርንሳ በሚመለከት

መጀመሪያ ሽሪፍ ኡመር ተይዞ ሀረር ሀረር እስር ቤት አንድ አመት ታስሮ ገባ ተመለሰ

መቼ ነው የታሰረው

ሳይያዝ በፊት ሳይያዝ በፊት ነው የተያዘው ሳይያዝ በፊት ነው የታሰረው

እሺ አሁን ሳይያዝ በፊት ታሰረ አልከን አይደለ ያኔ የታሰረበት ዐ/ምቱ ምን ያህል ነው ስንት አመተ ምህረት ላይ ነው በለው

ያንን አመተ ምህረቱን አላውቅም

እሺ በምን ምክንያት ነው የታሰረው

ለአባዎ ተደራጅ ተብለው ነው ይዘው ያሰሩት እኔ እንኳን እሱን አላውቅም

እሺ ካሰሩትስ በኋላ ታሰረ አንድ አመት አልከን ታስረው ከተለቀቀስ በኋላ

ከተመለሰና ወደ እቤቱ ከተመለሰ በኋላ ብዙ ጊዜያትን ሳይቆይ ፌደራል መጥቶ ቤቱን ፈትሾ እሱንም ወሰደው

ምን አገኘ ቤቱ ሲፈተሽ

እቤት ውስጥ አንድ ጠመንጃ አለ ቀበሌ የሚያውቀው የወንድሙ መሳሪያ ነው የሚለው ያንን መሳሪያ ከቤቱ ወሰዱ ነው የሚለው

ፌደራላዊ ጠ/ፍ/ቤት ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ከእዚህ ሌላስ የተገኘበት ነገር አለ ወይ

ሌላ እዛ እቤት ውስጥ ምንም የተገኘ ነገር የለም

እሺ ምን አድርገል ተብሎ ነው ታዲያ የዛን ጊዜ ከተለቀቀም በኋላ በድጋሚ የተያዘው የታሰረው

አንድ ሰውዬ ነው አንድ ከአባዎ የገባ ሰውዬ እሱ ነው መጥቶ የወሰደው

እሱ ነው የወሰደው

አዎ

ከአንድ ከአባዎ ውስጥ የነበረ ሰውዬ እና የገባ እሱ ነው መጥቶ ይዞት የወሰደው

መከላከያ መጥቶ ወሰደው አልከን

ፊት አባዎ ነበረ

እሺ

እና ከመከላከያ ጋር ነው የሚሄደው ነው የሚለው

ማን

ይሄ --- ተመለሰ የሚለውን ሰውዬ ነው የሚለው

ደንበል የሚባለውን ማለት ነው

አዎ

እሺ

እሱ ነው ከእነሱ ጋር ይዞት ነው የሄደው ነው የሚለው

በቃ እሺ ጨርሰናል

አበቃችሁ ዐ/ሕግ

ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ችሎት 4

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

------- አብዱሽኩር ኡመር እና ማንን ነው በልልኝ እስቲ

ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል

ኢብራሂም

መሀመድ ጅብሪል

ስለ እነሱ ምንም የሚያቁት ነገር የለም

ምንም ነገር አላውቅም ፌደራል ነው የወሰዳቸው

እሹ ዜይነባን በተመለከተ --- ከእቤትዋ ውስጥ የክላሽ ጥይት ተገኝቷል ብለዋል ወንድሟም ሚኒሻ ነበር ብለዋል ወንድሟ ሚኒሻ ሆኖ ምን አይነት መሳሪያ ነበር የሚታጠቀው

ክላሽ ነው ክላሽ ነው የሚታጠቀው

ክላሽ ነው የሚታጠቀው ስለዚህ በእቤትዋም የተገኘው

እ

በእቤቷ ውስጥም የተገኘው ጥይት የሚኒሻ ወንድሟ የነበረው ጥይት እንጂ አባዎ መሆን አለመሆኑን ያውቃሉ ወይ

ከእዛ በኂላ ነው የገመገምነው

ስለዚህ የወንድሟ ጥይት እንደሆነ ነው የሚያውቁት

ቤተሰቡ በሙሉ የመሰከረው ልጁ ሞቷል የወንድሟ ነው ብለው ነው ቤተሰቡ በሙሉ የመሰከረው

እሺ ከእዛ ውጪ አባዎ ውስጥ እሷ ትደራጅ አትደራጅ የሚያቁት ነገር አለ እንዴ ዜይነባ

ተቃውሞ አላችሁ

ቆይ ቆይ አንዴ ቆይ አንዴ መቃወሚያ ይመዝገብ

በዋና ጥያቄያችን ላይ አብዱራህማን ዜይነባና ረብላ አብረው በአባዎ ተደራጅተው ነበር ብለው ተናግረዋል ለዚህ በድጋሜ መጠየቁ አስፈላጊ አይደለም ስለዚህ 1ኛ ለማፍረሻም አይባልም ስለዚህ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም

በእናንተ በኩል በእኛ በኩል መልስ አለን --- በዋና ጥያቄ የተጠየቀው ላይ ነው በትክክል ቃላቸውን ለመፈተን የምናቀርበው ጥያቄ ስለሆነ በዋና ጥያቄ ላይ ነው መጠየቅም ያለብን ስለዚህ ተገቢ የሆነ ጥያቄ ነው

እሺ ጥያቄው ይቀጥል

ዘይነባ አባዎ ውስጥ ተደራጅታ መሆን አለመሆንዋን የሚያውቁት ነገር አለ ዜይነባ

ቅድም ከተናገርኩት ውጪ ምንም የማውቀው ነገር የለም

--- ጥያቄውን የመመለስ ግዴታ አለበዎት በላቸው

እኔ በይቅርታው ጊዜ ስለ 10 ብሩ ብቻ ነው እንጂ የማውቀው ሌላ የማውቀው ነገር የለም

ስለዚህ ሌላ የሚያውቁት ነገር የለም እርግጠኛ ሁኑ በላቸው

------- ምንም አላውቅም

እሺ 10 ብሩን በተመለከተ -- በተመለከተ እዛው ከተማ ውስጥ ከእዛ በፊት ጫት አትነግድም ወይ እሷ

ፊት ለሚኒሻ ነው የሚሰሩት እና ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ

በምን አወቁ ለሚኒሻ

አንድ ሀገር አይደለም ወይ ያለነው ለሚኒሻ መስራታቸውን አውቃለሁ አንድ ሀገር ነው ያለነው ነው

እኮ በምን አወቁ ነው ጥያቄው

እኔም አብሬ ነው ያለሁት ጥይትም እኔም እዛው አንዱ ጋ ነው ጥይት የተተኮሰብን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

7/10

እኮ አብረው ምን ይሰሩ ነበረ የዛኔ

የቀበሌ ሊቀመንበር ነኝ ነው የሚሉት

ስለዚህ ---- ሲነግዱ ለአባዎ ሲሰጥ እርሶ ነበሩ ወይ ነው

እሱ ከእኔ በፊት ነው እኔ የሰማሁት አይደለም እኔ ያው በይቅርታው ጊዜ ነው የሰማሁት

ስለዚህ ያዩት ነገር የለም ማለት ነው

ምንም ያየሁት ነገር የለም እኔ ምንም እኔ ለምን እደብቃለሁ

እሺ አብዱራህማን ሁሴንን በተመለከተ አባል ከነበረ በኋላ ተመልሶ ሚኒሻ ሆኗል ብለዋል ሚኒሽ እያለ ነው ወይ የተያዘው ለመንግስት እያገለገለ

አዎ ሚኒሻ ከሆነ በኋላ ነው ፌደራል መጥቶ የወሰደው

እሺ ----- እነደዚሁ መንግስት የሚያውቀው ጠመንጃ አንድ ጠመንጃ አለው ብለዋል እሱም መንግስትን እያገለገለ ነው ያ ጠመንጃን የተሰጠው

እሱ ለመንግስት ምንም አይሰራም መሳሪያው የወንድሙ ነው

ታዲያ መንግስት እንዴት ሊያውቀው ቻለ እርሶ እዛ ሊቀመንበር ከሆኑ የቀበሌው

የመጣው ሰውዬ ነው ስሙን የነገረን እና ፌደራል ጋር የመጣው ሰውዬ ነው ውሰዱን እኛን ያለን

የእነዚህ ተከሣሾች ቀበሌ ውስጥ የእዛ ቀበሌ ሊቀመንበር ነዎት ወይ

የመጀመሪያውን ኦ ኤል ኤፍ ገድሎት እኔ በእዛን ሰአት ነው የሆንኩት

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ሁሉም ላይ አሁን የመሰከሩባቸው ላይ 6 ሰዎች ጠቁመው አሳይተዋል 4ቱን 2ቱ ላይ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም 4ቱም ላይ ግን ሲባል ሰማሁ እንጂ ሲያደርጉ ምንም መንግስት የሚጐዳ ነገር ሲያደርጉ በአይናቸው አይተው አያውቁም አውቃለሁ ወይም አላውቅም ብቻ ብለው እንዲመልሱ ነው የምንፈልገው

ይሄ ከእኔ በፊት ነው እኔ የማውቀው ነገር የቆየ ነው እኔ የማውቀው ነገር አይደለም

7/11

የሚያቁት ነገር የለም

አዎ ከእኔ በፊት

በቀጥታ ማለት ነው እኔ ፌደራል ብቻ መጥቶ ከእዛ መልቀሙን ነው እንጂ ሰዎቹን የማውቀው ሌላ የማውቀው ነገር የለም ነው

ጨርሰናል

ድጋሜ ጥያቄ ይኖራቹሀል ይመዝገብ ለሪኮዱ

የለንም

ድጋሜ ጥያቄ የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

12ኛ ተከሣሽን በተመለከተ አብዱራህማን ሁሴንን በተመለከተ ተመልሶ የሚኒሻ አባል ሆኗል ብለሀል ረብላንም እንደዚሁ

አቤት

ከሚኒሻ ጋር ስትሰራ ነበረ ብለካል

ምግብ ትሰራ ነበረ ነው የሚለው

እያልክ ያለከው ሚኒሻ የኦነግ ሚኒሻ ነው ወይስ የመንግስት ሚኒሻ ነው

የመንግስት ነው

ቀጥሉ

የመንግስት ነው እኔ በዛን ሰዓት ነው ወደ ቀበሌ የመጣሁት

አሁን ለምሳሌ ከህዝብ ፊት ይቅርታ ጠይቀው ከተመለሱ በኋላ ኢብራሂም ሁሴንና ረምላ ለመንግስት ያመለከቱት ነገር አለ ወይ አብዱረህማን ሁሴን ማለቴ ነው እና ረምላ

7/2

እዛ ምግብ ለጦሩ ምግብ ይሰሩ ነበር በዛን ሰዓት በተደረገው ጦርነት ሰው ስላለቀብን የወረዳው ጦር ተመድቦ ጦሩም እዛ ነው ያለው

ለየትኛው ጦር ነበር ትሰራ የነበረው ምግብ አብዱረህማንስ

አብዱረህማን ከተመለሰ በኂላ አብሮን እዛው ተተኩሶብን እዛው 6 ሰው ሞተብን አብዱረህማንም እዛው ከእኛው ጋር ነው

አብዱረህማን ከማን ወገን ሆኖ ነበር ይተኩስ የነበረው

ከመንግስት ጋር ሆኖ ነው ከቀበሌ ጋር

ከማን ጋር ነበር ሲታኮስ የነበረው

ከቀበሌው ሚኒሻ ጋር ነው ኦ ኤል ኤፍን ሲመታ የነበረው

እሺ የእነዚህ የኢነብ አባት ቤት መሳሪያ ተገኝቷል ብለከን ነበር

ክላሽ ነው የተገኘው

በመቀጠል ደግሞ ይህ መሳሪያ የወንድሟ ነው ወንድሟም ሚኒሻ ነበር ብለሃል ጥያቄ አልጨረስንም እኮ እና ወንድሟ የማን ሚኒሻ ነበር

የቀበሌ ሚኒሻ ነው

የኦነግ ነው ወይስ የመንግስት ነው

የመንግስት ነው

ይህ መሳሪያ የሱ መሆኑን እንዴት አወቅህ አንተ

መንደሩ ሁሉ ነው የመሰከረው ጠመንጃው እዛ የለም ጥይቱ ግን የእሱ ነው ብለው መንደሩ ሁሉ ነው የመሰከረው

ጠመንጃው የት ነበር ያን ጊዜ

መሳሪያው ተይዞ በቁጥር በቁጥሩ ፎቶ ነው በዛን ሰዓት ያወጣው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

713

ከማን ላይ ነው የተያዘው

እዛ የልጁ የሞተው ነው ወረቀት አለው እና ወዲያው መከላከያ አይቶት ወዲያውኑ መሳሪያውን ለቀቀ

የወንድሟ የዛ የሞተው የሚኒሻው መሆኑ ተረጋግጧል እንዴ

ይደገም

የወንድሟ መሆኑ ተረጋግጧል ወይ ክሳሹ አሁን መከላከያ ወረቀት አይቶ ለቀቀ ብለሃል

እሺ በዚሁ አብቅተሃል እናመሰግናለን መሄድ ትችላለህ ዐ/ህግ የአበል በተመለከተ ምስክር አልቋል አደም

አዎ አበላቸው በጽ/ቤት በኩል ይፈጸማል ነገር ግን አሁን ካሉት ከቀሪ ምስክሮች በተጨማሪ ትላንትና የመሰከሩት 51ኛ፣ 63ኛ እና 64ኛ ምስክሮች በ8ኛ ተከሳሽ

51ኛ፣ 64ኛ እና

51ኛ፣ 63ኛ እና 64ኛ ትላንትና ፋጥሽ በምትባለው ፋጤ አሜ በምትባለው በ8ኛ ላይም ሊመሰክሩ ነበር ጭብጥ ስናስይዝ በእሷም ላይ እንደሚመሰክሩ አስረድተን እነሱም እሷን ጠርተው ነበር ትላንትና በህመም ምክንያት ስላልመጣች ነው ያልተመሰከረባት በቀጣይ ቀጠሮ ላይ እነዚሁ ምስክሮች ተጣርተው እንድናቀርባቸው ፍ/ቤቱ ቀጠሮን በተመለከተ እንዲታዘዝልን

ጥሩ ጀናን በተመለከተስ የምታመለክቱት ነገር አለ

ጀናን በተመለከተ የምናሳስበው ያው ፍ/ቤቱ በዋስ ከለቀቃት በኋላ እዛ እያለች ምስክሮችን ያው ፍ/ቤቱ እንደተረዳውም በግልጽ እንዳስረዱት እያስፈራራች ነው

ጀና ተነሽ

እያስፈራራችብን ያለበት ሁኔታ ነው ያለው ስለዚህ ሌሎች ምስክሮች እዛው አካባቢ ያሉ ስለሚኖሩ በተለይ ደግሞ ያልተገኙና ያልመጡ ስላሉ በምስክር አቀራረባችን ላይ በዚህ መልኩ እያስፈራራችብን አስቸጋሪ ስለሚሆን ዋስትናዋ ተነስቶ እዚሁ በማረሚያ ሆና እንድትከራከር ነው የምናሳስበው።

ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

አስተርጓሚ እስቲ አስተርጉማት አሁን የተባለውን በዐ/ህግ በኩል አሁን የተባለው በላት አንቺ ይሄ ፍ/ቤት ዋስ ፈቅዶ ከወጣሽ በኂላ በምስክር ላይ ተከታታይ የሆነ የማስፈራራት ስራ እያደረግሽ ነው ምስክር እያስፈራራሽ ነው የዋስትና ግዴታሽን አላከበርሽም ስለዚህ ዋስትናው ተነስቶ ማረሚያ ቤት ትግባልን ነው ያሉት ዐ/ህግ ጥሩ በዚህ ነጥብ ላይ ተከላካይ ጠበቃ የምታነሱት ነገር አለ

የተከበረው ፍ/ቤት

ይመዝገብ ስጧቸው እስቲ

ዐ/ህግ ያቀረቡት ምክንያት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ-ስርዓት አንቀጽ 74 መሰረት አንድ ዋስትና የተሰጠው ሰው ፍ/ቤቱ ነው ዋስትና ሊያነሳበት የሚችለው አዲስ ነገር ተገኝቶ ከሆነ ነው ዐ/ህግ ባመለከቱት መሰረት ወይ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት አዲስ ነገር አልተገኘም ስለዚህ የተከሳሿ የዋስትና መብት ሊነሳ የሚችልበት የህግ ምክንያት የለም ነው በእኛ በኩል የምንለው።

እሺ ጨረሳችሁ አደለም

ይሄንን የተፈቀደበትን ምክንያት በወቅቱ ዋስትና ሲፈቅድ ፍ/ቤቱ የተሰጠበትን ምክንያት አላወኩም እና

ጠይቁና እሺ ጥሩ

ተጨማሪ ነገር የተከበረው ፍ/ቤት ---------- ዋስትናም የተፈቀደላት በወሊድ ምክንያት ነው ስለዚህ ምናልባትም እንኳን የቀረበውን ምክንያት በዐ/ህግ በኩል----------- በማስጠንቀቂያ ---------- ምክንያቱም ህፃን ልጅ ወልዳ ነው ባለፈውም ዋስትና የተፈቀደላት እና ለህፃኑም ደህንነት ሲባል በበቂ ማስጠንቀቂያ ቢያልፉት ጥፋተኛ

እሺ የምትሉት ነገር አለ

የተከበረው ፍ/ቤት እኛ አሁን ለተነሳው አዲስ ነገር ለተባለው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት 67 መሰረት ማለት ነው ምስክር ያሸሽ ያሚል በቂ ጥርጣሬ ካለ ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን ሳያከብር ሊጠፋ የሚችል መሆኑ በቂ ጥርጣሬ ካለ እያለ ህጉ ይዘረዝራል አሁን ከበቂ ጥርጣሬ አልፎ በተጨባጭ ምስክር እያስፈራራች መሆኑን ለፍ/ቤቱ በማያሻማ ሁኔታ ምስክሩ ቀርበው

አስረድተዋል ስለዚህ ይሄ ደግሞ ከአዲስም ነገር ባለፈ ነው አለ ለእኛ አዲስ ነገር ነው ይሄ ማስፈራራቷ እንዲህ ማድረጓ አዲስ ነገር ነው ስለዚህ ከዚህ በላይ በዋስትና ለማስከበር በቂ ምክንያት የለም ዋስትና በሚሰጥበት ሰዓት ላይ ማለት ነው እንደዚህ አይነት ነገሮች አይከሰቱም በሚል ነው ጥርጣሬ ቢኖር እንኳን ዋስትናው እንደሚከለከል ህጉ ይደነግጋል አሁን ደግሞ ይሄ አዲስ ነገር ነው እንደገና ደግሞ ወሊድም የተባለውም ቢሆን ወልዳ አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያለችው ሌሎችም ወልደው ልጅ የያዙበት ሁኔታ የምናይበት ሁኔታ አለ ስለዚህ የአራስ ጊዜዋንም የጨረሰች ስለሆነ ምስክሮችም ደግሞ አሁንም የሚቀርቡ ከዛ አካባቢ የሚመጡ በርካታ ምስክሮች ስላሉ ያልቀረቡትም አወዳይ አካባቢ ያሉ በርካታ አወዳይ ቀርበው ነው እሷ ያለችበት አካባቢ ማለት ነው ስለዚህ ምስክር አቀራረብ ላይ ለፍትህ አሰጣጥ እጅግ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ስለሆነና በህጉም ላይ በግልጽ የተደነገገ ስለሆነ ዋስትናዋ ወርዶ ማረሚያ ሆና እንድትከራከር ነው፡፡

እሺ በዚህ መዝገብ ላይ በተነሳው በግራቀኛችሁ በተነሳው በጀና በ22ኛ ተከሳሽ ጀና መሀመድ አዳስን በተመለከተ ዐ/ህግ የዋስትና ጥያቄ ተነስቶ በማረሚያ ቤት ሆና ክርክሯን እንድትቀጥል በማለት ያነሱት ክርክር ላይ የግራ ቀኙን እንዲሁም የተከሳካይ ጠበቃው ክርክር እንደዚሁም የዐ/ህግ መልስ በተጨማሪ ተመዝግቦ ተቀርጿል ፍ/ቤቱ ጥቂት ደቂቃዎችን ወስዶ ከችሎቱ በጉዳዩ ላይ ተመካክሯል በአጠቃላይ በመዝገቡ ውስጥ የተመዘገበው ሂደትና ክርክር የተነሱትን ክርክሮች ከህጉ አንፃር መርምሮና ተመልክቶ በዚህ ጉዳይ ላይ ብይን መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ለዚሁ አጀንዳ ይያዛል በተመሳሳይ በቀሪው የዐ/ህግ የምስክሮች አቀራረብን በተመለከተ በሚሰጠው የጊዜ ቀጠሮ ላይ የሚታይ ይሆናል ስለዚህ አጀንዳ እንይዛለን ማለት ነው ለብይኑ እስከዛ 22ኛ ተከሳሽ ጀና በጣቢያ እንድትቆይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል ቀጣይ ቀጠሮ ለመጋቢት 23 ዐ/ህግ ቀሪ ምስክሮቻችሁን እንድታቀርቡ ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ሰጥቷል በዚህ ምስክርነት መስማት ሂደት ፍ/ቤቱን በትርጉም የረዱት በሁለቱም ቀናቶች በአስተርጓሚነት ለረዱት አቶ ምንዳ እና ለአቶ ሻረው በደንቡ መሰረት የፍ/ቤቱ አስተዳደርና ፋይናንስ ክፍያ እንዲፈጽሙላቸው ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል ዐ/ህግ ቀሪ ምስክሮቻችሁን ለመጋቢት በተያዘው ቀጠሮ እንድታቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል በሌላ በኩል የካቲት 25 እና የካቲት 26 የነበሩትን በመደበኛ የተያዙት ቀጠሮዎችን በተመለከተ አስቸኳይ ጉዳዮች ከመሆናቸው የሚቀርብ ካለ በማመልከቻ ወይ በአቤቱታ ወደፊት እየተሳበ መታየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ቀጠሯቸው የካቲት 25 እና 26 ለሚያዝያ 14 እና 15 ተላልፏል ይኸው በማስታወቂያ ስሌዳ እንዲገለጽ ፍ/ቤቱ በጥብቅ አዟል

716

የካቲት 25 እና 26ን በተመለከተ ግን በአቤቱታ እና በአስቸኳይ ጉዳዮች የሚመለከቱ ጉዳዮች ከተነሱ በማንኛውም ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ቀርቦ ችሎቱን እየሳበ ቀጠሮ ማየት እንደሚችል በዚሁ ግንዛቤ እንዲያዝ በዚሁ መሰረት በዚህ መዝገብ ላይ ያለው የክርክር ችሎት እንደዚሁም ለዛሬ የተያዘው ቀጠሮ በዚሁ አብቅቷል ማረሚያ ቤት ተነግረው መሰረት።

ማ/ተ

717

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 23/7/2002 ዓ/ም

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ በዚህ መዝገብ ተሰይመናል

ከሳሽ - ዐ/ህግ አቶ ማሙሸት አበበ እና አቶ እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ ከማረሚያ ቤት 68 ሰዎች ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው የዐ/ህግ ምስክሮች ካሉ ለመስማት ነው በዚህ መሰረት በጽ/ቤት መቅረባቸው የተረጋገጡት ሶስት የዐ/ህግ ምስክሮችን መስማት ችሎቱ ይቀጥላል ጥራቸውና መሀላ አስፈጽማቸው ማን ይጠራ በቅድሚያ ዐ/ህግ

አብዲ ሼክ

በተጨማሪ ከፖሊስ ኮሚሽን አንድ ተከሳሽ መቅረባቸው ተረጋግጧል ለሁሉም ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አቶ ሳሙኤል አሰፋ መቅረባቸውን እንደዚሁ ተረጋግጧል ፍ/ቤቱ ምስክርነቱን መስማት ይቀጥላል ስንተኛ ምስክራችሁ ናቸው 81ኛ ማን ናቸው አቶ ፋሚ ኢብራሂም በስንተኛ ላይ ነው ጥሩ ምስክሩን ጥሯቸው መሀላ አስፈጽሙ አቶ ፋሚ ኢብራሂምን

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ፡፡

ጥሩ በዛሬው እለት አንድ ምስክር ቀርቧል በአስተርጓሚ እየተረዳ

የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አሚን ጣሂር

አድራሻ- ገደገራ አውዲ ይባላል

ለምስክርነት ነው የመጣከው

አዎ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ኑሬ ኡስማን ጭሮ ላይ

ፀብ ዝምድና አለህ ከእሱ ጋር

ዝምድና የለኝም

ፀብስ

አልተጣላሁም

እስቲ አሳየን ተነሳና አቶ ኑሬን አሳየን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ምስክሩ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

አቶ አሚን የመጣሁት ለምስክርነት ነው በአቶ ኑሬ ላይ ነው ብለህ አቶ ኑሬን ለይተህ ምንድን ነው ስለ እሳቸው የምትመሰክረው ለፍ/ቤቱ ዘርዘር አድርገህ አስረዳ በእሳቸው ላይ የምትመሰክረውን

እኔ የማውቀው እሱ ላይ ምስክርነት የምሰጠው በ2001 ዓ/ም ውስጥ እኔ ገበሬ ነኝ ፅፌም የያዝኩት ነገር የለም ስላልተማርኩኝ ቀኑን እንደዚህ በእርግጠኝነት መናገር አልችልም ህዳር 5 ቀን መሰለኝ ሌንጮ የሚባል የኦሮሞ ነፃ አውጪ ወታደር ከኑሬ ኡስማን ጋር ጫት ግዛ አሉኝ ጫቱንና ስኳሩን ገዝቼ ለኑሬ ኡስማን ሰጥቻለሁ ይሄንን ካላመጣህ ህይወትህን ታጣለህ ስላሉኝ ሰጥቻለሁ

ኑሬ ከዛ በፊት ምን ነበር

በ84 ዓ/ም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ወታደር ነበር

ከዛ በኋላስ

ከዛ በኋላም እንደዛው ነው ያው ወታደር መሆኑን ነው የምናውቀው

ሴንጮ የሚል ስም ጠርተሃል ሴንጮ ምንድን ነው

የኦሮሞ ነፃ አውጪ ወታደር ነው ሴንጮ

ከማን ጋር ነበር በወቅቱ በጠቀስከው 2001 ዓ/ም የመጣው እናንተ ጋር ከማን ጋር አብሮ መጣ 2001 ዓ/ም ህዳር 5 ብሎ በተጠቀሰው ጊዜ ከማን ጋር አብሮ መጣ

ተቃውሞ አለ እሺ ተቃውሞ ይመዝገብ

የተከበረው ፍ/ቤት የዐ/ህግ ምስክር ያስረዳል ተብሎ የሚጠበቀው በ41ኛ ክስ በክሱ በ11ኛ ተከሳሽ ላይ ባለው በክሱ ጭብጥ መሰረት ነው አሁን ግን ምስክራቸው እየመሰከሩ ያሉት በተመሰረተው ክስ አግባብና ጭብጥ አይደለም ስለዚህ አስተካክለው እንዲጠይቁልን

ከጭብጥ ውጪ ነው በአጭሩ

ከጭብጥ ውጪ ነው

እሺ በእናንተ በኩል ያለው

የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ምስክሩ እየመሰከረ ያለው ከማን ጋር በወቅቱ እንደመጣና ምን ይሰራ ነበር እነኛ ሰዎች ስራቸው ምንድን ነው ምክንያቱም ህብረተሰቡን ከኦነግ ነፃ አውጪ ግንባር አላማ ይዞ ይቀሰቅሳል ተብሎ ነው እና ያነሳሳል የሚል ክስ ነው ያቀረብነው ያን ጊዜ ከማን ጋር ነበር የሚለውን መሰረታዊ ነገር ነው ጉዳዩ ላይ ምክንያቱም ይሄ ነገር የሚያስረዳው ብቻውን ነው ከሌላ ሰዎች ጋር ነው ምን ነበር የሚለውን እየጠየቅን ያለነው እና ቀኑንም በትክክል ተናግሯል የተደረገበትን ድርጊቱ የተፈጸመበትን ስለዚህ ጥያቄአችን አግባብ ነው

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ጥያቄው ተስተካክሎ ይቀጥል ተብሏል ቀጥል

ምንድን ነው ያደረገው በዛን ቀን ከመጡ በኋላ ምን አደረገ ምን አደረገ ኑሬ ከሴንጮ ጋር ምን አደረገ ምን እያለ ነበር

የኦሮሞ ነፃ አውጪ ወታደሮች ጠዋት ላይ 10 ነበሩ ከዛ በኋላ 10 ሰዎች ደግሞ ተጨምረውበታል አለ

ከዛ ምን እናድርግ አለ

720

እኔ የማውቀው እውነቱን እስከዚህ ድረስ ነው

በወቅቱ ምን ይዞ ነበር

በእጁ ላይ ማለት ነው

አዎ

በእጁ ላይ ምንም ያየሁት ነገር የለም እኔ

የኦነግ ወታደሮች ድሮ አስር ነበሩ ብሎ የተናገረው ማን ነው

በዛን ሰዓት ላይ የመንግስት ታጣቂ ሚኒሻዎች መጥተው ስለነበረ ለእነሱ ነው የተናገረው

ቦታው የት ነው

ደደር የሚባል አካባቢ

የት ነው ደደር የሚባለው የት ነው

ደደር

ዞን ነው ምንድን ነው

በሲቃ የሚባል ዞን

ማለት አሁን በትክክል ቦታውን ንገረን የት ነው የት አገር ነው ሐረር ነው ድሬዳዋ ነው የት አካባቢ እንደሆነ ይሄንን ለፍ/ቤቱ አስረዳ

ጭሮ የሚባል

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ አለ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ቅድም ለፍ/ቤቱ ስትናገር አልተማርኩም ቀን መቁጠር አልችልም ብለህ ነበር

721

እኔ እንደተረዳሁት እንጂ አዎ ቀን መቁጠር አልችልም

እንዴት

ቆይ ቆይ ተማከሩ እርዱአቸው

እሺ ስለዚህ መቁጠር የማትችል ከሆነ ቅድም ስትመሰክር ህዳር 5 ነው ብለሃል ስለዚህ ህዳር 5 ይሄ ነገር እንደተደረገ ካወቅህ ህዳር 6 በወቅቱ ዝናብ ዘንቧል አልዘነበም ይሄንንስ ማስታወስ ትችላለህ

እኔ ተምሬ ይሄንን ዘንቧል አልዘነበም ብዬ የምለየው ነገር የለኝም የተረዳሁትን ብቻ ነው

አደለም

ተቃውሞ አላችሁ ተቃውሞ ይመዝገብ

አንደኛው ምስክራችን ይመስለኛል ይመስለኛል ያልተማርኩም ህዳር 5 ብሎ የተናገረው ሁለተኛ ዝናብ ዘንቧል አልዘነበም የሜትሮሎጂ ባለሞያ አይደለም ምስክራችን እዛ ያዩትን ነገርና የሚያስታውሱትን ነገር ሊመሰክሩ ብቻ የመጡ ስለሆነ ጥያቄው አግባብነት የለውም ነው አመሰግናለሁ

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት አንድ ምስክር ሆኖ የሚቀርብ ሰው የሚያስታውሰውን ወይ የሰማውን ነገር ሲናገር በአይን የሚታይ ወይም ደግሞ ማንኛውም ሰው ሊለየው የሚችለውን ድርጊት ይገነዘባሉ ተብሎ ነው ብቁ የአእምሮ ሁኔታም አላቸው ተብሎ ነው እዚህ መጥተው የሚመሰክሩት ስለዚህ በወቅቱ በቀጥታ ቀኑን የሚያስታውሱት ከሆነ ድርጊቱ ተፈጸመ ከተባለ ሁለት አመት ነው ስለዚህ ዝናብ መዝነብና አለመዝነብን በማየት የሚታይ እንጂ በሜትሮሎጂ ባለሞያ የሚረጋገጥ አይደለም የእኛ ጥያቄ አግባብነት እንደውም በእርግጥም ቀኑን ማስታወስ ችለው ነው አሁን እየነገሩን ያሉት ወይንስ የተጠና ነገር ነው እየነገሩን ያሉት ይሄንን ለፍ/ቤቱ ለማገናዘብ እንዲሆነው ነው ጥያቄውን እያቀረብኩ ያለሁት

አበቃችሁ አደለ

አዎ

እሺ ጥያቄው ይቀጥል እስቲ

እሺ በሚቀጥለው ምንድን ነው

መልሱን ስጠን በለው ዝናብ ዘንቦ ነበር አልነበረም

ተናገረ ይሄንን እኔ መለየት አልችልም ብሏል ተናግሯል

ሌላ ጥያቄ

እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በወቅቱ አንተ ተናገረ ያልከው ለመንግስት ወታደሮች ነው

ተቃውሞ አላችሁ እሺ

ቅድም የተናገረው ነገር ይሄ አይደለም ምናልባትም ምስክሩ እንዳያሳስቱት ነው የመንግስት ወታደሮች አላለም ሚኒሻ ታጣቂዎች ነው ያለው እሱ በትክክል እና ይሄንን ከዚህ ጋር አያይዘን

እናስተካክላለን ችግር የለም

አስተካክሉ ፍ/ቤቱም እየተከታተለው ስለሆነ

እሺ የሚኒሻ ወታደሮች ማለት ሚኒሻዎቹ የማን ናቸው የመንግስት ናቸው የኦነግ

የመንግስት ናቸው

ስለዚህ ለመንግስቱ ወታደሮች ኦነግ 10 ነበር ሲጀምሩ ማለቱ ለምንድን ነው እንደዛ ያላቸው አንተ ከነበርክ በወቅቱ ለምን እንዳላቸው

ይደገምልህ ወይ ጥያቄው በለው

ጥያቄው ይደገምልኝ

ስለ ኦነግ የነገራቸውን ለሚኒሻዎቹ ከሆነ ለምን -----------

ለምን እንደተናገረ እኔ አላውቅም እንደዚህ ብሎ ተናገረ እንጂ ለምን እንደተናገረ እኔ አላውቅም

ሌላው ጫት ተገዝቷል ብለሃል እና ጫቱን የገዛው ማን ነው ለምንድን ነው የተገዛው

የገዛሁት ጫቱን እኔ ነኝ የገዛሁት ምክንየቱም ህይወትህን ታጣለህ እንገልሃለን ስላሉኝ ነው የገዛሁት

722

ሌላ ጥያቄ

ታዲያ ከአሁኑ ተከሳሽ ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለ

እኔ ህይወትህን ታጣለህ ስላሉኝ በቃ ተገድጄ ነው የገዛሁት ለዚህ ነው የገዛሁት

እነማን ናቸው ያሉህ

ሌንጮና ኑሬ ኡስማን ጭሮ

ኡስማን ማለት አሁን እዚህ የለየክልን ሰው ነው

አዎ

ኑሬ ኡስማን ነው በለው

አዎ ኑሬ ኡስማን ነው

እሱ ታዲያ በወቅቱ የኦነግ አባል ነበር እንዴ

እኔ እሱ ታጣቂ ወታደር ይሁን አይሁን ማወቅ አልችልም ግን እኛ ወዳለንበት ስለመጣ ነው

በቃ ጨርሰናል

አበቃችሁ ድጋሚ ጥያቄ ይኖራል ዐ/ህግ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

የኦነግ ወታደር ነው ብለከናል በለው ተከሳሹ የኦነግ አባል ወታደር ስለሆነ

አዎ

በምንድን ነው የለየከው

ከሰዎቹ ጋር መጥቶ ጫት ግዛና አምጣ ስላለኝ

723

ማን ናቸው ሰዎቹ

አንዱ ሴንጮ የሚባለው ብቻ ነው ወታደሩን ስሙን የማውቀው እሱን ነው የተረዳሁት

ሴንጮስ ያልከው

ሲልከኝ በአይን አይቼዋለሁ

እሱ ታጥቆ ነበር ወይ ተከሳሹ

በዛን ሰኣት ላይ እጁ ላይ ምንም እቃ አላየሁም

ሌላ ከሴንጮ ጋር ስላየከው ነው እንጂ ሌላ ምን ማስረጃ አለህ እሱ የኦነግ ወታደር ስለመሆኑ

ጫቱ ከተገዛ በኂላ ሴንጮ አይደለም ጫቱን የተቀበለኝ እሱ ነው ጫቱን አምጣ ብሎ የተቀበለኝ

ማን ነው የቃመው ጫቱን ሴንጮ ነው ወይስ ራሱ

ከእኔ ላይ የወሰደው እሱ ነው

ለማን ሰጠው ታዲያ

ከእኔ ላይ ወስዶ መሄዱን እንጂ ለማን እንደሰጠ አላውቅም

የኦነግ ወታደር ሆኖ ታጥቆ አይተከዋል ወይ

እኔ በ84 ዓ/ም እኔ ህፃን ነበርኩ በዛን ወቅት አይቻለሁ

ከዛ በኂላ ታሀድሶ ስለመግባቱ የምታውቀው ነገር አለ ወይ

አብረው መጥተው ጫት ግዛ ማለቱን ነው የማውቀው

ከዛ ውጪ ሌላ የምታውቀው ነገር የለህም

ይሄንኑ ነው የማውቀው

እሺ እናመሰግናለን መሄድ ትችላለህ ጨርሰሃል ማን ይጠራላችሁ ስንተኛ ናቸው አቶ ዋሂድ በስንተኛ ላይ ነው እሺ ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር ቀርቧል መሀላ ፈጽሟል

ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

724

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ፡፡

ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አብዱልዋሂድ መሀመድ ሼክ አብዱረህማን

አድራሻ- በአዌ በቲና ገዲሃሪያ ከሚባል ቀበሌ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ኑሬ ኡስማን ጭሮ

ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

አልተጣላንም ጉርብትና አለን እንጂ ዝምድና የለንም

እስቲ አሳየን ከዚህ ለይ ጥሩ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

አብዱልዋሂድ

ቆይ እስቲ አንዴ አልተነሳም እንዴ አላሳያችሁትም ለይቶ አሳይቷል 71ኛ ተከሳሽን

አቶ አብዱላሂ ስለ ተከሳሹ የምታውቀውን ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለሃል እስቲ ለፍ/ቤቱ አስረዳልን

ለሊት በጠዋት አካባቢ ላይ አባኦ እኛ ሰፈር መጣ እኛ ሰፈር ከመጡ በኋላ አንድ ላይ ሰብስበውን ቁርስ አምጡ አሉን ቁርስ ይዤ መጥቼ ሰጠኋቸሁ ቁርስ ካመጣሁ እሱ እና አንድ የአባዎ የሰውና እሱ አንድ ላይ ቁጭ ብለው መጣሁባቸው እስኪ ወደእኛ ና አለኝ

ማን ነው ያለህ

ኑሬ እስኪ ወደ እኛ ና አለኝ ወደእኛ ና ሲለኝ የአባዎ ሰውዬ ደግሞ ዝም ብለህ አፍህን ይዘህ ሂድ አለኝ እኔ ደግሞ ዝም አልልም ያየሁትን ነገር እናገራለሁ

ምንድን ነው ያየከው እንዳትናገር የከለከሉህ ምንድን ነው ያየከው

725

የመንግስት ወታደሮች መጥተው እነሱ እዛ አካባቢ አሉ ብለው ከጠየቁኝ እናገራለሁ

ምግቡን ማን ነው አምጣ ያለህ አለው

የአባዎ ወታደር ነው

አንተ ለማን ሰጠህ

ለአባዎ ወታደር ነው የሰጠሁት

ኑሬ ምን ነበር በዛን ጊዜ

እሱ እዛው ከማህበረሰቡ ጋር እዛው ሰፈር ውስጥ ነበር

ምንድን ነው የሚሰራው ከእነሱ ከአባዎቹ ጋር ከኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅት አባዎ ከተባሉት ጋር ምን ነበር የሚሰራው

የሚሰራውን ነገር አላውቅም በዛን ሰዓት ላይ እዛ አብረው ቁጭ ብለው ነበር

የተነገረህ ነገር ምን ነበር በወቅቱ

እሱ እንደዚህ የተናገረው ነገር እንደዚህ ለይቼ ባላውቅም አብሮ እየተቀመጠ ነው የመጣሁት

ምንድን ነው ያደረገው

ዝም ------- አለኝ እኔ ደግሞ ዝም አንልም እንናገራለን አልኩት

ስንት ነበሩ ያን ጊዜ ስንት ነበሩ ቁጥራቸው

አጠቃላይ 4 ሰው

አንተን አያውቁህም አባሎች እንዴት ምግብ አምጣ አሉህ

በጠዋት ስለመጡ አምጡ ምግብ አሉኝ እና እኔ ስማቸውን አላውቅም

ማን ነው ይዧቸው የመጣው እናንተ ጋ

እኔ በዚህ ለይቼ ማወቅ አልችልም

ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

726

ቁጭ ብለው ነበር ብለሃል ማን ቤት ጋ ነው ቁጭ ብለው የነበረው

በለሊት የመጡት እኔ ቤት ነው በለሊት የመጡት

ከአንተ ቤት ወደ አንተ ቤት ይዟቸው የመጣው ማን ነው እየመራ የመጣው ማን ነው

እኔ መምጣታቸውን ነው እንጂ የማውቀው ያመጣቸውን አላውቅም

እነሱን የአንተን ቤት ያውቁት ነበር ወይ

አያውቁትም

ኑሬስ

ኑሬም አያውቅም

እና ማን ነው

ኑሬ የእኔን ቤት ያውቀዋል

ኑሬ አብሯችሁ መጥቷል አልመጣም

በዛን ሰዓት አልመጣም

ታዲያ መቼ ነው የመጣው

ከዛ በፊት ሰፈር ይመጣ ነበር

ሰፈር ይመጣ ነበር ከማን ጋር

ብቻውንም ይመጣል

ከዛ በፊት ኑሬ ምን ነበር

በ82 ዓ/ም የአባዎ ወታደር ነበር ከዛ በኋላ ትጥቁን ፈቶ ህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሏል

የት አገር ነው የአንተ አገር የት ነው

አቢጉዲና ገደሀሪያ የሚባል ቀበሌ

727

ወደ አንተ ቤት ከአንተ ቤት አካባቢ ወይም እዛ አካባቢ ከኡነግ ወታደር ጋር ቁጭ ብሎ ምግብ አምጣ ያለህ ጊዜው መቼ ነው

ተቃውሞ አላችሁ እሺ

ምስክራቸው እያሉ ያሉት በወቅቱ ቁርስ መጥተው ሲጠይቁኝ የእኔ ደንበኛ ኑሬ ኡስማን አብሯቸው አልመጣም ነው ብሎ የመሰከሩላቸው አሁን ዐ/ህግ ግን እያሉ ያሉት የዛን ቀን አብሯቸው ኑሬ እያሉ ነው ያሉት ስለዚህ ፍ/ቤቱም እየተከታተለው ያለው ነገር ስለሆነ ያልተባለ ነገር ነው ዐ/ህጉ እያነሱ ያሉት አስተካክለው ይጠይቁ

እሺ በዚህ ላይ

አስተካክለዋለሁ

ታስተካክላላችሁ

አዎ

እሺ በሌላ መልክ አስተካክሉና ቀጥሉ

ኑሬ የት ነበር አንተ ምግብ ወስደህ ስትሰጥ ኑሬ የት ነበር

ከአባዎ ሰው ጋር አብረው ቁጭ ብለው ነው እኔ የመጣሁባቸው

ይሄ ጊዜ መቼ ነው

በጠዋት

አመት ምህረቱን ታስታውሰዋለህ ወይ

2፡00 ሰኣት አካባቢ

አመት ምህረቱን ታስታውሰዋለህ ወይ

ህዳር 5 ቀን

አመት ምህረቱስ

2001 ዓ/ም መሰለኝ አልገባኝም

ጨርሰናል

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ ይኖራል አማክሯቸው ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ምስክርነት ሲሰጡ አንድ አካባቢ ጎረቤት ነን ብለዋል

አዎ ከእኛ ሰፈር ወደ ላይ ነው ያሉት ያው አንድ አካባቢ ነን

ስለዚህ ታሀድሶ ወስዶ 82 ላይ የኦነግ ታጣቂ ነበር ከዛ በኋላስ ያለውን ህይወት ያውቃሉ ወይ እንዴት ነበር

ያው ማህበረሰቡን ተቀላቅሎ አብሮ መኖሩን ነው የማውቀው

በሰላማዊ ህይወት ሲኖር ነው የሚያውቁት

አዎ ሰዎቹ ህብረተሰቡ መሀላ ተቀላቅሎ ያው እንደህብረተሰቡ መኖሩን ነው የማውቀው

እሺ ስለዚህ የዛን ቀን ወደ እርሶ ቤት አባዎች የመጡ ቀን ኑሬም አብሮ መጥቷል ብለሃል ስለዚህ የዛን ቀን እሱን እንዳንተ አስገድደውት ነው የመጣው ወይስ እንዴት ነው

ኑሬ አልመጣም

አብሮ አልመጣም

አብሮ አልመጣም

ስለዚህ የት ነው ያየከው አንተ ቀን የመጣ ቀን የት ነው ያየከው

ቁርስ አምጣ ያሉኝ ጊዜ ቁርስ ሳመጣ ነው ያየሁት

እንዴት ብሎ ነው ያየከው

ማለት

አቀማመጡ ታስሮ ነው ወይንስ

...ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ፍ/ቤት ... ቁጥር 4

በሰላም እየተቀመጠ ነበር

ምግብ ይዞ ነበር የመጣው እንደ አንተ

እኔ ምግብ ማምጣቱን አላውቅም መቀመጡን ነው የማውቀው

ከአንተ በፊት ነው ከአንተ በኋላ

ከእኔ በፊት ነው

ከአንተ በፊት ከሆነ ቅድም እያልከን ያለከው መርቶ ወደ እኔ አላመጣም ትላለህ አሁን እንደገና ደግሞ ከእኔ በፊት ነው የመጣው ትላለህ ስለዚህ ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው እሱን ያየከው

እኔ ጋ ሲመጡ ብቻቸውን ነበር የመጡት ቁርሱን ግን ወደዛ ይዤላቸው ስሄድ እሱ ከእነሱ ጋር ነበር

ስለዚህ ኑሬ የአንተን ቤት የጠቆመብህ ኑሬ አለመሆኑን ታውቃለህ ነው እሱ ነው የጠቆመብህ

ጥያቄውን

ቤትህን የጠቆመብህ ኑሬ ነው አይደለም

ኒኪ አካባቢ ነው በእርግጥ ተኛቼ ነበር እኔ ማወቅ አልችልም

በወቅቱ እነሱ ሁሉም እዛ መደዳ ያለውን ሰው ነው ቁርስ አምጡ የሚሉት

ሁሉንም እዛው ሰፈር ያሉትን ነው አምጡ ያሉት

ጨርሻለሁ

ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ተከሳሹ የኦነግ ሰራዊት ነበር ከዛ በኋላ ትጥቅ ፈቶ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሏል

ከዛ በኋላ በሰው መሀል ተቀላቀለ እንጂ ከዛ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

730

ጥያቄው አላለቀም ተከሳሽ የኦነግ ሰራዊት ነበር ከዛ በኋላ ትጥቁን ፈቶ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሏል የተቀላቀለው መቼ ነው ወደ ህብረተሰቡ

ከ82 ዓ/ም በኋላ ነው

እርግጠኛ ነህ ወይ

እኔ እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም ግን በዛ ወቅት ላይ መሰለኝ ከዛ በኋላ ነው ያው ሂሱን ያወረደው

አንተ በ82 ስንት አመትህ ነበር

15 ዓመት ሳይሆነኝ አይቀርም

ስለዚህ ያኔ ነው ወይ በ82 ነው ወይ ትጥቅ ፈቶ

እነሱ ስላሉ ነው ከዛ በፊት ይሁን ከዛ በኋላ እርግጠኛ መሆን አልችልም

ይሄንን እርግጠኛ አይደለህም

አዎ እርግጠኛ መሆን አልችልም

ወደ ህብረተሰቡ ከተቀላቀለ በኋላ ወደ ኦነግ ተመልሶ ወይም ህብረተሰቡ ላይ ችግር ፈጥሮ ነበር ወይ

ሰፈራችን ወይ መንደራችን የተራራቀ ስለሆነ ይሄንን እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም ማወቅ አልችልም

ወይ ግልፅ እንዲሆንልህ ወደ ህብረተሰቡ ከተቀላቀለ በኋላ ፀረ-ሰላም ሆነ ተግባሮቹ ውስጥ ተሳትፏል ወይ

አቤት

ከተቀላቀለ በኋላ ወደ ህብረተሰቡ ፀረ-ሰላም በሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም የህብረተሰቡን ፀጥታ የሚነሱ ተግባራቶች ላይ ተሰማርቷል ወይ

ከዛ በፊት ነው እኔ ላውቅ አልችልም

731

የምታውቀው ነገር የለም ያየከው ወይም የሰማከው ነገር አለ

የዛን ቀን ነው አንድ ላይ የተገናኘነው ከዛ በፊት ያለውን ሳውቅ አልችልም

ከዛ በኋላ ያለውን ከተቀላቀለ በኋላ ያለውን

የተራራቀ ሰፈር ስለሆነ ሳውቅ አልችልም

የሰማከውስ ነገር አለ

የሰማሁትም ምንም የለኝም

እሺ እናመሰግናለን ጨርሰሃል ከኋላ ቁጭ በል ማን ይጠራ ዐ/ህግ ስንተኛ ነው ከድር በስንተኛ ላይ ነው ከድር ሼክ ኡመር ከሊፍ እሺ ቀጣይ ምስክር ቀርቧል መሀላ አስፈጽሙት

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ፡፡

ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ከሊፋ ሼክ ኡመር አሊ

አድራሻ- ገደሀሪያ የሚባል ቦታ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ኑሬ ኡስማን ጭሮ

ፀብ ዝምድና አለህ ከኑሬ ጋር

ዝምድና የለኝም አልተጣላንም

እስቲ አሳየን ተነሳና ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ከሊፍ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለሃል እስቲ ስለኑሬ ስለተከሰሰበት ነገር ካለ ለፍ/ቤቱ አስረዳ

432

መጀመሪያ ላይ ለሊት ጠዋት አካባቢ ሊነጋጋ አካባቢ አባዎ ወደ እኛ ሰፈር መጥተው ቁርስ ወሰዱ የእኛ ወታደሮች ደግሞ አባረሯቸው በፊት አባዎች 10 ነበሩ ከዛ በኋላ 10 ተጨመሩበት አለ

ማን ነው ይሄንን ያለው

ኑሬ ነው ያለው

ከማን ጋር ነበር ይሄንን ሲል

እኛን ነው ያለው

እናንተ ማለት ስንት ናችሁ

የሰፈር ሰዎች ብዙ ነን

መቼ ነበር የሆነው አመተ ምህረቱ

2001 ዓ/ም ነበር

ወሩስ የምታስታውስ ከሆነ

ህዳር 5 ቀን መሰለኝ

ቦታው የት ነው

ገደራ

አባዎቹ እነማን ነበሩ ስማቸውን ብትገልጽልን

እነ ለንጮ የሚሏቸው እኔ የማውቀው ሌንጮን ብቻ ነው

አይተከዋል ወይ በአይን ታውቀዋለህ ወይ

ለዛ ሰዓት በአይኔ አይቼዋለሁ አሁን ግን ጠፍቶብኛል

ከማን ጋር ነበር ሌንጮ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ከዛ በፊት እኛ ሰፈር አንድም ቀን መጥተው አያውቁም ያን ቀን ነው የመጡትና ከማን ጋር እንደሆነ አላውቅም

ማን አመጣቸው

እኛ ተኝተን ነበር ለሊት ንጊ ላይ አካባቢ ነው የቀሰቀሱን ተኝተን ነበር

ማን ቀሰቀሳችሁ

አባዎ ነው የቀሰቀሰን

ኑሬ የት ነበር ያን ጊዜ

ሰፈሩ ነው ያለው

ከማን ጋር

እዛው ሰፈር አካባቢ ነው ያለው

ይሄንን ቅድም ያልከው 10 ነበሩ አሁን 20 ሆነዋል ሲል እነ ሌንጮ አብረውት ነበሩ ወይ

እሱ ነው ያለው ይሄንን

ኑሬ አብሮ ነበር ወይ አብረው ነበሩ ወይ

ኑሬ ነው መጥቶ የነገረን ለእኛ

አደለም ስትጠይቀው እኮ አብረው ቆይተዋል ነው የሚለው እኮ ኦሮምኛው

ቆይ ቆይ እስቲ አብረው ነበሩ ወይ

አብረው ነበሩ ማለት

ጥያቄ ጥያቄ አብረው ነበሩ ወይ በልና ጠይቀው

ስለማልችልበት ነው

734

አሃ ነው እሺ እንደሱ ቀላል እኮ ነው እስቲ ሌላ ቋንቋ የሚችል ሰው የሚያግዘው ከማረሚያ ቤት የሚመጣው የት አለ ያ ልጅ ሌላ የሚችል አለ አሁን የተነሳችዋን ብቻ የሚጠይቅ እስቲ ቢጫ ያደረከው ናና አሁን የተባለውን ብቻ ጠይቀው የትኛው ነው አሁን ያስቸገረው ቃላት

አብረው ነበሩ ወይ የሚለውን

አብረው ነበሩ ወይ በልና ጠይቀው

ኦነግ 10 ነበር አሁን 20 ሆነዋል ብሎ ሲናገር ሴንጮ ከኑሬ ጋር አብሮ ነበር ወይ

ቁጭ በልና ጠይቀው ግድ የለም እዚህ ቁጭ በል ድገምለት

ኑሬ ድሮ ኦነጎች 10 ነበሩ አሁን 20 ሆነዋል ብሎ ሲናገር ሴንጮ አጠገቡ ነበር ወይ

አዎ አንድ ላይ ነው ያለው

አሁንስ

አሁን ተመልሷል

እናመሰግናለን

ቦታው የት ነበር አገሩ ምን ይባላል

ደገሀራ

የት ነው ክልሉ ዞኑ

ገደሀራ የሚባል ቀበሌ ነው

ቁርስ አምጡ ካሏችሁ በኋላ ቁርሱን ለማን ነው እሄዳችሁ ትሰጡ የነበረው

ጥያቄው ይደገም

ቁርስ አምጡ ብለዋችሁ አመጣችሁና ቁርስ እያመጣችሁ የምትሰጡት የሚቀበላችሁ ማን ነበር

ቁርሱን ማን ነው የሚቀበላችሁ

አባዎ ነው

736

ቁርሱን ስታመጡ ኑሬ የት ነበር የዛን ጊዜ

አብሮ ነው ያለው

አብሮ ነበር

አብሮ ቁጭ ብሎ ነበር

ጨርሰናል

ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ካለ አማክሩትና

የተከሳሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አንድ አካባቢ እንደምትኖሩ ነግረከናል እና

ተከሳሹን ማለትህ ነው

አዎ አንድ አካባቢ ነን

ምን ያህል ይራራቃል

ትንሽ ይርቃል

ስለዚህ ትንሽ የሚርቅ ከሆነ መጀመሪያ አባዎቹ የት ሰፈር ነው የደረሱት መጀመሪያ ሲገቡ

እኛ ቁርስ አምጡ ሲሉን ነው እንጂ ሲሰበሰቡ ያየነው መጀመሪያ የት ይኑሩ አላውቅም

አይ በየት በኩል መጥተው ነው የሰበሰቧችሁ በነ ኑሬ በኩል ነው በእናንተ በኩል ነው በየት በኩል ነው

በተለያየ አቅጣጫ ነው የገቡት እነሱ ብዙ ናቸው

ስለዚህ በተለያየ አቅጣጫ ሲመጡ

እነሱ አራት ናቸው

በተለያየ ቦታ ሲገቡ ኑሬም እንደ እናንተ ቁርስ አምጣ ተብሎ ታዞ ነው ወይ ያመጣው

736

እኔ እኛ ሰፈር ነው ይዘዙት አይዘዙት አላውቅም

እየመረጡ ነበር እንዴ ታዲያ የሚያዙት ሰውን

አምጡ ነው እንጂ ያሉት የመረጡት ሰው የለም

ስለዚህ አምጡ ሲባል ሁሉም የመጣው እንደ እናንተ እንደማንኛውም ገበሬ ነው እንጂ ከኦነጎቹ ጋር የሚያገናኘው ወይም እናንተን አሂችኋል ወይ እሱ

አባዎ ነው አምጡ ያለን እንጂ እሱ ሲያዘን አልሰማሁም እሱ እዛ አጠገባቸው ቁጭ ብሎ ነበር

አጠገባቸው ቁጭ ብሏል ብለሃል ሌሎቹ ሰዎችስ እዛ ያሉ ገበሬዎች እነሱ አጠገብ ቁጭ ብለው ነበር ወይ

እሱን ነው እንጂ ሌላ ሰው አላየሁም

ስለዚህ ብቻውን ታዲያ መቀመጡ አሁን ቅድም ከነገርከን ጋር ምንድን ነው የሚያገናኘው

ብቻውን ይቀመጣል አላልኩም ከእነሱ ጋር ይቀመጣል ነው ያልኩት

ከእነሱ ጋር ምን ገበሬ ነው እሱ የኦነግ አባል ነው እንዴ

እኔ አላውቅም በዛን ሰዓት አየሁት እንጂ እኔ አላውቅም

ታዲያ ምንድን ነው ልትመሰክር የመጣከው

ተቃውሞ አላችሁ ተቃውሞው ይመዝገብ

የማውቀውን ለመናገር ነው የመጣሁት

ተከላካይ ጠበቃው የሚጠይቀው መስቀለኛ ጥያቄ ነው ሊመሰክር የመጣው በዋና ጥያቄ መጠየቅ ያለብን እኛ ባለ ጉዳዮች ነን ስለዚህ መጠየቅ የሚችሉትን ጥያቄ ጠይቀው መልስ ነው እንጂ መጠየቅ ያለባቸው ምን ልትጠየቅ ነው ተብለው ልትመሰክር ብለው ባልተነሳ ጉዳይ ላይ መጠየቅ አይችሉም

እሺ ፍ/ቤቱም ሰምቷል ይሄ ክርክርም አይጋብዝም እንደዚህ ያለ ጥያቄ አግባብ አይደለም መስተካከል አለበት

737

እሺ አስተካክላለሁ ቅድም የሆነ ወታደሮች ሲጀምሩ 10 ነው ብሎ ተናግሯል ብለህ ለፍ/ቤቱ ተናግረሃል

አዎ ብሏል

ለምንድን ነው ያለው ለመቀስቀስ ነው ወይንስ በጨዋታ መሀል እዛ ከእናንተ ጋር ሲነጋገር ነው ወይንስ እናንተን ለመቀስቀስ ነው የተናገረው

እሱ መጥቶ ለእኛ ነገረን ለምን እንደነገረን ግን አላውቅም እኛ ከነገረን በኋላ ሄደን ለወታደሮች ተናገርን

ጨርሻለሁ

በቃችሁ ድጋሚ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

ድጋሚ ጥያቄ የለም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግናለን ጨርሰዋል መሄድ ይችላሉ ዛሬ የተሰሙት የዐ/ህግ ምስክሮች አብቅተዋል ቀሪ ምስክሮችን በተመለከተ በቀጣይ ታቀርባላችሁ ማረሚያ ቤት 8ኛ ተከሳሽ ፋጤ አልመጣችም አሁንም አዲስ አበባ ናት በሚቀጥለው እንድትቀርብና ማረጋገጫም እንዲቀርብ ከህክምና ማዕከልም የቆየችበትን ሁኔታ እና የቆየችበትን ጊዜ የሚገልጽ ማለት ነው ለአስተርጓሚ በዋስትና ጥያቄ ላይ ብይን ለመስጠት ፍ/ቤቱ ተነጋግረን እንገባለን ክርክር አብቅቷል በዚህ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቱ ለብይን ነው የቀጠረው ከስርዓት ውጪ መሄድ የለበትም ሙግት ስንመለስ ሌላ አቤቱታ ካለ እጅ ያወጣውንም እንሰማለን እሺ ትጠብቃላችሁ።

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ሌሎች ቀደም ሲል በተሰሩ ስራዎች በተመለከተ ምስክሮች በቀጣይ ቀጠሮ እንዲቀርቡ የቀጣይ ቀጠሮ ለግንቦት 12 መያዙን እንድትመዘግቡ በዚህ መዝገብ በትርጉም ለሰሩት እረዳት ሳጅን አለም የደንቡ ክፍያ እንዲከፈል በሌላ በኩል 22ኛ ተከሣሽን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮ በአብላጫ ድምፅ ትእዛዝ ሰጥቷል።

738

ት እ ዛ ዝ

ትእዛዙ 22ኛ ተከሣሽን በተመለከተ በአብላጫ የተሰጠው ድምፅ የዋስትና ጥያቄ ተከሣሽዋ ምስክርን ስለመሳደቧ ተጨማሪ ተነሺ ተጨማሪ ምስክር ባይቀርብም ፍ/ቤቱ የምስክሯን ቃል እና የዐ/ሕግን ጥያቄ በማዳመጥ እንዲሁም የተከሳካይ ጠበቃውን ተከሣሽዋ አቤቱታ በቀረበባት ጊዜ አንስቶ ለ28 ቀናት በእስር ላይ ስለነበረች ይሄ የታሰረችበት ጊዜ መቀጣጫ እና ትምህርት ይሆናታል በማለት ተከሣሽም ተከሣሽዋም ህፃን ልጅ የያዘች በመሆኑ በመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በነበረችበት ወይም ቀደም ሲል በተፈቀደ ዋስትና እንድትቆይ በአብላጫ ድምፅ ታዟል፡፡ ስለዚህ በዋስ ትቆያለች ማለት ነው በዚህ መዝገብ ላይ የልዩነት ሀሳብ ተመዝግቧል የልዩነት ሀሳቡ እንደሚከተለው --- ይመዘገባል ስነ ስርአቱ በሚያዘው በተራ ቁጥር 1 የተመዘገብኩት ዳኛ 22ኛ ተከሣሽ በዚህ ፍ/ቤት ቀርባ 22ኛ ተከሣሽ በዚህ ፍ/ቤት በተመለከተ ቀርቦ የተሰማ ምስክር ምስክርነቱ ከመሰጠቱ በፊት በምትኖርበት አካባቢ እንዳይመሰክር ተፅእኖ ማድረስ ማድረሷ በመረጋገጡ የዐ/ሕግ ምስክሮች እየቀረቡ የሚሰሙትም 22ኛ ተከሣሽ ከምትኖርበት አካባቢ በመሆኑ 22ኛ ተከሣሽ በፍ/ቤት ከተረጋገጠባት ተግባር አንፃር በቀጣይ ምስክርነት አሰማም ላይ ይሄው ተፅእኖ ይቀጥላል ተብሎ የሚገመት በመሆኑ በተጨማሪ በችሎት ምስክርነቱ መሰማት ሂደትም 22ኛ ተከሣሽ በችሎት የምታሳየው በሀሪ የዋስትና ግዴታውን በመፃፍ የፈፀመችውን ተግባር ጋር በአንድነት ሲታይም በቀጣይ ፍ/ቤቱ የፈቀደውን ዋስትና ታከብራለች ተብሎ የሚወሰድ ባለመሆኑ እና እየተሰማ ካለው ማስረጃ ክብደትም የዋስትና መነሳት ጥያቄው ከዚህ አንፃር በመመዘን በጥንቃቄ ሊታይ ይገባዋል የሚል እምነት በመኖሩ በአብላጫ ድምፅ ለ22ኛ ተከሣሽ በዋስ እንድትቆይ ከሰፈረው ምክንያት የተለየበትን ምክንያት በማመልከት 22ኛ ተከሣሽ በዋስትና ቀሪ ሆኖ ወይም ተነስቶ በማረሚያ ቤት ሆና ክርክሯን እንድትቀጥል ወይም ልትከታተል ይገባል በማለት የልዩነት ሀሳብ ተመዝግቧል፡፡ በዚሁም ትርጉም ንገራት ባክህን ላኪም በአብላጫ ድምፅ ዋስትና ተፈቅዶልሻል በማስጠንቀቂያ አንድ ዳኛ ግን ተለይቷል በሀሳብ የፈፀምሽው ከባድ ስለሆነ ማረሚያ ቤት ልትገቢ ይገባል የሚል ነው በአጭሩ ይሄ ነው፡፡ በሌሎች መዝገቦች የተያዙ አጀንዳዎችን በተመለከተ ዐ/ሕግ ለዛሬ የተያዙ ሌሎች ቀጠሮዎች

ማ/ተ

739

የመ/ቁ - 04486

ቀን - ግንቦት 19 ቀን 2002

ዳኞች - ብርሀነመስቀል ወጋሪ

- ደርጋ አይቼህ

- እልፍነሽ ወሎሬ

ከሣሽ - ዐ/ሕግ ሐረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሣሾች - እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ሰዎች ውስጥ 8ኛ ከ8ኛ 48ኛ 31ኛ ተከሣሾች በስተቀር ሌሎች ተከሣሾች መቅረባቸውን በችሎት አረጋግጠናል

መዝገቡ ከቀጠሮ በፊት ሊቀርብ የቻለው ዐ/ሕግ ምስክሮቹን ወደ ሰፈራ የሚሄዱ በመሆናቸው መዝገቡ ተሰብሮ የመዝገቡ የተያዘው ቀጠሮ ተሰብሮ ምስክሮች ይሰሙልን በማለት በማመልከታቸው ነው የቀረቡት መስክሮችም አሁን ባሉት ተከሣሾች ላይ የሚመሰክሩ ስለሆነ ይሰሙልን ብለዋል ምስክሮችም ቀርበው ማለትም የዐ/ሕግ ምስክሮች 22ኛ 25ኛ 82ኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች ቃለ መሀላ ፈፅመዋል ተከሣሾቹም ከዚህ ቀደም በጠበቃ እየታገዙ ይከራከሩ የነበረ በመሆኑ አሁን ጠበቃቸው ባለመገኘታቸው በችሎት የተገኙትን ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ የጥበቅና አገልግሎት ወይም የመማከር አገልግሎት እንዲሰጧቸው ፍቃደኛ በመሆናቸው ችሎቱ እሳቸውን መድቦላቸዋል ተከሣሾቹም ከእነሱ ጋር እየተመካሩ እንዲከራከሩ ብለናል በመሆኑም ዐ/ሕግ ምስክሮቹ ከመቅረባቸው በፊት እነዚህ ምስክሮች የሚመሰክሩትን ጭብጥ አንድ ጊዜ አስመዝግቡ

እሺ 22ኛ ምስክር ኡመር መሀመድ በ58ኛ ተከሣሽ ላይ ነው የሚያስረዳልን የሚያስረዳውም 1ኛ በግል እውቀቱ እሱ በቅጥታ የሚያውቀውን ከሰኔ 2000 ዓ/ም ጀምሮ በምእራብ ሀረርጌ ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ቡርቃናሚስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ 58ኛ ተከሣሽ በአባዎ በአባዎ ወይንም ደግሞ ኦነግ ተብሎ የሚጠራው ድርጅት ውስጥ ተደራጅቶ ሲንቀሳቀስ የነበረ መሆኑን የሚያውቅ ስለመሆኑ ያስረዳልናል በ2ኛ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ይሄ ተከሣሽ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ/ም ከቀኑ 9:00 ሰአት አካባቢ በዚሁ በምእራብ ሀረርጌ ቡርቃ ዲምቱ ፖሊስ ጣቢያ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ቡርቃአናሚስ ቀበሌ ገበሬ መሀበር ውስጥ በተከሣሽነት ተይዞ ስለ እዚህ ሲጠየቅ በኦነር ስር ተደራጅቶ ሲንቀሳቀስ የነበረ መሆኑን አምኖ ለመርማሪ ፖሊሶች ቃሉን ሲሰጥ የሰማ መሆኑንም ይሄንንም ያስረዳልናል ማለት ነው

እሺ. ሌላስ 25ኛ

ቀጥሎ 25ኛ ተከሣሽ ምስክራችን ሼክ ሀሰን ዳርጋ የሚባለው በ55ኛ ተከሣሽ ላይ ነው የሚያስረዳው እንደ ክስ አቀራረባችን ያስረዳል ሌላስ 82ኛው

82ኛ ምስክራችን ኡስማኤል ኡመር ሙመድ የተባለው በ40ኛ እና በ70ኛ ተከሣሾች ላይ እንደ ክስ አቀራረባችን ያስረዳል

እሺ. ማን ይምጣላችሁ

22ኛ ምስክር ኡመር መሀመድ ይምጣልን

እሺ. አንድ ጊዜ ከተከሣሾች ውስጥ አማርኛ ብዙዎቹ የማይሰሙ ስለሆነ ---- ዛሬ ከቀጠሯችሁ በፊት የቀረባችሁት የዐ/ሕግ ምስክር የሆኑት ሊመሰክሩ ስለሆነ ነው ስለተገኙ ነው ጠበቃም ቢሆን በችሎት የተገኙትን እሳቸውን ወርቅዬ አባይነህን ተመድበውላቹሀል እሳቸው ጋር እየተመካከራችሁ ክርክራችሁን ታካሂዳላችሁ በላቸው አሁን ኤው 55ኛ 58ኛ 40ኛ 70ኛ ተከሣሾች ትነሳላችሁ እዚህ አካባቢ ትሆናላችሁ ሌሎቻችሁ ቁጭ በሉ ተራ ቁጥራቸውን አያውቁም እሺ. ለምሳሌ 40ኛ አህመድ ሼክ አህመድ ተነስ 55ኛ ጀማል ሁሴን

በየቀኑ ቁጥራችሁ ሲነገራችሁ እኮ አይገባም ቁጥራችሁን ሁሌም እወቁ እንጂ እንዴ እየሰማችሁ ነው እየሰማችሁ አይደለም እ ቁጥራችሁን እወቁ ስንቴ ነው የምትጠሩት

ኡመር መሀመድ

ክቡር ፍ/ቤት ኡመር መሀመድ የሚለው በስህተት ነው አደም መሀመድ ---

እሺ. ዐ/ሕግ ኡመር መሀመድ ያልኩት 22ኛ ምስክር የስም ስህተት ስለሆነ ይስተካከልልን ብለዋል በማን ይስተካከልላችሁ አስመዝግቡ በሚይሉ

አደም መሀመድ ሐረዌ በሚለው ይስተካከልልን ቅድም ኡመር መሀመድ ያልነው አደም መሀመድ ሐረዌ በሚለው ይስተካከልልን 22ኛ ምስክር

----አለህ እሺ 70ኛ 22ኛ -----

አዎ እሱ 22ኛ ነው 82ኛውን እኛ የፈለግነው አሁን 22ኛውን አደም መሀመድ ይቅረብልን

አይሰማም

------በዚህ መሰረት ምስክር መስማቱን ሂደት እንቀጥላለን በዚሁ መሰረት 22ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ቀርቧል ስምህ ማን ነው በለው

22ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም -አደም መሀመድ ሐረዊ

እድሜ - 45

ስራ - አርሶ አደር

አድሻ - ቡርቃራሚስ የሚባል አረዳ ወረዳ ጭሮ ሐረር ውስጥ ጭሮ ማለት ነው የቤት ቁጥር የለውም

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክር ነው የመጣሁት

በማን ላይ ለመመስከር ነው የመጣከው

ኡመር ሙመድ መሀመድ

ኡመር መሀመድ መሀሙድ

አዎ

በ58ኛ ተከሣሽ ላይ ማለቱ ነው ታውቀዋለህ ወይ

አዎ አውቃለሁ

ፀብ ዝምድና አለህ ወይ ከእሱ ላይ በለው

7ሀ2

የለኝም

በዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እሺ አደም አሁን ልመስክር የመጣሁት በኡመር መሀመድ ላይ ነው ብለህል ምንድነው የምታውቀው በእሱ ላይ ምንድነው የምታስረዳው እስቲ

ፖሊሶች ቃለ መጠይቅ ሲያደርጉለት ነው በእዛ በአካባቢው ነበርኩኝ በቦታው

አካብቢውንስ ብዙ ነገር አልጠራልህም አካባቢዎች አልገረህም

ቡርቃ ዲምቱ አረዳ ቡርቃናሚስ በሚባል አረዳ

----- እሱ የሚናገረውን በአጠቃላይ አሁን እሱ ሐረርጌ ምናምን ምናምን ብሎ ብዙ ነገር ተናግሯል ያንን

አዎ

ያንን አልጠራልህንም ------

ትንሽ ኮንፐሌክስ ሆነብኝ

እ

ኮንፐሌክስ ሆነብኝ እሱ የሚናገረው

እኮ ካልገባህ እኮ አልገባኝም

ቡርቃ ዲምቱ አረዳው ደግሞ ቡርቃናሚስ የሚባል ቦታ

አረዳ የሚልህንም ወረዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር እያልክ ተርጉምልን ወደ አማርኛው እንድንሰማ እንግዲህ ፍ/ቤቱ የሚጠብቀው አንተ የሰማከውን እንድትለን ነው

እንዴ ተርጉመው አንተ እራስህ

ወረዳ ማለቱ ነው አና ማለት

እኮ ታዲያ እኛ አናውቅማ ተርጉምልን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

7/43

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ

ቀበሌ ገበሬ ማህበር በለው

ቀበሌ አረዳ አረዳ ቡርቃናሚስ

ቡርቃናሚስ ቀበሌ አለ አይደለ

እሺ በእዚህ ቦታ ላይ የት አካባቢ ነው ቅድም ሀረርጌ ነው ሲል ነበረ የት አካባቢ ነው ሀረርጌ ያልከው

ጭሮ የሚባል

እሺ እዛ አካባቢ አሁን የነገርከን ቦታ ላይ ምንድነው የተፈጠረው ተከሣሹ ምንድነው ያደረገው

በቡርቃናሚስ ወረዳ ውስጥ ሌሲሳ እና ብራሳ ነው የ---ሂደው

ምንድነው አሁን ያልካቸው ነገሮች ምንድናቸው

አባዎ ነው

አባዎ ማለት ምን ማለት ነው እስቲ

ኦሮሞ ሊብሬሽን ፍሮንት የሚባለው ነው

እኮ እሱን በለዋ በአማርኛ

ግራ ተጋብቶ ነው

አሁን ከግራ ቀኙ ሰምተሀል ምን እንደተባለ አይደለ ተረጋጋ አሁን ቅድም ኦሮሞ ሊብሬሽን ፍሮንት ብለከናል አይደል እና ምናልባት እንግሊዘኛ ለሚያውቅ ሰው ሊገባው ይችላል ሌላ ለሚያውቅ ሰው ደግሞ ግልፅ አይደለም ስለዚህ አንተ በአማርኛ እንድትነግረን ነው ውጪ ያልነውም ተግባርህ ይሄ ይሄ ነው ስለዚህ ተረጋግተህ አንድ ጊዜ የተናገሩትን በአማርኛ መናገር አታቁረጥርጠው እሺ

እሺ

742

ምንድነው አባዎ

--እያልክ ነው የምትነግረን ማለት ነው

አባዎ ማለት ኦነግ ማለት ነው

እሺ እነዚህ ቅድም ያልከን

ይቅርታ ያው ትለምዳለህ አንተ ጉበዝ ሰራተኛ እንደሆንህ እናውቃለን በትርጉሙ ---

እሺ እነዚህ አሁን ቅድም ያልከን

እሺ ዐ/ሕግ በዋና ጥያቄ ላይ ነው አላለቀም ቀጥሉ

እሺ አደም ይሄ ቤረሳ ያልከው ቅድም የኦነግ ምንድን ናቸው

የሰው ንብረትን የሚዘርፍ ኦሮም ሽፍታ ነው

እ

ሽፍታ ነው

ከእነሱ ጋር ምን አደረገ ተከሣሹ ምንድነው ከእነሱ ጋር የሚያደርገው

ከእነሱ ጋር ተደራጅቶ አብሮ ይንቀሳቀስ ነበረ ነው

ማይኩን ከፍ አድርጉልን እያለሱ ነው ተከሣሾች ድምፃችሁን ከፍ አድርጉ

ከእነሱ ጋር ተደራጅቶ ይንቀሳቀስ ነበረ

ይንቀሳቀስ ነበረ ማለት ምን ያደረግ ነበረ ማለት ነው

ቡርቃናሚስ ቀበሌ ውስጥ ከእሱ ጋር 7 ሰዎችን ወደ እዛ አስገብቶ አብሮ ይንቀሳቀስ ነበረ ነው

ምንድን ነበረ የሚያደርጉት 7 ሆነው የሚንቀሳቀሱት ምን ምንድን ነበረ የሚንቀሳቀሱት ከአባዎስ የሚያገናኛቸው ነገር ------- ምንድነው

እኔ በምስክርነት የማወጣው ለልማት ተብሎ 5 5 ብር ብማህበር 5 5 ብር ስናዋጣ ነው አዋጡ ስንባል ነው የማውቀው ነው በዚህ ላይ ነው ምስክርነት የምወጣው

745

እ

በዚህ ላይ ነው ምስክርነት ቃሌን የምሰጠው

እኮ 5 5 ብር አዋጡ የሚለው ለማን ነው አዋጡ የተባለው

ለኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር

መቼ ነው ይሄ ጊዜ

2000 ዓ/ም ላይ ነው

እ እ

አንድ አመት ከ4 ወር ይሆነዋል

ቆይ አንተ እንዴት አወቅህ ይሄንን ---

ሰኔ ወር ላይ ነው አጠገቤ ቁጭ ብሎ በአፉ የተናገረው ነው

የት ነው የት ሆኖ ነው የተናገረው

ቡርቃዲምቱ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ ነው ተናገረው አጠገቤ

መቼ ነው እንዲህ ብሎ የተናገረው ምን ያህል ጊዜ የሆነዋል

አንድ አመት ከግማሽ ይሆነዋል ከመንፈቅ

ስንት ሰአት ላይ ነው

ከ8 ሰአት ጀምሮ እስከ 9 ሰአት ባለው ሰአት ነው

በቃሉ ነው

አዎ በአፍ ቁጭ ብሎ ነው የተናገረው ለፖሊስ

ቀን ወይስ ማታ

ቀን ነው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እሺ ይሄንን በፖሊስ ጣቢያ ሲናገር ሰምቻለሁ ብለሀል ይሄንን የተናገረው እስቲ በምን ሁኔታ ላይ ነው ማን ሲጠይቀው ነው

አደም አሶ የሚባል ፖሊስ ነው

እሺ ይሄንን እሱ ሲናገር ሰምቻለሁ ብለሀል አንተ እሱ ከመናገሩ በፊት ተከሣሹ ምን እንደሆነ ነው የምታውቀው አንተ ------- እሱ የዛን ቀን ----- ከተናገረው ውጪ

እሺ ምንድነው ተቃውሞ

እዚህ ላይ የተከበረው ፍ/ቤት ዐ/ሕጉ ተከሣሹ ምን እንደሆነ ነው የምታውቀው የሚለውን ተከሣሹን እንዲህ እንደሆነ ነው የማውቀው የሚል መልስ የሚያሰጥ እና ተከሣሽን የሚጐዳ ስለሆነ በዚህ አይነት አንዳይጠየቅ እንቃወማለን

እስቲ መልስ

ይሄ ምናልባት በዋና ጥያቄ ላይ መሪ ጥያቄ ነው የሚከለከለው መምሪት ማለት ደግሞ እሱን እንደዚህ ነው ወይ ታውቃለህ ነው አይደለም እያለ የሚመልስ እኔ ግን የጠየኩት በጥቅሉ ምንድነው የሚል ማነው ከፈለገ የመሰለውን እንዲናገር ብቻ ነው

እሺ ያው አሁን የተነሳው የጠበቃው ተቃውሞ ከዋና ጥያቄ አቀራረብ ሁኔታ ጋራ የሚጋጭ አይደለም በመሆኑም ተቃውሞው ተገቢ አይደለም ያው እያብራሩ ነው እንጂ እየመሩ አይደለም ቀጥሉ

እሺ ጥያቄውን ድገምለት ከእዛ በፊት ፖሊስ ጣቢያ እንደዛ ሲናገር ሰምቻለሁ ብለሀል ከእዛ በፊት ምን መሆኑን ነው የምታወቁው አንተ ተከሣሹን

ከእዛ በፊትም መንግስት ይዞት እያለ ትቶ እንደገና ተመልሶ ተመልሶ እዛ ወደ እዛቡድን ውስጥ ገባ ከእዛም እንደገና ተመልሶ

ወደ ምን ምን ውስጥ ነው የገባው

በዚሁ ጉዳይ ላይ እዛው ውስጥ ነው የገባው ነው

ይሄ ጉዳይ ያልከው ምኑን ነው

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

7417

በዚህ አሁን አባዎ ብሎ በኦሮሞ ነፃዊነት ግንባር ተጠርጥሮ ተይዞ ነበረ ከእዛ በፊትም ከእዛ ተመልሶ እንደገና ከተለቀቀ በኂላ ወደ እዛ ተመልሶ ገባ ነው

እሺ አንተ

ያንን መሆኑን አውቃለሁ

በዚህ በፖሊስ ጣቢያ ቅድም በነገርከን ፖሊስ ጣቢያ ይሄ በቡርቃዲምቱ ፖሊስ ጣቢያ ባልከው የዛሬ አመት ከ6 ወር ወይም አመት ከግማሽ ይሆናል ብለህል ተመልሶ ወደ እዛው ገብቷል ያልከው ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል ከእዛ በፊት

ምን እንደሆነ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የታሰረው ታስሮ ነበረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ግን አላውቅም ወደ ጭሮ ዞን ሄዶ ነበረ

ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል በግምት የታሰረበትን ሳይሆን አንተ አውቃለሁ ያልከውን ነገር

አይ ታስሮ ነበረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አላውቅም ወደ ጭሮ ሄዶ ነበረ ነው እሱ ያለው

ቀጥል ወደ ሌላ እኛ --

መታሰሩን እንጂ የማውቀው ሌላ

በቃ ጨርሻለሁ

እሺ ዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ አበቃ የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ምንዳ ቁጭ በል እና አንተ ተነስ እና የሚለውን ሰምተህ ለእሳቸው ትነግራለህ መስቀለኛ ጥያቄ ይጠይቁ እርሶ የያዙት ካለ ይጠይቁ እስከ እዛ

እሺ እኔ የያዝኩት አለ አቶ አደም መሀመድ አሁን ምስክርነት የሰጡበትን ተከሣሽ ያውቁታል

አዎ አውቀዋለሁ

ከእዚህ ውስጥ አለ ሊያሳዩኝ ይችላሉ

ተነስ ተነስ ተነስ

አመልክቷል ተከሣሹን

እሱ ነው እሺ

አዎ እሱ ነው

ቀጥሉ

ተከሣሹ 7 ከሚሆኑ ዘራፊዎች ጋር ነበረ አብሮ ብለዋል ለፍ/ቤቱ እነዚህ ዘራፊ የሚሏቸው ሰዎች እነማን ናቸው

መሀመድ ሳኒ የሚባል 7 ናቸው ከእሱ ጋር ተደራጅተው ያሉት ብያለሁ አንዱ መሀመድ ሳኒ ብያለሁ ሻሚል አብዱለጢፍ

የት ነው የሚኖሩት እነዚህ ሰዎች

ቡርቃናሚስ ቀበሌ ነው

አሁን አሉ እዛ ቦታ ላይ ወይንስ የሉም

እዛው ነው ያሉት

በሰላም እየኖሩ ነው

አዎ በሰላም እየኖሩ ነው ያሉት

እሺ ተከሣሹ ፖሊስ ጣቢያ ቃል በሚሰጥበት ጊዜ ነበርኩኝ ብለዋል ተከሣሹ ፖሊስ ጣቢያ ቃል ሊሰጥ የሄደው በፈቃደኛነት ነው ወይንስ ምን ሆኖ ነው

ሳይገደድ ነው እንደዚሁ ቁጭ እኔ እንዳልኩት ቁጭ ብሎ ነው ቃሉን የሰጠው ሳይገደድ

ታስሮ ነበረ ወይ

የለውም እስር እስር የለውም ንፁህ ነው

ፖሊሱ ታዲያ ለምንድነው ካልተከሰሰ ወይ ካልታሰረ ቃሉን የተቀበለው

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

749

በህግ ታስሮ ሊሆን ይችላል አላውቅም እንጂ እጁ ላይ ግን እስር አላየሁበትም ህግ ግን አስሮት ሊሆን ይችላል

በዛን ጊዜ ይሄንን ቃሉን ከሰጠ በኋላ ተለቆ ወደ እቤቱ ሄደ ወይስ እዛው ቀረ

እኛ እዛው እያለን ቃሉን ከሰጠ በኋላ ከ---- ጋር ወደ እዛ ሄደ እኛ ደግሞ ወደ እዚህ ሄድን

ወደ እዛ ሄደ ሲሉ -- ተለቆ ወደ እቤቱ መሄዱ ነው ወይንስ ወደ እስር ቤት መግባቱ ነው

ወደ እዛ ሲሄድ ነው የማውቀው እንጂ ወደ እስር እቤት ይግባ ወደ ምን አላውቅም

ፖሊሱ ተከሣሽን ቃሉን በተቀበለው ጊዜ ምን ነገረው

ማነው ስምህ አንተ ኡመር ነው ብሎ አለ ስም ማነው ስመህን መጠሪያ ስምህ ሌላ ደግሞ ቡርቃዶዮ እባላለሁ ብሎ ነው ያለው ነው

ከዚህ ውጪ የነገረው ነገር አለ ወይ የሚሰጠው ቃል በሚመለከት ፖሊሱ ለተከሣሹ ያለው ነገር ነበረ ወይ

ቤሊሳ እና ቢረሳ አደራጅተውን ነው ያለነው እኛ ብሎ እዛ ሲናገር ነው የሰማሁት ሌላ ነገር አልሰማሁም

ፖሊሱ ሌላ ያለው ነገር አለ ወይ

ሌሊሳ እና ቢረሳ የሚባሉት ሰዎች ናቸው ያደራጁን

ኦነጎች ናቸው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

ኦነጎች ናቸው የኦሮሞ ነፃነት ግንባታ

አዎ ---

አሁን እኔ እሱ አይደለመ ጥያቄዬ ፖሊሱ ለተከሳሹ ቃሉን ከመቀበሉ በፊት ምንድነው ያለው ስለሚሰጠው ቃል

ወይ ግልፅ አድርጉለት ስለመብቱ --

ፌዴራላዊ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ቁጥር 4

750

አዎ ስለ መብቱ ተከሣሹ ተከሣሹን ስለመብቱ ፖሊሱ ተከሣሹን ቃል ሲቀበለው ስምህ ማን ነው ብሎ ከመጠየቅ ውጪ ይሄ የሚሰጠው ቃል ማስረጃ እንደሚሆንበት መርማሪው ለተከሣሹ ነግሮት ነበረ ወይ

ኤው ግልፅ አድርግለት ይሄ አሁን የምትሰጠው -- አለመስጠት ትችላለህ ከፈለክ የምትሰጠው ነገር ግን የህግ ማስረጃ ይሆንብሀል ብሎ ነግሮታል ወይ

ይሄ ማስረጃ ይሆናል የሚለውን ነገር አልሰማሁም ስሙን ጠይቆ አስፈርሞታል እኛንም ምስክሮች ናችሁ ብሎ አስፈርሞናል

አልጨረስኩም ምንድን ነው የሚለው አሁን ይሄ እሱ የመሰከረውን ቀደም ሲል በዚህ አሁን እሱ በመሰከረው ጉዳይ ላይ ተይዤ ታስሬ ትምህርት ተሰጥቶኝ ተለቅቄአለሁ ከዛ ወዲህም ይሄንን ወንጀል አልፈጸምኩም እና ይሄንን አያውቅም የመጀመሪያው ነው ነው የሚለው

እኮ ጠይቁ

እሺ አቶ አደም ተከሳሹ ይሄንን ቅድም ያሉትን ከ7 ሰዎች ጋር አብሮ ይሄድ ነበር ተይዞም ነበር ብለዋል አሁን የሚሉትን ነገር አደረገ ያሉት በመጀመሪያ ጊዜ ከመያዙ በፊት ያደረገውን ነው ወይስ ከዛ ተይዞ ከተፈታ በኋላ ያደረገውን ነው

እኔ አላውቅም እሱ ነው የተናገረው

እኮ መቼ ከሰኔ 2000 ዓ/ም በፊት ነው ወይስ ከዛ ወደዚህ ነው ስንት አመት ይሆነዋል

አንድ አመት ከግምሽ ይሆናል

ከእነዛ 7 ሰዎች ጋር አብሮ ነበር ተከሳሹ ብለው ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል አብሮ ከመሆን ውጪ ምን የሰራው ነገር ነበር

እሱ ነው ያለው እኮ 5 5 ብር እንለቅማለን ብሎ ነው በዛ ነው የተደራጀነው ብሎ ነው ያለው እሱ ነው እኮ ያለው

ከዚህ እሱ ከሚናገር በስተቀር ከዛ በኦነግ ውስጥ ስለመደራጀቱ 5 5 ብር እንለቅማለን ስለማለቱ በሌላ ሰው የተነገረ ነገር ነበር ወይስ እርሶ ባሉበት ሰው ሰብስቦ ይሄንን ሲናገር ሰምተዋል

በ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

751

እሱ ሲናገር ነው እንጂ የሰማሁት እኔ ከሌላ አልሰማሁም

5 5 ብር ለቅመናል ብሏል እርሶ ከፍለው ነበር 5 ብር

ቆይ አንደኛ እሳቸው በራሳቸው መስካሪ ናቸው እንጂ ራሳቸውን ለመወንጀል ምስክርነት ቃል አይሰጡም

አይሰጡም እሺ

ስለዚህ ሌላ 5 ብር ነው ጥያቄ የተናገሩት ነገር ካለ በእሱ ዙሪያ ቀጥሉ

5 5 ብር ተሰብስቧል ነው የሚሉት

ማን ነው እሳቸው አውጥቻለሁ አሉ

አዎ 5 5 ብር ተሰብስቧል ብለዋል ይሄንን 5 ብር የተሰበሰበውን እርሶ እንደ ሌላው አውጥተዋል ወይ ነው እኮ ያልኩት እና እሳቸው ካሉት በመነሳት ነው የተከበረው ፍ/ቤት

እሺ ቀጥሉ

እኔ አልከፈልኩም አላሉም ቅድምም አልከፈልኩም እሱ ሲል ነው እንጂ የሰማሁት

ሲዋጣም ገንዘቡ አላዩማ

አላየሁም

እሺ ቀጥሉ

ፖሊስ ጣቢያ ተከሳሹ ቃል በሚሰጥበት ጊዜ ከእርሶ በስተቀር ሌላ ሰው ነበር

ቅድም ጠየቁ እኮ አይድገሙት ጊዜም የለንም

አልደገምኩም ግን በፊት ያልኩት ተከሳሹ ስለ ተከሳሹ አሁን ግን ከእርሶ ሌላ ሰው ነበር ወይ ነው ያልኩት

እኔ እና አብዱማሊክ አብረን ነበርን ነው ቁጭ ብለን ነበር

እሺ ቀጥሉ ቁጭ ብለን ነበር

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

752

በቃኝ ይበቃኛል

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አበቃ

የዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ

አደም ቅድም ፖሊሱ ኡመርን ስምህ ማን ነው ብሎ ሲጠይቀው ኡመር መሀመድ ነኝ አለ ከዛ ሌላ ስም አለህ ወይ ብሎ ሲጠይቀው ቡርቃ ዶዮ ነኝ አለ ብለሃል ምንድን ነው ይሄ ቡርቃ ዶዮ የምን ስም ነው

የስም ነው የመጠሪያ ስም ነው ቡርቃ ዶዮ

የማን ስም

አንዴ ቆይ

እኛ ኡመር መሀመድን ነው የምናውቀው ሰው ሌላ የማያውቀው ሰው ስሙ ደግሞ ቡርቃ ዶዮ ነው እሱም በኦነግ ውስጥ እያለ የትግል ስሙ ነው ቡርቃ ዶዮ

ማዴ አባዎ እያለ ነው እኮ በአባዎ የተደራጁበት ስም ነው እሺ በቃ ጨርሰናል ድጋሚ ጥያቄ ጨርሻለሁ

ቅድም ተናገሩ አባዎ እንዲህ ነው ብሏል አደለም

አዎ አይ በቃ ጨርሰናል

ድጋሚ ጥያቄ አበቃ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

አሁን የተናገርከው መጨረሻ ላይ የተረጎምከው ግልጽ ስላልደለ ንገረን

ምን አሁን የመጨረሻውን

አዎ

ኡመር መሀመድ ነው ስሙ

ለዐ/ህግ ሲጠይቁ መጨረሻ ላይ እሱ እየገለጸ ያለውን ትርጉሙን በተመለከተ ቃል በቃል እሱ ያለውን

ኡመር መሀመድ ነው ስሜ ቡርቃ ዶዮ ደግሞ የተደራጀንበት ስም ነው

ማን ነው ያደራጃችሁ

ኢሊሳና ቢረታ ነው ያደራጁን

ቢሊሳና ቢረሳ የአባታቸው ስም ማን ነው

አላውቃቸውም የአባታቸውን ስም

ቢሊሳ እና ቢረሳ የአባታቸው ስም ማን ነው

እሱም አልተናገረም እኛም አናውቃቸውም

ማጣሪያ ጥያቄ ጨርሰናል ጨርሰሃል

25ኛ የዐ/ህግ ምስክር ሼክ ሀሰን ዳርጋ

ሼክ ሀሰንን ጥሯቸው

ሼክ ሀሰን ዳርጋ ቦሩ

25ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ሼክ ሀሰን ዳርጋ ቦሩ

እድሜ - 55

ሥራ - ገበሬ

አድራሻ- ምእራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ነኝ ቀበሌ ዲምቱ በርሄ ቀበሌ ገ/ማህበር

ዛሬ ለምን መጡ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

754

ማን ላይ ለመመስከር

ጀማል ሁሴን ላይ

ፀብ ዝምድና አሎት ወይ ከጀማል ሁሴን ጋር

ትንሽ እንቀራረባለን

ምንድን ነው ቅርርባችሁ

አማች እንሆናለን በአማች እንገናኛለን በጋብቻ

የጋብቻ ዝምድና

አዎ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ሼክ ሀሰን ጀማል ላይ ነው የምመሰክረው ብለዋል ምንድን ነው የሚያውቁት ጀማል ላይ ምንድን ነው የሚያስረዱት

አባዎ ማለት ኦነግ ሰራዊት ውስጥ ተቀላቅሎ ገብቶ ተኩስ መክፈቱን ነው የማውቀው

መቼ ነው

2001 ዓ/ም

ምን ወር ላይ ነው

ጥቅምት ይመስለኛል

ቀኑስ ስንት ላይ ነበር

20 ይሁን አላውቀውም በውል ብቻ ጥቅምት መሆኑን አስታውሳለሁ

ጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም ብሎናል የት ነው ቦታው

ዲምቱ በሬዳ የሚባል ቀበሌ ውስጥ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ወረዳውስ ዞኑስ የት አካባቢ ነው

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ውስጥ

እዚህ ቦታ ላይ ምንድን ነው ያደረገው እስቲ ተከሳሹ ምን ነበር ምን አደረገ ዘርዘር አድርገህ

እሮጠ እዛ አባዎ ኦነግ ውስጥ ተቀላቅሎ ገብቶ ከእነሱ ጋር ሆኖ ተኩስ ከፈተ

ማን ላይ ነው ተኩስ የከፈተው

እሱ ኦነግ ውስጥ ገብቶ ለእሱ ሲል የኦነግ ሰራዊት እኛ ሃይል ላይ ተኩስ ከፈተ ነው ያልኩትኝ

እናንተ የምን ሃይል ነበራችሁ ምን ነበራችሁ እናንተ

እኔ ሽማግሌ ነኝ

ጥያቄ ግልጽ አድርገህ ጠይቅላቸው እናንተ ማን ናችሁ ተኩስ የተከፈተባችሁ

እሳቸው የተናገሩት

አሁን እሱ የተናገረው ፖሊስ ይዞት ነበር እሱን ፖሊስ ሲይዘው ሮጦ ከፖሊሱ አምልጦ የኦነግ ሰራዊት ውስጥ ገባ በእሱ አማካኝነት የኦነግ ሰራዊቶች የእነሱ የወረዳቸው ፖሊስ ላይ ተኩስ ከፈተ

እሺ ተኩስ ከፈተብን ብለሃል ስለዚህ እሱ ምንድን ነው ጀማል ማለት ምንድን ነው

የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ፓርቲ ነው

አንተ አይተሃል እንዴ ሲተኩስ ተኮሰ ብሎ ለፖሊሶቹ ያልከውን አይተሃል ወይ

እሱ ሲተኩስ አላየሁም እሱ ሮጦ እዛ እነሱ ጋር ሲቀላቀል እነሱ በእኛ ሰራዊት ላይ ፖሊስ ላይ ሲተኩሱ ነው የማውቀው እንጂ እሱ ሲተኩስ አላየሁም

እነሱ ሲተኩሱ አይቻለሁ እያልክ ነው እሱ የት ነበር የዛን ጊዜ የአባዎ የኦነግ ሰራዊቶች ሲተኩሱ ወደ እናንተ ወደ ፖሊሶች እሱ የት ነበር

እዛ ገብቶ ነበር እነሱ ጋር ተቀላቅሎ ነበር

የፌ.ጠ.ፍ/ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀዳሚ

756

እነሱ ጋ ተቀላቅሎ የምትለው ከማን ጋር ነው

ከኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ነው የገባው

ሌላስ

በቃ ጨርሻለሁ

እሺ ዋና ጥያቄ አበቃ

የተከሳሽ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ሼክ ሀሰን ተከሳሹ ፖሊስ ያዘው ብለዋል ቅድም ለምን ነበር ፖሊስ የያዘው

አንተ ከኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ተደራጅተሃል በማለት ነው የያዘው

ታስሮ ነበር ወይ

እነሱ ይዘውት እየሄዱ ነው ከእጃቸው አምልጦ የሄደው

ከእጃቸው አምልጦ ሄዷል ጠይቁ

እነዚህ ኦነግ ቅድም ያሏቸው ሰዎች ጋር ተከሳሹ ከፖሊስ አምልጦ የሄደው ለምንድን ነው

ምን አሉ አንዴ ይድገሙልኝ

ተከሳሹ ፖሊሶች ይዘውት ሲሄዱ ሸሽቶ የኦነግ አባሎች ጋር ተቀላቀለ ብለዋል ለምንድን ነው የተቀላቀለው እንዲያድኑት ነው ወይስ ምን እንዲሆን ነው

ከእነሱ ስር ለማምለጥ ብሎ ነው ወደዛ የሄደው

ወደዛ የሄደው

አዎ

ተኩስ ተከፈተ ብለዋል አብረውት ከነበሩት ተከሳሽ ከተቀላቀላቸው ሰዎች መካከል እርሶ የሚያውቋቸው ሰዎች ነበሩ

አላውቅም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

757

ተከሳሹ ከፖሊሶቹ ሸሽቶ እነዛ ሰዎች ጋር ከመቀላቀል በስተቀር በግሉ ምን ያደረገው ነገር አለ

እኔ ምንም ያደረገውን ነገር አላውቅም ወደዛ ሮጦ መግባቱን ነው የማውቀው

ከእነሱ ጋር ተቀላቅሏል ብለዋል የዛ ድርጅት አባል መሆን አለመሆኑንስ የሚያውቁት ነገር አለ

አዎ ስለሆነ አይደለም ወይ ወደዛ ሄዶ የገባው

እርሶ የሚያውቁበት ነገር አለ ወይ

እኔ ይሄንኑ ነው እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር የለም

አብሮ ስለተቀላቀለ ነው ወይ የእነሱ አባል ነው ያሉት

አለ እኮ ይሄንን ነው የማውቀው ብሏል ሌላ አሎት

ተከሳሹ ከፖሊስ አምልጦ እነዛ ሰዎች ጋር ሲቀላቀል መሳሪያ ይዞ ነበር

የለውም

ምንም የያዘው ነገር የለም

ከመንደር ነው ይዘውት የሄዱት ምንም ነገር የለውም

እሺ ጠይቁ

ተከሳሽን ለማዳን የኦነግ ወታደሮች በመንግስት ወታደር ላይ ተኩስ ከፈቱ ብለዋል ቅድም ተኩሱ የተከፈተው የመንግስት ወታደሮችና የኦነግ ወታደሮች ተገናኝተው ተኩስ ራሳቸው በራሳቸው ከሚከፈቱ በስተቀር ተከሳሽ እዛ ውስጥ አልነበረም በዛን ወቅት

ነበር ወይ አልበረም

አዎ

በጥያቄ መልክ ያድርጉ

ተከሳሹ ተኩሱ ውስጥ አልነበረም

ነበረ ወይስ አልነበረም ብለው ይጠይቁ

758

ነበረ ወይስ አልነበረም

እሱ ሮጦ እዛ ገባ ነው የምለው ነው

ቀጥሉ

እሱ ሮጦ እዛ መግባቱ ነው የማውቀው

በቃን

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አበቃ የዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ

የለንም

ድጋሚ ጥያቄ የለም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ጥያቄ አበቃ ጨርሰዋል እናመሰግናለን

82ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ኡስማኤል ኡመር

እድሜ - 33

ሥራ -

አድራሻ- ድሮ አሰበ ተፈሪ 01 ቀበሌ ነበርኩ አሁን ለሰፈራው ምእራብ ኦሮሚያ ነው የገባሁት አሁን ምእራብ ኦሮሚያ ኢሊባቡር ዞን ነው የመጣሁት

አድራሻ የት ነው

መጀመሪያ ምስክር የሰጠሁበት በ97

ግድ የለም አሁን የት ነው የምትኖረው

አሁን አባቡራ እና ጨዋቃ ቀበሌ አጄ ኦሮሚያ

በአማርኛ አድርግልን ስለምትችል ነው የምጠይቅህ

ወረዳው ጨዋቀ

759

እሺ ቀበሌው

ቡርጂ ኦሮሚያ ይባላል

ቀበሌው

አዎ ቀበሌው

ተከሳሾችን ታውቃቸዋለህ

አውቃለሁ

ማን እና ማንን ነው የምታውቀው

አህመድ ሼክ ዩሱፍ የሚባልና አህመድ አብዶ

ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ

አይ የለኝም

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እሺ ኡስማኤል አሁን የጠራካቸውን ሁለቱን ሰዎች አውቃቸዋለሁ ብለሃል እስቲ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቃቸው ለፍ/ቤቱ አስረዳልን

ለፍ/ቤቱ እነሱ እንግዲህ መጀመሪያ ተጠርጣሪ ብሎ ህዝቡ ሲያወራ ነው የምንሰማው አደለም ከዛ በኋላ ቁጥጥር ስር ሲውሉ እኛ አካባቢ እንደዚህ አይነት ጥፋት ---------- ተደራጅተን አባዎ ሆነን በቃ ይሄንን እንደዚህ አይነት ነገር ሰርተናል ይቅርታ አድርጉልን ብሎ ለህዝብ ሲያሳውቁ አይተናል ሰምተናል የእነሱ መረጃ

አባዎ ምንድን ነው

አባዎ ማለት ያው አሸባሪ ነዋ

የምን አሸባሪ

ያው ስለ ሰላም አሸባሪ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

760

እኮ ምን ይባላል አባዎን በትክክለኛ ትርጉሙን ንገረን

አባዎ ማለት እንግዲህ

አባዎ አሁን እያልከን ያለከው እንግሊዘኛ ነው በአማርኛ ነው ወይስ በኦሮምኛ ነው

ያው ስማቸው አባዎ ይላሉ

አባዎ የምትለውን በአማርኛ ነው ወይስ በአማርኛ ንገረን እንዲገባን ፍ/ቤቱ በአማርኛ ነው የሚሰራው

ኦነግ ይላሉ እነሱ

ኦነግ ያልከው እሺ እስቲ የት አካባቢ ነው ይሄ ነገር የተከሰተው የት አካባቢ ነው

እዛ አሰበ ተፈሪ

አሰበ ተፈሪ

አዎ ምእራብ ሐረርጌ

ምእራብ ሐረርጌ አሰበ ተፈሪ ከተማ

አዎ

የት አካባቢ የት ቀበሌ

ያው እኛ የምንኖረው በዛን ጊዜም 01 አካባቢ

ቀበሌ 01

አዎ

ምን ይባላል ሰፈሩ

ሰፈሩ ቻይና ሰፈር ይባላል

እሺ ቻይና ሰፈር ስንት አመተ ምህረት ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

761

በ1997

ከምን ወር ጀምሮ ነው

ያው ከሐምሌ ጀምሮ መሰለኝ

ከሐምሌ ጀምሮ 1997 ጀምሮ አንተ በአካል በቀጥታ በአይንህ ማለት ነው እነሱ ሲናገሩ የሰማሁት ነገር አለ ብለከኛል እሱን በኋላ ትነግረኛለህ በቀጥታ የምታውቀው ነገር አለ እንዴ እነዚህ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሹ ላይ እኔ የማውቀው ቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ

ከመዋላቸው በፊት የምታውቀው ነገር አለ መጀመሪያ

ያው ከዛ በፊት እነሱ ከተማሪ ጋር ይሄዳሉ ብሎ ሰው ሲያማክሩ ምናምን ሲሉ ሰምተናል

ከምን ተማሪ ጋር ነው የ ሚሄዱት

ያው ረብሻ ሁካታ ለማንሳት ከተማሪ ጋር አብሮ አሉ ይላሉ በዛን ጊዜ

ማን ነው እንደዚህ ብሎ ያለህ

ያው የታሰሩ ተማሪ ናቸዋ በዛን ጊዜ

በምን ምክንያት የታሰሩ

በጥፋት ነዋ በዛን ጊዜ በሁካታ ብዙ ረብሻ ስለነተሳበት ከዛ ወዲህ ነው በእያንዳንዱ እኛ ግልጽ ሆኖብን ያየነው እንጂ ከዛ በፊት አላየንም እነዚህን ሰዎች ይሄ ነገር እኮ በድብቅ ነው የሚሰራው እንጂ ወጣ የሚሉት በምስክር ላይ የሚሰራ ነገር አይደለም

አንተ ምንድን ነው ስራህ

እኔ በዛን ጊዜ ታጣቂ ነበርኩ

ታጣቂ ነበርክ

አዎ

762

የማን ታጣቂ ማለት ነው

የ01 ቀበሌ

ማለት የመንግስት ታጣቂ

አዎ

እሺ የመንግስት ታጣቂ ነህ

አዎ

እሺ ስለዚህ በፊት ለፊት የሚደረግ ስላልሆነ በቀጥታ አላውቅም ነው እያልክ ያለከው

አዎ

ሰማሁም ያልከው በረብሻው ምክንያት ከተያዙ ሰዎች ነው

አዎ

እሺ በኂላ ላይ መቼ ያዛችኂቸው

በዛን ጊዜ በሰኔ ወር ነው አካባቢ ተይዘው

ስንት አመተ ምህረት ላይ ተያዙ

በ1997 አልኩህ

እሺ በ1997 ተያዙ

አዎ አመቱ ስለቆየብን እያስታወስኩ እነግርሃለሁ እንግዲህ በዛን ጊዜ መሰለኝ ተይዘው እኛ እንደዚህ ተደራጅተን በማዴ ይባላል እንግዲህ በአማርኛው ማዴ የሚባል ነገር ስለማልችል ይቅርታ አድርጉልኝ

ማዴ የሚለው ቃል በምን ቋንቋ ነው

እኔ እንጃ እንግዲህ ለራሴው

763

እሺ ምን ማለት ነው አንተ የተገነዘብከው

ሴል ይባላል እንዲህ

እሺ እንግሊዘኛው ማዴ

አዎ በሴል ተደራጅተን ይሄንን መንግስት ለመገልበጥ ተነሳን ብሎ ሲያወሩ እነሱ በዛን ጊዜ ነው የሰማሁት

እንደዚህ ብለው የሚያወሩት ለማን ነው በቁጥጥር ስር ውለዋል ብለከናል ለማን ነበር የሚያወሩት

ለህዝብ

እሺ በየትኛው ህዋስ ስር ማዴ ወይም ሴል ያልከው በየትኛው ሴል ወይም በየትኛው ማዴ ስር ተደራጀን አሉ

በዛው ለኦነግ ነዋ የተደራጁት

ስርዓት አድርግ ቀጥሉ

በኦነግ ሴል ወይም ማዴ ተደራጅተን ምን እናደርግ ነበር አሉ ምን ስናደርግ ከረምን አሉ

ይሄንን መግንስት ለመገልበጥ ተነስተን በማዴ አደራጅተን እንደዚህ ብለን ነው የተነሳነው

ምን ስናደርግ ከረምን አሉ ተነሳን አሉ አደለም ከዛ በኋላ ምን አሉ

ያው ብዙ ነገር ነው ረብሻም ተማሪም

ተማሪውን ምን አደረግን ረብሻውን ምን አደረግን

ተማሪ ሁሉ ተነስቶ በዛን ጊዜ ውስጥ የሰው ህይወትም የጠፋ አለ በዛን ጊዜ ብዙ ማዴ ተነሳ ተይዘዋል እነሱ

እሺ እነሱ ተያዙ እነዚህ ሰዎች ደግሞ ስትይዧቸው ያሁ ረብሻ ላይ ድርሻችን ምን ነበር ብለው ነው ሲናገሩ የሰማከው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

764

ያን ጊዜ በየወረዳው ሊቀመንበር ነን ይላሉ በዚሁ በምእራብ ሐረርጌ ተወካይ ብለህ እኛ ነን ሰውን ያደራጀን እከሌ እኔ ሃላፊነት አለ እከሌ ብለው ሲናገሩ ያው እነሱ እኮ ተቀርፆ አለ እኮ የማይካድ

እሺ ቀጥል ግድ የለም

በዛን ጊዜ ነው ያየሁት እኔ

እሺ አሁን እነሱ ይሄ ከተያዙ በኋላ ያሉን ነው ብለሃል መጀመሪያ ላይ ረብሻው ሲነሳ ተማሪዎች በረብሻው ምክንያት የተያዙ ነገሩኝ ያልከው አለ ተማሪዎቹ ምን እያሉ ነበር በተከሳሾች ላይ ሲነግሯችሁ የነበረው በረብሻው ምክንያት የተያዙ ተማሪዎች አንተ የመንግስት ታጣቂ ሆነህ ምን እያሉ ነበር የሚነግሩህ

በዛን ጊዜ ነኝ አላለም ለህዝብ ነው የተናገሩት እኮ ተማሪም አብረው ነው የተያዙት አደለም እነሱ ነው እኛን ያደራጀው

እነማን አደራጁን

እነ አህመድ ዩሱፍ

እነዚህ ተከሳሾች

አዎ እነዚህ ናቸው ያደራጁን በዛን ነው የተነሳነው ብለው ለህዝብ ይቅርታ አድርጉልን ብለው የጠየቁት የዛን ጊዜ ነው የሰማሁት ምስክር ያየና የሰማ ነው አደለም በዛ በቃ ይሄንን ሁለቱን ሰማሁትና አየሁት

ጨርሰናል።

ዋና ጥያቄ አበቃ

የተከሳሽ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አቶ ኡስማኤል

አቤት

ተማሪዎቹ ተከሣሾች ናቸው ያደራጁን ብለው ሲናገሩ ነገሩኝ ነው የሚሉት ተከሣሾቹስ ተማሪዎቹን እኛ ነን ያደራጀናቸው ብለው ነግሮዎታል

ለእኔ

እህ

ከእኑ ጋራማ አልተነጋግርኩም እኮ

ጥያቄው ገብቶዎታል

አዎ ገብቶኛል

ተማሪዎቹ ተከሣሾቹ ናቸው ያደረራጁን ብለው ነገሩኝ አሉ

አዎ

እነዚህስ ተከሣሾች ተማሪዎቹን አደራጅተናቸዋል ብለው ለእርሶ ነግሮዎታል

በእዛን ጊዜ

እህ

አደባባይ ላይ መጥተው ነው አኮ ለእኔ

የለም ነግሮዎታል ወይ አሁን ግድ የለም እሱ

ለእራሴ

አዎ

ለእራሴ አይደለም እኮ እኔ አሁን ምስክር የወጣሁበት በአደባባይ --------

እኔ አሁን አጭር ጥያቄ እኮ ነው ነግሮዎታል ወይ ነው ነግረውኛል አልነገሩኝም ነው

ለእራሴ

አዎ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ሲሉ ሰማሁታ --- እንደዚህ አይነት ሲባል ጊዜ አይደለም በግሌ አይደለም እኮ ያው እነሱ እኛን እንደዚህ አደራጅተናል ሲሉ ጊዜ ነው እንጂ ጉን ቆምቼ የሰማሁትኝም አከሌ ኡስማኤል ብሎ ለእኔ ስሜን ጠርቶ አይደለም የነገረኝ

እ

በእዛን ጊዜ ነው የሰማሁት ማለቴ ነው

ህዝብ መካከል ደግሞ ተሰብስበው ያለውን ሁኔታ ይገልፁ ነበረ ነው ያሉት

አዎ

በምን ሁኔታ ነው እዛ ስብሰባ ውስጥ ሊገኙ የቻሉት ተከሣሾቹ

አይ አንግዲህ በእዛን ጊዜማ ተጠርጣሪ ብሎ ተያዙ እና በቃ ከተያዙ በኋላ በእያንዱንዱ እየተጠቆሙ እኔም እንደዚህ አይነት ጥፋት አጠፋሁትም በቃ ይሄንን ነገር ግልፅ አውጥተን በቃ ይቅርታ እንጠይቃለን ብሎት ተናገሩ

ተጠርጣሪ ብሎ የያዛቸው ማን ነው

ያን ጊዜ የመንግስት አካል ነዋ

የመንግስት አካል ስብሰባው ላይ ነበረ

አሉዋ ያን ጊዜ

ምን አይነት ሀይል ለምሳሌ ፖሊስ መከላከያ ወይ ደግሞ

ፖሊስ ነው

እ

ፖሊስ

ፖሊስ ነበረ የነበረው

አዎ ፖሊስ ነበረ

7868

እነሱ ይሄንን ሲናገሩ ህዝቡ መካከል በቁጥጥር ስር ውለው ነው ወይስ ታስረው ነው ወይስ ሳይታሰሩ ነው

በዛን ጊዜ ታስረው ነው

ታስረው ነው

አዎ

ታስረው ነበረ እንደዛ ይሉ የነበረው

አዎ ይቅርታ ጠየቁ እና ይቅርታ ህዝቡን ጠይቁ እና ያው እናንተ ጥፋት እናተ ጥፋታችሁ እና እናንተም ስራችሁን ህዝቡ ይወቅ ብሎ አደባባይ ላይ ህዝቡን አውጥቶ ተናገሩ በእዛን ላይ

በእዛን ጊዜ ተናገሩ

አዎ

አህን 2 ተከሣሾች ነው አውቃለሁ ያሉት

አዎ

2 ተከሣሾች ናቸው እዛ ነበሩ ያሉት

አዎ

ከ2ቱ ተከሣሾች ማንኛው ነው እዛ ህዝብ መካከል ይሄንን አሁን የሚሉትን የተናገረው

2ቱ መሀመድ እና መሀመድ አብዶ 2ቱም እዛው ነበሩ

ጥሩ ያን ጊዜ ታስረው ህዝብ መካከል ገቡ እና ይሄንን እንዲናገሩ ተደረገ

አዎ

ይሄንን ከተናገሩ በኋላ ህዝቡ ይቅርታ አደረገላቸው ወይስ በዛዉ ታሰሩ

በዛን ጊዜ

እህ

በዛን ጊዜው ህዝቡ ይቅርታ ተደርጐበታል እንግዲህ በመሀል በየት እስር ቤት እንደገቡ እኔ ለሰፈራ ነው የሄድኩት ከእዛ ወዲህ እኔ አላውቅም

በእዛን ጊዜ ግን ይቅታ ተደርጐላቸው ህዝቡ መካከል እነዚህ ተከሣሾች ተለቀቁ

በዛን ጊዜ

አዎ

አንድ 3 ቀን ነው 4 ቀን ታስረው በቃ ከእዛ ወዲህ የወጡ መሰለኛ

እሺ አሁን ምስክር የሚሰጡት ይቅርታ ተደርጐላቸው ከተለቀቁ በኋላ ሌላ ጥፋት ወይም ደግሞ እንደዚህ አይነት ድርጊት መስራታቸውን እርሳ የሚያውቁት አለ

እኔ

እ

እኔ ከእዛ ወዲህ ለሰፈራ ነው የሄድኩት ወዲያ

ሰፈራ ---

ለሰፈራ ሄጄ ከእዛ አሁን ነው የመጣሁ በቃ

ይቅርታ በተደረገበት ጊዜ በእዛ ይቅርታ በተደረገላቸው ጉዳይ ተይዘው አንድ አመት ያህል ታስረው መለቀቃቸውን ያውቃሉ አያውቁም

ታስረው

እህ

እሺ ተቃውሞው ምንድነው እስቲ

1ኛ ምስክሩ ማለት ነው እንደ እሳቸው አባባል ለህዝቡ ይቅርታ ካሉ በኋላ ህዝቡ ይቅርታ ብሎላቸው በ3ኛው ቀን የተፈቱ መሆኑን አውቃለሁ ከእዛ በኋላ ግን ለሰፈራ ወደ ሌላ ሀገር ሄጃለሁ አላውቅም ነው ያሉት አሁን ድጋሚ ጥያቄውን በመደጋገም የሚመጣ ነገር ስለሌለ

570

እንዲተው ነው ምክንያቱም አንድ አመት ታስረው ተለቀቁ አላሉም ከ3 ቀን በኂላ ተለቀዋል ከእዛ ውጪ አላውቅም ብለው አስቀምጠውታለ ነገሩን

በተቻለ መጠን አይደጋግሙት እ እሱ ከእዛ በኂላ ስላለው ጉዳይ አላውቅም ብሏል ይሄንን በተለያየ መንገድ እንትን ማለቱ የእኛንም ጊዜ ነው የሁላችንንም ጊዜ ነው የሚጨርሰው

ሌላ ጥያቄ ካለዎት

እነሱን ጠይቁ ልላቸው እችላለሁ ግን እንዳይሆን ብዬ ነው እኔ ብጠይቅ ይሻላል

አይ ተገቢ መሆኑንም እንትን እያላችሁ እስቲ ጠይቅ አንተ

ልጠይቅ

አዎ

ስንተኛ

40ኛ ተከሣሽ

40ኛ እሺ

በአማርኛ ልጠይቅ

ቆይ ግድ የለም በአማርኛ ከቻልክ በአማርኛ

በአማርኛ እጠይቃለሁ በቃ

እሺ

ግንቦት በ1998 ግንቦት 17 እሮብ እለት ያው ህዝብ አደባባይ ወጥተን ከእዛ ወፊት ታስረን በ--- ተደራጅተን ብለን ታስረናል ከታሰርን በኂላ የዛን ጊዜ ህዝብ ሰብሰባ ተጠርቶ ህዝብ ይቅርታ ተደርጐልን ወጣን ከወጣን በኂላ በ19/98 ሰኔ10 ቀን ታስሬ በ19/99 ታህሳስ ወር ታህሳስ 10 ቀን ከእስር መውጣቴን አታውቅም ወይስ ታውቃለህ

ይሄንን ታውቃለህ ወይ

ያ እንግዲህ እኔ አላውቅም

አውቃሁ አላውቅም ነው

አላውቅም እኔ

አላውቅም

በቃ ይበቃል

እሺ

70ኛ ነህ አንተ

አዎ 70ኛ ነኝ

70ኛ ተከሣሽ በግሉ መስቀለኛ ጥያቄ

እኔ 1997 እዛ ስብሰባ ላይ አይቻለሁ ብለሀል ያን ጊዜ እኔ ምን እንደተናገርኩ ታውቃለህ

አዎ

ምን ተናገርኩ እስቲ ምን ብዬ ነው የተናገርኩት

ይቅርታ አድርጉልኝ ---- ብለህ

አንተ ያን ጊዜ ከማን ቤት ነው

እ

አንተ ንገረኝ አስረዳኝ ለፍ/ቤቱ አስረዳኝ ኬት እንደተያዝኩ ከማን ጋር እንደተያዝኩ ለፍ/ቤቱ እንድታስረዳኝ ስለፈለኩ ነው ለምን በጅምላ እየተናገረ ስለሆነ በግልፅ

ቆይ እሺ ቆይ ይንግርሀል ከማን ጋር ነው የተያዝኩት

የእነሱ ጉደኛ

472

አከሌም አብሮን አለ የእኛ ሴል ነው ተብሎ ስለጠቆመ ተይዟል በእዛን ጊዜ መጣ እና አደባባይ ላይ ወጥቶ ተናገረ አሁን ውሸት ነው ካለ የተቀረፀ ፊልም አለ የእነሱ ያሉት ያው ምእራብ ሀረርጌ አለ መጥቶ ያንን የተቀረፀውን

ጓደኛህ ጋር ማለት ነው -----

አዎ ቆሞ ሲቀረፅ አለ ያንን የተቀረፀውን ለእነሱ ምስክር ይሆናል እንደውም

በል እሱን ተወው እና ዞሮ ዞሮ ከጓደኛህ ጋራ በህዝብ ፊት ተናግረሀል

መናገሩ እዛ ላይ ተገኝቻለሁ እሱ እንደዚህ አደረገ እንደዚህ ደረገ የሚለውን እዛ ላይ ምንም እንዳልተናገርኩ ነው እኔ ቃሌን እንዳልሰ

ተናግረሀል እያለህ ሌላ ጥያቄ ካለህ ጠይቅ

እሺ

እንግዲህ እሱ ነው ተናግረሀል ካለ እኛ ምን እናድርግ

---የተያዘው

ያው እንግዲህ በዛን ጊዜ ተያዘ

የለ አሁን በእዛን ጊዜ ተያዘ መያዙ አልተካደም ግን ከማን ቤት ተያዘ

ታዲያስ ከተያዘ በኋላ ቤቱ ---- ምን ብዬ ልንገርህ እኔ

በቃ ከማን ቤት ተያዘ አይዞህ ተረጋጋ የተያዘበትን ቤት አላውቅም ከእዛ በኋላ ተይዞ መጥቷል ነው የምትለው አይደል

አዎ

ይሄንን መልስ

አላገኙ-- ቤቱን ደብቆ ነው ከተያዘ በኋላ ተጠቁሞ ከእዛ ጋ ነው የመጣው እሱ

ጓደኛው ማን ማን

እ

ማነው ጓደኛው ሲሉ ማን

በዛን ጊዜ

በዛን ጊዜ አዎ

እሺ ጓደኛ የእሱ ጓደኛ

እህ

መአት ነው ማን ሴል የተባለው እኮ ቀላል ሰው አይደለም አከሌ ብለህ የምትናገር ሰው አይደለም እኮ በወቀረት ካልያዝክ እንዲ እንደሱ 2 አይደለም እኮ ሴሎቹ ትቶ ነው እንጂ መንግስት እኮ

የለም እኛ አሁን

ከሙሀመድ ኡስማን ቤት መሀመድ ኡስማኤል ቤት ነው የተያዘው ይሄ እራሱ እዛ ጋ ተደብቆ

መሀመድ ኡስማኤል ቤት

አዎና ተደብቆ

ቀጥሉ ሌላ

ሌላ ከዚያ ወዲህ እኔ የማውቀው ነገር የለኝም ጨርሻለሁ በእራሴ በኩል

ቆይ ቆይ አይዞህ አይዞህ ደከመህ አይደል በዛብህ አይዞህ ትንሽ ይቀርሀል እስቲ ቀጥሉ

እየነገርኳቸው ነው እኮ አቶ ኡስማኤል

አቤት

ተከሣሾቹ ይቅርታ ተደርጎላቸው በህዝቡ ወደ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ለብዙ ጊዜ አብራችሁ አንድ አካባቢ ኖራቹሀል አልኖራችሁም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

772

እኔ በእዛን ጊዜ አንድ ሰፈር ነን ሲወጡ አይቻለሁ ከእዛ ወዲህ ለሰፈራ ነው የሄድኩት ነው ያልኩት እኮ

ለሰፈራ ሄጃለሁኝ

አዎ

ከእዛ ወዲህ የሆነውን አላውቅም ነው

አዎ

እሺ በቃን

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አበቃ

አዎ

ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ድጋሜ ጥያቄ የለም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እናመሰግንሀለን ጨርሰሀል

እሺ

ያው እንግዲህ አንድ ልጅ--- የራሴ ማለት ነው

እሺ እንስማ

ከሩቅ ቦታ ነው የመጣሁት

አሳስቡ እስቲ ያው -- ቀጠሮ ቀሪዎቹን እናቅርብ ነው

በቃ ይሄው ነው የምናሳስበው

እሺ ትእዛዝ ሰጥተናል

775

ት እ ዛ ዝ

ዛሬ የተሰሙት ምስክሮች የምስክርነት ቃል ተገልብጦ የመዝገቡ አካል እንዲሆን ታዟል። ዐ/ሕግ ቀሪ ምስክሮቹን በመደበኛው ቀጠሮ እንዲያቀርብ ታዟል። ያው መደበኛው ቀጠሮ ታውቁታላችሁ ቀጠሮው ያው የድሮው ቀጠሮ ነው ቀጠሮ አልተለወጠም እሺ እናመሰግናለን።

መ/ወ

776

የመ/ቁ. - 04486

ቀን - ሰኔ 4 ቀን 2002 ዓ/ም

ዳኞች - ብርሃነ መስቀል ወጋሪ

- ይርጋ አይቼህ

- እልፍነሽ ወሎሬ

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ 73 ሰዎች

የቀረቡትንና ያልቀረቡትን ተከሳሾች እንለያለን 1ኛ. አብዱረህማን ባሌ ከማረሚያ ቤት ቀርቧል፣ 2ኛ ሽሪፍ አሊ ቀርቧል፣ 3ኛ. አህመድ ኑር ቀርቧል፣ 4ኛ አህመድ ዲን ኢብራሂም ቀርቧል፣ 5ኛ ከማል አሊዪ ቀርቧል 6ኛ መሀመድ ኢብራሂም ቀርቧል 7ኛ ሲራጅ አህመድ ቀርቧል 8ኛ ፋጤ አሜን በተመለከተ የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ህክምና ያልጨረሰች መሆኑን በስልክ የገለጹልን ስለሆነ ለሰኔ 4 ለማቅረብ አልቻልንም ብሎ ማረሚያ ቤቱ በ4/10/2002 በተፃፈ ደብዳቤ መልስ ሰጥቷል 9ኛ አልቀረቡም 10ኛ ጀማል ሀምዛ ቀርቧል 11ኛ ጣሃ አህመድ ቀርቧል 12ኛ ዙቤድ ሁሴን ቀርቧል 13ኛ አብዱረሃማን ሁሴን ቀርቧል 14ኛ ረምላ ሽሪፍ ቀርባለች 15ኛ ኢብራሂም ሁሴን ቀርቧል 16ኛ ኪሚያ አሚን ቀርባለች 17ኛ ዘይነባ መካን ቀርባለች 18ኛ አብዲሹኩር ኡመር ቀርቧል 19ኛ ሽፊፍ ኡመር ቀርቧል 20ኛ አብዲ ኡስማን ቀርቧል 21ኛ መሀመድ አሊዩ ቀርቧል 22ኛ ጀና መሀመድ በዋስ ቀርባለች ሌሎቹ ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል 23ኛ አብዱልአሚድ መሀመድ ቀርቧል 24ኛ ሼክ መሀመድ 25ኛ ሻም ኢብራሂም 26ኛ አብዲ አህመድ ኑር ቀርቧል 27ኛ ኢብራሂም አህመድ ቀርቧል 28ኛ አብዲ አሊ አህመድ ቀርቧል 29ኛ ጀማል ከድር ሳኒ ቀርቧል 30ኛ ራሃማ መሀመድ ቀርባለች 31ኛ ሰሚራ ሙሜ አብዱላሂን በተመለከተ የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ መሞት አለመሞቷን ለማረጋገጥ ቀበሌ የጠየቀ መሆኑንና ቀበሌው ተለዋጭ ረጅም ቀጠሮ ለማረጋገጫ ጠይቋል አልቀረበችም ወይ መሞቷ አልተረጋገጠም 32ኛ ጫልቱ ኢብራሂም ቀርባለች 33ኛ አብዲ ሀጂ ሙሳ ክሱ ተቋርጧል 34ኛ ጀማል ከድር ቀርቧል 35ኛ አዱኛ መሀመድ ቀርባለች 36ኛ ዱርሲቱ አብደላ ቀርባለች 37ኛ አብዲ በሽር ኡስማኤል 38ኛ ኮከብ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

777

መሀመድ ዩሱፍ ቀርቧል 39ኛ ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ ቀርቧል 40ኛ አህመድ ሼክ ዩሱፍ ቀርቧል 41ኛ ሰልዩ አብደላ ቀርቧል 42ኛ መሀመድ አሊ ቀርቧል 43ኛ አህመድ ኡስማኤል ቀርቧል 44ኛ ሀጂ ጣሃ ሀሰን ቀርቧል 45ኛ ዩሱፍ ጨሌ አህመድ ቀርቧል 46ኛ ሙክታር አብዱልመጅድ ቀርቧል 47ኛ አሊዩ አብደላ ቀርቧል 48ኛ ዘሀራ አብዶሻ ቀርባለች 49ኛ መሀመድ ኡመሬ ቀርቧል 50ኛ ጃፈር ኡመር ቀርቧል 51ኛ የሱፍ ዳውድ ቀርቧል 52ኛ ጀማል አደም ቀርቧል 53ኛ በከር ጣሲ ቀርቧል 54ኛ አህመድ ነጃሽ ቀርቧል 55ኛ ጀማል ሁሴን ቀርቧል 56ኛ ከድር አደም ቀርቧል 57ኛ ሼክ ከድር ቱሬ ቀርቧል 58ኛ ኡመር መሀመድ ቀርቧል 59ኛ አብዱላሂ ሙሳ ቀርቧል 60ኛ ሸክር ቱኬ ቀርቧል 61ኛ መሀመድ አሊ ቀርቧል 62ኛ መሀመድ አጀባ ቀርቧል 63ኛ አድነን ጎሼ ቀርቧል 64ኛ መሀመድ ኑር አህመድ ቀርቧል 65ኛ ሰኢድ አደም ቀርቧል 66ኛ ከሊፍ አህመድ ቀርቧል 67ኛ ኢብራሂም አብዱላ ቀርቧል 68ኛ አብደላ መሀመድ ቀርቧል 69ኛ ሀሰን መሀመድ ቀርቧል 70ኛ መሀመድ አብዶ ቀርቧል 71ኛ ኑሬ ኡስማን ቀርቧል 72ኛ ጫላ ሙክታር ቀርቧል 73ኛ አብዶሽ ሙሜ ቀርቧል ያልቀረቡት ከ1 እስከ 73 ውስጥ ያልቀረቡት 8ኛ፣ 31ኛ ሲሆን 33ኛ ተቋርጧል 22ኛ በዋስ ቀርባለች ሌሎቹ የተቀሩት ከ1 እስከ 73 አሁን ከተጠሩት ውጪ ሁሉም ከማረሚያ ቤት ቀርቧል መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው የዐ/ህግ ምስክሮች ለመስማት ነው የዐ/ህግ ምስክሮች ለ3 ተከታታይ ቀናት ዛሬ አርብ ቀጣይ ሰኞ እና ማክሰኞ ለሶስት ጊዜ ተከፋፍሎ ለመስማት ሌሎቹን አጀንዳ ዝግ በማድረግ በተከታታይ ተይዞ ነው ዐ/ህግ ምስክሮች አቅርቦ እንደሆነ ተጠይቆ ምስክሮቻችን አልቀረቡም ጭሮ ደርሰዋል ከሰዓት ቢመጡ ነው የሚል አስተያየት ነው የሰጡት ይሄንኑ ያስመዝግቡ ዐ/ህግ ማን ምስክሮቻችሁ እንደሆኑ እና የት እንደደረሱ

የዛሬ የተሰጠን ቀጠሮ መሰረት ምስክርነት እንድናቀርብ አሁን ሁለት ምስክሮች በትራንስፖርት ከጭሮ የጭሮ ፖሊስ ኮሚሽን አሳፍሯቸው ወደ ድሬዳዋ እየመጡ ይገኛሉ ሁለት ምስክሮች ሌሎች ምስክሮቻችንን በተመለከተ ከሩቅ ቦታ ከቦኬ ምናምን ከሚባለው ቦታ አሁን ወደ ጭሮ ይገባሉ ተብሎ እየተጠበቀ ነው እስከ ለሰኞ ቀጠሮ ይደርሳሉ ሁለቱ ግን አሁን እየመጡ ነው ለከሰዓት ይደርሳሉ ከሰዓት መስማት ይቻላል ከ9፡00 በኋላ ይገቡልናል ሁለቱ ምስክሮች አሁን እንዳረጋገጥኩት፡፡

እሺ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ

የተከበረው ፍ/ቤት ከሰዓት ስንት ሰዓት

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

778

9፡00 ሰኣት ብለዋል

የተከበረው ፍ/ቤት

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አቶ አድማሱ ይቀጥሉ

ደጋግመን አመልክተናል እንደው ሁለት ምስክር ሊያቀርቡ ሊያቀርብ ከፈለገ ዐ/ህግ በእውነት ሊያስረዳ ከፈለገ ዐ/ህግ አብዛኛው ምስክር እኮ ያለው ድሬዳዋ አለማያ ሐረር እኮ ነው ያለው ሐረር ነው ያለው ተመልከቱ ጭሮ ፍሰጋ አሁን እነዚህን 9፡00 ሰኣት ሲደርስ ለ10፡00 ሰኣት ነው 10፡00 ሰኣት ሲደርስ ለ11፡00 ሰኣት ነው ይባላል የስራ ሰዓት እንጂ እውነት አይቀርቡም በእርግጠኝነት ነው የምናገረው ዛሬ ምስክር አይቀርቡም ሊያቀርቡ ከፈለጉ ይኸው እዚህ ድሬዳዋ ከተማ አሉ እኮ ምስክሮች ምንም እኮ ክርክር ይኸው ተከሳሾችም ያውቃሉ ምስክሮቻቸውን ያውቋቸዋል ለምን አያቀርቧቸውም ምንድን ነው የድሬዳዋ ምስክር የማይቀርብበት ምንድን ነው ድሬዳዋ ያለ ምስክር የማይመሰክረው ምዕራብ ሐረርጌ ካልሆነ በስተቀር ምስክር መጥቶ የማይመሰክርበት ምክንያት ምንድን ነው ወይ ከተዋችሁ ትተናችኋል ይበሉ ለምስክር ብቻ እየተባለ የተቀጠረው ቀጠሮ በእውነት መዝገቡን ብታዩት ጉድ ነው የምትሉት እኔ የሚጠየቁትም የሚመጡት የሚናገሩት አንድ ቋንቋ ነው የሚናገሩት አንዴ ፖሊስ ይላሉ ፖሊስ ደግሞ እዛ ጭሮ ላለው አስተዳዳሪ ፖሊስ ይላል ለምን እዚህ ያሉትን መጀመሪያ አያመጧቸው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ትኩረት ሰጥቶት እዚህ አካባቢ ያሉትን አቅርቦ እንዲያሰማለን ካሉ ይመስክሩባቸውና ይፈረድባቸው ከነሱ ወዲህ ስንት ፍርድ እያገኘ ነፃ የሚወጣ ይወጣል ቆይ አሁን ይሄንን ያህል ታስሮ ነፃ ቢባል አንድ ሰው ካሳውን እስቲ ካሳው እውነት ነፃ ወጥቷል ወይስ ፍትህ አገኘ እንደው ይሄም ሊታሰብ ይገባል ነገ በእኔም ሊባል ይገባል

ከጠበቃችሁ ጋር ተነጋገሩና አግባብነት ያለውንም የሌለውም ሁሉ ነገር እኛ ከሰዓት በኋላ ይደርሳሉ ብለዋል ፍ/ቤቱም የዐ/ህግ ምስክሮች ከሰዓት የሚመጡ ከሆነ ከሰዓት ለመስማት ቀጠሮ ለ9፡00 ሰኣት ነው ዐ/ህግ ያሉት ለ9፡00 ሰኣት ተቀጥሯል ዐ/ህግ በዚህም ማሳሰቢያ የምትሰጡት ችሎቱ ምናልባት ሌሎች አጀንዳም እንዳንሰራ አድርጋችሁ ዛሬ አሁን ምስክር ከሰዓት በፊት እንሰማለን ብለን አስበናል ይሄንን አሁን ጭሮ የተሳፈሩትን ትናንትና ቢሳፈሩ ይቀርቡ ነበር ያን አለማድረጋችሁ ግድፈት ነው አሁን በተከላካይ ጠበቃ በኩል እየተገለጸ ካለው ሁኔታ እና ብዛት ያላቸው እስረኞች ከመሆናቸው አኳያ ይሄንን ትኩረት አለማድረጋችሁ

ከፍተኛው ፍ/ቤት

779

አግባብ ሆኖ አናገኘውም ትኩረት ሰጥታችሁ ምስክሮቻችሁ ካሉ በተያዘው ፕሮግራም እንድታቀርቡ ይሄንን ለማለት ነው የምፈልገው ቀጠሮ ለ9:00 ሰኣት፡፡

ማ/ተ

790

ዐ/ሕግ አልመጡም ብሩ ወንዴ በችሎት አሉ ጉዳዩን የያዙ ዐ/ሕግ አልቀረቡም ብለዋል ተከሣሾች እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ተከሣሾች አሁን 9፡05 ነው ያው ከሰአት በኋላ ምስክር ለ9፡00 ሰአት ለመስማት ነው የተቀጠረው ሌላ ዐ/ሕግ ነበረ አይደለ በፊት እየመጡ ነው ዐ/ሕግ ማንን ልሰይም

ባዝን አብረሀም

እሺ ባዝን አብረሀም ቀርበዋል መዝገቡ ከሰአት በኋላ ለ9 የተቀጠረው ያው የከሳሽ ምስክሮችን ለመስማት ነው አሁን 9፡20 ሆኗል አርፍዳችሁ ነው የመጣችሁት ምስክሮቻችሁ ቀርበዋል

የዛሬ ምስክሮቻችን አልቀረቡም ፖሊስ እስከ አሁን ድረስ ጭሮ ነበርኩ እኔ ፐርሰናሊ በመኪና ልኳቸዋል እኛ ይዘን እንመጣ ነበረ እንደ አጋጣሚ እኛ አላገኘናቸውም 5ኛ እና 26ኛ ምስክሮቻችንን ፖሊስ ይዞ እያመጣቸው ነው ስቲል ስንደውልም መንገድ ላይ ነን ነው የሚሉት አልደረሱልንም በስህተት ቀሪዎቹ ምስክሮች እስከ አሁን ድረስ ስንፅፍ የነበረው ለምእራብ ሐረርጌ ፖሊስ መምሪያ ነበረ ከእዛ ነው ሲመጡ የነበረው እና ምእራብ ሐረርጌ ያሉትን ምስክሮቻችንን ስለጨረስን ቀሪ 3 ምስክሮች ብቻ ነው ናቸው ምእራብ ሐረርጌ ያሉን ምስራቅ ሐረርጌዎችን ያው ትእዛዝ አድርሰናል ምናልባት ሰኞ እና ማክሰኞ ላለው ቀጠሮ ሊመጡልን ይችላሉ ምእራብ ሐረርጌ ግን 3 ምስክር ነው የቀረን ከእነሱ 2ቱ አሁን በመንገድ ላይ ናቸው 2ቱም

እሺ አስተርጓሚ ሰምተሀል አይደል እሺ ዐ/ሕግ ያሉትን ንገራቸው የእነሱንም ሀሳብ እንሰማለን እሺ በእዚህ ላይ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቆች የምትሉት ነገር ካለ አስመዝግቡ

እኛ ቅድም ተናግረናል የተከበረው ፍ/ቤት ምንም ልንል ቅድም ተናግረናል ምንም ልንለው የምንችለው ነገር የለም ያው ዝም ብሎ እንዲሁ መናገር ብቻ ነው የሚሆነው ስለዚህ እኛ እንግዲህ በዚህ ይብቃን

እንግዲህ ዛሬ አሁን ከሰአት በኋላም ምስክሮች አልቀረቡም ያው ትእዛዝ ተሰጥቷል

ት እ ዛ ዝ

781

የዛሬው ምስክሮች ስላልቀረቡ ምናልባት ደግሞ ያው ለሰኞም ለማክሰኞም ቀጠሮ ተይዟል በእለቱ ያቀረባችሁት ቀጠሮ ላይ የምታቀርቡ ከሆነ እንሰማለን ያው ተከታታይ ቀጠሮ ቀደም ሲል የተሰጠ ስለሆነ ሰኞ ለሰኞ ተቀጥሯል በቀድሞው ትእዛዝ መሰረት ማለት ነው

እሺ ምናልባት ለፍ/ቤቱ ከእነዚህ ዛሬ መንገድ ላይ ያሉት እና በተራንስፖርት ምክንያት ከቀሩት በተጨማሪ ሌሎች 2 ከዋቤ ወንዝም ተነስተው እየመጡ ያሉ አሉ ከእነሱ ጋ አንድ ላይ ወይ ሰኞ ወይ ማክሰኞ ያው እናቀርባለን በእዚሁ ትእዛዝ ይሰጥልን

በትክክልም እየመጡ ነው

ለሰኔ 7 2002 ነገራቸው

መ/ወ

782

የመ/ቁ. - 4486

ቀን - ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ/ም

ዳኞች - ብርሃነ መስቀል ወጋሪ

- ይርጋ አይቼህ

- እልፍነሽ ወሎሬ

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ እያሱ መኮንንና አረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ---------- ቀርበዋል በዋለው ችሎት ያልቀረቡት በዛው መልኩ ያልቀረቡ መሆኑ የተለወጠ ነገር አለመኖሩን ችሎቱ አረጋግጧል፡፡

ዛሬ የተቀጠረው የዐ/ህግ ምስክሮችን ለመስማት ነው ዐ/ህግ ምስክሮቻችሁን አቅርባችኋል ማን ስንት ሰው ቀረበ

ምስክሮቻችን አሁን 17 ሰው ቀርቦልናል

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ማን እና ማን ነው ያለው

እየመጡ ያሉ 6 ምስክሮች እየመጡ ነው

የ23ኛ፣ 37ኛ እና 38ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ ቀርበዋል

የሌሎች ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ

ቀርበዋል ምስክሮች ስለመቅረባቸው አስተርጓሚ ለተከሳሾቹ ንገራቸው

የቀረቡ ምስክሮች በጥቅሉ 4ኛ ምስክር 12ኛ ምስክር 31ኛ ምስክር 32ኛ ምስክር 33ኛ ምስክር 34ኛ፣ 35ኛ፣ 39ኛ፣ 44ኛ፣ 45ኛ፣ 50ኛ፣ 53ኛ፣ 62ኛ፣ 65ኛ፣ 67ኛ፣ 68ኛ፣ 86ኛ ምስክሮች ቀርበዋል

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ማን ማን ላይ እንደሚያስረዳ

ሲገቡ ምስክሩ ሲመጣ በዚህ ክስ ላይ በእነከሌ ተከሳሾች እያልኩኝ ልናገር ቃለ መሀላ እየፈጸሙ ሲገቡ

ቃለ መሀላ ይፈጽሙና ሲቀርቡ ማን ምስክር እንደሆነ እያረጋገጥን ምን ጭብጥ እንደሚያስረዳ እያስመዘገብን እንሄዳለን ብለዋል ዐ/ህግ በዚሁ መልኩ እንቀጥላለን ምስክሮቹ ቃለ መሀላ ይፈጽሙ፡፡

አሁን ለቃለ መሀላ የቀረቡት ምስክሮች 3ኛ፣ 26ኛ፣ 4ኛ፣ 39ኛ ናቸው እነዚህ ናቸው ቃለ መሀላ

አመዲን አህመድ

አመዲን መሀመድ

አመዲን መሀመድ አደም፣ አህመድ ከሊፍ በከር፣ አብዲ አህመድ፣ ሀሰን ዩሱፍ፣ የዐ/ህግ ክስ ዝርዝር 3፣ 4፣ 26 እና 39 ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ቀርበዋል ማንነታቸውን ስማቸውን አቤት ብለዋል ቃለ መሀላ ይፈጽሙ በእውነት ለመመስከር

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እንምላለን

ጭብጡን አስመዝግቱ 3ኛ ምስክር ማን ምን እንደሚያስረዳላችሁ ጭብጥ አስመዝግቡ ዐ/ህግ

ጭብጥ

3ኛው ምስክር የሚያስረዳልን 3ኛው ምስክራችን ማለት አህመዲን መሀመድ አህመድ ነው በ42ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የሚመሰክርልን ጭብጥ 42ኛው ተከሳሽ አሁን ካልተያዘው አብደላ መሀመድ የተባለው ግለሰብ እኛን ተደራጁ አብደላ መሀመድ የተባለው ምስክራችንን ተደራጅ በኦነግ ሴል ስር ተደራጅ እያለ የጠየቀውና ያደራጀው መሆኑን አሁን ግን 42ኛ ተከሳሽን በመልክ እንደማያውቀው 42ኛ ተከሳሽን የሚያውቀው አብደላ መሀመድ የተባለ ያልተያዘው ሰው የነገረው መሆኑን ይሄንን ነው የሚያስረዳልን፡፡

ጭብጡ ግልጽ ነው ምስክሩን ጥሯቸው

ክሱ ካስፈለገ 24ኛ ክስ

24ኛ ክስ ላይ ነው 42ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ነው ብለዋል መተያየትም ስላልተቻለ እነሱንም ማየት አልቻልንም ምስክሩን እና ማን እየመሰከረ ለመከታተል ስለሚያስቸግር ለ5 ደቂቃ እናቋርጥና

የተከበረው ፍ/ቤት እዚህ ላይ ተቃውሞ አለን

እሺ የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ አቶ አድማሱ ተቃውሞው ምንድን ነው

አብዲ መሀመድ አህመድን ዐ/ህግ የቆጠረው ለ42ኛ ተከሳሽ አይደለም በክስ ቻርጁ ላይ የ21ኛ ተከሳሽ ምስክሬ ነው ብሎ ነው የቆጠረው ስለዚህ ሊያሰማ አይገባውም

መልስ ስጡበት

ትክክል ነው ክሳችን ቻርጅ ላይ እንደዛ ይላል ግን አሁንም ጭብት አስይዘናል ያንኛውም ክሳችን ላይ አለ በሁለቱም ላይ ያስረዳልናል

በሁለቱም ሲሉ

በክስ ቻርጃችን ላይ በቀረበው ቅድም እኛ ጭብጥ ባስያዝናቸው

ሁለቱንም ያስረዳልናል ነው

አዎ

እሺ ምስክሩን ወደ መስማት ነው የምንሄደው

ያልተቆጠረ ምስክር እኛ የማናውቀው እከሌ ይመሰክርባችኋል ተብለን ያልተባልነው ዝም ብሎ እዚህ ሲመጣ

የግድ ምስክርን ማወቅ ብይኑ ምንድን ነው እንዲህ ምስክር ምስክር ሆኖ ክሱ ላይ በጠቅላላ ሁኔታ ተቆጥረዋል ተገልፀዋል አሁን ጭብጥ ሲያስይዙ ዐ/ህግ በዚህ ጉዳይ ላይ በዚህ ሁኔታ የሚለውን መድገም ስለሌለብን ያስሙልናል ብለዋል በእናንተ ተቃውሞ የሰጡት መልስ አሁን በተቃውሞአቸው በገለጹትም በጭብጥም ባስመዘገብነው ይመሰክሩልናል የሚል ስለሆነ የቀረበውን ተቃውሞ አልተቀበልነውም ምስክሩን ወደ መስማት እንቀጥላለን ምስክሩን እናንተ

785

ማወቅ አለማወቅ ሌላ ነገር ነው እዚህ ምስክሩን የሚጠይቀውን የሚመሰክረውን ትጠይቃላችሁ በመስቀለኛ ጥያቄ

3ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አመዲን መሀመድ አህመድ

እድሜ - 22

ሥራ - አርሶ አደር

አድራሻ- ጎይቶ ቀበሌ ምዕራብ ሐረርጌ ወረዳ ዳሎ ወለቡ ወረዳ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

በነማን ጉዳይ

በእነ አብደላ መሀመድ ኡመር

አብደላ ማን

አብደላ መሀመድ ኡመር

ምን አድርጎ እንደተከሰሰ ታውቃለህ ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለኝም

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

አብደላ መሀመድ ያለው አሁን አሉ ወይ

እዛ ነው ያለው

የት

ወረዳ ዳና ረጉ

786

ምንድን ነው አብደላ መሀመድ ምንድን ነው ያደረገው

ሰዎችን ሲያደራጅ ሰማሁና ተደራጀን

አሁን የተናገረውን ነገር ንገረን

እነ መሀመድ ሀጂ ነው ያደራጁኝ ብሎን እናንተንም አደራጃችኋለሁ ብሎ እኛ ጋ መጣ

መሀመድ ሀጂ አሁን የት ነው ያለው

እዚህ ነው ያለው ይላሉ ግን የት እንዳለ አላውቅም

የት እዚህ ማለት የት ነው

እስር ቤት ያለው እሱ ነው ሲባል ሰማሁ እንጂ የት እንዳለ አላውቅም

በምልክት ታውቀዋለህ እንዴ

አላውቅም

በምን አደራጃቸው መሀመድ ሀጂ በምንድን ነው ያደራጀው

እነሱ ተደራጅተው በኦነግ ፓርቲ ተደራጅተው ነው ያሉት በዛ ነው እንረዳችኋለን በማለት ያደራጁት

ማን እናንተን አደራጁዋችሁ እኛ አደራጀ እያለ ነው

አዎ

ጠይቀው አዎ አትበል የራስህን እውቀትህን መተርጎም መብት የለህም ጆሮህ በደንብ የማይሰማ ከሆነ ወይም ያልሰማህ ከሆነ እንደገና ድገምልኝ በል ቃላቱ ልዩነት አለው

አዎ አብደላ ነው ያደራጀን መሀመድ ሀጂ ነው እንዲህ አደራጃችኋለሁ በማለት የነገረኝ

ተደራጅታችሁ ምን አደረጋችሁ ምንድን ስራችሁ እስቲ

ከተደራጀን በኋላ ብር አዋጥተን ኦነጎችን በመርዳት በዛ ብር ኦነጎችን በመርዳት በሀገር ውስጥ እንዲኖሩ እናደርጋለን

ገንዘቡን ማን ነው የሰበሰበው ያዋጣችሁትን ገንዘብ

አብደላ

ለማን ሰጠሁ አለ አብደላ

ለነ መሀመድ ሀጂ ነው የምሰጠው አለ

መቼ ነው

በግምት ሶስት አመት ይሆናል

ወሩን ታውቃለህ

ነሐሴ

ቀንስ ታውቃለህ

ማክሰኞ መሆኑን አውቃለሁ በቁጥር ስንት እንደሆነ አላውቅም

የት አገር ነው ቦታው እንዲህ ያደረጋችሁበት ቦታ የት ነው

ዳሮ ረቡ ወረዳ ቦይዶ ቀበሌ

ጨርሰናል፡፡

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል ብለዋል

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

መሀመድ ሀጂ የተባለውን ሰው አላውቀውም ብለሃል እስር ቤት አለ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለሃል አንተ እሱ ይሁን አይሁን በምን ታውቃለህ የማታውቀውን ሰው

እኔ ያየሁት የለም አብደላ ሲለኝ ነው የማውቀው አብደላ ነው የነገረኝ

የአብደላን ወሬ ነው የሰማኸው

አዎ የአብደላን ወሬ ነው የሰማሁት

788

እናመሰግናለን ይበቃናል።

ድጋሚ ጥያቄ አለ

ምናልባት ፍ/ቤቱ 42ኛ ተከሳሽንም መሀመድ ሀጂን ግንዛቤ እንዲወስድልን ብቻ ነው መሀመድ ሀጂ የተባለው 42ኛ ተከሳሽ መሆኑን

42ኛ ተከሳሽን ፍ/ቤቱ አስነስቶ ያሳይልኝ የሚለው የማያውቀውን ቢያየውስ ያውቀዋል

አላሉም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

አመዲን ለአንተ ማን ነው የነገረህ

አብደላ ነው የነገረኝ

አብደላ የት ነው የነገረህ

ከእሱ ጋር ከአሁን በፊት ምስክር ተብሎ እዚህ ድሬዳዋ መጣን አንተ እኔ ላይ ምስክር እንድትሆን ነው የምፈልገው እኔ መሀመድ ሀጂ ላይ ምስክር እንድሆን ነው የሚፈልጉኝ አንተ ግን እኔ ላይ ምስክር እንድትሆን ነው የምትፈለገው አለኝ

ብሎ አብደላ ነገረኝ አለ

አዎ እንደዛ ብሎ አብደላ ነገረኝ

አብደላ የነገረህ ቀኑ መቼ ነው ወይም አመቱ

አንድ አመት በዚሁ አንድ አመት ውስጥ ነው የነገረኝ

በዚህ አመት ስትል የትኛው ወር

ባለፈው አመት በዚሁ ሰኔ ውስጥ መጣን በዛው ነው የነገረኝ

የት ስትመጡ

እዚህ ፍ/ቤት ስንመጣ ቀኑ ቀጠሮ አልፎ ሄድን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እዚህ ፍ/ቤት ስትመጡ ነው የነገረህ አብደላ

አዎ አብረን ነው ከአንድ ቦታ ተነስተን ወደዚህ ስንመጣ ነው የነገረኝ

አብደላ ለምን ነበር ወደዚህ የሚመጣው አንተ ለምን ነበር ወደዚህ የምትመጣው

የዐ/ህግ ምስክሮች በማለት ነው ይዘውን የመጡት

መንገድ ላይ ነው የነገረህ ማለት ነው አብደላ

ከሰፈራችን አንስተው ወደ ወረዳ ሲያመጡን ነው የነገረኝ

ከዛ በፊት አልነገረህም

ከዛ በፊት የሚያውቀውን ካልሆነ በስተቀር ሌላ አልነገረኝም

እኮ ከዛ በፊት አንተ ምን ታውቅ ነበር

ሰዎቹን ሲያደራጅ ብቻ ነው የማውቀው

ብር አዋጥተናል ብለሃል በለው

አዎ አዋጥተናል

ምን ያህል ብር ነው ያወጣችሁት በአጭሩ እንዲናገር ስንት ብር አወጡ ማስታወስ የሚችል ከሆነ

ስንት ስንት

20 ብር 5 ብር 10 ብር ነው የነው የምናዋጣው

ብሩን የሰበሰበው አብደላ ነው ብለሃል

አዎ

ብሩን ሲሰበስብ ለሀጂ መሀመድ እሰጣለሁ ሲል ነበር ብሎኛል ነው ያልከው እና ይሄንን ብር አብደላ ራሱ ይውሰደው ለሀጂ መሀመድ ይስጠው አንተ የምታውቀው ነገር አለ ወይ

የማውቀው ነገር የለኝም ግን በኦነግ ድምጽ ሬዲዮ አዳምጡ አለን

790

ብሩን ስለመስጠቱ አለመስጠቱ የማውቀው ነገር የለም ነው ያለው

አዎ የማውቀው ነገር የለም ግን እሱ በሬዲዮ ስለምናስተላልፍ በሬዲዮ አዳምጡ አለን

እሺ ጨርሰሃል እናመሰግናለን።

4ኛ ምስክር ማን ላይ ምን እንደሚያስረዳ ጭብጥ አስመዝግቡ

ጭብጥ

4ኛ ምስክራችን 11ኛ ክስ ላይ ነው የሚያስረዳው በ21ኛ ተከሳሽ ላይ

ስንተኛ ክስ

11ኛ ክስ 21ኛ ተከሳሽ ላይ

ምንድን ነው የሚያስረዳው ጭብጥ

የሚያስረዳው ጭብጥ በኦነግ ሴል ውስጥ እንዳደራጀው ተከሳሹ በኦነግ ሴል ውስጥ ለመደራጀት እንደቀሰቀሰው ከዛ በኋላ ሌላ የኦነግ ታጣቂዎችን ሁሉ መንገድ እየመራ ሲወስድም ነበር እሱንም አስገድዶት እንዲወስድ ስላደረገው ነው ተጨማሪው ግን እንደ ክስ አቀራረባችን ያስረዳል

ጭብጡ ግልጽ ነው አህመድ ከሊፍ በከር

4ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አህመድ ከሊፍ

እድሜ - 36

ሥራ -

አድራሻ- ሚደጋ ቶላ ኦሮሚያ ክልል ሚደጋ ቶላ ወረዳ

ዛሬ ለምን መጣህ

ያየከውን ነገር ትመሰክራለህ በማለት ነው ይዘውኝ የመጡት

791

ምን አየህ ማን ላይ ነው የምትመሰክረው

መሀመድ አሊዪ ላይ ትመሰክራለህ በማለት ነው የመጣሁት

መሀመድ አሊዪን ታውቀዋለህ

አዎ አውቀዋለሁ

ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለኝም

------------------ ታውቃለህ

አዎ አውቀዋለሁ

ምን አደረገ ተብሎ ነው አርእስቱን ብቻ ንገረን ዝርዝሩን በዐ/ህግ ስትጠየቅ ትነግረናለህ

በኦነግ ይሰራል በማለት

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

መሀመድ አሊዪ አውቀዋለሁ ብለከናልና ለይልን እስቲ ከዚህ

እስቲ ተነስና ለይተህ አውጣ እሺ እጅህን አውጣ መሀመድ አሊዪ 11ኛ ተከሳሽን ምስክሩ በችሎት ለይቶ አሳይቷል ከብዙ ሰዎች ውስጥ 21ኛ ተከሳሽን አሳይቷል ይቀጥሉ

መሀመድ አሊዪን አሁን ለይተህ ያሳየከው ተከሳሽ ምንድን ነው ያደረገው ምን ነበር እሱ

ሲያደራጅ ነው አብረን እንሰራለን በማለት

በምንድን ነው ያደራጀህ

በኦነግ አደረጃጀት እናደራጃለን በማለት ነው ያደራጀን

አንተን አደራጅቶሃል ማለት ነው

አዎ በዛን ጊዜ አደራጅቶኛል

ከፍተኛው ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ወንጀል ችሎት ቁጥር 4

አደራጅቶህ ምን ምን ሲያደርግ ነበር በኦነግ ሴል ውስጥ አደራጅቶህ አንተን ምን አድርግ ሲል ነበር እሱስ ምን ያደርግ ነበር

እኔ የማውቀው አንድ ቀን ብቻ ሁለት ሰው ሰጥቶኝ እቤቴ አድርስልኝ ብሎ ሰጠኝ እንጂ የማውቀው ነገር የለም

እነዚህ ሁለት ሰዎች ምንድን ናቸው

እኔ ሳያቸው እነሱ ናቸው ብዬ ገመትኩኝ

እነሱ እነማን ናቸው

ስማቸውን አላውቃቸውም

አደለም በአመለካከት ያወካቸው ምንድን ናቸው ብለህ አወካቸው በአመለካከት

ኦነግ በማለት ነው

ምን ይዘዋል

ምንም በእጃቸው የያዙት ነገር የለም

ወዴት ወሰድካቸው

ከአደሬ ወስጄ ወደ ሚደጋ የሱ ቤት ወሰድኩኝ

ከአደሬ አደሬ የት ነው

ሐረር

ከሐረር ወስደህ የት አደረስካቸው

የእሱ ቤት ወሰድኩ

የእሱ ቤት የት ነው ያለው

ሚደጋ ደላ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

የት ዞን ነው የት ወረዳ ነው አደሬ የት ዞን ነው ሚደጋ የት ዞን ነው አንድ ዞን ነው ወይስ የተለያየ ነው አንተ ሹፌር ነህ ስንት ኪሎ ሜትር ነው በኪሎ ሜትርም ቢሆን ንገረን

56 ኪሎ ሜትር ነው ከሐረር የሚርቀው

በኦነግ ተደራጅ ብሎ አደራጀኝ ብለሃል እና ተደራጅተህ ምን አደረግህ እስቲ ያደረግከው አስተዋጽኦ ካለ ምንድን ነው

በመጀመሪያ ጥያቄ ላይ መሪ ጥያቄ አይፈቀድም አሁን አዎ እሺ ነው ምናምን የሚስገኝ ጥያቄ ነው

ምን ምን አደረገ ነው የተባለው እኮ መሪ አይደለም

መሪ ነው እንጂ የተከበረው ፍ/ቤት

ምን ምን አደረገ ጥያቄ ነው እንጂ መልስ ያዘለ አይደለም

------------------------ የሚለው

አልተቀበልንም

እሺ አህመድ መሀመድ ምን እያለ ነበር ሲያደራጅ የነበረው አንተ ያደረከውን ተወውና እሱ ሲል የነበረውን በወቅቱ

እኔ የተለያዩ ኢንፎርሜሽኖችን ለኦነጎች አደርሳለሁ በማለት ነው እየነገረኝ የነበረው

ምን እያለ ከዚህስ ሌላ ምን እያለ ነው እስቲ ንገረን ምን ሁኑ እያለ ነበር እንደዚህ የሚለው

ይዘቱ ምንድን ነው መረጃው

ሌላ ይህ እንዲህ ነው ይህ እንዲህ ነው ብሎ የለየልኝ ነገር የለም ያለውን ኢንፎርሜሽን ወስጄ እሰጣቸዋለሁ በሌላ በኩል ደግሞ የሚሰጡት የሚጠጡት ነገር ካለ እንዲህ እንዲህ ብሎ ያስረዳኝ ነገር የለም

ያደራጀው አንተን ብቻ ነው ወይስ ማን ማንን ነው ያደራጀው

እኔን ብቻ ነው ያደራጀው

አንተ የምን ሹፌር ነህ

የፈረንጆች መኪና ነው የማሽከረክር

የምን

እስራኤሎች ጋ ነው የምሰራው

የውሃ መኪና

በወቅቱ እሺ ይቀጥሉ

እሺ አህመድ እስቲ ከሐረር ወደ የት ነው ያልከን ቦታ ወደ ሚደጋ ወስጃቸዋለሁ ሁለት ሰዎችን ብለሃል ሚደጋ ወደ ማን ጋ ነው የወሰድካቸው

የእሱ ቤት ነው የወሰድኩት

መቼ ነው

ቀኑን አላስታውስም ትንሽ ቆይተናል

ስንት አመት ይሆናል

ሶስት አመት ሁለት አመት በላይ ይሆናል

ምን ወር ነው ክረምት ነው በጋ

በጋ ይሁን ክረምት ይሁን አላስታውስም

ጨረሱ

አዎ ጨረስን

እሺ ጨርሰናል ብለዋል መስቀለኛ ጥያቄ አለ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አንተ መኪና ላይ የምታሳፍራቸውን ሰዎች ሁሉ ይሄ ፖለቲካ ድርጅት ሊሆን ይችላል ብለህ መገመት የሚያስችል እውቀት አለህ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

195

የተሰጠኝ በማለት ነው የገለጽኩት እንጂ እኔ የማውቀው የለም እንደዛ

ሰዎቹ መሳሪያ አልያዙ ምን አልያዙ አሳፈርካቸው

ሰው ነው በአደራ መልክ የሰጠኝ እና የወሰድኩት እኔ ኦነጎች ናቸው በማለት ነው የሰጡኝ ብዬ ነው የገለጽኩት

ኦነጎች ናቸው አድርሳቸው ብሎ ነው ወይ የሰጠህ

አዎ

ድጋሚ ጥያቄ አለ እሺ ድጋሚ ጥያቄ በፊት መስቀለኛ ጥያቄ አልጨረስንም ብለዋል

እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት

መስቀለኛ ጥያቄ ይበቃናል ብለዋል ድጋሚ ጥያቄ አለ

የዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አንተ የውሃ ታንከር መኪና ነው የምጭነው ብለሃል ሌላ ተሳፋሪ ትጭናለህ እንዴ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

ሰዎቹን ወደ ቤቴ አድርስልኝ ያለው ተከሳሹ ወደ ቤቴ አድርስልኝ ብሎ ሁለት ሰዎችን ሰጥቶኝ አድርሻለሁ ብለሃል እና እነዚህ ሁለት ሰዎች መጀመሪያ በዐ/ህግ ስትጠየቅ መስሎኛል ነው ያልከው አሁን ደግሞ የተከሳሽ ጠበቃ ሲጠይቁ ኦነጎች ናቸው ብሎ ተከሳሹ ነግሮኛል ብለሃል እና የትኛው ቃልህ ትክክል ነው እነዚህ ሰዎች በአንተ ግምት ኦነጎች ናቸው ነው ያልከው ወይስ ተከሳሽ ኦነጎች ናቸው ወደ ቤቴ አድርስልኝ ብሎህ ነው

እንዲህ አደራጅቶኝ እንዲህ ሰጠኝ ብዬ መጀመሪያም ተናግሬ ነበር

እነዚህ ወደ ቤቱ የላካቸውን ሰዎች --------------------------- መሰሉኝ የያዙት ነገር በእጃቸው የለም ብለህ ኦነጎች በእኔ ግምት መስሎኛል ነው ያልከው በኋላ ደግሞ ጠበቃውን ሲጠይቁ

796

የተከሳሽ አነጎች ናቸው ወደ ቤቴ አድርስልኝ ብኋል ተከሳሽ ነው ያልከው እና ሁለት ቃል ነው የተናገርከው በእኔ ግምት ነው ማለት እና ተከሳሽ ናቸው ማለት ሁለቱ ስለሚለያዩ ማለት ነው

መጀመሪያም አደራጅቶ ሰጠኝ ነው ያልኩት ቃሌ ይሄ ነው

ኦነግ መሆናቸውን እሱ ነገረህ ወይስ አንተ ኦነግ መሆናቸውን ስለተጠራጠርክ አወቅህ

እሱ ነው የነገረኝ

ጨርሰሃል እናመሰግናለን፡፡ በቅደም ተከተል ነው አደለም የምትሄዱበት

አይደለም

ማን ይጠራ

26ኛ ምስክራችን አብዲ አህመድ ሼካ

26ኛ ምስክር ማን ነው ስሙ ስንተኛ ተከሳሽ ላይ ስንተኛ ክስ ላይ ነው የሚያስረዳላችሁ

የሚያስረዳልን 3ኛ ክስ ላይ ነው

ስንተኛ ተከሳሽ

44ኛ እና 57ኛ ተከሳሾች ላይ

ምንድን ነው የሚያስረዱላችሁ

እንደክሳችን

ምን ፍሬ ነገር ነው የሚያስረዳው ነው

44ኛው ተከሳሽ በፊት ገንዘብ የሚያስተላልፍበት ቦታ ነበር ያኔ ገንዘብ የሚያስተላልፍበት ቦታ የለምና ለኦነግ በቲፋና በኩርፋ በኩል ለኦነግ ገንዘብ አስተላልፍልኝ ብሎ ጠይቆኝ ገንዘብ በዛ አስተላልፌለታለሁ በሚስጥር ለኦነግ እንደሚሰራ ነግሮኛል እኔ አስተላልፍልኝ ብየዋለሁ አሁን እነሱ ያስተላልፉ ነበር የሚለውን ነገር ነው የሚመሰክርልን 57ኛ ተከሳሽን በተመለከተ እንደክሳችን ያስረዳል ነው የምንለው እሱ ያቀረበው ይጠየቅልን ነው

እሺ ጭብጡ ግልጽ ነው ግልጽ አይደለም አልተባለም ምስክሩን ጥሯቸው

ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

26ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አብዲ አህመድ ሼካ

እድሜ - 33

ስራ - ንግድ መደብር

አድራሻ- ቦኬ ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ኦሮሚያ ክልል 4ኛ ዞን

ዛሬ ለምን መጣህ

ምስክር በማለት ነው ይዘው ያመጡኝ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ሀጂ ጣሃ ላይ ነው ልመሰክር ያመጡኝ

ሀጂ ጣሃን ታውቃለህ

አዎ አውቀዋለሁ

ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለኝም

ሌላስ ማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ሌላ የለኝም

ሀጂ ጣሃ ምን አድርጎ እንደተከሰሰ ታውቃለህ ምን አደረገ ተብሎ ነው

አዎ እሱ የተከሰሰበት አውቀዋለሁ

ምን አደረገ ተብሎ ነው

ለኦነጎች ብር አስተላለፈ ተብሎ ነው የተከሰሰው

ማስተላለፉን አንተ ታውቃለህ አታውቅም

778

አውቃለሁ

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ሀጂ ጣሃን በምልክት ትለየዋለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ

እስቲ ከእነዚህ ውስጥ ለይልን

ይኸው እሳቸው ናቸው

እሺ ማን ነው ስሞት ሀጂ ጣሃ ዱምቡሎ ነኝ ብለዋል ምስክሩ 3ኛ ተከሳሽን አሳይቷል

ለኦነግ ገንዘብ ማስተላለፉን አውቃለሁ ብለሃል እንዴት ሊያስተላልፉ ቻሉ

እሱ የነገረኝን ነው የማውቀው

እስኪ ንገረን እሱን

ሀጂ ጣሃ መጥቶ እኔን አነጋግሮኝ ነበር

ምን አነጋገረህ እስቲ ንገረን

መጀመሪያ በጋራሙለታ በኩል ይተላለፍ ነበር አሁን ግን ወደ እኛ ወረዳ ስለመጣህ ብሎ ነው የነገኝ ታስተላልፋለህ በማለት

በጋራሙለታ በኩል ለማን ነው--------------

ለኦነጎች

አሁን በእኛ ወረዳ ያለው በየት ነው የእናንተ ወረዳ

ቦኬ ወረዳ

በምን በኩል አስተላልፋለሁ አለ

እኔ የልጆች አባት ስለሆንኩኝ ማስተላለፍ አልችልም አልኩት ይሄንኑ ነው የማውቀው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

7.99

መቼ ነው

በ19/2001

ወር ታውቃለህ ስንት አመት ይሆነዋል

ወሩን አላስታውስም

እናንተ ወረዳ ልዩ ስም ካለው እስቲ ንገረን ከሚደጋ ውጭ በዚህ በኩል አስተላልፍ የተባለ ልዩ ስም ካለ ንገረን

በዛን ጊዜ ቦኬ ይባላል አሁን ነው የተለያየው እንጂ ሌላ ስም የለውም

የዛን ጊዜ እንደዚህ ብሎ ያነጋገረህ---------------------------

ኩርፋና ቴሴ መሀል እየሄድን ነበር በመኪና

ስንት ብር ነው አስተላለፍ ያለህ

ማለት ነው እንጂ ይሄንን ያህል ብር ብሎ አልነገረኝም

ምን ብሎ ነገረህ ግን በይፋ ነው የነገረህ እንዴት ነው የነገረህ

ሌላ ሊነግረኝ የቻለበት ምክንያት የለም እኔው ብሩን ወስጄ እንዳስተላልፍ ስለፈለገ ነው

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል ብለዋል መስቀለኛ ጥያቄ አለ በተከላካይ ጠበቃ በኩል የምጠይቀው ጥያቄ የለኝም ብሏል ተከሳሹ ግን ጥያቄ አለኝ ብሏል ጠይቁ

ለተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

እኔ ስለ ገንዘብ ስል ማን አጠገባችን ነበር ስለ ገንዘቡ ስነግርህ

ማንም አጠገባችን አልነበረም

እኔ በ2001 ታህሳስ 10 ላይ ተይዤ ስለ ብሩ ተጠይቄ በገመድ ሲሰቅሉኝ ታውቃለህ ወይ ስለ እሱ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

800

አሁን እሱ ስለጠየቀው ነገር ነው ይሄ ተቃውሞውን አልተቀበልንም ጥያቄውንም አልተቀበልንም ሌላ ጥያቄ

ያኔ አብረን የተያዝን ጊዜ ስለ ገንዘቡ ተጠይቂ ስታሰር ስለ እሱ የምታውቀው ነገር አለ ወይ

ድጋሚ ጥያቄ አለ ድጋሚ ጥያቄ የለንም ብለዋል

ለፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

ገንዘቡ ከየት ወዴት ነው አስተላልፍ ያለህ በምንድን ነው የሚተላለፈው በባንክ ነው በእጅ ነው

እኔ የተነገረኝ እሱ እንድታስተላልፍ ብሎ ያለኝ ከየት ይምጣ ከየት ይምጣ እኔ አላውቅም ብሩን ብቻ ሰጥቶኝ እንዳስተላልፍ ነው

በምንድን ነው የምታስተላልፈው አንተ

እኔ በመኪና ስለምሄድ ከላይ ወደ ታች ስለምመጣ በዛው እንዳስተላልፍ ነው

ስንት ብር ነው

ሃሳቡን ነው የነገረኝ እንጂ ይሄንን ያህል ነው ብሎ አልነገረኝም

ከየት የሚመጣ ብር ነው አለህ ለምን የሆነ ብር ነው አለህ ሀሳቡ

ብሩ ከየት እንደሚመጣ አልነገረኝም ብሩ ብቻ ለኦነጎች መሆኑን ነው የነገረኝ

አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቅህ ነበር እንግዲህ በዋና ጥያቄ አልተነሳም በሚል ነው ያቋረጥነው ተከሳሹ እና አንተ ታስረህ ነበር ወይ ከእሱ ጋር ከተከሳሹ ጋር

አዎ አብረን ታስረን ነበር እነሱ ከታሰሩ በኋላ አንድ ሳምንት ታሰርኩኝ እኔ

ከዛ በኋላ ነው ወይስ ከዛ በፊት ነው የታሰርከው

ከነገረኝ በኋላ ነው የታሰርኩት

እሺ ጨርሰሃል እናመሰግናለን። ማን ይምጣላችሁ

39ኛ ምስክር ሀሰን የሱፍ ቱሬ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ስንተኛ ተከሳሾች ላይ

16ኛ እና 19ኛ ተከሳሾች ላይ 40ኛ ክስ

ምንድን ነው የሚያስረዳላችሁ ጭብጥ አስመዝግቡ

ጭብጥ

ለኦነግ አላማ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች ከተከሳሾቹ ቤት ውስጥ መገኘቱን ያስረዳልናል ታዛቢ ሆኖ ተገኝቷል

እሺ ታዛቢ ሆኖ ተገኝቶ ብለዋል ጥሩት ምስክሩን

39ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ሀሰን ዩሱፍ ቱሬ

እድሜ - 38

ሥራ -

አድራሻ- ነገያ ሚደጋ ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነጋ ሚደጋ ቀበሌ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

በማን ላይ ልትመሰክር መጣህ

ዘይኑ እና ሸሪፍ ላይ

ዘይኑ እና ሸሪፍን ታውቃቸዋለህ

ዘይኑን አላውቃትም ሌላ ሰፈር ስለሆነች እሷ በዛን ቀን ባውቃትም አሁን ላውቃት አልችልም

ሸሪፍንስ

ሸሪፍን አውቃለሁ

902

ፀብ ወይ ዝምድና አለህ ከሸሪፍ ጋር

የለኝም

ዘይኑ እና ሸሪፍ ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ

በዛን ጊዜ እንደ ሽማግሌ ሆኜ በመሄድ ነው በቦታው ነው የማውቀው

እኮ ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ ወይ ምንድን ነው የምትመሰክረው

ተይዘው እንደሄዱ አውቃለሁ

ዘይኑን አሁን እዚህ ውስጥ ታሳየናለህ

እኔ ከቀበሌ ነው ወደዛ የሄድኩት እና በዛን ቀን ነው ያየኂት አሁን ላውቃት ግን አልችልም

ሸሪፍንስ

አውቀዋለሁ

አሳየን ሸሪፍ እጅ አውጣ እሺ በቃ ተው እጅህን መልስ ከዚህ መልስ ፈልግ ዙር ወደዚህ ማን ነው ስምህ ሸሪፍ ኡመር ነኝ ብሏል ምስክሩ ከተከሳሾች ውስጥ ሸሪፍ ኡመርን ተከሳሹን ለይቶ አውጥቷል ፀብ ወይ ዝምድና አለህ ከእሱ ጋር

የለኝም

ምን አድርጎ እንደተከሰሰስ ታውቃለህ እሱ ይዞ ሲሄዱ ካልከው ውጪ

የለኝም የማውቀው

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ዘይኑን አንድ ቀን ብቻ ስላየኂት አሁን ለይቼ አላውቃትም ብለሃል አሁን ደግሞ ሸሪፍን ለይተህ አሳይተከናል እንደ ሽማግሌ ሆኜ ተገኝቼ ነው ያየሁት ብለሃል እንደ ሽማግሌ ሆነህ ተገኝተህ በቦታው ላይ ከእነሱ ዘንድ ምን ሲገኝ አየህ

ከፖሊሶች ጋር ነው ቤት ሲፈተሽ አብሬ ሄድኩኝ

ምን አየህ ምን አገኘህ

ሁለት ፍሬ ርሳስና አንድ በፌስታል የተጠቀለለ ባንድራ ይሉታል እሱን ነው ያገኘነው

ርሳስ ምንድን ነው በራስህ አፍ ነው እንዴ የምትነግረን ወደ አማርኛ ተርጉመህ ንገረን

ጥይት

ባንድራው የማን ባንድራ ነው የምን ባንድራ

ትንንሽ ወረቀት ስለሆነች ምን እንደሆነች እውቀትም የለኝም ስለ እሱ

የምን ባንድራ ነው ሲባል ሰማህ

ሌላስ ከማን እቤት ነዉ ይሄ የተገኘው ከማንኛቸው እቤት ነው ከ--- እቤት ነው ከእሷ እቤት ነው

እሷ እቤት የላትም ዘይኑ እቤት ስለሌላት ከአባቷ እቤት ነው የተገኘው

አባቷ ማነው

መዳን አህሚድ

እና አሁን አሁን ያልከን ባንዲራው እና ጥይቱ ተገኘ ያልከን ከማንኛቸው ከ2ቱም እቤት ነው ወይንስ ከማንኛቸው እቤት ነው እሱ አባትም ቢሆን እሷ የምትኖርበት ቤት ስለሆነ በለው

ከአባቷ እቤት ነው የተገኘው

እ ሽሪፍ እቤትስ

ከሽሪፍ እቤት የተገኘው አንድ ክላሽ መሳሪያ እና አንድ ካርታ ቀስላ ይባላል በእነሱ

ካርታ ምንድው ካርታ

እርሳስ የሚቀመጥበት የሉም አዎ እርሳስ ጥይት የሚቀመጥበት አንዷ ካርታ የምትባለዋ እሱ ነው የተገኘው ከእሱ እቤት እና አንድ ክላሽ

804

እሺ ጨርሱ

እሺ አንድ ክላሽ እና ይሄ ተገኘ ይሄንን የተገኘውን ነገር ምን አደረጉት ፖሊሶቹ

ወስደው ነው የሄዱት

መቼ ነው

በእዛው እለት ነው በእዛው ቀን ነው

ወሩን አመተ ምህረቱን ስንት አመት ይሆናል ይሄ ከሆነ

2 አመቱ ወይ ሊሞላ ነው ወይ ሊሞላ አካባቢ ደረሷል

ወር እና ቀን ታወቃለህ የምታውቅ ከሆነ ንገረን በለው

አላውቅም

የት ቦታ ነው የት ሀገር ነው ክልሉ የት ነው በለው

---ሚደጋ ወረዳ ቀበሌው

ዞኑስ

ነጋያ ዞን

የት ክልል ነው አማራ ክልል ነው ትግራይ ክልል ነው

ወደ ፊዲስ አካባቢ ጋለቲ የሚባል ወደ ፊዲስ አካባቢ

ኦሮምያ ክልል ነው

አዎ ኦሮምያ ክልል

እሺ ምእራብ ሐረርጌ ነው ምስራቅ ሐረርጌ ነው የት ነው ይሄ

ምስራቅ ሐረርጌ

ጨርሰናል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

905

እሺ ጨርሰናል ብለዋል

ለመስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ይሄንን የያዛችሁት ይሄ መሳሪያ ፖሊሶቹ አገኙ ይሄንን መሳሪያ ከየት አመጣሁት ተብሎ ተጠየቀ ወይ ሰውዬው

እኛ እያለን በአጠገባችን አልጠየቁም

አልጠየቁትም እሱስ ምን አለ

እቃው የወንድሜ ነው አለ በቃሉ

በቃሉ የወንድሜ ነው አለ

ወንድሙ ማነው

አብዱረዛቅ ኡመር

አብዱረዛቅንም አልጠየቃችሁትም

እኔ አልጠየኩም በበኩሌ

እሺ ይሄ ይብቃን እና ባንዲራ ተገኘ ብለሀል ጨርቅ ነው ስእል ነው

በእጃቸው ነው ያየሁት እንጂ እሷ ወረቀት ነች በወረቀት ነው ያለችው እና ጥልቅ ሆኜ አላየሁትም በደንብ

በወረቀት ላይ የተሳለ

ፖሊሶች የኦነግ ባንዲራ ነው ብለው በእጅ ሲይዙት ነው ያየሁት

ሲይዙት ነው እንጂ ያየከው ከየት ያምጡት ከየት ያምጡት አላየክም

ከእቤት ነው ያን ጊዜ የወሰዱት

አንተ አብረህ ገብተሀል ወይ ሲያነሱ አይተካቸዋል ወይ

አዎ እዛው ቆሜ ነበረ

806

እዛው ቆመህ ነበረ ከምን ላይ አነሱት

ከቦርሳው ውስጥ ነው የወሰዱት

የምን ቦርሳ

የምን ቦርሳ ነው

የልብስ ቦርሳ

ቦርሳ ነው ያለው ምስክሩ

አዎ ሻንጣ

እና ሻንጣና ቦርሳ አንድ ነው

በኦሮምኛ

ምስክረ ያለው ሻንጣ አለ ----

አይ ---

እዚህ ጠረጴዛው ላይ እንዳለው አይነት ነው ወይ ከለሩን አይደለም ግን እንደው ቅርፁ ልክ እንደዚህ አይነት ነው ወይ ያገኙት

እንደዚህ አይደለም

እሺ እንዲህ አይነት አይደለም ብሎ ምስክሩ የመለሰው የቢሮ የሚቀመጥ የ ቢሮ ጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ የባንዲራ መጠንን በማሳየት ነው ይሄንን አይነት አይደለም ነው ብሎ ምስክሩ የመለሰው ችሎት ላይ ያለውን ባንዲራ በማሳየት ነው ችሎት ላይ የሚቀመጥ ሳይዙ ትንሽ የሆነ ማለት ነው ደብተር ወይ መፅሀፍ የሚያክል ይቀጥሉ

እሺ እንደዚህ ትንሽዬ ቁራጭ ጨርቅ ነው ወይንስ በወረቀት ላይ ያለ ነው እስቲ ግለፅ ይሄንን ግልፅ አድርገው በለው እስቲ

እንደ ካርድ ነገር ነች በእጁ ውስጥ ያለችው ያየሁት ካርድ የምትመስል ነገር በእጃቸው ውስጥ ያለች ነው ያየሁት

807

እንደ ካርድ ነገር ያለች ናት

አዎ

እርሶ ባንዲራውን የኦነግ የእገሌ ብለው ያውቁታል ለይተው

ፖሊስ ሲል ነው የሰማሁት እንጂ አላውቅም

ይበቃናል

መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሜ ጥያቄ አለ

የለንም

የለንም ተብሏል

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ከተከሣሾች እቤት ተገኘ የምትለው ክላሽ ጥይት እና የክላሽ ምንድነው ያለው 1ኛው ካርታ

አዎ ካርታ

እሱ በኋላ አንተ ስትሰማ የኦነግ ስለመሆኑ ሰምተሀል ወይ ከእዛ በኋላ ያረጋገጥከው ነገር አለ ወይ በለው

ግልፅ የወጣልኝ የሰማሁት ነገር የለም

እርሶ ሽማግሌ ሆኜ ሄጃለሁ እያሉ ነበረ ሽማግሌ ሆነው ነው ወይንስ ታዛቢ ሆነው ነው የሄዱት

በቀበሌ የነበርን ታጣቂ ነበርን እና በእዛን ጊዜ ነው ከእኛ ጋ ሁኑ ብለው የወሰዱን

ስንት ሰው ነበራችሁ ከእርሶ ጋራ ሌላ ሰው ነበረ ሽማግሌዎች ታዛቢ ሌላ እንደዛ ያወኩት ሰው የለም ሊቀመንበራችን ከእኛ ጋ ነበረ

እሺ ጨርሰዋል

908

ኤው እርሶ ከፖሊሶች ጋ ሲሄዱ ፖሊሶች ምንድነው ያሏቸው ምንድነው የምትታዘቡት ተብሎ ምንድነው የተነገራቸው በፖሊሶቹ

ሌላ በግልፅ የነገሩን ነገር የለም ቤት ልንፈትሽ ስለሆነ ኑ ከአጠገባችን ሁኑ ብለው ነው የጠሩን

የሚፈተሸው ወይንም የተጠረጠረው ነገር ምን እንደሆነ ነው ፖሊስ የነገረህ ላንተ

የለም የነገሩን ነገር የለም

ፖሊሶቹ ለእናንተ መሳሪያ አለ ባንዲራ አለ ኑ እንፈትሽ ነው ያሉት ወይንስ ኑ ዝም ብለን እንፍትሽ ነው ያሉ

የነገሩን ነገር የለም የእናንተ ሰዎች በኋላ እቤት ስንፈትሽ የእኛን እቃ ወረሱ ወይንም ወሰዱ ሊሉን ስለሚችሉ ኑ ከእኛ ጋ ቆማችሁ ታየላችሁ ብለውን ነው የወሰዱን

እዛ ሲፈትሹ በምን የጠርጥረው ነው የጠረጠሩበትን ነገር አልተነገረህም ወይ አልተገለፀልህም ወይ

የለም የነገሩኝ

ቅድም ስትናገር የኦነግ ባንዲራ መሆኑን ፖሊስ ነግሮኛል ብለሀል ብለሀል አይደል

አዎ

ባንዲራው ከተገኘ በፊት ነገረህ ወይንስ ሳይገኝም ነግሮሀል

ከወሰደ በኋላ ባንዲራው የኦነግ ነው ሲል ከአፋ ሰማሁ

አንተ ታጣቂ ነበርክ ወይንስ ሽማግሌ ነበርክ የእዛ

2ቱንም ነኝ

2ቱም ከሆንክ በኦነግ ይጠረጠራሉ እዛ የምንፈትሸው ነገር አለ ብሎ ፖሊስ ቀድሞ ወደ እዛ ስትሄዱ አልነገረህም ምንም ፍንጭ ምንም ነገር አልነገረህም አንተ ታጣቂ ነህ አልነገረህም ወይ ቅድም ደግሞ ነግሮኛልም ስትል ነበረ

የለም የተነገረኝ እኔ በእዛን ጊዜ አዲስ ነኝ እና አልነበርኩም አልነገረኝም አልተነገረኝም

909

እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን

አሁን ደግሞ 50ኛ 62ኛ 44ኛ እና 12ኛ ስላሉ አንድ ጊዜ ቀርበው ቃለ መሀላ ፈፅመው ቢወጡልን

እ

---መጥተዋል

አዎ ከጠኚቱም በመጡት ላይ ቃለ መሀላ ያልፈፀሙት ናቸው የፈፀምት መስክረው ስላለቁ ነው

እሺ

50ኛ

አብዱላሂ ሳኒ

እሺ

62ኛ ኑሪዬ ሀሰን 44ኛ ---

44ኛ

---- 42ኛ ሶፊያ የሱፍ

4 ናቸው

አዎ

62ኛ ማነው አላችሁ

ሶፊያ የሱፍ

62ኛስ

62ኛ ኑሪዬ ሀሰን

እሺ ኑ በእውነት ለመመስከር ቃለ መሀላ ፈፅሙ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

አንድ ላይ

እሺ 50ኛ 62ኛ 44ኛ እና 12ኛ አብዱላሂ ሳኒ ኑሪዬ ሀሰን ሙኒር ሼክ እና ሶፊያ የሱፍ ቃለ መሀላ እንደሚከተለው ፈፅመዋል ይቀጥሉ እሺ እደጅ ቆዩ እሺ ምስክሮቹ ቃለ መሀላ ፈፅመዋል

50ኛ ምስክር አብዱላሂ ሳኒ እንዲገባልን የሚያስረዳውም በ12ኛ

ማን 50ኛ

50ኛ ምስክር አብዱላሂ ሳኒ ይባላል

አዎ

12ኛ ክስ ላይ ከተዘረዘሩት በ12ኛ በ13ኛ በ16ኛ በ17ኛ እና በ18ኛ ተከሣሾች ላይ ነው የሚያስረዳልን

12ኛ 14ኛ

12 13 16 17 እና 18 በእነዚህ ተከሣሾች ላይ ሆኖ የሚያስረዳው የሚያስረዳውም በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እነዚህ ተከሣሾቹ እህል በማስፈጨት ለኦነግ ሰራዊት የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን የሚያውቅ ነው ይሄንን የሚያስረዳልን

ማን ይምጣላችሁ

አብዱላሂ ሳኒ

እሺ ጥሩት

እሺ ቋንቋ ትችላለህ አማርኛ

አልችልም

እሺ በአስተርጓሚ

የዐ/ሕግ 50ኛ ምስክር

ስም - አብዱላሂ ሳኒ ፊሬ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እድሜ - 39

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ነገያ ሚደቃ ቀበሌ ወረዳ ሚደቃ ቶና ወረዳ ምስራቅ ሀረርጌ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

ማን ላይ እነማን ላይ

አብዱራህማን ሁሴን፣ ሰኢኖ መታን፣

እሺ ሌላስ

ሽሪፍ ኡመር

እሺ

አብዲ ሽኩር

ሌላስ

ኢብራሂም መሀመድ

ሌላስ

እነዛው ናቸው

12ኛ 16ኛ 17ኛ እና 18ኛን ጠርቷል ሌላ ደግሞ ማንን ነው የጠራው

13ኛ

ሌላስ

በቃ ሌላ አልቀረም

እሺ አሁን የጠራካቸውን ስማቸውን የነገርከን ታውቃቸዋለህ ፀብ ወይም ዝምድና አለህ ታውቃቸዋለህ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

8/12

ዝምድናም ፀብም የለኝም

ታውቃቸዋለህ

አዎ እዚህ ውስጥ ካሉ አውቃለሁ

እስቲ ልታሳየን ትችላለህ

አዎ

እስቲ ቁም እና ተነስ ተነስ ተነስ ብለህ አስነሳቸው አሁን የጠራካቸውን እሱ የሚያሳያችሁ ተነሱ ማነው ስምሽ --- ሽሪፍ ነኝ ብላለች 13ኛ --- አብዲ ማን

17ኛ

እሺ17ኛ አብዲ ---ነኝ ብሏል አሳይቷል ኢብራሂም መሀመድ ነኝ ብሏል 18ኛን አሳይቷል 12ኛ አብዱራሀማን ሁሴን ነኝ ብሏል 12ኛን አሳይቷል ማነው ስምህ ስንተኛ ነው እሱ እሺ 19ኛን አሳይቷል እሺ 12ኛ 13ኛ 16ኛ 17ኛ 18ኛ እና 19ኛ ተከሣሾችን በችሎት ላይ ምስክሩ አሳይተዋል እሺ ፀብ ወይንም ዝምድና የለኝም ብሏል እሺ ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ አሁን ያሳየከን

እነሱ ለአባዎ ወይንም ለኦነግ እህል ሲያስፈጩ ነው የማውቃቸው

በሰዎች ፊት ለፊት ቆመው ለኦነጐች እህል እናስፈጫለን ሲሉ ነው የማውቃቸው

የምን ሰዎች

ትንሽ እዚህ ጋ የሚረዳኝ ሰው እፈልጋለሁ እዚህ ጋ የሚረዳኝ ሰው ነው የምፈልገው

የት ----የሰማከው ማን ---የሰማከው ይሄ አሁን የተናገርከውን ድገምልን አሁን የተናገርከውን በለው

በሰፊው ህዝብ መካከል በቀበሌ የምክር ቤት አባሎች የህዝብ ተወካዬች መካከል ነው ይሄንን ነገር የነገሩን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ነገሩ ምንድነው የነገሯችሁ

ለገንፎ የሚሆን የተፈጨ እህል ወሰዱላቸው

ለማን ወሰድን አሉህ

ለኦነጎች ነው የሰጠነው

ብለህ ሲናገሩ ሰማሁ ነው ያልከው እሺ ቀጥሉ

እሺ እንደዚህ ሲሉ የሰማከው መቼ ነው

በ99 ዓ/ም ውስጥ ነው

የት ነው የት አካባቢ ነው እንዲህ ያሉት የት ዞን

እሺ ይሄ ያልከው ቦታ ይሄ ሚደጋ ቶላ የሚባለው ወረዳ የት ዞን ነው ያለው የት አካባቢ ነው የትኛው ሀረርጌ ክፍል ነው በለው

ምስራቅ ሀረርጌ ውስጥ ነው የሚገኘው

እሺ ምስራቅ ሀረርጌ እዚህ ቦታ ላይ ለህዝብ ሲናገሩ ሰምቻለሁ ብለሀል

ምን ተብለው ሲጠየቁ ነው እንዲህ ያሉት ምን ለምንድነው ይሄንን ሲሉ የቻሉት ምን ሲባሉ ነው

ጥርጣሬ እኛ አካባቢ ተፈጥሮ ነበረ

የምን ጥርጣሬ ነበር ---

ኦነጎች ነበሩ እዛ አካባቢ ባለንበት አካባቢ የሆነ ወንዝ አካባቢ ኦነጎች ነበሩ እና እንደዚህ አይነት ጥርጣሬ ነበረ ነው

እሺ ስለዚህ ኦነጎች ነበሩ ብለሀል በእዛ ተጠራጥረን ስንጠይቃቸው ነው እነሱ እንደዚህ ---- ብለሀል ምን ምን አይታችሁ ነው ከእዚህ በዘለለ ከሌላው ሰው በተለየ እነሱን ልትጠራጠሩ ልትጠይቁ የቻላችሁት ምን አጊኝታችሁባቸው ነው ምን አይታችሁ ነው

814

ለገንፎ የሚሆን ብዙ እህል ሲያስፈጩ ስላየን ነው የጠረጠርነው

እነማን እነማን ናቸው ለገንፎ የሚሆን እህል ብዙ ሲያስፈጩ ያየከው እነማንን ነው እስቲ እነማ እነማ እቤት ወይንም ደግሞ እነማ እነማ እቤት ይሄ ነገር ሲዘጋጅ አየህ

እነዚህ አሁን የተጠረጡሩት ሰዎች ናቸው

እሺ አሁን ያስነሳካቸው ሰዎች 5ቱ ናቸው

አዎ 5ቱ ናቸው

እሺ ስለዚህ ያንን በርካታ ሲፈጭ አይታችሁ ስለነበረ ጠየቃችሁ እነሱ እንደዛ አሉ እኛ

የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ እኮ የሚለው እነዚህ ሰዎች ፊታቸውን

እሺ ተቃውሞ ነው

እቀበሌ ስብሰባ--- ሰማሁ ነው መነሻው ይሄ ነው መሰረቱ እሱ የሚጠይቃቸው ስለማስፈጨት ሲያስፈጩ አያችሁ ወይ ነው ሲያስፈጩ ስላዩ አይደለም እነሱ ተነስተው እንዲህ እነዲህ አጥፍተናል እንዲህ እንዲህ አድርገናል ብለው ሲናገሩ ሰማሁ

ምስክሩ እንግዲህ ዋና ጥያቄ ተጠይቋል ምስክሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን ነው የሚያስረዳው ከእዛም በተረፈ ለምንድነው ከሌሎቹ የሚለየው በምን ጠረጠራችሁ የሚለው ብዛት ያለው እህል ሲያስፈጩ በእዚህ ምክንያት ጠርጥረን ነው በአካባቢው ኦነግ በወንዙ ውስጥ አለ የሚል ነው ምስክሩ የሚያውቀውንም ከጭብጡም በላይ ሰፋ አድርገው የሚያቁትን ነገር ነው የመሰከሩት ተቃውሞውን አልተቀበልንም

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ይሄንን ሃሳብ የተናገረው የእኛ አካባቢ ጠረፍ ነው ወደ ዳር ስለሆነ እና ወንዝ ውስጥ ኦነጎች አሉ ተብሎ ሲለሚጠረጠር በዛ ስብሰባ ላይ እንዲወጡና እንዲናገሩ ሲናገሩ ሰማሁ የጥርጣሬው መነሻ የአካባቢያችን ወደ ጠረፍ መሆን ነው የሚል ነገር ነው የተናገረው ይሄንን አልተገለጸበትም

የትርጉም ችግር መኖሩ በየጊዜው እሱም እዚህ ላይ አግዘኝ እያለ አስተርጓሚም መቸገሩም ጭምር የተመዘገበ ስለሆነ አቶ ኢብራሂም ስለ ትርጉሙ እናመሰግናለን --------- የሆነ ትርጉም መኖሩን ማሳሰቦትን ያንን ችግር ወደፊት የሚቀረፍ ይሆናል በተቻለ መጠን ትርጉም እንደዚህ

አይነት ነገር ሊኖረው ይችላል ከዛ በተረፈ ግን በዋናነት የቀረበው መቃወሚያ አልተቀበልንም ጥያቄውን ይቀጥሉ

ጨርሰናል፡፡

ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ይጠይቁ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አሁን እነዚህ ሰዎች በስብሰባ ላይ ሲናገሩ ነው የሰማከው ከየት ነው የሰማከው

ስብሰባ ላይ ሲያወሩ ነው የሰማሁት

ስብሰባው ላይ የሚናገሩት ምን ለማግኘት ወይ ምን ለመሆን ነው

ከእነሱ ጋር ያው ስብሰባው ላይ ግምገማ አደርግ ነበር ያንን ግምገማ ላይ ሂሳቸውን ሲያወርዱ ነበር

አውርደውስ ምን ሊያደርጉ

አውርደውስ ይቅርታ ተደረገላቸው ወይ

ህዝቡ ይቅርታ አድርጎላቸው ወደ ስራ ተመልሰዋል ------------ በር ላይ ያዘው እዛ የምንሄድበት ሚኒሻ የተባሉት ሰዎች 5 ሰው

ስንት ሞተ ከእኛ አለ

6 ሰው ከእኛ ሞተ

ኢብራሂም መሀመድ ምንድን ነው ሲል የሰማከው

ተቃውሞ ነው ተቃውሞ ከሌለ ቁጭ ይበሉ መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥሉ

ኢብራሂም መሀመድ ሂስ ሲያወርድ ሰምተሃል ወይ

ሰዎቹን አይቻለሁ ነው እንጂ ያለው እዛ ገንፎ የሚደረግበት ቦታ ላይ ሂሱን አላወረደም

ምኖቹን አይቻለሁ ጠይቀው እንደገና

816

ለምን ትረብሻላችሁ ችግር አለ

እንደዚሁ አብዲ ሽኩር ሲናገር ሰምተከዋል

ስለዚህ

በዚህ ጉዳይ ነው ታስረው የተለቀቁት

ግን ሲናገሩ ሰምተሃል ወይ ስብሰባው ላይ

አብዲ ሽኩር በዚህ ገንፎ በሚደረግበት ቦታ ላይ አንድ ቀን ሳሙና ገዝቶ ሲመጣ ይሄ ጉዳይ ተነግሮታል

አደለም እሱ እንዲህ አድርጌአለሁ ብሎ ሲናገር በጆሮህ ሰምተከዋል ወይ

ቆይ አቶ አድማሱ እርሶ አስቸገሩ እኮ ለምንድን ነው

አብዲ ሽኩር በዛ በገንፎ በሚባለው ነገር ውስጥ የለም

ምኑ ውስጥ ነው ያለው

ሳሙና እገዛለሁ ብሎ በዚህ ምክንያት ነው የታሰረው

የምን ሳሙና ለማን

ለኦነጎች ነው እገዛለሁ ብሎ

ስንት ሳሙና

እንዴት አወቅህ

ታስሮ ሲመለስ ------------------------------- ብሎ ተናገረ ተጣርቶ ነው የተመለስኩት

ጨረሱ

አዎ

8/7

መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ የለንም ብለዋል የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የለም ጨርሰዋል እናመሰግናለን። እንደ ክስ አቀራረባችን ስትሉ ፍሬ ነገሩ ምንድን ነው 5ኛ ክስ ላይ ምን ፍሬ ነገርን ነው የሚያስረዳው ፍሬ ነገሮቹ ብዙ ናቸው በክሱ ላይ ያሉት

62ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ኑሪያ ሀሰን ሙመድ

እድሜ - 30

ስራ - የመንግስት መ/ቤት የወረዳው የሚኒሻ አስተዳደር

አድራሻ- ምስራቅ ሐረርጌ ጎሎዳ ወረዳ ቀበሌ ዳረጋፋ

ሐረርጌ አለህ ስም ነው ለሁሉም ትርጉም አያስፈልገውም እኮ እንሰማለን ሐረርጌ ማለቱን ሰምተናል ትርጉም አያስፈልግም ምእራብ ሐረርጌ ነው ምስራቅ ሐረርጌ ነው

ምስራቅ ሐረርጌ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት ነው ጠርተውኝ የመጣሁት

ማን ላይ ልትመሰክር ነው

ኢብራሂም ደረሴ የሚባል

ታውቀዋለህ

አዎ አውቀዋለሁ

ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለንም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምን አድርጎ እንደተከሰሰ ታውቃለህ

አዎ አውቃለሁ

ምን አድርገዋል ተብሎ ነው

በቀበሌአችን ነበር ከኦነግ ወታደሮች ጋር ነው የሄደው

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ኑሪዬ ኢብራሂም ደሬሳ ላይ ነው የማስረዳው ብለሃል ኢብራሂም ደሬሳ የሚባለውን ታውቀዋለህ ልታሳየን ትችላለህ ከዚህ ውስጥ

አዎ

እስኪ ተነስና አሳየኝ

መልስ እጅህን ፈልጋቸው ከዚህ ወደዛ ፈልግ ማን ነው ስምህ ኢብራሂም ሁሴን ነኝ ብሏል ምስክሩ ኢብራሂም ሁሴንን አሳይቷል ከብዙ ተከሳሾች ውስጥ እሺ ይቀጥሉ

አሁን የለየከው ተከሳሽ ምን ሲያደርግ ነው የምታውቀው

እሱ ተከሳሹ የኦነግ ወታደሮች ወስዶ የሆነች ትንሽ ከተማ ጨቤ የምትባል ትንሽ ከተማ አለች እዛ ላይ ጦርነት ከፈቱብን

ምን ያህል ሰዎችን ነው የኦነግ ሰራዊቶችን ወደ ጨቤ የወሰደው

ሂሳባቸውን ወይ ቁጥራቸው ብዛታቸውን ስንከታተል 120ም 70ም ይባላል

እንዴት ነው 120ም 70 ማለት ቁጥር ትችላለህ በትክክል ቆጥራችኋቸዋል ወይስ በግምት ነው በትክክል ግልጽ አድርገህ እንደዚህ ብለህ አስረዳን ካላወቅህ በግምት ምን ያህል እንደሚሆኑ

በግምት እስከ 75 ድረስ እንገምታለን

እነዚህን ሰራዊት ይዞ ምን አደረገ እዚህ ያልከን ቦታ ምን አደረገ

እኔ በዛን ጊዜ የቀበሌው መዋቅር ነበርኩ በዛ ነው ወታደሮችን ታጣቂዎቹን ይዘው ጦርነት የከፈቱብን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

819

ከማን ጋር ጦርነት ከፈቱ

ከኦነግ ጋር

እነዚህን ቅድም ያልካቸው ተከሳሹ የሚመራቸው ተከሳሹ ይዟቸው የሚመጣው 75 የሚሆኑ የኦነግ ሰራዊት ያልካቸው እማን ላይ ተኩስ ከፈቱ

የቀበሌ አስተዳደርና በእኛ አስተዳደራችን ላይ ነው መጥተው ጦርነት መጥተው የከፈቱብን አዎ ሚኒሻ አልኩኝ

በቀበሌው አስተዳደርና ሚኒሻው ላይ ጦርነት ከፈቱ በጦርነቱ ምን ጉዳት ደረሰ ምን ተከሰተ

አራት ሰው ሞተ

እነማን ሞቱ

ኡስማን ሞዱል፣ ያቆብ አብዱልዋሃብ፣ መሀመድ አሊዪ፣ አሊዪ መሀመድ

እሺ እነዚህ ምን ሆኑ

እኔም ቆስዬ ነበር እነሱ ከእጠገቤ ሞቱ

በምን ምክንያት ነው የሞቱት

ምክንያቱን አላወቅንም እኛ በዛን ጊዜ የህብረተሰቡን የእነሱን እንትን ነው የምናስተላልፈው በዛን ጊዜ ማለት ነው ሰዎቹን እንትን ነው የምናስተላልፈው ሃሳቦችን ማለት ነው እና በዛን ጊዜ መንግስትና ሰዎች መንግስት ከእኛ ላይ ጥል አለው እንደማለት ነው እኔ ሀሳባቸው

ቆይ አልተረዳዳችሁም ጥያቄ አጠያየቅ ሰዎቹ ሞቱ እኔ ቆስያለሁ ብሏል አደለም ምን ሆነህ ቆሰልክ በምን ቆሰልክ በለው እስቲ ምን አቆሰለህ

ኢብራሂምና እሱ ይዟቸው የመጣው ወታደሮች ናቸው ያቆሰሉኝ

እነዛ ወታደሮ እና ኢብራሂም ምንድን ናቸው የመጡት

የማን ወታደሮች ናቸው የመንግስት ወታደሮች ናቸው

የኦነግ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

920

ከዛስ በዚሁ ተፈጸመ ወይስ ሌላ ነገር የተከሰተ አለ

እኔም ቆሰልኩኝ ሌሎቹም ሞቱ የእኛ ጉልበታችን አነስተኛ ስለሆነ በዛው እነሱ ሌላም እቃ ወስደው ሄዱ

ይሄ የሆነው መቼ ነው

በ2000 2ኛው ወር 22 ቀን

ስንት ሰአት ላይ ነው

12፡30

ጠዋት ነው ወደ ማታ ነው

ጠዋት

እነዚህ 75 ያልካቸው ሰዎች ይሄንን የቀበሌው አስተዳደርና ሚኒሻዎቹ ላይ ጦርነት ሲከፍቱ ኢብራሂም የት ነበር ምን ያደርግ ነበር

እሱ የመንገድ መሪ ሰፈሩንም በደንብ እያንዳንዱን ስለሚያውቅ ከእነሱ ጋር ሆኖ እየመራ መጥቶ አብረው ጦርነት ከፈቱብን

ጨርሰናል

ዋና ጥያቄ አብቅቷል ለተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሽ ጠበቃ ይጠይቁ መስቀለኛ ጥያቄ አለ እሺ ተከሳሹ መስቀለኛ ጥያቄ አለኝ ብሏል ማን ነው ስምህ ኢብራሂም ሁሴን ጠይቅ ምንድን ነው ጥያቄህ

የተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ኑሪዬ በዛን ጊዜ አንተ በጦርነቱ ውስጥ ነበርክ ብለሃል እና ያን ጊዜ እኔ እዛ መኖሬን በአይንህ ነው ያየከኝ ወይስ ሰው ነገረህ

ህብረተሰቡ እንዳለ እሱ ነው ያመጣቸው ብለውን ነው የነገሩን በዛን ጊዜ ሳይመቱን በፊትም እሱ ነው መንገድ እያሳየ በሰፈር ውስጥ ያመጣቸው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

በስብሰባ ሰዎችን ሰባስበህ ነው ወይ እኔ እዛ እንዳመጣኋቸው የሰማከው ወይስ ሰው ነው መጥቶ በሚስጥር የነገረህ

ሁሉም ህብረተሰቡ ነው የነገረን ለእኛ

ሌላ ጥያቄ

አንተ በወቅቱ በአይንህ አይተከኛል ወይ

ሁለት ጠላት ጥይት አይን በአይን አይተያይም እና አላየሁክም

ተርጉም አሁን እሱ ያለውን

ትንሽ ስላራዘመው

ማዳመጥ ነዋ ቢያራዝምም እዚሁ አደለም እንዴ ያለከው አዳምጥ ተረጋጋ እና አዳምጥ መስማት ብቻ እኮ እሺ ድገምለት እሺ አቶ ኢብራሂም አሁን ምስክሩ ያለውን በአጭሩ ቢነግሩን

አልሰማሁትም ያለውን

ምንድን ነው ያልከው

የተከሳሹ ጥያቄ ግን በአይንህ አንተ አይተከኛል ወይስ አላየከኝም የሚል ነው

አንተ አይተከኛል ወይስ አላየከኝም ብሎ ሲጠይቅ በአይን በጦርነት አይተያይም ማንም ግን ከሰው ሰማሁ ከብዙ ሰው ሰማሁ አለና ብዙ ሰው ማን እንደሆነ ሲነግር ነበር ከማን ማን ነው የሰማከው ከሌሎች

የነገረኝ ሚኒሻዎች

እሱን አዳምጠው ባክህ የራስህን እውቀት ነው እንዴ የምትነግረን የእሱን እውቀት ንገረን እሱን አትድገመው የተመዘገበው ተመዝግቧል እሱ የተናገረውን አንተ ያልተረጎምከው ፓርት አለ እሱን አስታውሰው ጠይቀውና ተርጉምልን ነው እሱን በአማርኛ ተርጉምልን አሁን ያልከውን

እሱ ማለት ነው ወታደሮቹን ይዞ የእኛ ወታደሮችን ይዞ መጥቶ ስለ ቀበሌ ስለ ሚኒሻ እና ስለ አስተዳደር እየጠየቀ መሆኑን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ማንን እየጠየቀ

ሰፈሩን እየጠየቀ መሆኑን

ማንን የሰፈር ህብረተሰብ የትኛውን ህብረተሰብ ክፍል እየጠየቀ

አህመድ የሬ መሀመድን ጠይቆ ስለ ሚኒሻ ስለ አስተዳደር ስለ ቀበሌ ሁሉ ጠይቆ ነበር እየሄደ የነበረው

ሌላስ ማንን ጠየቀ ልጆች ያልከው

ልጆች ደግሞ ከብት የሚጠብቁት ልጆችንም ጠይቆ ነበር

እሺ ጨርሰሃል ከብቶች የሚጠብቁ ልጆችንም ሰፈር ውስጥ ሲጠይቅ ነበር ሚኒሻና ቀበሌዎች የት ነው ያሉት ብሎ ኢብራሂም ሲጠይቅ ነበር ብሎ ምስክሩ መግለጹን ተተርጉሟል ጨርሰሃል መስቀለኛ አላችሁ መስቀለኛ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄም የለም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም ጨርሰናል ማን ይምጣላችሁ

በ45ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የምታስረዳው የምታስረዳውም ጭብጥ ----------------------

ስንተኛ ምስክር 44ኛ

12ኛ

ስንተኛ ክስ

45ኛ ክስ ላይ

አማርኛ ስለማትሰማ ነው

ዐ/ህግ ማይካችሁ አይሰማም ክፍት ያድርጉና እንደገና ተናገሩ አሁን ያሉትን ተናገሩ አልገባም

12ኛ ምስክር ሳፊያ ዩሱፍ የምታስረዳው በ45ኛ ተከሳሽ አመዲን ኢብራሂም ላይ ነው ክሱም በ35ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰውን ነው ጭብጡ የምታስረዳው በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ ተከሳሹ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በተለይም ደግሞ ገንዘብ በጥሬው ለኦነግ አመራሮች ሲልክ እንደነበር

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

823

ምስክሯ ቋንቋም ስለማይችሉ ጭምር ነው ጭብጡ እዚህ እያሉ የተማው ቴክኒካሊ ብዙም ችግር የለውም

12ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ሳፊያ የሱፍ

እድሜ - 30

ስራ - የቤት እመቤት

አድራሻ - አደሌ 05 ቀበሌ ሐረማያ ወረዳ

ዛሬ ለምን መጣሽ

አቶ ዳይና የሚባለው ላይ ምስክር ለማውጣት

አቶ ማን

አቶ ዳይና

አቶ ዳይናን ታውቂዋለሽ

አዎ

ፀብ ወይንም ዝምድና አለሽ

የለኝም

ምን አድርጐ እንደተከሰሰ ታውቂያለሽ

አላውቅም

እዚህ አለ አውቀዋለሁ ብለሻል ልታሳይን ትችያለሽ

አዎ

ማነው ስምህ አህመዲን አብራሂምን አሳይታለች እሺ ቁጭ በል

824

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ቅድም ሳሳስብ ለችሎት 45ኛ ነበረ ያልኩት በስህተት ነው 4ኛ ነው

እ

45ኛ ተከሣሽ አህመዲን እያልኩ ነበረ የገለፅኩት 4ኛ ተከሣሽ ነው በክስ ቻርጃችን ላይ ያው ግንዛቤ ፍ/ቤቱ እንዲወስድልን ነው

ስለዚህ 4ኛ ነው እሱ

አራተኛ ነው እኔ ሳሳስብ አህመዲን እያልኩኝ ተከሣሹን ነገር ግን 45ኛ ተከሣሽ እያልኩ ነበረ

ይቀጥሉ አሁን ጥያቄ ይቀጥሉ

እሺ ሶፊያ ይሄንን ተከሣሹን ለይተሽ አሳይተሻል ምንድነው የምታውቂው በእሱ ላይ ምንድነው የምታስረጂን እስቲ በላት

እሱ ሾፌር መሆኑን አውቃለሁ

በምንድው እስቲ የተከሰሰው እስቲ ምን ስላደረገ ነው ተከሶ የቀረበው ይሄንን አስቲ ንገሪን በላት

እሱ እዚህ የመጣበትን አላውቅም

ሶፊያ ሾፌር ሆኖ ምን ሲሰራ ነው የምታዉቂው ከሽፍርነቱ ከሾፌርነቱ በተጨማሪ ምን አድርጓል ምንድነው የምታውቂው ፍ/ቤት እንድታስረጂ የተፈለገው ጉዳይ አንቺ የምታውቂው ምንድነው እስቲ

እሺ ይቀጥሉ ዋና ጥያቄ ዐ/ሕግ ይቀጥሉ

አህመዲንን በተመለከተ ፖሊስ ጣቢያ ላይ ቃል ሰጥተሻል ወይ በላት

አዎ

ያንን የሰጠሽውን ቃል እያስታወስሽ ንገሪን

እሺ

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

925

ቀጥይ በላት

ውጪ ተቀምጬ ልብስ እያጠብኩኝ ነበረ የሆነ ሰውዬ የእነ አብዱራህማን ቦኩ ቤት ታውቃለህ ወይ ብሎ መጣ ከመጣ በኋላ ዳይና ይሄን እቃ አስቀምጪልኝ ብሎሻል እና እቃው በፌስታል ነው ያለው በፌስታል ወስጄ አስቀመጥኩኝ ከእዛ በኋላ ትንሽ ከቆየን በኋላ መጥቶ ወሰደ እሱ ያንኑ ነው የማውቀው

ይሄ በፌስታል ምንድነው

እቃው ምንድነው

ውስጡን አላወኩትም

ምን አይነት ነገር ነው እቃው ፈሳሽ ነው ጠጣር ነው ወረቀት ነው ምንድነው

ከፍቼ አላየሁትም ግን እቃው ክብደት አለው ይከብዳል

እሺ ሌላ ጥያቄ

አህመድ ኢብራሂምን በአካል ትለይዋለሽ

አዎ እለየዋለሁ

ዳይና የምትይው ማንን ነው

አህመድን እራሱን እኔ በዳይና ነው የማውቀው

እሺ

ያ በፌስታል የነበረ አስቀምጪ ብሎ አለኝ ያልሽው ነገር በኋላ ምን ሆነ ሲባል ሰማሽ ምንድነው

ብር ነው ሲባል አሉኝ ብር ነው አሉኝ ያ አንቺጋ አስቀምጠው የወሰዱት ነገር እቃው ብር ነው አሉኝ

ማነው ያለሽ

ፖሊሶች ነው ያሉኝ

826

ለምን የሚሆን ገንዘብ ነበረ ብለው አሉሽ ለማን የሚሰጥ ለማን የሚሆን ለምን የሚሆን

ቡርቃ ነው የሄደው ቡርቃ የሚባል አካባቢ ነው ያለው

ቡርቃ ምንድነው

ሀገር ነው

እዛ ምን አለ

እዚህ ነው ያሉኝ ምን እንዳለ ግን አላውቅም ብሩ ወደ ቡርቃ ሄደ ነው ያሉኝ

ቡርቃ ለእነማን ሄደ

እነሱ ናቸው እዚህ ያሉኝ ለማን እንደሄደ ግን አላውቅም

እሺ ያ ፖሊሶች ነገሩኝ ብር ነው ብለው ነገሩኝ ብለሻል ፖሊሶቹ አንቺ ቤት የተቀመጠው በፌስታል ያለው ነገር ብር መሆኑን በምን አውቀው እንዴት አውቀው ነው ለአንቺ ሲነግሩሽ የቻሉት

እሺ ተቃውሞው ምንድነው ተቃውሞ አለኝ ብለዋል የተከሣሽ ጠበቃ

ፖሊሶቹ እንዴት አወቁ እንደዚህ ብለው የጠየቁሽ ይሄ የሞያ ጥያቄ ነው እሷ ፖሊሶቹ የነገሯትን ተናገረች ይሄ የሞያ ጥያቄ ነው ፖሊሶቹ እንዴት ይወቁ እንዴት ይመለሱ

አሳጥሩዋ

ማወቅ ይሄ ከእሷ እውቅና ውጪ ነው

እሺ መልስ ስጡበት ስጡዋ በማይኩ አሳጥሩት

ከእኔ እቤት በላስቲክ እቃ አስቀምጠው ወሰዱ ከእዛ በኋላ ፖሊሶች ያ እቃ ብር መሆኑን ነገሩኝ እያለች ነው ፖሊሶቹ እንዴት ሊያውቁ ቻሉ እያልን እየጠየቅን ነው እሷ ቀጥታ የሞያ ሌላ ባለሞያ ሆና ሳይሆን ፖሊሶቹ እንዴት እንዳወቁ የምታውቅ ከሆነ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንድትነግረን ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

827

እሺ ተቃውሞውን አልተቀበልነውም ምስክሯ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያውቁትን ነው የሚመሰክሩት ---- ሆኖ ይቀራል የሚቁ ከሆነ የሚያውቁትን ነው የሚናገረው እሱ ወደ ፊት የሚመዘን ነው የሚሆነው ምስክሯ ይሄንን ጥያቄ ሲጠየቁ አይገባም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ አግባብነት ሆኖ አላገኘነውም ይጠይቁ ይመልሱ

እሺ ፖሊሶቹ በላስቲክ ውስጥ ያለው እቃ አንቺ እቤት ተቀምጦ የነበረው ብር እንደሆኑ ነገሩኝ ብለሻል ፖሊሶቹ በምን አውቀው ነው ለአንቺ ሊነግሩሽ የቻሉት

አህመዲን ነው ያለን አሉኝ

ለምንድነው ያ ብር ነው ብሎ ለፖሊስ ያላቸው ምን የተደረገ ብር ነው ብሎ ነው ያላቸው አለን ያሉት ብር ነው ብሎ ያ እቃው ምን የተደረገ ብር ነው ብሎ የነገረ---

ከእኔ ቀድመው ነው የጠየቁት አላውቅም

ኤውልሽ ታዲያ ብር ማንም ሰው ይይዛል በላስቲክ ብር ማንም ሰው ቢይዝ ምን ችግር አለው ፖሊሶቹ በወቅቱ ምን ተጠራጥረው ምን ተደረገ ብለው ነው ወደ ቡርቃ ማንም ሰው ብር ሊልክ ይችላል ዛሬ እኔም ተነስቼ ልልክ እችላለሁ ወደ ቡርቃ በምን ምክንያት በምን ተጠርጥሮ ነው ሊያዝ የቻለው የሰማሽው

ለማን የተላከው ወደ ቡርቃ በምን ምክንያት ነው የምታውቂ ከሆነ የማታውቂም ከሆነም ንገሪን በላት

እኔ ብር መሆኑን መጀመሪያ ስላላወኩት አላውቅም

እሺ ጨረሱ

እሺ ይሄ የሆነው መቼ ነው እስቲ ጊዜውን ንገሪን

በግምት 4 አመት 5 አመት ሊሆን ይችላል

እሺ የት ነው ቦታው

አዎ ይሄ የአንቺ እቤት እና ይሄ እቃውን መተው ያስቀመጡበት ቦታው የት አካባቢ ነው የት ነው የሚገኘው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

928

ድሬሳ የሚባል መንገድ ዳር ነው የእኔ እቤት

ጨረሱ

ወደ አንቺ እቤት የዴይና እቃ ነው ብለው ያመጣው ሰው ምን እንደሆነ ምን እንደሚሰራ የምታውቂው ነገር አለ ወይ

አይቼም አላውቅም አንድ ቀን አይቼም አላውቅም ምን እንደሚሰራም አላውቅም

እሺ ፖሊሶቹስ ያንን የተያዘው እቃ ብር ነው ካሉሽ በኋላ በዚህ በዚህ ምክንያት ነው የተጠረጠረው ብለው ሲያወሩም ሆነ ሲናገሩ የሰማሽው ነገር የለም ወይ ቃልስ ስትሰጪ ስለ እዚህ የተጠየቅሽው ነገር የለም ወይ ታውቂያለሽ አታውቂም ወይ ተብሎ

ተጠይቄም አላውቅም ነው አላውቅም አላየሁም አልኳቸው እቃውን

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አለ ዋና ጥያቄ አብቅቷል ብለዋል

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ

ቅድም ለምስክርነት ነው የመጣሁ አልሽን ዳይና ላይ ነው የምመሰክረው አልሽ ዳይና አሳይን ስንልሽ አንድ ሰው አሳይተሽን ያሳየሽን ሰው ደግሞ ስሙን ስንጠይቀው አህመዲን ኢብራሂም ነኝ ብሏል እና አህመዲን ኢብራሂምን እኔ በዳይና ነው የማውቀው አልሽ ዳይና ቅፅል ስሙ ነው ወይንስ በ2ቱም ስሙ ነው የምታውቂው ወይንስ እንዴት ነው የምታዉቂው

እኔ በዳይና ነው የማውቀው

የት ነው የምታውቂው

እሱ ሾፌር ነው

ገራዥ እቤቴ አጠገብ ስላለ ሾፌር ስለሆነ አንዳንዴ ስኮርታ ጉማዎችንም አምጥቶ እዛ እኔ ጋ ያስቀምጣል

የምን መኪና ሾፌር ነው

አይሱዙ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እ

አይሱዙ መኪና ነው የሚያሽከረክረው

እሺ ቅድም በእሱ ላይ በተከሣሹ ላይ ለመመስከር ቃለ መሀላ ፈፅመሻል የምታውቂውን ኤው የምታውቂውን ነገር በትክክል መስክሪ ሀሰት መመስከርም ወንጀል ነው እንደገና በቃለ መሀላ ደግሞ ሀሰት አልመሰክርም ብለሻል የምትውቂውን በተክክል መስክሪ በሀሰት መመስከር ወንጀል ስለሆነ ይሄንን ልናስገነዝብሽ እንወዳለን በላት

እኔ የማውቀው ይሄንኑ ነው

ሌላ የማውቀው የለኝም ነው የምትለው

አዎ

እሺ ጨርሰሻል እናመሰግናለን

ቀጥሎ ማነው የሚሰማላችሁ 62ኛ ነው 44ኛ

44ኛ 62ኛ ተሰምቷል

62ኛ መቼ ተሰማ እሺ 44ኛ ሙኒር ሼክ ስንተኛ ተከሣሽ ላይ ምን ፍሬ ነገር ነው የሚያስረዳው

በ35ኛ ክስ ላይ በ65ኛ እና በ66ኛ ተከሣሾች ላይ ነው እሱ የሚያስረዳው ምንድነው ተከሣሾቹ ጥር 17/2001 ዓ/ም ከጠኋቱ 2:00 ሰአት ላይ በቦሎ --ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ በዐ/ሕግ ክስ ቻርጅ ላይ የጠቀስነውን ድርጊት ፈፅመናል ብለው አምነው ቃላቸውን ሲሰጡ የሰማ የደረጃ ምስክር

65ኛ እና 66ኛ ተከሣሾችን ማለት ነው

እሺ ጥሯቸው

የዐ/ሕግ ቀጣይ ምስክር

ስም - ----ሼክ መሀመድ

እድሜ - 27

930

ስራ - ገበሬ

አድራሻ - ኩንቢ ወረዳ ኩንቢ ጅማ ምስራቅ ሀረርጌ

ዛሬ ለምን መጣህ ለምስክርነት

በማን ላይ

ሰይድ አደም እና ከሊድ መሀመድ ሼካ ላይ

አሁን ያልካቸውን ታውቃቸዋለህ ወይ

አዎ

ልታሳየን ትችላለህ

አዎ አሳያለሁ

እስቲ ተነስ እና ከእዚህ ከተቀመጡት ተነሱ ብለህ አሳየን ከእዚህ

እሺ ስምዎት ማነው

ሰኢድ አደም

ሰኢድ አደም ነኝ ብሏል ከሊፍ ማን ከሊፍ መሀመድ ነኝ ብሏል ምስክሩ ያሳያቸው 2ቱ ተከሣሾች ስማቸው ከላይ የተመዘገበው ነው ፀብ ወይንም ዝምድና አለህ

የለኝም

ምን አድርገው እንተከሰሱ ታውቃለህ

አዎ አውቃለሁ

ምን አደረጉ ተብሎ ነው

በፊት ሰኢድ ላይ ኦነግ ጠርቶን አመካከረኝ አወያየን ኤሌሚኖ ላይ ጠርቶን አወያዩን 2ኛ በሰፈሬ መጥተው ሰፈር ስር ሆነው 2 ሰው ጠራኝ ---

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

831

እሺ ሙኒር እስቲ ተከሣሾቹ ምን እንዳደረጉ ነው ይምታውቀው በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ምን ማድረጋቸውን ነው የምታስረዳው

እነሱ በፖሊስ ላይ የተናገሩትን ነው የማውቀው

ምንድነው የተናገሩት

ጠርተዋቸው እንዲያወያያቸው የተናገሩት

---እስቲ ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ማለት ነው ምንድነው ያወያይዋቸው ምንድነው ያሉት ምንድነው እስቲ የተፈጠረው ነገር የሰማከውስ አንተ ምንድነው

ሰኢድ ነው የተናገርኩት ያለሁኝ ጠርተውን አወያዩን

እሺ ሰኢድን ጠርተው አወያዩት ሰኢድ ምን አለ ሲጠይቁት ምን አለ

ከእዛን ጊዜ ሰኢድ ያስቀመጠው ነገር እኔ የቀበሌው አስተዳደር ነኝ ኦነግ ጠርቶ እኔን ማወያየቱ ጥፋት ነው ብሎ ነው የተናገረው ያንን ነው እኔ ከእሱ የሰማሁት

ኦነግ ጠርቶኝ ምን አደረገኝ ነው ያለው ምን ማድረጉን ነው ጥፋት ነው ብሎ የገለፀው እስቲ ዘርዝረህ አስረዳን ምንድነው በወቅቱ የተረዳከው ያለው

እኔ የአንድ ቀበሌ አስተዳደር ሆኜ ኦነግ እኔን ጠርቶ ማወያየቱ ጥፋት ነው ብሎ ነው

ከኦነግ ከማን ጋ ነው የተወያየሁ ብሎ ያለው ከማን ጋ ነው ---ጥፋት ነው ያለው

ኦብሳ ሌንጮ ከእነ ኦብሳ ሌንጮ ጋ ነው

እነ ኦስሳ ሌንጮ ምን ብለው አወያዩኝ ምን አድርግ አሉኝ ብሎ ነው ጥፋት ነው ብሎ ያለው

እኛም አንነካችሁም እናንተም አትንኩን ስለዚህ ስለ ኑሮ እኛ እንደምንኖር እናንተ ነው የምታስተካክሉልን የምታበጁልን ነው ብሎ ነው ብለን ነው የተወያየነው ነው ያለኝ

እሺ ይሄንን ነው ጥፋት ነው ብሎ ተናገርኩ የሚለው ይሄንን ተጠይቆ የተናገረው የት ቦታ ነው ለማን ነው እንዲህ የተናገረው ጥፋት ነው ከእሱ ጋ መወያየቴ ያለው

በፖሊሶች ላይ ነው ያን ቀን ያን ጊዜ የተናገረው

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

832

ምን ፖሊስ ጣቢያ ነው የት ወረዳ የት አካባቢ የሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ነው

ወረዳው ጉሎዳ ይባላል ሚኖራ ዞን እዛ ነው እንዲህ በሎ የተናገረው ያስቀመጠው

መቼ ነው በ2001 5ኛው ወር በ17ኛ ቀን

ስንት ሰአት ላይ ነው

ጠኋት 2 ሰአት

እሺ ስንት ሰአት ላይ ነው ----

2 ሰአት

እሺ በወቅቱ አንተ ማለት ነው እስቲ ምን ታደርግ ነበረ

እነሱ የሚናገሩትን አዳምጡ ተብለን ተቀምጠን እያዳመጥን ነበር

እሺ እያዳመጣችሁ ነበረ እሱ ይሄንን ሲናገር የነበረው በምን ሁኔታ ላይ ሆኖ ነው ሲጠይቁት በፍቃደኝነት ነው ወይንስ ከእዚህ በተለየ መልኩ ነበረ ሲያሰረዳ የነበረው ምን ነበረበት ያኔ በሚጠይቁበት ሰአት በንግግሩ ወቅት

ምንም እሱ ላይ የደረሰ ነገር የለም

እሺ ጥሩ ከሊፍንስ በሚመለከት ምንድነው የምታወቀው አንተ

ኦነጎች እስከ እቤት ድረስ መጥተው እኔ ጋ መጥተው አንተ የቀበሌው አስተዳደር ነህ ይሄንን ስራ ትተዋለህ ወይንስ አትተውም ነው ያሉኝ ይሄንን ስራ አላቆምም ካልክ ወይ አልተውም ካልክ እኛ አንለቅህም ብለው አሉኝ ነገ ሚኖ ላይ ና አሉኝ

ሚኖ ላይ ምን አለ ማነው ሚኖስ ላይ ና ብሎ የጠራው

እነ ቢሊሳ ናቸው እንደዚህ ያሉኝ

እነ ቢሊሳ ምንድን ናቸው

አባዎ ኦነግ ናቸው

እሺ ከእዛ ና ሲሉት ምን አደረኩ አለ ምን አደረገ

እዛ ቀጠሮ የያዝንልህ ቦታ ና ብለውኝ በማግስቱ ሄድኩኝ ሄጄ ምን አደረኩ አለ

እዛ ጠርተውን አወያዩን

ምን ተብሎ ተወያዩ

ይሄንን ስራ ታቆማለህ ወይንስ አታቆምም ብለው አወያይተውኝ ይሄንን ስራ የማታቆም ከሆነ እኛ ደግሞ አንለቅህም አሉኝ

ከእዛ ተወያይቶ ከመጣ በኋላ ምን አደረገ

እሱ ይሄን ማድረጌ ጥፋት ነው ብሎ ነው ያለው ግን ከእዛ በኋላ የሰራውን ነገር እኔ የሰማሁት ነገር የለም

ሚኖ ሄዶ ከእነ ቅድም ካልካቸው ከኦነግ --- ከተነጋገረ በኋላ እነሱ አትስራ አሉኝ ብሏል ከእዛ በኋላ ምን ሲያደርግ እንደቆየ ነው ሲናገር የነበረው አትስራ ብለውታል ካልተውክ እኛ አንለቅህም ብለው አሉኝ ከእዛ ተመካክሮ ከመጣ በኋላ ምን ወስኖ ምን ሲያደርግ ከረመ ያንን ምን ብሎ ተናገረ

በወቅቱ እሱ ከዲማ እና ከኦብሳ ጋ የተወያዩትን እዛ ውስጥ ተናገረ

ዲማ እና ኦብሳ ማን ናቸው

ኦነጐች ናቸው

እሺ ተነጋግሮ ከመጣ በኋላ ስራ ቀጠለ ወይንስ ስራ ሲሰራ ቆየ

እዛው ነው ያቋረጡት ተያዘ

ከእነሱ ጋ ተነጋግሮ ከመጣ በኋላ አቋርጦ ነው ወይንስ በምን ሁኔታ ነው የተያዘበት

አቋረጠ አለ እኮ

በቃ እሺ ጨርሻለሁ

መስቀለኛ ጥያቄ አለ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቋሚ 4

ከሊፍ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ

የ66ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ቆይ ጥያቄ ካለ ምናልባት እናንተ እንደሌለ ነው ለእሱ እርካታ ነው እንዲጠይቅ ያደረጋችሁት አሁን የእሱ ሃሳብ ከተረዳችሁ በጥያቄ መልክ አድርጋችሁ በአጭሩ ብትጠይቁለት ከዚህ አንቀጽ በፍቃደኝነት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን እንዴት ቃል እንደሰጠ ቁጭ ሲያደርግ ነበር ብሏል ቃሉን አምኗል ብሏል በሱ ዙሪያ ጠየቁት

ተከሳሹ እኔ በወቅቱ በኦነጎች ከፍተኛ የኦነግ ጦር በአካባቢው ላይ ስለነበር በእነዚህ ሰዎች ተይዤ ለመወሰዴና ከዛ በኋላ ደግሞ የመንግስት ጦር መጥቶ ቦታውን ሲያስለቅቅ እኔ በዛው አካባቢ የመንግስት ጦርም እኔን መጥቶ ኦነጎች የት ነው ያሉት በሚል ይዘውኝ እንዳሰሩኝ ታውቃለህ ወይስ አታውቅም አሁን የሚለው ምንድን ነው እኔ አሁን የተናገርኩት ነገር መጀመሪያ በኦነግ ጦር ተይዤ ታስሬ የተደበደብኩ መሆኔ ከዛ ደግሞ የኦነግ ጦር ይሄንን የመንግስት ስራ ትለቃለህ ወይስ አትለቅም ካለቀቅህ አንለቅህም ብለውኝ ዝተውብኝ ከዱላ ከተረፍኩ በኋላ ደግሞ የመንግስት ጦር መጥቶ ደግሞ እንደያዘኝና ይሄንኑ ለፖሊስ ስናገር የነበረ መሆኑን ሰምተሃል ወይስ አልሰማህም በደረጃ ምስክርነት አንተ ተቀምጠህ በነበረበት ጊዜ

ድጋሚ ጥያቄ የለም

ለፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ሙኒር ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ ነበርኩ ስህተቴ ነው ጥፋቴ ነው ብሎ ሲያምን ነበርኩ ብለሃል አደለም ጠይቀው

አዎ ነበርኩኝ ለፖሊስ ሲሰጥ

ምንድን ነው ስህተቴ አለ ምን በመስራቴ ነው የተሳሳትኩት ምን በመስራቴ ነው ጥፋቴ ያለው ጥፋቴ ይሄ ነው ብሎ የተናገረው ምንድን ነው ጥፋቱ እሱ በገለጸው የተረዳከው የሰማከው

እሱ ያስቀመጠው ቀጠሮ ይዞለት እንደመጡለት ነው እሱ ያስቀመጠው

ቀጠሮ ይዤ ከእነሱ ጋር መነጋገሬ ነው ስህተት ብሎ ያስቀመጠው

አዎ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ቁጥር

835

ማን ነው ይሄንን ያለው ከሊፍ ነው ሰኢድ ነው

ከሊፍን ይዘውት ይህንን ስራ መተውና አንተ ነብስህ መገደል የትኛው ይሻልሃል በማለት እንደ ምርጫ ያቀረቡለት ነው እሱ ነው ከሊፍ ትተዋለህ ወይስ አትተውም ስራውን በማለት በዛን ጊዜ ምን ሆነ ብሎት ነው የሄዱት እዛ ነው የሄደው እሱ ያንን ነው እሱ የተናገረው

ስራው ምን ነበር ከሊፍ

የቀበሌ ቡርቃ የሚባል ቀበሌ አስተዳደር ነበር

እኮ አሁን በዛን ጊዜ ስራውን የተወው እንገድልሃለን ስላሉት ነው ወይስ እሱ ደግሞ ከእነሱ ጋር መቀላቀል መተው ፈልጎ ነው ወይስ ምንድን ነው የተረዳከው ከእሱ ቃል ከእሱ ሁኔታ ስትሰማ ተገዶ ነው ወይስ ፈቅዶ መተዉን ነው ያስቀመጠው እሱ በዛን ጊዜ

ጊዜውም አልቆየም አልተራዘመም እሱ እንደዛ ብሎ ኦነጎች ሲይዙት ከመንግስት ወታደሮችም መጡ በዛው ነው እሱም እንዲህ እንዲህ አሉኝ ብሎ የተናገረው

ይሄ ቀጠሮ ተይዞለት ቀጠሮ የተያዘለት ስለመሆኑ ተናግሯል ምን ለማድረግ ነው የተያዘው ቀጠሮ

እሱን ለማነጋገር ነው ከእሱም እንደነገረን ሊያነጋግሩኝ ነው ብሎ ነው

በምን ጉዳይ ነው የሚያነጋግሩት እነማን ናቸው የሚያነጋግሩት

ኦብሳና ዲማ

ምንድን ናቸው ኦብሳና ዲማ

ኦነጎች

ምንድን ነው የሚያነጋግሩት የነበረው

አንተ ነህ ሰዎቹን ህዝቡን ወደ መንግስት ስር ይዘህ የምትሄደው ለምንድን ነው ይሄንን ስራ የማትተወው ብለው ነው ያነጋገሩት

ይሄንን ያነጋገሩት ስለመሆኑ ለፖሊሶች ተናግሯል ወይ በምርመራው ወቅት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጥር

836

እሱ መጀመሪያ ሰዎቹ አነጎቹ ከያዙት ጊዜ ጀምሮ ሁሉንም ዝርዝር ዘርዝሮ አስቀምጦ ነበር

ለማን

ለፖሊሶች ነው ያስቀመጠላቸው እኛም እዛ ሆነን እያዳመጥን ነበር

አሁን አንተ አዳምጫለሁ ብሏል ያዳመጠው አሁን ያልኩህን ነገር ምን ምን እንዳለ ለፖሊሶቹ የነገራቸውን ነገር ምን ምንድን ነው በዝርዝር አስረዳ

እቤት ድረስ መጥተው እሱን መያዙን ከዛ ቦታ ደግሞ እሱን እንደወሰዱት ይሄን ስራ ትተዋለህ ወይስ አትተውም ማለቱን ይሄን ስራ የማትተው ከሆነ ደግሞ እኛ የማንለቅ መሆኑን ሲናገሩት በሚኖ እንዲመጣ ቀጠሮ ሲይዙለት እዛ ወስደው ሲያወያዩት እሱ ያስቀመጠው ይሄንን ነው

ማን ነበር ከአንተ ሌላ የታዘዘ ይሄንን

አንድ ሰው ነው

ማን ነው አሁን መጥቷል ወይ

አልመጣም

ማን ነው ስሙ አለ

ኑሮ በከር አራርሳ

ማጣሪያ ጥያቄ አብቅቷል እናመሰግናለን ዐ/ህግ የምትሉት ነገር ካለ ምስክሮች ጠዋት የገለጻችሁትን አሰማችሁ መሰለኝ

አላሰማንም እስከ አሁን ያሰማነው ምስክር 8 ብቻ ነው

አዎ 8 ተሰምቷል

አሁን ግን 10 አካባቢ ምስክሮች አሉን

እየመጡ ወይስ የመጡ

እዚህ አሉ አሁን ያሉ

837

እዚህ አሉ

እዚህ አሉ አዎ ስለዚህ ተከሳሾች ምሳ መብላት ያለባቸው ይመስለኛል እና ከምሳ በኋላ ብንቀጥል ነው የሚሻለው

እሺ ትዕዛዝ ተሰጥቷል

ት ዕ ዛ ዝ

አሁን ሰዓት እንግዲህ ለ7 ሩብ ጉዳይ ነው ከሰዓት በኋላ እንቀጥላለን የተቀሩት 8፡30 እናድርገው የምሳ ሰዓት ስላራዘምንባቸው ቅድሚያ ለእነሱ አድርሱና ከዛ በኋላ እሺ 9፡00 ሰኣት ከሰዓት በኋላ ቀሪ ምስክሮች ለመስማት ለ9፡00 ሰኣት ተቀጥሯል፡፡

ማ/ተ

እሺ ከሰአት በኋላ

በወመ/ቁጥር - 04486

ቀን - ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ/ም

ዳኞች - ብርሀነመስቀል ወጋሪ

- **ይርጋ አይቼህ**
- **እልፍነሽ ወሌሮ**

ከሣሽ - ዐ/ሕግ ሀረጋይ እንደሻው እና ማሙሸት አበበ ቀርበዋል

ተከሣሾች - ያው ጠኋት የቀረቡት እነ አብዱራህማን ባሌ ቀርበዋል

ቀሪ ምስክሮችን ለመስማት ነው ምስክሮች መጥተዋል ከሰአት ማን ማን ነው ቀሪ ምስክሮቻችሁ እሺ አሁን ከአሁን በኋላ ---የምታሰሙት

እሺ እየመጡ እሺ ጥሯቸው ቃለ መሀላ ያልፈፀሙ አሉ

ጠኋት የገለፃችሁ አሉ 32 33 34 35 የሚል አለ 68 86 ---- እሺ ከሰአት በኋላ ቃለ መሀላ ያልፈፀማችሁ ምስክሮች ስማችሁ ማን ነው

አብዲ አዩ

ቃለ መሀላ ፈፅሙ ስማችሁን እየተናገራችሁ አስመዝግባቸው ስማቸውን 4 ናቸው አይደል ስምህን ስምህን በለው እና 4ቱንም --

አብዲ ----

ወይ አንተ አላስመዘገብክ ወይ እሱን አላስደረግህ እኮ አየር ላይ ሆነ እኮ

----ዩ ሚካ---

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እሺ

አብዱላሂ አመዴ

እሺ

ታጅር የሱፍ ሰቡር ጅንዳ

እሺ በእውነት ለመመስከር ቃለ መሀላ ፈፅሙ ምስክሮቹ ቃለ መሀላ ፈፅመዋል እሺ እደጅ ውጡ ማነው ሚቀርላችሁ

አብዲ --

አብዲ አዩብ ስንተኛ ነው

67ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ነው

እሺ ስንተኛ ክስ ላይ ስንተኛ ተከሣሾ ላይ ነው ምን የሚያስረዳው

በ23ኛ ተከሣሽ ላይ 43ኛን ክስ ማለት ነው

እንደ ክሱ ነው አይደል ጭብጡ የተለየ ነገር አለ

አዎ ---

የተለየ ነገር ካለ አስመዝግቡ እንደ ክሱ ካላችሁ ምስክሩን እንቀጥል ጊዜ እንትን አትበሉ

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አብዲ አዩብ ሚካይ

እድሜ - 38

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ኮንቦልቻ ወረዳ ቀበሌ - ቁሬንሳ ማሬ ሰፈር

ዛሬ ለምን መጣህ

አብዲ አሊ ላይ ለመመስከር ነው የመጣሁት

አብዲ አሊን ታውቀዋለህ ታውቃለህ አታውቅም አብዲን ታውቀዋለህ አታውቅም

ፊቱን አይቼ አላውቀውም ያለኝን ነው የማውቀው

እሺ አብዲ አሊ ምን አድርጐ እንደተከሰሰ ታውቃለህ አርእስቱን ብቻ ንገረን ዝርዝሩን በዐ/ሕግ ስትጠየቅ ትነግረናለህ በለው

የአባ ገዳ ኮሌጅ እንደሚማር እና ስሙ አብዲ አሊ እንደሆነ ነው የነገረኝ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እሺ አብዲ አዩብ ይሄ አብዲ አሊ የተባለው እስቲ ከሰዎቹ መሀል ብታየው አታውቀውም ልትለየው አትችልም

መብራት እያለ መብራት አጥፍተው በጭለማ ሆነው ነው ያናገሩኝ

እሺ ጥሩ ስለዚህ ልትለየው አትችልም ማለት ነው

አዎ ----

እሺ ይሄ የማትለየው አብዲ አሊ ይባላል ያልከው ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው እስቲ አሁን ---ምናምን ያልከው ምንድው የተፈጠረው ምንድነው የሆነው

መብራት እያለ ድንጉ ሻማ ማለት ነው አበሩ 6 ወታደሮች ነበሩ

የምን ወታደሮች ነበሩ

የኦነግ ወታደሮች ነበሩ

እሺ ከእዛ ምን አደረጉ

እኛ ኦነጐች ነን የኦሮምያ ነፃነት ባንድሮች ነን እነሱ እንደዛ ሲሉን

ኤውልህ በደንብ አድርገህ --- ቦታ ላይ በደንብ አድርገህ ጠይቀው እና ሌላ ሰው እንዲያግዝህ እንደ ቅድሙ አድርገህ ተናገር ወታደሮቹ የማነው አልከን በለው

841

የኦነጐች

እሺ ቀጥሉ

እሺ ምንድነው ያደረጉት የኦነግ ወታደሮች ምን አደረጉ ከእዛ በኋላ

የሆነ ወሬ አወሩ

ምን ብለው አወሯችሁ ምን

እሺ ምን እያሉ ነበረ ሲሰበስቧችሁ የነበረው ምን እያሉ ነበረ ወታደሮቹ ሲያነጋግሯችሁ የነበረው

አንድ ምሽት ብቻ ነው የተገናኘነው

የዛን ምሽት የተገናኛችሁ እለት ያሉህን ነው እኛም የምንፈልገው

እኛ የኦነጐች ወታደሮች ነን እና የሆነ ባንዲራ አሳይተውን ይሄ ባንዲራ ደግሞ የኦነጐች ባንዲራ ነው ለወደፊት ብር አሰባስበን ለእነሱ ለኦነግ ወታደሮች እናደርጋለን እንደገናም ደርሞ ይሄንን መንግስት ደግሞ እንገለብጣለን በማለት ነው የነገሩን

---እናደርጋለን ነው ያለው

አዎ

ኤውልህ --መንግስት እንገለብጣለን አሉ እነዛ ሰዎች ነው እያለ ያለው ለሌላ ሰዎች ታዋጣላችሁ ----ስለዚህ ለሌላ ሰው ማዋጣት እና ለእነዛ ሰዎች ማዋጣት የተለያየ ነው እና እያዳመጥክ -----

ይሄን መንግስት እንድንገለብጥ እና መዋጮ እንድናዋጣ ነው

ለማን ነው የምታዋጡት ለማን እንድታዋጡ ነው

ለኦነግ ድርጅት መዋጮ እንድናዋጣ

እሺ እነዚህ 6 ሰዎች የኦነግ ሰራዊት ናቸው ብለህል ይሄ አብዲ አሊ ያልከውስ ምን ነበረ ከእነሱ ጋ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

የኦነግ አባል እና የአባ ገዳ ኮሌጅ ተማሪ ነኝ

እሺ ይሄ የሆነው ማለት ነው መቼ ነው ጊዜው መቼ ነው ጊዜው ወሩ እና አመተ ምህረቱን ታስታውሰዋለህ ወይ

98 ዓ/ም ነበረ ህዳር

ቀኑን ታስታውሳለህ ወይ

ቀኑን አላውቀውም

ስንት ሰአት ላይ ነው ሰአቱስ

4፡00 ሰአት

4፡00 ሰአት ጠዋት ነው ወይንስ ማታ

ከምሽቱ 4፡00 ሰአት

እንደዛ ብለው ካነጋገሯችሁ በኋላ እናንተ ያደረጋችሁላቸው ነገር አለ ወይ

ምንም ነገር ያደረግንላቸው ነገር የለም ጥለን ነው የሄድነው

ጨርሰናል

እሺ የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ አለ

ለመስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ኤው ይሄ አብዲ አሊ የምትለው መልኩንም አላየከውም ስራው በትክክል ምንም እንደሆነም አታውቅም

ታውቃለህ አታውቅም

መብራት እያለ አጥፍተውት ነው ስሙን ሲጠሩ የሰማሁት ነው ኩራዝ አበሩ ነው ፊቱን አይቼ መልኩን አይቼ አለየሁትም

ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

8413

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሜ ጥያቄ አለ

የለንም

እሹ ድጋሜ ጥያቄ የለንም ብለዋል

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

የኦነግ አባል መሆኑን እንዴ አወቅህ አብዲን

መጨረሻ ላይ እኔ የኦነጐች አባል ነኝ የአባ ገዳ ኮሌጅ ነው የምማረው አለ

መቼ

በ1998 ህዳር ወር ውስጥ

እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ አብቅቷል ጨርሰሀል እናመሰግናለን እሺ ቀጥሎ ስንተኛ ነው የምታሰሙት

ስንተኛ ተከሣሽ ላይ

በ27ኛ እና 35ኛ ላይ

----

15 16 እና 17

እሺ 60ኛ ምስክር ሙሉ ስምዎትን

60ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ታጅር ዩሱፍ --

እድሜ - 29

ስራ - አርሶ አደር ገበሬ

8214

አድራሻ - ጨለንቆ ቀበሌ - 01 የቤት ቁጥር - የለውም

ዛሬ ለምን መጣህ እ ምን አልክ አብራሂም መሀመድ አብዶ አይ እሱ ያለውን ነው ---

አዱኛ መሀመድ ጅብሮ

እሺ

አብራሂም መሀመድ አብዶ

ኢብራሂም አህመድ አብዶ እና አዱኛ ላይ ታውቃቸዋለህ አሁን ያልካቸውን

አዎ አውቃቸዋለሁ

ፀብ ወይንም ዝምድና አለህ

የለኝም

አሁን ያልካቸውን ሰዎች እዚህ ቢኖሩ ልታሳየን ትችላለህ

ተነሱ በላቸው እስቲ ዞረህ እያቸው እና --ተከሣሽን አሳይቷል ማነው ስምህ ኢብራሂም አህመድን 27ኛ ተከሣሽን ምስክሩ ከሌሎች ተከሣሾች ውስጥ አሳይቷል 27ኛ እና 35 ተከሣሾችን ለይቷል እሺ ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ አርእስቱን ብቻ ንገረን እና በዝርዝር ስትጠየቅ ትመልሳለህ

ተማሪዎችን በመበጥበጥ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ኢብራሂም እስቲ ኢብራሂም አህመድ ምንድነው ያደረገው

በ1998 እሱ ተከሣሹ ማለት ነው ተማሪዎችን ፊት ለፊታቸው እየሄደ ብጥብጥ እንዲያነሱ የመራ የነበረ ነው

ምን እያለ ነው የሚያነሳሳቸው --ስለምንድነው የሚነግራቸው

ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጡ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐ... የፌ.ዴ.ራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

845

ኢብራሂም አህመድ ምንድነው

እሱ ተማሪ ነው በሰፈሩ አስተዳደርም አንተ አድብ ስለው አንተ እራስህ አድብ ብሎ ከእሱ ጋ እንትን ሲሉ የማውቀው

ስለማን እና ስለምን ነበረ የሚቀሰቅሰው በወቅቱ እንዲነሳሱ የሚያደርገው ስለምንድነው በለው የምን አባል ነው

በእዛን ጊዜ በጣም እረብሻ ነበረ በትምህርት ቤት ውስጥ ከእዘ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ አባዎ አባ ቢያ አባዎ አባ ቢያ ኦነግ የሀገር አባት ኦነግ የሀገር አባት እያሉ ይፎክሩ ነበረ

እስ ስለ ኦነግ ምን እያለ ነበረ የሚነግራቸው

እሱ የሚነግራቸውን እኔ አላውቅም እሱ ከአስተዳደሩ ጋ ሲፎካከር --------

ሲፎካከር ነው መፎክር ነው ያሰማው

አንተ ሲፎካከር ትላለህ እሱ ሲፎክር ይላል

ከአስተዳደሩ ጋ

እ

ተማሪዎቹ እየፎከሩ ነበረ

አይ እሱ ያለውን

---ሳይሆን መፎክር ያሰሙ ነበረ አልክ አንተ እሱ ምን አለ

መጀመሪያ አስተዳደሩ መጥቶ ተማሪዎችን ለማወያየት ሰብስቦ ነበረ እሱ ደግሞ ተከሣሹ አንተ እራስህ ቁጭ በል ነው ያለው

እሺ ከእዛስ ምን ሆነ

ከእዛ ተማሪዎቹ ተሰብስበው ወጡ እና እየጨፈሩ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ድንጋይ እየወረወሩ ነበረ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

846

ምን ላይ ነው ድንጋይ የወረወሩት

ፖሊስ ላይም ድንጋይ ---2ኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ሄደው ድንጋይ ወርውረው --- እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችንም በድንጋይ አባረው አወጧቸው

ከእዛ ት/ቤት እና አሁን ፖሊስ ጋ ከሄዱ በኂላ ያደረጉት ነገር ነበረ ወይ

በወቅቱ ተማሪዎቹ ባንዲራውንም አውርደው አቃጥለው ነበረ

የማንን ባንዲራ ነው

የመንግስቱን ባንዲራ ነው የፌደራል ባንዲራ

የፌደራል የሚል ቋንቋ እየሰማን ነው አሁን የፌደራል እና የምን ቋንቋ እያለ ነው አይደለ እንዴ

አዎ --

እንደዛው አትተረጉምም ታዲያ

እሺ የኦሮሚያ እና የፌደራል ባንዲራዎችን አውርዶ አቃጥሏል

ታዲያ አትናገርም እንደዛ ብለህ

እሺ ሌላስ ያደረገው ነገር ነበረ ወይ በወቅቱ

በቃ ሌላ ያየሁት ነገር የለም ከልጆች ጋራ እየተሯሯጡ ድንጋይ ሲወረውሩ ነበረ

እሺ አዱኛ መሀመድስ ምንድነው ያደረገችው

እኔ በወቅቱ እሷን እዛ አላየኂትም ከእዛ በኂላ ከፖሊሶች ጋ የእሷ እቤት ስንሄድ ልጆችን እያወያየች ነው በማለት ጠቁመዋልት ከፖሊሶች ጋ ስንሄድ

ስለምንድነው የምታወያየው

በወቅቱ ልጆች የምታወያዩት የለም እሷ እና አብራሂም ሆነው አንድ ላይ ሺሻ ሲያጨሱ ነበሩ

እሷን በተመለከተ ከእዚህ በፊት የሰማከው ምንድነው

847

ከአሁን በፊት እንደሰማሁት እሷ በውትድርና ውስጥ እንደነበረች ነው የሰማሁት

በየትኛው ወታደር

ከኦነጎች ጋ ሄዳ ነበረ ሲባል ሰማሁ

ታዲያ ወታደር ከነበረች መቼ ነው የመጣችው

እኔ መቼ እንደመጣች አላውቅም ግን በ97 ነው ከእሷ ጋ የተዋወኩት

ቅድም እቤቷ ልጆችን እየሰበሰበች ታወያያለች ብለህል አሁን ደግሞ ከኦነግ ወታደር ሆና ስታገለግል ነበረ ብለህል ከእዚህ አኳያ የሰማከው ምንድነው ስለምን ነበረ የምታወያያቸው

እንደ ኢንፎርሜሽን እሷ እና ያኛው ተከሣሽ አብረው ቁጭ ብለው ነበረ እቤት ውስጥ እኛ የሰማነው እሱን ብቻ ነው ያየነው ሌላ የማውቀው የለም

እሺ አንተ የፀጥታ ዘርፍ ሰራተኛ ነህ ከእዚህ በፊት እና ያን ጊዜ ስራ በምትሰራበት ጊዜ ከእነሱ ጋ ታወያያለች ተብሎ ስለምን ስለተወያየች ነው ልትይዟቸው እና ቤታቸው ልትሄድ የቻልከው በለው

ከእኛ በፊት ያሉት እነሱ ናቸው ይሄንን ኢንፎርሜሽን አጊኝተናል በማለት ወደ እሷ የላኩን

መረጃው ምንድነው አገኘን ያሉት የሰማከው

ልጆች ልጆቹ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጡ ነው የምታወያያቸው ከእዛን በኋላ ነው ልጆቹ አባዎ የሀገር አባት እያሉ ሲፎክሩ የነበረው

አባዎ እሱ በኦሮምኛ ነገረህ አባዎ አሀገር አባት አባዎ ማን እንደሆነ

ኦነግ የሀገር አባት

እሺ አሉ

አዎ

ሌላስ

848

በወቅቱ ከእቤቷ ሰዎች ተያዙ ብኋል ሲወያዩ እነማን ናቸው እስቲ የምታውቃቸው ከእቤቷ የተያዙ ሰዎች እነማን ናቸው

ስንት ይሆናሉ ብዛታቸ

2 ሰው ነው 3 ሰው ነው ያየሁ 2ቱን አውቃቸዋለሁ 2ቱን አንድ አብራሂም እና የሆነ ልጅ ደግሞ አውቃቸዋለሁ

እዚህ አሉ አሁን

የሉም

ጨረሳችሁ

ይሄ ቦታው የት ነበረ ጊዜውስ መቼ ነው በለው እስቲ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡት መቼ ነው የት --ነው ዞኑ የት ነው

ሜታ ወረዳ

እሺ መቼ ነበረ ጊዜው

6ኛው ወር 1998

እህ

98

ስንቴ ነበረ እረብሻ የተካሄደው

2 ጊዜ እኔ በእርግጥ የያዝኩት 2 ጊዜ ነው አንድ ጊዜ በ1998 6ኛው ወር በ18 ቀን አንደኛው ደግሞ 7ኛው ወር ላይ ቀን 15 በ1998

ይሄ አንተ በትክክል የምታስታውሰው ነው [illegible] ቀኑን የማታስታውሰው አለ ወይ

እኔ ገጠር ውስጥ ሄድኩኝ ሌላ ቀኑን የማላስታውሰው ት/ቤት እና ፖሊስ ላይ እረብሻ የተካሄደበት ይኖራል 2 ወር አንድ ጊዜ ወረቀት ይለጥፋሉ

እህ

በቃ እረብሻ ውስጥ ነው ያሳለፍነው 2 ወር ከእዛ በኂላ አብራሂም ጠፍቶ ነበረ ከእዛም በኂላ ተይዞ ወደ ሀገር ተመለሰ

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ጠይቁ የተከሣሾች ጠበቃ

የተከሣሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አሁን አንተ ልጆችን ታማክራለች ተብላችሁ ተነግሯችሁ እሷ እቤት ሄዳችሁ እሷ እቤት ስትሄዱ ሺሻ ሲያጨሱ አገኛቹሀቸው ከእዛ ውጪ ምን አገኛችሁ

እኔ በወቅቱ እሷ ጋ አብረው የተቀመጡ ልጆች እንጂ ሌላ ያየሁት የሰማሁት የለም እሷን ይዘን ወደ ፖሊስ አምጥተን መስጠታችንን ነው የማውቀው

ይሄ የሆነው ከሰላማዊ ሰልፉ በፊት ነው ከሰላማዊ ሰልፉ በኂላ

ሰልፍ ሳይወጡ በፊት ነው ሰላማዊ ሰልፍ ሳይወጡ በፊት

የታሰረችው ከእዛ በፊት ነዋ

ተጠርታ በፖሊስ ተለቃ ነበረ ጠርተው አጣርተው ለቀቋት ከእዛ በኂላ

አጣርተው ነው ያለው ወይንስ መርምረው ነው ያለው አጣርተው ነው ያልከው አንተ ደግሞ

ይለያያሉ አጣርተው ለቀቋት እና መርምረው ለቀቋት በጣም ብዙ ልዩነት አለው እባክህ በአግባቡ አስተርጉም

ጠርተው መርምረው ለቀቋት

እሷ ተማሪ ናት

እሷ ተማሪ አይደለችም እሷ ልትያዝ የቻለችው እሷ ታወያያለች እና ልጆቹም እሲ እቤት ስለሄዱ ነው እሷ የተያዘችው

ምንድነው የምታወያየው ስታወያይ ሰምተሀል ወይ አወያየችው የተባለውን ነገር አውቀሀል ወይ ስለምንድነው ውይይቱ እሷ ያወያየችው አርእስት ጉዳይ ስለምን እንደሆነ ተረድተካል ወይ አውቀሀል ወይ ምንድነው የሰማከው ወይ ያወኩውን

ከእዛም በኂላ ስለ እሷ ነገር ጥናት ያደረጉት ወይንም ደግሞ

ጠይቀው እሱ ጋ እኮ አለ እሱ አይደለም ቃሉ የእሱ እኮ አይደለም እንደገና ጠይቀው እና እሱ ያዳምጥ አንተ ካላዳመጥክ

ፖሊሶች እና ማለት ኬዙን የመረመሩት ሰዎች እንደተናገሩት ነው የሚለው እሷ ነች የምታወያየው

ውይይቱ አርእስቱ ጉዳዩ ምንድነው ታወያያለች 10 ጊዜ ተናግረሀል በለው ስለምንድነው የምታወያየው ይዘቱ የውይይቱ ይዘት ምን ነበረ

ከሰዎቹ እንዳጣራሁት አባዎ ማለት ኦነገር የአገሪቷ አባት ብለው ተነሳስተው እንትን እንዲሉ እሷ ነበረች የምታነሳሳው ይሄንን ነው የማውቀው ነው

እንዴት አወክ ማነሳሳቷን

ያጣሩ ሰዎች ነው የነገሩኝ ያጣሩት ሰዎች ነው ሲያወሩ የሰማሁት ---የነገሩኝ ነው የሚለው

እኼቱ ናቸው ያጣሩ የምትላቸው

ፖሊሶቹ እና የአስተዳደሩ የፀጥታ ጉዳይ እነሱ ሲያወሩ ነው የሰማሁት

እንጂ ሌላ ሰው አልነገረህም ከእሷም አልሰማህም

ከእሷም አልሰማሁም ከሌሎች ሰዎችም አልሰማሁም

እነዚህ ቤት አገኟቸው እቤቷ ውስጥ አገኟቸው የምትለው ሰዎች ዘመዶቿ ይሁን ለእዚህ ጉዳይ የሄዱ ይሁኑ በምን ታውቃለህ

ትምህርት ቤት ውስጥ አብራሂም የሚባለውን ነው እንደ በአንደኛ ደረጃ እዛ ያየሁት እሷ እቤት ከአስተዳደሮች ጋ እሱ ሲነጋገር አይቼዋለሁ ነው እና አስተዳደሮቹ እዛ ሲያወሩ እና ሲነጋገሩ ነው የሰማኋቸው ነው የሚለው

የስጋ ዝምድና አላቸው ወይ

እኔ አላውቅም ይሄንን

በእዚሁ ጉዳይ በ1998 ዓ/ም እረብሻ ሲያደርግ ነበር ወይንም አይቼው ነበረ ብለህለ በእዚሁ ጉዳይ ፍ/ቤት ተከሶ ስለመቅረቡ እና የተወሰነበት ስለመሆኑስ ታውቃለህ ወይ

እሺ የ7ኛ ተከሣሽ ጠበቃ ከላይ የተጠየቀውን ጥያቄ አቅርበዋል ዐ/ሕግ በቀረበው ጥያቄ ላይ እንቃወማለን ብለዋል

ተቃውሟችን ምንድነው መስቀለኛ ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው በዋና ጥያቄዎች በተነሱ ጉዳዮች ላይ ነው ስለመታሰሩ ስለመዳኘቱ በእዚህ ነገር የተነሳ የለም ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ሊጠየቅብን አይገባም ውድቅ ሊሆን ይገባል

እሺ እንግዲህ የቀረበው መቃወሚያ ላይ ብይን ተሰጥቷል ታስሮ ነፃ ከወጣ ያው የክስ መቃወሚያ ነው የሚመጣው ይሄ ከሆነ ማስረጃውን ማቅረብ እና የሚፀና ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ምንጊዜም ሊቀርብ ይችላል የሚፀና ፍርድ የማያሰጥ ከሆነ ይሄ አሁን ያቀረባችሁትን ጥያቄ አልተቀበልነውም ሌላ ጥያቄ ይቀጥሉ

አንተ የደህንነት አካል ነኝ ብለህል በ1998 ዓ/ም ላጠፋው ጥፋት ይሄ አሁን የተያዘው ወይንም ተከሣሹ የታሰረው 2001 ነው የደህንነት አካል ከሆንክ ለምን እስከ ዛሬ ድረስ ዝም አልከው ለምን ተጠያቂ እንዲሆን አላደረክም

ጥያቄው ምን ነበረ እንደገና ንገሩን በደንብ አልተሰማም

ተከሣሹ በእንትን ላይ

እኛ መጀመሪያ ተቃውሞ አለን እሱ ያለው ምንድነው

--ጥያቄው እራሱ አልገባንም ---

አይደለም አሁን ተለውጧል ጥያቄው እኮ ተለወጠ ቅድም ሌላ ነበረ

ከተለወጠ ---

ተከሣሹ 1998 ዓ/ም በእረብሻው ላይ አይቼዋለሁ ብለሀል ተከሣሹ አሁን ተይዞ የታሰረው በ2001 ዓ/ም ነው አንተ የደህንነት አካል ነኝ ብለሀል እስከ እዛን ጊዜ ድረስ ይሄ ተከሣሽ የደህንነት አካል ከሆንክ እንዴት ዝም አልከው

ከእዛ በፊት እረብሻው ሲነሳ እሱ ጥሎ ሄደ ከእዛን በኋላ ፖሊሱ ሲመለስ አንድ አንድ ነገር አልቆምም ሲል እሱ እያነሳሳ ነው በማለት ተያዘ እሱ እያነሳሳ ነው በማለት ተይዞ ነበረ ቀኑን አላስታውስም ከእዛ ከእረብሻው ወዲህ መለስ ስንል ነው

ጨረሱ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሜ ጥያቄ አለ

ድጋሜ ጥያቄ የለንም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ኢብራሂም መሀመድ አመፁን ሲመራ ነበረ ብለሀል የት ቦታ ላይ ነው አመፁን ሲመራ የነበረው ተማሪዎቹ --- ሲመራ የነበረው የት ላይ ነው የት ቦታ ሆኖ ነው

ጨለንቆ

ጨለንቆ ት/ቤት ነው ወይንስ ቀበሌ ላይ ነው ወይንስ ምን ላይ ነው

ከትምህርት ቤት ጀምሮ ከተማ ውስጥ

ተማሪዎቹን ምን እንዲሉ ነው አመፅ ሲያነሳሳ የነበረው

ተማሪዎቹን

ተማሪዎቹ ምን እንዲሉ ነው አመፅ ሲያነሳሳ የነበረው

መንግስት ላይ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጡ

ምን በማለት

አባዎ አባ ቢያ አባዎ አባ ቢያ ኦነግ የሀገር አባት ኦነግ የሀገር አባት እያሉ ከተማ ውስጥ እየረበሹ ድንጋይ እየተወራወሩ ነበር

እሺ ማጣሪያ ጥያቄ ጨርሰናል

ፌዴራላዊ ጠ/ፍ/ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ቁጥር 4

ቀጥሎ ማንን ነው ---እሺ ስንተኛ

በስንተኛ ክስ እነማን ላይ

እሺ ተከሣሾቹ እነማን ናቸው 27 እና 35 ላይ

አዎ

እሺ 65ኛ ምስክር በ27ኛ እና በ25ኛ ተከሣሾች ላይ በክስ 15 16 እና 17 ላይ ያለውን ነው የሚያስረዳልን ብለዋል 61ኛ ምስክር ሙሉ ስምህን

61ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ሰቡር ጅንዳ ኡስማኤል አሊሾ

እድሜ - 30

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ጨለንቆ ቀበሌ - 01 የቤት ቁጥር - የለውም

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

በእነማን ጉዳይ ላይ

አብራሂም አብዶ እና አዱኛ ምሀመድ ጂብሮ

ታውቃቸዋለህ ልታሳየን ትችላለህ

አዎን

አሳየን

እሺ 27ኛ ተከሣሽን ምስክሩ አሳይቷል እሺ አዱኛ አህመድን እና ኢብራሂም አህመድን አውቃቸዋለሁ ብሎ አሳይቷል ፀብ ወይም ዝምድና አለህ

የለኝም

ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ

አዎን

ምን አደረጉ ተብሎ ነው

ከኦነጉች ወታደሮች ጋ ዘምተሀል በማለት ነው

ማን

አዱኛ

ሌላውስ

እሱ ተማሪዎችን መሪ በመሆን በማደራጀት መሪ ሆኖ ማደራጀቱን ነው የማውቀው

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ሰቡሬ ኢብራሂም ተማሪዎችን ምን አድርጐ ነው ያደራጃቸው

እኛ ሰላም ለማስጠበቅ እየሄድን ነበረ እሱ ነው ተማሪዎቹን ያደራጀው እና መሪ የሆነው ሲባል ነው የሰማነው

ምን እያደረገ ነው የሚያደራጃቸው ስለምንድን ነው

ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተን በኦነጐች እንደራጃለን በማለት ነው ሲመራቸው የነበረው

እስቲ ምንድነው ያደረጉት በወቅቱ እንደዛ ካደረጉ በኋላ ካደራጃቸው በኋላ ምን አደረጋቸው

በተነገረን ጊዜ በ1998 6ኛው ወር ቀን 18 በሀይስኩል ተማሪዎች እየተማሩ እያለ ትምህርት ትተው መውጣታቸውን ተሰባስበን በነበርንበት ቦታ ተማሪዎቹ ትምህርት ጥለው ወጥተዋል በማለት ጠሩን እኛ እዛ እንሄድ ሁሉም ተማሪዎች ወጥተዋል አስተዳደሮቹም ወጥተው ከፊታቸው ቁጭ ብለው ነበረ ከወንዙም እኛ በኢንፎርሜሽን እሱ ነው የሚመራቸው ብለን

855

እንደሰማነው እንደተነገረን ከእነሱ ፊት ሆኖ አስተዳደሮቹን እየተናገረ የነበውም እሱ ነው እናንተ ወታደሮች ማንም ሰው እንዳትገቡ እኛን አሉን አስተዳደሩ እንደዛ ብሎን ወደ ኋላ እንድንመለስ አደረገን ከእዛን በኋላ አስተዳደሮቹ ከእነሱ ጋ ቁጭ ብለው ውይይት ካደረጉ በኋላ ከእዛን በኋላ ተማሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ ሆነው ወጥተው ተሰባስበው ወደ እኛ መጡ እኛ መንገድ ለቀቅንላቸው እና እነሱ እስከ መሀል ድረስ ወደ ከተማ ወጥተው እየሄዱ እያለ ከእነሱ ስር የቀሩ ሰዎች ለምንድነው ከእኛ ስር የምትቀሩ ብለው በድንጋይ እነሱን መምታት ጀመሩ ከእዛን በኋላ ፖሊስ እና ሰላም ጠባቂዎች እነሱ ድንጋይ ሲጀምሩ በሰላም ሂዱ እና ግቡ ብለን አበታተናቸው

ምን እያሉ ነበረ ያን ጊዜ የሚሄዱት

ኦነግ እያሉ ነው የሚሄዱት

ኦነግ ምን ሆነ ነው የሚሉት

ምን እንደሆነ አላውቅም አባዎ ኦነግ ኦነግ እያሉ ነው የሚሄዱት

ወጡ ብለሀል መስተዳደሮቹንም ከእነሱ ተወያይተው ነው ከእዛ በኋላ የወጡት ከወጡ በኋላ ምን እያሉ ነበረ የሚፎክሩት አባዎ ምን ሆነ ነው አባዎ ምን ሆነ ነው የሚሉት የሰማከውን አስታውስ

በእዛን ጊዜ እንዲህ ኢፋ ወጥቶ የገባኝ ነገር የለም ከተማው ሁሉ ነው ተነስቶ አባዎ አባዎ ኦነግ ኦነግ እያለ የሚሄደው

ወዴት ነበረ የሄዱት ከእዛ በኋላ

እነሱ ድንጋይ ከእነሱ በኋላ የቀሩትን ሰዎች በድንጋይ መምታት ሲጀምሩ ፖሊሶች እና ሰላም ጠባቂዎቹ አበታተናቸው በሰላም እንዲገቡ

ወደ ሌላ መ/ቤት አልሄዱም ወይ

በእዛን ወቅት አልሄዱም በእዛን እለት አልሄዱም

መቼ ነው የሄዱት

856

በ1998 7ኛው ወር 15ኛ ቀን

ሄደው ምን አደረጉ

ጉልማሳ የሚባል ትምህርት ቤት ሄዱ ከእዛ ተነቅለው እንደገና ገደሉን ተሻግረው ከእዛ በኋላ እ

ገደሉን ተሻግረው

የትምህርት ቤት ስም እየጠቀሰ አይደል

ነገርኩት እኮ ትምህርት ቤቱን

ጉርማሳ የሚባል ትምህርት

ከጉርማሳ የሚባል ትምህርት ቤት ተነስቶ እስከ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሄዱ በድንጋይ ትምህርት ላይ ያሉትን ተማሪዎች እናንተስ ምን ትማራላችሁ ተነሱ በማለት በድንጋይ ቆርቆሮውን እየመቱ ከዛም ተማሪዎቹም አንድ ላይ ሆኑ እዛ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን ባንድራ አውርደው በር ላይ አምጥተው አቃጠሉ

የማንን ባንድራ የምን ባንድራ ነው

የኦሮሚያ ባንድራና የፌደራል ባንድራ

በወቅቱ ተከሳሽ የት ነበር

እኛ በወቅቱ እሱ ያለፈውን ስላየንበት እየፈለግነው ነበር የሁለት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብዙ ሆነው እየሄዱ ስለሆነ እሱን አላየነውም

ከየት ትምህርት ቤት በመጀመሪያ የተነሱት

በቅድሚያ የጀመረው ሀይስኩል ነው

የት የሚገኘው ሀይስኩል ነው

የጨለንቆ ከተማ ሀይስኩል

857

ስንት ቀን ነበር ረብሻው እንደዚህ

ሁለት ቀን ሶስት ቀን ነው የቆየው

እስቲ ስለ አዱኛ የምታውቀውን ደግሞ ንገረን

አዱኛ ከወታደሮች ጋር መሄዷን ሰምቻለሁ

ከምን ወታደር ጋር

የኦነግ ወታደሮች ጋር ከዛን በኋላ ወደ አገር ተመለሰች እንደሰማሁኝ ደግሞ ከትጥቅ ጋር ነው የተያዘችው ታስራ ከዛ ወጣች ሱቅ ከፍታ እየሸጠች ነበር እነዚህ እረብሻ ውስጥ የነበሩ ልጆችን ትደብቃለች የሚባል ስሰማ በጊዜው የአስተዳደሩ ግምገማ ተነስቶ ነበር ከዛ ወደ እሷ ላኩን ጠዋት ሄደን ከቤቷ ጠራናት አስተዳደሩ አቅርቡ ባለን ቦታ አቀረብናት ከዛን በኋላ አጣርቶ ምርመራ አድርገው ከዛን በኋላ እንዴት እንደለቀቁ ከዛን በኋላ ምርመራ ካደረጉ በኋላ ለቀቋት ይሄንኑ ነው ስለ እሷ የማውቀው

ኢብራሂምና የአዱኛ ግንኙነት ምንድን ነው

አንድ ቀን ልጆች ረብሻ የሚያደርጉትን ልጆች እዛ ትደብቃለች እንደዛ የሚል ኢንፎርሜሽን ደርሶን እሷ ጋር ስንሄድ እዛ ሆኖ እየቃመ ነበር በወቅቱ ምሽት ስለነበር ፖሊስ ከአጠገባችን ስለሌለ ሄደን ማውጣት አንችልም አልን

ሌላስ ማን ነበር በወቅቱ

እኛ እና ታጣቂዎች አብረን ነበርን ይሄንኑ ነው እኔ የማውቀው

ቅድም ተማሪዎች ሲወጡ ኦነግ ኦነግ እያሉ ነበር አንተ የፀጥታ ሰራተኛ ነህ ኦነግ ኦነግ የሚሉት ኦነግን በመደገፍ ነው ወይስ በማግለል ነው

ለኦነግ ያላቸውን ውዴታ እየገለፁ ነው የሚሉት

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል።

ዋና ጥያቄ አብቅቷል

868

ለተከሳሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

አዱኛ የኦነግ ወታደር ነች ብለሃል በስንት አመተ ምህረት ነው መቼ ነው ተከትላ ሄዳለች ሲባል ሰምቻለሁ ብለሃል

እሷ የኦነጎች ወታደሮች ጋር የሄደችበትን ወር አላስታውስም

አመቱስ

አመቱንም አላውቀውም

ምን ያህል አመት ይሆነዋል በግምት እሷ የኦነግ ሰራዊት የነበረችበት ጊዜ እና ተያዘች የተባለች ጊዜ ምን ያህል ጊዜ ነው አሁን አንተ ምስክር ሆነህ መጥተሃል ትላንትና ነው መቼ ነው ነው አመቱን ጊዜውን ንገረን

በጣም ስለቆየ ወቅቱ ሩቅ ስለሆነ ስለቆየ አሁን ረስቼ ሳይሆን አይቀርም

ምን ያህል አመት ነው ሀምሳ አመት ነው አምስት አመት ነው አንድ አመት ነው ተናገር

እገልጻለሁ ካልኩኝ እዋሻለሁ

ሳትዋሽ መግለጽ አትችልም ወይ በግምት

በአእምሮዬ ውስጥ ካለ ነው በግምት ልናገር የምችለው በአእምሮዬ ውስጥ ስለሌለ ልዋሽ እችላለሁ

አእምሮህ ውስጥ የለም ወይስ አታስታውስም

ረስቼዋለሁ

ሌላ ጥያቄ

በወታደር ውስጥ መሆኗን ወይም ደግሞ የሰማከውን ነው የተናገርከው

በወቅቱ ሄድኩኝና አለችኝ ሄጀ ታግዬ ተሀድሶ አዎ እሷን ለመያዝ ስንሄድ ሄጀ ትግሉ ላይ ተሀድሶ ወስጄ ታግዬ መጣሁኝ ብላ አለችኝ

ተሀድሶ ማን ነው ተሀድሶ የሰጠ ለማን ነው የተሰጠው መቼ ነው ተሀድሶ የተሰጠው አለች

እኔም በወቅቱ ጠለቅ ብዬ እንትን አላልኩም እሷ ነች አሳጥራ እንደዛ ያለችው

አንተ ነህ ያልካት ወይስ እሷ ነች በፍላጎቷ የነገረችህ

ከዛም ሄደች ተጠራች ጨርሰሽ የለም ወይ ብዬ እኔ ኢንፎርሜሽን ስጠይቃት ነው እሷ የነገረችኝ

ተሀድሶ የተሰጠኝ ያለችህ መቼ ነው

አስተዳደሩ ጥራት ባለን ጊዜ ልንጠራት ስንሄድ ነው ያለችኝ

መቼ ስለተሰጣት ተሀድሶ ነው ስትናገር የነበረችው ማን ነው ተሀድሶውን የሰጣት

ስጠይቃት ነው የነገረችኝ ማን እንደሰጣት አልነገረችኝም

አንተ በወቅቱ ተሀድሶ ሲሰጥ ለነበሩት ሰዎች የምታውቀው ነገር አለ ወይ እና ያንን ጊዜ በግምት መቼ ይመስልሃል ስለ ተሀድሶ የምታውቀው ነገር አለ ወይ እና ያ ተሀድሶ ይሰጣል በሚባልበት ጊዜ ደግሞ መቼ ነው

ስለ ተሀድሶ የማውቀው ነገር የለኝም

ሌላ ጥያቄ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ ካለ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

ለፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ለማን ነው አዱኛ ታግዬ የመጣሁት ተሀድሶ ወሰድኩኝ ያለችው ለማን ነው ታግላ የመጣችው

በወቅቱ እኔ ስጠይቃት ለወቅቱ ሄጄ ነበር እኔም ከዛ በፊት ውስጡን ጠለቅ ብዬ ስለማውቀው

ምንድን ነው የምታውቀው

ከኦነጎች ጋር ሄዳ መመለሷን

ስለማውቅ

960

ጩርሰሽ እንደሆነ አስተዳደሩ አሁንም ስለሚፈልግሽ ስለሚጠራሽ ሄደሽ ተመርምረሽ ምርመራሽን ጨርሰሽ ትመለሺያለሽ አልኳት ይሄንኑ ነው

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ አብቅቷል ቀጣይ ምስክር ማን ነው ጨርሰሃል እናመሰግናለን። ከሰአት ያልነበሩ እንደገና መጥተዋል እያሱ መኮንን 0/ህግ መጥተዋል ቀሪ ምስክሮች ቃለ መሀላ እንዲፈጽሙ ጠይቀዋል እንግዲህ አሁን ከሰኣት በኂላ ነው ይሄንን ሁሉ ሳንሰማ እንችላለን መምረጥ እንደየ ማደር ወይም ማደር የማይችሉትን እያደረጋችሁ ብትለዩ ለራሳችሁ ቃለ መሀላ ፈጽሙ ስማቸውን እያስመዘገብክ ቃለ መሀላ አስፈጽማቸው 6 ምስክሮች ቀርበዋል ሲራጅ መሀመድ፣ ከዝና ሀሰን ሰዲቅ፣ ጋረው ---------- ሙዴ፣ መሀዲ መሀመድ አብዱላ አማን መሀመድ ሁሴን፣ ከድራ ሙስጠፋ መሀመድ፣

በእውነት ለመመስከር ቃለ መሀላ ፈጽሙ ስማቸው ከላይ የተመዘገበው ነው

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ቃል እንገባለን

ማን ይሰማላችሁ

እሺ አቶ እያሱ ጭብጥ አስመዝግቡ

ጭብጥ

34ኛ እና 35ኛ ምስክሮቻችን የሚያስረዱት አንድ ጭብጥ ስለሆነ በአንድነት አስይዘዋለሁኝ የሚመሰክሩልን ነገር ምንድን ነው 62ኛ፣ 65ኛ፣ 66ኛ፣ እና 68ኛ ተከሳሾች ላይ ነው የሚመሰክሩት

ስንተኛ ክስ

35ኛ እና 36ኛ ክስ የሚመሰክሩት ጭብጥ ምንድን ነው 62ኛ ተከሳሽ መሀመድ አብዱልጀባር የተባለው ሲናገር የሰሙትን ነው 65ኛ፣ 66ኛ ተከሳሾች ጋር ሆኖ ከመንግስት የመጋዘን በቆሎ ውስጥ 12 ኩንታል ወይም 12 ጣቃ በቆሎ አውጥቶ ለኦነግ ሰጥተናል ያለውን ነገር ይህን ነገር ሲናገር የሰሙ መሆናቸውን 68ኛ ተከሳሽ ደግሞ አንድ መኪና አስቁሞ 5 ሰዎች ገድለን አቃጠልን ዘረፍን የሚለውን ነገር ሲናገር የሰሙ መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው ሁለቱ ምስክሮቻችን

861

አንድ መኪና አቁመው

አምስት ሰዎች ገድለው ያቃጠሉና የዘረፉ መሆኑን

ክሱ ላያ ያለው ነው

ክሱም ላይ አለ እነሱ የሚያስረዱትን ነገር አውጥተን እያሳየን ነው

ማን ቀድሞ ይሰማላችሁ

ካዝና ሀሰን ትጠራ 34ኛ ምስክር

34ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ካዝና ሀሰን

እድሜ - 45

ሥራ - የቤት እመቤት

አድራሻ- ቡርቃ ከተማ ጎሎውዳ ወረዳ ምስራቅ ሐረርጌ

ዛሬ ለምን መጣሽ

ለምስክርነት

ማን ላይ

መሀመድ አጆባ የሚባል

ታውቂዋለሽ መሀመድ አጆባን

አላውቀውም አይቼ አላውቅም ታዛቢ ነኝ

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልሽ

ከመሀመድ አብዱጆባ ውጪ ከእሱ ውጪ ሌሎች ላይ የምትመሰክሪው ካሉ ስማቸውን ንገሪን

አብደላ መሀመድ ሀማ

ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

862

ሴላስ

ሴላ መሀመድ አብረን ነበርን ያለው ነው እንጂ ሌሎቹን አላውቅም

እሱን ስማቸውን ንገሪን

ሰኢድ አደም እና ከሊፍ መሀመድ ሼካ

አሁን ከጠቀስሻቸው ሰዎች ውስጥ በአይን በአካል የምታውቂው ማንን ነው

በወቅቱ እኔ እነሱን በዛን ጊዜ በወቅቱ ነው ያየኋቸው እንጂ ስማቸውን ድምጽ ሲሰጡ ነው የማውቃቸው እንጂ ከዛ በፊት አላውቃቸውም

አሁን የዛን ጊዜ ቃል ሲሰጡ አይቻለሁ እያልሽ ነው እና አሁን ብታያቸው ታስታውሻቸዋለሽ

ስለቆየ አሁን አላውቅም

አታስታውሺም

አላስታውስም

እስቲ በመልክ ለማስታወስ ይከብደኛል ብለሻል --- ምን ብሎ ሲናገር ሰምተሻል

በሚኖ ቀበሌ ውስጥ እኔ ሊቀመንበር ነኝ ሰኢድ መሀመድም ሊቀመንበር ኢጀጎዳ ሊቀመንበር ከሊፍም የኩርፋ የሮቃ ቀበሌ ሊቀመንበር ነበር

አብደላ መሀመድስ ምን ሲናገር ነው የሰማሽው

አብደላ የሚሄደውን የአስተዳደር መኪና ከኦነግ ሰዎች ጋር ሆነን መኪናውን መተን መኪናውን አቃጥለን አምስት ሰው ከውስጡ ገደልን

መሀመድ አብዱጀባል ምን ብሎ ሲናገር ሰማሽ

እኔ እና ሰኢድ አደም ከሊፍ መሀመድ አብረን ሆነን ተወያይተን እህልን ከአዳራሽ አውጥተን 12 ኩንታል አውጥተን ለኦነግ ሰዎች ሰጠን ብሎ ሲናገር ሰማሁ

ከሊፍና ---------------- ሊቀመንበር ብላለችና የት የት

ኢጀጎዳ ሰኢድ አደም የኢጀጎዳ ቀበሌ ሊቀመንበር ነበር ከሲፍ መሀመድ ደግሞ የሮቃ ቀበሌ ሊቀመንበር ነበር አብረን ሆነን ከመጋዘን እህል አውጥተን 12 ሉቃ በቆሎ ሰጥተናል ለኦነግ ብሎ ሲናገር ሰማሁ ባለ 50 ኪሎ

እሺ ሉቃ ባለ 50 ኪሎ ኪስ መሆኑን ምስክሯ ገልጻለች እሺ ቀጥሉ

አብደላ መሀመድስ

አብደላ መሀመድ ደግሞ

አብደላ መሀመድ ምን ብሎ ሲናገር ሰማሽ

አብደላ መሀመድ ደግሞ ሲናገር የሰማሁት ወደ ሚኖ የሚበሩ መኪና የአስተዳደር መኪና ከኦነጎች ጋር ሆነን መኪናውን አቃጥለን 5 ሰው በውስጡ ገድለናል ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ

መቼ ነው እንደዛ ሲናገሩ የሰማሽው

በ2000 ዓ/ም

ወሩን ታውቂዋለሽ

ወሩን ላውቀው አልችልም

ቀኑንስ

ቀኑን አላውቀውም ሰዓቱን ግን በ8፡00 ሰኣት ነው

የት አገር ነው የት ቦታ

ቡርቃ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ

እንዴት ነው ቃሉን ሲሰጥ በምን ሁኔታ ነው ተገዶ ነው ወይስ

አይ ግዴታ የለም በፍላጎቱ ነው የተናገረው ማለት ነው

ጨርሻለሁ፡፡

ዋና ጥያቄ አብቅቷል

ለተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ማን ነበረ ስምሽ ካዝና እነኚህ ሰዎች አላውቃቸውም ወይም አላስታውሳቸውም ብለሻል ቃላቸውን ሲሰጡ ፖሊስ ላይ ነው የሰማሽው

አዎ

እሹ ፖሊስ እስቲ እንዴት እንደጠራሽ እና ከአንቺ በፊት እነሱነበሩ እዛ ቦታ ላይ ወይንስ አንቺ ነሽ መጀመሪያ የመጣሽው ፖሊሶች ጋ

አይ እኔ እንኳን ለጉዳይ ለሌላ ጉዳይ መጣሁ እንደመጣሁ ገባሁኝ እና ያው የእራሴን ጉዳይ ከፈፀምኩ በኋላ እስቲ ቆይ የሆኑ ሰዎችን ቃል እንቀበላለን እና ታዛቢ ትሆኛናለሽ ብለው ተቀመጥኩኝ

ፖሊሶች ገልፀውልሻል ይሄንን

አዎ

እሺ

እና በቃ ቁጭ ብለን

ከየት መጡ ከየት መጡ ሰዎቹ

ከእስር ቤት ከእዛው

እስር ቤት አለ እዛ

አዎ ፖሊስ ጣቢያ እስር ቤት አለ

እሺ

ከእዛ አንድ በአንድ ተጠርተው አንድ በአንድ ገብተው ድምፃቸውን ሱሰጡ ሰማሁ ማለት ነው

እዛ ቁጭ ብለሽ ነበረ

አዎ እዛው ቁጭ ብዬ ነበረ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

እዛ ያ የሰሙት የሰጡት ቃል ተመልሶ ለእነዚህ ሰዎች ተነቦላቸዋል

አዎ

ተነቦላቸውስ ፈርመዋል

ተነቦላቸዋል

ፈርመዋል እራሳቸው ቃላችን ነው ብለው ፖሊስ አንብቦላቸው ፈርመዋል

በእርግጥ ቃላቸውን ሲቀበላቸው እንጂ የፈረሙ አይምስለኝም

በደንብ የምታስታውሺው ቃሉ ቃላችሁ ነው ይሄ ነው የሰጣችሁት ቃል

ተነቦላቸዋል አዎ አዎ

ተነቦላቸዋል

አዎ

እ

አዎ

ፈርመዋል

ሲፈርሙ ግን አላየሁም አልፈረሙም

እሺ ይበቃናል

ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አለ

ለዐ/ሕግ ድጋሚ ጥያቄ የምስክር መልስ

ካዝና አሁን እያልሽን ያለነው ሲነበብ ሰምቻለሁ መፈረም አለመፈረማቸውን አላስታውስም እያልሽን ነው

አይ ሲፈርሙ በእርግጥ ማስፈረማቸውን አላየሁም ቃላቸውን ግን ተቀብሎ እዛው አጠገባቸው ማንበቡን አንብቦላቸዋል

966

ጨርሻለሁ

ለፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

ቃላቸውን ሰጥተዋል ቃላቸውን ሲሰጡ እኔ ለጉዳዬ ነበርኩ እዛ ሰምቻለሁ ቃሉም ተነቦላቸዋል እያሉ ነው ስንት ሰዎች ናቸው ቃላቸውን የሰጡት

2 ሰዎች

ማን እና ማን

መሀመድ ወንጀባ እና አብደላ መሀመድ ሀማ

ስማቸውን ነው የምታውቂው

ስማቸውን ነው በወቅቱ እነሱ ስማቸውን ጠይቆ ስማችን ይሄ ነው ብለው ሲሉ ነው እንጂ እኔ መልካቸውን እንኳን ላውቃቸው አልችል

አታውቂያቸውም ከእዛ በፊት እነሱን

አላውቃቸዋም ከእዛ በፊትም አላውቃቸውም እነሱ ሌላ ከተማ ውጪ ናቸው እና እኔ እዛ ከተማ ውስጥ ነኝ እነሱ ሚኖ የሚባል አካባቢ ናቸው

ምን ያህል ይርቃል ሚኖ ከእናንተ እርሶ ካሉበት

200 ኪሎ ይሆናል

እ

200 ኪሎ ሜትር ሳይሆን አይቀርም በእግጠኝ--

አሁን እዚህ ቢያይዋቸው ሊለዩ አይችሉም ሊያስታውሱ አይችሉም

አለይም አልዋሽም

አልችልም ብለዋል ጨርሰዋል እናመሰግናለን

35ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ካዲራ ሚስተኩም መሀመድ

እድሜ - 25

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ ቀበሌ - 01 የቤት ቁጥር - የለውም

ዛሬ ለምን መጣሽ

ለምስክርነት ማን ላይ ነው የምትመሰክሪው በእነማን ጉዳይ

አህመድ ኡጁንባ ኡጀንባ መሀድ አጀንባ

ሌላስ

አብደላ ሀማ

ሌላስ

አህመድ ሼክ ሰኢድ

አሁስ ስማቸውን የጠራሻቸው ሰዎች ፀብ ወይ ዝምድና አለሽ ወይ

የለኝም

ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቂያለሽ የአሁኑ ሰዎች ስለ እነሱ ምንድነው የምታስረጂ በዝርዝር ለፍ/ቤቱ አስረጂ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

መሀመድ አብዱጀባር እና አብደላ መሀመድን በአካል ታውቂያቸዋለሽ እንዴ

አላውቅም

የት ነው የምታውቂያቸው

እኔ ለጉዳይ በፖሊስ ጣቢያ ስሄድ እዛ እኔ እያለሁ ቃላቸውን ሲሰጡ ነው የማውቃቸው

እስቲ መሀመድ አብዱልጀባ ምን ብሎ ቃል ሲሰጥ ሰማሽ ንገሪን

አዳራሽ ገብተን 12 ኩንታል 50 ኪሎ ግራም ማለት ነው ለኦነጌች አባል ሰጠን ሲል ሰማሁ

12 ኩንታል ምን

በቆሎ

ኩንታል ነው ኪስ ነው እያላችሁ ክሊር እያደረጋችሁ ሂዳዋ

እሺ ይቅርታ 12 50 ኪሎ የተባለው 12 50 ኪሎ እሺ ከማን ከማን ጋር ሆኜ ነው ያወጣሁት ብሎ ሲናገር ሰማሽ

አብደላ ሰኢድ እና መሀመድ ሼካ ጋ ሆነን ነው ያወጣነው አሉ

እሺ አብደላ መሀመድስ ምን ብሎ ሲናገር ሰማሽ

እሱን አላየሁትም

አህመድ አብጀባ ነው የተናገረው

አይ አብደላ መሀመድ የተባለው የእዛን ጊዜ ቃል የእዛን ጊዜ ቃል ሲሰጡ የሰማሽው ስንት ሰዎችን ነው በላት

አህመድ አብጀባ ብቻ ነው ቃሉን የሰጠው

አብደላ መሀመድ ቃል ሲሰጥ አልሰማሽም

አልሰማሁም

ምንም የምታውቂው ነገር የለም የሰማሽውም የለም

አዎ

እሺ መሀመድ አብዱጀባ መቼ ነው ቃል ሲሰጥ የነበረው ጊዜው አመተ ምህረቱ

በ2000 ዓ/ም

ወሩን ታውቂዋለሽ

አላስታውስም

ሰአቱስ ስንት ሰአት ላይ ነው

2 ሰአት ነው 3 ሰአት ገደማ ነው አላስታውስም በትክክል ያለውን ሰአት

እሺ የት የት ቀበሌ ነው

እነሱ የሰሩበት ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ነው

አንቺ ብቻ ነሽ እዛ ቃል ሲሰጥ ስትሰሚ የነበው ወይንስ ሌላ ሰው ነበረ

እኔ እና አሁን እዚህ ጋ ሆኖ የነበረች ካዝና አብረን ነበርን

ታዲ የስንት ሰአት ላይ ነው ይሄንን የሰማችሁት ቃል ሲሰጡ የሰማችሁት

እኔ ለሌላ ጉዳይ ነው የሄድነው እና ለሌላ ጉዳይ ነው የሄድነ 3 ሰአት ይሁን 4 ሰአት ይሁን እንደዛ አልያዝኩም በጭብጥ

አታስታውሺውም

አላስታውስም

የእዛን ሰአት ታዲያ አብራችሁ ከሆሆናችሀ አብደላ መሀመድሀ የተባለ ሌላ 2ኛ ሰው ቃል ሲሰጥ አልሰማሽም

አላየሁም

ጨርሰናል

ዋና ጥያቄ አብቅቷል ለተከሣሾች መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ ጠይቋቸው ካለ መስቀለኛ ጥያቄ የለንም ብለዋል ድጋሚ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም ጨርሰዋል እናመሰግናለን እሺ ቀጥሉ

45ኛ ምስክር ---

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

870

1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ 6ኛ 7ኛ 8ኛ 11ኛ 14ኛ 59ኛ 60ኛ እና 69ኛ ተከሣሾች ላይ

ስንተኛ ክስ

1ኛ ክስ 2ኛ ክስ 3ኛ ክስ 4ኛ ክስ እና 5ኛ ክስ ላይ

እሺ ቀጥሎ የሚሰማልን 45ኛ ነው ብለዋል 45ኛ ምስክር 1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ 6ኛ 7ኛ 8ኛ 11ኛ 14ኛ 59ኛ 60ኛ እና 69ኛ ተከሣሾች ላይ ነው የሚያስረዱልን ክሶቹም 1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ እና 5ኛ ክሶችን የተመለከተ ነው የሚል ነው እሺ 45ኛ ምስክር ሙሉ ስም

45ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ጋሩምሳ ባቲ ---

እድሜ - 22

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ ቀበሌ - ገራ.ጋፋ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

እነማን ላይ

12 ሰዎች ላይ ነው ምስክር የምወጣው

ማን እና ማን

በአይን የማውቃቸውም አሉ

እሺ

በሰማሁትም በአይን የማውቃቸው አሉ

እሺ ማን እና ማን ናቸው ስማቸውን ንገረን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ችሎት 4

ወሩን ታውቂዋለሽ

አላስታውስም

ሰአቱስ ስንት ሰአት ላይ ነው

2 ሰአት ነው 3 ሰአት ገደማ ነው አላስታውስም በትክክል ያለውን ሰአት

እሺ የት የት ቀበሌ ነው

እነሱ የሰሩበት ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ነው

አንቺ ብቻ ነሽ እዛ ቃል ሲሰጥ ስትሰሚ የነበው ወይንስ ሌላ ሰው ነበረ

እኔ እና አሁን እዚህ ጋ ሆኖ የነበረች ካዝና አብረን ነበርን

ታዲ የስንት ሰአት ላይ ነው ይሄንን የሰማችሁት ቃል ሲሰጡ የሰማችሁት

እኔ ለሌላ ጉዳይ ነው የሄድነው እና ለሌላ ጉዳይ ነው የሄድነ 3 ሰአት ይሁን 4 ሰአት ይሁን እንደዛ አልያዝኩም በጭብጥ

አታስታውሺውም

አላስታውስም

የእዛን ሰአት ታዲያ አብራችሁ ከሆሆናችሁ አብደላ መሀመድሀ የተባለ ሌላ 2ኛ ሰው ቃል ሲሰጥ አልሰማሽም

አላየሁም

ጨርሰናል

ዋና ጥያቄ አብቅቷል ለተከሣሾች መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ ጠይቋቸው ካለ መስቀለኛ ጥያቄ የለንም ብለዋል ድጋሚ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም ጨርሰዋል እናመሰግናለን እሺ ቀጥሉ

45ኛ ምስክር ---

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

በአይን የማውቃቸው አንድ ጊዜ ያየኋቸው አብደላ ---

እሺ

ሲራጅ አህመድ

እሺ

አመኖ ሩጌ

እሺ

ከሊል ጃለላ እኔ ያየኋቸው

ጆሮ የሰማኋቸው

ዳይና

እሺ

አብዱራህማን ባሌ

እሺ

ሻኪር ቱኬ

እሺ

ፋጤ አሜ

እሺ

ሀሰን መሀመድ

እሺ እሺ ምንድነው ያየከው ምንድነው የሰማከው በዝርዝር ለፍ/ቤቱ አስረዳ --

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

873

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

አሁን እኚህ 12 ተከሳሾች ላይ ነው የምመሰክረው ብለሀል እና እኚህን 12 ተከሣሾች በመልክ ትለያቸዋለህ ወይ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ክቡር ፍ/ቤት እንዲለያቸው ይፈቀድልን

ለያቸው

እስቲ ከእዚህ ውስጥ አውጣቸው

እሱን እዩት እናንተ እሱን እሱን እዩ ወደ ኋላም እየዞርክ እይ በለው ሴቶች ነበሩ

አዎ ሴት ነበረች

እ

ያልነበረችውን የሌለችዋን ነው

አዎ 8ኛ በቃ ና ቁጭ በል በለው

ምስከሩ ተከሣሾችን ስም እየጠራ ከብዙ ተከሣሾች ውስጥ አውጥቷቸዋል ለይቷቸዋል እሱ የለያቸው ስማቸውን እንዲገልፁ እናደርጋለን ስምህ ማነው አብዱራህማን ባሌ ድምፅ ተናገር ተራ በተራ ስማችሁን ተናገሩ ዙቤር ሁሴን አብደላ ሙሴ ማመዲን አብራሂም ሀሰን መሀመድ አህመድ ኑር ሁሴን ጅዋድ አማ ዚያድ አማ ሲራጅ ከማል ሲራጅ አህመድ ሲራጅ አህመድ ነው ሲራጅ አህመድ ነው ብሏል እሺ ስምህ ማነው አንተ ሸሪ ፈዲ ጃኪር ጡቁ ሻኪር ጡቁ ኢብራሂም ማን ኢብራሂም ሁሴን መሆናቸውን ገልፀዋል ሌላኛዋ ሴት ናት የሚል ነገር ነው የተገለፀው ሴቷ ስሟን ታወቃታለህ

ፋጢሺ አሜ

ፋጢሺ አሜ ብሏል ያው 8ኛ ተከሣሽ ናት ያው በህክምና ምክንያት የሌለች መሆኑን በመዝገቡ ላይ ሰፍሮ ይገኛል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

874

እሺ አሁን የጠራካቸውን ሰዎች ታውቃቸዋለህ

እኔ እነሱን በአይን የማውቃቸውም አለ

ስለ እነሱ የማውቀው የሰማከውም በአይን ያየሁትም አለ ብለህል እሱን ሳይሆን የተጠየከው ፀብ ወይም ዝምድና አለህ አሁን ከጠራካቸው ሰዎች

የለኝም

ፀብም ዝምድናም የለኝም ስለ እነሱ የሰማሁትም ያየሁትም አለ ብሏል ያየከው ምንድነው የሰማከው ምንድነው በዝርዝር አስረዳ ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

በአይን የማውቀው አለ ያልከው በአይንህ ያየካቸው ማን ማንን ነው እስቲ

በአይን የማውቃቸው እኔ ወታደር ሆኜ የማውቃቸው አብደላሂ ሙሳ ሲራጅ አህመድ አመኑ ሩጌ እነዚህን ሶስቱን ነው ያየኋቸው

እሺ እኚህ 3ቱ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቀው

ኢብሳ ለሜ --- ጫት እየቃሙ ነበረ እያሉ ነው እኔ የመጣሁኝ

ኢብሳ ለሜ ምንድነው

ኦነግ ነው

ጫት እየቃሙ ምን ይባባሉ ነበረ

እኔ ስመጣ ምን እንዳሉ አላውቅም ጥበቃው ዋርድያውን ያዘው አሉኝ

እሺ ይዘህስ ምን ሰማህ

ከእዛን በኋላ ከእነሱ ይሄንን ነው ያየሁት ከሌላ ሰዎች አሁን ተነሱ ብዬ ካቆምኳቸው ሰዎች ውስጥ አብዱራህማን ባሌ ዳይና ሻኪር ቱኬ ፋጤሼ አሜ ሸረፍ አሉ ሀሰን መሀመድ ከእነሱ ደግሞ የሰማሁት የእኛ አዛዥ ሰልክ ደውሎ ሸረፍ አሉ እነ ሸረፍ

875

ምስክሩ

እሱ ምን እያደረገ ---

ስልክ የደወለው ማን ነው

የእኛ መቶ ሐለቃ ነው ስልክ የደወለው

የእናንተ መቶ ሐለቃ ምንድነው እሱ መቶ ሐለቃ ይሄ የማን መቶ ሐለቃ ነው

እሱ ኦነግ ነው

አሀ አንተ ነበርክ ማለት ነው እዛ ውስጥ

እኔ ዋርዲያ ላይ ነበርኩኝ በእዛን ጊዜ ስልክ

ዋርዲያ ምንድነው

ጥበቃ

ስልክ አነሳሁኝ እና ወደ እዚህ እየመጣሁ እያለሁ ከጐኑ ነው እኔ ጥበቃ ዋርዲያነት እየጠበኩ የነበረው እነሱ አሁን ስማቸውን ጠርቼ ያቀምኳቸው ሰዎች ልብሱ አልተሰፋም ወይ አልተገዛም ወይ ብሎ ጠየቀ

የምን ልብስ

የወታደርና ልብስ

ለማንኛው ወታደር የሚሆን

ለኦነግ

ሌላስ

ከእዛ እሱን ጠይቆ እኔን ሲያየኝ ከጐኔ ወደ እዛ ሄደ ከእነሱ ላይም ይሄንኑ ነው የማውቀው

ከልብስ ውጪ ሌላ የጠየቃቸው ነገር ምን አለ

እሱ የጠየቀው ይሄንኑ ነው የሰማሁት

976

በምንድነው የጠየቃቸው

በኢንተርናሽናል ሞባይል ነው የጠየቀው

እነሱ መሆኑን በምን አወክ አንተ እነሱን የጠየቀ መሆኑን በምን አወክ

በፊትም ሰዎቹን እኔ አውቃቸዋለሁ

የምታውቃቸው በምንነታቸው ነው

በፊት ህብረተሰቡ ውስጥ እያለሁ ነው እነሱን የማውቃቸው

የምታውቃቸው ምን ሆነው ነው

እኔ በፊት ነው ከድሮ ነው ሰዎቹን የማውቃቸው

እሺ

ስማቸው ሲጠራ ወይ ስማቸው ሲነሳ ነው ያወኩኝ

ስማቸውን ጠርቶ ነበረ ወይ እሱ እያለ ነው

ስማቸውን እያነሳ ስራው እንዴት ነው ብሎ ሲያነሳ ነበር

የትኛው ስራ

የትኛው ስራ እንደሆነ አላውቅም ልብሱን ነው በእዚህ መሀል ያስገባው

ልብሱን ነው በእዚህ መሀል ያስገባው

እነሱ የዛን ጊዜ ምን ሆነው ነው ሲንቀሳቀሱ የነበረው

ኦነጎች ነው የምትለው ወይ

አላልኩም እኔ እየጠየኩህ ነው

ኦነጎች ነው የምትለው ወይ ነው ያለው

ኦነግ ሆነው ነው የሚንቀሳቀሱት ነው አባባሉ ወይንስ ምንድነው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

አይደለም

እ

አንተ ጥያቄውን ምን አልከው

እኔማ ጥያቄ ነው ያመጣሁት

እነሱ ምን ሆነው ሲንቀሳቀሱ የእዛን ጊዜ ምን ሆነው እየተንቀሳቀሱ ነበረ ነው ይሄ የሚደዋወሩ እና የሚጠያየቁት

እነሱን እኔ በእዛኑ ወቅት ነው ሲል የሰማሁት እንጂ ከእዛን በፊት እንደዛ አላሉም

ሲል የሰማከው ምንድነው በምን ይንቀሳቀሳሉ ሲል ሰማህ

እኔ ስሰማ ሚስጥሩን እኔን ለመደበቅ ወደ እዛ ሄደ ስራ እንዴት ነው ብሎ ወደ እዛ ሄደ እኔ ስመጣ ሚስጥሩን እንዳልሰማ እራቀኝ

እሺ እሱ አመራር ነው ብለከን ነበረ እና የምን አመራር ነው የምን ሀለቃ ነው ሀላፊ ነው ስልክ ደዋይ -- ስልክ ደዋዩ ማነው ስሙ

ኢብሳ ---

ማእረጉ ምንድነው

መቶ ሐለቃ ነው ማእረግ የላቸውም

የምን መቶ ሐለቃ የምን አመራር ነው የምን ሀላፊ ነው

የኦነግ

የኦነግ ሀላፊ ነው ይሄንን ታውቃለህ ወይ

መቶ ሐለቃ ነው

እኮ የኦነግ ሀላፊ መሆኑን ታውቃለህ ወይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

998

አዎ አውቀዋለሁ

በምን አወቅህ

እኔ የእነሱ አባል ነኝ

የምኖቹ አባል

በእዛን ጊዜ ጅማ ጅሎ የሚባለው ነው እኛን የሚያንቀሳቅሰው

የኦነግ አባል ነበርክ ወይ አንተም

አዎ

እና በእዛ ነው ወይ ያወከው

አዎ በእዛ ነው ያወኩት

ኤውልህ ስልክ የሚደውለው መቶ ሐለቃ ኢብሳ የሚባለው የኦነግ አመራር ነው ብለሀል አንተም ዋርዲያ ሆነህ እዛው አጠገቡ ቆመህ ትጠብቅ እንደነበር ነግረከናል እሱ በስልክ ደውሎ ስራችሁን እየሰራችሁ ነው ወይ በሎ አዛዡ ሲጠይቃቸው የነበሩት እነ አብዱራህማን ጀቦ ያልካቸው ቅድም የጠራካቸውን ሰዎች በስልክ ጠርቶ ስራቸውን እየሰሩ ነው ወይ ልብሱስ ተገዛ ወይ የሚላቸው ምን ስለነበሩ ነው እነሱ ---አመራር ነው ብለሀል እኔ ደግሞ የኦነግ አባል ሆኜ ዋርዲያ ነኝ በእዛን ሰአት ነበርኩ ብለሀል ስልክ አምጥቶ ከደወለ በኋላ ከእኔ እራቅ ብሎ ሲያነጋግራቸው ነበር ብለሀል ስራችሁን እየሰራችሁ ነው ወይ ልብሱስ ተገዛ ወይ ብሎ ሲጠይቃቸው ነበረ ብለሀል እነሱ ምን ስለሆኑ ነው እየደወለ እንደዛ ሲጠይቃቸው የነበረው

እኔ በውስጤ በአስተሳሰቤ አብረው ነው ስራ ያላቸው መስሎኝ ነው በውስጤ

የምን ስራ

እንደ ፓርቲ ሆነው ይሆናሉ ብዬ ነው ያሰብኩት ግን እኔ -------

በየትኛው ፓርቲ

ይሄን ፓርቲ እሱ ካደራጀ ብዬ እሱም ውስጡን ደበቀኝ ለእዛ የእሱ ያደራጀው ፓርቲ ብዬ ነው የገመትኩት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

899

መቶ ሐለቃ ያደራጀው ፓርቲ ምንድው ሲያደራጅ የነበረው አንተም አባል የሆንክበት እሱ ያደራጀው ፓርቲ ምንድነው

እስቲ ይሄ ነገር የሆነው የተፈፀመው መቼ ነው ጊዜው

እ/ኤ/አ 2008

እሺ በ2008 ወሩስ

አላስታውስም ወሩን

የት ቦታ ነው አሁን ይሄ በስልክ ደውለው ሲያነጋግራቸው የነበረው እነዛ 3ቱ ደግሞ ከእሱ ጋ ጫት አብረው ሲቅሙ እና ሲመካከሩ የነበረው የት ቦታ ነው ዞኑ የት ነው ምእራብ ሐረርጌ ምስራቅ ሐረርጌ የትኛው ነው

ምስራቅ ሀረርጌ

የት ወረዳ

ጕሎዳ ወረዳ

ቦታውስ ልዩ ቦታው ቀበሌው

ጋራ ጋፋ ቀበሌ ጊሌ የሚባል ቦታ

ቅድም አብደላ ሙሳ ሲራጅ አህመድ እና አህመድ ኑር ጫት አብረው ይቅሙ ነበረ ይሄንን አይቻለሁኝ ከእዛ እኔም ዋርድያ ነበርኩ ብለሀል ቦታው የማን እቤት ነው ነው ምን አይነት ቦታ ነበረ ኦኬ ስማቸው ቅድም በአይን አየኋቸው ያልካቸው ምስክሮች አሉ አብደላ ሙሳ ሲራጅ አህመድ አህመድ ኑር ኡርጌ እነዚህ ሰዎች ቁጭ ብለው ከእዛ ከመቶ ሐለቃው ከኦነግ አመራር ጋ አብረው ጫት እየቃሙ ሲነጋገሩ የነበሩበት ቦታ ሰው የሚመጣበት ቦታ ግልፅ ቦታ ነው ወይንስ ምን አይነት ቦታ ነበረ

እኛ እዛ ቁጭ ብለን ወታደሮችን ከራሳችን የምንጠብቅበት ቦታ ነው

የማን ወታደር የኦነግ ወታደር ማለትህ ነው ወይስ

የመንግስት ወታደር

የመንግስት እንዳይመጣባችሁ ነው ወይስ ምንድን

አዎ ወደ እኛ እንዳይመጡ ነው

ጨርሻለሁ

ስልክ ሲደወል ሰማሁ ነው ያልከው

እሺ ዋና ጥያቄአ ብቅቷል

ለተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ከወዲያህ ተቀባዩ ወይ ለነማን እንደሚደወል እንዴት ታውቃለህ አንተ

እኔ የሰማሁት ማን እንደደወለ እኔ እንጃ ግን የሰማሁት የእኛ መቶ አለቃ እነሱን ሲያነጋግር ነው የሰማሁት

እነማን በምን አወቅህ እነማን አነጋገሩ

ስራው እንዴት ነው ብሎ አለቃችን ሲናገር ለእነ አብዱረህማን ባሌ፣ ሻፊር ቱቂ፣ ዳይና

ሌላ

አላስታውስም ሌላ ስም

አሁን አንተ ሰዎቹን አላየህም ድምጻቸውንም አልሰማህም

አዎ እሱ ነው ዳይና ብሎ 4ኛ ተከሳሽን አሳይቷል

ድምጻቸውን አንተ አይሰማህም

የደዋዩን ድምጽ አልሰማም የአለቃችን ድምጽ ግን እሰማለሁ

አለቃችሁ እገሌ እገሌ እያለ ስም ይጠራል

አዎ ስማቸውን በዛው ነው ሰምቼ ልጠቅስ የቻልኩት

ስማቸውን መጥቀሱ ሌላ አብዱረህማን ባሌ የለም ወይ በአገር ውስጥ ሌላ መሀመድ አህመድ ሌላ እገሌ የሚል የዛን አይነት ስም ያለው ሰው ሌላ ሐረር ውስጥ የለም ወይ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ቁጥር 4

881

በዛ ላይ እኔ ልል የቻልኩበት እነሱን በፊትም አውቃቸዋለሁ ------ ውስጥ እያለሁ እነሱን አውቃቸዋለሁ

ሰዎቹን የማወቅ ጉዳይ እኮ አይደለም አሁን እገሌ እገሌ እያለ ሰውየው ስም ይጠራል እነዚህን ሰዎች በትክክል መጥራቱን በመልክ አላየካቸውም በስም ነው ስማቸው የተለያየ ስም አለ ሰው የተለያየ ስም አለው እነዚህ ሰዎች ለመሆናቸው በምንድን ነው የምታረጋግጠው ማረጋገጫህ

እኔ እነሱን መሆናቸውን ላውቅ የቻልኩበት በዛ በወቅቱ እኔ ወታደር ውስጥ ስነበርኩኝ እጅ ሰጥቼ ተሀድሶ ወስጄ ወደ ቀበሌ ወደ ወረዳዬ ተመለስኩኝ በዛ እጅ በሰጠሁበት ጊዜ ነው ይሄንን ሀሳብ የሰጠሁት ከዛን በኋላ እነሱም በቁጥጥር ስር ውለዋል እኔም ወደ ወረዳዬ ስመለስ በቁጥጥር ስር ውለዋል እነሱ ለእዛ አንተ በፊት ሀሳብ የሰጠህባቸው ሰዎች ቁጥጥር ስር ስለዋሉ ና ምስክር ቃልህን ስጥ ስላሉኝ ነው በዛ ነው እነሱ መሆኑን ያረጋገጥኩትኝ

እኮ አሁን ግምት ነው እንጂ ማረጋገጫ አለ ወይ

እኔ መጀመሪያ ራሱ ሶስት ሰዎች ብቻ ነው ያየሁት ግን ሌሎቹ እንደሰማሁት ገልጬ ነበር መጀመሪያ መስማቴ ነው እንጂ ስለማየቴ አይደለም

ተምረሃል

አልተማርኩም

2008 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የሚለውን እንዴት አወቅከው

እኛ በዛ በውትድርና ውስጥ በነበርንበት ጊዜ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ስለምንቆጥር በዛ ነው ላውቅ የቻልኩት

በቃን

መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ አለ

የለንም

ድጋሚ ጥያቄ የለም

ለፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

892

ኢንተርናሽናል ሞባይል የያዘው ማን ነው

ኢብሳ ለሚ

እንዴት አወቅህ ኢንተርናሽናል ሞባይል መሆኑን

የእነሱ ፓርቲ ስለነበርኩኝ አውቀዋለሁ

በዚህ ኢንተርናሽናል ሞባይል ከየት ነው ኢብሳ ለሚ የሚደውለው

ከጋራ ቃፋ ቀበሌ ነው የሚደውለው

ማን ላይ ነው የሚደውለው የማን ስልክ ላይ ነው የሚደውለው

ማን ጋ እንደደወለ አላውቅም ግን እያወራ ነው እኔ ዋርዲያ እየጠበኩኝ እያለ ወደ እኔ መጣ ከዛ እኔን ሲያየኝ ወደ ኋላ ተመልሶ ወደጎን ሄደ

አንተ ዋርዲያ እየሆንክ አንተ ጋር ደርሶ ተመለሰ ብለሃል ቅድም ደግሞ የሆኑ ሰዎች ስም ጠርተሃል እነማንን ነበር የጠራከው

እዛ እሱ ሲናገር ከአፉ የሰማሁት ሰዎች አብዱረህማን ባሌ፣ ሻፊር ቱቂ፣ ዳይና፣ ፋጢሽ አሜ፣ ሀሰን መሀመድ፣ ሸሪፍ አሊ እነዚህ ናቸው ከአፉ ሲናገር የሰማሁት

እነዚህ ምን አደረጉ ምን ሆኑ ነው የሚለው

ስራ እንዴት ነው ብለው ይናገር ነበር

አንተ ጋር መጥቶ ከተመለሰ እነዚህን ሰዎች ሲጠራ እንዴት ልትሰማ ቻልክ

መጀመሪያ አላየኝም ነበር እሱ የሚያስተላልፈው ሚስጥር ስለነበር እኔን አላየኝም እየሄደ እኔ ጋር ሲደርስ ነው የተመለሰው

የሰዎቹን ስም እስከ አባት እየጠራህ ነበር ያ ስልክ የሚያናግረው ሰውዬ እስከ አባታቸው እየጠራ ያናግር ነበር

የአባታቸውን ስም አልነካም የእነሱን ስም ብቻ ነው እየጠራ የነበረው

883

ስለዚህ ቅድም አሁን አንተ የመረጥካቸው ሰዎች ይሁኑ በስልክ ያ መቶ አለቃ ያናግር የነበረው ምክንያቱም በአባት እስካለየ ድረስ እነዚህ ሰዎች ይሁኑ ሌሎች ሰዎች ይሁኑ በምንድን ነው መለየት የምትችለው

እኔ ታሀድሶ ወስጄ ነው ወደ ወረዳ የተመለስኩት መጀመሪያም ተናግሬ ነበር

ሁለታችሁ እያወራችሁ እኮ ነው

እኔ መጀመሪያም ተናግሬ ነበር ታሀድሶ ወስጄ ነው ከዛ ውስጥ የተባሁት ወደ ወረዳ የተመለስኩት

ስለ ታሀድሶ ምናምን አይደለም እዛ እያለ በስልክ ወቅት እነዚህ ሰዎች መሆናቸውን እንዴት ለየህ

አንተ ገብቶሃል

አዎ እኔ ገባኝ

ምክንያቱም እስከ አባታቸው እየጠራህ ነው እሱ እስከ አባት አልጠራም ብለሃል እና እነዚህ ሰዎች ይሁኑ አይሁኑ እዛው ማለት ነው አሁን ታሀድሶ ወስዶ መመለስ ሌላ ቀጥሎ ያለው ሂደት ነው ከዛ በፊት በነበረው ሁኔታ አሁን ሲነግረን የነበረው የበፊቱን ነው ስለዚህ በምን ለይቶ ነው እነዚህ ይሁኑ ሌሎች ሰዎች ይሁኑ በምን አውቆ ነው

እኔ እጅ ስሰጥ በወረዳዬ ነው እጅ የሰጠሁት በዛን ጊዜ ሰፈር ውስጥ የነበረ ኢንፎርሜሽን እናንተ በኦነግ ውስጥ የነበራችሁ ሰዎች ስለዛ ስለነዛ ማዴ ወይም ፓርቲዎች ምን ያህል ታውቁ ነበር ብለው እየተጠየቅን ነበር ምንም የምናውቀው ነገር የለም ግን በእኛ አለቃችን አፍ እንዲህ እንዲህ ስም ሰማን ብዬ አልኩኝ እኛ ምስክርም ስላላገኘን ነገሩም ኢፋ ስላልወጣልን ተሀድሶ ወስደህ ትመለስልናለህ ብለው አሉኝ ከዛ እኔ ተሀድሶ ወስጄ ስመለስ እነሱም ቁጥጥር ስር ውለው ነበር በዛ ነው ኢፋ ሊወጣ የቻለው

በአንድ ጊዜ ነው እነዚህን ሰዎች ስም ሲጠራ የነበረው ወይስ በተለያየ ጊዜ ነው የሰማከው እነዚህን ሰዎች በአለቃህ አፍ በአለቃህ አንደበት በአለቃህ አፍ የሰማከው በተለያየ ጊዜና ቀናት የሰማከው ነው ወይስ በአንድ ጊዜ ነው

884

በአንድ ጊዜ

ስራ እንዴት ነው ይል ነበር ስራ የምን ስራ ነው

ያለ ልብስ አልተሰፋም ወይ ወይ ደግሞ ልብሱ ተገዝቶ አልመጣም ወይ እያለ ነበር

የምን ልብስ መሆኑን ነው ያወከው

ልብሱ የወታደር ልብስ ነበር ልብስም ተገዝቶም ሆነ ተሰፍቶ ሳይመጣ ነው እኔ እጅ ሰጥቼ ከዛ የሄድኩት

የኦነግ ወታደር ምን ያህል ጊዜ ይሆንሃል አንተ

አራት አመት

አራት አመት የኦነግ ሰራዊት ሆነህ ስትኖር አሁን የጠራሃቸውን ሰዎች በኦነግ አባልነታቸው ወይም በዚህ እንቅስቃሴአቸው ታውቃቸው ነበር አባላት ሆነህ በነበርክ ጊዜ አንተ በግልህ በአራት አመት በሆንክበት ጊዜ በኦነግ እንቅስቃሴ ወይም አባልነታቸው ታውቃቸው ነበር ወይ

አላውቅም

እሺ ጨርሰሃል እናመሰግናለን ቀጥሎ ስንተኛ ነው የምታስመዘግቡት

53ኛ ምስክር ሲራጅ መሀመድ አሊ የሚመሰክረው በ1ኛ፣

እንግዲህ አሁን 11:30 ሆኗል ጀምረን ካለማቋረጥ ነገ በማለዳ በጠዋት የምታመጡበትን ሁኔታ ብታመቻቹ ነው የሚሻለው እሺ ትዕዛዝ ተሰጥቷል

ት ዕ ዛ ዝ

ቀሪ የዐ/ህግ ምስክሮችን ለመስማት በአዳር ለ2:00 ሰኣት ተቀጥሯል። በዚህ መሰረት 67ኛ፣ 60ኛ፣ 61ኛ፣ 34ኛ፣ 35ኛ፣ 45ኛ፣ ከሰዓት በኋላ ተሰምተዋል ቀሪ ምስክር በአዳር 2:00 ሰኣት ለመስማት በአዳር ተቀጥሯል። በአዳር ለመስማት ለሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ/ም ተቀጥሯል።

ማ/ተ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቁጥር 4

በወመ/ቁ - 04486

ቀን - ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ/ም

ዳኞች - ብርሀነመስቀል ወጋሪ

- ይርጋ አይቼህ
- እልፍነሽ ወሌሮ

ከሣሽ - የፌደራል ዐ/ሕግ ማሙሸት አበበ እያሱ መኮንን ሀረጋይ ንደሻው ቀርበዋል

ተከሣሾች እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ተከሣሾች

ቀደም ሲል ሰኔ 4 ጀምሮ ያው በተከታታይ ምስክሮች ስንሰማ ነው ምናልባት ማረሚያ ቤት ከትላንትና ከቀረቡት ወይንም ከቀሩት የተለየ የቀረቡ ወይም የቀሩ ካሉ ማረሚያ ቤት ብትነግሩን እሺ ከትላንትና የተለየ ነገር አለመኖሩ እና ተከሣሾቹ ሰኔ 4 እና ሰኔ 7 የቀረቡት እንደቀረቡ ነው ሰኔ 4 እና 7 ያልቀረቡት እንዳልቀረቡ ማለትም 8ኛ 31ኛ እና 33ኛን በተመለከተ ነው ሌሎች 22 በዋስ ሌሎቹ ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል መዝገቡ የተቀጠረው ቀሪ ምስክሮችን ለመስማት ነው ዛሬ የቀረቡ ምስክሮች ማን እንደሆኑ እና ምን ያህል እንደሆኑ ዐ/ሕጐች ብትገልፁ የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቆች አቶ አድማሱ እና አቶ ኢብራሂም ቀርበዋል

ዛሬ 7 ምስክሮች ቀርበውልናል 65ኛ 53ኛ 33ኛ 32ኛ 31ኛ 28ኛ እና 68ኛ ምስክሮች ቀርበዋል

እሹ ትላንት የቀረቡት መሀላ የፈፀሙ ናቸው አይደለ

አዎ

ከእነሱ ውጪ ጥሯቸው እና ቃለ መሀላ ይፈፅሙ

በድጋሜ የፈፀሙ አሉ

886

ያልፈፀሙት ቃለ መሀላ እንዲፈፅሙ አድርጉ ትላንትና ቃለ መሀላ ያልፈፀሙ መሆኑን ጠይቃቸው

3 ሰው አሉ

ቃለ መሀላ ያልፈፀሙ ማን ማን ናቸው አስፈፅማቸው

መሀመድ ሀሰን የሱፍ አልይ ሼካ አመራ-- በክሪ አብዱላሂ ሙሜ

ማነው ስምሽ

ዘይኑ ---

ስንተኛ ተከሣሽ ነሽ

አስራ --

እሺ አሁን ማነው የሚሰማላችሁ ስንተኛ ምስክር ነው የምታሰሙት በስንተኛው ክስ እና ስንተኛ ተከሣሽ ላይ እንደሆነ ግለፁልን

እሺ 53ኛ ምስክር የሚመሰክረው በ1ኛ በ10ኛ በ8ኛ እና በ14ኛ ተከሣሾች ላይ ነው የሚመሰክርባቸው ክሶች 1ኛ ክስ 2ኛ ክስ እና 3ኛ ክስ ላይ ነው

እሺ የሚያስረዳው ምንድነው --

1ኛ ተከሣሽ ላይ የሚያስረዳው ጭብጥ 1ኛ ተከሣሽ ላይ ለኦነግ ሰራዊት ገንዘብ እንደላከ ሰው እንደሚያደራጅ የመንግስት ሰራተኛን እንደሚደበድብ እና የኦነግ አባል እንደነበረ ይመሰክርልናል 1ኛ ተከሣሽ ላይ

እሺ

10ኛ ተከሣሽ ላይ የኦነግ አላማን ለማሳካት በአንድ ወቅት ሽጉጥ ይዞ ሲንቀሳቀስ እና እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ የኦነግ አባል መሆኑን ያስረዳልናል 8ኛ ተከሣሽ ላይ የኦነግ ድርጅት ውስጥ የተደራጁ እንደነበረ ነው ለድርጅቱ ገንዘብ እንደምታዋጣ በህዝብ ፊት እራስዋል እንዳጋለጠች ይሄንን ያየ ስለመሆኑ ይመሰክርልናል

አሁን እዚህ የለችም

887

የለችም አዎ

በህመም ምክንያት ስለሌለች

ጠበቃዋ ስላሉ

እ

ጠበቀዋ ስላሉ 14ኛ ተከሣሽ ላይ

ጠበቃዋ ያው እሷ በሌለችበት

ሌላ ጊዜ 8ኛ ላይ የምታቀርቡትን ምስክር 8ኛ ዛሬ ስላልቀረበች ሌላ ጊዜ እሷ ባለችበት የሚሰማ ይሆናል አሁን እሷ በሌለችበት እሷን በተመለከተ

እሺ 14ኛ ተከሣሽ ላይ ከመንግስት ሚኒሻዎች ላይ መሳሪያ ለመቀማት ሙከራ

አሁን እዚህ የለችም እስከ አሁን ስለ እሷ የተመሰከሩ እሷ በሌለችበት እለት ከሆነ ያው ድጋሚ ነው የምታሰሙ እንጂ በሌለችበት ባልተከላከለችበት አይፈረድባትም ለመከላከል ደግሞ መስቀለኛ ጥያቄም መጠየቅ መከራከር አንዱ መከላከል መብት ነው ጠበቃዋ ጋራ መመካከር መብት ነው ይሄ እድሉ ስለሌለ እነዚህን ምስክሮች ጊዜ ሳታባክኑ 8ኛ ላይ የምታሰሙትን ብታሰናብቱ ሌላ አያይዞ የሚያሰማ ከሆነ አቀይታችሁ የምታሰሙ ቢሆን እንደዛ ነው የምንቀጥሉ 8ኛ ላይ ብቻ ላይ የሚሆን ደግሞ አንሰማም ሌላ ጭብጥ ታስመዘግባላችሁ ማለት ነው 53ኛ

እሺ 14ኛ ተከሣሽን በተመለከተ

እሺ

ከመንግስት ሚኒሻዎች መሳሪያ ለመቀማት ሙከራ ማድረጉን የኦነግ ወታደር ሆኖ መንግስትን የወጋ መሆኑን ይመሰክርልናል

እሺ 53ኛ ምስክርን ጥሩት

በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

888

53ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ሲራጅ መሀመድ አሊ ሙዴ

እድሜ - 26

ስራ - የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኛ የአስተዳደር እና የፀጥታ ኮሚቴ ምክትል ነኝ የወረዳ

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ ቀበሌ - ቡርቃ 01

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

ማን ላይ ነው የምትመሰክረው

4 ሰዎች ላይ ለመመስከር ነው የመጣሁኝ

እነማን ናቸው 4ቱ ስማቸውን ልትነግረን ትችላለህ

አዎ እችላለሁ

ንገረን

አብዱራህማን ባሌ

እሺ

ዙቤይድ ሁሴን ሙመድ

እሺ

---ሴንጂሳ

እ

ዙቤይዲ ሁሴን ሙመድ ወይንም ደግሞ ሴንጂሳ ቦኬ

እሺ

889

ኢብራሂም ሁሴን ጉራቻ

እሺ

ፋጢሺ አሜ

እሺ አሁን የጠራካቸውን ሰዎች እዚህ ልታሳየን ትችላለህ

አዎ እችላለሁ

እስቲ አሳየን ተነሱ ተነሱ በላቸው

--ፋጢሻ የለችም ተከሣሾች ምስክሩ ከሴቶች ውስጥ ፋጢሻን እንዳላገኘ አረጋግጧል ፋጢሻ ያው በወቅቱ አሁን በህመም ምክንያት አለመኖርዋም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ሌሎቹን 1ኛ 10ኛ እና 14ኛ ተከሣሾችን አሳይቷል ለይቶ አውጥቷል እሺ 1ኛ አብዱራህማን ባሌ 14ኛ ኢብራሂም ሁሴን እና 10ኛ ዙቤር ሁሴን መሀመድን አውጥቷል እሺ አሁን ከጠቀስካቸው ሰዎች ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለኝም

እሺ ምን አድርገው እንተከሰሱ ታውቃለህ ምን አደረጉ ተብሎ ነው

አዎ አውቃለሁ

ምን አደረጉ ተብሎ ነው አርእስቱን ንገረን

እነሱ ከኦነጎች ጋ በመሆን ሰዎት ላይ በደል በማድረሳቸው ነው እዛም የተከሰሱት

ለ0/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

እሺ ልቀጥል አብዱራህማን ባሌ ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው ንገረን

አብዱራህማን ባሌ ከኦነጎች ባርቲ ጋ ሆኖ ሲሰራ ነው የማውቀው

ምን ምን ሲሰራ ነው የምታውቀው

እሱ ፓርቲ ወይንም ሴል ሲያደራጅ ነው የማውቀው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

890

እሺ አደራጅቶ ምን አደረገ

መዋጮ ከእነሱ የብር እገዛ እየተቀበላቸው ነበረ እየሰበሰበ ነበረ አስር አስር ብር በ1999 መጨረሻ አካባቢ 10 10 ብር መዋጮ ከሰዎች ሲቀበል ነው የማውቀው

እሺ ሌላስ

እንደገና ደግሞ የመንግስትን ሚኒሻዎች በማባረር መሳሪያ ሲቀማቸው ነው የማውቀው እሱ ላይ ይሄንኑ ነው የማውቀው

እስቲ ከእነማን ነው ገንዘብ የሰበሰበው

ከእራሱ ጀምሮ ነው

ከእነማን ከእነማን ስር ሌሎች የምታውቃቸው ሰዎች ካሉ

እንደ እነ ደረሳ እንደ እነ ደረሳ እና እሱ ያደራጃቸው ሌሎች ከእነሱ ነው የሚሰበስበው

በምን አወቅህ

በ1998 በደተደረገው እንደ መድረክ አድርግተን እዛ ላይ ሰዎችን ሰባስበን ስንጠይቃቸው ጥናት ስናካሂድ በእዛ ላይ ነው በእራሱ በቃሉ እንዲህ እንዲህ እየሰራሁ ነበረ በማለት የነገረን 2000 ህዝብ በተሰበሰበበት እዛ ነው የነገረን

ከእዛ በፊትስ የሰማከው ነገር የለም ነበረ ወይ

ከእዛ በፊት አልሰማሁም

እሺ ዙቤር ሁሴን

ዙቤር ሁሴን ደግሞ ከደህንነት ከፌደራል ወታደሮች ጋር አብረው ሆነው ሽጉጥ ማክሮፍ የሚባል ሽጉጥ ተቀብለናል መሳሪያ

ወጂን ታኔቲ ምን ማለት ነው

አብረው ሆነው ማለት ምን ማለት ነው አልገባኝም እስቲ አብራራልኝ በለው ከማን ጋር ሆኖ ነው ማክሮፍ ሽጉጥ የተቀበለው

ከደህንነት እና ከፌደራል ወታደሮች ጋር ሆነው ያ ሽጉጡን ካስቀመጠበት ወስዶ አመጣው

ኢንፎርሜሽን አጊኝተው ከላይ መጥተው ጀቢል ወረዳ በሚባለው ቦታ ሄደው ያንን አወጡ እና ወሰዱ

ማነው ያወጣው

ኤው ጥያቄው ምንድነው ከላይ ከላይ መጡ ከላይ መረጃ ደርሷቸው መጡ እና ከላይ መረጃ ደርሷቸው የመጡት እነማን ናቸው በልልኝ

ስማቸውን እንደዛ አላውቅም

እነማን ናቸው ስንል ምንድንናቸው

አንዱ ደህንነት ነው አንዱ የፌደራል ወታደር ነው

የምን መረጃ ደርሷቸው ነው የመጡት

እሱ ከአሁን በፊት ከኦነግ ወታደሮች ጋር አብሮ ሆኖ ተይዞ እዛ ስለነበረ ነው

እሺ መጥተው ምን ሰሩ

እሱን ቀስቅሰውት ይዘው ሄደው ሽጉጡን ካስቀመጠበት ወሰዱ

ይሄ እሺ ኢብራሂም ሁሴንስ ምን ማድረጉን ነው ይምታውቀው

ኢብራሂም ሁሴን የኦነጐች ፓርቲ ወይም ሴል መሆኑን ነው የማውቀው ኢብራሂም ሁሴን ከሴሎች ላይ ብር እየሰበሰበ እያለ እንደገና ወደ ኦነጐች ወታደር ሲቀላቀል ነው የማውቀው እንደገና በሌላ በኩል ደግሞ ከመንግስት ሚኒሻዎች ላይ መሳሪያ ለመቀማት ትግል ሲያደርግ ነው የማውቀው ሲታገል

---ማለት ነው ሌላስ ምን አደረገ -- ምን አደረገ ነው ያልከው ---

ከኦነግ ወታደር ውስጥ ከገባ በእኛ ወታደሮች ላይ ችግር ሲያደርሱ ነው እኔ የማውቀው እንደገና ደግሞ ከመንግስት ወታደሮች ላይ መሳሪያ ለመቀማት ትግል ሲያደርግ ነው

892

ሌላስ የምታውቀው ነገር ካለ አስረዳን

ይሄንኑ ነው የማውቀው

በእዚህ ጥፋቱ ደግሞ ፍ/ቤት ቀርቦ ነበረ

እሺ የት ቦታ ነው ይሄ ነገር የተፈፀመው የት ክልል ነው ክልሉ የት ነው

ጉሎዳ ወረዳ በቡርቃ ከተማ 01 ቀበሌ

ዞኑ የት ነው ዞኑ

ምስራቅ ሀረርጌ

መቼ ነው አሁን ይህ ነገር የተፈፀመው መቼ ነው ጊዜው

በ1998 ጀምሮ ነው

ጨርሻለሁ

እሺ ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሮች መልስ

የተከሣሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ኤው ገንዘብ ሲሰበስብ ነበረ ብለሀል ከእነማን ነው የሰበሰበው

ከእራሱ ጀምሮ እየሰበሰበ መሆኑን በእራሱ ቃል ነው የተናገረው

የት

ጉሎዳ ወረዳ ቀበሌ 01 ቡርቃ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ

ነው እንጂ ሲሰበስብ አላየከውማ

እሱ ነው እዛ እንዲህ አደረኩኝ በማለት የተናገረው እንጂ እኔ አላየሁም ኢስኪሌ ሲያደርግ ነው የሰማሁት

እሺ --- እና --- ሲያደርግ ነው የሰማከው ነው የሚለው

የኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

893

አዎ

ምንድነው የእሱ ስራ

ተማሪ ነው እሱ

ተማሪ ነው እሺ ፍ/ቤት ቀርቦ ነበረ ብለህል ምን ተፈረደበት

ተቀጥቶ ነበረ

ስንት ቀን ስንት አመት ወይ ስንት ወር

በብር ነው የተቀጣው

የት ፍ/ቤት

የጉሎዳ ወረዳ ያለው ፍ/ቤት

ኤው አባረረ ወታደሮችን አባረረ ብለህል አቤት

ድምፅዎትን ከፍ ያድርጉ

እሺ አባረረ ወታደሮችን ብለህል እሱ መሳሪያ ይዟል

--- አባረረ ---ነው ያሉት

ኤው አባረረ

ማባረሩንነው እኔ ያየሁት በአይኔ

ባዶ እጁን ነው ወይንስ መሳሪያ ይዟል

የሚያባርሩት መሳሪያ ይዞ ነበረ ሚኒሻ ነው እሱ ግን ምንም እቃ የያዘ የለም

የያዘው የለም እሺ ይበቃኛል በሬቹ ታስሮ ነበረ ከላይ መጡ እና ያዙት ከእዛ በኋላ ምን ሆነ ሽጉጡን ካስረከበ በኋላ

ከእዛ በኋላ እኔ አላውቅም

894

መታሰሩንስ አታወቅም

አዎ አውቃለሁ

ስንት ቀን ታሰረ

እነዛ ወታደሮች ነው ይዘው ከእኛ ወስደው የሄዱት

ምን ያህል ጊዜ አሰሩት

ከ---ጋር ነው ይዘውት የሄዱት

ምን ያህል ጊዜ አሰሩት

አላውቅም

ኤው ኢብራሂም ሁሴን በጥርጣሬ ተይዞ ነበረ ብለህል ታሰረ እሺ ታሰረ ከእዛ በኋላስ ተሀድሶ ወስዶ መፈታቱን አታውቅም

ተጠርጥሮ ሳይሆን በግልፅ ይሄንን በደል ፈፅሟል ተብሎ የኦነግ ወታደሮች ውስጥ ገብቷል በማለት ታሰረ

ከእዛ

ኦነግ ወታደሮች ጋ ከገባ በኋላ በደል መፈፀሙን ነው እኔ የማውቀው ከእዛን በኋላ አላውቅም

ኤው ታስሮ ተሀድሶ መውሰዱን አታውቅም ወይ

ይሄ እንግዲህ ምስክር የዐ/ሕግ ምስክር ነው --- አይደለም --- በዋና ጥያቄ የተነሳ ነገርም አይደለም ሌላ ጥያቄ ይጠይቁ ከጨረሱ ደግሞ ያው ጥያቄው

በቃን በቃን

መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ አለ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

ድጋሚ ጥያቄ የለም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

895

ለፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

ማን ነው ጉዳቱን ማድረሱን አውቃለሁ ያልከው ማን ነው ጉዳት አድራሹ

ኢብራሂም ደሬሳ

ኢብራሂም ደሬሳ ምን ጉዳት ነው ያደረሰው ማን ላይ ነው ጉዳት ያደረሰው

የኦነግ ወታደሮች ይዞ በመምጣት ጦርነት ሲከፍቱብን ወደ አምስት ገደማ የሚሆኑ ሰዎች ከእኛ መሀል ሞቱ

በምን ሞቱ

በጥይት

ማን ገደላቸው

እሱ ከኦነግ ወታደሮች ይዞ እኛን እየፈለገ ነበር ይሄንን ነው የማውቀው

እሱ የኦነግ ወታደሮችን ማምጣቱ በምንድን ነው ያወከው

እኔም የዛ ሰፈር ትውልድ ነኝ እሱም የዛ ሰፈር ትውልድ ስለሆነ እዛ ነበርን የእከሌ ጥይት ነው ይሄንን ሰው የገደለው ብዬ ባላውቅም እሱ የኦነግ ወታደሮችን ይዞ ሲፈልገን ስለነበር ነው የማውቀው በፊትም የኦነግ ሴል ውስጥ ሆኖ እየሰራ ስለነበር ነው

ይፈልገናል ነበር ያልከው ማን ማንን ነው የሚፈልገው ምን ስለሆናችሁ ነው የምትፈለጉ የነበረው

እኛ የመንግስት ወታደሮች ነን ለዛ ነው የሚፈልጉን

ጨርሰሃል እናመሰግናለን

65ኛ ምስክር መሀዲ መሀመድ

እሺ ስንተኛ ምስክር ነው

65ኛ ምስክራችን ነው 1ኛ፣ 10ኛ፣ 14ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ላይ ነው ክሱ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 14ኛ ክስ ላይ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (stamp)

896

65ኛ ምስክር በ1ኛ፣ 10ኛ፣ 14ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ላይ ክስ 1 እስከ ክስ 3 እና ክስ 14 ላይ ነው ብለዋል እሺ. ጥሩት

65ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - መህዲ መሀመድ አብዱላሂ

እድሜ - 29

ሥራ - የመንግስት ሰራተኛ ፀሐፊ

አድራሻ- ምስራቅ ሐረርጌ ጎሎውዳ ወረዳ 01

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በምን ጉዳይ በነማን

ስለ ኦነጎች ወታደር የሆኑ ሰዎችና የእነሱ ፓርቲ የሆኑ ሰዎች ላይ ለመመስከር ነው የመጣሁት

እነማን ናቸው

አብዱረህማን ባሌ፣ ዙቤድ ሁሴን ሙመድ፣ ሌንጪሳ ------ ኢብራሂም ደሬሳ፣ ኢብራሂም ሁሴን፣ ከማል አሊዪ አህመድ፣ ፋጢሽ አሜ

አሁን የጠራካቸውን ሰዎች ታውቃቸዋለህ እዚህ ልታሳየን ትችላለህ ወይ

አዎ እችላለሁ

አሳየን

ከማል እና ፋጢሽ

ፈልጋቸው እሺ ምስክሩ 1ኛ፣ 5ኛ፣ 10ኛ፣ እና 14ኛ ተከሳሾችን ከበርካታ ተከሳሾች ለይቶ አውጥቷል 8ኛ ተከሳሽን ፈልጎ ሊያገኝ እንዳልቻለ ነው 8ኛ ተከሳሽ በህመም ምክንያት የሌሉ መሆኑ የተረጋገጠ ነገር ነው አሁን ያሳያካቸውን ሰዎች ፀብ ወይም ዝምድና አለህ ወይ

997

ምንም ዝምድናም ሆነ ጥልም የለኝም

የት ነው የምታውቃቸው እነሱን

አንድ ወረዳ አንድ ቀበሌ ውስጥ አብረን ነው የምንኖረው

ምን አድርገዋል እነዚህ

እነዚህ ሰዎች ከ1997 ጀምሮ እስከ 1991 የኦነግ ሴል የነበሩ ናቸው

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

አብዱረህማን ባሌ ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው

አሁን ጥያቄ አለኝ ቅድም እንደሰማን ከ1997 እስከ 1991 ስህተቴ እንዳልሆነ ለማስገንዘብ ነው

አብዱረሃማን ባሌ የኦነግ ጠንካራ የኦነግ ሴል ሆኖ ብር ሲያሰባስብ

ከማን ነው የሚያሰባስበው

ከሰዎች እያጠራቀመ እያሰባሰበ ሴልም

ገንዘቡን የሚሰበስበው ለማን ነው

ለኦነግ

ሰውስ የሚያደራጀው ለማን ነው ሰው እያደራጀ አልከን አደለ ሰው የሚያደራጀው ለማን ነው

በዚህ መንግስት አንተዳደርም ይሄንን መንግስት እንገለብጣለን በማለት ነው ሰዎቹን ያደራጀው

በምን

የእረብሻ ሰልፍም አውጥቶ ነበር

በምን ስር ነው የሚያስተዳድራቸው መንግስት እንገለብጣለን ብሎ የበላዩ መሪ ወይም በምን መጠሪያ ስም ነው

ለማን ነው የሚያደራጀው

898

ለማን ነው የሚያደራጀው ያንን ሰው ያደራጃል ብለሃል የሚደራጅበት አላማውን ነግረከናል ግን ለማን ነው እያደራጀ የሚያስተላልፈው ለማን ነው

ለኦነግ

ዙቤድ ሁሴንስ

እሱም በዚሁ በተመሳሳይ መልኩ የኦነግ ወታደር ነበር ተሀድሶ ወስዶ ገባ እሱ በዚሁ መልኩ ተሀድሶ ወስዶ ከመጣ በኋላ ከእንደገና የኦነግን ሴል ሆኖ ከእነሱ ውስጥ በመገኘቱ ነው ተይዞ የመጣው ቢራሳ ዶዩ የሚባለውን የመንግስት አካል የሆነውን በመግደል ነው ከዛን በኋላም አንድ ሽጉጥ ማክሮቭ የሚባል ሽጉጥም ከእሱ እጅ በፌደራል ወታደር ተቀምቷል ከኢብራሂም ጁንዲ ቤት ያንን ሽጉጥ የፌደራል ፖሊስ ተይዞ እሱን አስወስዷል

ከማልስ ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው

እሱ ሄዶ ወደ ሶማሊያ ክልል ሄዶ ስልጠና ወስዶ ነበር እሱ የኦነግ ካድሬ በመሆን ነው እኔ የማውቀው በዚህም መልኩ ከአብዱረሃማን ባሌ በተመሳሳይ መልኩ የረብሻ ሰልፍን አውጥቶ ነበር እሱም

የት አገር ነው የረብሻ ሰልፍ ያስወጣው

ጎሎውዳ ወረዳ ቀበሌ ቡርቃ ቀበሌ 01 ውስጥ እዛ ላይ ሰዎችን አውጥቶ መሳሪያ እንኳን ለመቀማት ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው

ከማን ነው መሳሪያ ሊቀሙ የነበረው

ከወታደር ታጥቆ የሚሄደውን ወታደር ለመቀማት

ከማን ወታደሮች ላይ

አሁን ለምሳሌ መሀዲ ከሚባል ሊቀሙት ነው

የማን ወታደር ናቸው

የመንግስት ወታደር

ሰልፉ አላማው ምን ነበር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

899

ሰላማዊ ሰልፍ የወጡበት ሰኣት ማለት ነው እንደመፈክር ሲሉ የነበሩት ነገር አለ

እስቲ ምንድን አንተ ንገረን ተርጉመህ

አንበሳ ጉድሩ ኦነግ የአገር አባት ምናምን የሚል ነው

በአማርኛ ግጥሙ ሲተረጎም ባለጉድሩ አንበሳ ኦነግ ወይም አባኦ ድሮም የእኛ እንደማለት ነው

ቀጣይም አለው

መንግስትን እንገለብጣለን

አንተ የቀረውን ነገር ተርጉም

ይሄንን መንግስት እንገለብጣለን

መቼ ነው

በ1998

ወሩን እና ቀኑን ታውቀዋለህ ወይ

ወሩን አላስታውስም

ጨርሰናል፡፡

ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ አለ

ለ1ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

በዚህ በፈጸምነው በደል ተማሪዎችን አወጣችሁ በማለት በፈጸምነው በደል ፍ/ቤት መቅረባችንን ታውቃለህ ወይስ አታውቅም

ተቃውሞ ምንድን ነው

አንደኛ በዋና ጥያቄ ላይ አላነሳነውም ሁለተኛ ነገር እንደገና ደግሞ በፍ/ቤት ቀርበው ተቀጥተው ነፃ ተብለው ከሆነ ይህ ማስረጃውን አቅርበው በመቃወሚያ ላይ ነፃ የሚባሉበት ነበር ያ ጉዳዩ ያለፈ ስለሆነ እዚህ ላይ መነሳቱ ተገቢ አይደለም ነው

እሺ ሌላ ጥያቄ ጠይቀው ተቃውሞውን ተቀብለናል በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ነው አማርኛውን ትተረጉማለህ እንዴ ማይኩን አትሰጠውም ጠይቀው በአማርኛ

ገንዘቡን ለቅመሃል ብለሃል እና ገንዘቡን ከማን ነው ብዛቱንስ ከማን ነው የለቀምነው

ብሩ በመጠን ብዙ ስለሆነ በቁጥር አላውቀውም ከህዝብ ነው የሰበሰባችሁት

ብዙ ብለሃል ስንት ነው ብዛቱ

ከ3 ሺህ በላይ ነው በወቅቱ የሰማሁት

ከ3 ሺህ በላይ መሆኑን በምን አወቅህ

በሂስ ክሌስ ሲናገሩ ነው የሰማሁትኝ

የራሳቸውን ሂስ ሲያደርጉ ነው የሰማሁት ብሏል ሌላ ጥያቄ

ራሳቸውን ሲያጋልጡ ሰምቻለሁ አልክ እና ብሩ ከማን ነው የለቀምነው እስቲ ሰዎቹን ስማቸውን ጥቀስልኝ ለማን ነው የሰጠነው ለማን ነው የላክነው

ስትናገር ነው የሰማሁት ብሏል እኮ አንተ ራስህ ስትናገር ነው የሰማሁት ሂስህን ስታወርድ ነው የሰማሁት ብሏል ስለዚህ እሱ ራሱ ነው የሚያውቀው ነው

ስራዬስ ምንድን ነው

መኪና ካሪ ነው የምትሰራው

ማን ነው ስምህ

ዙቤድ ሁሴን

ለ10ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

10ኛ ተከሳሽ ቁጥሬ 11 ነው

አዎ 11ኛ እሺ ለ11ኛ ተከሳሽ ዙቤድ ሁሴን መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ ቅድምም 10 ያላችሁት 11ኛ ነው ጭብጣችሁ 10ኛ ተከሳሽ የተባለው 11ኛ ተከሳሽ ነው የታይፒን ስህተት ነው 10 10 ሁለቴ የተባለው 11ኛ ተከሳሽ መሆኑ ነው እሺ ይቀጥሉ

ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

901

ለ11ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ፖሊስ ወይም የመንግስት ወታደር እኔን ይዞኝ ሽጉጡን ሲቀሙኝ በዛን ወቅት ታስሬ መሆኑን ታውቃለህ ወይ

ከእቃው ጋር ተይዞ መሄዱን ነው የማውቀው

የዛ ወረዳ ነዋሪ ነህ እና ያን ጊዜ ይዘውኝ ከሄዱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቼ ነው የተመለስኩት

አላውቅም ምን ያህል ጊዜ እንደቆየህ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ አለ የ11ኛ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል

ለ14ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ረብሻ አድርጓል እንደገና ደግሞ ብር አሰባስቧል ብለሃል አንተ በዛን ጊዜ ሚኒሻ ነበርክ በመንግስት ስር ተይዘናል ወይስ አልተያዝንም

በዛን ጊዜ አምልጣችሁ ወደ አነግ ሰራዊት ውስጥ ስለሄዳችሁ በዛ ነው የማውቀው

ተሀድሶ ወስጀ ተመለስኩኝ ተመልሼ ገባሁ ወይስ አልገባሁም

ተመልሰህ መግባትህን አውቃለሁ ግን ምን ወስደህ እንደመጣህ አላውቅም

ተሀድሶ መውሰድህን አላውቅም ብሏል ሌላ ጥያቄ ጨርሰሃል

አንተ ከምትለው ጫካ ነው ወይስ የመጣሁት ከአዲስ አበባ ከመንግስት እጅ ነው የመጣሁት አንተ እንደምትለው ከጫካ ነው ወይስ የመጣሁት ከአዲስ አበባ ነው ወይስ ታስሬ የመጣሁት

ከእስር ነው የመጣከው የት እንደታሰርክ ግን አላውቅም

እሺ ጨርሰዋል ሌላ ጥያቄ አለህ ከማል ጥያቄ የለህም እሺ 5ኛ ተከሳሽ የለኝም ብሏል ድጋሚ ጥያቄ አለ

ለዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ የምስክር መልስ

ከ3 ሺህ ብር በላይ ሰበሰብኩኝ ብሎ ሂስ ሲያወርድ ሰማሁት ያልከው ማንን ነው

ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ቁጥር 4 ከፍተኛው ፍ/ቤት የፌዴራል

እነሱ እንደ ፓርቲ ናቸው አጢሺ ቤት ነበር እየተቀመጡ ያሉት እዛ ነው የሰማሁት እነሱ አራቱም አንድ ስራ ነው የሚሰሩት

እና የሰማከው የት ነው

ጎሎውዳ ወረዳ

ጥያቄዬ ይሄንን ከ3 ሺህ ብር በላይ መሰብሰባቸውን ብር እንደሚሰበስቡ ያወከው እንዴት ነው

እነሱ በራሳቸው ይሄንን ሰራን ብለው ሲያወርዱ ነው የማውቀው እዚህ የምንመሰክረው የሰማነውንና ያየነውን ነው የምንመሰክረው

እዛ ቀበሌ ላይ ከመናገራቸው በፊት የሰማከው ነገር የለም ወይ ገንዘብ ስለመሰብሰባቸው

በቀበሌ ብቻ ሳይሆን ከየዞኑ ነው አንድ ላይ ሆነው በጥምር የሚሰሩት ብሩን የሚሰበስቡት

ይሄንን በፊት ታውቅ ነበር ወይ

አዎ አውቃለሁ የሰማሁት ነው ይሄ

መሰብሰባቸውን ነው በፊት የሰማከው

አዎ

ጨርሻለሁ፡፡

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የለም ጨርሰሃል እናመሰግናለን፡፡

33ኛ ምስክር በ62ኛ፣ 63ኛ

ስንተኛ ምስክር

33ኛ

ስንተኛ ተከሳሾች ላይ

በ62ኛ፣ 63ኛ፣ 64ኛ፣ 65ኛ እና በ66ኛ ተከሳሾች ላይ

ክስ ስንት ነው

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

35ኛ ክስ

የዐ/ህግ ምስክር

ሙሉ ስምህን

ስም - አህመድ መሀመድ ሁሴን

እድሜ - 36

ስራ - በፊት የኦነግ ወታደር ውስጥ ነበርኩኝ ከእዛ ታድሰዬን ወስጄ ጨርሼ አሁን ገብቼ እርሻዬን እያረስኩኝ ነው የምገኘው

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለ4 ሰው ምስክር ነው የመጣሁኝ

እነማን ናቸው

መሀመድ ኦጀባ ከሊፍ መሀመድ ሼካ አደረን ጉሼ ሰኢድ አደም

አሁን ያልካቸውን ሰዎች ልታሳየን ትችላለህ ወይ

አዎ

ፀብ ወይም ዝምድና አለህ ወይ

የለንም

የት ነው ይምታውቃቸው

እዛ ሚኖ ወረዳ ውስጥ ነው የማውቃቸው

እስቲ አሳየን

አሁን ያቆምከውን ስማቸውን ንገረን

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አደረን ጉሼ ከሊፍ መሀመድ ሼካ ሰኢድ አደም መሀመድ አጀባ

የሚባሉትን ተከሣሾች አሳይቷል አውጥቶ ለይቷቸዋል ማነው የሚቀርህ ያላሳየከን

እኔ የማውቀው አንድ ነው የቀረኝ

ማነው እሱ

መሀመድ ኑር አባ ቡሌ

ፈልገህ አሳየን እሺ ማንን ነው ያሳየከን አሁን

መሀመድ ኑር አባ ቡሌ

አሳይቷል ምን አድርገው እንደተከሰሱ ታውቃለህ

አዎ አውቃለሁ

ምን አደረጉ ተብሎ ነው

እኔ ያን ጊዜ ከኦነግ ወታደሮች ጋ ነበርኩኝ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

በ1998 ውስጥ ነው

አንተ በፊት ነበርኩኝ አሁን ተሀድሶ ሆኜ በሰላማዊ እኖራለሁ ብለከናል ቅድም እነሱስ ለምሳሌ እያንዳንዳቸው ምን ምን እንዳደረጉ እሱን ንገረን እና አንተ በሰላም እየኖርክ ነው እነሱ ምን ምን እንዳደረጉ ንገረን በለው

እኔ ያኔ አባዎ ውስጥ ኦነግ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ ነው የእነሱን ስራ የማውቀው

ንገረን እሱን

አንተም ኤውልህ አንተ ቆይ እሱ -- እየተናገረ እያቋረጠ ነው እየጠበቀ ነው ፖውዝ አድርጐ ልክ እሱ ሲያቋርጥ አንተ ትተረጉማለህ እንደዛ ሳይለ እሱ አያይዞ -- አንተ አጠቃለልክ እኮ እሱ አሁን ፖውዝ ነው ያደረገው እንጂ አልጨረሰውም እሱ ፖውዝ ሲያደርግ አንተም ፖዉዝ አድርግ አቁመው እሱ አቆመ እኮ አንተ ሌላ ስልጣን የለህም እሱ ሲያቆም አቁም

905

የምታጠቃልል ከሆነ እየቋጨህ ነው እየቆረጥከው ነው ይሄንን ደግሞ ብዙ ጊዜ እያደረክ ነው አሁንም እያየሁ ነው ስለዚህ እሱ አንተን እየጠበቀህ ነው አንተ ለምን ትደመድማለህ

ሀሳቡ ለምሳሌ እሱ ---እየሰራሁ ካለ የሚቀር ሀሳብ ነው ማለት ነው

እኔ እነሱ ኦነግ ነበርኩ እዛ ሳለሁ ጊዜ እያለ እየቆረጥክ ሳለሁ ጊዜ ብለህ ተርጉመህ ነው እሱን መጠበቅ ያለብህ እንጂ እኔ ኦነግ ነበርኩኝ ብለህ አይደለም ሳለሁ ጊዜ ካለ እሱ ቀጣይ ሊነግርህ ነው ለምን እንደዛ አትሄድም ትርጉም አልባ አደረከው ስራህን

እሺ

ስራህ እኮ በጣም እንትን ማድረግ አለብህ እሺ

አንተ እዛ የኦነግ ወታደር በነበርክበት ጊዜ እነሱ

በዝርዝር ንገረን እያሉት ነው እሱ የሆነ ቦታ ላይ እያቋረጠ እየተናገረ ነው አንተም እሱ እየተናገረ ያለውን

እነሱ ምን ምን ማድረጋቸውን ነው ንገረን

----እንዳትሄድ ነግሬካለሁ

እነሱ በእዛን ጊዜ የአካባቢው ሊቀመንበር ነበሩ አህመድ ኑር አህመድ ቡሌ ውጪ ሌሎቹ ሊቀመንበር ነበሩ የአራት ቀበሌ ሊቀመንበር ነበሩ ማህመድ አጀባ የእዛ ከተማ ሊቀመንበር ነበረ የመንግስት አደራሽ ራሽን የሚቀመጥበት መጋዘን ቁልፉን የያዘ እሱ ነበረ በእዛን ጊዜ ነው እኛ አሊ ከሚባለው እየመጣን ነበረ ሚኖ ከምሽቱ 2:00 ሰአት ገባን በእዛ ወቅት እነዚህ ሊቀመንበሮች ሰበሰብናቸው በእዛን ጊዜ መሀመድ አጀባ ጋ ሆነን ሊቀመንበሮቹን አሰባስበን የእኛ የኦነግ ሰብሳቢ የነበረው አንድ ላይ አማከርናቸው በእዛን ጊዜ የእኛ ከፊታችን ያሉት እንደ ---መሪ የሆኑት ያነጋገሯቸው ኦብሳ ሌንጮ፣ ፋርጋስ ቀጀላ 2ቱ ነው እነሱን ያመካከሩት በእዛው ከተማ ላይ እኔ በእዛን ጊዜ ከእነሱ ዋርድያ እየጠበኩኝ ነው በጆሮዬ የሰማሁት በእዛን ጊዜ አዲስ ልጆች ወደ ስልጠና የምንወስዳቸው እኛ ሬጋ ሰላም እናንበ የኦሮሞ ልጆች እስከሆናችሁ ድረስ ይሄን የመንግስት እህል ቁልፉን ስለያዛችሁ አምስት ባለ 50 ኪሎ ግራም እገዛ እንደታደርጉልን በእዛን ጊዜ መሀመድ አጀባ ቁልፉን ይዞ ነበረ ቤቱን ከፍቶ ወይም አዳራሹን ከፍቶ 5 ሐምሳ ኪሎ ግራም እህል ሰጠ 5ቱን 50 ኪሎ ግራሙን ሲሰጠን ወስደን ሄድን እኛ ከእዛ ሄደን

908

ሀረቦረኒ የምትባል አካባቢ እዛ ላይ ነው መሀመድ አጀባ ተከትሎን መጣ እኛን ተከትሎ በመጣ ጊዜ ጫት እና የባትሪድንጋይ እና ሳሙና ይዞ ገዝቶ መጣ ኢንፎርሜሽንም ከመንግስት ወታደሮች ላይ እያቀበለን ነበረ ይዞልን እየመጣ ነበረ እኔ ከመሀመድ አጀባ በኩል ይሄንን ነው የማውቀው በአይኔም ያየሁት ይሄንን ነው የሰማሁትም ይሄው ነው

ከሊፍ መሀመድስ

ከሊፍም ያንን 5ቱን 50 ኪሎ ግራም እህል ሲሰጠን አብሮ ነበረ ስብሰባውን አንድ ላይ ነው ያካሄድነው ያንን ውይይት አብረን ማካሄዳችንን ነው እሱ ላይ የማዉቀው

ሰኢድ አደምስ

ሰኢድም በውይይቱ ጊዜ ውይይቱን ስናደርግ ከእኛ ጋ አብሮ ነበረ እሱላይ ከእዛም በኂላ የማውቀው ነገር የለኝም በውይይቱ ጊዜ አንድ ላይ ነበርን መሀመድ ኑር አ-- ደግሞ ሚኒሻ ነበረ እሱ በእዛን ጊዜ ከእኛ በስተቀር የመንግስት ወታደር እዞ ቦታ አልነበረም እኛ እዛ ሚኖ ከተማ ገባን የኦነግ አስተዳደሮች

ጠይቀው ባለቃሉን ጠይቀው እሱ ጋ ነው እሱ ከነገረህ እሱ ጋ ለምን ታያለህ ምንድነው ያልከው ብለህ እሱን የተናገረውን ጠይቀው ካልገባህ እኮ ይነግርሀል እንደገና ሬዲዮ አይደለም አንዴ የሚያልፍህ ደግመህ ጠይቀው

እሺ እጠይቀዋለሁ

ካልተረዳህ ማለት ነው የእራስህን ትርጉም እንዳትናገር እኔ ---

የእራሴን ትርጉም ሳይሆን ሄድ ማለት ብዬ ነው እኮ የጠየኩት

ሄድ ማለት ምንድነው

እሺ ጠይቀው

የኦነግ አመራሮች የነበሩት ወረቀት ፅፈው መሀመድ ኑር አህመድ ቡሌን ወረት ፅፈው ላኩለት እሱ በእዛን ጊዜ የመንግስት ሚኒሻ ነበረ በሰላም በኩል ወታደር ውስጥ ሳትቀመጥ መሳሪያህን ይዘህ ወደ ላሞች ወደ እንስሶችህ ሂድ አሉት እሱ ወደ እኛ ሳይመጣ በፊት እኛ ሚኖ ከተማ አቋርጠን ስንሄድ ለወረቀቱ መልስ ሳይሰጠን ሳያደርግልን የመንግስት ወታደሮች ሚኖ ከተማን

907

መጥተው ገቡ እሱ መሳሪያውን ይዞ የመንግስትን ወታደሮች እየሸሸ እያለ ኡቱዬ የሚባል ወንዝ ላይ ውሀ እየቀዳን እያለ ወደ እኛ መጥቶ አማራዎች መጥተው ከተማ ይዘዋል እኔ በበኩሌ ሸሸሁኝ እናንተም ይሄንን ---- ስሙ ብሎ ነገረን ይሄንኑ ነው በእሱ ላይ የማውቀው

ማን ላይ ነው ይሄንን የምታውቀው

መሀመድ ኑር አባቡሌ

እሺ ይቀጥሉ

አድና ጉሽስ ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው

የኢጀቡርቃ ሊቀመንበር ስለነበረ ስለ እህሉ ውይይት ውስጥ ቡርቃ ነጋያ ቀበሌ ላይ ሊቀመንበር ስለነበረ ስለ እህሉ ውይይት ውስጥ ነበረ በመሪነት እነሱ ያንን እህል ሲሰጡን ነው እሱን የማውቀው ይሄንን ነው እሱ ላይ የማውቀው

ከሊፍ መሀመድ የየት ቀበሌ ሊቀመንበር ነበረ የእዛን ጊዜ

የሩቃ ቀበሌ ሊቀመንበር ነበረ

ሰኢድ አደምስ

የኢጀጉዳ ሊቀመንበር ነበረ

አድና ---

የቡርቃነገያ ቀበሌ ሊቀመንበር ነበረ አደናን ጉሼ

መሀመድ አብጀባስ

የሚኖ ሊቀመንበር ነበረ የከተማ

ታዲያ እኚህ ያልከን የተለያዩ የ4 ቀበሌ ሊቀመንበሮች በጋራ ነው የሰጧችሁ ወይንስ እንዴት ነው የሰጧችሁ ይሄንን ነገር

አንድ ላይ ሆነው እያሉ ከተማ ውስጥ አንድ ላይ ሄደን ያዝናቸው እኛ አንድ ላይ አሰባስበን አመካከርናቸው እኔ በእዛን ጊዜ ጥበቃ ወይንም ዋርድያ እየጠበኩላቸው ነበረ

የፌ/ዴ/ሪ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ስንት ሰአት ላይ ነበረ ጊዜው

ከምሽቱ 2:00 ሰአት ጀምሮ እስከ 5:00 ሰአት አወያየናቸው 6 ሰአት ላይ ደግሞ እህሉን ከእቤቱ አወጡልን እና እህሉን አስረን 5ቱንም 50 ኩሎ ግራሙ በጀርባችን ታስረን ከእዛ ሄደን ወደ ጫካ ሄድን ገባን

ይሄ መቼ ነው ወሩ ቀኑ አመተ ምህረቱ

ወሩን ግን አላስታውስም በ1998

ሌላ ጥያቄ

ከሚኖ ቀበሌ ማህበር ገበሬ ማህበር መጋዘን ውጪ ከሌሎቹ ቀበሌ ገበሬ ማህበር መጋዘንስ የወጣ ነበረ ወይ

የለም አላስታውስም

ጨርሰናል

ዋና ጥያቄ አብቅቷል ስንተኛ እና ስንተኛ ተከሣሽ --ለ63ኛ እና

4ቱም ላይ

እሺ ለ4ቱም ተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ ይጠይቁ

ለ4 ተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ቅድም ስትናገር 4ቱንም ተከሣሾች አንድ ላይ ከተማ ውስጥ ያዝናቸው አልክ እነዚህን ሰዎች ስትይዟቸው በምን ሁኔታ ላይ ነበረ የያዛቹሀቸው በማስገደድ ነው ማለት መሳሪያ ይዛችሁ አስገድዳችሁ ነው ያስገባቹሀቸው ወይንስ በፍላጐታቸው ነው የመጡላችሁ

በፍላጐት ላይ ተስማምተን ነው

አንተ እነዚህ ሰዎች ስንመካከር እኔ ዋርድያ እየጠበኩ ነው ብለሀል

የእኛን አዛገሮች ዋርድያ እየጠበኩኝ ነው እነሱን

909

እነሱን ያነጋገሯቸው ያንተ አዛዦች ናቸው ወይንስ አንተም እዛ ቦታ ወስጥ ከእነሱ ስብሰባ ጋ ነበርክ ወይ በለው እቤት ውስጥ ነው ውጪ በለው

እኔ ከእነሱ ትንሽ ወደ እዛ እራቅ ብዬ ቆሜ እየጠበኩኝ ነበረ እነሱ የሆነ ጥላ ስር ተቀምጠው እየተወያዩ ነበረ ግን በጆሮዬ እሰማለሁ

ቤት ውስጥ ነው ወይንስ ውጪ በለው

የሆነ ትንሽ ቤት ውስጥ ነው

አንተ ከቤቱ የት ባታ ላይ ነበርክ በለው ወይ ምን ያህል እርቀህ ነበረ

ከእዚህ ከተቀመጥኩበት የውጪ ግርግዳ አሳይቶ እስከ እዛ ያህል ነው የምንርቀው

በግምት ግምቱን

እሺ በግምት ---ፖሊስ

አሁን ካለንበት ያችን ግርግዳ እያለ ነው

5 ሜትር 5 ሜትር ይሆናል እርቀቱ

ይበልጣል ከ5 ሜትር ይበልጣል

እ

5 ሜትር ይበልጣል

-----ይችላል

5 6

ከ5 እስከ 10 ሜትር --

ከ5 እስከ 10 ሜትር

እሺ አንተ ከ5 እስከ 10 ሜትር በግምት የሚሆን ቦታ ላይ ቆመህ እነሱን ትንሽ እቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ይመካከሩ ነበረ ብለህ ትንሽ እቤት ውስጥ እነሱ ቁጭ ብለው ይማከሩ ነበረ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

910

ብለሀል እነሱ ሲመካከሩ የነበሩትን ነገር አስገድደዋቸው ይሁን ወይንም በፍላጐታቸው ያንን ነገር ስለመፈፀማቸው እንዴት አወቅህ ወይንስ ግምትህን ነው የምትናገረው በለው

እኔ የግምቴን ሳይሆን አንድ ጊዜ ከምጠብቅበት ቦታ ወደ እነሱ እየመጣሁ አንዴም ወደ ምጠብቅበት እየተመለስኩኝ ነው እያዳመጥኩ የነበረው የግምቴን አይደለም የዋርድያ ስራ የዋርድያ ጥበቃ ዋርድያ ጥበቃ ላይ እንደፈለክ እየተንቀሳቀስክ መጠበቅ ከቻልክ አካባቢው ሌላ የምትሰጋበት ነገር አልነበረም ወይ

እኛ ስለ አካባቢ ስጋት አላስመሰከርንም እኮ ክቡር ፍ/ቤት አካባቢውን ያሰጋል ነበረ ወይ አያሰጋም ነበር አላስመሰከረንም

ለተቃውሞ መልሳችን --

ጥበቃ ስለተባለ እንግዲህ በወቅቱ ጥበቃ ምን ስለሚጠብቅ ምን ስለሚዘጋ መሆኑ በአንድም በሌላ ከዋና ጥያቄ ጋ የተቆራኘ ነው ስለዚህ ተቃውሞውን አልተቀበልንም ይጠይቁ

የመንግስት ወታደሮች ወደ ወረዳ ስለሄዱ ማ--- የሚመራው እዛ አካባቢ ከእኛ በላይ ደግሞ የኦነግ ወታደሮች ቦታውን ይዘው ስለነበረ የምንፈራው የለም

ቁልፉን ከማን ነው ያገኘከው ከማን ወሰድክ በለው

እሱ በእዛን ጊዜ የመንግስት ሰራተኛ ነበረ በእዛኑ ጊዜ ነው የእኛ አባል የገባው እንጂ እኔ የኦነግ ወታደር ስለሆንኩኝ ከማን ይቀበል ከማን ያግኝ አላውቅም

የመንግስት ሰራተኛ ስትል በህዝብ ተመራጭ ነው ወይንስ የመንግስት ሰራተኛ በመደበኛ ቢሮ ውስጥ የሚሰራ ነው ይሄንን ለይተህ ተናገር በለው

ህብረተሰቡ በእሱ ላይ እምነት ጥሎ ቁልፉንም ሰጥቶ ይሄንን መጋዘኑን ጠብቅ ብለው እንደ አደራ ነው የሰጡት

መጋዘኑ የእራሱ ጠባቂ የለውም ወይ በለው

በወቅቱ የለውም የሚጠብቀውም እሱ ነው

እሺ

911

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሜ ጥያቄ አለ

የለንም

የለንም ተብሏል

ለፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

አንተ በወቅቱ የአነግ ወታደር መሆንህን ነግረከናል ነግረከናል አይደል

አዎ

እነዚህ አሁን የጠራካቸውን ሰብስበን አንድ ላይ አንድ ላይ ነበሩ አወያየናቸው ብለካል

አዎ

ውይይት ስናደርግ እኔ ጥበቃ አደርግ ነበር ሀለቃዬም ያወያያቸዋል ብለህ ነበረ

አዎ

የእዛኔውኑ እንዳወያያችሁ ነው እህሉ የተሰጣችሁ ወይንስ ሌላ ጊዜ ነው በተወያያችሁ ሁኔታ እህሉ የተሰጣችሁ

በእዛኑ ጊዜ ልንሄድ ስንል 6 ሰአት ላይ ነው የተሰጠን እህሉ

ስንት ሆናችሁ ነው ያወያያችሁ ከአነግ

የእኛ አዛዥ 2 እና 12 ወታደሮች ነበሩ አንድ ላይ 17 ሰው ነን

17 ሆናችሁ ነው ይሄንን ያወያያችሁት

አዎ

እንዴት እዛ ጋ 4ቱም የተለያዩ ቀበሌ ሊቀመንበር እንደሆኑ ገልፀሀል ምንድነው በእዛን ሰአት 2 ሰአት ምሽት 2 ሰአት ላይ አንድ ላይ የሰበሰባቸው እንዴት ነው የተሰበሰቡት ድንገት አጊኝታችሁ ነው ወይንስ ጠርታችሁ ሰብስባችሁ ነው ወይንስ በምን ሁኔታ ነው ምሽት ላይ እዛ ሊሰበሰቡ የቻሉት የቻላችሁት በማታ 2 ሰአት

912

እኛ ምንም የምናውቀው ነገር የለም በወቅቱ ሄድን መጣን ከእዛ በፊትም እየሄድን መጣን ከእዛ በፊትም የላክንባቸውም የለም እነሱም የእኛን አመጣጥ አያውቁም ነበረ ለእራሳቸው ውይይት ይመስለኛል እዛ የተሰበሰቡት እዛው ነው የያዝናቸው

እኮ አስረድዳችሁ ነው ወይንስ አሁን እነዚህን 4ቱን አስገድዳችሁ የኦነግ ወታደር ስለሆናችሁ አስገድዳችሁ በመሳሪያ ነው ወይንስ እራሳቸውም ፈቅደው ፈልገው ነው ይሄንን ውይይታቸውን ያወያዩት ወይንስ እህሉንም የሰጧችሁ በፍቃድ ነው ወይንስ የሀይል ነገር የማስገደድ ነገር ነበረ በየትኛው መልኩ

እኛ በእዛን ጊዜ ምንም ያስገደድናቸው ነገር የለም አላስገደድናቸውም ጠየቅን እና እናንተ የመንግስትን አደራሽ ቁልፍ ስለያዛችሁ እህል ስጡን ብለን ስንጠይቃቸው አብረን አንድ ላይ ሆነን የእኛ መሪዎች አወያይተው ከእዛን በኋላ እህል ሰጡን

እሺ የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ አብቅቷል ጨርሰሀል እናመሰግናለን

ከሰዓት በኋላ 9፡00 ሰኣት ትመጣላችሁ ከሰዓት እንሰማችኋለን ምስክሮቻችሁን እንግዲህ ማኔጅ አድርጉ ራሳችሁ

ከቆምንበት እንቀጥላለን ሰኔ 8 ከሰዓት በኋላ

የመ/ቁ. - 04486

ቀን - ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ/ም

ዳኞች - ብርሃነ መስቀል ወጋሪ

- ይርጋ አይቼህ

- እልፍነሽ ወሌሮ

ከሳሽ - ዐ/ህግ ማሙሸት አበበ፣ አረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጠዋት የቀረቡት ቀርበዋል

ቀሪ ምስክሮችን መስማት እንቀጥላለን ማን ነው የሚሰማላችሁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

913

32ኛ ምስክር መሀመድ ሀሰን

ስንተኛ ስንተኛ ተከሳሽ ላይ

በ63 እና በ67ኛ

ስንተኛ ክስ

በ35 እና በ38ኛ ክስ

እንደክሱ ነው ወይስ የተለየ ጭብጥ የምታስመዘግቡት አለ

የተለየ የለንም

እሺ ጥሩት ምስክሩን

32ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - መሀመድ ሀሰን ዩሱፍ

እድሜ - 45

ስራ - አናፂ

አድራሻ- ቡርቃ ጎሎዳ ራሱን የቻለ ወረዳ ነው 01 ቀበሌ ምስራቅ ሐረርጌ የቤት ቁጥር የለም

አማርኛ ይችላሉ አይደለም

ትንሽ ትንሽ ነው

ዛሬ ለምን መጡ

ዛሬ የመጣሁበት ምክንያት ኒሮ የሚባል አሁን ወረዳ ሆኗል በዛን ቀን ዞን ነበር ለስራ እዛው እንደሄድኩ

ለምስክርነት ነው የመጡት

አዎ

914

እነማን ላይ ነው ሊመሰክሩ የመጡት

አብራሂም አብዱላ ዋሪሮ፣ አድናን ጎሼ፣

ሌላስ

ያው አብራሂም አብዱላ ነው

አሁን እነዚህ የጠሯቸውን ቢያዩ እዚህ ያውቋቸዋል

እና ነገርየው እንግዲህ

ያውቋቸዋል ወይ

እንግዲህ የቆየ ነገር ስለሆነ በስም እንዲጠራልኝ እፈልጋለሁ አውቃቸዋለሁ ሳይ

ስታዩ ያውቃሉ

አዎ

ፀብ ዝምድና አሎት

ምንም የለንም

እስኪ እርሶ መጀመሪያ ከዚህ ቁጭ ካሉት ከተከሳሾቹ ማን ማን እንደሆነ ይለዩልን ቀስ ብለው ይዩዋቸው ዞረው እዩ ውስጥ ገብተው አሁን ምስክሩ የጠሩዋችሁ ሰዎች እጃችሁን አውጡ እርሶ እንዳይዞሩ ወደ ኋላ ተነሱ አንድ ጊዜ አሁን ከዚህ መደዳ ጀምሮ ማለት ነው ከዚህ መደዳ ውስጥ ፈልጓቸው እሺ ማን ነው ስምህ

አድናንን ምስክሩ አሳይቷል ሌሎቹ አሁን ካላየኋቸው ልለያቸው አልችልም በዛን ጊዜም እንግዳ ነኝ ብለዋል አሁን ስማቸውን የጠሩዋቸውን ፀብ ወይ ዝምድና አሎት

የለንም

ምን አድርገው እንደተከሰሱ ያውቃሉ

ያኔ በ2000 ዓ/ም ውስጥ በኦነግ ሰራዊት ጋር ተቀላቅለው ስላሉ እዛ ከእነሱ ጋር እንትን እያሉ እኛም ለስራ እንደሄድን በ2001 እዛ ታስረው እኛም እዛ ደረስን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

9/5

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

አቶ መሀመድ እስቲ ያን ጊዜ ያዩትና የሰሙት ነገር ለዚህ ችሎት አስተዱልን መጀመሪያ አቶ ኢብራሂም

በዛን ቀን ከስር ቤት ወጥተው ደግሞ የፖሊስ ጣቢያ የመጡት ሰራዊቶች ሲመረምሯቸው እኛም እዛ ነበርን እንግዲህ ለታዛቢነት ጠርተውን እኛም ተቀምጠናል እዛ እና እኛ በዛው ጋ 2000 ዓ/ም ውስጥ አቶ ኢብሳ ሌንጮ አርያ ዳዲን ከለሊቱ በ11፡00 ሰኣት እስከ እኔ ቤት አምጥቶ ይሄንን ሰውዬ ወንድሜ ነውና እስከ ቦኬ ድረስ ሸኝልኝ ብሎ እኔ እሱን ይዤ ወንዙን እና ጫካውን ሁሉ ተሻግሬ ውሃ መዋኘት ስለምችል እሱን ወደ ማዶ ወደ ቦኬ አውጥቼ ተመልሻለሁ የጠላታችን ሃላፊ መሆኑንና ጠላት መሆኑን ከዛን በኋላ እኔም ተረድቼዋለሁ ስለዚህ ይህ ነገር በአሁኑ ጊዜ ውስጥ ጥፋቴ መሆኑን ከራሴ ጀምሮ አውቃለሁ ብሎ ቃል መስጠቱን ነው የማውቀው

በወቅቱ ማለት ነው ይሄ ማነው ሌንጮ ያልከው ምንድን ነው እሱ

የቱ

ኢብሳ ሌንጮ

የኦነግ ሃላፊ ነው እሱ --------- ለእሱ የሰጠው ለኢብራሂም የሰጠው

ስንት ሰዎች ናቸው

እንግዲህ አሁን አንደኛውን አውቃለሁ ሁለተኛውን እንኳን እዛው ጠቅሶ ነበር ያው እንግዲህ መሀመድ ማን ነው እንግዲህ

የአባቱን ስም አያስታውሱትም

መሀመድ ሀጂ ዳዲ

ወዴት ነው የወሰዷቸው ነው የተባለው

ወደ ቦኬ

ቦኬ ማለት የት አካባቢ ነው

916

ቦሌ እንግዲህ ከዛው ሚኖ አቅጣጫ እንግዲህ ወንዙን ገብቶ ጫካውን አቋርጠው ወንዙን ገብተው ወደ ቦሌ ማሽጋገሪያ መንገድ ላይ ነው

ሰዎቹ መንገዱን አያውቁትም ማለት ነው

እንግዲህ አላውቅም እንደዛ ተብዬ ነው ያሻገርኩት ነው ያለው ያላቸው

አግናን ጎሽስ ምንድን ነው ያደረገው

አግናን ጎሽ የኦነግ ሰራዊት በዛን ቀን እኔ ከብቶቼ በረት ላይ ነው ከብቶቼን እዛ ለመጠበቅ እንዳለሁ እዛ ተሰብስበው መጡብኝ ሁለት ሰራዊቶች ሲመጡ በዛን ጊዜ ምሳችንን ምናችንን ሁሉ አቅርብልን ብለው ያንን ያለኝን እህል ለእነሱ ገንፎ ቀቅዬ ያለኝን ጨምሬበት ሰጥቻቸው አስተናግጄ መሸኘቴ እርግጥ ነው አላቸው በየት ነው ቢባል በራሚስ አካባቢ ሸኝቻቸዋለሁ

መቼ አመተ ምህረት ነው ይሄንን ያደረኩት አለ

በ2000 ዓ/ም ቃሉን የሰጠበት በ2001 ነው

ያን ጊዜ ይሄንን ቃላቸውን ሲሰጡ በምን ሁኔታ ላይ ነበሩ ተገደው ነው ወይስ ፈልገው ነው

አልተገደዱም በፍቃደኝነታቸው እንደተጠሩ ቁጭ ብለው እኛም ባለንበት ቃላቸውን ሰጥተው ጥፋታቸውንም እንደዛው እዛ ላይ ማመናቸውን ነው የምናውቀው

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥሉ

የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ከየት መጡ እነዚህ ሰዎች ቃል ለመስጠት ከየት መጡ

አሁን ነው

የዛን ጊዜ

እዛው አካባቢ መ/ቤታቸው እንግዲህ እዛ ግቢ ስላለ

የማን መ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

9/7

የአረዳው እና የማህበሩ እስር ቤት አለ አይደለም እዛ እንግዲህ ሰብስቧቸው ጥፋተኞች ተሰብስበው እንዳሉ ከዛ እያወጡ ቃል ሲጠይቁ ነው እኛም እዛ ስራ ሄደን የተገናኘነው

በራሳችሁ ፈቃድ ነው ወይ የምትሰጡት ብላችሁ ጠየቃችኋቸው

አዎ ጠይቀናቸዋል እንዲህ ይሄ ነገር እንደዚህ አላችሁ ትክክለኛ ፍቃዳችን ነው የሰራነው ስራ ስለሆነ ምንም እንትን የምንክድበት ነገር የለም ጥፋታችን ነው ብለው አምነዋል

ይበቃል፡፡

ድጋሚ ጥያቄ የለንም ብለዋል

ለፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

ጥፋታችን ነው ብሎ ማን ማን ነው ያመነው

ያው እዚህ አብራሂም አብደላ እና ይሄ ማን ነው አድናን

ስንት ሰኣት ላይ ነው ይሄንን ያመኑት

ከ6፡00 ሰኣት እስከ 7፡00 ሰኣት ድረስ እዛ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው እስከ 7፡00 ሰኣት ድረስ ተቀምጠው መልሰዋል

የት ጋ ነው ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው

ሚኖ ላይ

ሚኖ ምን መስሪያ ቤት

እንግዲህ ሚኖ በዞን ነበር በቡርቃ ስር የሚተዳደር ነበር አሁን ራሱ ወረዳ ሆኗል ያን ጊዜ ዞን ነው

እኮ የምን መ/ቤት ላይ ነው ይሄንን እምነት ቃላቸውን የሰጡት

ቀበሌ አለ አይደለም እዛ ላይ የሚሰራ የማህበር ቀበሌ እዛ ላይ እንደተሰሩ ነው

ህዝብ ፊት ስብሰባ ላይ ነው ወይስ ፖሊስ ጣቢያ ነው ወይስ ቀበሌ ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

918

ፖሊስ ጣቢያ ከፖሊስ ጣቢያ አመራሮቹ መጥተው በፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት እዛ ቤቱን ይዘው እንደተቀመጡ ነው በፖሊስ ጣቢያ ላይ ወታደሩ ላይ ቃል የሰጡት

እርሶ ነበሩ

እኛም እዛ ነበርን

አግናን የተባለው ሰው ሲናገሩ የኦነግ ሰራዊቶችን አብልቼ ሸኝቻለሁ ነው ያሉት

እሱ እንዳለው የኦነግ ሰራዊት እስከ 6 ሰው እዛ ከብቶቼ በረት ላይ እኔ ከብቶቼን በመጠበቅ ላይ እንዳለሁ እዛ ቤቴ ድረስ መጥቶ ምግብ ስጠን ብለውኝ ያንን ምግብ ያለኝም አብስዬ ያለኝን ጨምሬበት እነሱን አስተናግጄ ሸኘኋቸው

ማለት አስገደዱኝ አሉ በፍቃዴ ነው የጋበዝኳቸው አሉ

በፍቃደኝነቴ ነው መጡብኝ ስጡን ብለው ስለጠየቁኝ እኔም ሰጠኋቸው በፍቃደኝነቴ

እና ጥፋቴ ነው ብለው ሲናገሩ ነበር

አዎ እንግዲህ እነሱ ምንም ሳልል መግቤ መሸኘቴ ጠላት ስለሆኑ ጥፋቴ ነው

አቶ ኢብራሂም አብደላ የተባሉት ሰው አላወኳቸውም ነበር ሸኚልኝ የተባሉትን ኢብሳ ሌንጮ ነው ሸኝልኝ ያለኝን ሰዎች ጠላቴ መሆናቸውን ሳላውቅ ሸኝቻለሁ ብለው ሲናገሩ ነበር ብለዋል አደለም

አዎ በመጀመሪያ ሲሰጠኝ ወንድሜ ነው ብሎ ነው አሻግርልኝ ሼካ ነው ብሎ ሰጠኝ

እና በዚህ እሳቸው ቃል ሲሰጡ እርሶ ሲሰሙ ማለት ነው ጥፋቴ ነው ይሉ ነበር

እንግዲህ ከዛ በኋላ እሱ ነው ያለው ከዛ ስመለስ ያ ሰውዬ የጠላት ሃላፊ መሆኑን ከተመለስኩ ነው የሰማሁት

የሸኘኋቸው ሰዎች

ጠላት መሆኑን እዛ ቀበሌያችን ስመለስ ነው የሰማሁት እና ያወኩት ሼካ መሆኑን ሼካ ሸኝቼው እኔ እንኳን ልጆቼን እልካለሁ ብዬ ደስ ሲለኝ ስመጣ ደግሞ ጠላት መሆኑን ገባኝ ነው

919

እናመሰግናለን ጨርሰዋል

31ኛ አሊዪ ሼካ

ስንተኛ ተከሳሽ ላይ

በ43 እና 64ኛ

ስንተኛ ክስ ነው

በ37 እና በ25ኛ

33ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አሊዪ ሼካ አህመድ ራቦ

እድሜ - 22

ሥራ - ሚኒሻ

አድራሻ- ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ቁንቢ ወረዳ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

በነማን ጉዳይ

አህመድ ኡስማኤል እና መሀመድ ኑር

ታውቃቸዋለህ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ፀብ ወይ ዝምድና አለህ

የለኝም

ምን አድርጎ እንደተከሰሰ ታውቃለህ

920

አዎ ሃሳባቸውን ሲቀበሉ ሰማሁ

እስቲ አሳየን እነሱ አሁን የምትላቸውን ከዚህ ውስጥ አውጣቸው ስማችሁን አህመድ ኡስማኤል፣ መሀመድ ኑር አህመድን አሳይቷል

ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

አሊዩ እስቲ ስለ እነሱ የምታውቀውን ነገር መጀመሪያ መሀመድ ኑር ጀምረህ አስረዳልን ለፍ/ቤቱ

መሀመድ ኑር አህመድ ቡሌ ሲል የሰማሁት ሚኖ ውስጥ ኦንጅባ የሚባለውን ወስዶኝ ሀሮቦረኒ ኡብሳ ሌንጮ የሚባል ጋ ወሰደኝና ኦብሳ ሌንጮ አንተ ሚኒሻ ነህ አትፈልገን ምግብና ወተት ምናምን ከሰፈር ውስጥ ሰብስብልን አለኝ እኛ ስለማንፈልጋችሁ አትንኩን ስለዚህ በፖለቲካ አደራጅተውን ስላለሁ ለዚህ ነው የተደራጀሁት ብሎ ሲናገር ሰማሁት ይሄንኑ ነው ከእሱ የሰማሁት

ምግብን በተመለከተ አምጣ አለኝ እየሰበሰብክ ከከተማ ብሎ ነበር እና አደራጅቶን ነበር ምግብም እርዳታ አድርጉልን ብሎ ነበር እና በምግብ ረዷቸው ወይስ እንዴት ነበር ከዛ በኋላ የሆነው

በምግብ በኩል ረዳሁኝ ብሎ ተናግሯል

መቼ ነበር ይሄ የሆነው አመተ ምህረቱን ንገረን

በ2002 ድምጽ የሰጡበት ወይም ቃላቸውን የሰጡበት ቀን በ2001 ነው

ድርጊቱ የተፈጸመው መቼ ነው ቃላቸውን ከሰጡ በኋላ ነው ወይስ በፊት ነው ግልጽ አድርገው

ቃላቸውን ሳይሰጡ በፊት ነው

ስለዚህ ቃላቸውን የሰጡት 2001 ነው ብለሃል ይሄ ነገር መቼ ነው የሆነው

2001 አላለም ምስክሩ

አለ ቅድም ሲናገር 2002 አደረጉት አለ ቃላቸውን የሰጡት ግን 2001 ላይ ነው አለ አሁን ቃላቸውን ነው መጀመሪያ የሰጡት ወይስ ድርጊቱ ነው የተፈጸመው ብለን ስንጠይቀው አይ

921

ድርጊቱን ከፈጸሙ በኋላ ነው ቃላቸውን የሰጡት አለ ያ ከሆነ ቃላቸውን የሰጡት 2001 ነው ያኛውስ መቼ ነው

ጠይቁት በጥያቄ አድርጉት 2001 መቼ ነው ቃል የሰጡት መቼ ነው ድርጊቱን ያከናወኑት ብለው አስታውሷቸው

ድርጊቱን ያደረጉት በ2000 ነው ድምፃቸውን ቃላቸውን የሰጡት ግን 2001 ነው

ቦታው የት ነው

ቃል የሰጡበት

ሚኖ

ሚኖ የት ቦታ ነው

የወረዳ ከተማ ነች

ለማን ነው ቃላቸውን የሰጡት

ለፖሊሶች

እስቲ ደግሞ አሁን የአህመድ ኡስማኤልን ንገረን

አህመድ ኡስማኤል የራሚስ ወንዝ ውስጥ አባኖ ኦነግ መጣብን ብሎ ሲናገር ነው ከብቶች ስጡን አሉኝ እዛ መጥቶብኝ አንድ ቁስለኛ ስላለ ላም ስጠን አሉ ሌላ ላሞች የለኝም ብር 500 ብር ሰጠሁ እህልና ወተትም ከሰፈር ውስጥ በመሰብሰብ ሰጠኋቸው በዛ ነው እኔን ጥለውኝ የሄዱት

ቁስለኛ አለ ብለሃል ቁስለኛውስ ምን ሆነ

ኦነግ ስለሆነ የት እንዳለም አላውቅም

በወቅቱ ቁስለኛ አለን ብለው ቁስለኛውን ይዘውት ሄዱ ወይንስ ለተከሳሽ ነው ወይ የሰጡት እንዴት ነው ሁኔታው

ተከሳሹ ያን ጊዜ ሰጡኝ አላለም ቁስለኛውን ለእኔ ሰጡኝ አላለም

መቼ ነበር ይሄ ነገር የሆነው

በ2000 ውስጥ ነው

ቃላቸውን የሰጡትስ መቼ ነው

2001

ቦታው የት ነበር አገሩ

ሚኖ ከተማ

የት ዞን ነው

ምስራቅ ሐረርጌ

ይሄንን ነገር ቃላቸውን ሰጥተው የነበረው ማለት ነው በፍላጎታቸው ነው ወይስ የሚያስገድድ ሁኔታ ነበር እንዴት ነበር ቃላቸውን የሰጡት

በወቅቱ በግዳጅነት አልሰጡም

ቅድም ላም ስጠን ሲሉ ገንዘብ ሰጧቸው ያለው ሰውየው ተገድጄ ነው ያለው ወይስ ፈቅጄ ነው ያለው

አላስገደዱኝም ይዘውኝ ነው የጠየቁኝ

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል፡፡

ዋና ጥያቄ አብቅቷል

ለተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ሚኖ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ነው ወይስ ሌላ ቦታ የት ነው ቃሉን ሲሰጥ አንተ የሰማከው የት ቦታ ነው

ቁንቢ ወረዳ

አንተ ያን ጊዜ ምን ታደርግ ነበር ምን ተብለህ ነው የሄድከው እዛ ቦታ ላይ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

923

እኔ ሚኒሻ ነኝ እዛ ነው ያለሁት

ታዛቢ ነህ ተብለህ ተቀምጠህ ነበር ወይ

ታዛቢ ተብዬ እዛ ነበርኩ

ፈርመሀል ወይ

አዎ በኋላ ላይ ምስክር እንድሆን ፈርሜ ነበር

መቼ ነው የፈረምከው

ጥናት ሲያካሂዱ በዛን ጊዜ ነው የፈረምኩት

ፖሊሱ ነው ቃል የተበቀለው ብለሃል ቃል ሲቀበል ቃላቸውን ሲሰጡ ነበር በፍላጎታቸው ብለህ ነበር

አዎ

አንተ ነህ ቀድመህ እዛ ቦታ የነበርከው ወይስ እነሱ ናቸው እዛ ቀድመው የነበሩት

እነሱ ሌላ ቦታ ስለነበሩ ፖሊሱ እነሱንም ጥራቸው ብሎኝ እኔ ነኝ ለፖሊሶቹ የጠራኋቸው

ከየት ነው የጠራሃቸው

እዛው በአጠገባችን በሌላ ቦታ ስላሉ ከዛ ነው የምጠራቸው

ምን ውስጥ ቤት ውስጥ ውጪ

እሺ ምን አለ ለአሁኑ ጥያቄ

ድገመው

ከሌላ ቦታ ነው እኔ ነኝ የጠራኋቸው ብለሀል የት ነው ያ ቦታ እቤት ውስጥ ነው ዛፍ ስር ነው የት ቦታ ነው ከየት ቦታ ነው የጠራካቸው

የሆነ ሸራ ስር ነው ያሉት እዛ የተለየ ቦታ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

በምን እየተጠበቁ ቁጭ ብለዋል ወይንስ ምን እየሰሩ ስራ እየሰሩ በምን ሁኔታ ነው እዛ ሸራ ውስጥ የመጡት

ታስረው ነበረ እዛ ውስጥ

እሺ አንተ እያንዳንዱን እየጠራሁ የነበርኩት እኔ ነኝ ብለህል ተመልሰህ ደግሞ ቁጭ ብለህም እየሰማህ ነበረ በእዚህ ሁኔታ ነበረ ወይ በለው

አዎ

ፖሊሱ ይሄንን ቃል የጠየቀው ፖሊስ ተከሣሾቹ ቃላቸውን ሲሰጡ በፍላጐታቸው እንደሚሰጡ ይሄ በፍላጐታቸው የሚሰጡት ቃል ወደ ፊት ማስረጃ ይሆንባቹሀል ፍ/ቤት ሲቀርብ ስለዚህ በፍላጐታችሁ የምትሰጡት ቃል ማስረጃ ሊሆን ስለሚችል መስጠትም አለመስጠትም ትችላላችሁ ብሎ ገልጾላቸዋል ወይ

አዎ ገልጾላቸው ነበረ

በሰጡት ቃል ላይ ተነቦላቸዋል ወይ ከሰጡ በኋላ

በወቅቱ አንብቦ ነበረ

ፈርመዋል እነሱስ

አዎ ፈርመው ነበረ

አንተስ

እኔም ፈርሜ

እርግጠኛ ነህ እርግጠኛ ነህ ወይ መፈረማቸውንም መነበቡም --

አዎ

ጫካ ውስጥ አገኛቸው ሰው ተመቶ አገኝዋቸው ሰው ተመቶብናል እና ላም አምጡ ---ላም አምጡ አልዋቸው ላም ስለሌለው 500 ብር ሰጠ ባይሰጥ ኖሮ አደጋ አይደርስበትም ነበር

በጥያቄው ላይ ተቃውሞ

925

ላም አደጋ ያደርስበት ነበረ ወይ

ተቃውሞ ምንድነው

ተቃውሟችን ምንድነው እሱ የደረጃ ምስክር ነው 2 በቦታው አልነበረም እሱ ሲናገር የሰማውን ነው ከእዚህም በተጨማሪ ደግሞ ፈልጐ ነው የሰጣቸው ብሎ ቅድም ተናግሯል ስለዚህ ይሄ 1ኛ የስነ-ልቦና ጥያቄ ነው ምን ሲሆን ይችላል ግምት ነው እንጂ ላይመልሰው የሚችል ጥያቄ ነው

ከእዚህም በተጨማሪ ምስክሩ ማለት ነው አንድ ላም ብቻ ነው ያለኝ ስለዚህ ብር ልስጣችሁ ብሎ ብር ሰጣቸው ነው ያለው ላም ሳይኖራቸው ሳይ--- ቀርቶ አንድ ላም ብቻ ስላለኝ ብር ልስጣችሁ ብሎ በፍቃዱ 500 ብር ሰጠ ብሎ ነው የተናገረው

በፍቃዴ ሰጠሁ ሲል ሰምተከዋል

አዎ ሰምቻለሁ

እሺ ድጋሜ ጥያቄ ካለ ድጋሜ ጥያቄ የለም

ለፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

አንተ በወቅቱ ሙሉ በሙሉ ቃል ሲሰጥ ተከታትለካል ወይንስ ያልተከታተልከው ክፍል አለ

ስለቆየ ከጠፋብኝ ነው እንጂ አዳምጥ ብለውኝ ተከታትዬ ነበረ

ካንተ ጋራ ---

አዎ አንድ ሰው ከእኔ ጋ ---

ማነው እሱ

ዩሱፍ ጅማ ዩሱፍ ጅማ የሚባል

ዛሬ መጥቷል አይተከዋል

አላየሁም

926

አንተ ከሽራ ስር የምትጠራበት ቦታ እና እነሱ ቃል የሚሰጡበት ቦታ ምን ያህል እርቀት ነበረው

ይቀራረባል

ምን ያህል ነው ልታሳየን ትችላለህ በግምት

ከእዚህ እስከ ውጪ ያለው ቤት ድረስ ይሆናል

እሺ ከአሁን ከምናስችልበት የላይኛው ክፍል ችሎት እስከ ፊት ለፊቱ ካሉ ኔትወርክ ወል ያለበት ቢሮ መሆኑን አሳይቷል እሺ በወቅቱ ቃላቸውን ሱሰጡ በፍላጐታቸው ነበረ ወይንስ በግዳጅ ለሚለው ግዳጅ አልነበረም ብለከናል

አዎ

እንዴት ተረዳህ በፍቃዳቸው መሆኑን

በዱላ አልተደበደቡም ቁጭ ብለው ሀሳባቸውን ተቀበላቸው

በቃ

አዎ ቁጭ ብለው ሀሳባቸውን ተቀበሏቸው በዱላ አልተመቱም

እሺ ጨርሰሀል እናመሰግናለን

ቀጣይ

28ኛ ምስክር በክሪ አብዱላሂ

ስንተኛ ተከሣሾች ላይ

በ53ኛ ተከሣሽ ላይ ነው የሚያስረዳው 31ኛ ክስን ነው እንደ ክስ አቀራረባችን ነው የሚያስረዱ

28ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - በክሪ አብዱላሂ ሙሜ

እድሜ - 27

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

927

ስራ - የጫት ነጋዴ

አድራሻ - አወዳይ ዞን - ምስራቅ ሀረርጌ ቀበሌ 01 የቤት ቁጥር - የለውም

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ላይ

በክሪ ላይ

በክሪን ታውቀዋለህ

ባየው አውቀዋለሁ

በክሪ ማን ነው

በክሪ ቃሲም ይሁን በክሪ አብዱሰላም ይሁን የአባቱን ስም አላውቅም

ፀብ ወይም ዝምድና አለህ

የለኝም

ምን አድርጐ እንደተከሰሰ ታውቃለህ በክሪ

መከሰሱን አውቃለሁ

ምን አድርጐ

እኔ አንድ ጊዜ ታስሬ ነበረ እሱ ግን እንደ ፖርቲ ውስጥ እንደነበረ ነው አባል ውስጥ እንደነበረ

አንተ በምን ምክንያት ታሰርክ

ስሜ በክሪ ነው እሱም በክሪ ነው እሺ አሁን እስቲ በክሪን አሳየን ከእዚህ ውስጥ የትኛው ነው

እሺ በክሪን ፈልጐ አላየሁትም ብሏል ከተከሣሾቹ ውስጥ ------ ሊያወጣ አልቻለም ግማሽ እስረኞች መሀል ተደርጐ ሊለያቸው አልቻለም ምን አድርጐ እንተከሰሰ ታውቃለህ አሁን በክሪ እስቲ የምታውቀውን የምትመሰክረውን በዝርዝር ለፍ/ቤቱ አስረዳ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

928

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እሱ በፊት ኦነግ ብለውት ተጠርጥሮ ነበረ አንድ የጫት ቤት አብረን እንሰራ ነበረ አብረን እየቃምን እሱ አንድ ቦታ አይቀመጥም በየ 30 ደቂቃው ይዞራል ለምን እንዲህ ትዞራለህ ብለን ስንጠይቀው እነዚህ አስተዳደሮች የአስተዳደር ሰዎች ይፈልጉኛል ብሎ እነሱን ነው የምፈራው ለእዛ አንተ ከእንዲህ አይነት ነገር ውስጥ ለምን እንዲህ ያለህን ስም ለምን አትሰርዝም ለምን አታጠፋም አንተስ አትፈልግም ወይ ብሎ አለኝ ይሄንኑ ብሎኝ

ምንድነው አንተስ አትፈልግም ወይ ያለህ

የኦነግ አባል መሆን አትፈልግም ወይ አለኝ እኔ ስራ እንጂ እንዲህ አይነት ነገር ውስጥ መግባት አልፈልግም አልኩት

አስተዳደሮቹ ለምን ነበረ የሚፈልጉት ለምንድነው ይፈልጉኛል አለህ

ሊያስሩኝ ነው የሚፈልጉኝ አለኝ

ይሄንን ያለህ መቼ ነው መቼ ነው ይሄንን ያለህ

የእናንተም ጠያቂ እንዲገባ አድርጉ ያው እሱ በኦሮምኛ የሚናገረው ስለማይገባው የእርሶ---

አብራችሁ የዛን እለት የቃማችሁት እና ይሄንን የነገረህ

አማርኛው ይግባህ ጥያቄው ----

እሺ አይ ቀለል ባለ አማርኛ የተባለ መስሎኝ ነው የለወጥኩት

ኖ እሱ በአማርኛ እየተናገረ አይደለም መልስ ብቻ ነው በአማርኛ የሚናገረው ጥያቄውን አይናገርም

እሺ መቼ ነው እንደዚህ አብራችሁ ስትቅሙ ይሄንን ነገር የነገረህ መቼ ነው እሱ

ከ2 አመት በፊት ነው

የት ነው ቦታው የት ነው

አወዳይ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት

እሺ አወዳይ ነው ብለከናል አብረን እንሰራ ነበረ ጫትም አብረን ቅመናል ብለካል ምን ያህል ጊዜ ታውቀዋለህ ማለት ነው በክሪን

2 አብረን በነበርን ጊዜ 2 ወር 3 ወር አውቀዋለሁ

እሺ 2 ወር 3 ወር አብረን በነበርን ጊዜ አውቀዋለሁ ብለሀል ታዲያ እዚህ ውስጥ የለም ወይ እሱ እርግጠኛ ነህ ወይ በደንብ አድርገህ አይተከዋል ወይ

እዚህ ውስጥ የለም ፊቱን በደንብ ነው የማውቀው እዚህ ውስጥ የለም

እሺ አንተን ያው በአባዎ ላደራጅህ ሲልህ አልፈልግም ብለከዋል አስተዳደሮችም በእዚሁ በአባዎነት ነው ፈልገው ሊያስሩት የነበው ብለካል

አንተን እንደዚህ ላደራጅህ እንዳለህ እንደዛ ብሎ ያደራጃቸው ሰው አለ ወይ ታወቃለህ ወይ

እኔ እሱ ያደራጃቸውን ሰዎችን በአይን አላየሁም ለእራሱ በድብቅ ነው እንደዛ እያደረገ የነበረው ይደብቅ ነበረ

ጨርሰናል

---- እንደዚህ ይኖራል ከ70 ሰው መለየት አቅቶህ ሊሆን ይችላል ፍ/ቤቱ አንድ 5 ሰው ቢያደረግልህ እና ከእዚህ 5 ሰው ውስጥ ልትለይ ትችላለህ ወይ ምስክሩን

እንደዛ ባይደረግም ፊቱን በደንብ ነው የማውቀው

እየው ከእዚህ ውስጥ ለይልን እና አሁን እዚህ ፊት ለፊት የተመረጡ ረንደምሊ የተመረጡ ሰዎች ከበክሪ ጋር ሊኖሩ ይችላሉ ከዚህ 5 6 ሰው ውስጥ ማን ነው በክሪ አንተ የዛኔ 2 ወር አብረህ የቃምከው

ከየት ይላል እንዴ ተነስ እና ጠጋ ብለህ እየው በለው

ከጀርባ እራሱ ባየው ስለማውቅ የለም

ጠጋ ብለህ እይ ከእዚህ ውስጥ

እያቸው አይን አይናቸውን ፊታችሁን አትሸፍኑ እጃችሁን ዘርጋ አድርጋችሁ ቁሙ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

930

እንዲሁ ነው የማውቀው የለም

ምንድነው ያለውን ንገረን

እሱ

አዎ

በደንብ ነው የማውቀው እዚህ ውስጥ የለም

በደንብ ነው የማውቀው እዚህ ውስጥ የለም ብሎ

ልጁን በደንብ ነው የማውቀው እዚህ ውስጥ የለም

እሺ ማነው በክሪ ከእዚህ ከ6ቱ ውስጥ እጅህን አውጣ ከ6ቱ ይሄኛው አይደለም ይሄ አሁን እጅ ያወጣው እሺ በክሪ ብሎ እጅ ያወጣውን እሱ አይደለም ብሎ አረጋግጧል እሺ ተመለስ እሹ 53ኛ ተከሣሽን ችሎቱ አሳይቶች እሱ አይደለም በክሪ የምለውን እኔ በደንብ አውቀዋለሁ ይሄኛው አይደለም በማለት አረጋግጧል እሺ ዋና ጥያቄ ጨርሳቹሀል

ያው ተከሣሹን አላውቀውም ስላለ ጨርሰናል

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አለ መስቀለኛ ጥያቄ የለም ድጋሜም ጥያቄ አይኖርም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

2 ወር አብረህ ጫት ቅመሀል ወይ አሁን በክሪ ከምትለው ሰው ጋር በለው እርግጠኛ ነህ ወይ

አዎ

መቼ ነው ጫት ቃምን የምትለው

ከ2 አመት በፊት

የት አካባቢ የሚኖር ሰው ነው በክሪ

አወዳይ ከተማ የጫት ከተማ ውስጥ ነው የሚኖረው

አንድ ከተማ ናችሁ ወይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

931

አዎ

በክሪ ማን ነው የአባቱ ስም ታውቃለህ ወይ

በክሪ አብዱሰላም ነው ያለኝ እኔንም ሸውዶ መንግስትም ከሸወደ ግን እኔ እንጃ እሱን አላውቅም

አይ አንተ የምታውቀው ትክክለኛ ስሙ ማነው ይሄ አንተ ጋር ጫት ቃመ የምትለው ሰው ትክክለኛ ስሙን አታውቅም ወይ

እርግጠኛ የሆነ የእሱ ስም በክሪ መሆኑን አውቃለሁ ግን የአባቱን ስም አላውቅም

እንግዲህ በክሪ ያልከው ሰው ልጅ ነው ጉልማሳ ነው ወይስ ሽማግሌ ነው

ገና አንድ የወለደ አካባቢ ነው

በእድሜ ስንት ይሆናል 25 23 ይሆናል

አሁን አይተከው ታውቃለህ ከእዛ ወዲህ የት ነው ያለው አሁን

ከእዛን በኋላ ---- አላየሁትም

አንድ ልጅ ወልዷል ያልከው ልጅ መውለዱን አውቀህል ወይስ አንድ የወለደ ይሆናል ብለህ መገመትህ ነው

አንድ ልጅ ወልዷል እዛ አወዳይ ውስጥ

እንዴት አወቅህ መውለዱን

ሚስት አለው

ሚስቱን ታውቃለህ

አዎ

ማናት ሚስቱ

በሰፈር ትንሽ ስለምንራራቅ ስሟን አላውቃትም

አሁን የት ነው ያለው ይሄ በክሪ የምትለው

932

አሁን የት እንዳለ አላውቅም እኔ ለስራ ስለምዞር የት እንዳለ አላውቅም

እሺ አሁን እዚህ የቀረቡት ተከሣሽ እድሜያቸው በክሱ ላይ 45 ነው የሚለው እድሜህ ስንት ነው በክሪ ስንት ነው እድሜህ እ የእርሶ ስም በከር ነው እሺ ስሜ በከር ነው በክሪ አይደለም ብሏል 53ኛ ተከሣሽ እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን፡፡

እሺ በእዚህ 5ኛ ተከሣሽ ላይ ሌላ ምስክር አላችሁ

አሁን የሚቀርብ ሌላ ምስክር የለንም

በ53ኛ ላይ

አሁን ዛሬ የሚቀርብ የለንም

ሌላ ጊዜ የሚመጣ አለ

ቼክ አላደረኩም እርግጠኛ አይደለሁም 57ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በ53ኛ ተከሣሽ ላይ ነው የቆጠርነው ነገር ግን ይመስክር ገና ይሁን እርግጠኛ አይደለሁም አለየንም

አሁን ማን ይሰማላችሁ ---- አሁን የሚሰማላችሁን አስመዝግቡ እና አመሳክሩ እሱን ቀስ ብላችሁ

አሁን የሚመጣልን 68ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

አሁን የሚመጣው ምስክር 68ኛ ነው አብዱላሂ አመዴ ይባላል

68ኛ

ምስክር ነው

ስንተኛ ተከሣሽ ላይ

በ25ኛ ተከሣሽ ላይ ነው

ስንተኛ ክስ

45ኛ ክስን ነው የሚያስረዳው

933

እንደ ክሱ ብላቹሀል

እንደ ክሱ ነው

68ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አብዱላሂ አመዴ ሙሜ

እድሜ - 30

አድራሻ - ቁሬርሳ ቀበሌ ዞን ኮንቦልቻ

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት

ኮንቦልቻ ቀበሌ ስንት ነው ከተማ ነው ገጠር ነው

ገጠር ውስጥ

ኮንቦልቻ ምን ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው የሚባለው

ቁሬርሳ

እሺ ቁሬርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነኝ ብሏል ለምስክርነት በማን ላይ ልትመሰክር ነው የመጣከው ስለ ምንድነው

አብዲ አሊ ላይ ስለ ኦነግ

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

እሺ አብዱላሂ አብዲ አሊን ትለየዋለህ ወይ አሁን ተነስተህ እስቲ ታሳየናለህ ወይ

አዎ

አሳየን እስቲ

ማነው ስምህ ምስክሩ አብዲ አሊን---- ከ70 ተከሣሾች ውስጥ ለይቶ አውጥቷል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

ይሄ የለየክልን አብዲ አሊ የተባለው ተከሣሽ ምን ማድረጉን ነው የምታውቀው እስቲ ንገረን

እሱ ያደረገው ኦነጎች ከእሱ በፊት እና ጋር ነበሩ እሱ ገንደ የሱፍ በሚባል ማታ እኛ ጋ መጣ እኛ ጋ መጥቶ አብረን ቁጭ አልን አብረን ተቀመጥን ኦነጎች ሰው እናደራጃለን በማለት ቁጭ ብለው ነበረ አብረን ሆነን ሰዎች ሰብስበንላቸው እሱ እኛ ጋ ሆኖ ደንበባ አደራጀ እሱ እኛ ጋ ሆኖ ደንበባ የሚባል አደራጀ

ደንበባ ምንድነው ስራው ምንድነው

ኦነግ ነው እሱ

እሺ ከአደራጃችሁስ በኋላ ምንድነው ያደረጉት ካደራጃችሁ በኋላ አብዲ አሊ ምን አደረገ የዛን ጊዜ ምን ሲላችሁ ነበረ አብዲ አሊ በእለቱ አብዲ አሊ ደንበባ ሲያደራጃችሁ አብዲ አሊ ምን እያላችሁ ነበረ ምን ሲያደርግ ነበረ ያመሸው

እሱ ቁጭ ብሎ ሰዎቹ ስማቸውን ሲጠየቁ አንተ ስምህ ማነው አንተ ስምህ ማነው ብለው ሲጠያየቁ እኔ ስሜ አብዲ አሊ ነው ተማሪ ነኝ አባ ገዳ ኮሌጅ ነው የምማረው እና ጋ ቁጭ ብሎ አብረን ቁጭ ብለን አብረን ሆነን እስከ 6:00 ሰአት አብረን ተቀምጠን ዘመዶች እዛ አካባቢ ስላለው ዘመዶቼ ጋር እሄዳለሁ ብሎ ሄደ

ከመሄዱ በፊት ምን አድርጉ አላችሁ ለአባዎ ይሄ ቅድም የጠራህልን ደንበባ የሚባለው ሰውዬ ሲያደራጃችሁ እሱ ምን ሲያደርግ ነበረ የዛን ቀንስ ምን ሲያደርግ ነው ወደ እናንተ ጋ የመጣው የዛን ቀን

ከእዛ እኛ ጋ ከመምጣት በፊት ትውውቅ ካላቸው ነው እንጂ ያን ቀን እኔ እና ሰዎች አብረን ቁጭ ብለን እያለ ነው የመጣው እሱ

ምን ሊያደርግ ነው የዛን ቀን የመጣው እሱ

ምን ሊያደርግ እንደመጣ እኔ እንጃ

የዐ/ሕግ ጥያቄ ይገባሀል አይደል

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምን ሊያደርግ እንደመጣ እኔ እንጃ መጣ አብረን ቁጭ ብለን እያለ እሱም መጥቶ ተቀላቀለን ከእነሱጋም ይተዋወቅ አይተዋወቅ እኔ ግን አላውቅም

እሺ እናንተ የተሰባሰባችሁት እነማን እነማን ነበራችሁ ከየት የመጣችሁ ሰዎች ነበራችሁ ወደ እዚህ የተሰባሰባችሁት ደንቦባ የሰበሰባችሁ

እኛ እዛው አካባቢ ከእዛው አካባቢ ነው የተሰባሰብነው

አብዲ አሊስ ከእዛው አካባቢ የተሰባሰበ ነው ወይ እዛው ከእናንተ ጋር ነው የሚኖረው ወይ

እሱ ከ

እሺ ቀጥሉ

እሱ ከአለማያ ድረስ የመጣው ምን ሊያደርግ ነው ደንቦባስ ከየት ነው የመጣው አብዲ አሊ

ከእነሱ ጋር ብተዋወቅም አላውቅም እኔ ከእኛ ጋር ተቀምጦ ሲነሳ ዘመድ እዚህ አካባቢ አለኝ ብሎ ነው የተነሳው

አብዲ አሊ ማለት ነው

ከእነሱ ጋር ትውውቅ ይኑረው አይኑረው አላውቅም እዛ ተሰባሰብን አብዲ አሊዪ ነኝ እዚህ ትምህርት ቤት እማራለሁ አለ ይሄንን ነው የማውቀው ነው ያለው ሌላ ጥያቄ ጠይቁ

አብዲ አሊ አድርጉ ያላችሁ ነገር አለ ወይ

የለም እኔም አብዲ አሊ እባላለሁ የአባገዳ ኮሌጅ ተማሪ ነኝ

ስለ ኦነግ የነገራችሁ ነገር የለም ወይ

የለም

መቼ ነው ይሄ የሆነው

በህዳር ውስጥ በ1998

የት ቦታ ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

936

ገንደ ዩሱፍ በሚባል አካባቢ

ስንት ሰኣት ላይ ነው

ከ3፡00 እስከ 4፡00 ሰኣት ይሆናል

ጠዋት ነው ማታ

ማታ

ጨርሰናል፡፡

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አለ

የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

መስቀለኛ ጥያቄ የለም ድጋሚ ጥያቄ አይኖርም

ለፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

የአንተ ስም ማን ነው

አብዱላሂ

አብዱላሂ አመዴ ሙሜ ነው አደለም ስምህ

አዎ

ስለ አብዲ አሊዩ ምንድን ነው ለዚህ ፍ/ቤት የምታረጋግጠው አንተ አብዲ አሊዩ በወንጀል ተከሶ እዚህ አለ አንተ የአብዲ አሊዩ ወንጀል ይሄ ነው የምትለው ምንድን ነው ለፍ/ቤቱ የምታስረዳው ስለ እሱ ምን ታረጋግጣለህ ምንድን ነው የምትነግረን

እኔ ይሄንኑ ነው እሱ ላይ የማውቀው

ምን ድምጽህን ከፍ አድርግ

አሁን የተናገርኩትን ነው የማውቀው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ዲ/ሬጅ ... ቁጥር 4

937

አብዲ አሊዩ ከእናንተ ጋር ቁጭ ብሎ የአባገዳ ኮሌጅ ተማሪ መሆኑን እና አብዲ አሊዩ ነው ስሜ ማለቱን ነው የምታውቀው

አዎ

ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም አታውቅም

እዛ መምጣቱን እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር ምንም ነገር የለኝም

እዛ አንተ ምን ነበር ስራህ በዛን ጊዜ የትኛው አባል ነበርክ ለምንድን ነው እዛ የሄድከው

እኔ ሰፈር ውስጥ ኦነጎች መጥተው ሰው እናደራጃለን ብለውኝ እቤቴ ድረስ መጥተው እዛው አንድ ላይ ተቀምጠን ነበር

በግድ ነው የጠሩህ ወይስ ፈልገህ ሄደህ ነው አንተ

በፍላጎቴ ነው የሄድኩት

እሱ መጀመሪያ አብዲ አሊዩ አንተ ከሄድክ በኋላ ነው የመጣው ወይስ ከአንተ በፊት እዛ ነበር

እኔ እዛ ከሄድኩ በኋላ ነው እሱ የመጣው

ስንት ትሆናላችሁ ብዛታችሁ

6 ሰው እንሆናለን

ማን እንደጠራው ታውቃለህ

ማንን እሱን ነው

አብዲ አሊዩን ማን እንደጠራው ታውቃለህ ወይ

አላውቅም

ጠርተውት ይሁን ድንገት መጥተው ይሁን የምታውቀው ነገር አለ ወይ

የለኝም አላውቅም

እዛ የተሰባሰባችሁበት ቦታ ቤት ነው ወይስ ውጪ ነው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

938

ቤት ውስጥ ነው

የማን ቤት ነው

የመሀመድ ጁንዲ ቤት ነው

ተሰባስባችሁ ምን ያህል አብራችሁ ቆያችሁ

ከእሱ በፊትም ትንሽ ቆይተናል

እኮ ምን ያህል ሰዓት ቆያችሁ

ከእሱ በፊት ራሱ ሶስት ቀን ቆይተናል አብረን እንደዛ እያለን ነው እሱ የመጣው

እኮ እሱ ከመጣ በኋላ ምን ያህል ጊዜ አብራችሁ ቆያችሁ

እሱ ከመጣ በኋላ እስከ 6:00 ሰኣት ቆየን አብረን

ለሊት

አዎ

ምን ተወያይታችሁ ምን ወሰናችሁ ስለምን ተጫወታችሁ ወይ ተነጋገራችሁ

እሱ በወቅቱ መጥቶ ሲቀመጥ እሱ በወቅቱ ሲመጣ እኔ ከሰፈር ውስጥ እናደራጃለን ያሉትን ሰዎች እየጠራሁ ነበር ከእሱ በፊት ሰው ከሰፈሩ እንድጠራላቸው አድርገውኝ ነበር

እዛ ምንድን ነው የተወያያችሁት ወይ ቁጭ ብላችሁ አብራችሁ ስትውሉ ስለምን ነገር ተነጋገራችሁ ነው አብዲ ኢሊዪ እያለ ስለምን ተነጋገራችሁ

እሱ ቁጭ ብሎ ነበር ደንበባ አነጋገረንና አማን መዋጮ አውጥተን እንድናግዘው ደንበባ እየነገረን ነበር

ማን ነው የነገራችሁ

ደንበባ

አብዲስ ምን አለ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

939

ሰዎቹ ስሙን ጠይቀው ስሙን ከተናገረ በኋላ ምንም አልተናገረም ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ ነበር

ጨርሰሃል እናመሰግናለን። ወይስ ጨረሳችሁ ለዛሬ

ለዛሬ ጨረስን የምናሳስበው ግን አለን

እሺ ይቀጥሉ በማይኩ ዛሬ ጨረሳችሁ ወይስ አልጨረሳችሁም የምታሰሙትን

ዐ/ህግ እያሱ መኮንን እባላለሁ ትላንትና 12ኛ ምስክር ሆና ቃሏን የሰጠች ሳፊያ ዩሱፍ ሙመድ የምትባል አለች እሷ ቃሌን ስሰጥ የሰጠሁት በድንጋጤ ምክንያት ተሳስቼ ነው ስለዚህ ቃሌን በድጋሚ መስጠት እፈልጋለሁ ቃሌን ማቃናት እፈልጋለሁ ብላለችና በወንጀል ህጉ 454 መሰረት ቃሏን ማቃናት በራሷ ፍቃድ ስለፈለገች ቃሏን አቃንታ እንድትሰጥ ፍ/ቤቱ ቢፈቅድልን እየጠየቅን ነው የወንጀል ህግ 454 መሰረት ምስክሯም እዚሁ ቀርባለች ቃሌን አቃንቼ ልስጥ ብላ እየጠየቀች ነው

አሁን ምንድን ነው ይሄ ማመልከቻ ነው አይ ስለምስክሮች ነው አሁን የተጠየቁት ስለ ምስክሮቹ ምስክር ለመስማት ነው አሁን የተቀጠረው ስለ ምስክሮቹ መጀመሪያ ይናገሩ ነው ምስክር አላችሁ ወይስ ጨረሳችሁ

ምስክርን በተመለከተ ለዛሬ ያቀረብናቸውን ምስክሮች ጨርሰናል

ጨርሳችኋል

አዎ

አሁን በኋላ የምታቀርቡት የለም ለዛሬ

ለዛሬ የለም አሁን ሁለተኛ ላይ የማሳስበው ነገር የወንጀል ህጉ 454 ላይ ቃል ማቃናት ወይ መለወጥ የሚል አለ እና ምስክሯ ከመደናገጥና ከመፍራት የተነሳ ቃሌን በትክክል አልሰጠሁኝም ስለዚህ ቃሌን በትክክል እንድሰጥ በዳግመኛ እንዲፈቀድልኝ በዐ/ህግ በኩል አሳስቡልኝ ብላ ስላለች ቃሏን እንደገና አቃንታ የምትሰጥ ስለሆነ ፍ/ቤቱ እንዲፈቅድልንና ቃሏን አቃንታ የምትሰጠውን እንዲቀበልልን እየጠየቅን ነው 12ኛ ምስክር ትናንትና የመሰከረች ሳፊያ የምትባል ምስክር ማለት ነው ሳፊያ ዩሱፍ ሙመድ

እሺ በዚህ ላይ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ሀሳብ ትሰጡበታላችሁ

940

የተከበረው ፍ/ቤት ዐ/ህጉ የጠቀሱት አንቀጽ ክስ ማቅረቢያ እንጂ ስለ ወንጀሉ ህግ አካሄዱ የሚመለከተው ህግ የስነ ስርዓት ህጉ ነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ላይ ያለ አንቀጽ አይደለም ዐ/ህጉ የጠቀሱት ስለዚህ ፍ/ቤቱ እንዲህ አይነቱን ነገር ፍ/ቤቱ መርምሮ ወይ ብይን ወይ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ለማጣራት ካስፈለገ ነው ይሄ የፍ/ቤቱ ስልጣን ነው የተሰጠውም ይሄ ስልጣን በስነ ስርዓት ህጉ ላይ ያለ ነው ምስክሮችን ድጋሚ የመጥራት ስለዚህ በዚህ ደረጃ ሊቀርብ የሚችል ሀሳብም አይደለም የዐ/ህጉ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ከህጉ ውጪ ነው እና

እሺ ይቀጥሉ አቶ አድማሱ ተጨማሪ ሀሳብ ብለዋል

እንደው ህጉ ራሱ ከተከሰሰ በኋላ እንዲህ ላቃና ምናምን ብሎ በራሱ የሚያቀርበው እንጂ ዐ/ህግ ራሱ የራሱን ምስክር ራሱ ጋር አስሮ አቆይቶ አምጥቶ እንደገና እሷን ወክሎ ስለ እሷ የሚያመለክትላት ዐ/ህግ ነው እንዴ እንደው በምን ህግ ነው ዐ/ህግ በምን ሂደት ነው የእሷ ወኪል የሚሆነው

እሺ እንቃወማለን ነው

አዎ

እሺ ብይን እንሰጥበታለን

ብ ይ ን

እሺ በቀረበው የዐ/ህግ ማመልከቻና በቀረበው ተቃውሞ ላይ ፍ/ቤቱ የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል በዚህ መዝገብ በእነ ኢብራሂም ባሌ ምስክሮች እየተሰማ ነው ያለው በዚህም ምስክር ትናንትና የተሰሙትን 12ኛ ምስክር በተመለከተ በመፍራት በድንጋጤ የሰጠችው ቃል ስለሆነ ቃሌን አቃንቼ የምሰጠው ቃል አለ ብላ ምስክሯ ስለጠየቀች ምስክሯ እዚሁ ደጅ ስላለች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 454 መሰረት ቃሏን እንድትሰጥ ፍ/ቤቱ ይፍቀድልን በማለት የችሎቱ ዐ/ህግ አሳስበዋል በቀረበው ማመልከቻ ላይ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ዐ/ህጉ የጠቀሱት መቃወሚያ አቅርበዋል ባቀረቡትም መቃወሚያ ምስክሯ ቃል ትስጥ ተብሎ ፍ/ቤት ከመሰከረች በኋላ አሁን የተጠየቀው እንዲሁም የተጠቀሰው የወንጀል ህግ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ክርክሩ የሚመራበት ሳይሆን የወንጀል ህጉን በመሆኑ አግባብነት የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል ራሳቸው ጋር አቆይተውም ምስክሯ የምትሰጠው ቃል ስለ ተከሳሿ የሚገልጽ ነው ይሄንን ዐ/ህግ በምን ስለ እሷ እንደጠየቁ አይገባንም በማለትም ተቃውሞ አቅርበዋል የቀረበውን

941

ተቃውሞ እና ጥያቄ እና ተቃውሞ እንዲሁም ከስነ ስርዓት ህጉ ጋር ስናየው የ ወንጀል ጉዳይ የሚመራበት የስነ ስርዓት ህግ አለ በዚህም ምስክር ሲሰማ ተጨማሪ ምስክርም የሚሰማበት የሚጠየቅበት ስነ ስርዓት ህግ ተደንግጎ አለ ምስክርን መልሶ የሚቀርብበት ተጨማሪ ምስክርም የሚሰማበት ሁኔታ አለ ሆኖም ግን አሁን በዚህ በቀረቡት ሁኔታ የጠቀሱትም ህግ አግባብነት የለውም ምስክርነቱን ፍ/ቤቱ ወደፊት የሚመዝነው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግራቀኙን የተጨማሪ ማስረጃ ፍ/ቤቱም የሚጠራበት ስነ ስርዓት ስላለ የቀረበውን ማመልከቻ ከቀረበው ተቃውሞ ጋር ስናይ የተቃውሞውን በመቀበል ማመልከቻውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ምስክርነቷ አሁን የሚሰማበት ሁኔታ አይኖርም ሌላ የምታመለክቱት ካለ ስለ ቀጣይ ምስክርነት፡፡

ሌላ የምናመለክተው ነገር 11ኛ ምስክሮችን በተመለከተ ነው

11ኛ ምስክር

አዎ 11ኛ፣ 14ኛ፣ 16ኛ ምስክሮቻችን ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ነው የሚገኙት 87ኛ ምስክራችንም ምስራቅ ሐረርጌ ማረሚያ ቤት ነው የሚገኘው እዚህ አለመገኘታቸው ፖሊስ ማረጋገጫ ሰጥቶናል ስለዚህ ፍ/ቤቱ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት እና ከምስራቅ ሐረርጌ ማረሚያ ቤት አስቀርቦ ምስክርነታቸውን ቃል እንዲሰማልን እንጠይቃለን ማስረጃው ካስፈለገ ለፍ/ቤቱ ፖሊስ የፃፈልንን ይሄንን እንሰጣለን ሌላ ኢብራሂም መሀመድ ከቢራ የተባለው 20ኛ ምስክራችን የሞተ ለመሆኑ አሁንም ማረጋገጫ ቀርቦልናል በተጨማሪ 21ኛ ምስክር 23ኛ ምስክር 5ኛ ምስክር እና 7ኛ፣ 49ኛ ምስክሮቻችን ደግሞ በቀበሌው የሌሉ ለመሆኑ ማረጋገጫ ከፖሊስ ደርሶናል 49ኛው ምስክርነት የቀበሌ ማረጋገጫ ደርሶናል 5ኛ እና 7ኛ ምስክርንም የቀበሌ ማረጋገጫ ደርሶናል ስለዚህ እነዚህ በቀበሌያቸው የሌሉ ምስክሮቻችን ስለሆኑ የእነሱን የሞተውንና በቀበሌያቸው የሌሉትን ምስክሮችን ፖሊስ ጣቢያ የሰጡትን ቃል እንድናያይዝና ፍ/ቤቱ እንዲመለከትልን እንጠይቃለን ማስረጃ ካስፈለገ እነዚህ ይህ ለመሆኑ እስከ አሁን የተናገርነው ነገር ለመሆኑ ከፖሊስ ጣቢያ እና ከቀበሌ የቀረቡ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

እሺ ሌላ የምታመለክቱት

ቀሪ ከእነዚህ ውጭ ያሉ ምስክሮችን በተመለከተ በሚሰጠን ተለዋጭ ቀጠሮ እናቀርባለን

ሌሎቹን ቀሪ ምስክሮቹን ስንት ናቸው አጀንዳ ለመያዝ እንዲያመቹን ማለት ነው ከዚህ ውጪ ቀሪ ምስክሮቻችሁ ማን ናቸው ስንት ናቸው ብዛታቸው

ከዚህ ውጪ ያሉ ቀሪ ምስክሮቻችን 13 ናቸው በድምሩ ተራቁጥራቸውም ካስፈለገ 2ኛ፣ 37ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 52ኛ፣ 54ኛ፣ 55ኛ፣ 56ኛ፣ 57ኛ፣ 73ኛ፣ 74ኛ፣ 85ኛ እና 86ኛ ናቸው በድምሩ 13 እነዚህ በሚሰጠን ተለዋጭ ቀጠሮ እናቀርባለን

የተከሳሹን ተከላካይ ጠበቃ ተከታትላችኋል የገለጹት 11ኛ፣ 14ኛ እና 16ኛ ምስክሮቻችን በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ስለሚገኙ እንዲሁም 87ኛ በምስራቅ ሐረርጌ ማረሚያ ቤት ስለሚገኝ 20ኛው ምስክር ኢብራሂም ከቢራ በህይወት የለም 21ኛ፣ 23ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣ 49ኛ በቀበሌ የሌሉ መሆኑን ማረጋገጫ ከፖሊስ ደርሶናልና አሁን የሞተውና የሌሉትን በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት ቃል ይያያዝልን ሌሎች ቀሪ ምስክሮች በቁጥር ብዛታቸው 13 የሆነ 2ኛ፣ 37ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 52ኛ፣ 54ኛ፣ 55ኛ፣ 56ኛ፣ 57ኛ፣ 73ኛ፣ 74ኛ፣ 85ኛ እና 86ኛ በተለዋጭ ቀጠሮ እናቀርባለን የሚል ነው በቀረበው ጥያቄ ላይ ሀሳብ እንድትሰጡ አሳጥሩ

እኛ በተለይ ጥፋተኛ ውሳኔ የተሰጠባቸው የተባሉት እስረኞች ቃሊት አሉ የተባሉት እስረኞች ምንም የአደባባይ ሚስጥር ነው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል ተቀጥተዋል ከመብት የመሻር ጉዳይ ቢመጡም አይመሰክሩም ከመብታቸው እንትን ስለሆነ ስለዚህ ጊዜ ለመግደል ካልሆነ በስተቀር ቢመጡም እኛ ግልባጭ አዘጋጅተን እንጠብቃለን ለፍ/ቤቱ እናቀርባለን

እሺ ሌላውስ ስለ ሌሎቹስ ስለ ሞተውና ቀበሌ በአድራሻቸው ስላልተገኙ ቃላቸው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት 145 መሰረት ይታይልን ብለዋል እሱ ላይም ሀሳባችሁን ግለጹ

ፍ/ቤቱ ይመለከተዋል እንጂ በግድ ይቀበለዋል ስለማይል ስነ ስርዓቱ

ሌላ የምታመለክቱት

ተጨማሪ ነው አሁን በቀረበው ተቃውሞ ላይ ተጨማሪ ነው እንደተባለው ፍ/ቤቱ ይመለከተዋል ነው እንጂ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል አይደለም አግባብነት ያለው ማስረጃ አይደለም ምክንያቱም ያውቃል ትክክለኛ ቃል በመሆኑ በመስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ሊቀርብበት የሚችል በዚህ መልክ በትክክል ያ እዛ ላይ የተሰጠው ቃል የሰውየው ነው አይደለም የሚለውንም ጥርጣሬ ላይ ስለሚጥልና በመስቀለኛ ያልተጣራ ስለሆነ ማስረጃው መቅረቡ አግባብነት የለውም

አይ መልስ አይደለም ሌላ የምታመለክቱት ነገር ኖሮ ከሆነ እሺ በቀረበው ጥያቄና ተቃውሞ ላይ ብይን ተሰጥቷል

943

ብ ይ ን

ምስክሮች ቃሊት ማረሚያ ቤት ነው ያሉት የተባሉት ምስክሮች በምን ጉዳይ እዛ እንደገቡ እሱ ወደፊት ምስክሩ ራሱ ቃለ መሀላ ፈጽሞ የሚመሰክር በመሆኑ ምስክሮች ካሉበት መጥተው ሊሰሙ ነው የሚገባው ተለዋጭ ቀጠሮ እንሰጣለን የ11ኛ፣ 14ኛ፣ እና 16ኛ ምስክሮችን የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲያቀርብ ከድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ጋር ተፃፅፈው እንዲያቀርቡ ለሁለቱም ክፍል ይፃፍ 87ኛ ምስክርም እንዲሁም ከምስራቅ ሐረርጌ ማረሚያ ቤት እንዲቀርብ ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመፃፃፍ እንዲቀርብ ታዟል ይቅረብ 20ኛ ምስክር ሞቷል የተባለ ሲሆን ሌሎች 21ኛ፣ 23ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣ 49ኛ ቀበሌ ውስጥ የሌሉ መሆኑ ማረጋገጫ ከፖሊስ የቀረበ በመሆኑ በፖሊስ የተሰጠ ምስክርነት ቃልን በተመለከተ ፍ/ቤት ስለመቅረብ ስለመቻሉ ስነ ስርኣት ህጉ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት 145 ይደነግጋል እንደተባለውም ይህንኑ ምስክር ለማስተባበል እድል መስጠት ስነ ስርዓት ህጉ በንዑስ 2 አስቀምጧል ፍ/ቤት ማየት ይችላል እናንተም ወደፊት አስተያየታችሁን በ145 ንኡስ 2 መሰረት አስተያየታችሁን በቀረበውና በደረሳችሁ የፖሊስ ቃል ላይ አስተያየት እንድትሰጡ ህጉ ስላስቀመጠ በዛ መልኩ የሚሆን ይሆናል ቃሉን እንዲያቀርቡ ተፈቅዷል ኮፒውም ይድረሳችሁ ሌሎች ቀሪ ምስክሮችን 2ኛ፣ 37ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 52ኛ፣ 54ኛ፣ 55ኛ፣ 56ኛ፣ 57ኛ፣ 73ኛ፣ 74ኛ፣ 85ኛ እና 86ኛ የዐ/ህግ ምስክሮችን በተለዋጭ ቀጠሮ ዐ/ህግ አሁን እንደሚያደርጉት አይነት ትኩረት አድርገው ካሉበት አድራሻ አቅርበው እንዲያሰሙ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል ቀጠሮን በተመለከተ እናንተም አጀንዳ ያዙና ዐ/ህግ በምን ያህል ጊዜ ማቅረብ ትችላላችሁ ያንን ፍ/ቤቱም አጀንዳ የሚይዘው ይሆናል ማለት ነው:: ይሄ አሁን የተባለውንም አስተርጉሙ ጥያቄውንም ተቃውሞውንም ብይኑንም ለተከሳሾቹ ንገሩ አቶ አብራሂም ንገሯቸው::

የመጡበትም አገርም ስለሆነ ከ15 ቀን ላላነሰ ጊዜ ቀጠሮ ይሰጠን እናቀርባለን ከዛ በፊት የሚመጡልን ካሉ ግን ተከሳሾቹን መርዳት ስለሆነ ፍ/ቤቱን በማመልከት እያቀረብን እናሰማለን 15 ቀን ላላነሰ ጊዜ ግን አጠቃላይ ይሰጠን::

እሺ ረዘም ያለ ጊዜ እንሰጣለን ዳግም ከምንቀጥል ቀጠሮን በተመለከተ ለመጨረሻ ጊዜ ተለዋጭ ቀጠሮ ቀሪ ምስክሮችን ለመስማት ቀጠሮ ለሰኔ 30 እና ሐምሌ 1 በተከታታይ ለሁለት ቀን አጀንዳ ተይዟል ምስክሮቻችሁን ለሰኔ 30 አቅርቡ ሰኔ 30 እንሰማለን ያላለቀውን ደግሞ ሐምሌ 1 በተከታታይ እንሰማለን ሰሞኑን የተሰማው በችሎቱ የተመዘገበው በመቅረጸ ድምጽ

944

የተመዘገበው የሰኔ 4 ሰኔ 7 እና ዛሬ የሰኔ 8 መቅረጸ ድምጽ ወደ ወረቀት ተገልብጦ ከመዝገብ ጋር የመዝገቡ አካል እንዲሆን ታዟል፡፡ ይፃፍ የምስክሮቹ ቃል ተገልብጦ ይያያዝ ቀጠሮ ለሰኔ 30 እና ሐምሌ 1 ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል ጨርሰናል፡፡

ማ/ተ

945

የመ/ቁ. - 04486

ቀን - 25/1/2003 ዓ/ም

ዳኞች - ሙሉጌታ ኪዳኔ

- ሽለመ በቀለ

- አለማየሁ ሻረው ተሟልተው ቀርበዋል

ከሳሽ - ዐ/ህግ አቶ አረጋይ እንደሻውና አቶ ማሙሸት አበበ ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ 22ኛ እና 48ኛ በዋስትና ከውጭ ቀርበዋል ሌሎች ከማረሚያ ቤት ተሟልተው ቀርበዋል።

መዝገቡ የተቀጠረው የቀሩትን የዐ/ህግ ምስክሮች ለመጠባበቅ ሲሆን በዛሬው እለት 54ኛ መሀመድ ፈሪሳ 55ኛ ጁሀድ ሰኢድ 56ኛ አህመድ ከሚል ቀርበዋል ዐ/ህግ የቀረቡት ይሰሙ በቀረቡትና ባልቀረቡት ላይ አስተያየት ካለ ይግለጹልን

እሺ በዛሬው እለት ቀሪዎቹን 13 ምስክሮች እንድናቀርብ ነበር ትእዛዝ የተሰጠው

ይሰየማሉ እንጠይቃለን ይቆዩ ይጠየቃሉ እሺ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

በዛሬው እለት 13 ምስክሮች እንድናቀርብ ነበር ትእዛዝ የተሰጠን ከ13 ውስጥ 3ቱን ፖሊስ አቅርቦልናል ቀሪዎቹን 10ቹ ግን በተለያየ ቦታ የሚገኙ ስለሆነ አሁን ለማቅረብ አልቻልንም የሚል ምላሽ ነው የሰጠን ስለሆነም ቀሪዎቹ ላይ ፖሊስ ለመጨረሻ ጊዜ አፈላልጎ እንዲያቀርብልን አሊያም ደግሞ የሌሉ ከሆነ የሌሉ መሆኑን ማረጋገጫ እንዲያቀርብ እያሳሰብን አሁን የቀረቡት ሶስቱ ግን እንዲሰሙልን እንዲሁም ደግሞ ባለፈው ቀጠሮ ማረሚያ ቤት እንዲያቀርባቸው የታዘዙ አራት ምስክሮች ነበሩ እነሱም አሁን እንዳልቀረቡ ነው እየተረዳን ያለነው ስለሆነም ሶስቱ የሚገኙት በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ስለሆነ የቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዲያቀርብልን አንደኛው ደግሞ 87ኛ ምስክር በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ማረሚያ ቤት የሚገኝ ስለሆነ እሱም በዛው መልኩ እንዲቀርብልን ጥብቅ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን ነው የምናሳስበው ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው ቀጠሮ ላይ የሌሉ ምስክሮች ያለመኖራቸው የተረጋገጡ የምስክሮችን

946

ቃል እንድናቀርብ ፍ/ቤቱ ባዘዘው መሰረት በጣቢያ የሰጡትን ቃል በ145 መሰረት ኮፒ አድርገን አቅርበናል እናቀርባለን ነው ለፍ/ቤቱ እንሰጣለን።

የሌሉት በምን ምክንያት እንደሆነና

ከዚህ በፊት በአድራሻቸው የሌሉ የሞቱ የጠፉ መሆኑ ተረጋግጦ በችሎቱ ተረጋግጦ ምክንያቱ ቀርቦ ችሎቱ በጣቢያ የሰጡትን የምስክርነት ቃል እንድናቀርብ ትዕዛዝ የሰጠው አለ በፊቱ ቀጠሮ ላይ ማለት ነው በዛ መሰረት እንደ ትእዛዙ ፈጽመናል ኮፒ አድርገን አቅርበናል።

ተከላካይ ጠበቃ ለነማን ጠበቃ እንደሆኑና ስሞትን ይግለጹልን

ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ በ23ኛ፣ 37ኛ እና 38ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ነኝ

ምስክሮች ይማሉና ውጪ ይቆዩልን

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እንምላለን።

ውጪ ይቆዩልን ምስክሮች የሚያረጋግጡትን ጭብጥ ለፍ/ቤት ያስይዛሉ እና በማን ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እንደሚሰጡ

እሺ 54ኛ የዐ/ህግ ምስክር መሀመድ ፊስ የሚያስረዳው በ7ኛ፣ በ59ኛ እና በ61ኛ ተከሳሾች ላይ ነው በነዚህ ተከሳሾች

እሺ ይነሱልን ስማቸው

ስማቸው 7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ 59ኛ ተከሳሽ አብዱላሂ ሙሳ

ሲራጅ አህመድ ይነሱልን ስንተኛ ነው ያሉት

ይሄ የአሁኑ ሲራጅ አህመድ 7ኛ ነው 59ኛ ተከሳሽ አብዱላሂ ሙሳ

አብዱላሂ ሙሳ

61ኛ ተከሳሽ መሀመድ አሊ ወይም ደግሞ መሀመድ ጉዳ በቅጥል ስሙ መሀመድ ጉዳ ተብሎ የሚታወቀው

መሀመድ አሊ ወይም ጉዳ ይነሱ ይቁሙ

947

በእነዚህ ሶስት ተከሳሾች ላይ ነው የሚያስረዳልን በሲራጅ አህመድ ሙሳ ላይ ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክስ ቀርቦበታል በአብዱላሂ ሙሳ ላይ 7ኛ ክስ ነው በመሀመድ አሊ ሀሰን ላይ 34ኛ ክስ ናቸው እነዚህ ክሶች እንደ ክስ አቀራረባችን ነው የሚያብራራልን 54ኛ ምስክራችን ማለት ነው

እሺ ሌላኛው ምስክር

ቀጥሎ ያለው 55ኛ ምስክር ነው ጀዋል ሰኢድ ይባላል የሚያስረዳልን በ3ኛ ተከሳሽ አህመድ ኑር ኡርጌ እና

3ኛ ተከሳሽ ይነሱልን

በአህመድ ኑር ኡርጌና በ7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ ላይ ነው የሚያስረዳው

7ኛ ቅድም የተነሱት ናቸው

አዎ ሲራጅ አህመድ በእነሱ በሁለቱ ላይ ነው የሚያስረዳውም ክስ 4ኛ ክስ እና የዐ/ህግ 7ኛ ክስ ሁለቱን ክሶች እንደ ክስ አቀራረባችን የቀጥታ ምስክር የሚያስረዳ ነው

ሌላኛው ምስክር

56ኛ ምስክር አህመድ ከሊፍ ሼክ ነው የሚያስረዳው በ7ኛ ተከሳሽ በሲራጅ አህመድ 59ኛ ተከሳሽ አብዱላሂ ሙሳ በ61ኛ ተከሳሽ መሀመድ አሊ ሁሴን

ቅድም የተገለጹት ናቸው እንዴ

አዎ

ተከሳሾች

ተከሳሾች አዎ ትክክል ክሱ በ7ኛ ተከሳሽ ሶስቱም ተከሳሾች ቀርቦባቸዋል በ8ኛ ክስ ደግሞ 7ኛ ተከሳሽ በ7ኛ እና በ8ኛ ክስ ላይ ያሉትን እንደ ክስ አመሰራረታችን የሚያስረዱ ናቸው

ምስክሮች የቀረቡት በእነዚህ አራቱ ሰዎች ላይ ብቻ ነው

አዎ

ማን ይቅረብላችሁ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

948

54ኛ ምስክር መሀመድ ሀንስ

54ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - መሀመድ ሀንስ

እድሜ - 19

ሥራ - አርሶ አደር

አድራሻ- ምእራብ ሐረርጌ ጎሎዳ ወረዳ ጋራ ጋፋ ቀበሌ የቤት ቁጥር የለውም

ዛሬ ለምንድን ነው የመጡት

ለምስክርነት

በማን ላይ ነው ለምስክርነት የመጡት ድምጾትን ከፍ ያድርጉና

መሀመድ ጉዳ እና አብዱላሂ ሙሳ ሲራጅ አህመድ

እነዚህ አሁን የጠሩትን ሰዎች ያውቃሉ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ፀብ ዝምድና ይኖሮታል

የለኝም

ምን አጥፍተዋል ተብለው ነው የተከሰሱት በጥቅሉ ምን እንዳጠፉ ነው

የኦነግ ተባባሪዎች ናቸው

ሶስቱም ናቸው ወይስ የኦነግ አባል ናቸው ያሉት ሶስቱንም ነው ወይስ ከእነሱ ውስጥ የተወሰኑ ናቸው

አንዱ ከኦነጎች ጋር ይሄድ ነበር ሁለቱ

ማን ነው እሱ ስሙን ይጥቀሱልን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

መሀመድ ጉዳ

ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይጠይቁ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ

እሺ መሀመድ ፈንስ ሲራጅ አህመድ እና አብዱላሂ ሙሳ ላይ እና መሀመድ አሊ ላይ ነው ልመሰክር የመጣሁት ብለሃል ታውቃቸዋለህ እንዴ ትለያቸዋለህ የምትለያቸው ከሆነ ተነስና ለይልን

ይሰማችኋል ተከሳሾች

አይሰማም

እሺ አሁን መጨረሻ ላይ የተባለውን ይግለጹላቸው ቀጥሎ ያለውን ካልተሰማ አይሰማንም ብለው ይግለጹልንና ያልተሰማውን እንገልጽላቸዋለን፡፡

የምስክሩ ቃል ድምጽ አይሰማም

ምስክሩ የሚናገረውን አስተርጓሚ ደግሞ ስለሚናገረው እሱ የሚለውን ከሰማችሁ እሱ እንደተናገረ ይቆጠራል

ማለት እዚህ ጋ አማርኛ አይችሉም እነሱ ተከሳሾቹም

ወደዚህ ቢቀርቡ ደግሞ ቦታ ይመችናል እንዴ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይጠይቁ

እሺ መሀመድ እስቲ የጠራሃቸው ሰዎች እስቲ ስም ስማቸውን እየነካህ ጥቀስልን

ሲራጅ፣ መሀመድ ጉዳ፣ አብደላ

ይቀመጡና ይመስክሩ

ምን ሲያደርጉ ነው ያየካቸው እነዚህ ሰዎች መሀመድ ጉዳ የሚባለው ከአባዎች ጋር ሲሄድ አይቻለሁ ብለሃል መቼ ነው ሲሄድ ያየከው

በ2000 ዓ/ም ውስጥ

ምን ወር ላይ ነው

950

4ኛ ወር ላይ

ቀን ስንት ላይ ነው

አላስታውስም አላውቅም

የት ነው ቦታው የት አካባቢ ነው

ራሚስና ሰጋ

እንዲለይልን ቦታውን ምእራብ ሐረርጌ እያለ አጠቃላይ

ምስራቅ ሐረርጌ

እዚህ የጠቀስከው ቦታ ከኦነጎች ጋር ሲሄድ አይቻለሁ ብለሃል ከእነሱ ጋር ሄዶ ምን አደረገ ምን የፈጠረው ነገር አለ የምታውቀው እስቲ ለፍ/ቤቱ የምታስረዳው

ክላሽ መሳሪያ ይዞ ከኦነጎች ጋር ሲሄድ ነው ያየሁት

ክላሽ መሳሪያ ይዞ ከኦነጎች ጋር ሲሄድ አይቻለሁ ኦነግ ምንድን ነው ምን የሚሰራ ነው

ኦነጎች ከመንግስት ጋር ፀብ ይፈጥሩና ለብቻቸው ሌላ መንግስት ለማቋቋም ነው የሚፈልጉት

እሺ ይሄ ከሆነ የኦነግ ስራው ታዲያ ምን አድርገዋል ይሄንን ስራ በሚመለከት ያደረጉት ነገር አለ ወይ የምታውቀው መንግስትን ያደረጉት ነገር አለ ወይ መንግስት ሰራዊትም ላይ ይሁን ያደረጉት ነገር

መሀመድ ጉዳ ኦነግና መንግስት ሲጣሉ ከኦነጎች ጋር መሆኑን አውቃለሁ

ከኦነጎች ጋር ሆኖ ምን አደረገ

ከኦነጎች ጋር ሆኖ መንግስት ላይ ፀብ ማድረጋቸውን አውቃለሁ

ምንድን ነው ፀብ አደረጉ የምትለው ምን የተፈጠረውን ነው ገልጸህ ንገረን እንደዚህ ነው ብለህ

እስቲ ድገምልኝ ጥያቄውን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

መሀመድ ጉዳ ከኦነጎች ጋር ሆኖ ከመንግስት ጋር ፀብ አደረጉ እያለ ነው አደለም ዘርዝረህ ንገረን ምንድን ነው ፀብ ያደረጉት ተጣሉ የምትለውስ ምንድን ነው መጣላትን የምትገልጸው

መሳሪያ ተተኳኩሱ

ተተኳሰሱ

አዎ

የተጎዳ ሰው ነበር

ከመንግስት ወታደሮች አንዱ ሞቷል ዘጠኙ ደግሞ ቆስለዋል

እሺ መሀመድ ጉዳ ላይ ይሄንን አልከን አብዱላሂ ሙሳ እና ሲራጅ አህመድስ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቀው

ከመንግስት ጋር ኦነግና መንግስት ፀብ ካደረጉ በኋላ ከቆመ በኋላ እነዚህ ተከሳሾች አሁን ስማቸው የተጠቀሱት ተከሳሾች ውሃ ይዘው ለእነሱ ሲወስዱ ነው ያየሁት

ለማን ሲወስዱ ነው ያየከው አሁን ይኸውልህ መንግስትና ኦነግ ተጣልቶ ከዛ በኋላ እነዚህ ሲራጅ አህመድና አብዱላሂ ሙሳ የተባሉት ውሃ ይዘው ሲሄዱ ነበር ብሏል ለማን ለየትኛው ሰራዊት ነው ውሃ ይዘው ሲሄዱ የነበረው

ለኦነግ ወታደሮች

እነሱ ይሄንን ነገር ሲያደርጉ መሀመድ አሊ ከኦነጎች ጋር ሆኖ ጦርነት ሲከፍቱ አይተሃል ወይ ታውቃለህ ወይ ያየከውን ነው ወይ የምትነግረን እነሱ ሲረዱ እንዲሁም ደግሞ በጦርነቱ ወይም ደግሞ በፀቡ ወቅት መሀመድ አሊ ከኦነጎች ጋር አብሮ ሆኖ ተኩስ ሲከፍት ያየከውና ያወከውን ነው የነገርከን ወይ መሀመድ አሊ ጉዳ

ያየሁትን ነው

እሺ ጨርሻለሁ

መስቀለኛ ጥያቄ የ7ኛ ተከሳሽ 7ኛ ነው የሚቀድመው አደለም

ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

952

ለተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክር መልስ

ተከሳሹ የጠየቀው ጥያቄ በዛን ጊዜ ውሃ እኛ ስንወስድለት ወሰድንለት ወይስ እነሱ ናቸው ሰፈር ድረስ መጥተው የጠጡት ወይም የመጡት

ውሃ ያመጡት ሰፈር የሌለበት ጫካ ውስጥ ነው

አንተ በወቅቱ ሰው የሌለበት አካባቢ ላይ ምንድን ነው የወሰደህ ለምንድን ነው የሄድከው

ምንድን ነው ተቃውሞ

ተቃውሚችን ምስክሩ የመጣው በእነሱ ላይ ሊያስረዳ ነው መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅም ያለበት በዋና ጥያቄ ባነሳ ወይም እነሱ ላይ በመሰከረባቸው ላይ ነው አሁን እየጠየቁ ያሉት አንተ ምን እየወሰድክ ነበር ብለው እሱን እየጠየቁ ነው ያሉት ይሄ ደግሞ በህገመንግቱም ሰልፍ ኢንክሪሚኔሽን የተከለከለ ስለሆነ ራሱ ላይ ይሄንን ወስጃለሁ ይሄንን አድርጌአለሁ ብሎ እንዲመልስ ሊጠየቅ አይገባም

መቃወሚያውን አልተቀበልነውም ቅድም ምስክሩ ሲመሰክሩ አይቻለሁ በአይኔ ነው ያየሁት ብሏል ጫካ ከሆነ እንዴት ሆኖ እንዳየ ማረጋገጥ ስላለብን ለምን እንደሄደ መመስከር አለበት

እኔ ለራሴም ከኦነጎች ጋር ነበርኩኝ ከዛ ከእነሱ ተመልሼ መንግስት ይቅርታ አድርጎልኝ ነው የተመለስኩት

ሌላ ጥያቄ

አሁን ያዩትን ተጠይቋል በምን ምክንያት ሄደው እንዳዩ ተናግረዋል አሁን ስለ እሳቸው ሳይሆን በመሰከሩት ጉዳይ ላይ ስለ እርሶ ጉዳይ ቢጠይቁት

7ኛ ተከሳሽ ጨርሷል መስቀለኛ ጥያቄ

ቀጥሎ ያለው ማን ነው ስሙን ይንገሩንና

መሀመድ አሊ

እኔ በዛን ጊዜ ጦርነት ያደረኩት ሰራዊት ሆኜ ነው ወይስ ለሌላ ጉዳይ ለራሴ ጉዳይ ነበር እዛ የመጣሁት ወይ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ምስክሩ ደግሞ መልሱን በጥያቄ አድርጎ ነው የመለሰለት መሳሪያ የታጠቀ ሰው ለምንድን ነው የሚሄደው ብለን ነው የምናስበው

ከማን ጋር

ምስክሩ

መሳሪያ ይዞ የሚሄድ ሰው ምን ይፈጽማል ተብሎ ይታሰባል ነው ያለው

አዎ

ዝም ብሎ ነው መሳሪያ ይዞ የሔደው ወይስ ከየትኛው ጉሩፕ ጋር ነው

ከኦነግ ወታደሮች ጋር ነበር

ሌላ ጥያቄ

አስተያየት እየሰጡ ነው

ጥያቄ ጥያቄ ይጠይቁ

ባጠፋሁት ጥፋት መንግስት ይቅርታ አድርጎልኛ ነው ያለው ወይስ ከዛ ወዲህ እስከ አሁን ድረስ በምን ሁኔታ ነው ያለሁት ወይስ ከዛን በኋላ ነው የተመለስኩት

መቃወሚያችን መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠየቅ የሚገባው በዋና ጥያቄ ላይ ከኦነጎች ጋር እንደዚህ ሆኖ ተኮስክ እንደዚህ ይሄንን ግጭት ፈጠርክ በተባለው ነው ፈጥሬአለሁ ወይስ አልፈጠርኩም የመሳሰለውን ጥያቄ መጠየቅ እንጂ ከድርጊቱ ወዲህ ያለውን ነገር ምህረት ተደረገልኝ ወይስ አልተደረገልኝም እየተባለ መጠየቅ እንዲህ አይነት ክሮስ

መቃወሚያውን ተቀብለናል አሁን መጠየቅ የሚችሉት ይሄንን ድርጊት ፈጽመዋል በዚህ ጊዜ ብሎ በተናገረው ነገር ላይ እንጂ አሁን ያሉበትን ሁኔታ ወይም ምን እንደሚሰሩ ስላልተጠየቁ እና በመጀመሪያ ጥያቄ ስላልመሰከሩ መስቀለኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ በተነሳው ጉዳይ ላይ ስለሆነ ይሄንን ጥያቄ አንቀበለውም ሌላ ጥያቄ ካለ ብቻ ሊነሳ ይችላሉ ጨርሰዋል

ታስሬ ገባሁ ወይስ ከአሁን በፊት ታስሬ ተመለስኩኝ ወይስ አልተመለስኩም ከአሁን በፊት ታስሬ ነበር ጨርሼ ነበር የተመለስኩት የገባሁት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

959

በፍ/ቤት ውሳኔ አግኝተው ነው የታሰሩት ወይስ

ከአሁን በፊት በፍ/ቤት ቀርበን ማመልከቻ ጽፈን ጠይቀን ከዛም ተለቀን በነጻ ገባን

ስለ እሱ ምስክሩ ሊያውቁ ስለማይችሉ በዋና ጥያቄ ስላልተነሳ አንቀበለውም

ጨርሻለሁ

እሺ ቀጥሎ ያለው ምስክር

አብደላ ሙሳ

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ጠይቁ

እኛ ውሃ የወሰድንላቸው ጊዜ ቀን ነው ምሽት ነው

ቀንም ያመጡ ነበሩ ማታም ያመጡ ነበሩ

ቀንም ስንት ሰኣት ነበር ማታም ደግሞ ስንት ሰኣት ነበር

አሁን ሁለተኛ አመቱ ስለሆነ አላውቅም

ቀን ነው ለሊት ነው

ቀንም ምሽትም ያመጡ ነበር

ሌላ ጥያቄ

ምን ወር ነበር

4ኛ ወር ላይ ነበር

ጨርሻለሁ

ቀጥሎ ያሉት ተከሳሽ ስሞትን ይገልጋሩንና አልተመሰከረም እሺ ድጋሚ ጥያቄ ዐ/ህግ

የለንም

የድጋሚ ጥያቄ የለም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

953

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክር መልስ

አንድ ሰው ሞቷል 9 ሰው ቆስሏል ብለዋል ስማቸውን ያውቃሉ

የሞተውን በአይኔ አላየሁም ሰምቼ ነው ስሙ ደግሞ ንጉሱ ይባላል

የቆሰሉትስ

አላውቅም

እሺ እናመሰግናለን ከኋላ መቀመጥ ይችላሉ 55ኛ ምስክር

55ኛ ምስክር ጀዋል ሰኢድ ነው

55ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ጀዋድ ሰኢድ

እድሜ - እድሜዬን አላውቅም

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ጉሎዳ ወረዳ ጋረጋፋ ቀበሌ ዞን ምስራቅ ሀረርጌ

ዛሬ ለምንድነው የመጡት

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በእነማን ላይ

ሲራጅ እና አህመድኑር ኡርጌ ላይ

ሲራጅ እና አህመድኑር እስቲ እጅዎትን ያውጡ አህመድ ኑር እሺ ምን አጥፍተዋል ተብሎ ነው የተከሰሱት

የኦነግ ደጋፊዎች ናቸው ----

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

956

እሺ ጀዋድ እነዚህ አህመድኑር እና ሲራጅን የኦነግ ደጋፊዎች ናቸው ብለህል እስቲ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቃቸው የምታውቀውን ነገር ንገረን

እነሱ ያደረጉት እንደዛም ትልቅ ነገርም አላውቅባቸውም ነገር ግን አንደ እለት ምሽት ሲራጅ እቤቴ መጥቶ

ስንት ሰአት ላይ መጣ አለ

2 ሰአት

እሺ

እሺ ምሽት 2:00 ሰአት መጥቶ

እዚህ ላይ እንሂድ ብሎኝ

እሺ

አህመድ ኑር ሰፈረ ሄደን እርሻ የሚቆፍርበት እዚህ ግቢ ውስጥ ቁጭ በል ብሎኝ የእዛ አካባቢ ወይንም ደግሞ አካባቢው የእሱ ግቢ መሆኑን ስለማውቅ

የማን ግቢ መሆኑን

አህመድ ኑር

እሺ አህመድ ኑር ግቢ እሺ

3 መያዣው --- የጥይት መያዣው 3 የጥይት መያዣ እንደገናም ደግሞ ቡታንቶች ስንት እንደሆነ አላውቅም

መያዣ ምን ቆይ ወደ እዛ አትሂድ ሰውዬው በደንብ አድርጎ እየነገረህ ነው ሰምተህ በደንብ ንገረን ምንድነው እያለ ያለው

ኮዳ ነው ያለው

ኮዳ ምን ውስጡ ምን ያለው

--ስለው ጥይት የሚቀመጥበት

957

እኮ ካርታው ስለዚህ ምን ደግመህ ጠይቀው እስቲ ኮዳው ምንድነው ያልከው ኮዳ ውስጥ ምንድነው ያለው ብለህ ግልፅ አድርገው ነው ማለት ያለብህ

ጥይት አለበት ኮዳው

ጥይት ያለው ስንት ኮዳ

3

3 ኮዳ ጥይት

3 ኮዳ ጥይት

እሺ 3 ኮዳ ጥይት እና ልላ --

ቡታንቲዎች ደግሞ

እ

ባንት ምን አያህል እንደሆኑ አላውቅም

እሺ ምን አይነት ባንት እያልክ የምትገልፀው ምንድነው እስቲ በደንብ ንገረን በለው

የሚለበስ ከስር የሚለበስ አጫጭር ባንቶች

እሺ እሺ እሱን እና ሌላስ

ከስር የሚለበስ ነው ወይንስ ቁምጣ ነገር ነው

ከሱሪ ስር የሚለበሰው

እሺ ሌላስ

እነዚህን ነው የማውቀው

እሺ እነዚህን ምን አደረገ

ይሄንን ከእዛ ወስደን አብረን ተመልሰን እነዚህ ኦነጐች እዛ እታች ስላሉ ያ ሰፈር አካባቢ ስላሉ ከእዛ ወሰድንላቸው እና ከእዛ ሂድ እና ግባ አሉኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ሂድ እና ግባ አሉህ

በእዛን ጊዜ ደግሞ 2 ሰው የሚቀመጡ ነው ያየሁኝ

እሺ እዛ የተቀመጡት 2 ሰዎች የሰጣቹሀቸው ምንድን ናቸው እዛ የነበሩ ሰዎች

ጐፈሬ ያላቸው የኦነግ ወታደሮች ናቸው

ይሄንን ማድረጋቸውን ነው የምታውቀው

አዎ

ይሄ የሆነው መቼ ነው

በ2001

ስንተኛው ወር ላይ ነው

4ኛው ወር ላይ

በቀን ስንት ላይ ነው

አላውቅም ቀኑን አላስታውሰውም

ቀኑን አላውቀውም የት ቦታ ነው የት አካባቢ ነው

ዲምቱ

የት ዞን ነው

ምስራቅ ሀረርጌ

የት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው

ጋራጋፋ ውስጥ

በቃ ጨርሰናል

መስቀለኛ ጥያቄ 7ኛ ተከሣሽ 7ኛ ነው ስንተኛ ነው ይሄኛው

7ኛ ተከሣሽ

እሺ ይቀጥሉ መስቀለኛ ጥያቄ በእርሶ ላይ ተናግሯል አይደል እጅዎትን ያውጡ እና አይደለም ከኪስዎ ውስጥ እጅዎትን ያውጡ እና ጥያቄ ጠይቁ

ለ7ኛ ተከሣሽ መስቀለኛ ጥያቄ

እኔ በ2፡00 ሰአት ላይ የአሀመድኑር ሰፈር የወሰድኩህ ጊዜ ወደህ ነው ወይንስ አስገድጄህ ነው ተገደህ ነው ወይንስ ወደህ ነው የሄድከው

ፈርቼ ሰዎቹ ስለማይለቁኝ በግዳጅ ነው የሄድኩት

ቆይ ቆይ እኔስ የሄድኩት ወድጄ ነው ወይንስ ተገድጄ ለነብሴ ስለሚያሰጋኝ ፈርቼ ነው የሄድኩኝ

እሱም እንደ እኔው በግዳጅ ቶሎ ብላችሁ እንዲህ እንዲህ ቦታ ሄዳችሁ ከአሀመድኑር ላይ እንዲህ እንድታመጡ ስለተባለ በግዳጅ ነው 2ታችንም የሄድነው

እሺ ሌላ ጥያቄ

ጨርሻለሁ

ቀጥሉ ስምዎትን ይንገሩን እና

አሀመድኑር ኡርጌ

እሺ ይቀጥሉ መስቀኛ ጥያቄ ካለ

የተከሣሽ መስቀለኛ ጥያቄ

እቃውን ከእኔ ጋ መውሰዱን እሱ ነው የነገረህ ወይንስ በአይንህ አይተህ ነው

ለብቻ ቁጭ በል እያሉት ነበረ አካባቢው ደግሞ እሱ የሚኖርበት አካባቢ መሆኑን ስለማውቅ እኔ እና እሱሳንነጋገር ይሄ ካባቢ የእሱ መሆኑን ስለማውቅ እና ድምፃቸው ደግሞ ሲነጋገር የእሱ መሆኑን ስለማውቅ እቃውን ከእዛ በኋላ አምጥተው እኔ ጋ አደረጉ

ሌላ ካለ ይቀጥሉ

960

ይሄንን እቃውን እኔ ነው ያመረትኩት ወይስ ከየት ነው ያመጣሁት ወይስ ከእኔ ጋ ወስዶ አንተ ጋ ማምጣቱን እንዳት ነው ልታውቅ የቻልከው

እኔ እሱ ያምርት አያምርት የማውቀው ነገር የለም ግን ከእሱ ጋ ተወስዶ እኔ ጋ እንደመጣ ብቻ ነው የማውቀው

በአይንህ አይተካል ወይ

ከየት እንደተወሰደ አላውቅም ነገር ግን ይዘው መንገድ ላይ ስንሄድ ከእሱ ጋ እንዳለን እቃውንም አይቻለሁ

በአይኔ አይቻለሁ አላየሁም ነው ያሉት

በአይን ከየት እንደተወሰደ አላየሁም ነገር ግን

እሱንስ አይተዋል አላዩም

እሱን በአይኔ አይቼዋለሁ

ከመሬት ውስጥነው ያወጣሁት ወይንስ ከቤት ነው ያወጣሁት ወይንስ ከየት ነው ያመጣሁት

የተገናኙት 2ቱ ነበሩ እኔ

ማን እና ማን

ሲራጅ እና አህመድ ኑር ነው የተገናኙት እኔን ግን እንደ ስውር አድርገው አንተ እዛ ቁጭ በል ብለውኝ ነው 2ቱ የተገናኙት

ከቦታው አብሬያቸው ሄድኩኝ ወይንስ አልሄድኩም ብሎ ሲጠይቅ አልሄድክም ብሎ መለሰለት ለምስክሩ ማለት ነው

ጨረሱ

ጨርሻለሁ

የድጋሜ ጥያቄ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

እሺ ጀዋድ እኔ በወቅቱ ፈርቼ ነው የሄድኩት ብለህል ከእነሱ ጋ ሲራጅ መጀመሪያ አንተ ጋ መጥቶ እንሂድ ሲልህ ማን ሂድ ብሎ እንዳዘዘው የምታውቀው ነገር አለ ወይ በእራሱ ፍቃድ ይሂድ ወይንም ሌላ ሰው ሄደህ ከአህመድ ኑር ጋ ያንን እቃ አምጣልን ብሎት ይሁን የምታውቀው ነገር አለ ወይ ወይ የሰማከው ነገር አለ ወይ

ሲራጅ ነው አይደለ ስሙ

አዎ ሲራጅ አንተ እቤት መጥቶ አንተን ና እንሂድ እና እንውሰድ ያለህ ሲራጅ ነው የሆነ ቦታ ደርሰን እንመጣለን በማለት ወደ አህመድ ኑር እርሻ ወሰደኝ ያልከው ከእቤት ነው ማታ መጥቶ ያልከው

አዎ ሲራጅ ነው

ሲራጅንሳ ሌላ ሰው ሄደህ አምጣ ብሎት ይሁን ለኦነጐች ሰራዊቶቹ ያንን እንድትወስድ ያደረገው በእራሱ ፍቃድ መጥቶ ይውሰድ የምታውቀው ነገር አለ ወይ በእራሱ ፍቃድ ይውሰድ ወይንስ ሌላ ሰው አዞት አንተን ይዞ ሄዶ ይውሰድ የምታውቀው ነገር አለ ወይ

በወቀቱ በግዳጅ ይሂድ አይሂድ አላውቅም ግን እሱ ብቻውን ነው ያስገደደው ሰው ከኋላ ይኑር አይኑር አላውቅም ግን እሱ ብቻውን ነው እኔ ጋ የመጣው

ጥሩ ብቻውን መጣ አንተስ ጋ ሲመጣ ምን ብሎ ነው የወሰደህ ወደ አህመድ ኑር ጋ ሊወስድህ ሲል ምንድነው ብሎ ያለህ ላንተ ቀጥታ

የሆነ የኦነግ ሰዎች ከእዚህ እታች ተቀምጠው እንዲህ እንዲህ ጋ ከአህመድ ኑር ጋ አምጣ ስላሉኝ ብቻህን አታምጣ ከሰው ጋር ሆነህ አምጣ ስላሉኝ አንተም እንቢ የምትል ከሆነ ለእነሱ እነግርልሀለሁ እና አብረከኝ ሂድ እና እንውሰድ ሲለኝ እኔም በቃ ፈርቼ እሺ ብዬ አብሬው ሄድኩኝ

ጨርሰናል

ጨረሱ

ነገሩም --- የቆየ ስለሆነ የነገሩ ትንሽ የቆየ ስለሆነ ትምህርትም ስለሌለኝ ነው

አሁን በመጨረሻ የመለስከው መልስ ላይ ነው ማጣራት የምፈልገው

962

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ቅድም እሱም እኔም ተገደን ነው ብለህል አንተን ያስገደደህ ሲራጅ ነው ወይንስ ሌሎች ሰዎች ናቸው ሲራጅ ነው ያስገደደህ ወይንስ ሌሎች ናቸው

በወቅቱ ሌላ ሰው ከእሱ ጋር እኔ ጋ አብሮ አልመጣም

አይደለም ሌላ አለ አላልኩም ያስገደደህ ሲራጅ ነው ወይንስ ሌላ ሌላ ሰው ከሌለ ሲራጅ ነው ማስጠንቀቂያው የሰጠህ ወይንስ ማን ነው

የሲራጅ ቃል ነው ሄዶ ለእነሱ ይነግረኛል ብዬ ነው የፈራሁት የእሱ ቃል ነው ያስፈራኝ ያስገደደኝ

በእዛ አካባቢ ላይ ሰዎች ላይ በደል እየፈፀሙ ስለሆነ እኔም ላይ እንዳይደርስ ነው

ሌላው ደግሞ ከእዚህ ጋር ተያይዞ እሱም እንደኔው ተገዷል ብለህል ቅድም ስታስመዘግብ የመጀመሪያ ጥያቄ ላይ መስቀኛ ጥያቄ ላይ ስለ እሱ መገደድ እንዴት ነው ያወከው ማነው ያስገደደውስ ስለ እሱ መገደድስ እንዴት አወቅህ

አላውቅም

ያስገደደውን ሰው ካላወቅህ ተገዷል ለማለት ለምንድነው የቻልከው

ላውቅ የቻልኩት ሰዎቹ በእዛ አካባቢ ስለቆዩ የሰውም ሀብትም እየያዙ ያርዱ ነበረ እንደገናም ደግሞ ሰዎቹንም ህዝቡንም እየደበደቡ ነበረ እሱም ከእነሱ ዘንድ ነው የመጣሁት ስላለኝ በእዛ ነው ላውቅ የቻልኩኝ እና እኔም ፈርቼ የሄድኩኝ ለእዛ ነው

ማለት መገደዱን ከእነሱ ጋ መምጣቱ መገደዱን ያሳያል

አሁን ስለ እሱ አይደለም የተጠየቁት ሲራጅ ተገዷል እኔም ተገድጄ ነው ብለዋል ቅድም ሲራጅ መገደዱን በምንድነው ያወቁት ከእነሱ ጋ መምጣት ማለት መገደድን ያሳያል

በሀሳብ ነው ተገዷል ያልኩት እንጂ በአይኔ አላየሁም

በግምት ማለት ነው

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አዎ በግምት ነው

እናመሰግናለን ከኋላ ቁጭ ይላሉ 56ኛ ምስክር

56ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አህመድ ካሚል

እድሜ - 28

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - ምስራቅ ሀረርጌ ወረዳ - ጉሎዳ ወረዳ ቀበሌ - ጋራጋፋ

ዛሬ ለምንድነው የመጡት

ለምስክርነት

በእነማን ላይ ለምስክርነት መጡ

እነ መሀመድ አሊ ሀሰን ላይ

ብቻቸውን ነው ሌላ አለ

አብደላ ሙሳ ሲራጅ አህመድ

አሁን ከቆሙት ውስጥ ነው እዩ እስቲ አንዴ

ሲራጅ አህመድ መሀመድ አሊ ሀሰን አብደላ ሙሳ

በእነሱ 3ቱ ላይ ነው

አዎ

እነዚህ 3ቱን ያውቃሉ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ፀብ ወይም ዝምድና ይኖርዎታል

የለኝም

ምን አጥፍተዋል ተብለው ነው የተከሰሱት

የኦነግ አባነሎች ናቸው ተብለው ነው

0/ሕግ ዋና ጥያቄ ይጠይቁ

የ0/ሕግ ዋና ጥያቄ

የህመድ የአባል የኦነግ አባል ናቸው ብለህል እስቲ የኦነግ አባል ሆነው ምንድነው ያደረጉት ምንድነው ወራናአብደቆቢ በለው እስቲ

እነሱ የአብደቆቢ ወታደሮች ነበሩ አለ እነዚህ ወታደሮች የመንግስት ወታደር ካዩ ይሸሻሉ ነገር ግን የኦነግ ወታደሮች ካዩ ግን አይሸሹም

የማንን ካዩ

የኦነግ ወታደሮችን አይሸሹም ይመንግስት ወታደሮች ካዩ ግን ይሸሻሉ

እስቲ እነዛ ወራናአብደቆቢ ያላቸው በምን ስር የተደራጁ ናቸው

ኦነግ ስር

እሺ ቀጥል በለው ምን እንዳደረጉ ይንገረን

እነሱ ሲመጡ እነሱ እነዛ ወታደሮች ሲመጡ ሰፈር ውስጥ ሄደው ምግም ምናምን ሲሰጡ

ሌላስ

እንደገናም ደግሞ እነዛን ወታደሮች ሲያዩ ከመንግስት ወታደር መሸግሸጋቸውን ወይንም መደበቃቸውን

ሌላስ

አንድ ቀንም እንዲሁ የኦነግ ወታደሮች መጥተው ሲራጅ እና አብዱላሂን ጥሩልኝ ብለውን የኦነግ ወታደሮች እና የመንግስት ወታደሮች ከእነሱ ጋር

965

ቀደም ብሎ ያለውን ተርጉመው ቀደም ብሎ ያለውን ተርጉም ጥራልኝ ብኋል እነማንን ነው ጥራልኝ ያለህ ይሄንን ተናግሯል በትክክል ተርጉመው

እነማንን ነው ጥራ ያለው

ኦነጐች ናቸው ጥሩ ያሉ

ማንን ነው ጥሩ ያሉት

ሲራጅ እና አብደላን

ከእዛስ ጠራቸው አልጠራቸውም

ጠራ

እሺ ከእዛስ

የእኛ ወታደሮች እና የመንግስት ወታደሮች ጦርነት ሲከፍቱ በእዛ ነው የተጠፋፋነው እና የእኛ ወታደሮች ካያችሁ ይዛችሁ አምጡልን አሉ

ከእዛ ምን ሆነ

ይዘው አመጡላቸው

ስንት ወታደሮች ሰበሰቡላቸው

አንድ 70 ሰዎች ይዘው ሰጧቸው

ሰብስበው ለማን ሰጡ

ለኦነግ

በ--- ሲራጅ አብደላ እና መሀመድ አሊ ወይንም አህመድ ጉዱ የሚባለው ምንድነው ትጥቅ ነበራቸው ወይንስ እንዴት ነው የሚንቀሳቀሱት ያለው ሲራጅ አብደላ ሙሳ እና መሀመድ አሊ ወይንም እህመድ ጉዳ ይሚባለው

ነበራቸውም

የፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

966

---መሳሪያው ምንድነው

ክላሽ

እሺ. ይሄ የሆነው መቼ ነው በለው አመተ ምህረቱ

2000

ወሩስ

ታህሳስ

እሺ. ቦታው የት ነበረ ይሄ የሆነበት

ጋራ-ጋፋ ዲምቱ የሚባል አካባቢ.

ዞኑስ

ምስራቅ ሀረርጌ

ወረዳውስ

ጋራ-ጋፋ

እሺ. ሌላ ጥያቄ የለም

ጉሎሮዳ ወረዳ ጋራ-ጋፋ ቀበሌ

እሺ. ጨርሰዋል

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

መስቀኛ ጥያቄ

7ኛ ተከሣሽ መስቀለኛ ጥያቄ

አንተን እንዴት አውቀውህ ነው አብደላ እና ሲራጅን ጥሩልን ያሉት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ማታ በሰፈር ድረስ መጥተው እኛ ሰፈር መጥተው አብደላ እና ሲራጅ ታውቃለህ ወይ አሉኝ አዎ አውቃቸዋለሁ አልኩኝ

ማናቸው እንደዛ የሚሉት

ማታ እደር እና ጠኒት ያሉበት ሄደህ ጥራልን አሉኝ

ማነው እንደዛ የሚሉት

ኦነግ

እነሱ እንዲህ ብለውኛል ሲናገሩ ወታደሮች ስለጠፉብን ይዛችሁ ሰብስቡልን ያሉ ጊዜ አንተ ከእኛ ጋር ነበርክ ወይ

እንዲህ አይነት ቦታ ስላለን እዛ ቦታ ጠርተህ አምጣልን ስላሉኝ እዛው እኔ እነሱን ይገና በሄድኩት ጊዜ እዛው ነው እነሱ ይሄንን ነገር ለእነሱ ያሳለፉት ወይንም የነገሩት

እኛ ሰብስበን ስናመጣ ይዘን ስናመጣ አይተሀል ወይ

እኔ ወደ እቤት ስሄድ ማታ እሱ ወታደሮቹን ይዞ ሲሄድ አየሁ

አንተ ሌላ ስራ የለህም ወይ

የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን በጥያቄዉ ላይ በዋና ጥያቄ ላይ የተነሳ ጥያቄም አይደለም ከጉዳዩ ጋም አግባብነት የለዉም

መሳሪያ አላቸው ብለሀል ያ መሳሪያ መንግስት የሰጠን ነው ወይንስ አባዎ ነው ኦነጐች ናቸው ያስታጠቁን

መሳሪያው የእራሳቸው የግላቸው ነው ለእራሳቸው ያላቸው ይሄ መሳሪያ መንግስት ያውቃል ወይንስ አያውቅም

መንግስት እነሱ እንዳላቸዉ ያውቃል

ሌላ ጥያቄ ካለ

7ኛ ተከሣሽ መስቀለኛ ጥያቄ ጨርሷል

968

እሺ ቀጥሎ ያለው ስንተኛ ተከሣሽ ነዎት ስምዎትን እሺ

የመሀመድ አሊ

መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥሉ

የተከሣሽ መስቀለኛ ጥያቄ

በወቅቱ እኔ ከኦነጐች ጋር ነበርኩኝ ወይንስ ከእናንተ ጋር ነበርኩኝ ወይንስ ከእነሱ ጋር ነበርኩኝ

እሱ ከእነሱ ጋር አልነበረም

ከእነማን ጋር

ከሲራጅ እና አብደላሂ ጋር መሀመድ አሊ አልነበረም

ይቀጥሉ ከእነሱ ጋር አልነበሩም ብለዋል ሌላ የሚጠይቁት ነገር ምንድነው

እኔ የምጠይቀው ይሄ ነገር ከአሁን በፊት በመንግስት ፊት ላይ ሄደን ሂስ እና ግሌይስ አድርግተን ያለቀ ጉዳይ ነው ወይንስ ከእንደገና የተመለስንበት ጉዳይ ነው

የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን ምስክር እየመሰከረ ያለው ---የሰሩትን ድርጊት ነው ከመንግስት ጋር በተያያዘ ነገር የተናገረው ነገር የለም በ2ኛ ደረጃ ደግሞ ወቅቱን ተናግሯል 2000 ዓ/ም ታህሳስ ነው ብሏል ዓ/ምቱንም ወሩንም ተናግሯል

መቃወሚያውን ተቀብለናል በዋና ጥያቄ ስላልተነሳ ይሄንን አንቀበለውም ሌላ ጥያቄ ካለ

ጨርሰዋል

እሺ ስምዎትን ይንገሩን እና ይቀጥሉ

ይቀጥሉ መስቀለኛ ጥያቄ

የተከሣሽ መስቀኛ ጥያቄ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እኔ እና ሲራጅን አነጐች እንዴት አውቀው እኛን ሲጠይቁ ቻሉ እንዴት እንዳወቁ እኔ አላውቅም ነገር ግን ሲራጅ እኛ አብደላ ሙሳን ታውቃቸዋለህ ወይ ብለው ሲጠይቁኝ አዎ አውቃቸዋለሁ ብያለሁ

ሌላ ጥያቄ

ይህ መሳሪያ እናንት መሳሪያ አላችሁ ያልካቸው ይሄ መሳሪያ የእኛ መንግስት

አሁን ከላይ ስለሌሎች ሳይሆን ስለ እርሳ ብቻ የእኔ ነው ወይንስ አይደለም ይሚለውን ከሆነ መጠየቅ ይችላሉ

ይሄ መሳሪያ የግል ንብረት መንግስት የሚያውቅ ንብረት ነው ወይንስ የጠላት መሳሪያ ነው

መሳሪያው የግሉ የእሱ የእራሱ ነው

ጨርሰዋል

መንግስት ያውቃል ወይንስ አያውቅም

ያውቃል

ጨርሰዋል

ጨርሰዋል

የድጋሜ ጥያቄ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

እሺ ቅድም መንግስት የሚያውቀ መሳሪያ ይዘዋል ብለሀል ከኦነግ ጋራ ሲቀላቀሉ የነበሩት ይሄንን መሳሪያ ይዘው ነው ወይንስ ሌላ መሳሪያ ይዘው ነው በለው

የእራሳቸውን ነው ያላቸው

እሺ ሌላው ቅድም መሀመድ አሊ ሁሴን መሀመድ ጉዳን አንተ አብረሀ አልነበርክም ከእነሱ ጋር ብለከው ነበረ ይሄ አብሮ ያልነበረው የተበታተኑት ወታደሮችን ፈልጉልኝ ሲሉ ነው ወይንስ መቼ ነው በለው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅ/ጽ

970

ጥያቄው ምንድነው

ቅድም መሀመድ ጉዳን አብረህ አልነበርክም ከእነሱ ከሌሎቹ 2ቱ ከሲራጅ እና ከአብዱላሂ ጋር አብረህ አልነበርክም ብሎታል አብሮ ያልነበረው ያን ጊዜ ማታ መጥተው 2ቱን ፈልግልን ሲሉህ ነው ወይንስ ደግሞ ሌላ ጊዜ ነው በለው

እንደዛ ነው አይደለ ጥያቄው ማታ ሲመጡ ነው ወይንስ በሌላ ጊዜ ነው

እሱ ከሲራጅ እን መሀመድ አሊ ጋ አልነበም

የለም ያለው መቼ ነው ማታ ነው

ስራጅ እና አብደላ ሙሳ ጥራልን ያሉ ጊዜ አልነበረም እሱ

አልነበረም እሺ ጨርሰናል

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ተበተኑ የተባሉት የኦነግ ሰራዊት በምን ምክንያት ነበረ ተበተኑ የተባለው

ከመንግስት ሰራዊቶች ጋር ስለተጣሉ በእዛ የነበረ እረብሻ ጊዜ ነው የተጣሉት

ሌላው ደግሞ የተበተኑትም አብደላ እና አብደላ ሙሳ እና ሲራጅ አህመድ መሀመድ አ--- ይዘው ሲሄዱ አይቻቸዋለሁ ብለሀል ከእነዛ ኦነግ ሰራዊቶች ውስጥ እነማን ነበሩ የምታውቃቸው አሉ ወይ ተበተኑ የተባሉት እና ይዘዋቸው

ዲማ ጅሎ ሚባል አውቃለሁ

ሌላስ

ኡርጌ ---- የሚባልም እውቃለሁ

ጥራ አሁንም የምታውቃቸውን

ኡርጌ እና ዲማ ነው የማውቃቸው

ቁጥራቸው ስንት ይሆናሉ ነው ያልከው

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

971

70 ሰዎች

70

70 ሰዎች

70 ሰዎች

አዎ

እነዚህ 70 መሆናቸውን በትክክል ቆጥረህ ነው ያረጋገጥከው ወይንስ ነግረውክ ነው የሰማከው

እነሱ እኔ ወደ እቤት ስሄድ እነሱ ደግሞ ወደ እዛ ሲሄዱ ዱካቸው እየተከተልኩኝ ነው የቆጠርኳቸው

እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ ፖሊስ የመጨረሻ ጊዜ አቅርብልን ያሉት ስንተኛ ስንተኛ ምስክር ናቸው

2ኛ ምስክር አብዲ ሁሴን

2ኛ

አብዲ ሁሴን

2ኛ በቁጥር ብቻ ንገሩን

2ኛ 37ኛ 42ኛ 43ኛ 52ኛ 54ኛ 54ኛ ቀርቧል ይቅርታ 57ኛ

በትክክል ያጣሩት እና

እሺ እሺ

የተሳሳተ ትእዛዝ እንዳንሰጥ

እሺ 57ኛ 73ኛ 74ኛ 85ኛ እና 86ኛ አንድ ጊዜ ልድገመው

ይቆዩ ትክክል አይደለም የቆጠሩት አሁን ከእዚህ ቦታ እንዲያቀርቡ የታዘዘው 13 ምስክሮች ነው አሁን 3ቱ ተሰምተዋል 4ቱ ቃሊቲ 3ቱ ቃሊቲ ነው ---

972

አይደለም አይደለም

አንዱ ሐረርጌ

የቃሊቲው እና የሀረርጌው ሳይደመሩ ነው ዛሬ 13 አቅርቡ የተባልነው የቃሊቲው እና የምስራቅ ሀረርጌው ከማረሚያ ቤት የሚቀርቡ ስለሆነ በእኛ አማካኝነት ላይ ---

እሺ ይቆዩ 2ኛ

2ኛ 37ኛ 42ኛ 43 52 57 73 74 85 እና 86 ፖሊስ እንዲያቀርብ

ፖሊስ አፈላልጐ እንዲያቀርብልን የሌሉ ከሆነም ስላለመኖራቸው ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ትእዛዝ እንዲሰጥልን

አቤት

ፖሊስ እነዚህን አፈላልጐ እንዲያቀርብልን የሌሉም ከሆነ ምስክሮቹ የሌሉ ከሆነ በአካባቢያቸው የማይገኙ ወይንም ይሞቱ የጠፋም ከሆነ ማረጋገጫ እንዲቀርብልን

እሺ ሌላ ከቃሊቲ የሚቀርቡት እነማን ናቸው

ከቃሊቲ የሚቀርቡት ጣሂር አሊ መሀመድ 11ኛ ምስክር ነው

11ኛ

11ኛ ምስክር ጣሂር ሀጂ መሀመድ

በቁጥር ብቻ ንገሩን

እሺ 14ኛ ምስክር 16ኛ ምስክር

16ኛ

ምስክር እነዚህ ከቃሊቱ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ስለሆነ ከእዛ በቀጣይ ቀጠሮ ማረሚያ ቤቱ እንዲያቀርቧቸው ትእዛዝ ደርሶት ከሆነ ለዛሬው ቀጠሮ ያላቀረበው ያላቀረበትን ምክንያት ለችሎቱ እንዲያስረዱ ነው ትእዛዝ እንዲሰጥልን ነው

እሺ 87ኛ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ቀጥሎ ደግሞ 87ኛ ምስራቅ ሀረርጌ ማረሚያ ቤት ነው ያለው የምስራቅ ሀረርጌ ማረሚያ ቤት ነው ያለው የምስራቅ ሀረርጌ ማረሚያ ቤት እንዲያቀርብልን በዛሬው ቀጠሮም ያላቀረቡበትን ምክንያት እንዲያስረዱ ትእዛዝ ይሰጥልን ጥብቅ ትእዛዝ ይሰጥልን

እሺ -- ምስክር ያሉት ምስክሮች በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት ቃል

እሺ በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት ቃል

በቀበሌ እንደሌሉ እና የሞቱ መሆናቸውን ከቀበሌ ማረጋገጫ ቀርቧል

ከቀበሌ ማረጋጫ ቀርቦ ችሎቱም ከተረከበ በኂላ አይቶ አገናዝቦ በ

የእነማን እንደሆኑ እንደሆኑ እና የገፁን ብዛት ኮፒውን

የሌሉ የጠፋ እና የሞቱትን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ሰኔ 8 ቀን 2002 በዋለው ችሎት እንድናቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል

ፍ/ቤት መቼ ነው ---

ሰኔ 8 2002 ዓ/ም ይሄ ትእዛዝ ተሰጥቷል እንድናቀርብ ታዞ የነበረውም 21ኛን 23ኛ 5ኛ እና 7ኛ ምስክሮች እንዲሁም 49ኛ ምስክሮች በቀበሌ የሌሉ መሆኑን ማረጋጫ አቅርበን በእዚሁ መሰረት እንዲቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል የእነሱ በጣቢያ የሰጡት ቃል እንድናቀርብ ትእዛዝ ተሰጥቷል በእዛ መሰረት ኮፒ አድርገን

እንደገና ደገመው የስንተኛ አሁን --- ምስክሮች

-- ቃል አልተሰማም እና ይሰማልኝ እያለ እያስመዘገበ ነው

21ኛ 23ኛ

21ኛ

23ኛ

23ኛ

5ኛ

5ኛ

7ኛ

7ኛ

49ኛ

49ኛ

በአካባቢው የሌሉ ስለሆነ የምስክርነት ቃላቸውን

ይሄ በቀበሌ ተረጋግጧል

አዎ ማረጋገጫ ቀርቧል ፍ/ቤቱም ትእዛዝ ሰጥቶበታል 20ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ደግሞ ኢብራሂም ከዲራ የተባለው የሞተ ስለሆነ እሱን ማረጋገጫ አቅርበናል ማረጋገጫ በመቅረቡ ምክንያትም ለዛሬ ቀጠሮ እንድናቀርብ የምስክርነት ቃሉን ኮፒ እንድናቀርብ ትእዛዝ ተሰጥቷል ዛሬ ይዘን ቀርበናል

ለተከሣሾችስ ኮፒ

አዎ ለተከሣሾች ኮፒ አለ እላዩ ላይ ማስታወሻም የእያንዳንዱም ምስክር በየትኛው ተከሣሽ ላይ እንደመሰከረም ጫፍ ጫፉ ላይ ማስታወሻ ተያይዞበታል

ከስር ያለው የፍ/ቤቱ ድርሻ ነው

እሺ የተከሣሾች ድርሻ በ2 ኮፒ ነው አቤት

23ኛ 37ኛ 38ኛ የ3ቱ ተከሣሾች

ስምዎትን ይንገሩ እና

ኢብራሂም መሀመድ

እሺ ምንድነው የሚያመለክቱት

የምናመለክተው የተከበረው ፍ/ቤት ዐ/ሕግ እስካሁን ድረስ ምስክሮቹን ሲያቀርብ እና በምስክሮቹ ማቅረብ ሂደት ላይ ትልቁ ችግር የፈጠረው እና ለፍትህም ስርአት እንቅፋት የሚሆነው በዐ/ሕግ በኩል የሚቀርቡት የምስክሮች የአቀራረብ ሁኔታ ነው በተለያየ ጊዜ ዐ/ሕግ የተለያየ ምክንያቶችን እያቀረበ የፍትህም ስራው እንዲጓተት ካደረገው እና እነዚህ ተከሣሾችም 3 አመት ያለ ፍትህ እንዲቆዩ ያደረገበትም ምክንያት አንዱ ይሄ ነው ይሄ ደግሞ የስነ ስርአት ህጉም የማይፈቅደው ነው አሁን የተመዘገበውን ነገር ባለፈው የዛሬ 2 ወር ያስመዘገበውን ጉዳይ ነው ዐ/ሕግ ባለፈው 11ኛ 14ኛ እና 16ኛ ምስክሮቻችን ቃሊቲ እስር ቤት ናቸው ያለውን በወቅቱ ለፍ/ቤቱ መቃወሚያ አቅርበናል ወደ ፊት ታቀርባላችሁ በሚል ነው የታለፈው ዛሬ እንደገና ደግሞ ምንድነው 20ኛው ምስክር የሞተ ስለሆነ ማረጋገጫም እንደሚያቀርብ በእዛን ጊዜ ቀጠሮ ይዞ ነው የተለየው ዛሬም አላቀረበም ሌሎቹ ዳግሞ በ21 በ23 5ኛ እና 7ኛ 49ኛ ምስክሮች የሌሉ ስለሆነ በፖሊስ ጣቢያ በኩል ይሰጡትን የማረጋገጫ ቃል እናያይዛለን የሚለው ነገር ያቀረበውም በእዛን ጊዜ ነው ነገር ግን ከእዛ ውስጥ ባልሳሳት 7ኛውን ተከሣሽ በተመለከተ ምስክሮቹ የሉም የተባሉት ማለት ነው 7ኛው ተከሣሽ ላይ ዛሬ ደግሞ ቀርበው ምስክሮች ተሰምተዋል ማስረጃውን አያይዛለሁ ከሚለውም ውስጥ አንዱ ማስረጃ የቀረበበትን ነው ማለት ነው ሌላው ደግሞ ባለፈው እንደዚሁ ከ2 ወር በፊት እነዚህን 13 ምስክር 13 ተከሣሾች ላይ ማነው 13 ናቸው የቀሩን ምስክሮች ብለው አስመዝግበዋል አሁን ያቀረባቸው ምስክሮች ደግሞ ከሌሉት ውስጥ ወይ ለማስረጃ ቃላቸውን እናቀርባለን ብሎ ካለው ውስጥ ነው ምስክሮች ያቀረበው 13ቱን የዛሬ 2 ወር ሙሉ ለምን ምክንያት ሊያቀርብ እንዳልቻለ አሁንም ግልፅ አይደለም ዐ/ሕጉ ስለዚህ ይሄ ደግሞ የበለጠ የፍትህ ስራውን ማጓተት የፍርድ ሂደቱንም ማጓተት ስለሆነ ዐ/ሕግ ከበቂ በላይ ማስረጃ አሰምቷል ከአሁን በፊትም በተለያየ ጊዜ ስናመለክት እንደነበረው የ2 ዞን ተከሣሾች ስለሆኑ አንድ ላይ የተጣመሩት ቢያንስ ሂደቱን እንኳን ለማፋጠን እንዲመች ተለይቶ በቀርብ ያሉት ምስክሮች ተሰምተው ሁኔታው ብይን ተሰጥቶ አንድ እርምጃ እንዲወሰድ ስንወተውት ነበረ

አህን መጀመሪያ የታለፈው እና በብይን ሌላ ዳኛ ያለፈው እሱን ሌላ ነው

አዎ ምንድነው ለማሳሰብ የፈለግነው አሁን እነዚህ የተባሉት ምስክሮች ከእዚህ በኋላም የሚቀርቡ ስላልሆኑ ነው ዐ/ሕግ የሚጠይቃቸውን ምስክሮች ታልፎ በብይን ታልፎልን ወደ ሚቀጥለው የስር ፍርድ ብይን ሂደቱ ቢኬድልን የሚል ማመልከቻ ነው ያለን የተከበረው ፍ/ቤት

976

ዛሬ 20ኛ ምስክርን በተመለከተ ማረጋገጫ እናቀርባለን ብለዋል አላቀረቡም ነው

አላቀረቡም

እና ምን ይሁንልን ነው

ይታለፍልን ነው የሚሉት ነገር ታልፎልን ብይን ይሰጥልን ምክንያቱም ዐ/ሕግ በየጊዜው አቀርባቸዋለሁ የሚለውን ማስረጃዎች ማቅረብ አልቻለም እስከ ዛሬ ድረስ ያለው ሂደት ማንተቱም የሚያሳየው ይሄንኑ ነው የሚያረጋግጥልን ስለዚህ ከእዚህ በኋላም እነዚህን ምስክሮች ማቅረብ ስለማይችል ቀሩኝ የሚሉት ምስክሮች ታልፎልን ብይን እንዲሰጥልን ነው የተከበረው ፍ/ቤት የምንጠይቀው

የመልስ መልስ በእዚ ጉዳይ ላይ አንፈልገውም

ለመልስ መልስ አይደለም ለችሎቱ እንደማሳሰቢያ ነው ከእዚህ በፊት በታዘዘው እና ሚስ--- ፋክት ስለሆነ ነው የፍ/ቤቱ መዝገብ ----

ይሄኛው በእዚህ ጉዳይ ላይ የመልስ መልስ አንቀበለውም የሚፈለገውን ነገር ይሄ ነገር ይደረግልን ብሎ ለፍ/ቤቱ ገልፀዋል ፍ/ቤቱ ይሄንን መቃወሚያ ሰምቶታል አስፈላጊም አይደለም የሚለውን እንደ እራሱ የሚሰጠው ትእዛዝ ስለሆነ ይሄኛው በምስክሮች ላይ መረጋገጫ እናቀርባለን ብላቹሀል እየተባለ ነው አሁን ደግሞ እናንተ አቅርበናል ብላቹሀል ተያይዟል ብለዋል አልተያዘ---ይኛው ማስረጃው ውድቅ እንደሚሆን ከአሁኑ አረጋግጣችሁ እኛ ገና አዲስ መዝገብ --- ስለሆነ ነገሩን አንድ በአንድ ስላላየነው ማስረጃ መጀመሪያ አስቀድሞ ፍ/ቤቱ ካልፈቀደ እና ካልተያዘ አሁን --- ፍ/ቤቱ ካመነ ነው የሚቀበለው ይሄንን በእዚህ ነው የምንዘጋው ስለሌላ ጉዳይ በተነሳው ነገር ላይ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ስለሚሰጥ ብይን ስለሚሰጥ ይሄንን እናቀርባለን እርሶ ምንድነው ለማለት የፈለጉት አጠር አደርገው ብቻ ይንገሩን

በ2001 ዓ/ም ነው እኔ የታሰርኩኝ እንደገና ደግሞ ተከስሼ ክስ ቻርጁ ተሰጥቶች ይገፔዋለሁ እንደገናም ደግሞ ዐ/ሕግ

አሁን ስለ --- ሁኔታ አይደለም የምንፈልገው ምስክሮች ይቅረቡ አይቅረቡ በሚለው ጉዳይ ላይ ብቻ ነው አስተያየት የምንቀበለው

977

በሌላኛው አንቀፅ ነው እንደገና ይሄንን ክስ ቻርጅ ተሰጥቶኝ ይገዩ እያለሁ በሌላኛው አንቀፅ ክስ ነው የቀረበብኝ ትላንትና ስናገረው ይሄንን ነው

ይሄንን መዝገብ ሲመረመር የምናየው ነገር ስለሆነ ይሄንን አንቀበለውም ጊዜያችንን --- አቤት ምስክርን በተመለከተ ብቻ ነው አስተያየት የምንቀበለው

ቃሊቲ አለው የተባለው ምስክር እድሜ ልካቸውን የተፈረደ ምስክር ነው ዐ/ሕግ ሆን ብሎ

የእኛ የፍ/ቤት ጉዳይ ስለሆነ ይሄንን አንቀበለውም

እና በተለይ

ይሄ የፍ/ቤት ጉዳይ ነው

እርሶ ማረጋገጥ የምንፈልገው ጠበቃችንም አላ---

ምስክሮች ይቀርባሉ አይቀርቡም ገና ብይን ልንሰጥ እያሰብን ያለውን እና የፍ/ቤት ጉዳይ ስለሆነ አሁን የምታነሱትን አንቀበለውም መቀጠል እንችላለን ይቆዩ በቃ ጨርሰናል አሁን ትእዛዝ እና ብይን ነው የምንሰጠው ተከሣሾች ያቀረቡት መቃወሚያ ምስክሮች ያሉት ግማሾቹ በማረሚያ ቤት ስለሆነ ማረሚያ ቤቱ ለምን እንዳላቀረበ መግለፅ ስላለበት አስፈላጊውን ፍትህ ለመስጠት ምስክሮችን የምስክሮች ቃል መስማት ወይ ደግሞ ያልተገኙ ከሆነ በህጉ መሰረት አስፈላጊውን ትእዛዝ መስጠት ስላለበት ለምን እንዳላቀረቡ በግልፅ ያስረዱት ነገር እና የገለፁት ነገር ስለሌለ ይሄ ሆኖ ባለበት ሁኔታ የምስክሮች መ--- አስፈላጊ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበለውም

ት እ ዛ ዝ

የዛሬ የችሎት ውሎ ተገልብጦ ከመዝገብ ጋር እንዲያያዝ ታዟል ዐ/ሕግ ከፖሊስ ጋር በመሆን 2ኛ 37ኛ 42ኛ 43ኛ 52ኛ 57ኛ 73ኛ 74ኛ 85ኛ እና 86ኛ ምስክሮችን ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያቀርብ ታዟል ይፃፍ የቃሊቲ ማረሚያ ቤት 11ኛ 14ኛ 16ኛ ምስክሮችን ያላቀረበበትን ምክንያት በመግለፅ ጭምር ከአሁን በኋላ ካላቀረበ ያላቀረበበትን በቂ ምክንያት ካላስረዳ በአስተዳደሩ ላይ አስፈላጊው የህግ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን አውቆ በቀጠሮ ቀን ከመግለጫ ጭምር እንዲያቀርብ ታዟል ይፃፍ የምስራቅ ሀረርጌ ዞን ማረሚያ ቤት እንዲሁ 87ኛን ምስክርን ያላቀረበበትን ምክንያት ከመግለፅ ጭምር እንዲያቀርብ ያለ በቂ ምክንያት

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

978

ያላቀረበውም ከሆነ አስፈላጊው የህግ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን አውቆ ከግለጫ ጭምር እንዲያቀርቡ ታዟል ይፃፍ ቀጠሮ ለጥቅምት 25/2003 ይመቻቹሀል ቀጠሮ እረዘም ያደረግነው ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ትእዛዙ ወጪ ሆኖ ደርሶ እስከሚያቀርቡ ድረስ ሌላ ችግር እንዳይፈጥሩ ነው በዛ ወይንስ አነሳ

25 ላይ -- ሌላ ቀጠሮ አለኝ ---

አቤት

23 ወይም --

እሺ 23 ላይ

አዎ ወደ እዞ ወይም ወደ እዚህ

ይሆናል 23 ላይ

አዎ

ከኋላ እጅ የሚያወጡት ምንድነው --- እዛጋ

ለጥቅምት 23 2:30

ተጨማሪ ትእዛዝ

ስምሽ ማነው

ፋጢያ

ፋጢያ ስንተኛ ተከሣሽ ነሽ ፋጤ ማን ፋጤ አህሚድ ፋጤ አሚ መቼ ነው ቀጠሮ ያለፈው መስከረም 3 ነበረ እና በተገኘው ጊዜ መሄድ ይችላሉ ስንተኛ ተከሣሽ እንደሆነ -- ያስታውሳሉ 8ኛ ተከሣሽ ተጨማሪ ትእዛዝ ተሰጥቷል 8ኛ ማተከሣሽ ፋጤ አሚ ከአጃቢ ፖሊስ ጋር በመሆን የት ሀኪም ቤት ነው የሚሄዱት ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝ ሆስፒታል ተወስደው እንዲታከሙ ታዟል ቀጠሮ አልተለወጠም ጥቅምት 23/2002 2:30

መ/ወ

979

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 24/2/2003ዓ.ም

ዳኞች - ሽለመ ቀበለ

- አለማየሁ ሻረዉ

- አብረሃም ተጠምቀ ተሞልተዉ ቀርበዋል

ከሳሽ - ዐ/ህግ አረጋዊ እንደሻዉ ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ 73 ሰዎች የ2ተኛ 37ተኛ 38ተኛ 3ተኛ 10ኛ 43ተኛ 47ተኛ 57ተኛ 59ኛ 65ተኛና 72ተኛ ተከሳሾች ከጠበቃ አቶ ኢብራሂም መሀመድ ጋር ቀርበዋል 4ተኛና 45ተኛ ተከሳሾች ከጠበቃ አቶ መሀመድኑር አብዱልከሪም ጋር ቀርበዋል 22ተኛና 43ተኛ ተሳሾች በዋስትና ከዉጪ ቀርበዋል ሌሎች ተከሳሾች ከማረሚያ ቤት ከመስሪያ ቤቱ ተከላካይ ተጠበቃ ብዙየዉ ተሾመ ጋር ቀርበዋል 8ተኛ ተከሳሽ ጥቁር አንበሳ እስፔሻላ ይዝድ ሆስፒታል ተኝቶ ይገኛሉ ተብሎ ተገልጾል

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረዉ የዐ/ህግ ቀሪ ምስክሮችን ለመጠባበቅ ሲሆን 74ተኛ ምስክር አብዱረህማን አብዱላህ ቀርበዋል ሌሎች አልቀረቡም ዐ/ህግ የምስራቅ ሐረር ጌ ፖሊስ ጽህፈት ቤት 2ተኛ 37ተኛ 42ተኛ 43ተኛ 52ተኛና 57ተኛ ምስክሮች ላይ ምላሽ ስላልሰጠን ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠን ብለዋል 73ተኛ መሀመድ 73ተኛ ምስክር መሀመድ ኡመር በድሬደዋ ማረሚያ ቤት ይገኛል ተብሎ ስለተገለፀ ይታዘዝልን 74ተኛ ምስክር የቀረበ ስለሆን ይሰማልን 85ተኛና 86ተኛ ምስክሮች ፖሊስ ለማግኘት ካልቻለ በማስረጃ አስደግፎ እንዲያቀርብ ይታዘዝልን ብለዋል 87ተኛም ምስክር ከምስራቅ ሐረር ጌ ማረሚያ ቤት እንዲቀርብልን 11ተኛና 14ተኛ እና 16ተኛ ምስክሮች ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዲቀርቡ ይታዘዝልን ብለዋል 8ተኛ ተከሳሽ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች ከሆስፒታል ይገለጽልን ብለዋል የ22ተኛና 37ተኛ 38ተኛ 2ተኛ 3ተኛ 10ኛ 43ተኛ 47ተኛ 57ተኛና 59ኛ 65ተኛና 72ተኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ከአንድ ወር በፊት ታዞ በትናንትና እለት ዐ/ህግ 6ቱ ምስክሮች በምስራቅ ሐረር ጌ ከምስራቅ ሐረር ጌ

ተንቀሳቅሰዋል እየመጡ ስለሆነ ይሰሙንል ብሎ ችሎት ስላልተሟላ ነገ ይሰማ ይሰማልን እንሰማለን ብሎ ፍ/ቤቱ በአዳር ይዞ ዛሬ ደግሞ ዐ/ህግ እነኛ 6 የተባሉት ምስክሮች የምስራቅ ሐረር ጌ ፖሊስ ምላሽ አልሰጠንም ማለቱ የዐ/ህግ አቀራረብ ተአማኝነት የሌለዉ ስለሆነ ይህ መዝገብ ለመጨረሻ ጊዜ ተብሎ የታዘዘዉ በሐምሌ ወር 2002 ዓ.ም ስለሆነ ይህ ችሎት በ25/1/2003 ዓ.ም ተሰይሞ ካስመዘገበዉ 13 ምስክር 3 ያህል የተሰሙ ሲሆን ዐ/ህግ በአንድ ላይ አቅርቦ አቀርባለው ያለ አሞልቶ ያላቀረበ ስለሆነ መቅጣት እንዳልቻለ ተመዝግቦ በተሰሙት ብይን እንዲሰጥ ብለን ለዛሬ የመጨረሻ ጊዜ ተቀጥሮ ያላቀረበ ስለሆነና በትናንትና እለት ያስመዘገበዉ ቃል የሚጋጭ ስለሆነ ይታለፈው 85ተኛና 86ተኛ ምስክሮች በተመለከ ፖሊስ ማግኘት እንዳለቻለ መግለጫ ሰቶ እያለ እነሱ የሰጡት ቃል በማስረጃነት ከማቅረብ ዉጪ እነሱን ማዘዙ አግባብነት የሌለዉ ስለሆነ ይታለፍ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ይቅረብልን ያሉት አስመልክቶ ፍ/ቤቱ ረዘም ያለ ቀጠሮ የሰጠዉ ትዕዛዙ እንዲደርሳቸዉ ታስቦ በመሆኑ እነኚህን ሰዎች ሊቀርቡ ሊያቀርቡ ስላልቻሉ መታዘዝ ድጋሚ አይገባዉም ዛሬ የቀረበዉ 74ተኛ ምስክር ቀደም ሲል እዚህ ቀርቦ የመሰከሩ ስለሆነ ድጋሚ ሊሰሙ አይገባም ብለዋል የ4ተኛና 45ተኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ዐ/ህግ ተከሳሾች ለብዙ ጊዜ ተስረዉ ማረሚያ ቤት እያሉ ምስክሮቹን ባለማቅረቡ መብታቸዉ እየተጣሰ ስለሆነ ከ87 ምስክሮች 77ቱን ያህል ያሰሙ ስለሆነ የማቅረብ መብታቸዉ ታልፎ መዝገቡ ለብይን እንዲቀጠር ይታዘዝልን ብለዋል የመስሪያ ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ የተለየ ሀሳብ የለኝም ብለዋል 74ተኛ ምስክር የዚህ በፊት ችሎት ቀርቤ በአብዲረህማን ባሌ ላይ ቃሌን ሰጥቻለዉ ብለዋል ፍ/ቤቱ የቀረበዉን አቤቱታና የተሰጠዉን መቃወሚያ መርምሮ በ23/2/2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት 6ቱ የዐ/ህግ ምስክሮች የምስራቅ ሐረር ጌ ፖሊስ እያመጣ መሆኑን ዐ/ህግ በስልክ አረጋግጠናል ይሰሙልን ብሎ እንደገና ዐ/ህግ በ24/2/2003 ዓ.ም ፖሊስ ምላሽ አልሰጠንም ብሎ መግለፁ በአጠቃላይ ዐ/ህግ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ ከግንቦት18/2001 ዓ.ም ጀምሮ ከ20 ጊዜ ታዞ ያላቀረበ ስለሆነ ዐ/ህግ 2ተኛ 37ተኛ 42ተኛ 43ተኛ 52ተኛና 57ተኛ እና 85ተኛ ምስክሮችን አቅርቦ የማሰመት መብቱ እንዲታለፍ ብይን ተሰቷል ዐ/ህግ 86ተኛ ምስክር ይሰሙንል ያሉ ከመዝገብ ተመርምሮ 86ተኛ ምስክር ቃላቸዉ መስጠታቸዉ ተረጋግጦል 74ተኛ የዐ/ህግ ምስክርን በተመለከተ ምስክሩ ቃሌን ሰጥቻለዉ ይበሉ እንጂ ፖሊስ ጣቢያ በተለያያ ቀን የምስክርነት ቃል በተለያያ ሰዎች ላይ የሰጡ ስለሆነ የተመዘገቡትን በዐ/ህግ ማስረጃነት በ74ተኛ 79ኛ ተራ ቁጥር ላይ ስለሆነ የዐ/ህግ 74ተኛ ምስክር በ79ኛ ተራ ቁጥር ላይ ተየቆጠረዉ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ በ74ተኛ ተራ ቁጥር ላይ 31ኛና 38ተኛ ተከሳሾች ላይ የተቆጠረ በመሆኑ በነሱ ላይ ያልተሰማ ስለሆነ በነሱ

931

ላይ እንዲሰማ ብይን ተሰቷል በሌሎች ጉዳዮች ላይ የዚኛዉን ዐ/ህግ ምስክር ከሰማን በኋላ ትዕዛዝ የሚሰጥ ይሆናል የዐ/ህግ 74ተኛ ምስክምር ቃለ መሀላ ይፈጽሙና ዉጭ ይቆዩልን ማይክራፎኑን ይያዙ

በእዉነት ለመመስከር በአላህ ስም ቃል እገባለዉ

የሚያረጋግጡልን 74ተኛ ፀብጥ ያሲዛሉ

74ተኛ ምስክራችን አብዱረህማን አብዱላ በ38ተኛ ተከሳሽ ላይ 21ኛ ክስን ነዉ የሚያስረዳዉ የሚያስረዳዉ ፀብጡን ማለት ነዉ በክሱ ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜና ቦታ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ ዝርዝር ተከሳሹ በሐረማያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ተይዞ የተከሳሽነት ቃሉ በሚሰጥበት ሰአት በፍቃደኝነት በክሱ ላይ የቀረበዉን ዝርዝር ማለት ነዉ በፍቃደኝነት ለምንም መገደድ ማድረጉን ይህንን አድርጎ ጥፍተኛ ነኝ ሲል የእምነት ቃሉን የሰሰጥ የሰማ መሆኑን ቀርቦ ያስረዳልናል

የዐ/ህግ 74ተኛ ምስክር አብዱረህማን

ስም - አብዱረህማን አብዱላህ

38ተኛ ተከሳሽና 31ኛ አንዴ ይግለፁልን 38 31ኛ 31 ላይ ያስረዳን አላሉም ዐ/ህግ 38ተኛ ላይ ብቻ ላይ ነዉ እሺ

እድሜ - 47

ስራ - የመንግስት ሰራተኛ ነኝ በአሁን ሰአት

አድራሻ - ሐለማያ ቀበሌ 01 የቤ/ቁ 416

ዛሬ ለምንድ ነዉ የመጡት

ለምስክርነት

ተከሳሽን ያቃሉ የቃሙትን

አይቼዋለዉ አዉ

ፀብ ዝምድና የሌትም

992

በፍፁም

ምን አጥፍቷል ተብሎ ነዉ የተከሰሰዉ

እኔ ምንድ ነዉ

ዝርዝሩን በኋላ ይነግሩናል በጥቅሉ ምን አጥፍቷል ተብሎ ነዉ

ያዉ የኦነግ ከኦነግ ንክኪ አለህ ተብሎ ነዉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እሺ አቶ አብዱረህማን ተከሳሹን አይቻዋልዉ ከኦነግ ጋርንክኪ አለዉ ተብሎ ነዉ የተከሰሰዉ ብለዋ እስኪ ምንድ ነዉ ከዚህ በተከሰሰበት ጉዳይ የሚያቁት ምን ማድረጉን ነዉ ምን መሆኑን ምን ማረጉም ነዉ የሚያዉቁት እስቲ

አንደኛ ነገር እንግዲ እኛ እንግዲ ምንድ ነዉ ጊዜዉ 1999 ዓ.ም ነዉ

እሺ

5ተኛ ወር አካባቢ ይመስለኛል

8ተኛዉ ወር ቀን ስንት ላይ እንደሆነ ትዝ ይሎታል

ቀኑን በፍፁም አላስታዉሰዉም ለጊዜ አለማያ ወረዳ ፖሊስ እኔ በዛ ጊዜ የህዝብ ተመራጭ ነበርኩኝ ነበርኩኝ ምንድ ነው የነሱን ጉዳይ ለማየት በታዛቢነት የሚሉት ነገር እድናዳምጥ እዛ ጋብዘዉን ነበር

የት ነዉ የተጋበዙት

አለማያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ እዛ ተጋብዘን የነሱን ጉዳይ እድናዳምጥ በታዛቢነት ጋበዘን ሄድን ከዛ በኋላ እንግዲ አነሱን ለፖሊስ ያለምንም ግዳጅ አለ አይደለም ያለምንም ተጽኖ ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ በትክክል ተመልክቻለዉ

ምን ብሎ ነዉ ቃል የሰጠዉ እስቲ

እንደኛ ነገር እሱ በዛ ጊዜ የመንግስት ሰራተኛ እንደነበረና

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ምን እንደ ነበር የሚሰራዉ

ጤና ጣቢያ አለማያ ወረዳ ፊንቅሌ አካባቢ የጤና ጣቢያ የጤና ባለሙያ ነበረ በጊዜ ዉስጥ አንደኛ ነገር ይሄ ሆኖ በዛ ወቅት ደግሞ እንደገና ከመንግስት አለ አይደለም በዛዉ በሚሰራበት ሴክተር መንግስት ለሕዝብ እንዲያድል የሰጠዉ የወባ መከላከያ አጎበር አጎበር ዉስጥ 30ዉም ለኦነግ እንደላከ ስናገር የሰዉ

እስቲ ለኦነግ ላኩ አለ

ላኩ ሲል -----

ማን ለሚባል የኦነጎቹ አመራር ማን ይባላል የምን ነዉ ላኩ ሲል የሰሙት

እኔ በዛ ጊዜ ዉስጥ ለማን እንደሆነ ለኦነግ ታጣቂዎች ልኪያለዉ ሲል ብቻ ነዉ እኔ የሰማሁት አንዱ ይሄ ነዉ 2ተኛ ነገር ደግሞ እንደገና -----የኦነግ ሲል ሆኖ የኦነጎ ለኦነግ በእንትን ስሰራ እንደ ነበረ ሲናገር የሰማሁት

ሌላ የሰጠዉ አሁን የቁስ የሰጠዉ ቁስአዊ እርዳታ አለ ከወባ መከላከያ አጎበር ዉጪ የሰሙት

አዉ ምንድ ነዉ ገንዘብ ነዉ መሰለኝ ገንዘብ ነዉ

ምን ያህል ገንዘብ

480 ብር አካባቢ 80 ብር አዉ

480 ብር ምን አርጊለሁን አለ

ይሄ አንድ ኢብሳ ሌንጮ የሚባል አለ ይህ ኢብሳ ሌንጮ የሚባለዉ እንደሱ አባባል ማረጊ ነዉ ለሱ የኦነግ ከፍተኛ አመራር ነዉ ከራሱ ጀምሮ ካሉት ከሕብረተሰቡ ------- እየለቀመ ወደዛ መላኩን ሲናገር በትክክል ሰምቻለዉ

እሺ ከመቼ እስከ መቼ ነዉ ይሄንን ስራ ሰራዉ ብሎ አምኖ ሲናገር የሰማህዉ ከመቼ ጊዜዉ ከመቼ እስከ መቼ ነዉ

እኔ በርግጥ 1997 እስከ 99 እስከተያዘበት ቀን ነዉ መሰለኝ እንደዛ ሲናገር ሰምቻለዉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐ/ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቆጥር

እሺ በወቅቱ ይሄንን ቃሉ ሲናገር በምን ሁኔታ ላይ ነዉ እስቲ እንዴት ሆኖ ለመርማራዉ ሲናገር

በትክክለኛ ያለ ምንም እኔ በታዛቢነት እንደ ሽማግሌዎች እዛ ምንም ነገር ያለ ምንም ተጽኖ አንድም ነገር ግዳጅ እንት ሳይል ሳያስገድዱት ሳያስገድዱት ሲናገር ሰምቻዉ እንግዲ

በቃ ጨርሻለዉ

ጨርሰዋል እሺ

መስቀለኛ ጥያቄ

የ38ተኛ ተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ አቶ አብዱረህማን

አቤት

አሁን ለፍ/ቤቱ ስገልጹ ተከሳሹ ያለ ምንም ተጽኖና ግዴታ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለዉ ብለዋል

በትክክል

ይሄንን ቃሉ ስሰጥ የሰሙት የት ነዉ

አለማያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ

እርሶ እንዴት እዛ ሄዱ

ታናገርኩኝ በታዛቢነት እድንገኝ እዛ እነሱ ቃላቸዉ ስሰጡ በታዛቢነት እኛ እድንገኝ ያን ጊዜ እኛ የሕዝብ ተመራጭ ነበርን

መርማሪዉ ማን ይባላል

እ

መርማሪ ቃሉን ሲቀበለዉ የነበረዉ እኛንተ በታዛቢነት ሆናቹ

ከክፍለ ሀገር ነዉ የመጡት እኔ በትክክል ስሙን ላቀዉ አልቻልኩም

ስንት ናቸዉ

እኛ ሶስት ነን እኛ

ፖሊሶቹስ

ፖሊሶቹ 2 ናቸዉ

ያዉቋቸዋል ስማቸዉን

እኔ ላቃቸዉም

እሺ ይሄ ተከሳሽ በዛን ጊዜ የት ነበረ እኛንተ ቀድማቹ ነዉ ቁጭ ያላቹት ወይስ እሱ ነው ቀድሞ ገብቶ ቁጭ ያለዉ

እኛ ቀድመን ቁጭ ብለናል እነሱ መጡ እነሱ ይዘዋቸዉ መጡ እኛ ቁጭ ባልንበት

ከየት እንዳመጧቸዉ ያዉቃሉ እኔ ላቅም ኬት እንደ መጡ እኔ አላዉቅም

ታዲያ በተጽኖ ስር ይሁኑ አይሁኑ በምን አረጋገጡ

እኔ ተጽኖ ስር ይኑሩም አይኑሩም የተናገርኩት ቃል የለኝም እኔ የተናገርኩት ምንድ ነዉ እነሱ በዛ ጊዜ ዉስጥ እኛ በታዛቢነት እዛ ቁጭ ብለን ስንሰማ ነገሩን አንድም ነገር የተደረገባቸዉ ተጽኖ አላየሁም ብዬ ለማለት ፈልጊ ነው

እሺ ተከሳሹ እነዛ ፖሊሶቹ በሚነግሩት ጊዜ አንተ የምትናገረ ቃል ወደ ፊት ማስረጃ ሆኖ በፍ/ቤት ላይ ይቀርብብሀል በፈቃደኝነት የምትሰጠ ቃል ይሄንን መብትህን ከፈለክ ዝም ማለት ትችላለህ ፈቀደኛ ከሆንክ ቃልህን መስጠት ትችላለህ ብለዉ ነግረዉታል ይሄንን ቃል ሲገልፁለት ሰምተዋል እርሶ

አልገባኝም አንዴ ድገመ እስቲ ማ ፖሊሶቹ ናቸዉ ለሱ እንዳዛ የሚሉት

አዉ ፖሊሶቹ ይሄ ቃል

እኔ አልሰማሁም እኔ እኮ አልሰማሁም ቢያለዉ እንዳዛ እንዳዛ ሲሉት እኔ አልሰማሁም እሱ የተናገረዉን ቃል ብቻ ነዉ ለፖሊስ ሲሰጥ ያየሁት እኔ አልሰማሁም

እንጂ ይሄንን ቃል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ምን ይናገር አልሰማሁኝም

አልሰማህም

አልሰማሁም

ይሄን ቃል እሱ ከሰጠ በኋላ ተገቦላታል

ለማ

ለተከሳሹ ወይንም አየሁት ላልከዉ

እኔ እዛዉ አብረን ቁጭ ብለናል እኛ አብረን ቁጭ ብለን እንዳለን ፖሊሶቹ አነበቡ በዚህ ቃል ነዉ የሰጡት ምን አምን ነገር ብለዉ እንትን ስሉ ሰምቻለዉ

ስንት ናቸዉ ቃላቸዉን የተቀበሏቸዉ ሰዎች

እነሱ 2 ናቸዉ አልኩኝ

አይደለም በዛን ጊዜ በተከሳሽነት ከገብተው እኛንተ ተዛቢነት ቁጭ ብላቹ ስታዩ ከዚህ ተከሳሽ በስተቀር ሌላም በእለቱ ቃሉን የሰጠ ሰወ ነበር

አንዱ አብዱረህማን ባሌ ነዉ

2ቱም በአንድ ቀን በዛን ቀን ነዉ የቀረቡት

በዛ ጊዜ ነበሩ አዉ

እሺ እነኝህ ተከሳሽ ይሄ ተከሳሽ ቃሉን ከሰጠ በኋላ ቃሉን ተነቦለት በነዛ ፖሊሶች ይሄ አንተ አሁን ሰማሁት ያልከዉን ቃል ላይ ፈርሜል

ሲፈርሙ አላየሁም

ተነቦለታል

ሲፈርሙ አላየሁኝም

ተገቦለታል አላልኩም

ተነቦለታል ነገር ግን ለኛም ለአጠቃላያች ነዉ የተነበበዉ

ለተከሳሹ

ለኛ ለአጠቃላያችን ተከሳሾቹ አሉ እኛም ታዛቢዎች 3 ነን እኛ እዛ አካባቢ አለን ይሄ ነገር ተነቦ እኛ ፈርማናል

ፈርሟል እሱስ

እሱ አልፈረመም እኔ ግን ፈርሚያለዉ እኛ ፈርማናል

ስለሱ አታዉቅም

እኔ ስለሱ የማዉቀዉ ነገር የለም

መርማሪዉስ ፈርሟል

እኔ እኛ ታዛቢዎች ነን የፈረምነዉ ታዛቢዎች ብቻ ነዉ

ይኸዉ የተጠየኩት የተጠከዉን ጥያቄ ብቻ መልስልኝ

እሱ እኔ

መርማሪዉ ስፈርም አይተሀል

አይ አላየሁም

እሺ ይበቃናል የተከበረዉ ፍ/ቤት

የድጋሚ ጥያቄ ዐ/ህግ

አንድ ቀረን አንደ ነጥብ

ቃል ከሰጡ በኋላ ተከሳሾቹ ይሄ ተከሳሽ ቃሉን ከሰጠ በኋላ ወዴት ነዉ የሄደዉ ወዴት እንደወሰዱት ታዉቃለህ

እኛ ወተን ነዉ የሄድ ነዉ እኛ ወደ ስራ ነዉ የሄዱ ነዉ እኛ ከዛ በኋላ ወዴት እንደ ሄዱ እኛ አናዉቅም

988

የዐ/ህግ የድጋሚ ጥያቄ

አቶ አብዱረህማን

አቤት

ተከሳሹ ቃል በሚሰጥ ሰአት በእርሶ ፊት ማለት ነዉ በኔ ፊት አልተገደደም ብለዋል

አዉ አልተገደደም

እስቲ አልተገደደም ተጽኖ አልደረሰበትም ሊሉ የቻሉት ከምን ተነስተዉ ነዉ እስቲ እሱስ ለፖሊሶቹ ሊነግራቸዉ የነበረዉ ምን እያለ ነበር እነሱ በል እያሉት ነዉ ወይስ እሱስ ምን እያለ ነዉ

አይደለም በፍጹም እኔ እኮ ቅድም እኮ ተናግራለዉ እኮ ይሄን ቃል በሚሰጥበት ሰአት እራሳቸዉ አለ አይለም የራሳቸዉን ሀሳብ አቀረቡ በቃ ይሄ አሁን የተናገርኩትን ነገር ------ በፍላጎታቸዉ

ምን ሆነ ብለዉ ነዉ መደምበሚያዉ ምን አደረኩኝ ወይስ ከ

አዉ ይሄን ነገር እንደዚህ ነዉ አሁን የሰጠሁት ቃል አለ አይደለም እንዲ ነበርኩኝ እንዲ ሳረግ ነበር የሚለዉ ቃል ሲናገር ነበረ እንዳዛ ነዉ የሰጠዉ

እሺ በቃ ጨርሻለዉ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ፖሊስ ቃሉን መቀበል ሲጀምሩ ምን ብሎ ነዉ የጀመረዉ እስቲ ተከሳሽ ነዉ የጀመረዉ ወይስ ፖሊሱ ነዉ የጀመረዉ

ቃል በሚሰጡበት ሰአት

አዉ

አይ የራሳቸዉን ቃል አለ አይደለም እነሱ ናቸዉ የጀመሩት

ማ ፖሊስ ቃልህን ስጥ ብሎ

አዉ እሱ አዉ እኛ ጋር በታዛቢነት አይደለም ቅድም ስትናገሩ የነበሩትን አለ አይደለም ቃላቹህን ስጡ አላቸዉ በቃ ቃላቸዉን

ቅድም ስትናገሩ የነበረዉን ቃላቹን ሰጡ አለ

ስጡ አላቸዉ በቃ ይሄዉ ነዉ በቃ

ከዛ በኂላ እነዚህ

ሰጡ

ይሄን ቃል መስጠት ጀመሩ

ይሄን ጀምረዋል

አሁን የተባለዉ አሁን የሚሰጡት ቃል ለወደፊቱ ፍ/ቤት በምስክርነት በናንተ ላይ ይቀርባል ቃል የመስጠት ያለመስጠር መብታቹ የተጠበቀ ነዉ ብሎ ፖሊስ ምንም አልነገረም

ምን ነገር አልሰማሁም እኔ አልሰማሁም ይሄ ነገር

ቅድም የተናገራቹትን ነገር በሉ ብቻ ነዉ

በቃ ይሄን ነገር ነዉ ቃላቹን ብቻ እንዲሰጡ አለ አይደለም ቃላቹን ስጡ ተበለ በታዛቢ ፊት ሰጡ

እናመሰግናለን ከፈለጉ መሄድ ይችላሉ

ትዕዛዝ ተሰቷል

ት ዕ ዛ ዝ

የዛሬ የችሎት ውሎ ተገልብጦ ከመዝገብ ጋር ተያይዞ እንድቀርብ ታዟል የምስራቅ ሐረርጌ ዛን ማረሚያ ቤት ሀላፊ 87ተኛ የዐ/ህግ ምስክርን ያላቀረበበትን ምክንያትና ለማቅረብ ምክንያት ያልገለጸበትን በአካል ቀርቦ በችሎት እንዲያስረዳ ታዟል ይጻፍ የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሀላፊ 11ተኛ 14ተኛና 16ተኛ የዐ/ህግ ምስክሮችን ያላቀረበበትን ምክንያት ያልገለጸበትን ያላቀረበበትን ምክንያት በአካል በችሎት ቀርቦ እንዲያስረዳ ታዟል ይጻፍ የድሬደዋ ማረሚያ ቤት 73ተኛ

990

የዐ/ህግ ምስክርን እንዲያቀርብ ታዟል የጥቁር አንበሳ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል 8ተኛ ተከሳሽ ፋጤ አሚ ሳዲቅ አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ እንዲገልጽ ታዟል ቀጠሮ አጀንዳቹን

ለህዳር 15 ወይ 16 ይመቻል

ህዳር ዉስጥ አይመቸንም

ህዳር 21

ህዳር ዉስጥ አይመቸንም

የተከበረዉ ፍ/ቤት አጀንዳ --------------

ታህሳስ 1 እስከ 22 ጊዜ እናርግ ይሄንን ብዙ መቆየታቸዉን ግምት ዉስጥ ከማስገባት ነዉ አሁን 1 ላይ ሊንይዝ የቻልነዉ

የተከበረዉ ፍ/ቤት ህዳር 27ና 28 አይመችም

በጣም ብዙ ስለሆነ ነዉ

ህዳር 29

አሁን እኮ አጨናንቀን መያዝ የ1ኛ የ2ተኛ 3ተኛ ችሎት ገና ነዉ አሁንም ይሄን ሰሞን ከዚህ ወተን ገና ባለጉዳይ ሌላ የሚጠብቀን ነገ እንደዛወ ነዉ እንደዚህ አጨናንቀን ስራዉንም አንሰራዉም እንደገናም ደግሞ ሰዉንም ማጉላላት ይሆናል አሁን ጠዋት የመጡት ዉጪ ናቸው ከዚህ ችሎት ስንወጣ ወደ ሌላ ችሎት ነዉ የሚንገባዉ አሁን እራሱ

ታህሳስ አንድ ላይ ይሁን እሺ

ታህሳስ 1 2003 2 ሰአት ተኩል

ማ/ተ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እነ አብዱራህማን /73 ሰዎች/ በተከሰሱበት መዝገብ ላይ 8ኛ ተከሣሽ የአይን ምስክር ያልተሰማ ስለሆነ ዐ/ሕግ ምስክሮቻቸውን ማቅረባችሁን አረጋግጡ

- በ8ኛ ተከሣሽ ላይ 4 ምስክሮቻችን ቀርበዋል ምስክሮቻችን እንዲሰሙልን እንጠይቃለን
- ምስክሮቹ ይጠሩ
- ተከሣሽ በግሉት ነው በተከላካይ ጠበቃ?
- /ግልጽ ያልሆነ/
- 8ኛ ከተከላካይ ጠበቃ አቶ መሳፍን አሸናፊ ጋር ቀርቧል
- ምስክሮቹ ቃለ መሐላ ይፈጽሙ
- ቃለ መሐላ አስፈጽማቸው
- በእውነት ለመመስከር በአላ ስም ምለናል ብለዋል
- በዐ/ሕግ በኩል የተሰየማችሁት
- ዐቃቢያ ዐቃቢያን ሕግ እያሱ መኮንን እና ባዚና /የማየሰማ/ ተሰይመዋል
- ጭብጥ የምታስመዘገቡት አለ?
- ጭብጥ የምናስመዘግበው ምስክሮቻችን የሚመሰክሩት 2ኛ እና 3ኛ ክስ ላይ ነው ከቀረበው ክስ ሌላ ነገር እንደክስ አቀራረባችን ነው
- በምን በምን ላይ እንደሚያስረዱ
- እንደ ክስ አቀራረባችሁ ነው
- እንደ ክስ አቀራረባችን ነው
- ማን ይግባ
- መአዲ መሐመድ አብደላ
- 65ኛ ምስክራችን ነው በክስ ዝርዝር የማስረጃ ዝርዝር ነው 65ኛ ምስክር ነው የተጠቀሰው
- 65ኛ
- ተከሣሽ ሙሉ ስሞትን እስከነአያት?
- መአዲ መሐመድ አብደላ
- እድሜ?
- 29

992

- ሥራ?
- የመንግስት ሠራተኛ
- የመኖሪያ አድራሻ?
- ምስራቅ አረርጌ ጉለዳ ወረዳ
- ቀበሌ ?
- 01
- ተከሣሽን ያውቋቸዋል?
- አዎ አውቃው
- ፀብ ዝሙድና
- ምንም
- የመጡበት ምክንያት ያውቃሉ
- አዎ አውቃለሁ
- ለምንድ ነው?
- ለምስክርነት
- የሚመሰክሩበትን ጉዳይ ያውቃሉ?
- አዎ አውቃለው
- ከተባለ በኂላ ለዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ የምስክሩ መልስ
- እስኪ የሚያውቁትን ነገር ይንገሩን እርሶን በተመለከተ?
- ወደ 96 መጨረሻ አካባቢ 4 ዓመት አካባቢ ይሆነዋል ዓመተ ምህረቱን በትክክል አላስታውስም በዚያን ጊዜ የኦነግ ፖርቲ አባል ነበረች በዚያን ተማሪዎች እዚያ በቡርቃ ከተማ ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ለረብሻ የሚያነሳሱ ሠላማዊ ሰልፍ የሚያስደርጉ አንድ ነች እንደሁ በሁለት ሰዓት አካባቢ በዚህ ሁኔታ በከተማ ውስጥ እየሄዱ የረብሻ ሠላማዊ ሰልፍ አድርገው ከተውን የበጠበጡ መሆኑን በዚያን ጊዜ እዜ ሠላም አስከባሪ ነበርኩኝ ትጥቅ ይዤ እየሄድኩኝ እያለሁ በዚያን ጊዜ የያዝኩትን መሣሪያዎችን እንቀማሃለን ብለው በድንጋይ አሯርጠውኝ በድንጋይ መቱኝ ከዚያ በሕግ ይዤያቸው ከዚያ እየሮጠኩኝ ሄጄ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሸሸሁኝ ከዚያን ደግሞ ፖሊስ ጣቢያ ስሄድ ፖሊስ ጣቢያ ስብሰባ ላይ ስለነበሩ ወደ ቀበሌው አስተዳደር ሄድኩኝ እንደገና ወደቀበሌ አስተዳደርም እየሄድኩኝ እያለሁ በድንጋይ አባረውኝ መሣሪያውን እንቀማሃለን ብለው በድንጋይ አባረሩኝ በወቅቱም በአፍህ አንተ ትሞታለህ ወያኔ ከአሁን በኂላ የጠፋን

993

አንተ በ1040 ነው የተገዛኸው እያሉ በአፍም ይናገሩኝ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው እኔ ላይ ድርጊት የፈፀሙትና በዚህ ነው እሷን የማውቃት በዚያን ጊዜ የነበረው ሰልፋም ኦነጉችን እያሞገሱ ነው የሚሄዱት ይህንን ነው ልመሰክር የመጣሁኝ

- ሠላማዊ ሰልፉ የወጡበት ሠላማዊ ሰልፍ ምክንያቱ ምድን ነው
- እነሱ የወጡት ሰልፍ የረብሻ ሰልፍ ነው መንግስትን እየሰደቡ ኦነጉችን እያሞገሱ ነው በዚያን ጊዜ
- ኦነጉችን እያሞገሱ መንግስትን እየተሳደቡ
- እሷ በዚያን ጊዜ ምን ታደርግ ነው ፋጥሽ?
- እሷ ሁለት ሰልፍ ነበር እሷ ያለችው መጀመሪያ ሰልፍ ላይ ነው ከተማ ውስጥ እየዞሩ ነው የሚሄዱት እና ወደ እኔ ተጠግተው ያሉት ጠንካራ ወንዶች ያሉበት ሰልፍ ነው ወደእኔ የተጠጉት በዚያን ጊዜ ሰልፋን የሚያከናውኑት ከነ ከማል ጋር የነበሩት ናቸው፡፡
- እና እሷ ከመጀመሪያ ሰልፍ ላይ ሆና እሷ ምን ታደርግ ነበር አንተንስ ምን የተናገረች ነገር አለ?
- በዚያን ጊዜ እሷ አየቺኝና አንተ ምንድን ነህ አለቺን እኔ ደግሞ ሰው ነኝ አታየኝም ወይ ስላት ይህንንስ መሣሪያውን ይዘህ ማንን ፍለጋ ነው የምትሄደው ስትለኝ አባውን ነው የምፈልገው እኔ አባሁ ነኝ
- አባሁ ማለት ምንማለት ነው ተርጉምል?
- ኦነግ ኦነግ ነኝ
- አባሁ ማለት በምንኛ ነው?
- በኦሮሚኛ ነው
- ከዚያ ጫማዋን ከእግሯ ላይ አውልቃ መታቺኝና በድንጋይም መታቺኝ
- ሌላስ እሷ ከእሷ በግላ ከሠላማዊ ሰልፍ ውጭ ምን የምታደርገው ነገር ነበራት?
- ተቃውሞ የቀረቡት የዐ/ሕግ ምስክሮተ በ2ኛ እና በ3ኛ ክሶች ላይ እንደክሱ ያስረዳሉ ነው የተባው አሁን ዐ/ሕግ እየጠየቁ ያሉት ግን ተከሣሿ በግል ምን እንዳደረገች የሚገልጽ ስለሆነ በግል አደረች የሚል ነገር አሁን በተጠቀሱት ክሶች ውስጥ ስላልተመለከተ ከጭብጥ ውጭ ነው ተብሎ ሊሰማ አይገባውም፡፡
- መልስ ይኖራችዋል?
- አዎ

በፌ.ዲ.ሪ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ቁጥር 4

994

- አሁን እሷ ያደረገችው ብለን ያልንበት ምክንያት ከእነሱ ተነጥላ አሁን በተከሣሽነት የቆመችው እሷ ብቻ ናት እሷን በተመለከተ እሷ የምታደርገውን እንቅስቃሴ የፈፀመችውን ነገር በዝርዝር ንገረን ነው እንጂ ያልነው ከክሱ ውጭ የሆነ ነገር ንገረን ኣላልንም የንግልም የቤተሰብ ሕይወታን አልጠይቅም
- ብይን ተሰጥቷል
- የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ ያነሱት መቃወሚያ በተከሣሿ ላይ ምስክር እየተሰማ በመኖሩ በክሱ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ተለይቶ መጠየቅና መጣራትም ያለበት በመሆኑ የዐ/ሕጉ ጥያቄ አግባብነት ያለው ስለሆነ መቃወሚያ አልተቀበልንም ምስክሩ መልስ እንዲሰጥ ታዟል
- ልቀጥል
- አዎ
- ጥያቄ
- እሷ ከዚህ ውጭ ያደረገችውን ነገር በዝርዝር ንገረን?
- እነሱ በብቻቸው የሚያከናውኑት ይደራጃሉ ብርም ይሰበስባሉ ሰቹንም ያደራጃሉ
- ከሣሿ በወቅቱ ምንድን ነው ያደረገችው?
- እሷ ለብቻ የምታከናውነው ነገር የለም ነገር ግን የሚሰሩትን የሚያከናውኑትን ሁሉ ተደራጅተው ነው በፖርቲ ነው የሚሰሩ
- ተደራጁ ያለው ይደራጁ ነበር ያልከን በምን ሥር ነው የሚደራጁት በማን ሥር ነው የሚደራጁት?
- በኦነግ ሥር
- ገንዘብ ያዋጡ ነበር ብለሃል ለማነው ገንዘብ የሚያወጡት?
- ለኦነግ ሰብስበው ይልካሉ ገንዘብ
- አዎ
- ገንዘብ የሚያዋጣው ማን ማን ነው እስቲ ገንዘብ የሚያዋጡት እነማን ናቸው ገንዘብ የሚሰበስቡትን ሰዎች ንገረኝ?
- የግል ጥያቄ ሌሎች ተከሣሾችን ከአሁን ምስክርነት ያሰሙትን ተከሣሾችን ጨምረው እየጠየቁ ነው ማን ማን ብለው ስለሆነም በቀረበችው ተከሣሽ ብቻ ምስክርነታቸውን እንዲያሰሙ
- መልስ ተሰጡበታላችሁ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ጽ/ቤት

995

- እኛ ማን ብለን እከሌ ነው ብሎ እንዲነግረን ነው ብሎ የምንፈልገው ስለዚህ የሌለው ሰው አይደለም ያለውን ተመልክተን ነገረናል ያለው ነው የሚመዘገበው
- ዐ/ሕጉ ቀጥታ ከመጠየቅ ቀጥታ ባልሆነ መልክ መጠየቅ ስለሚገባው እነማን ናቸው ብሎ መጠየቁ አግባብነት ያለው ስለሆነ ጥያቄውን ተቀብለናል
- የሚያደራጀው ማነው ገንዘቡን የሚሰበስበው ማን ማን ብለህ ነው?
- እነሱ የተደራጁት በጣም ብዙ ናቸው ከአሁን በፊት የተመሰከርንባቸው ጋር አንድ ነው ተያያዥነት ስላላቸው በግሩኘ ተደራጅተው ነው የሚሰሩት
- ያሉት ያስቀረው ነገር አለ የተወሰነ ሰው አለውና ከዚያ ውስጥ ስላሳቸው ድርሻ የተናገሩት
- እሷም ከእነሱ ውስጥ አንድ ላይ ሆነው በግሩኘ ሆነው የሚሰሩት እነዚያ ከአሁን በፊት መጥተን የመሰከርንባቸው ሰዎች ጋር ሥራ አላቸው
- ስለዚህ በትክክል እየሰማን አንድ በአንድ የእሱን ቃል መተርጉም አለብህ
- እሷም ከዚያ ውስጥ አብራ ነበር ነው?
- ከእነሱ ውስጥ እሷም አንድ ነች
- ከመቼ አስከመቼ ነው እያደራጁ የነበረው ገንዘብ ይሰበስቡ የነበረው ከመቼ እስከ መቼ ጊዜ ነው
- ጊዜውን ነው የተጠየቁት የሚያስታውሱ ከሆነ /ግልጽ ያለሆነ/ የሚያውቁ ከሆነ አለማወቃቸውን ገልጸው እንዲያልፉ ይህንን በትክክል /የማይሰማ/
- ከመቼ ጊዜ ጀምሮ እስከ መቼ ጊዜ ሰው ሲያደራጁ የነበረው ገንዘብ እየሰበሰቡ ለኦነግ ሲልኩ የነበረው መቼ ከመቼ ጊዜ ጀምሮ እስከመቼ ጊዜ ድረስ ነው ጊዜ ነው የጠየኩት
- ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ኢፋ የወጣበት 1999 ነው እስከ 2001 ድረስ ነው
- የት አገር ነው ይህን ነገር ሲሰሩ የነበረው?
- ወሎዳ ወረዳ
- የትኛው የት አገር ውስጥ የት ዞን?
- ምስራቅ አገርጌ ውስጥ ጉለዳ ወረዳ ውስጥ
- ቀበሌ ቡርቃ ውስጥ ነው
- **ተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ**
- ተከሣሽን ከዚያ እለት በፊት ታውቃታለህ ወይ?
- አዎ አውቃታለሁ

996

- ጉረቤት ነች ወይስ በምን አወቅቃት ዝምድና የለኝም ብለሃል?
- አንድ ቀጠና ወስጥ ነው ያለነው ጉረቤቴ አይደለችም
- ያኔ አንተ ትጥቅ ይዘህ በቅርብ እየተከተልክ ሰልፍ ሲያደርጉ አይቻለሁ ብለሃል በሰልፉ የደረሰ ምን ጥፋት አለ
- እኔ በዚያን ጊዜ አነሱን እየተቆጣጠርኩኝ አልነበርኩኝ ነገር ግን ለሥራ እየሄድኩኝ እያለ
- የለረሰ ጥፋት ምንድ ነው በአጭሩ ጠይቃቸው ሰልፈኛው ያደረሰው ጥፋት ምንድ ነው?
- እነሱ የፈፀሙት በዚያን ጊዜ ሰዎቹን በድንጋይ መምታ ሌሎችን ማባረር እንደገናም እቃ ለመዝረፍ ሙከራ ለማድረግ ነው ለመቀማት
- እኔ ያኔ እነሱ ጋር አልነበርኩም ብኋል ሠላም እያስከበርኩ ነበር አላልክም ወይ የማንን ሠላም ነው የምታስከብረ?
- ለሥራ ወደ ገጠር እየሄዱክኝ ነው ወደ ቆምቢ ጉሃ ቀበሌ ለሥራ እየሄዱኝ ነው እነሱን አላስቆምኳቸውም እንጂ ለሥራ ነው እየሄድኩኝ ያለሁት እኔ መሣሪያ ስለያስኩኝ ሲያዩኝ ነው ያሯሯጡኝ እንጂ
- ለምን ሥራ ነው የሚሄዱት?
- ለሠላም ሥራ ነው የምሄደው ሠላም ለማስከበር
- አንተ ምንድ ነህ ብላ በጫማ የመታችህ በዚሁ ሥራ ላይ እየሄድክ ነው ወይ
- እኔ ለዛኛው ሥራ እየሄድኩኝ እያለሁ ነው ከሰልፍ ውስጥ ጫማ አውጥታ ዬጭ ብላ የመታችኝ
- እሄድበታለው ያልከው ቦታ ምን ያህል እርቀት አለው?
- ቦታው በጣም ይርቃል
- እያሳጠርክ
- ምን ያህል ቀት ነው
- በሰዓትም መገመት ትችላለህ
- 60 ኪሎ ሚትር ይሆናል ይርቃል
- 60 ኪሎ በእግር ልትሄድ ነው ወይ የተንቀሳቀስከው የነበረው ተዲያ?
- በመኪና ልሄድ ነበር በእግሬ አይደለም
- የኦነግ አባል ነበር 1998 ብለሃል
- አዎ ወይም አይለም በአጭሩ
- አዎ

997

- የኦነግ አባል መሆኗል በምድንድ ነው መታወቂያ አይተሃል ወይ?
- እነሱ በሚሰሩት ድርጊት ነው ሰው በማደራጀታቸው ብር በመሰብሰባቸው እንዲሁም በሴል እየተደራጁ እና ሰው እንደውም አምጥተው በሽጉጥ ለማስገደል ድረስ ስለደረሱበት ነው የማውቀው
- የኦነግ አባል ማለት ሰልፍ የሚያደርገው ገንዘብ የሚያዋጣው የኦነግ አባል ብቻ የሆነ ነው ወይ?
- በዚያ ወቅት እኔ የማውቀው የኦነግ አባል ነው በወቅቱ እንደዚህ ሰላማዊ ሰልፍ የሚያደርጉ በሕጋዊ መንገድ ነው
- አንተ እንኚህን ድርጊቶች ስታይ ከአንተ ሌላ ማን ነበር?
- ብዙ ሰው ነበር
- በምስክርነት ከመጡት ሰው የለ ሰው ነበር ወይ?
- አዎ አለ
- ማን የሰውየውን ስም ተናገር?
- ሞጌ፣ ሀሰን አወል
- ስንት ሰዓት ነው ያኔ ቦታ ላይ
- ከ2፡00 ጀምሮ እስከ 4፡00 ከምናምን
- ሁለቱንም ሰዓት ሙሉ አብረሃቸው ሄዳሃል ወይ?
- አንድ ጊዜ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሸሸውኝ ከዚያም ስወጣ እንደዚያው አባረሩኝ
- ከአንተ ሌላ ከዚያ ከሰልፈኞቹ መሣሪያ የያዘ ነበር ወይ?
- አላየሁም
- ያበረሩህ መሣሪያ ያልያዙ ሰዎች ናቸው?
- አዎ መሣሪያ አልያዙም እነሱ
- መድንጋይ ነው ያባረሩህ
- አልተኮስክም?
- አዎ አልተኮስኩም
- ከአሁን በፊት በምስክርነት መጥቻለሁ ብለሃል?
- አዎ
- ያኔ 8ኛ ተከሣሽን በተመለከተ አልመሰከርክም ወይ?

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

998

- ተቃውሞ ባይነሳም መስክረሃል ወይም አልመሰከርክም የሚለው ቅድሚያ ምስክር ሲቀርብ ነበር መቃወሚያ መቅረብ ያለበትና ቀጥታ ዋና ጥያቄ በተነሣው /ግልጽ ያልሆነ/ ተከሳካይ ጠበቃው /የማይሰማ/
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- **ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ**
- አዎ
- ጥይት የተኮሰው ማነው?
- የተተካሰ ጥይት የለም ከዚያ በኋላ ግን ሰልፉን ፖሊስ በተናቸው
- ፖሊስ እንዴት ሊመጣ ቻለ?
- እኔ እየሩጥኩኝ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ስለገባሁን በዚያ ምክንያት ነው ፖሊስ ሊመጣ የቻለው
- ጨረስን
- ፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክሩን እናመሰግናለን
- ሥራጅ መሐመድ አሊ
- 53ኛ ይህንን ስም አይለም የሚናገረው በደንብ እያረጋገጣችሁ ምስክሮቻችሁን ስንተኛ ምስክር እንደሆኑ ይህንን ማረጋገጥ አለባችሁ 53ኛ አብዲላይ አመዴ ሙሜ ነው የሚለው
- ስንት ጊዜ ነው ያቀረባችሁን
- ትክክለኛ ስሞትን
- ስራጅ መሐመድ አሊ
- እድሜ?
- 26
- ሥራ?
- /የማይሰማ/ አስተዳደር ምክትል
- አድራሻ?
- ጉሎዳ ወረዳ
- ቀበሌ?
- ቡራቃ 01

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

- ተከሣሿን ያውቃሉ?
- አዎ
- ፀብ ዝሙድና?
- የለንም
- የመጡበት ምክንያት ያውቀሉ?
- አዎ አውቃለሁ
- ለምንድ ነው የመጡት?
- ለምስክርነት
- የሚመሰክሩበትን ጉዳይ ያውቃሉ?
- አዎ አውቃለሁ
- **ዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ ለምስክሩ ይቅረብ**
- ይንገሩን የሚመሰክሩትን የሚያውቁትን ነገር ይንገሩን /የማይሰማ/ በተመለከ
- እሷ ላይ ነው የማውቀው የኦነግ አባል መሆኗል አውቃወሁ እንደገና ደግሞ ከሯሷ ጀምራ ብር መዋጮ አውጥታ ለኦነግ ሠራዊቶች መላኩን አውቃለሁ ይህንንም ላውቅበት የቻልኩት ምክንያት በ1998 ዓ.ም. ውስጥ በተካሄደው ስብሰባ በከተማ ውስጥ የተደረገው ስብሰባ ላይ የኦነግ አባል ሆኜ እየሰራሁ ነበርኩኝ በማለት አድርጋ ስትናገር እንዲሁም ብርም ከራሴ ጀምሮ አስር ብር አዋጥቼ የኦነግ ሰራዊቶች እንዲበረታቱ በማድረግ ይህንን ስትናቀር ጥፋቴ ነው ብላ ስትናገር በጆሮዬም ሰምቻለሁ በአይኔም አይቻለሁ
- ጥያቄ ካላችሁ ቀጥሉ
- የት አገር ነው አገሩ?
- የመጨረሻውን ሃሳብ ድገመው እስኪ
- የእራሷን ጥፋት በሕብረተሰቡ ፊት ለፊት መናገሯል ወይም ማስቀመጧን የኦነግ አባል ሆና መስራቷል ከራሷ ጀምር አስር ብር አዋታ የኦነግ ሠራዊቶች እንዲበረታቱ በማውጣቴ ጥፋተኛቴ ነው ብላ ስትናገር በጆሮዬም ሰምቻለሁ በአይኔም አይቻለሁ
- የት ቦታ ነው?
- ጉሎዳ ወረዳ ቡርቃ 01 ቀበሌ ውስጥ
- ዞንስ የት ነው?
- ምስራቅ ሐረርጌ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1000

- ከመቼ እስከ መቼ ነው አዋጥቻለሁ ብላ የተናገረችሁ
- ከዚያ እስካሁን ድረስ 4 ዓመት ይሆናል
- **ለተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ**
- አስር ብር ካወጣችው ሌላ ሌላ ያየኸው አለ ወይ?
- ጥፋቷን ስትናገር ነው
- እኮ ከዚያ ሌላ ስታወጣ የዚያን እለት አስር ብር አውጥታ ስትሰጥ ሰጥቻለሁ ስትናገር ሰምቻለሁኝ ብለዋል?
- አዎ
- ከዚያ ሌላ ብር ስለማዋጣቷ ታውቃለህ ወይ ከዚያ ከ10 ብር ሌላ?
- አላውቅም
- ስብሰባ ላይ ነው የተናገረችው ስብሰባው የኦነግ ስብሰባ ነው የመንግት አስተዳደር አካላት የጠሩት ስብሰባ ነው ወይስ የማነ ስብሰባ ነው
- የሠላም አካላት የመንግስት ስብሰባ ነበር እኛ ነን እዚያ የሰበሰብናቸው
- ያኒ ታዲያ ስህተቴ ነው ከዚህ በኋላ አልሆን ነው ወይስ እስካሁን የሰራሁትን ይቅርታ ይደረግልኝ ነው ወይስ ከዚያ በኋላም እቀጥልበታለሁ ነው ያኔ ተፀጽታ የተናገረችው ምንድን ነው?
- መቃወሚያው ምንድ ነው
- እኛ እያስመሰከርን ያለነው የዚያን ጊዜ ይቅርታ ተደርጉላታል አልተደረገላትም ስለሚለው አይደለም አሁን በፍ/ቤቱ በተያዘው ጉዳይ ላይ ነው እየተነጋገር ያለነው ስለዚህ ስለይቅርታው ስለምኑ ሕገ መንግስቱ በሚያዘው ሌሎችም ሕጐች በሚያዙት መሠረት ሂዶ ከተከላይ ጠበቃው መከራከር ይችላሉ እንጂ አሁን እዚህ ላይ ማንሳቱ አላስፈላጊ ነው በዋናው /የማይሰማ/ የተነሣው
- **ተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መልስ አሎት**
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ተነስቷል ለሕብረተሰቡ ተሳስቻለሁ ብላ ተፀጽታ ተናገረች ነው ያሉ ምስክሩ ስለዚህ በዚያ ጥያቄ ላይ መፀፀቷን ነው የሚያሳያው ያ ነገር ወይስ በኦነግ አባልቷ መግፋቷን ነው የሚያሳያው መንፈሱን ግልጽ ስላላደረጉ ነው፡፡
- **ብይን ተሰጥቷል**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቆጥር

1001

- በዋና ጥያቄ ጊዜ ምስክሩ በዚህ በቀጥታ ባይጠየቁም ይቅርታ ጠይቃለች ሲሉ በምስክርነት ቃላቸው ሰጥተው ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ጥያቄ ቢጠየቅ ተገቢነት ስላለው መልስ ሊሰጡ ይገባል፡፡
- አዎ በዚያን ጊዜ ብዙ ሰውም ነበር ብዙ ሕብረሰተቦች ነበሩ ተፀጽታ ነው ያን ጊዜ የተናገረችው እና ኢስና ግሌስ ማድረጓ ነው
- ግሌስ የተናገረችው ነገር መልእክቱ ምንድን ነው
- ተፀጽታው ነው ወይስ አይደለም ለተባለው ምስክሩ በቀጥታ የመለሱ ስለሆነ ሌላ ጥያቄ ካሎት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሻለሁ
- **ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ**
- ድጋሚ ጥያቄ የለኝም
- ለፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክሩን እናመሰግናለን
- ቀሪ ምስክሮች ከዚህ የተለየ ስለማያስረዱ ምስክሮች /የማይሰማ/ ይበቃናል በዚሁ ብይን እንዲሰጠን እንጠይቃለን በተጨማሪ ተከሣሽን በተመለከተ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት የእምነት ቃል ስለተያዘ ከዚያ ጋር አብሮ ተዳምሮ እንዲታይልን እንጠይቃለን ምስክር ማሰማታችን በዚሁ ሳለ በዚሁ አጠናቀናል፡፡
- ሌሎች የምስክርነት ቃላቸው ያልሰጡት ወደ ችሎት እንዲገቡ ይጠሩ
- በ8ኛ ተከሣሽ ላይ ከቀረቡት 4 ምስክሮች ውስጥ 68ኛ እና 53ኛ ምስክርች ቃላቸውን ሰጥተዋል ስንተኛና ስንተኛ ናቸው እንዲመለሱ የተባሉት 51ኛ እና 53ኛ የተሰሙት ምስክሮች 53ኛ 65ኛ ናቸው አሁን ይበቁናል ይመለሱ ያልናቸው 51ኛ 63ኛ ምስክሮች ናቸው
- በ8ኛ ተከሣሽ ላይ የዐ/ሕግ ምስክሮች ቃል ያበቃ ሲሆን የመከላከል መብት በሚመለከት ከተቀሩት ተከሣሾች ጋር አብሮ የሚታይ በመሆኑ መደበኛ ቀጠሮ ሌሎች 73ቱም ምስክሮች ተሰምተው ከበቃ በኋላ አብሮ የሚታይ ይሆናል፡፡ ዛሬ የእለቱ ውሎ ከመቅረፀ ድምጽ ወደ ጽሁፍ ተለውጦ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ቀጠሮ አልተለወጠም፡፡
- **ለጥር 24 የተቀጠረው አልተለወጠም**

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1002

በወ/መ/ቁ - 04486

ቀን - 9/7/2003

ዳኞች - አቶ እረዳይ በላይ

- እልፍነሽ ወእሎሬ
- ብስራት ተሽልቁ

ከሣሽ - እነ አቶ ማሙሽት አበበ እና አቶ እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሣሾች - እነ አብዱራህማን ባሌ ጃጉ 73 ሰዎች የማረሚያ ቤት ጉዳይ አስፈፃሚ ሰርጀንት ዘውዱ 69 ተከሣሾች መቅረባቸውን አረጋግጠዋል

- 22ኛ እና 48ኛ ተከሣሾችም መቅረባቸውን አረጋግጠናል የተከሣሾቹ ተከላካይ ጠበቃ በቅድሚያ አቶ ኢብራሂም መሀመድ የ23ኛ 37ኛ 38ኛ እንዲሁም የ2ኛ የ3ኛ የ7ኛ የ10ኛ የ43ኛ የ47ኛ የ57ኛ የ59ኛ የ61ኛ 65ኛ 69ኛ እና 72ኛ ተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ ቀርቤያለሁ
- እስካሁን ከተጠሩት ተከሣሽ በስተቀር የሁሉም ተከሣሽ በሙሉ ተከላካይ ጠበቃ አለምሰገድ ካህሣይ ቀርቤያለሁ
- እሺ ዛሬ መዝገቡ የተቀጠረው የቪዲዮ ካሴቱን ለማየት ነበረ በእዚህ መሰረት ዐ/ሕጐች አቅርባችሁ ከሆነ እንዲታይ የተጠየቀው በ67ኛ ተከሣሽ ላይ ተቀርጿል የተባለውን ቪዲዮ ካሴት በወረዳው እንደሌለ የተገለፀ መሆኑን በመጥቀስ በፍትህ ሚኒስቴር የድሬዳዋ ፍትህ ፅ/ቤት በዛሬው እለት በተፃፈ ደብዳቤ ያመጣ ሲሆን አባሪ አንድ የሚለው ግን ለእኛ አልመጣም አባሪ አንድ የሚል አለው አባነ አንድ የተባለው እንዲሁ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

1003

ከምስራቅ ሐረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ የምርመራ እና ፍትህ መስጠት የስራ ሂደት ቡድን በ6/7/2003 ዓ.ም. የፃፈው እና ምንም ዓይነት በቪዲዮ ማስረጃ የሌለ መሆኑን እንገልፃለን የሚል የፃፈበት ነው አባሪ አድርጎ የተላከው 14ኛ ተከሣሽ ማለትም 14ኛ ምስክር አልተሰማም እኔ በማጣራት ያገኘሁት 14ኛ ተከሣሽም እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ሲታዘዝ የቆየ ቢሆንም 48ኛ ተሰምቷል 48ኛ ምስክር ኪሚያ ማነች ኪሚያ ሐሚድ መጣን የለችም መጣን ዘይነባ መታለች እሷ ነች ልጅ የያዘች ከ11ኛ እና 27ኛ የመጣው ባለፈው ቀጠሮ ተሰጥቷቸዋል እንዴ አስተያየት ከፍርድ በፊት በመቅረፀ ድምፅ ነው የሰጣችሁት እሺ ዛሬ 14ኛ የዐ/ሕግ ምስክር አለመሰማቱን አረጋግጠናል ከዚህ በኋላ ከመቅረፀ ድምፁ በወረቀት የተገለበጠውና ዛሬ ያላገኘነው በመዝገባችን በ1ኛ እና 27ኛ ተከሣሾች ከፍርድ በፊት ሊያግድ የሚችል ነገር አለ ብለው ያቀረቡትን አቤቱታና ማስረጃ እንዲህ ዐ/ሕግ ከሰጠው አስተያየት ጋር ከመዝገቡ አካል እንዲሆን አድርገናል ስለዚህ ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

➢ ት ዕ ዛ ዝ

እሺ. 37ኛ ክስ በ64ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 64ኛ ተከሳሽ መሀመድ ኑር አህመድ መሀመድ ኑር ቀርበሃል ክሱ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲጋራ ባትሪ ድንጋይና የመሳሰሉትን እቃዎች ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠት በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ የሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ በማሰብ ወሩ እና ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለመርዳት ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲጋራ ባትሪ ድንጋይ የመሳሰሉ እቃዎችን ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠት በፈጸመው የተንኮል ድርጊት ተከሷል ግልጽ ነው፡፡ 38ኛ ክስ በ67ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 67ኛ ተከሳሽ

እሺ 38ኛ ክስ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር የሆነው መሀመድ ሀጂ ዳዲ ወይም አሪያ ዳዲን ከምስራቅ ሐረርጌ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ መንገድ እያሳየ በመውሰዱ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በመተባበር በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ እሺ ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም ውስጥ መሀመድ ሀጂ ዳዲ ወይ አሪያ ዳዲ የቡድኑ ከፍተኛ አመራርን ከምስራቅ ሐረርጌ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ መንገድ እያሳየ ወስደሃል በመሆኑ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በመተባበር በፈጸምከው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ወንጀል ተከሰሃል የሚል ነው ግልጽ ነው ገብቶሃል ወይ እሺ 39ኛ ክስም በ67ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው አንተኑ ነው የሚመለከተው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1063

ይህም በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅበት ጥር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ልዩ ቦታው አህመድ ኢብራሂም የተባለ ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል ሁለት የጦር መሳሪያዎችን ከ34 ጥይቶች ጋር አዘጋጅቶ በማስቀመጡ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ጥር 23/2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ልዩ ቦታው አህመድ ኢብራሂም የተባለ ቦታ ላይ ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል ሁለት የጦር መሳሪያዎች ከ34 ጥይቶች ጋር አዘጋጅቶ አስቀምጠሃል በፈጠርከው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰሃል ግልጽ ነው ወይ እሺ ቁጭ በል 40ኛ ክስ በ12ኛ፣ 16ኛ፣ 18ኛ፣ እና 19ኛ ተከሳሾችን የሚመለከት ነው 12ኛ ተከሳሽ አብዱረህማን ሁሴን ጅብሪል ዘይነባ መታን ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል ሸሪፍ ኡመር ኤለን ይሄ ክስ እናንተን ይመለከታል በጥሞና ተከታተሉ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው በተለያዩ ቀኖችና ወሮች በ2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነገያ ቀበሌ ውስጥ በሚገኝ መኖሪያ ቤቶች ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እና ጥይቶችን አዘጋጅቶ በማስቀመጣቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የተለያዩ ጥያቶችን ለፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለሆነው ኦነግ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እና ጥይቶችን አዘጋጅታችሁ አስቀምጣችኋል ነው ግልጽ ነው ወይ ከገባችሁ መቀመጥ ትችላላችሁ 41ኛ ክስ በ71ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 71ኛ ተከሳሽ ኑሬ ኡስማን ይህ ክስ አንተን ይመለከታል ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅ ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ህሚ ጉዳና ወረዳ ድሬ ገዳዳ በተባለው ቦታ ራሱን ኦነግ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በማቀድ የኦነግ ወዛደሮች ድሮ 10 ነበሩ በማለት ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳሳ በመቀስቀሱ በፈጸመው መገፋፋት እና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ፋይናንስ ... ዳይሬክቶሬት

1064

ተከሷል የሚል ነው በአጭሩ የኦነግ ወታደሮች ድሮ 10 ነበሩ ብለህ ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳሱ አድርገሃል ነው ግልጽ ነው ገብቶሃል እሺ ቁጭ በል 42ኛ ክስ 72ኛ ተከሳሽን የሚመለከት ነው 72ኛ ተከሳሽ ጫላ ሙክታር ሙሜ እሺ አንተ የተከሰስክበት የህግ አንቀጽ የወንጀል ህግ ቁጥር 27/1 እና 238ለን በላልፈሃል በሚል ነው ይህም ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት ህዳር ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ በማቀድ ኤፍ ዋን ቦንብ ለማፈንዳት በከተማው መስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ወርውሮ ሳይፈነዳ ቢከሽፍም በፈጸመው በህገ መንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አንተ አማርኛ አይገባህም የተነበበው ገብቶሃል እሺ መቀመጥ ትችላለህ፡፡ 43ኛ ክስ በ73ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 73ኛ እና የመጨረሻው ተከሳሽ አብዶሽ ሙሜ ጁሞ ወይም ሸፎ ይህ ክስ አንተን ይመለከታል በጥሞና ተከታተል ወንጀሉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 37/1 እና 238ለን ተላልፈህ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበህ ከላይ በ42ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ 72ኛ ተከሳሽ የወረወረው ኤፍ ዋን ቦንብ ገዝቶ በመስጠቱ እና ወንጀሉ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በማመቻቸቱ በፈጸመው ተባባሪነት መሆን በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አማርኛ ይገባሃል የተነበበው ገብቶሃል ግልጽ ነው፡፡

ተከሳሾቹ እና እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ ጊዜ ይቀርባሉ እሱ እንትን ማድረጉ አያስፈልግም ስለዚህ ክሱ ተነቧል ክሱ ከተነበበ በኋላ የምታመለክቱት ነገር ካለ አመልክቱ እና ፍ/ቤቱ አስፈላጊ የሆኑትን ትዕዛዞች ይሰጣል፡፡ በአጠቃላይ ለማቅረብ ማለት ነው እንግዲህ አስቀርጹ ይቀረጽ አሁን የተባለው

ተከሳሾቹ አንደኛ በርካታ ናቸው በአንድ ጊዜ ለከሌ ዋስ መብት ይጠበቅ ለከሌ አይጠበቅ ለማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን አንዳንድ አንቀጾች ሲታዩ የዋስ መብት የሚያስጠብቁ ሆነው አይተናቸዋል ስለዚህ እነዚህን ለይቶ ተደጋጋሚ ክስ የሌለባቸው ከሆነ ወይም ደግሞ ተደጋጋሚ --- ያው የዋስ መብት የሚያስጠብቁ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ እነሱን ለይቶ እምነት ክህደቱን ለመስጠት እንዲቻ አንድ ረዘም ያለ ቀጠሮ ይሰጠንና ከተከሳሾቹ ጋር ተነጋግረን

መቃወሚያ በተመለከተ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ቁጥር

1065

አዎ መቃወሚያውንም በሚመለከት በዛው ጋር አጠቃለን እናቀርባለን

አብራችሁ ታነሳላችሁ

አዎ አብረን አንድ ጋር በጽሁፍ አጠቃለን

ስለዚህ ቀጠሮ ይሰጠን ነው

አዎ

ሌላ ተከሳሾቹን በተመለከተ ግን አስተርጓሚው የት አለ አስተርጓሚ እዛ ጎናቸው ሁንና አስተርጉም ንገራቸው እናንተ የተከሰሳችሁት አሁን የክስ ማመልከቻው ሁሉም ደርሷችኋል የተጠየቃችሁበት ነገር በዝርዝር እዛ ላይ ሰፍሯል እያንዳንዳችሁ የተጠየቃችሁበት በዝርዝር ወረቀቱ ላይ ሰፍሯል የደረሳችሁን ወረቀት ሳይሆን ደግሞ የክስ ማመልከቻ ነው እዚህ ፍ/ቤት ተከሳሾች ናችሁ ማለት ነው ጠበቃ ፍ/ቤቱ አቁሞላችኋል ስለዚህ አሁን ወደፊት የሚቀጥለው ክርክር በሚቀጥልበት መልክ ከጠበቃችሁ ጋር እየተማከራችሁ የሚቀጥል ሙግት ነው የሚሆነው በግልም ሆነ በሌላ የምትጠይቁት ጥያቄ በጠበቃችሁ እየታገዘ ነው የሞያ ስራ ነው የሚሰራው ጠበቃ ማቆም የሚችል አለ እንዴ ፈልግ በግሉ ቁሙ በግላችን ደግሞ ማቆም እንችላለን የምትሉ በግላችን ጠበቃ እናቆማለን በገንዘብ ገዝተን የምትሉ ብቻ ተከላካይ ጠበቃ ይይዛሉ ስም ዝርዝራቸውን እነዚህን ሌላ በቃ ሌሎቻችሁ አትይዙም ሌሎቻችሁ አትችሉም አደለ

አንችልም

እሺ ሌሎቻችሁ ከቆማችሁት ውጪ አዳምጡ ከቆማችሁት ውጪ አሁን የሚባለውን እንትን ትላላችሁ ለፍ/ቤቱ እኛ ከቆማችሁት ውጪ ሌሎች የተቀመጣችሁት አሁን የሚባለውን ደግማችሁ በሉ መሀላ ነው እኛ ጠበቃ ለማቆም ሀብትና ገንዘብ የሌለን መሆኑን ለፍ/ቤቱ እናረጋግጣለን የቆሙት ማን ነው አንተ ስምህ ማን ነው 3ኛ ተከሳሽ ዐ/ህግ እስቲ እያያችሁ

45ኛ

እስቲ አንብቡት 5ኛ ማን ነው

የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ... ልደታ ምድብ

1066

45ኛ ------------- አህመድ

ጨሎ አህመድ ሌላ ማን ነው አንተ ከኋላ ያለከው

ኑሬ ኡስማን ጭሮ

ኑሬ ኡስማን ጭሮ ስንተኛ ነው

71ኛ

እስኪ አንብቡት

ኑሬ ኡስማን ጅሎ አዎ እሱ ነው

አንተ ነህ

አዎ እኔ ነኝ

እሺ አንተም ጠበቃ ማቆም ትፈልጋለህ በራስህ እሺ ሌላ ሶስተኛው ማን ነው ማን ነው ስምህ

37ኛ ተከሳሽ

አንተ ስምህ ማን ነው

አብዲ --------- ኡስማኤል

37ኛ ነው ዐ/ህግ

አዎ አረጋግጠናል

አንተ ጠበቃ ታቆማለህ በራስህ ትገዛለህ በገንዘብ እሺ 37ኛ ተከሳሽ እገዛለሁ ብሏል ኑሬ ኡስማን ጭሮ እየተባለ ያለው ገብቶሃል ወይ

አዎ ጠበቃ መግዛት የምትፈልገት ነው የተባለው

በገንዘብህ ትገዛለህ ጠበቃ

አዎ እገዛለሁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1067

ጠበቃ ገንዘብ ይፈልጋል

ስለተቸገርኩኝ የደም ብዛት በሽታ ስላለብኝ እሱን ጠበቃን ማቆም ፈለኩኝ

ፍ/ቤቱ ገንዘብ አቅም ከሌለህ ፍ/ቤቱ ያቆማል አይ ገንዘብ አለኝ እገዛለሁ ካልክ ጠበቃ መግዛት ትችላለህ ይሄን ለይ ጊዜ አትግደል አንተ አልተጠየክም ዩሱፍ ጨሎ አንተ ቁጭ በል አንተ እገዛለሁ ብለሃል አንተ ቁጭ በል

ብዙ ገንዘብ የለኝም

ገንዘብ የለህም

ብዙ ገንዘብ የለኝም

ስለዚህ ጠበቃ ፍ/ቤቱ ያቁምልህ ወይ በነፃ ኑሪ

ፍ/ቤቱ እንዳለው

ገንዘብ አለህ እንዴ አንተ ምንድን ነው የምታወራው

በስንት ነው የሚገዛው

ቆይ አዳምጥ በለው ባክህ አንተ አዳምጥ እዚህ ስራ ነው እየተሰራ ያለው የማይገባህ ከሆነ ሌላ ጉዳይ ነው አዳምጥ አንተ በገንዘብህ ከውጪ አሁን ፍ/ቤቱ የሚለውን ትላለህ እኔ 71ኛ ተከሳሽ ኑሪ ኡስማን ጀሎ በግሌ ጠበቃ ለማቆም ገንዘብና ሀብት የሌለኝ መሆኑን ለፍ/ቤቱ በመሀላ አረጋግጣለሁ ተቀመጥ አሁን ተከላካይ ጠበቃ ለ7ኛም ኖት አብዲ በሽር አንተ እገዛለሁ ብለሃል ሌላስ ጠበቃ በራሱ ሊያቆም እሺ ማን ነው ስምህ ሚካኤል አብዱላሂ ስንተኛ ተከሳሽ ነው 0/ህግ

39ኛ

እስኪ አንብቡት

ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ

39ኛ ትገዛለህ በራስህ እሱን ተወው ባክህ ሀተታውን ተወው ገንዘብ አለህ ትገዛለህ ጠበቃ ከውጭ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1070

ከዚህም ካገኘሁ ይበቃኛል

ባክህን አዳምጥ ሚካኤል አዳምጥ የሚባለው ግልጽ አኮ ነው ሌላ ነገር አታምጣ ይሄ ቀላል አማርኛ ነው 45ኛ እንደዚሁም 37ኛ ተከሳሾች በግላችን ጠበቃ እናቆማለን ስላሉ የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ እነዚህን ተከሳሾች በተመለከተ የሙያ ግልጋሎት አይሰጡም ቀሪ ሌሎቹ ተከሳሾች ግን የቀረቡትን በተመለከተ የሞያ እገዛ ያደርጋሉ ማለት ነው ተከላካይ ጠበቃ በግልጽ መዝግቧቸው 45ኛ፣ 37ኛ እና 39ኛን በተመለከተ አይመለከቶትም ሌሎቹን ግን እኚህ ጠበቃ እናንተን ባጎችሁበት ያማክራሉ ለፍ/ቤቱ የሚቀርበውን ክርክር ያቀርባሉ እሺ ይቀመጡ ተከላካይ ጠበቃ ዐ/ህግ ይሄን ጉዳይ በተመለከተ ከዐ/ህግ አቀራረብ ከተመለከተ በአንድ ዐ/ህግ ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ በሆነ በቲም በጉሩፕ መሰራት አለበት

አዎ ለዛ ብለን ነው

ስለዚህ ከዚህም በላይ መሆን አለበት ብሎ ፍ/ቤቱ ስለሚያምን በዚህ መልክ እንድታስተካክሉ ነው

እሺ እናስተካክላለን

22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ ምንድን ነው የምታመለክቱት ነው አልያዛችሁም 22 እና 48

ቅድም ባመለከትነው የወሊድ ጊዜአቸውን

ማን ማን ናቸው 22ኛ ነው 48ኛ በፖሊስ ተለቀቁ ስትሉ አልነበር እንዴ

አዎ

ታዲያ ምንድን ነው

ጀና መሀመድ

22ኛ ጀና መሀመድ እና 48ኛ/

ዘሀራ አብዶሽ እነዚህ ናቸው

ምንድን ነው የምታመለክቱት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1071

እነሱ ያው አራስ ጊዜአቸውን እንደጨረሱ

እየተቀረፀ ነው

ነፍሰ ጡር በመሆናቸውና በመውለዳቸው ምክንያት በፖሊስ በዋስ ተለቀዋል ያንን እንደጨረሱ ወዲያውኑ እናቀርባቸዋለን

በወሊድ ምክንያት ነው

አዎ

በቀጣዩ ቀጠሮ ታቀርቧቸዋላችሁ

እናቀርባለን

የተመለከተ ወይስ ያመለክታል

የምናመለክተው ይሄንኑ ነው የማረሚያ ቤት

ይበቃል በቃ ይቀመጡ ዐ/ህግ እነዚህን በሙሉ ተከሳሾች በሃላፊነት ይዘህ የመጣከው አንተ ነህ የቀረቡትን በሙሉ ዛሬ የቀረቡትን ችሎት

አዎ አጠቃላይ የቀረቡትን እኔ ይገኙ ቀረብኩኝ ያው የጉዳዩ ባለቤት ማለት መርማሪም ስለነበርኩ አጠቃላይ በጊዜ ቀጠሮ ስለነበሩ በመደበኛ ዛሬ እንዲቀርቡ ይገኙ የቀረብኩ እኔ ነኝ

71ንም ይዘህ የቀረብክ አንተ ነህ

ትክክል

እሺ ስምህ ማን ነው

ዋና ኢንስፔክተር ብርሃኑ ታጀበ

ከየት ነው ይዘሃቸው የቀረብከው

ከድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን

አጅበህ ነው ይዘህ የመጣከው

1072

አዎ አጅቤ ነው

------------ ምንድን ነው የምታመለክቱት

ያው ተከሳሾቹ በቂ ምግብና ህክምና በሌለበት በጣቢያ የሚገኝ ስለሆነ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩልን

መከላከያ ጠበቃ መቼ ነው ትቆያላችሁ አደለ እዚህ

አዎ

--------- አይታችሁ ---------

እናደርጋለን

አሁን ስለታዘዘ ይሄንኑ አድርጉ ሌሎች መብቶችም ስለሚኖሩ በሚሰጡት አጀንዳዎች መጠቀም አለባችሁ

እሺ

የሚሰራ ነገር ካለ በዚህ ቀጠሮ መጠቀም አለባችሁ ፍ/ቤቱ ከእንግዲህ የራሱን ስራ ብቻ ነው የሚሰራው ይሄን ታሳቢ ሁሌ ማድረግ አለባችሁ

እሺ

በራካታ ተከሳሾች ናችሁ ስለ አቀራረባችሁ ክርክር ሂደቱን አመራሩን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ሲመረምር የሚሰጣቸው ነው የሚሆነው የሚመለከታቸው ነገሮች ስለዚህ እናንተ ግራ ቀኛችሁን ይሄንን እያሰባችሁ መግቢያ መውጫ አለበት በዚሁ የረጅም ቀጠሮ እያሰባችሁ ቆዩ የማስረጃ ሌላው የመሳሰለ ማለት ነው

እሺ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል

1073

ት ዕ ዛ ዝ

ተከላካይ ጠበቃው ባመለከቱት መሰረት በክሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በቀጣዩ ቀጠሮ እንዲያቀርቡ ታዟል ተከሳሾች ከጠበቆቻቸው ጋር በመተባበር እና በመመካከር የእምነት ክህደት ቃላቸውን ለመስጠት ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ አዘናል ዐ/ህግ ባመለከተው መሰረት ቀሪ ተከሳሾቹን እንዲያቀርብ ብለናል ተከሳሾች እስከዚያው በድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ቆይተው ይቅረቡ ብለን ለግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ/ም አጀንዳ ይዘናል።

ነገራቸው ማን ነው ስምህ

ኮንስታብል ፋኡድ አሊዬ

በዛሬው እለት በማስተርጎም ለረዱት ኮንስታብል ፋኡድ አሊዬ ከፍ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል 50 ብር እንዲከፈለው አዘናል በሂሳብ ክፍል በኩል 50 ብር ጠይቀህ ትወስዳለህ እናመሰግናለን።

ማ/ተ

የመ/ቁጥር 04486

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

1. አብዱረህማን ባሴ ጅጐ
2. ሽሪፍ አሊ መሀመድ
3. አህመድ ኑር ኡርጌ ሁሴን
4. አህመዲን ኢብራሂም ሀሰን
5. ከማል አልይ አህመድ
6. መሀመድ ኢብራሂም አደም
7. ሲራጅ አህመድ ሙሣ
8. ፋጤ አሜ ሣዲቆ
9. ጀማል ሀምዛ ቂልጦ
10. ጣሀ አህመድ አብዱሮ
11. ዙቤር ሁሴን መሀመድ
12. አብዱረህማን ሁሴን ጅብሪል
13. ረብላ ሽረፍ ኡመር
14. ኢብራሂም ሁሴን ጉራቻ
15. ኪሚያ አሚን ዩሱፍ
16. ዘይነባ ሙክታር አህመድ
17. አብዲ ሺኩር ኡመር ኤሌሞ
18. ኢብራም መሀመድ ጅብሪል
19. ሽሪፍ ኡመር ኤሌሞ
20. አብዲ ኡስማን አደም
21. መሀመድ አሊይ ሰግዱ
22. ጃና መሀመድ አዳ[illegible]
23. አብዱል ሀሚድ መሀመድ አሊ
24. ሼክ መሀመድ ኡስማንጊኖ
25. ሻም ኢብራሂም አብዱላ

ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

26. አብዲ አህመድ ኑር
27. ኢብራሂም አህመድ አብዶ
28. አብዲ አሊ አህመድ
29. ጀማል ከድር ሣኒ
30. ረህማ መሀመድ አብዱረህማን
31. ሰሚራ ሙሜ አብዱላሂ
32. ጫልቱ ኢብራሂም አብዱልቃድር
33. አብዲ ሀጂ ሙሣ መሀመድ
34. ጀማል ከድር አህመድ
35. አዱኛ መሀመድ ጀብሮ
36. ዱርሲቱ አብደላ አህመድ
37. አብዲ በሽር ኡስማኤል
38. ኮከብ መሐመድ የሱፍ
39. ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ
40. አህመድ ሼክ ዩሱፍ
41. ሳሊዩ አብደላ ሙመድ
42. መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም
43. አህመድ ኡስማኤል መተኮ
44. ሀጂ ጠሀ ሀሰን ቡሌ
45. ዩሱፍ ጨሎ
46. ሙክታር አበዱል ጀሊል
47. አልይ አብዱሌ ኡስማን
48. ዘሀራ አብዶሽ ኢብራሂም
49. መሀመድ ኡመሬ ሙመድ
50. ጀፈር ኡመር አብዱሌ
51. የሱፍ ዳውድ ዩሱፍ
52. ጀማል አደም ኡስማን
53. በከር ቃሲም ካዩ
54. አህመድ ነጀሽ ሼክ አብዱልሀሚድ

1076

55. ጀማል ሁሴን ሙሣ

56. ከድር አደም ጠደቻ

57. ሼክ ከዲር ቱራ ሊዬ

58. ኡመር መሀመድ መሀሙድ

59. አብዱላሂ ሙሣ

60. ሸኪር ቱኬ ሀሰን

61. መሀመድ አሊ ሁሴን

62. መሀድ አንጀባ

63. አድናን ጉሼ አህመድ

64. አህመድ ኑር አህመድ ቡሌ

65. ሠይድ አደም አሊ

66. ከሊፍ መሀመድ ሼክ

67. አብራሂም አብደላ ዋሪዬ

68. አብደላ መሀመድ ሰይድ /ሀማ/

69. ሀሰን መሀመድ አህመድ

70. መሀመድ አብዶ አህመድ

71. ኑሬ ኡስማን ጂሎ /ቢ.ቴ ጄሎ/

72. ጫላ ሙክታር ሙሜ

73. አብዶሽ ሙሜ ድምኦ /ሻቦ/

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 6

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 11/9/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ በዚህ መዝገብ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌዴራል ዐ/ህግ አቶ ፌይሰል አብዲ፣ ረድኤት ይልማ እና እንተነህ ጌታቸው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ 73 ተከሳሾች ቀርበዋል

ማረሚያ ቤት እናንተ ጋር ያሉት 7 ተከሳሾች ቀርበዋል በዋስ ያሉት 3 ተከሳሾች ቀርበዋል 21ኛ ተከሳሽ ሰሚራ መሀመድ አሊ፣ አለህ የት አለ ሰሚራ ሙሜ፣ መጥተሻል ጀና መሀመድ፣ የት አለች

አልቀረበችም መሰለኝ

ጀና መሀመድ፣ ዘሀራ አብዶሽ፣

አለች ይቸውና

እሺ. በዋስ ያሉት ተከሳሾች 22ኛ፣ 48ኛ፣ ተከሳሾች አሉ 31ኛ ተከሳሽ ግን የለችም 31ኛ ተከሳሽ በዋስ እንድትቆይ የተደረገ ቢሆንም ዛሬ አልቀረበችም ሌሎቹ በማረሚያ ቤት ያሉት 71 ተከሳሾች መቅረባቸው ተረጋግጧል እሺ. በጠበቃ በኩል እራሳችሁን አስመዝግቡ

የ23ኛ፣ 37ኛ፣ እና 38ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ

እሺ.

በጠበቃ ከተወከሉት ውጪ ያሉት ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አድማሱ መለሰ ቀርቤአለሁ

እሺ. ጠበቆችም ራሳቸውን አስመዝግበዋል አንድ ጠበቃ ቀርቧል አደለ

አዎ

አቶ ፀጋዬ

አቶ ፀጋዬ

እሺ. ዐ/ህግ በዛሬ እለት አመጣችሁ የታዘዘውን

አዎ የተከበረው ፍ/ቤት መከላከያ እንዲሁም በ26ኛው በ28ኛው ተከሳሾች ላይ ያቀረብነውን ክስ ይዘን ቀርበናል

እሺ. በ26ኛ

እና በ28ኛ ተከሳሾች ላይ ያቀረብነው ክስ ይዘን ቀርበናል እና መቃወሚያ ባለፈው ላቀረበው በአቶ አድማሱ ብቻ ላይ ላቀረቡት መቃወሚያ ምላሽ ይዘን ቀርበናል ሁለት ነው እሱኛውን በተመለከተ ሌሎቹንም መቃወሚያ ከተመለከተ ነው

ለጠበቆቹም ስጡ እንጂ. ዐ/ህግ

ዐ/ህግ ስለ ዋስትናውስ የጽሁፍ

አዎ አቅርበናል

የት አለ

አንድ ላይ ነው

እየለያችሁ አልጻፋችሁትም እንዴ

ለይተናል የዋስትናውን ለብቻ ጽፈናል ሌሎቹንም ለብቻ ነው የጻፍነው

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት

አሁን ለአቶ አድማሱ መቃወሚያ ብቻ ነው የሌሎቹንም እያየን እንጨምራለን ብለን እኮ ነው

ምንድን ነው እያያችሁ የምትጨምሩት ባለፈው ታዟል እኮ

1079

አሁን ለምሳሌ የአቶ አብራሂምም ሊኖር ይችላል የአቶ ፀጋዬም ሊኖር ይችላል አሁን ለየብቻ እያደረግን ነው ያለው ስለዚህ ----------- ችግራችንን ክቡር ፍ/ቤት ይረዳዋል መብራት የለም ምን የለም

እሺ በእናንተ በኩልስ

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው በታዘዘው መሰረት ለሶስቱ ተከሳሾች የጽሁፍ መቃወሚያችንን እና የዋስትና ጥያቄ መብቶችን አያይዘናል ብለናል

አቅርቡ እሺ

የ23ኛው ተከሳሽ

ቅድም ያልነበረችው ተከሳሽም ቀርባለች

ሰሚራ ሙሜ

አቤት

የት አለች አሁን ነው የመጣሽው

-------------- ከዚሁ ነው የቀረበችው ጀና መሀመድ

ጀና መሀመድ የት ነው ያረፈድሽው እስቲ አስተርጓሚ ኦሮምኛ

ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው

ሀኪም ቤት ሄጂ ነው

አዎ ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው የመጣሁት

እና ፍ/ቤት አንቺን መጠበቅ አለበት ዋስ የጠበቀለሽ ፍ/ቤት ነው

የተከበረው ፍ/ቤት ከሐረር መጥቼ ከዛ ሆስፒታል ጎራ ብየየ እንትን ስል መኪናም ችግር ነበረብኝ

ከየትም ነይ ይሄ ፍ/ቤት ግን ዋስትና ጠብቆልሻል ስለዚህ ዋስትና በዋስትና መብትሽ አልተጠቀምሽም ነገሯት በቋንቋ እቡ ንገራት ያላከበረ ሰው ደግሞ ዋስትና ይወርዳል ይታሰራል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1080

ቁጭ በይ ዐ/ህግ 28ኛ ተከሳሽ ከዚህ በፊት ክስ አልቀረበበትም ተከሳካይ ጠበቃ 28ኛ ላይ ተቃውሞ ነበራችሁ እንዴ 26 ብቻ ነው የሚለው ጽሁፉ ላይ

አዎ

አልቀረበበትም መቃወሚያ

አብዲ አሊ አህመድ ወደዚህ ኑ ሁለታችሁም እዛ ላይ ቁሙ በሳቸው እሺ በእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ላይ ዛሬ ክስ ስለቀረበ ክሱ በንባብ ይሰማል አብዲ አህመድ ኑር አስተርጓሚ አብዲ አህመድ የት ነው የምትኖረው እድሜ ስንት ነው

ሥም - አብዲ አህመድ

እድሜ - 20

ሥራ - ገበሬ

አድራሻ- ወተር

ሥም - አብዲ አሊ አህመድ

እድሜ - 27

ሥራ - አስተማሪ

አድራሻ- ሀረማያ

እሺ ተከሳሾች 26ኛ እና 28ኛ በክሱ በተመለከተው መልክ ማንነታቸውን ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል ክሱን ፍ/ቤቱ ያሰማል፡፡

እሺ 44ኛ ክስ በ26ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ነው ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 27/1 እና 238/1 ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ከማይታወቅ 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀን እና ወሩ በትክክል እስከማይታወቅ 2000 ዓ/ም ድረስ ከሚኖርበት ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመቀላቀል የዚህን ቡድን

1081

አላማ ከግብ ለማድረስ በወታደርነት ሲያገለግል በመቆየቱ በፈጸመው በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

45ኛ ክስ በ28ኛ ተከሳሽ ላይ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ህዳር ወር 1998 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 4:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ኮምቦልቻ ወረዳ አሬሳ ቦቶ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ልዩ ቦታው ዩሱፍ መንደር አካባቢ አንደኛ አብዲ አዩ ሁለተኛ አብዱላሂ አህመድ እና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ሰብስቦ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድንን አርማ በማሳየት ይህንኑ ቡድን በገንዘብና በጉልበት እንዲደግፍ በመቀስቀስ በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ይሄን ስጢቸው እያየሀ አስተርጉምላቸው አንዱ ለአብዱ ስጡትና እያየ አስተርጉሙላቸው

አንደኛው አስተማሪ ነው ያውቃል ይሰማል

ማን ነው 26ኛ ተከሳሽ

አብዲ አሊ ይሰማል

28ኛ ኦኬ ለ26ኛ ተከሳሽ ይተርጎም

እሱን

አዎ ወይ አጠር ባለ መልኩ ሲገለጽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስበሀ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀኑ ወይም ወሩ በትክክል እስከማይታወቅበት 2000 ድረስ ከምትኖርበት የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ ኦነግ ብሎ ራሱን የጠራው አሸባሪ ቡድን በቀላቅለሃል የዚህ ቡድን አላማ ከግብ ለማድረስ በወዛደርነት ስታገለግል በመቆየትህ በፈጸምከው በህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስት ስርዓቱ ላይ የሚደረግ ሙከራ ወንጀል ተከሰሃል፡፡

ክሱን ተረድታችኋል ወይ የተነበበው ገባችሁ

አዎ ገብቶኛል

1082

ግልጽ ነው

ግልጽ ነው

እሺ. ተከላካይ ጠበቃ ተቃውሞውንና የእምነት ክህደት ቃሉን በተመለከተ ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለየ የምታስመዘግቡት ነገር አለ

ባለፈው ያቀረብነው ተመሳሳይ ነው በዛው መሰረት እንትን ይባልልን የዋስትናውም በዛው ይታይልን

እሺ. ቁጭ በል

አብዲ. በሽር ስለ 37ኛ ተከሳሽስ ግንቦት 11 የሚለውን በተጨማሪ ነው የያዛችሁት ግንቦት 11/2001 የሚለውን

ከዋስትናው ጋር የተያያዘ ነው

አንድ ላይ ስላደረጋችሁት ነው

አዎ አንድ ላይ ስላደረግነው ነው ዋስትናውንና መቃወሚያውን አንድ ላይ አድርገነዋል

እሺ. ተከሳሾች ባለፈው በታዘዘው መሰረት ነው ያቀረባችሁት

ዋስትናውን እና መቃወሚያውን

ክርክሩን በአጠቃላይ

አዎ

እሺ. የ33ኛ እና የ36ኛ ተከሳሾች እና 4ኛ ጠበቃ አልቀረቡም 4ኛ ተከሳሽ አመዲን ኢብራሂም አማርኛ ትሰማለህ እስቲ አስተርጓሚ. [illegible] ጠበቃ የሉም ዛሬ በለው አላገኘሃቸውም ወይ አሃ አንተ ማረሚያ ቤት ነው ያለከው ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው አብዲ ያዲ የአንተም ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው ድርሲቱ አብደላ አንቺም ጠበቃሽ ዛሬ የለም እሺ. ቁጭ በሉ ድርሲቱ እስቲ ተነሽ የሰጠሽ ነገር አለ እንዴ ጠበቃው

1083

እሻ የሰጠሽው ነው

አዎ

እሺ ማን ነው አመዲን አንተስ ጠበቃ የሰጡህ ነገር አለ ወይ

ለሳቸው ሰጠሁ

ለማን አቶ አድማሱ የተቀበሉት ነገር አለ አብዲ ያዲን አንተስ ሰጥተሃል እስቲ ለዐ/ህግ ስጧቸው ይሄን አመዲን ኢብራሂም

እሺ ቆይ አንዴ እስቲ አመዲን አንተ ያንተ የለም ነው የምልህ እሺ የሌሎቹ የሁለቱ ደርሷችኋል

አንድ ነው

ደርሷችኋል ከዛ በፊት የሁለቱንም የያዛችሁትን ነገር እዩ

አዎ ------------ ቀደም ሲል ከቢሮ የተቀበልነው ነው

ዐ/ህግ አብዲ ሀጂ አሁን የደረሳችሁ ነው ድርሲቱ ቀደም ብሎ ተሰጥቷችኋል እዩት እስቲ የያዛችሁት ወረቀት ላይ

አለን እሺ አዎ ደርሶናል

ስለ 33ኛ ተከሳሽ አብዲ ሀጂ በዚህ ፍ/ቤት ሌላ መዝገብ አላችሁ እንዴ

አዎ አለን

አለን እኮ ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት የምናስመዘግበው ለፍርድ የቀረበ ሌላ መዝገብ አለን እርግጥ በዚህ ላይ ያው የፍ/ቤቱንም እማንክደው ነው ክስ አንስተናል ብለን ተናግረናል ግን በዛኛው መዝገብ ላይ ለዛሬ እንደውም ለነ ለፍርድ የተቀጠረ መዝገብ አለን በ1999 ለተፈጸመ ወንጀል እና የጽ/ቤታችን አቋም ምንድን ነው እስከ ዛሬም ሊቆይ የቻለው በዚህ መዝገብ ዋስትና በመከልከሉ ነው እርግጥ በዛኛው ተፈቅዶ ነበር ለፍርድ በቀረበው ላይ ስለዚህ ፍርዱን ነገ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1094

ለፍርድ የተቀጠረ ስለሆነ በዛው መሰረት ቀይቶልን ፍርዱን እንዲሰጥልን ነው የምናመለክተው ለነገ የተቀጠረ ነው በዚህ ላይ ያቀረብንበትን ክስ አንስተናል ጽፈናል በጽሁፍም

ዐ/ህግ ስለ ሌሎቹስ የጻፋችሁትን ነገር የምትሉት ነገር አለ በቃል ወደ ምርመራ ከማምራታችን በፊት የምትሉት ነገር አለ

ምናልባት የአሁን አቶ አባይን መቃወሚያም አይተን አሁን የአቶ ፀጋዬንም አይተን ጨምቀን ሁለቱንም እናቀርባለን

እሺ በእናንተ በኩልስ

የተከበረው ፍ/ቤት

አስመዝግቡ

መቃወሚያውን በተመለከተ የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያውን በተመለከተ ስለ ክሱ በአጠቃላይ ክሱን በተመለከተ መቃወሚያችን በዝርዝር በጽሁፍ ሰጥተናል ነገር ግን ከዛ በፊት መቃወሚያው ወደፊት ተመርምሮ ብይን የሚሰጠው ቢሆንም በዋስትናም ጥያቄ ላይ የዋስትናውን ጥያቄ በተመለከተ ክቡር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶት ዋስትናው ጥያቄ ላይ ብይን ቢሰጥልን ይሄንኑ ነው የምናመለክተው፡፡

በእናንተ በኩልስ

በእኛም ይኸው ነው የተከበረው ፍ/ቤት በዋስትናው ጥያቄ ላይ ባለፈው ዐ/ህግ መልስ ሰጥቷል እኛም አቤቱታችንን አቅርበናል ፍ/ቤቱም ይሄን ተቀብሎናል የሱ ብይን ይታይልን ነው መቃወሚያውን በሚመለከት መልስ ተሰጥቷል የነሱ መልስ ቀረን ካሉ አቀባብሉ እንዲታይ ነው ግን የዋስትናው ጥያቄ ክርክሩ የተጠናቀቀ ስለሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን በሚመለከት አንድ ውሳኔ እንዲሰጥልን ነው የምንጠይቀው በአክብሮት፡፡

ባለፈው በታዘዘው ትእዛዝ መሰረት የቀረበው የጽሁፍ መልሶች አሉ ያልቀረቡም አሉ በሌላ በኩል ዛሬ ቀርበው ክሳቸው የተሰማ ተከሳሾችን በተመሳሳይ በተከላካይ ጠበቃ በኩል መቃወሚያው እንዲመዘገብ ስለተደረገ በተመሳሳይ ይኸው የቀረበው መከላከያ እና በዐ/ህግ በኩል የቀረበው አስተያየት ወይም መልስ በተመሳሳይ ለእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ክስ የተሰማላቸው ሁለት ተከሳሾችን ፍ/ቤቱ የሚመረምረው ይሆናል ከዚህ ውጪ የሚቀረው ነገር

1085

በዚህ መዝገብ ላይ በዋስትና የተነሳው ክርክር ላይ ብይን መስጠት ነው በቅድሚያ የሚሆነው እና ቀጣይ የክርክሩ አመራር ሂደት በተመለከተ ሁኔታዎችን ማመልከት ነው በዚሁ መዝገቡ ሰፊ ስለሆነ ትንሽ ጊዜ ወስደን ፍ/ቤቱ ምርመራ ያደርጋል አጀንዳ ትይዛላችሁ ማለት ነው ለዚሁ ለዚሁ ብይን ለመስጠት የምንይዘው አጀንዳ በተመሳሳይ የዛሬ ሳምንት ግንቦት 18 ጠዋት ላይ

ግንቦት 18 --------- አንድ ላይ ቢሆንልኝ

ፍ/ቤቱ ከግንቦት 18 ውጪ ትንሽ ድምጽ

አንደኛ እንዲታዘዝልን ሁለተኛ

አስመዝግቡ

አንደኛ አበል ያለፈው ሳምንት ነው የተጠናቀቀው የክሱም ብዛት የተከሳሾቹም ብዛትና የክሱን ሁኔታ አይቼ ነው ተቸግሬ ነው ያለሁት ስለዚህ ይሄ የሚሰጠው ቀጠሮ እኔ አዲስ አበባ ደርሼ የምመለስበትን ያገናዘበ መሆን አለበት እዛ ሄጄ አበል አሳዝዤ ምናምን ብዬ ተመልሼ መምጣትን ይጠይቃል

የእንግዲህ በኋላ ያለውን የቆይታ ጊዜውን ፍ/ቤቱ ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያሳውቃል በዚህ መልክ ያለውን ነገር ተነጋግሮ መጨረስ ነው ስለዚህ በሌላ በኩል እነዚህ ተከሳሾች ቁጥራቸው ብዙ ነው በእስር ላይ ነው ያሉት ስለዚህ በአስተዳደር መፈታት ያለበት ነገር በአስተዳደር መፈታት አለበት ፍ/ቤቱ ለዚህ ትዕዛዝ ይሰጣል ስለዚህ ያለውን ቆይታ ጊዜ ለሚባለው የአስተዳደር ክፍል እንዲደርስ እና በሚያዘው አጀንዳ ድረስ እንዲቆዩ ነው የሚሆነው ማለት ነው ስለዚህ የአጀንዳው ምን አሉ የሚቸግር ነገር አለው ይሄ

አይ የሚቸግር የለውም

ስለዚህ በአጀንዳ በኩል ቅድም በተነሳው ምክንያት ዋናው ምክንያት ግንቦት 18 ነው መሆን ያለበት ምክንያቱም ብዙ ናቸው በጠበቃ በኩል የተነሳውን ጥያቄ በተመለከተ እርሶ የሚወክሏቸው ተከሳሾች ሶስት ናቸው በቁጥር ሌሎቹ በርካታዎቹ ደግሞ በተከላካይ ጠበቃ የተወከሉ እንደዚሁም -------- ትንሽ ቁጥራቸው ሶስት በተመሳሳይ የተወከሉ ናቸው እና በአብዛኛው መንግስት ባቆመው ጠበቃ የሚወከሉ እና ቁጥራቸውም ሰፊ ስለሆነ አጀንዳን

1086

በተመለከተ መቀየሩ ብዙም አስፈላጊ አይሆንም ሌላ የሚሰጠው ብይን ነው በብይን ጊዜ መገኘት የቻለ ይገኛል ያልተገኘም የፍ/ቤት ስራ ስለሆነ የፍ/ቤቱ ስራ በአደባባይ በችሎት ማሳወቅ ነው የሚሆነው እና ይሄንን ፍ/ቤቱ ያሰማል ግንቦት 18 ላይ ስለዚህ አጀንዳን በተመለከተ የተነሳውን ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ለግንቦት 18 ፍ/ቤቱ አጀንዳ ይዟል ብይን ይሰጣል ግንቦት 18 ማረሚያ ቤት ታቀርቧቸዋላችሁ በዋስ ያሉትም ተከሳሾች በዚሁ መሰረት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ በጥብቅ ያሳስባል ምንድን ነው አቡ አስተርጉም ስምሽ ማን ነው መጀመሪያ ስምሽን ስጧት ድምጽ እንትኑን ስጧት ስምሽ ማን ነው በላት

ኪሚያ አሚን

ምን ፈለግሽ

ሰባት ልጆች አባት የሌላቸውን እያሳደኩ ነው ያለሁት አሁን ልጆቼ ተበትነዋል እኔ ነኝ ልጆቼን የማሳድገው አሁን እኔ በመታሰሬ ልጆቼ ተበትነዋል 4 ወር ሙሉ ያው እስር ቤት ነው ያለሁት

በቃ ይሄን ለማለት ነው ሌላ አለሽ

ይሄው ነው ችግሬ

እሺ ሌላ እጁን ያወጣ ማን ነው ማን ነው ስምህ

ጫላ ሙክታር እባላለሁ

ስንተኛ ጫላ

42ኛ

ጫላ መቀጠል ትችላለህ

ሐረር በዚሁ ጉዳይ ተከስሼ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቤ ማለት ነው የዋስ መብት ተጠብቆልኝ እያለሁ እስከ ዛሬ ይኸው እዚሁ ቆየሁ

ጽፈከዋል አደለ እሱን

እዚህ ላይ ጽፌዋለሁ ወረቀቱ ላይ

1087

ጽፈ.ከዋል አደለ እሱ ነው የደገምከው

አዎ

አይተነዋል እኛ ስለዚ.ህ ተቀመጥ ጫሳ

እሺ.

ሌላ እንግዲህ ጊዜ አታባክኑ አቡ ንገራቸው ጊዜ አታባክኑ ይሄ በስርዓት የሚመራ ፍ/ቤት ነው እያንዳንዳችሁ የምትሰሙበት ጊዜ አስፈላጊ ሲሆን ይኖራል አሁን ግን ለብይን ነው የተቀጠረው አሁን ባላችሁበት በቆይታችሁ የተቸገራችሁት ነገር ብቻ ካለ አንድ ሁለት ሰው እንሰማለን ሌላ ግን የዋስትና ጥያቄ ገና ብይን አልተሰጠበትም ማስረጃ የሚሰማበትም ሂደትም ገና ስለሱ የተያዘ ቀጠሮም የለም ከወዲሁ ማንሳት የምትችሉት የመብት ጥያቄ በማረሚያ ቤት አሁን ባላችሁበት ቆይታ ጋር በተያያዘ የሚያያዝ ጥያቄ ነው ሌላ ለፍ/ቤት የሚቀርብ የህግ ጥያቄ እና ክርክር ግን በጠበቃ በኩል ቀርቧል በጽሁፍም ቀርቧል ፍ/ቤቱ እሱን መርምሮ ብይን ይሰጣል ይሄን ለማድረግ ለግንቦት 18 ነው የተቀጠረው የዛሬ ሳምንት ማለት ነው ገባችሁ ወይ አሁን እጅ ያወጣችሁት ለምንድን ነው እስቲ አንድ ሰው ማን ነው ስምህ

መሀመድ ኡመር

የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ ግንቦት 17 ነው ፈተናው የሚሰጠው የ10ኛ ክፍል ማትሪክ የሚሰጠው ስለዚ.ህ ትዕዛዙን ወደ ሚመለከተው ቢ.ያሳውቁልኝ

እሱን በጽሁፍ አመልክት ማረሚያ ቤት እንደዚ.ህ አይነት ነገር እርዳታ ያደርጋሉ ስላልጠየክ ነው ጠይቅ እነሱ እንዴት እንደሚቀርብ ይረዱሃል ሌላ ሌላ የሚናገር ሰው እስቲ ስጣቸው ማን ነው ስምህ

ያለኝ ችግር

ስምህ ማን ነው ስምህ

ሀጂ. ጣሀ

ሀጂ. ጣሀ እሺ. ምንድን ነው ችግርህ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1088

ከልጆቼ ላይ ገንዘብም ወስዷል እኔም እንደዚህ እጄ ሽባ ሆኗል እጄ ምንም አይሰራም ብሏቴም አይሰራም

ቆይ ቆይ ይበቃል ይበቃል ይሄን ወደፊት አሁን እሱን እያጣራን አይደለንም ሌላ ጥያቄ ሌላ አንድ ሰው ብቻ ነው ከአሁን በኋላ የሚፈቀድለት

45ኛ ተከሳሽ ነበርከ

ስምህ ማን ነው

ዩሱፍ ጨሎ

አው ዩሱፍ ጨሎ እሺ

አልተጠራሁም ቅድም ሶስት ነው የጠራችሁት አራት ነበር እኔ ከአህመድ አብራሂም ጋር

እነሱ በጠበቃ ስለተወከሉ ነው

እኮ እኔም ጠበቃ ከእነሱ ጋር ነኝ

ጠበቃ አላስመዘገቡም ባለፈው

አስመዝግበዋል 45 ብለው

45

አዎ

አልመጡማ ያንተ ጠበቃ

አልመጣም አዎ ጠበቃው አልመጣም ግን አስመዝግቦ ነበር

ቆይ አንተ 45ኛ ነህ አይደለም

አዎ

45ኛ ተከላካይ ጠበቃ ይሄን ታስታውሳላችሁ አደለም 45ኛ ተከሳሽ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1089

አዎ ግን እናንተ የጻፋችሁት ላይ ስለ 45ኛ ተከሳሽ

45ኛ ተከሳሽ ------------------

ስላላችሁ ነው

አዎ

አንተ ጠበቃ አመጣለሁ ያልከው ነው

ዛሬ አልቀረበም እንጂ እኮ አስመዝግቧል

አዎ ባለፈው አላስመዘገቡም

አስመዝግቧል 45 ብሎ

አላስመዘገቡም

አስመዝግቦ ነበር እዚሁ

አላስመዘገቡም እኛ እናስታውሳለን እዚህ ተመዝግቧል አቶ ፀጋዬ ፈቲህ ያስመዘገቡት 4ኛን፣ 33ኛ እና 36ኛ ተከሳሾችን ብቻ ነው ዞሮ ዞሮ ጠበቃ ይወክሉሃል አደለም

ወክዬዋለሁ እሱን

ወክለከዋል

አዎ

በቃ አሁን ጠበቃ አልቀረቡም መቅረብ ነበረባቸው በተመሳሳይ የሚታይ ይሆናል የአንተን ልዩነት አያመጣም

እሺ

በቃል ክርክሩ ስለተሰማ የዋስትናው አዎ እኛ ግን መዝግበናል አላስመዘገቡም 45ኛን በተመለከተ በጽ/ቤት ተከሳሹ ጠበቃውን ጠይቀናል ምክንያቱም ይሄ ተከሳሽ መጀመሪያ ላይ ጠበቃ አመጣለሁ ያለ መሆኑን ስለምናስታውስ ነው ጠበቃው ግን ይሄን አላስመዘገቡም ጥፋቱ የጠበቃው ሊሆን ይችላል እሱን ወደማጣራት እንሄድም ዞሮ ዞሮ ግን የዋስትና ክርክር ግን

ለወከሏቸው ጠበቆች ለተከሳሾች በቃል አስምተዋል ይሄን ሰው እወከላለሁ ካለ የሚወክሉት ከሆነ ልዩነት አያመጣም የወንጀል ጉዳይ ስለሆነ ያው ይመዘገባል ሌላ እስቲ ይኼኛው ማን ነው ማን ነው ስምህ ሁሴን እስቲ ስጠው ማን ነው ስምህ

ዙቤድ ሁሴን

ተቀበለው አቶ አቡ እሺ ምንድን ነው የምትፈልገው

ተመሳሳይ ቅድም እዚህ ጋ ከቀረበው ጋር ከአሁን ቀደም በሌላ በከፍተኛ ፍ/ቤት እንትን ብዬ ወጥቻለሁ ነው የሚለው

እሱ በብይን ጊዜ የሚታይ ነው በጽሁፍም አድርገከዋል አይተነዋል ስለዚህ እዚሁ ይመረመራል አትድገሙ እንደዚህ አይነት ነገር አትድገሙ ቁጭ በል ሌላ በዚሁ ይበቃናል ማን ነው እሺ እርሶ ስሞት ማን ነው

ሚካኤል አብዱላሂ

እሺ ምንድን ነው የሚፈልጉት

እኔ 90 አመቴ ነው እጄ አይሰራም ያመኛል ስለዚህ አሁን እኔ በ90 አመቴ በማላውቀው ነገር ነው እዚህ ውስጥ ያው በ90 አመቴ

እሱ ወደፊት በማስረጃ ይጣራል አሁን ግን ተጠርጥረው ቀርበዋል ፍ/ቤቱ ደግሞ ህግ በሚያዘው መሰረት ይመለከታል የእርሶን ጉዳይ በላቸው አበቃችሁ በላቸው ሁሉንም ማረሚያ ቤት በዚሁ ሌላ ነገር ዐ/ህግ የምታሳስቡት ሌላ አለ

ምንም የለንም

ከሌለ በእናንተም በኩል የለም ከሌለ በዚሁ ለግንቦት 18 ጠዋት 2:00 ሰዓት ላይ አጀንዳ በመያዝ ችሎቱ ስራውን አብቅቶ ተነስቷል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ማ/ተ

1091

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 11/9/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን

- ዩሱፍ መሀመድ በዚህ መዝገብ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌዴራል ዐ/ህግ አቶ ፌይሰል አብዲ፣ ረድኤት ይልማ እና አንተነህ ጌታቸው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረሀማን ባሌ ጎጆ 73 ተከሳሾች ቀርበዋል

ማረሚያ ቤት እናንተ ጋር ያሉት 7 ተከሳሾች ቀርበዋል በዋስ ያሉት 3 ተከሳሾች ቀርበዋል 21ኛ ተከሳሽ ሰሚራ መሀመድ አሊ፣ አለህ የት አለ ሰሚራ ሙሜ፣ መጥተሻል ጀና መሀመድ፣ የት አለች

አልቀረበችም መሰለኝ

ጀና መሀመድ፣ ዘሀራ አብዶሽ፣

አለች ይችውና

እሺ በዋስ ያሉት ተከሳሾች 22ኛ፣ 48ኛ፣ ተከሳሾች አሉ 31ኛ ተከሳሽ ግን የለችም 31ኛ ተከሳሽ በዋስ እንድትቆይ የተደረገ ቢሆንም ዛሬ አልቀረበችም ሌሎቹ በማረሚያ ቤት ያሉት 71 ተከሳሾች መቅረባቸው ተረጋግጧል እሺ በጠበቃ በኩል እራሳችሁን አስመዝግቡ

የ23ኛ፣ 37ኛ፣ እና 38ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ

እሺ

በጠበቃ ከተወከሉት ውጪ ያሉት ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አድማሱ መለሰ ቀርቤአለሁ

እሺ ጠበቆችም ራሳቸውን አስመዝግበዋል አንድ ጠበቃ ቀርቷል አደለ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1092

አዎ

አቶ ፀጋዬ

አቶ ፀጋዬ

እሺ. ዐ/ህግ በዛሬ እለት አመጣችሁ የታዘዘውን

አዎ የተከበረው ፍ/ቤት መከላከያ እንዲሁም በ26ኛው በ28ኛው ተከሳሾች ላይ ያቀረብነውን ክስ ይዘን ቀርበናል

እሺ. በ26ኛ

እና በ28ኛ ተከሳሾች ላይ ያቀረብነው ክስ ይዘን ቀርበናል እና መቃወሚያ ባለፈው ላቀረበው በአቶ አድማሱ ብቻ ላይ ላቀረቡት መቃወሚያ ምላሽ ይዘን ቀርበናል ሁለት ነው እሱኛውን በተመለከተ ሌሎቹንም መቃወሚያ ከተመለከተ ነው

ለጠበቆቹም ስጡ እንጂ. ዐ/ህግ

ዐ/ህግ ስለ ዋስትናውስ የጽሁፍ

አዎ አቅርበናል

የት አለ

አንድ ላይ ነው

እየለያችሁ አልጻፋችሁትም እንዴ

ለይተናል የዋስትናውን ለብቻ ጽፈናል ሌሎቹንም ለብቻ ነው የጻፍነው

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት

አሁን ለአቶ አድማሱ መቃወሚያ ብቻ ነው የሌሎቹንም እያየን እንጨምራለን ብለን እኮ ነው

ምንድን ነው እያያችሁ የምትጨምሩት ባለፈው ታዟል እኮ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ. ሪፐብሊክ

አሁን ለምሳሌ የአቶ አብራሂምም ሊኖር ይችላል የአቶ ፀጋዬም ሊኖር ይችላል አሁን ለየብቻ እያደረግን ነው ያለው ስለዚህ ----------- ችግራችንን ክቡር ፍ/ቤት ይረዳዋል መብራት የለም ምን የለም

እሺ በእናንተ በኩልስ

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው በታዘዘው መሰረት ለሶስቱ ተከሳሾች የጽሁፍ መቃወሚያችንን እና የዋስትና ጥያቄ መብቶችን አያይዘናል ብለናል

አቅርቡ እሺ

የ23ኛው ተከሳሽ

ቅድም ያልነበረችው ተከሳሽም ቀርባለች

ሰሚራ ሙሜ

አቤት

የት አለች አሁን ነው የመጣሽው

-------------- ከዚሁ ነው የቀረበችው ጀና መሀመድ

ጀና መሀመድ የት ነው ያረፈድሽው እስቲ አስተርጓሚ ኦሮምኛ

ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው

ሀኪም ቤት ሄጄ ነው

አዎ ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው የመጣሁት

እና ፍ/ቤት አንቺን መጠበቅ አለበት ዋስ የጠበቀለሽ ፍ/ቤት ነው

የተከበረው ፍ/ቤት ከሐረር መጥቼ እቶ ሆስፒታል ጎራ ብየየ እንትን ስል መኪናም ችግር ነበረብኝ

ከየትም ነይ ይሄ ፍ/ቤት ግን ዋስትና ጠብቆልሻል ስለዚህ ዋስትና በዋስትና መብትሽ አልተጠቀምሽም ንገሯት በቋንቋ አቡ ንገራት ያላከበረ ሰው ደግሞ ዋስትና ይወርዳል ይታሰራል

1094

ቁጥ በይ ዐ/ህግ 28ኛ ተከሳሽ ከዚህ በፊት ክስ አልቀረበበትም ተከሳካይ ጠበቃ 28ኛ ላይ ተቃውሞ ነበራችሁ እንዴ 26 ብቻ ነው የሚለው ጽሁፉ ላይ

አዎ

አልቀረበበትም መቃወሚያ

አብዲ አሊ አህመድ ወደዚህ ኑ ሁለታችሁም እዛ ላይ ቁሙ በላቸው እሺ በእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ላይ ዛሬ ክስ ስለቀረበ ክሱ በንባብ ይሰማል አብዲ አህመድ ኑር አስተርጓሚ አብዲ አህመድ የት ነው የምትኖረው እድሜ ስንት ነው

ሥም - አብዲ አህመድ

እድሜ - 20

ሥራ - ገበሬ

አድራሻ- ወተር

ሥም - አብዲ አሊ አህመድ

እድሜ - 27

ሥራ - አስተማሪ

አድራሻ- ሀረማያ

እሺ ተከሳሾች 26ኛ እና 28ኛ በክሱ በተመለከተው መልክ ማንነታቸውን ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል ክሱን ፍ/ቤቱ ያሰማል።

እሺ 44ኛ ክስ በ26ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ነው ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 27/1 እና 238/1 ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ከማይታወቅ 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀን እና ወሩ በትክክል እስከማይታወቅ 2000 ዓ/ም ድረስ ከሚኖርበት ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመቀላቀል የዚህን ቡድን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1095

አላማ ከግብ ለማድረስ በወታደርነት ሲያገለግል በመቆየቱ በፈጸመው በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

45ኛ ክስ በ28ኛ ተከሳሽ ላይ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ህዳር ወር 1998 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 4:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ኮምቦልቻ ወረዳ እሬሳ ቡቶ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ልዩ ቦታው ዩሱፍ መንደር አካባቢ አንደኛ አብዲ አዩ ሁለተኛ አብዱላሂ አህመድ እና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ሰብስቦ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድንን አርማ በማሳየት ይህንኑ ቡድን በገንዘብና በጉልበት እንዲደግፍ በመቀስቀስ በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ይሄን ስጧቸው እያየህ አስተርጉምላቸው አንዱ ለአብዱ ስጡትና እያየ አስተርጉሙላቸው

አንደኛው አስተማሪ ነው ያውቃል ይሰማል

ማን ነው 26ኛ ተከሳሽ

አብዲ አሊ ይሰማል

28ኛ ኦኬ ለ26ኛ ተከሳሽ ይተርጎም

እሱን

አዎ ወይ አጠር ባለ መልኩ ሲገለጽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስበህ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀኑ ወይም ወሩ በትክክል እስከማይታወቅበት 2000 ድረስ ከምትኖርበት የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ የኦነግ ብሎ ራሱን የጠራው አሸባሪ ቡድን በቀላቅለሃል የዚህ ቡድን አላማ ከግብ ለማድረስ በወዛደርነት ስታገለግል በመቆየትህ በፈጸምከው በህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስት ስርዓቱ ላይ የሚደረግ ሙከራ ወንጀል ተከሰሃል፡፡

ክሱን ተረድታችኋል ወይ የቀነበበው ገባችሁ

አዎ ገብቶኛል

1096

ግልጽ ነው

ግልጽ ነው

እሺ ተከሳካይ ጠበቃ ተቃውሞውንና የእምነት ክህደት ቃሉን በተመለከተ ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለየ የምታስመዘግቡት ነገር አለ

ባለፈው ያቀረብነው ተመሳሳይ ነው በዛው መሰረት እንትን ይባልልን የዋስትናውም በዛው ይታይልን

እሺ ቀጭ በል

አብዲ በሽር ስለ 37ኛ ተከሳሽስ ግንቦት 11 የሚለውን በተጨማሪ ነው የያዛችሁት ግንቦት 11/2001 የሚለውን

ከዋስትናው ጋር የተያያዘ ነው

አንድ ላይ ስላደረጋችሁት ነው

አዎ አንድ ላይ ስላደረግነው ነው ዋስትናውንና መቃወሚያውን አንድ ላይ አድርገነዋል

እሺ ተከሳሾች ባለፈው በታዘዘው መሰረት ነው ያቀረባችሁት

ዋስትናውን እና መቃወሚያውን

ክርክሩን በአጠቃላይ

አዎ

እሺ የ33ኛ እና የ36ኛ ተከሳሾች እና 4ኛ ጠበቃ አልቀረቡም 4ኛ ተከሳሽ አመዲን ኢብራሂም አማርኛ ትሰማለህ እስቲ አስተርጓሚ አቶ ጠበቃ የሉም ዛሬ በለው አላገኘሃቸውም ወይ አሃ አንተ ማረሚያ ቤት ነው ያለከው ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው አብዲ ያዲ የአንተም ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው ድርሲቱ አብደላ አንቺም ጠበቃሽ ዛሬ የለም እሺ ቁጭ በሉ ድርሲቱ እስቲ ተነሽ የሰጠሽ ነገር አለ እንዴ ጠበቃው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1097

እሄ የሰጠሸው ነው

እዎ

እሺ ማን ነው አመዲን አንተስ ጠበቃ የሰጡህ ነገር አለ ወይ

ለሳቸው ሰጠሁ

ለማን አቶ አድማሱ የተቀበሉት ነገር አለ አብዲ ያዲን አንተስ ሰጥተሃል እስቲ ለዐ/ህግ ስጧቸው ይሄን አመዲን ኢብራሂም

እሺ ቆይ አንዴ እስቲ አመዲን አንተ ያንተ የለም ነው የምልህ እሺ የሌሎቹ የሁለቱ ደርሷችኋል

አንድ ነው

ደርሷችኋል ከዛ በፊት የሁለቱንም የያዛችሁትን ነገር እዩ

አዎ ------------ ቀደም ሲል ከበ.ሮ የተቀበልነው ነው

ዐ/ህግ አብዲ ሀጂ አሁን የደረሳችሁ ነው ድርሲቱ ቀደም ብሎ ተሰጥቷችኋል እዩት እስቲ የያዛችሁት ወረቀት ላይ

አለን እሺ አዎ ደርሶናል

ስለ 33ኛ ተከሳሽ አብዲ ሀጂ በዚህ ፍ/ቤት ሌላ መዝገብ አላችሁ እንዴ

አዎ አለን

አለን እኮ ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት የምናስመዘግበው ለፍርድ የቀረበ ሌላ መዝገብ አለን እርግጥ በዚህ ላይ ያው የፍ/ቤቱንም እማንክደው ነው ክስ አንስተናል ብለን ተናግረናል ግን በዛኛው መዝገብ ላይ ለዛሬ እንደውም ለነገ ለፍርድ የተቀጠረ መዝገብ አለን በ1999 ለተፈጸመ ወንጀል እና የጽ/ቤታችን አቋም ምንድን ነው እስከ ዛሬም ሲቆይ የቻለው በዚህ መዝገብ ዋስትና በመከልከሉ ነው እርግጥ በዛኛው ተፈቅዶ ነበር ለፍርድ በቀረበው ላይ ስለዚህ ፍርዱን ነገ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1098

ለፍርድ የተቀጠረ ስለሆነ በዛው መሰረት ቀይቶልን ፍርዱን እንዲሰጥልን ነው የምናመለክተው ለነገ የተቀጠረ ነው በዚህ ላይ ያቀረብንበትን ክስ አንስተናል ጽፈናል በጽሁፍም

ዐ/ህግ ስለ ሌሎቹስ የጻፋችሁትን ነገር የምትሉት ነገር አለ በቃል ወደ ምርመራ ከማምራታችን በፊት የምትሉት ነገር አለ

ምናልባት የአሁን አቶ አባይን መቃወሚያም አይተን አሁን የአቶ ፀጋዬንም አይተን ጨምቀን ሁለቱንም እናቀርባለን

እሺ በእናንተ በኩልስ

የተከበረው ፍ/ቤት

አስመዝግቡ

መቃወሚያውን በተመለከተ የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያውን በተመለከተ ስለ ክሱ በአጠቃላይ ክሱን በተመለከተ መቃወሚያችን በዝርዝር በጽሁፍ ሰጥተናል ነገር ግን ከዛ በፊት መቃወሚያው ወደፊት ተመርምሮ ብይን የሚሰጠው ቢሆንም በዋስትናም ጥያቄ ላይ የዋስትናውን ጥያቄ በተመለከተ ክቡር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶት ዋስትናው ጥያቄ ላይ ብይን ቢሰጥልን ይሄንኑ ነው የምናመለክተው፡፡

በእናንተ በኩልስ

በእኛም ይኸው ነው የተከበረው ፍ/ቤት በዋስትናው ጥያቄ ላይ ባለፈው ዐ/ህግ መልስ ሰጥቷል እኛም አቤቱታችንን አቅርበናል ፍ/ቤቱም ይሄን ተቀብሎናል የሱ ብይን ይታይልን ነው መቃወሚያውን በሚመለከት መልስ ተሰጥቷል የነሱ መልስ ቀረን ካሉ አቀባብሎ እንዲታይ ነው ግን የዋስትናው ጥያቄ ክርክሩ የተጠናቀቀ ስለሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን በሚመለከት አንድ ውሳኔ እንዲሰጥልን ነው የምንጠይቀው በአክብሮት፡፡

ባለፈው በታዘዘው ትእዛዝ መሰረት የቀረበው የጽሁፍ መልሶች አሉ ያልቀረቡም አሉ በሌላ በኩል ዛሬ ቀርበው ክሳቸው የተሰማ ተከሳሾችን በተመሳሳይ በተከላካይ ጠበቃ በኩል መቃወሚያው እንዲመዘገብ ስለተደረገ በተመሳሳይ ይኸው የቀረበው መከላከያ እና በዐ/ህግ በኩል የቀረበው አስተያየት ወይም መልስ በተመሳሳይ ለእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ክስ የተሰማላቸው ሁለት ተከሳሾች ፍ/ቤቱ የሚመረምረው ይሆናል ከዚህ ውጪ የሚቀረው ነገር

1099

በዚህ መዝገብ ላይ በዋስትና የተነሳው ክርክር ላይ ብይን መስጠት ነው በቅድሚያ የሚሆነው እና ቀጣይ የክርክሩ አመራር ሂደት በተመለከተ ሁኔታዎችን ማመልከት ነው በዚሁ መዝገቡ ሰፊ ስለሆነ ትንሽ ጊዜ ወስደን ፍ/ቤቱ ምርመራ ያደርጋል አጀንዳ ትይዛላችሁ ማለት ነው ለዚሁ ለዚሁ ብይን ለመስጠት የምንይዘው አጀንዳ በተመሳሳይ የዛሬ ሳምንት ግንቦት 18 ጠዋት ላይ

ግንቦት 18 --------- አንድ ላይ ቢሆንልኝ

ፍ/ቤቱ ከግንቦት 18 ውጪ ትንሽ ድምጽ

አንደኛ እንዲታዘዝልን ሁለተኛ

አስመዝግቡ

አንደኛ አበል ያለፈው ሳምንት ነው የተጠናቀቀው የክሱም ብዛት የተከሳሾቹም ብዛትና የክሱን ሁኔታ አይቼ ነው ተቸግሬ ነው ያለሁት ስለዚህ ይሄ የሚሰጠው ቀጠሮ እኔ አዲስ አበባ ደርሼ የምመለስበትን ያገናዘበ መሆን አለበት እዛ ሄጀ አበል አሳዝገቼ ምናምን ብዬ ተመልሼ መምጣትን ይጠይቃል

የእንግዲህ በኋላ ያለውን የቆይታ ጊዜውን ፍ/ቤቱ ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያሳውቃል በዚህ መልክ ያለውን ነገር ተነጋግሮ መጨረስ ነው ስለዚህ በሌላ በኩል እነዚህ ተከሳሾች ቁጥራቸው ብዙ ነው በእስር ላይ ነው ያሉት ስለዚህ በአስተዳደር መፈታት ያለበት ነገር በአስተዳደር መፈታት አለበት ፍ/ቤቱ ለዚህ ትዕዛዝ ይሰጣል ስለዚህ ያለውን ቆይታ ጊዜ ለሚባለው የአስተዳደር ክፍል እንዲደርስ እና በሚያዘው አጀንዳ ድረስ እንዲቆዩ ነው የሚሆነው ማለት ነው ስለዚህ የአጀንዳው ምን አሉ የሚቸግር ነገር አለው ይሄ

አይ የሚቸግር የለውም

ስለዚህ በአጀንዳ በኩል ቅድም በተነሳው ምክንያት ዋናው ምክንያት ግንቦት 18 ነው መሆን ያለበት ምክንያቱም ብዙ ናቸው በጠቅላላ በኩል የተነሳውን ጥያቄ በተመለከተ እርሶ የሚወክሏቸው ተከሳሾች ሶስት ናቸው በቁጥር ሌሎቹ በርካታዎቹ ደግሞ በተከላካይ ጠበቃ የተወከሉ እንደዚሁም --------- ትንሽ ቁጥራቸው ሶስት በተመሳሳይ የተወከሉ ናቸው እና በአብዛኛው መንግስት ባቆመው ጠበቃ የሚወከሉ እና ቁጥራቸውም ሰፊ ስለሆነ አጀንዳን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ቁጥር

1100

በተመለከተ መቀየሩ ብዙም አስፈላጊ አይሆንም ሌላ የሚሰጠው ብይን ነው በብይን ጊዜ መገኘት የቻለ ይገኛል ያልተገኘም የፍ/ቤት ስራ ስለሆነ የፍ/ቤቱ ስራ በአደባባይ በችሎት ማሳወቅ ነው የሚሆነው እና ይሄንኑ ፍ/ቤቱ ያሰማል ግንቦት 18 ላይ ስለዚህ አጀንዳን በተመለከተ የተነሳውን ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ለግንቦት 18 ፍ/ቤቱ አጀንዳ ይዟል ብይን ይሰጣል ግንቦት 18 ማረሚያ ቤት ታቀርቧቸዋላችሁ በዋስ ያሉትም ተከሳሾች በዚሁ መሰረት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ በጥብቅ ያሳስባል ምንድን ነው አቡ አስተርጉም ስምሽ ማን ነው መጀመሪያ ስምሽን ስጧት ድምጽ እንትኑን ስጧት ስምሽ ማን ነው በላት

ኪሚያ አሚን

ምን ፈለግሽ

ሰባት ልጆች አባት የሌላቸውን እያሳደኩ ነው ያለሁት አሁን ልጆቼ ተበትነዋል እኔ ነኝ ልጆቼን የማሳድገው አሁን እኔ በመታሰሬ ልጆቼ ተበትነዋል 4 ወር ሙሉ ያው እስር ቤት ነው ያለሁት

በቃ ይሄን ለማለት ነው ሌላ አለሽ

ይሄው ነው ችግሬ

እሺ ሌላ እጁን ያወጣ ማን ነው ማን ነው ስምህ

ጫላ ሙክታር እባላለሁ

ስንተኛ ጫላ

42ኛ

ጫላ መቀጠል ትችላለህ

ሐረር በዚሁ ጉዳይ ተከስሼ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቤ ማለት ነው የዋስ መብት ተጠብቆልኝ እያለሁ እስከ ዛሬ ይኸው እዚህ ቆይቻለሁ

ጽፈከዋል አደለ እሱን

እዚህ ላይ ጽፌዋለሁ ወረቀቱ ላይ

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ዲሬክቶሬት ... ቁጥር 4

1101

ጽ/ፈ.ከዋል አደሰ እሱ.ን ነው የደገምከው

አዎ

አይተነዋል እኛ ስለዚህ ተቀመጥ ጫላ

እሺ

ሌላ እንግዲህ ጊዜ አታባክኑ አቡ ንገራቸው ጊዜ አታባክኑ ይሄ በስርዓት የሚመራ ፍ/ቤት ነው እያንዳንዳችሁ የምትሰሙበት ጊዜ አስፈላጊ ሲሆን ይኖራል አሁን ግን ለብይን ነው የተቀጠረው አሁን ባላችሁበት በቆይታችሁ የተቸገራችሁት ነገር ብቻ ካለ አንድ ሁለት ሰው እንሰማለን ሌላ ግን የዋስትና ጥያቄ ገና ብይን አልተሰጠበትም ማስረጃ የሚሰማበትም ሂደትም ገና ስለሱ የተያዘ ቀጠሮም የለም ከወዲሁ ማንሳት የምትችሉት የመብት ጥያቄ በማረሚያ ቤት አሁን ባላችሁበት ቆይታ ጋር በተያያዘ የሚያያዝ ጥያቄ ነው ሌላ ለፍ/ቤት የሚቀርብ የህግ ጥያቄ እና ክርክር ግን በጠበቃ በኩል ቀርቧል በጽሁፍም ቀርቧል ፍ/ቤቱ እሱን መርምሮ ብይን ይሰጣል ይሄን ለማድረግ ለግንቦት 18 ነው የተቀጠረው የዛሬ ሳምንት ማለት ነው ገባችሁ ወይ አሁን እጅ ያወጣችሁት ለምንድን ነው እስቲ አንድ ሰው ማን ነው ስምህ

መሀመድ ኡመር

የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ ግንቦት 17 ነው ፈተናው የሚሰጠው የ10ኛ ክፍል ማትሪክ የሚሰጠው ስለዚህ ትዕዛዙን ወደ ሚመለከተው ቢያሳውቁልኝ

እሱን በጽሁፍ አመልክት ማረሚያ ቤት እንደዚህ አይነት ነገር እርዳታ ያደርጋሉ ስላልጠየክ ነው ጠይቅ እነሱ እንዴት እንደሚቀርብ ይረዱሃል ሌላ ሌላ የሚናገር ሰው እስቲ ስጣቸው ማን ነው ስምህ

ያለኝ ችግር

ስምህ ማን ነው ስምህ

ሀጂ ጣሀ

ሀጂ ጣሀ እሺ ምንድን ነው ችግርህ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁ. ጋር

1012

ከልጆቼ ላይ ገንዘብም ወስዷል እኔም እንደዚህ እጄ ሽባ ሆኗል እጄ ምንም አይሰራም ብልቴም አይሰራም

ቆይ ቆይ ይበቃል ይበቃል ይሄን ወደፊት አሁን እሱን እያጣራን አይደለንም ሌላ ጥያቄ ሌላ አንድ ሰው ብቻ ነው ከአሁን በኋላ የሚፈቀድለት

45ኛ ተከሳሽ ነበርከ

ስምህ ማን ነው

ዩሱፍ ጨሎ

አው ዩሱፍ ጨሎ እሺ

አልተጠራሁም ቅድም ሶስት ነው የጠራችሁት አራት ነበር እኔ ከአህመድ አብራሂም ጋር

እነሱ በጠበቃ ስለተወከሉ ነው

እኮ እኔም ጠበቃ ከእነሱ ጋር ነኝ

ጠበቃ አላስመዘገቡም ባለፈው

አስመዝግበዋል 45 ብለው

45

አዎ

አልመጡማ ያንተ ጠበቃ

አልመጣም አዎ ጠበቃው አልመጣም ግን አስመዝግቦ ነበር

ቆይ አንተ 45ኛ ነህ አይደለም

አዎ

45ኛ ተከላካይ ጠበቃ ይሄን ታስተውሳላችሁ አደለም 45ኛ ተከሳሽ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1103

አዎ ግን እናንተ የጻፋችሁት ላይ ስለ 45ኛ ተከሳሽ

45ኛ ተከሳሽ ------------------

ስላላችሁ ነው

አዎ

አንተ ጠበቃ አመጣለሁ ያልከው ነው

ዛሬ አልቀረበም እንጂ እኮ አስመዝግቧል

አዎ ባለፈው አላስመዘገቡም

አስመዝግቧል 45 ብሎ

አላስመዘገቡም

አስመዝግቦ ነበር እዚሁ

አላስመዘገቡም እኛ እናስታውሳለን እዚህ ተመዝግቧል አቶ ፀጋዬ ፈቲህ ያስመዘገቡት 4ኛን፣ 33ኛ እና 36ኛ ተከሳሾችን ብቻ ነው ዞሮ ዞሮ ጠበቃ ይወክሉሃል አደለም

ወክዬዋለሁ እሱን

ወክለከዋል

አዎ

በቃ አሁን ጠበቃ አልቀረቡም መቅረብ ነበረባቸው በተመሳሳይ የሚታይ ይሆናል የአንተን ልዩነት አያመጣም

እሺ

በቃል ክርክሩ ስለተሰማ የዋስትናው አዎ እኛ ግን መዝግበናል አላስመዘገቡም 45ኛን በተመለከተ በጽ/ቤት ተከላካይ ጠበቃውን ጠይቀናል ምክንያቱም ይሄ ተከሳሽ መጀመሪያ ላይ ጠበቃ አመጣለሁ ያለ መሆኑን ስለምናስታውስ ነው ጠበቃው ግን ይሄን አላስመዘገቡም ጥፋቱ የጠበቃው ሊሆን ይችላል እሱን ወደማጣራት አንሄድም ዞሮ ዞሮ ግን የዋስትና ክርክር ግን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1104

ለወከሏቸው ጠበቆች ለተከሳሾች በቃል አሰምተዋል ይሄን ሰው እወከላለሁ ካሰ የሚወክሉት ከሆነ ልዩነት አያመጣም የወንጀል ጉዳይ ስለሆነ ያው ይመዘገባል ሌላ እስቲ ይኼኛው ማን ነው ማን ነው ስምህ ሁሴን እስቲ ስጠው ማን ነው ስምህ

ዙቤድ ሁሴን

ተቀበለው አቶ አቡ እሺ ምንድን ነው የምትፈልገው

ተመሳሳይ ቅድም እዚህ ጋ ከቀረበው ጋር ከአሁን ቀደም በሌላ በከፍተኛ ፍ/ቤት እንትን ብዬ ወጥቻለሁ ነው የሚለው

እሱ በብይን ጊዜ የሚታይ ነው በጽሁፍም አድርገከዋል አይተነዋል ስለዚህ እዚሁ ይመረመራል አትድገሙ እንደዚህ አይነት ነገር አትድገሙ ቁጭ በል ሌላ በዚሁ ይበቃናል ማን ነው እሺ እርሶ ስሞት ማን ነው

ሚካኤል አብዱላሂ

እሺ ምንድን ነው የሚፈልጉት

እኔ 90 አመቴ ነው እጄ አይሰራም ያመኛል ስለዚህ አሁን እኔ በ90 አመቴ በማላውቀው ነገር ነው እዚህ ውስጥ ያው በ90 አመቴ

እሱ ወደፊት በማስረጃ ይጣራል አሁን ግን ተጠርጥረው ቀርበዋል ፍ/ቤቱ ደግሞ ህግ በሚያዘው መሰረት ይመለከታል የእርሶን ጉዳይ በላቸው አበቃችሁ በላቸው ሁሉንም ማረሚያ ቤት በዚሁ ሌላ ነገር ዐ/ህግ የምታሳስቡት ሌላ አለ

ምንም የለንም

ከሌለ በእናንተም በኩል የለም ከሌለ በዚሁ ለግንቦት 18 ጠዋት 2:00 ሰዓት ላይ አጀንዳ በመያዝ ችሎቱ ስራውን አብቅቶ ተነስቷል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ማ/ተ

1105

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 18/9/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን

- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ

73 ተከሳሾች መካከል ያለውን ክርክር ፍ/ቤቱ ማየት ይቀጥላል፡፡ እሺ መዝገቡ የተቀጠረው በቀረቡ መቃወሚያዎች ላይ የዋስትና ጥያቄ ላይ ብይን ለመስጠት ነው በሌላ በኩል ደግሞ በመዝገቡ ምርመራ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ክስ በንባብ አለመሰማቱ በመረጋገጡ በቅድሚያ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ክሱ ችሎቱ ያሰማል ዐ/ህግ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ያቀረባችሁትን የክስ ማመልከቻ ስጧቸው ጀና መሀመድ፣ ዘሀራ አብዶሽ፣

ባለፈው በሰጠነው 9ኛ ክስ ውስጥ 22ኛው ተከሳሽ አለች በ28ኛው ክስ ውስጥ 18ኛ

የክስ ማመልከቻ ስጡ ነው የተባላችሁት ከሌላችሁ የለንም በሉ ፍ/ቤቱ እሱን ይመዘግባል

እሺ

የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠቀባ ለ22ኛም ለ48ኛም ተከሳሾች ተመድበዋል 48ኛ ተከሳሽ ማስረጃ ቀርቧል በወሊድ ላይ መሆኗን የሚገልጽ ነው በ18/9/2001 ዓ/ም የተፃፈ ነው ከቀበሌ 01 ከሐረር ከተማ አስተዳደር 9ኛ ክስ ብቻ ነው የሚመለከተው

አዎ

ለ22ኛ ተከሳሽ ክሱን እንደሚከተለው ይሰማል ክሱ በ9ኛ፣ 15ኛ፣ በ22ኛ፣ በ25ኛ፣ በ29ኛ፣ 30ኛ፣ 33ኛ፣ 34ኛ፣ 37ኛ፣ 54ኛ ተከሳሾች ላይ ተጽፎ የቀረበ ነው ዝርዝሩ በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና 257/ሐን በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሾች በዋና

1106

ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገር እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት በ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ በሆነው ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤታቸው ድረስ በማምጣትና በመደበቅ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲሁም ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀሳቸው የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባር ወንጀል በመፈጸም ተከሰዋል የሚል ነው ሌላ ክስ የለባትም አደለ ዐ/ህግ

አዎ

አስተርጓሚ አለም ኦሮምኛ የሚያስተረጉም ሰው የለም እንዴ እስቲ ጥሩ አስተርጓሚ ኦሮምኛ ይችላሉ እስቲ ያስተርጉሙ የምንነግሮትን ለሷ አንቺ የተከሰሽው በወንጀል ህግ ውስጥ በቁጥር 257ሐ ስር የተመለከተው ተላልፈሻል ተብሎ ነው አደረግሽ የተባለው ነገር ደግሞ በዝርዝር ከ1999 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ዞን ሐረርጌ አወዳይ ከተማ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ በሆነው ኦነግ ተብሎ በሚጠራ አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤትሽ ድረስ በመምጣት በመደበቅ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ቁሳቁሶች በማቅረብ ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀስ በህገ መንግስቱና በመንግስት ላይ የመገፋፋትና የማሰናዳት ወንጀል ተከሰሻል ተብሎ ነው አዳመጥሽ ወይ

እሺ

በአስተርጓሚ እየተረዳች ክሱን እንድትረዳው በችሎት ተደርጓል መስማቷንም ለችሎቱ አረጋግጣለች በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ ለሌሎች ተከሳሾች ፍ/ቤቱ ያቆማቸው ተከላካይ ጠበቃ ስለተመደቡ ተከላካይ ጠበቃ የምታሳስቡት ነገር ካለ

የክስ መቃወሚያውን በሚመለከት ባለፈው ግንቦት 6/2001 ባቀረብነው መሰረት በተራ ቁጥር 3 መሰረት መቃወሚያው ለነዛ የተመዘገበው ለሷም እንዲመዘገብላት የዋስትና ጉዳይ አስቀድሞ የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ እናልፋለን

እሺ ተቀመጪ በሷት ማረሚያ ቤት 70 ተከሳሾች ቀርበዋል

አዎ

ማረሚያ ቤት በዚህ መዝገብ ከዋስ ውጪ በስር የሚገኙት 70 ተከሳሾች መቅረባቸውን ለችሎቱ አረጋግጦ ተመዝግቧል በሌላ በኩል 48ኛ ተከሳሽ በወሊድ ምክንያት አለመቅረቧ ተመዝግቧል ዐ/ህግ ፍ/ቤቱ በቅድሚያ በ11/9/2001 ዓ/ም ለፍ/ቤቱ በፃፋችሁት መልስ ላይ ተራ ቁጥር 1 ላይ 31ኛ ተከሳሽ በተመለከተ በድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ያለው የአየር ሁኔታ ለህይወቷ አስጊ በመሆኑ የተከሰሰችበትን የህግ አንቀጽ ዋስትና ስለማይከለክል በመጥቀስ መቃወሚያ ማቅረቧን ከመዘገባችሁ በኋላ በዚሁ ላይ በፃፋችሁት አስተያየት ተከሳሽ የተከሰሰችበት የህግ አንቀጽ የዋስ መብት የማይከለክል መሆኑን ካስፈራችሁ በኋላ ሆኖም የ7 ወር ነፍሰ ጡር በመሆኗ ምክንያት ብቻ ግንቦት 6/2001 በዋለው ችሎት የዋስ መብት መከበሩን በማረጋገጥ ጽፋችኋል በዚህ እለት ለችሎቱ ባቀረባችሁት ክርክር እና በፍ/ቤቱ ማህደር የተመዘገበው እንደሚያሳየው 31ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ህመም ብቻ ሳይሆን የዋስትና ጥያቄውን እንደማትቃወሙ በግልጽ ለችሎቱ አስመዝግባችኋል በጽሁፍ ተመልሶ የመጣው ግን ለችሎት ያስመዘገባችሁት እና ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠበትን በግልጽ ትዕዛዝ የሰጠበትን የሚነካ ትርጉም ያለው ነገር በማህደሩ ውስጥ እንዲያያዝ አድርጋችኋል ይሄ የተደረገበት ምክንያት ምን እንደሆነ ፍ/ቤቱ ማወቅ ይፈልጋል ስለዚህ በዚህ ላይ የምትሰጡት ማብራሪያ ካለ ማብራሪያ ስጡ ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት

አንዴ ቢደገምልን የተከበረው ፍ/ቤት

በቃል የጻፋችሁት የዚህ ችሎት አስመዝግባችሁ የዋስትና መብት የተፈቀደበት እና ግንቦት 11/2001 ዓ/ም በዛው ችሎት በዚህ ፍ/ቤት ግራ ቀኛችሁ በቃል ያደረጋችሁት ክርክር እንደወረደ ሳይጨመር ሳይቀነስ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ክርክሩን በተፋጠነ ሁኔታ ለመምራት ያመነበትን ትዕዛዝ በሰጠበት ሁኔታ በጽሁፍም እንድታቀርቡ ታዞ ግራ ቀኛችሁ በጽሁፍ አቅርባችኋል በጽሁፍ በዐ/ህግ በኩል የቀረበው ግንቦት 11/2001 ዓ/ም የተጻፈው በተለይ ስለ 31ኛ ተከሳሽ የዋስትና ጉዳይ በተነሳው ላይ በችሎት ያስመዘገባችሁት እና በጽሁፍ የጻፋችሁት የጎላ ልዩነት ይታይበታል በጽሁፍ የጻፋችሁት ላይ በነፍሰ ጡር በመሆኗ ምክንያት የተከሰሰችበት ህግ የዋስ መብት የማይከለክል ሳይሆን ነፍሰ ጡር በመሆኗ ባለባት የጤና ችግር ምክንያት ችሎቱ ግንቦት 6/2001 ዓ/ም በአስቻለበት ጊዜ በዋስ መብቷን ስላከበረላት አሁን የተነሳው መቃወሚያ ላይ በጽሁፍ መልስ መስጠቱ አስፈላጊ አይደለም በሚል በጽሁፍ

1108

አስፍራችሁ ለፍ/ቤቱ ማህደር ውስጥ እንዲያያዝ አድርጋችኋል ሆኖም በዛን እለት በዋለው ችሎት 31ኛ ተከሳሽ እንደዚሁም ደግሞ በተመሳሳይ 22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ በተነሱት ጥያቄዎች 22ኛ እና 48ኛን በተመለከተ ቀድሞ በፖሊስ በዋስ መቆየታቸውን አሁንም ደግሞ በችሎት ሲታዩ ጤናቸው የታወከ መሆኑን በቀረበው የዋስትና ጥያቄ በግልጽ የማትቃወሙ መሆኑን አስመዝግባችኋል 31ኛ ተከሳሽንም በተመሳሳይ የ7ወር ነፍሰ ጡር ነች በሚል በተከላካይ ጠበቃ በተነሳው አቤቱታ በዋስትና ጥያቄው ላይ ተቃውሞ እንደሌላችሁ በግልጽ አስመዝግባችኋል

እኛም አስመዝግበናል

በጽሁፍ በተጻፈው ላይ ግን ይሄ አይነት ልዩነት ለምን ተደረገ ነው ይሄ ፍ/ቤት የሚፈልገው እያንዳንዱ በመዝገብ ውስጥ የሚያያዝ ማህደር ትርጉምና ከሚሰጥ የዳኝነት ስራ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት በመሸሽ የሚሰጡ የክርክር እና የሚመዘገቡ ክርክሮች መኖር የለባቸውም ይህ ታስቦ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ይሄ ማብራሪያ ይፈልጋል ከእናንተ ነው ይህ ማብራሪያ መቅረብ ያለበት ስለዚህ የምትሰጡትን ማብራሪያ ፍ/ቤቱ ይፈልጋል በአጭሩ

የተከበረው ፍ/ቤት ኢንቴንሽናችንን ያውቃል በመሸሽም ያደረግንበት ምናልባትም የታይፕ ስህተት ሊሆን ይችላል እኛ ኢንቴንሽናችን መጀመሪያውኑ እዚህ እንደሰጠነው ሶስቱም ተከሳሾች ከፍተኛ የጤና ችግር ነበረባቸው እርጉዞች ነበሩ እንደውም አሁን የተወለደ ልጅ ይዘው ነው የቀረቡት ያንንም በማየት ነው የዋስትናውንም አንቃወምም ያልነው በጽሁፍም በዛ ------------ ይሆናል የተጻፈው ምናልባት በስራ ጫና ኢንቴንሽኑ ሊቀያየር ስለሚችል እንጂ ------------------ ----- በዛ አንቃወምም

እያስመዘገባችሁ

መጀመሪያውኑም እዚህ የተናገርነው ሶስቱም ተከሳሾች በከፍተኛ ሁኔታ የጤና እንትን ነበረባቸው ምንም እንኳን ይህ ባይኖር የዋስትናውንም ጥያቄ የምንቃወም ቢሆንም በነበረባቸው በግልጽ ችሎቱም በሚያየው ሁኔታ እዚህ ሲባል የዋስትና መብታቸው ላይ ተቃውሞ እንደሌለን ሶስቱን በተመለከተ ብቻ ነው ያልነው ምናልባት ጽሁፉም በዛኑ አይነት አንደርስታንዲንግ ነው የተጻፈው እና በዛን አይነት ኢንቴንሽን ቢያይልን ፍ/ቤቱ

እዚህ ጽሁፍ ላይ

1109

የሥራ ጫናዎች እየተደራረቡብን መጥቷል ክቡር ፍ/ቤት እንደውም አሁንም በሚቀጥለውም ጠቅላላችን ልንሄድ ስለሆነ በጣም ሩጫ ላይ ነን

ዐ/ህግ ተከሳሿ የተከሰሰችበት የህግ አንቀጽ የዋስ መብት የማይከለክል ስለሆነ ብላችሁ ስጻችኂል

እንደዛ ይሄ እንግዲህ በታይፕ ስህተት የገባ ይመስለኛል የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ያስመዘገብነው እዚህ ላይ የዋስትናውን መብት ተቃውመን ግን እነዚህን በተመለከተ ኤክስብሽናሊ ባለባቸው የጤና ችግር የተከበረው ችሎት በሚያየው ሁኔታ ነው ያልነው

ስለዚህ በጽሁፍ የጻፋችሁት ነገር በዚህ በቃል ካስመዘገባችሁት ውጪ ነው ማለት ነው

ነው አዎ

ስህተት ነው የተፈጸመው እያላችሁ ነው

አዎ

ሌላ ዐ/ህግ በተጻፉት ክስ ዙሪያ በዝርዝሩ ላይ እነዚህ ወንጀሎች ከህገ መንግስታዊ ስርዓት ጋር ወይም ህገ መንግስቱን ------------ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብሎ በወንጀል ህግ ውስጥ የተመለከተውን በዚህ መልክ የተጻፈውን ወይም እነዚህ ወንጀሎች የሚሸፈኑበት የወንጀሉን ክፍል በመጽሀፍ ውስጥ ያለውን በማመልከት ክስ መጻፋችሁ ዝርዝሩ ላይ መረዳት ይቻላል ሆኖም ግን የጠቀሳችሁት ህግ ላይ ግን በዝርዝር የተጻፉትን የሚጠቁም ወይም የሚለይ የህግ ድንጋጌ አላመለከታችሁም ከመገፋፋት በዋና አድርገዋል የተባለው ወንጀል የሚያመለክት የህግ አንቀጽ አለ አስቀምጣችኂል እነዚህ የተፈጸሙት ግን የተባለው በዝርዝሩ ላይ ያመለከታችሁትን ወንጀል አንቀጽ የሚያመለክት ነገር ግን የለም ስለዚህ ይሄ ለምን ሆነ የሚለውን ነገርም ማብራሪያ ብትሰጡበት ችሎቱ ይሰማል

የተከበረው ፍ/ቤት ወደፊት ምናልባት ምስክሮቻችንን አቅርበን በምናሰማበት ጊዜ ግልጽ ይወጣል ብለን ነው እርግጥ እነዚህ ከ248 338 የሚቀጥሉትን ያመለክታሉ በሚል ነው እኛ ያላስገባናቸው ነገር ግን ምስክር ሰሚዎች ውስጥ በሚሰማበት ጊዜ እነኛን ድርጊቶች ቁልጭ አድርገው ያወጣሉ በሚል ነው እና ወደፊት በሚነሳም ተቃውሞ ክሳችንን እያየን ፍ/ቤቱ አድርጉ በሚለን አካሄድ እያሻሻልን እንሄዳለን በሚል እሳቤ ይዘን ነው የተነሳነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1110

በሌላ በኩል ከተጠቀሱት ፍ/ቤቱ ለማጣራት ካነሳቸው እና በመጨረሻ ላይ ትዕዛዝ ከሚሰጥባቸው ፍሬ ነገሮች ባሻገር መዝገቡ በዋናነት የተቀጠረው የተነሱ መቃወሚያዎች እንዲሁም የዋስትና ጥያቄ ለያይቶ ተገቢ ነው የሚለውን ብይን በመዝገቡ ላይ ማስፈር ነው በዚሁ ፍ/ቤቱ መዝገቡን አይቶ የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል፡፡

ማለት የተከበረው ፍ/ቤት

አስተርጓሚው የታል

የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ለቀረበው መቃወሚያዎች ምላሽ አምጥተናል

ቁጭ ትላለህ በደንብ አትችልም ሌላ ሰው ፈልጉ እሺ እናመሰግናለን ተመለስ ሌላ ሰው ባለፈው አልታዘዝም ግን የጽሁፍ ስለሆነ እስቲ ተቀበሏቸው ያስተረጉማሉ

አዎ

እሺ ማን ነው ስሞት

አብደላ አሊዬ

በአቶ አብደላ አሊዬ አስተርጓሚነት ፍ/ቤቱ የሰራውን ብይን በንባብ ያሰማል ያስተረጉማሉ ብይን ተሰጥቷል ከሳሽ የፌደራል ዐ/ህግ

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ አቶ ፌይሰል አብዲ ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ 73 ተከሳሾች መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል፡፡

ብይን

1ኛ. በ39ኛ ተከሳሽ ክሱ ሳይጣራ በሀሰት የቀረበ ነው ብሚል የተነሳው መቃወሚያ በህጉ የተፈቀደ መቃወሚያ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

1111

2ኛ. 33ኛ ተከሳሽ ዐ/ህግ ክሱን በማንሳቱ በዚህ መዝገብ ከቀረበበት ክስ እንዲሰናበት ፍ/ቤቱ አዟል

3ኛ. 26ኛ ተከሳሽ ክስ አልቀረበብኝም በሚል የተነሳው ጥያቄ ዐ/ህግ ክሱን አቅርቦ በማሰማቱ ታልፏል

4ኛ. ዐ/ህግ በፃፋቸው ክሶች ወንጀሎቹ ተሰሩ ያለባቸውን ጊዜ በማመልከቱ ወርና ቀን አልተመለከተም በሚል ክሱ እንዲሰረዝ የቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

5ኛ. የዐ/ህግ ሶስተኛ ክስ የቃላት ግድፈት አለበት በሚል የተነሳው መቃወሚያ ግድፈቱ የተጻፈውን ክስ ለመረዳት የማያዳግት እና መሰረታዊ ስህተትም ባለመሆኑ በቀላሉ ሊስተካከል የሚችል በመሆኑ ክሱ እንዲሻሻል ከማዘዝ ዐ/ህግ የቁጥርና የቃላት ግድፈቱን በችሎት እንዲያስተካክል ፍ/ቤቱ አዟል።

6ኛ. 5ኛ ተከሳሽ ክስ በቀረበበት ወንጀል ተከሶ ለመቀጣቱ ማስረጃ ባለማቅረቡ በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በእስር ላይ ነበርኩ የሚለውም ክርክርም ቢሆን ወደፊት በማስረጃ የሚጣራ እንጂ ከወዲሁ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም

7ኛ. ተከሳሾች ኮኮብ መሀመድ እና ጫላ ሙክታር በሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዋስ መለቀቃቸውን በመግለጽ ያነሱት ክርክር ይህ ፍ/ቤት በቀረበለት ክስ በህግ ባገኘው ስልጣን የሚሰጠውን የዳኝነት ስራ ቀሪ ሊያደርግ ስለማይችል ተቀባይነት የለውም በተጨማሪም በህጉ የሚሸፈን መቃወሚያ አይደለም

8ኛ. ክሱ ግልጽነት ይጎድለዋል ከህጉ አነጋገር ጋር አይጣጣምም የመከላከል መብት ያጣብባል ተብሎ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ ፍ/ቤቱ ክሶቹን በወንጀለኛ ስነ-ስርዓት ቁጥር 111 እና 112 ላይ የተመለከተውን ክስ ማመልከቻ መሟላት ያለበትን መያዙን በመረዳቱ በተመሳሳይ አልተቀበለውም

9ኛ. ክሶቹ ተነጥለው ሊታዩ ይገባል በሚል የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ተከሳሾች በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ እና የተለያዩ ድርጊቶች በመፈጸም ወንጀል ሰርተዋል በሚል ተጠርጥረው የተከሰሱ በመሆናቸው ክርክሩን በፍጥነትና በሚመች ሁኔታ ለመስማት ክሶቹ

1112

በአንድነት በቀረበበት ሁኔታ እንዲታዩ የተሻለ ሆኖ ፍ/ቤቱ በማግኘቱ በዚህ ረገድ የተነሳውን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

10ኛ. ዋስትናን በተመለከተ

10.1. ተከሳሾች ወንጀሉን ተፈጸ በተባለበት አካባቢዎች ቋሚ ነዋሪ መሆናቸው እና ፍ/ቤትም ቀርበው ይሄንኑ በአድራሻነት በማስመዝገባቸው

10.2. ክሶቹን ለማስረዳት ማስረጃዎቹን ተከሳሾች ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚቀርቡ በመሆናቸው

10.3. ክሱ በመንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ ወንጀል ተፈጽሟል በሚል እንደመቅረቡ የክሱ ስፋትና ክብደት በክሱ አሰማምና በተከሳሾች አቀራረብ ላይ በግምት የሚያዝ ምክንያት ሆኖ በመገኘቱ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከሳሾች በዋስ ቢቆዩ ዋስትና ግዴታቸውን በማክበርና እንዲሁም በቀላሉ እየቀረቡ ይከራከራሉ ተብሎ ባለመታመኑ እንዲሁም ምስክሮቹን ሊያባብሉ እና ማስረጃም ጥፋት ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ በመታመኑ ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበለውም በአጭሩ ትነግራቸዋለህ፡፡

በአብዛኛው ያነሳችሁት መቃወሚያ ስጡት እስቲ እንትኑን በአብዛኛው የተነሱ መቃወሚያዎች ከክሱ አቀራረብ እና አጻጻፍ እንዲሁም አንዳንዶቻችሁ ክሱ ወርና ጊዜ አልተጻፈበትም ክሱ በሀሰት የተጻፈ ነው እኛን ለማጉላላት የተደረገ ነው በማለት የተነሱት በአብዛኛው ለክስ መቃወሚያ የሚበቁ አደሉም ከማስረጃ መስማት ጋር በአብዛኛው የሚያያዙ ስለሆነ ወደፊት የእናንተ ክርክር ሲሰማ የሚታወቅና እርግጠኛ መሆን የሚቻል ከወዲሁ ግን ክሱን ሊያስቆም አይችልም በሌላ በኩል በክስ አጻጻፍ ላይ የቁጥር የቃላት ስህተትን በተመለከተ ጥያቄዎች በተመለከተ ክሱን ለማሻሻል መሰረታዊ ባለመሆናቸው እንዲሁም በዚህ ፍ/ቤት የተሰማውን ክስ ለመረዳት እንቅፋት ሆነዋል ተብሎ መውሰድ ስለማይቻል በዚህ ዙሪያ የተነሳውም እንደዚሁ በተመሳሳይ ተቀባይነት አላገኘም በሌላ በኩል የተወሰናችሁት በሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የዋስ መብት ተጠብቆልናል በማለት ያነሳችሁት አለ እናንተ ተጠርጥራችሁ የተከሰሳችሁበት ጉዳይ በዚህ ፍ/ቤት ቀርቧል ይሄ ፍ/ቤትም ደግሞ በሰፊው የዳኝነት ስራ ይሰራል ስለዚህ በዞን ፍ/ቤቱ በዋስ ተለቀቅን የሚለው ክርክር የዚህን ፍ/ቤት ስራ አያስቆምም ህጋዊ መቃወሚያም አይሆንም ሌላ 5ኛ ተከሳሽ የተከሰሰበት ጉዳይ ተፈርዶብኝ ተቀጥቻለሁ የሚል ክርክር ለማንሳት በጽሁፉ ተሞክሯል ሆኖም ግን ማስረጃ አልተያዘበትም ስለዚህ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

1113

በማስረጃ ስለሚሰራ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ እስር ላይ ነበርኩ የሚለው ወደፊት በማስረጃ የሚጣራ ነው በሌላ በኩል ጉዳዮቹ እየተነጣጠሉ ይታይ የሚል የተነሳ ክርክር አለ እናንተ ሁላችሁም ዐ/ህግ የከሰሳችሁ በመንግስት ላይ የሚሰራ ወንጀል አድርጋችኋል ተብሎ ነው እያንዳንዳችሁ የተጠየቃችሁበት ድርጊት የክስ ማመልከቻው እንደሚያሳየው ይለያያል ወንጀሉ ግን እንደተባለው በመንግስት ላይ የተሰራ ነው ስለተባለ በዚሁ መዝገብ በአንድነት ቢታይ ክርክሩን ያፋጥነዋል አመቺም ነው ብሎ ይህ ፍ/ቤት ያምናል በዚህ ምክንያት በአንድነት ነው ከዚህ በኋላ ክርክሩ የሚቀጥለው ለሁላችሁም በጋራ በተደጋጋሚ የቀረበው በዚህ መዝገብ ላይ የዋስትና ጥያቄ ነው በዚህ ላይ ሰፊ ክርክር በግራ ቀኛችሁ በኩል ቀርቧል ይሄ ፍ/ቤት እንዳመነው ግን እናንተ ድርጊቱን የተጠረጠራችሁበትን ድርጊት ፈጸማችሁ የተባለው በሌላ አካባቢ ነው በዛ አካባቢ ደግሞ ቋሚ ነዋሪ መሆናችሁን ለፍ/ቤቱም አስመዝግባችኋል በዚህ ችሎት ይቀርባል የተባለው ማስረጃም ከዚህ አካባቢ ይመጣል የተባለ ነው የቀረበው ክስም ሰፊ ነው ወንጀሉም በመንግስት ላይ የተሰራ ስለተባለ ክብደት አለው ይኸው ግን በክስ አሰማም እና በእናንተ አቀራረብ ላይ ግምት የተያዘበት ሌላ ምክንየት ሆኖ ተገኝቷል ይኸውም ምክንያት እናንተ እንዴት ትቀርባላችሁ ወደፊት በሚለው ላይ ግምት እንዲያዝ አድርጎታል በእናንተ መቅረብ ላይ ግምት ውስጥ እንዲገባ ማለት በሌላ አነጋገር አሁን በተባሉት ምክንያቶች እናንተ በዋስ ብትቆዩም አሁን እየቀረባችሁ በምትከራከሩበት መንገድ አክብራችሁ ትቀርባላችሁ ተብሎ ለመገመት ፍ/ቤቱ አልቻለም በቀላሉ ትቀርባላችሁ ብሎ እንደዚሁም አልተገመተም ማስረጃው ደግሞ እናንተ ከምትኖሩበት አካባቢ ይመጣል ስለተባለ ለማስረጃው ካላችሁ ቅርበት በተለይ ምስክሮች ስለሆኑ ወደውጪ ብትወጡ ላይመሰክሩ ይችላሉ ስለሆነም በእነዚህ ምክንያቶች የዋስትና ጥያቄውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ቀጣይ የሚሆነው ፍ/ቤቱ በሚይዘው የማስረጃ አሰማም ክርክሩ የሚሰማበትን ቀጠሮ ማሳጠር ብቻ ነው፡፡

ተከላካይ ጠበቃ የምትሉት ነገር አለ እምነት ክህደት ቃል መስጠት ይችላሉ ዐ/ህግ የእምነት ክህደት ቃላቸውን የቀረቡትን ተከሳሾች ይጠይቃል ከዚህ በኋላ ማስረጃ የሚሰማበትን አጀንዳ ይይዛል፡፡

አብዱረህማን ባሌ አስተርጓሚ ና ወደዚህ አብዱረህማን አንተ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በቀረበብህ ክስ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ነው የምለው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1114

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሸሪፍ አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በልና ጠይቀው

አልፈጸምኩም

ሁለተኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አህመድ ኑር አርጌ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አልፈጸምኩም

አመዲን ኢብራሂም 4ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አላምንም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል 4ኛ ተከሳሽ

ከማል አሊዩ አህመድ 5ኛ ተከሳሽ ጠይቀው

እስር ቤት ነበርኩኝ እና ይሄንን ጉዳይ አልፈጸምኩም

ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

መሀመድ ኢብራሂም አደም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

6ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሲራጅ አህመድ ሙሳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

7ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ፋጤ አሚን ሳዲቅ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1115

8ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏለች

ጀማል ሃምዛ ቂልቱ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ጣሃ አህመድ አብዱሮ

ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ዙቤድ ሁሴን መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አብዱረህማን ሁሴን ጅብሪል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ረምላ ሸሪፍ ኡመር ጥፋተኛ ነሽ አይሰለሽም

ጥፋተኛ አይደለሁም አላምንም

13ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

ኢብራሂም ሁሴን ጉራቾ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ሰርቼም አላውቅም አላጠፋሁም

14ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

15ኛ ተከሳሽ ኪሚያ አሚን ዩሱፍ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብላ አስመዝግባለች

ዘይነባ መታ መሀመድ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

ጥፋተኛ አይደለሁም አልፈጸምኩም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች 16ኛ ተከሳሽ

አብዲ ሹኩር ኡመር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ሸሪፍ ኡመር አሴም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ምንም ጥፋት የለብኝም አላምንም

አብዲ ኡስማን አደም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ተመዝግቦለታል ቃሉ

መሀመድ አሊዩ ሰግዳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትችላለህ አሁን ያልኩትን ሰምተሃል ገብቶሃል ጥፋተኛ ነህ አይደለም ሲባል እሺ 21ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ጀና መሀመድ ሃዳስ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

ፈጽሜ አላውቅም

እሺ ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

አብዱልሃሚድ መሀመድ አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትችላለህ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሼክ መሀመድ ኡስማኤል ኪኖ

ጥፋተኛ አይደለሁም እኔ የባህል ህክምና ባለሞያ ነኝ

እሺ ጥሩ ይበቃል ጥፋተኛ አይደለም በሚል ቃሉ ተመዝግቦለታል

ሻም ኢብራሂም አብደላ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ፊጽሜ አላውቅም

እሺ 25ኛ ተከሳሽም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

26ኛ አብዲ አህመድ ኑር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትችላለህ በደንብ ትሰማለህ

አዎ

እሺ 26ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ኢብራሂም መሀመድ አብዶ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጥፋተኛ ነህ አደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ እሺ ተቀመጥ

አብዲ አሊ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አጥፍቼ አላውቅም

ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግቧል 28ኛ ተከሳሽ

ጀማል ከድር ሳኒ አማርኛ ትሰማለህ ጥፋተኛ ነህ

አደለሁም

አደለህም 29ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ራህማ መሀመድ አብዱረህማን ጥፋተኛ ነሽ ራህማ አማርኛ ትሰሚያለሽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች

ሰሚራ ሙሜ አብዱላሂ ሰሚራ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም ትሰሚያለሽ አማርኛ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች

ጫልቱ ኢብራሂም አብዱልቀድር ጥፋተኛ ነሽ ጫልቱ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች 32ኛ ተከሳሽ

አብዲ ሀጂ ሙሳ መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ተቀመጥ

ጀማል ከዲር አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትሰማለህ በደንብ ጠይቀው

አላጠፋሁም

እሺ 34ኛ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አዱኛ መሀመድ ጅብሮ ወይም ዱንኛ ጠይቃት ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

አላጠፋሁም

ዱርሲቱ አብደላ አህመድ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

አብዲ በሽር ኡስማኤል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ አይደል

እሺ ኮኮብ መሀመድ ዩሱፍ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ሚካኤል ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አህመድ ሼክ ዩሱፍ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ ተቀመጥ

ሳላይ አብደላ ሙመድ አማርኛ ትሰማለህ እስቲ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አላጠፋሁም

መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም አብዱላ አማርኛ ትሰማለህ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም እሺ አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቦለታል

አህመድ ኡስማኤል መተኩ አማርኛ ይሰማሉ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አጥፍቼ አላውቅም አላምንም

እሺ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

ሀጂ ጣሃ ሀሰን ጉሌድ ጥፋተኛ ነህ እስቲ በኦሮምኛ ጠይቀው

ጥፋተኛ አይደለሁም

በማለት ተመዝግቧል ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1119

ዩሱፍ ጫሎ አህመድ አማርኛ ትችላለህ

አዎ

ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አይደለሁም

እሺ ተቀመጥ

ሙክታር አብዱልጀሊል አህመድ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

አሊ አብደሌ ኡስማን ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

እሺ 48ኛ ተከሳሽ ዛሬ ስላልቀረበች የእምነት ክህደት ቃል አልተመዘገበም

መሀመድ ኡመሬ ሙመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

አማርኛ ትችላለህ በደንብ አሁን የተባለው ገብቶሃል እሺ ተቀመጥ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

ጃፈር ኡመር አብዱሌ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጠይቀው በኦሮምኛ

አላጠፋሁም አፈጸምኩም ድርጊቱን

አላጠፋሁም በሚል ተመዝግቧል

ዩሱፍ ዳኦድ ዩሱፍ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

አደለሁም ብሏል

1120

መሀመድ አንደባ አብዱላ ወይም ፋልመታ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

አድናን ጉሼ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

እዚሁ ነው የሰማሁት

አህመድ ኑር አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ሰኢድ አደም አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ከሊፍ መሀመድ ሼክ ሰኢድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ኢብራሂም አብዱላ ዋሪዬ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አላውቀውም ጥፋተኛ አይደለሁም

አብደላ መሀመድ ሰኢድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ወደ ዞን ተጠርተሃል ተብዬ ነው የመጣሁት እንጂ ጥፋቱን እዚህ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ሀሰን መሀመድ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚህ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

መሀመድ አብዶ አህመድ 70ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ እሺ ቁጭ በል

ኑሬ ኡስማን ጃሎ ወይም ቢቲ ጀሎ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1122

ጀማል አደም ኡስማን 52ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጀማል

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል 52ኛ ተከሳሽ

53ኛ ተከሳሽ በከር ቃዚም ካዬ በከር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው አማርኛ ትችላለህ በደንብ እሺ ተቀመጥ ጥፋተኛ አይደለሁም በሚል ተመዝግቧል

አህመድ ነጃሽ ሼክ አብዱልሃሚድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጀማል ሁሴን ሙሳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም ድርጊቱን አልፈጸምኩም

ከድር አደም ጠደቻ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ድርጊቱን ጥፋተኛ አይደለሁም

ሼክ ከድር ቱራ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም በሚል ተመዝግቧል

ኡመር መሀመድ ማሙድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ሸኪብ ቱኬ ሀሰን ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ምንም የማምነው የለም ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

መሀመድ አሊ ሁሴን ወይም መሀመድ ሶዳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1121

በቂም ነው የታሰርኩት ጉዳዩንም አላውቀውም ጥፋተኛም አይደለሁም

ጫላ ሙክታር ሙሜ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትሰማለህ በደንብ እሺ ቁጭ በል

አብዶሽ ሙሜ ጁሞ ወይም ሻሞ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

በሀሰን ነው የቀመጠብኝ ጥፋተኛ አይደለሁም

48ኛ ተከሳሽ ባለመቅረቧ 33ኛ ተከሳሽ ደግሞ በብይን ከክሱ በመሰናበቱ ከነዚህ ውጪ ያሉ ተከሳሾች በሙሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ተጠይቀው ጥፋተኞች አይደለንም ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል ዐ/ህግ

እንደ ክስ አቀራረባችን የሚያስረዱልን ማስረጃዎች እናቀርባለን ግን ለፍ/ቤቱ አጀንዳ አያያዝ እንዲያመችልን ከግንቦት 24 ለአንድ ወር በአጠቃላይ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እኔ እና አቶ ዝማም ብቻ ስንቀር ሁላችንም ወደ አዲስ አበባ ነው የመጀመሪያ ደረጃም የከፍተኛ ዐ/ህጎችም ይሄዳሉ ለቢፒአር ሲባል በአገር ሁሉ ደረጃ ነው የተደረገው ስለዚህ እኔ ብቻዬን ነኝ ይሄንን ግምት ውስጥ አስገብቶ በምናቀርበው የምስክሮች አቀራረብ ግምት ወስዶ ከአንድ ወር በኋላ እንዲያቀርብልኝ ብቻዬን ነኝ ጠቅላላውንም ችሎቶች የከሰዓቱንም የጠዋቱንም የምሸፍነው እኔ ብቻ ነኝ ማንም የለም ለዚህ ሁሉ ተከሳሽም ብቻዬን መቆም ያዳግተኛል እና ክቡር ፍ/ቤቱ እንዲያቅልኝ ከግንቦት 24 ጀምሮ ይሄዳሉ

ተከላካይ ጠበቃ የምትሉት አለ አስመዝግቡ

እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እነዚህ ሰዎች አንደኛ የዋስ መብት ተከልክለዋል

አንዴ ይቅርታ እስከዛ አስተርጓሚ ቁጭ በሉ እሺ ቀጥሉ

የዋስ መብት ተከልክለው በእስር ቤት ያሉ ናቸው ግማሾቹ አዛውንት ናቸው ግማሾቹ ሴቶች ናቸው ይሄንን ከግምት ውስጥ አስገብቶ የተከበረው ፍ/ቤት የምስክሩን መስማት ሁኔታ በአፋጣኝ ይይልን እና ዐ/ህጉ ከሌሎች ክሶች ላይ የተለየ ስለሆነ እንደምንም አጣርቶ ምስክሮቻቸውን አቅርቦ ማሰማት ስለሚችሉ ምስክሮቹ የሚሰሙበትን ጊዜ ቀጠሮ እሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን አጠር ባለ በ15 እና በ10 ቀን ውስጥ እየተቀጠርን ይሰማላቸው ነው እኔ የማመለክተው::

1/123

በሌላ በኩል ማረሚያ ቤት ይሄ ፍ/ቤት ፈተና እንዲፈተኑ የፈቀደላቸው ሁለት ተከሳሾች አሉ 22ኛ እና መሀመድ ኡመር መሀመድ፣ ፋጤ አሚን፣ መሀመድ ኡመር ሙመድ አንተ ነህ ስንተኛ ተከሳሽ ነህ 29ኛ ስምህ ሌላ ነው እንዴ 29ኛ መሀመድ ኡመሬ ሙመድ ማመልከቻህን የጻፍከው መሀመድ ኡመር ሙመድ ብለህ ነው ዐ/ህግ ማረሚያ ቤት ፈተና እንዲፈተኑ አልተደረገም አይደለ ለምንድን ነው ያልተደረገው

የፋጤስ

የሷ ደግሞ ጋራሙለታ ---

ፋጤ አማርኛ ትችያለሽ

ክፍያም እኔ እፈጽማለሁ ብዬ ጋራሙለታ እና ጉልላ ጉልላ የሚባል ቦታ ነው ጎሎኦዳ የሚባል ወረዳ ነው እዛ ክፍያም እኔ እከፍላለሁ ብዬ ጠይቄ ነበር

መቼ ነው ፈተናው

ማትሪክ ነበረ ዛሬ ተጀምሯል ትናንት ተጀምሯል ሁለት አጃቢ አቅም የለኝም ብዬ ብጠይቃቸውና አንድ አጃቢ ይበቃኛል ብዬ ብል ማረሚያ ቤቱ ስላልተመቻቸው ይሆናል አልተቀበሉኝም

ለምን አንተ እነሱ ሁለት ሲሉ አንተ አንድ አልክ

-------------------------- ለመክፈል አልችልም የልጆች አባት ነኝ

ቀጣዩ የማስረጃ የሚሰማበትን አጀንዳ መያዝ ነው ይሄን በተመለከተ በዐ/ህግ በኩል ስራ ስራተኞቹ በሙሉ ወደ አዲስ አበባ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ፍ/ቤቱ በተጠቀሰው በአንድ ወር እና ወይም ከዛም በላይ በሆነ ጊዜ ዐ/ህጎች ሊገኙ ስለማይችሉ አጀንዳው ከዚህ አንጻር ታይቶ ይያዝልን የሚል ጥያቄ ቀርቧል በሌላ በኩል በተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ በኩል ተከሳሾች ዋስትና መብታቸው ተነፍጎ በማረሚያ ቤት ያሉ በመሆናቸው ማስረጃ መስማቱ ሂደት በአጭር ቀጠሮ እየተሰማ እንዲቀጥል ለፍ/ቤቱ አሳስበዋል ፍ/ቤቱ እነዚህን የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጥር

1124

ት ዕ ዛ ዝ

ዐ/ህግ ተከሳሾች የዋስትና መብታቸው ዛሬ ተነፍጎ ከአሁን በኋላ ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን ሰምቶ ሌላ ተለዋጭ እስከልተሰጠ ድረስ በማረሚያ ቤት የሚቆዩ መሆናቸው እየታወቀ በሌላ በኩል የክሱ ባለቤትና የጉዳዩ ባለቤት መሆኑ እርግጥ በሆነበት ሁኔታ በቀጣይ ማስረጃ አሰማም ሂደት መስሪያ ቤቱ ይንቀሳቀሳል የለም በሚል የቀረበው ምክንያት ለዚህ ችሎት ተቀባይነት ያለው ሆኖም አልተገኘም አግባብነትም ያለው ሆኖ አልተገኘም ስለዚህ ዐ/ህግ ያቀረበውን ክስ የማስረዳት ግዴታ ሸክሙ በሱ ላይ መሆኑን ተረድቶ ፍ/ቤቱ በሚሰጠው አጀንዳ በዚህ ጉዳይ ላይ አሉኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ በድጋሚ ያዛል በዚህ መሰረት አጀንዳው የሚያዝ ነው የሚሆነው በሌላ በኩል ማረሚያ ቤት ባለፈው ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሁለት ተከሳሾችን በተመለከተ መሀመድ ኡመር ሙመድ እና ፋጤ አሚን በተመለከተ ይህ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል ትዕዛዙ አለመፈጸሙን በማረሚያ ቤት የተወከሉት አብራርተዋል ሆኖም ፍ/ቤቱ ይህ ትዕዛዝ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ያልተከበረበትን ምክንያት በተመለከተ ማረሚያ ቤቱ በግልጽ ማብራሪያ በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማዘዝ እንዳለበት ገልጾናል ይኸው እንዲፈጸም በጥብቅ ታዟል ቀጣይ ትዕዛዝ የሚቀጥል ነው የሚሆነው በሌላ በኩል በአስተርጓሚ በኩል ተከሳሾች ዛሬ የዋስትና መብታችሁ ተነፍጓል በዚህ ላይ ቅሬታ ካላችሁ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ አንድ መብት አላችሁ በማለት ለሁሉም ነገሯቸው ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው የሚሆነው የአጀንዳ ሁኔታ ነው ፍ/ቤቱ ከፍ ሲል እንደተመለከተው በትዕዛዝ ወቅት ይሄ መዝገብ ሰፊ ተከሳሾች ያሉበት ነው በሌላ በኩል ደግሞ የዋስ መብት መነፈጉ ከግምት መግባት አለበት ስለዚህ የሚቀጥለውን የክርክር አመራር ከዚሁ አንጻር ፍ/ቤቱ ለሌሎች መዛግብቶች በርካታ መዛግብቶች ያሉትን አጀንዳዎች በመሰረዝና በማጣበብ ይህን ጉዳይ መስማት እንዳለበት ያምናል ስለሆነም አጀንዳው በዚህ መልክ የሚያዝ ነው የሚሆነው ስለዚህ የፍ/ቤቱ የመጀመሪያ አጀንዳ በሌሎች መደበኛ ችሎቶች የተያዙትን አጀንዳ በመፋቅ ሰኔ 15 እና 16 በሁለቱም ቀን በተከታታይ በዚህ መዝገብ ላይ የሚቀርቡትን የዐ/ህግ ማስረጃዎች ከቀረቡ ችሎቱ ይሰማል በቀጣይ የሚያዙት አጀንዳዎችም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ በአጭር ቀጠሮዎች የሚያዙ መሆኑን ዐ/ህግ ከዚሁ እንዲያስተውሉ ፍ/ቤቱ ያሳስባል በዚህ ምክንያት በዚሁ ምንክያት ሰኔ 15 እና 16 የዐ/ህግ ------------------ መስማት ሂደት ፍ/ቤቱ ----------- ይሄንኑ ለተከሳሾቹ ነገሯቸው በአጭሩ የእናንተ ማስረጃ የሚሰማው ሰኔ 15 እና 16 በዐ/ህግ በኩል የቀረበውን የሰው ሃይል ያንሳል ቀጠሮ እንዲረዝም በሚል

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

መ/ተ
ፊርማ

1125

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 24/10/2003 ዓ.ም.

ዳኞች - እንደሻው አዳነ

- ሰይድ ጉደታ

- ሁሴን ይመር

ከሣሽ - የፌደራል ዐ/ሕግ አቶ ማሙሸት አበበ ቀርቧል

ተከሣሾች - 1ኛ/ አብዱረህማን ባሌ

2ኛ/ ሽሪፍ አሊ መሐመድ

3ኛ/ አህመድ ኑር ኡርጌ

4ኛ/ አመዲን ኢብራሂም

5ኛ/ ከማል አልዩ አህመድ

6ኛ/ መሐመድ ኢብራሂም አደም

7ኛ/ ሲራጅ አህመድ ሙሣ

8ኛ/ ፋጤ አሜ ሳዲቆ

9ኛ/ ጀማል ሃምዛ

10ኛ/ ጣሐ አህመድ

11ኛ/ ዙቤር ሁሴን

12ኛ/ አብዱረህማን ሁሴን

13ኛ/ ረበላ ሽሪፍ

14ኛ/ ኢብራሂም ሁሴን

15ኛ/ ኪሚያ አሚን

16ኛ/ ዘይነባ መሃን

17ኛ/ አብዱሽኩር ዑመር

18ኛ/ ኢብራሂም መሐመድ

1126

19ኛ/ ሽሪፍ ዑመር

20ኛ/ አብዱ ዑስማን አደም

21ኛ/ መሐመድ አልዩ

22ኛ/ ጀሃ መሐመድ

23ኛ/ አብዱልሃሚድ መሐመድ

24ኛ/ ሼክ መሐመድ ዑስማን

25ኛ/ ሻም ኢብራሂም አበደላ

26ኛ/ አብዲ አህመድ ኑር

27ኛ/ ኢብራሂም አህመድ

28ኛ/ አብዲ አሊ አህመድ

29ኛ/ ጀማል ከድር

30ኛ/ ረሃማ መሐመድ

31ኛ/ ጫልቱ ኢብራሂም

32ኛ/ ጀማል ከድር

33ኛ/ አዱኛ መሐመድ

34ኛ/ ዱርሲቱ አብደላ

35ኛ/ አብዲ በሽር

36ኛ/ ኮከብ መሐመድ

37ኛ/ ሚካኤል አብዱላሂ

38ኛ/ አህመድ ሼክ ዩሱፍ

39ኛ/ ሳሊ አብደላ

40ኛ/ መሐመድ ሐጂ ኢብራሂም

41ኛ/ አህመድ ዑስማኢል

42ኛ/ ሐጂ ጠሃ ሐሰን ቡሌ

43ኛ/ የሱፍ ጨሎ አህመድ

1127

44ኛ/ ሙክታር አብዱልመጂድ

45ኛ/ አብዱልጀዲድ አህመድ

46ኛ/ አልዪ አብደላ ዑስማን

47ኛ/ ዘሃራ አብዶሽ

48ኛ/ መሐመድ ዑመር

49ኛ/ ጃፋር ዑመር

50ኛ/ ዮሴፍ ዳውድ

51ኛ/ ጀማል አደም

52ኛ/ በክር ቃሲም

53ኛ/ አህመድ ነጃሽ

54ኛ/ ጀማል ሁሴን ሙሣ

55ኛ/ ከድር አደም ጠደቻ

56ኛ/ ሼክ ከድር ቱራ

57ኛ/ ዑመር መሐመድ መሐሙድ

58ኛ/ አብዱላሂ ሙሣ

59ኛ/ ሻኪብ ቱኬ

60ኛ/ መሐመድ አሊ

61ኛ/ መሐመድ አንጀዋ

62ኛ/ ሃድናን ጉሼ

63ኛ/ መሐመድ ኑር አህመድ

64ኛ/ ሰዒድ አደም አሊ

65ኛ/ ካሊድ መሐመድ ሰዒድ

66ኛ/ ኢብራሂም አብደላ ዋሪዩ

67ኛ/ አብደላ መሐመድ ሰዒድ

68ኛ/ ሐሰን መሐመድ

69ኛ/ መሐመድ አብዶሽ

70ኛ/ ኑሬ ዑስማን ጅሎ

71ኛ/ ጫላ ሙክታር

72ኛ/ አብዶሽ ሙሜ

መዝገቡ ተቀጥሮ የነበረው የዐ/ሕግ ምስክር የሆኑት ጣሂር ሐጂ መሐመድ እና መሐመድ ሐጂ ዳሊጃራ ለመስማት ታዞ ነው የድሬዳዋ ፖሊስ በቁጥር ወ554/2573/03 በቀን 23/10/03 በተፃፈ ደብዳቤ የዐ/ሕግ ምስክሮችን ያቀረበ መሆኑን ገልጿል 23ኛ 37ኛ 38ኛ 2ኛ 3ኛ 7ኛ 10ኛ 43ኛ 44ኛ 47ኛ 57ኛ 59ኛ 61ኛ 65ኛ 69ኛ 72ኛ ተከሣሾች ጠበቃ አቶ ኢብራሂም መሐመድ ቀርበዋል የሌሎች ተከሣሾች ጠበቃ የነበሩት አቶ መሣፍንት አሸናፊ አልቀረቡም የዐ/ሕግ ሃሳብ

- ---- ፍ/ቤቱ ነው ምስክሮቹን የጠራው 11ኛ እና 16ኛ በእኛ በኩል ፍ/ቤቱ በማጣሪያ ምስክርነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ለማጣራት መስማት አለባቸው ካመነ ሊሰማ ይችላል ዐ/ሕግ ግን ያው እኛ በእኛ በኩል ከዚህ በፊት የተሰጠ በ22/04/2003 የተሰጠ ትዕዛዝ አለ በዛ መሠረት እንዲሰራልን ነው የምንፈልገው
- የተከሣሾች ጠበቃ
- እሺ በእኛ በኩል የምናቀርበው ለክቡር ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በዐ/ሕግም እንደተገለፀው እነዚህ ተከሣሾች ማነው የዛሬዎቹ ምስክሮች የእድሜ ልክ እሥራት ቅጣት የተፈረደባቸው ስለሆነ ተጠርተው ከቀረቡ በኋላ ይሄው ተገልፆ ለፍ/ቤቱ ስለቀረበ ፍ/ቤቱ አልፏቸው ምስክሮቹን የእነሱ ቃል የሰጡትን ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር እንዲያያዝ መደረጉ ይታወሳል በእርግጥ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ማናቸውንም ምስክሮች ፍ/ቤት ሊጠራ እንደሚችል ግልፅ ነው ሕጉ ይፈቅዳል ነገር ግን ስለ ምስክሮቹ ብቃት ብቁ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነገር ላይ መቃወሚያ ማቅረብ እንደሚቻል አሁንም ሕጉ የሚገልፀው ነገር ነው እና በእኛ በኩል ምንድነው እነኚህ ዛሬ በፍ/ቤቱ በኩል ለማጣሪያነት የቀረቡት ምስክሮች መቅረባቸው ወይም መጠራታቸው አግባብ ነው ግን ስለምስክሮቹ ብቃት ግን የእኛ ምንድነው በእኛ በኩል ምስክሮቹ ይሄንን ምስክርነት ወይንም ለፍ/ቤቱ የሚጡትን የማጣሪያ እንትን ለማድረግ ብቁ አይደሉም የምንልበት ምክንያት ምንድነው አንድ ተጨማሪ ቅጣት ላይ ፍ/ቤቱ እነኚህ ተከሣሾች እድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው ሰዎች በተጨማሪ ቅጣት ከሕዝባዊ መብትም መሻር እንደሚሻሩ ሕጉ ይደነግጋል ይሄንን ምንድነው

1129

በ124 ንዑስ ቁጥር 2 ሥር እነኚህ የሞት ወይንም የፅኑ እሥራት ቅጣት ፍርድ ከሕዝባዊ መብት የመሻርን ጉዳይ በግድ ማስከተል አለበት ብሎ ነው ሕጉ ያስቀመጠው እና በተለይ ደግሞ የሞት ፍርድ ወይም የእድሜ ልክ እሥራት ቅጣት እዚህ መካከል ስለ ምህረት እና ስለመሰየም እንደተጠበቀ ሆኖ ከመብት የመሻሩ ቅጣት ለዘወትር ፀንቶ ይቆያል ነው የሚለው ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ምስክሮች ስለሆኑ ፍ/ቤቱ በእርግጥ ምስክሮችን ሕጋዊ ግዴታ የተጣለባቸው ቢሆን መመስከር ግዴታ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ከመመስከር አግዷቸዋል ስለዚህ ፍ/ቤቱ ይሄንን ሊቀበል አይገባም የሚል ነው ያለን ሃሳብ

- የተከበረው ፍ/ቤት 22/04/2003 በቀረበው
- ዐ/ሕግ የሰጡት ምስክሮቹ መሰማት ላይ የሰጡት ሃሳብ ምስክሮቹ የቀረቡት በፍ/ቤቱ የማጣሪያ ተጨማሪ ምስክር ሆነው ነው ያሉትን ድጋሚ እንዲያብራሩት ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ ያ ስላልሆነ
- እኛ በ22/04/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እነዚህ ምስክሮች ቀርበው ምስክሮቹ የእድሜ ልክ እሥራት የተፈረደባቸው ስለሆነ በወንጀል ሕጉ 124 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ከሕዝባዊ መብታቸው የተሻሩ ስለሆነና ይሄም ፀንቶ የሚቆይ ስለሆነ እራሳችን ነን ሊሰሙ አይገባም ስለዚህ ከመከሰሳቸው በፊት ግን የሰጡት የምስክርነት ቃል ስላለ እሱ ይያዝልን ብለን በዚህ በችሎት አሳስበን ችሎቱ ተቀብሎን ምስክሮቹ ወደ መጡበት ተመልሰዋል አሁን ይሄው ችሎት ነው የከዚህ በፊት የነበረውን ብይን ወይንም ትዕዛዝ ሽሮ ነው ሊሰሙ ይገባል ያለው ስለዚህ እኛ አሁንም ቢሆን አንፈልጋቸውም እነሱንም እንዲሰሙ አልጠራናቸውም ፍ/ቤቱ ነው የጠራው ፍ/ቤቱ ደግሞ ከተጠራ ችሎቱ ሊሰማቸው ይገባል የእኛ ሃሳብ
- ስለዚህ ምስክሮቹን አንፈልጋቸውም
- ከዚህ በፊት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲከናወን ነው የምንፈልገው በ22/04/2003 የተሰጠ ትዕዛዝ አለ በዛ መሠረት እኛ ከዚህ በፊት አቅርበን ይሄንኑ ሃሳብ አይሰሙም የሚል ነገር አቅርበናል ለፍ/ቤቱ ፍ/ቤቱም ትዕዛዝ ሰጥቶበታል ይሄኛው ችሎት ደግሞ አሁን ችሎቱ ይሰማሉ ካለ ከእኛ ፍላጎት ውጪ ነው ፍ/ቤቱ በራሱ የሚሰማቸው ማለት ነው
- ዐ/ሕግ ፍ/ቤቱ ባለፈው የተሰጠውን ትዕዛዝ የተመለከተው ተከሣሾቹ ምስክሮቹ የእድሜ ልክ ፍርደኛ በመሆናቸው ከመብታቸው ተሽረዋል ብሎ ፍ/ቤቱ የሄደበት

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1130

አግባብ ከመብት መሻር በምስክር ከሚደርሰው ግዴታ መመስከር ግዴታ ስለሆነ ግዴታን ቀሪ አያደርግም መመስከር ግዴታ ነው በወንጀልም የሚያስጠይቅ ተግባር ነው ስለዚህ ምስክሮቹ ቀርበው መሰማት አለባቸው በሚል ነው ምስክሮቹን ያዘዘው በዚህ ጊዜ ምስክሮቹ የቀረቡት የዐ/ሕግ ምስክሮች ሆነው ነው እንጂ የፍ/ቤቱ ተጨማሪ ምስክሮች ሆነው አይደለም ዐ/ሕግ እነዚህን ምስክሮች አልፈልጋቸውም በቀረበው ምስክር ይሰማልኝ ካለ ፍ/ቤቱ በዛው የሚቀጥል እንጂ ተጨማሪ ምስክር አድርጎ የቀጠላቸው አይደለም

❖ በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊትም ትዕዛዝ ተሰጥቶበት መዝገቡም ያደረው ለብይን ነው ማስረጃ አጠቃለናል ባቀረብናቸው የሰው ማስረጃ እና

❖ ዐ/ሕግ እዚህ ጋር እንድንግባባ ማለት ነው እነዚህ ምስክሮች በዋናነት የእናንተው ምስክሮች ናቸው በእናንተ ማስረጃ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ናቸው እነዚህ ምስክሮች ቀርበው ነበር የቀረቡት በእናንተው ጥያቄ እናንተ ማስረጃ ዝርዝር ውስጥ ስላሉ ነው ፍ/ቤቱ እናንተ ያቀረባችኋቸውን ማስረጃ ግን ሳይሰማ የቀረበት ምክንያት አግባብ አይደለም የሚል አቋም ላይ ስለደረስን ይሄንን የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለነውን አርመናል ብይን ስላልተሰጠበት ገና በመዝገቡ ላይ ስለዚህ እዚህ ላይ ምስክሮቹ ሊሰሙ አይገባም ስለተባለ በ27 የሰጡት ቃል መዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል አሁን ምስክሮቹን አንፈልጋቸውም ካላችሁ ፍ/ቤቱ ወደኋላ ተመልሶ በ27 የተሰጠውን ቃል የሚመለከት አይመስለኝም ለማለት ነው ውጤቱን ማወቅ አለባችሁ

❖ እኛ አሁን አቋማችን አንፈልጋቸውም አይደለም ከዚህ በፊት ከመብታቸው ተሽረዋል ሊሰሙ አይገባም የሰጡት የምስክርነት ቃል አለ በ30 ያ ይያያዝልን ከዚህ በፊትም ደግሞ ይሄው ችሎት ያንን ነገር ተቀብሎን ለብይን ያደረ መዝገብ ነው ነው እንትናችን ምስክርነት የተቆጠሩት ደግሞ እድሜ ልክ ሳይፈረድባቸው በፊት ነበረ እኛ መስክርነት የቆጠርናቸው ከመከሰሳቸው በፊት አሁን ምስክርነት እየተሰማ እያለ ግን ሰዎቹ ፍርደኛ ናቸው በዛ መሠረት ሊመሰክሩ አይገባም ብለን ነው በ22/4/2003 ዓ.ም. በዋለው ቀጠሮ ነው ለፍ/ቤቱ አሳስበን ብይን እንዲሰጠን

❖ ዐ/ሕግ አላጠቃለልክልንም ለዚህ ባቀረብናቸው ክስ እና ባቀረብናቸው ማስረጃዎች መሠረት ውሳኔ ይሰጠን እነዚህ ምስክሮች መሰማት ጨርሰናል አንፈልጋቸውም ብላችኋል

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1131

- አዎ ከዚህ በፊት ባቀምነው መሠረት ምስክር አብቅተናል ብለናል ምክንያታችንን ገልፀናል ያቀረብነው የሰነድ ማስረጃ በዛን ጊዜ የዕድሜ ልክ ፍርደኛ ከመሆናቸው በፊት ነው የእድሜ ልክ ፍርደኛ ከሆኑ በኋላ ሊመሰክሩ
- ዐ/ሕግ በዚህ ላይ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ስለቀረቡ ወደኋላ እየተመለስን አሁን በቀረበው ላይ ምስክሮቹ ከዚህ ቀደም ቀርበው የተመለሱ ስለሆነ በተሰሙት ማስረጃዎች ውሣኔ ይሰጠኝ ማለት ይቻላል
- አዎ ከዚህ በፊት የሰው ማስረጃም የሰነድ ማስረጃም አጠቃለን አቅርበናል ፍ/ቤቱ ይሄንኑ መርምሮ ብይን ይስጥ ብለን ባሳሰብነው መሠረት የተከበረው ፍ/ቤት ከዚህ በፊት ያሰማናቸው ምስክሮች አሉ የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች አሉ እነዛን አይቶ ብይን እንዲሰጥልን ነው የምናሳስበው
- እሺ ምስክሮች እንዲገቡ ይደረግ እሺ ምስክሮቹ መሐመድ ሐጂ ዳዲ እና ጣሂር ሐጂ ጀም ሐጂ መሐመድ እንዲመጡ ጣሂር ሐጂ መሐመድ መሐመድ ሐጂ ዳዲ ዛሬ እዚህ ችሎት የቀረባችሁት እነ አብዱረህማን ባሴ በተከሰሱበት ጉዳይ የዐ/ሕግ ምስክር ሆናችሁ ነበር ዐ/ሕግ ቀደም ሲል ያቀረባቸው ማስረጃዎች እና የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መሠረት ተደርጎ ውሣኔ ብይን እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ምስክር ሆናችሁ የቀረባችሁበት ጉዳይ ለመስማት አልተቻለም ስለዚህ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት እዚህ ድረስ ስለመጣችሁ እናመሰግናለን እና ጨርሳችኋል ። ዐ/ሕግ የቀረቡት ያቀረበውን ክስ እና ማስረጃ አገናዝቦ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ ተይዟል። ተርጉምላቸው ንገራቸው **ቀጠሮ ለሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. ---- ወደ ዕሁፍ ተመልሶ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ።**

- **ራ/መ**

1132

የመ/ቁጥር 04486

ነሐሴ 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡-እንዳሻው አዳነ

ሰይድ ጉደታ

ሁሴን ይመር

ከሳሽ፡- የፌዴራል ዐ/ህግ ማሙሸት አበበ - ቀርቧል

ተከሳሽ፡- 1. አብዱረህማን ባሌ ጃኀ - ቀርቧል

2. ሸሪፍ አሊ መሀመድ - ቀርቧል

3. አህመድ ኑር ኡርጌ - ቀርቧል

4. አህመዲን ኢብራሂም ሀሰን /ዳይና/ - ቀርቧል

5. ከማል አልይ አህመድ - ቀርቧል

6. መሀመድ ኢብራሂም አደም - ቀርቧል

7. ሰራጅ አህመድ ሙሣ - ቀርቧል

8. ፋጤ አሜ ሳድቆ ቀርባለች

9. ጀማል ሀምዛ ቂልጡ - ቀርቧል

10. ጠሃ አህመድ አብድሮ - ቀርቧል

11. ዙብሬ ሁሴን መሀመድ /ሌንጅሳ/ - ቀርቧል

12. አብዱራህማን ሁሴን ጅብሪል - ቀርቧል

13. ረብሳ ሸሪፍ ዑመር - ቀርባለች

14. ኢብራሂም ሁሴን ጉርቼ - ቀርቧል

15. ኪሚያ አሚን የሱፍ - ቀርባለች

16. ዘይነባ መታን አህመድ ቀርባለች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ ሪፐብሊክ ፌ.ጠ.ፍ.ቤት ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

1133

17. አብዲሹኩር ዑመር ኤሌም - ቀርቧል

18. ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል - ቀርቧል

19. ሸሪፍ ዑመር ኤልሞ - ቀርቧል

20. አብዲ ዑስማን አደም - ቀርቧል

21. መሀመድ አልይ ሰኢድ - ቀርቧል

22. ጀና መሀመድ አዳሰ - ቀርባለች

23. አብዱልሀሚድ መሀመድ አሊ - ቀርቧል

24. ሼክ መሀመድ ዑስማኤል ጊኖ - ቀርቧል

25. ሻማ ኢብራሂም አብደላ - ቀርቧል

26. አብዲ አህመድ ኑር ሐሶ /ቡራሌ/ - ቀርቧል

27. ኢብራሂም አህመድ አብዶ - ቀርቧል

28. አብዲ አሊ አህመድ - ቀርቧል

29. ጀማል ከድር ሣኒ - ቀርቧል

30. ረሀማ መሀመድ አብዲረሀማን - ቀርባለች

32. ጫልቱ ኢብራሂም አብዱልቃድር - ቀርባለች

34. ጀማል ከድር አህመድ - ቀርቧል

35. አዱኛ መሀመድ ጂብሮ - ቀርባለች

36. ዱርሲቱ አብደላ አህመድ - ቀርባለች

37. አብዲ በሽር ዑስማን - ቀርቧል

38. ኮኮብ መሀመድ ዮሴፍ - ቀርቧል

39. ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ - ቀርቧል

40. አህመድ ሼክ ዮሴፍ አህመድ - ቀርቧል

41. ሳሊዮ አብደላ ሙመድ - ቀርቧል

1134

42. መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም - ቀርቧል

43. አህመድ ዑስማን መቱከ - ቀርቧል

44. ሀጂ ጣሀ ሀሰን ቡሌ - ቀርቧል

45. የሴፍ ጨሎ አህመድ - ቀርቧል

46. ሙከታር አብዱልጃሊል አህመድ - ቀርቧል

47. አልይ አብደሌ ኡስማን - ቀርቧል

48. ዘሀራ አብዶሽ ኢብራሂም - ቀርባለች

49. መሀመድ ኡመሬ ሙመድ - ቀርቧል

50. ጃፋር ዑመር አብዱሌ - ቀርቧል

51 የሱፍ ዳውድ ዩሱፍ - ቀርቧል

52. ጀማል አደም ዑስማን - ቀርቧል

53. በከር ቃሲም ከዬ - ቀርቧል

54. አህመድ ነጃሽ ሼክ አብዱልሀሚድ - ቀርቧል

55. ጀማል ሁሴን ሙሣ - ቀርቧል

56. ከድር አደም ጠደቻ - ቀርቧል

57 ሼክ ከድር ቱራ ሊዬ - ቀርቧል

58. ዑመር መሀመድ መሀሙድ - ቀርቧል

59. አብዱላሂ ሙሣ ሀሰን - ቀርቧል

60. ሽኪር ቱኬ ሀሰን - ቀርቧል

61. መሀመድ አሊ ሁሴን /መሀመድ ጉዳ/ - ቀርቧል

62. መሀመድ አንጃባ አብደላ /ፍልመታ/ - ቀርቧል

63. አድናን ጉሼ አህመድ - ቀርቧል

64. መሀመድ ኑር አህመድ - ቀርቧል

1135

65. ሠይድ አደም አሊ - ቀርቧል

66. ካሊፍ መሀመድ ሼክ ሠኢድ - ቀርቧል

67. ኢብራሂም አብዱላ ዋሪዮ - ቀርቧል

68. አብደላ መሀመድ ሰዓድ /ሀግ/ - ቀርቧል

69 ሀሰን መሀመድ አህመድ - ቀርቧል

70. መሀመድ አብዶ አህመድ - ቀርቧል

71. ኑሬ ዑስማን ጂሎ /ቡቴ ጀሎ/ - ቀርቧል

72. ጫላ ሙክታር ሙሜ - ቀርቧል

73. አብዶሽ ሙሜ ጁምአ /ሻቦ/ - ቀርቧል

መዝገቡ የተቀጠረው የዐቃቤ ህግን ማስረጃ አገናዝቦ ብይን ለመስጠት ነው። በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ብይን ተሠጥቷል።

ብይን

ዐ/ህግ በቁጥር 113/2001 በቀን 08-07-2001 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የሚከተሉትን ክሶች በተከሣሾች ላይ አቅርቦል:-

1ኛ ክስ በ1ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሹ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ-መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስቦ ቀኑና ሰዓቱ በትክክል በማይታውቅ ታህሣሥ ወር 1997 ዓ.ም በኦሮምያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጎላ አዳ ወረዳ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩትን የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር /ኦ.ነ.ግ/ ብሎ ለሚጠራው ፀረ ሰላም አሸባሪ ቡድን ተደራጅተው እንዲታገሉ እና እንዲደገፍ በመገፋፋቱ በፈፀመው የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

2ኛ ክስ፡- በ1ኛ፣8ኛ እና 14ኛ

ተከሣሾች ላይ 238/1/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርአቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ቀኑን ወሩን በትክክል በማይታወቅ 1999 ዓ/ም በኦሮምያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጉርስም ወረዳ ቡርቃ ከተማ ልዩ ቦታው ቁጠና 2 ጤና ጣቢያ አካባቢ እራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር /ኦነግ/ ብሎ የሚጠራውን አሸባሪ ፀረ ሰላም

1136

ቡድን በመደገፍ የተነሳውን አረብሻ በማነሳሳታቸው እና በመምራታቸው በፈፀሙት በህገምንግስትና በህገመንስት ስርአት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል።

3ኛ ክስ -በ5ኛ፣2ኛ፣4ኛ፣8ኛ፣10ኛ፣44፣57ኛ 60ኛ እና 69ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወ/ህግ ቁጥር 32/1 እና 257/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንስታዊ ስርአቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው በ2000 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮምያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጉላ ኦዳ ወረዳ ቡርቃ ከተማ ውስጥ እራሱን የኦሮም ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ በሚጠራው አሸባሪ እና ፀረ ሰላም ቡድን ውስጥ አባል በመሆን የእዚሁ ቡድን እኩይ አላማ እንዲሳካ ገንዘብ በመስጠት በማዘዋወር ለሽፍቶች መንገድ በማሳየት እና በመምራት ሞባይል በመግዛት የወታደር ልብስ በመግዛትና በማቅረብ እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማቅረባቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት መሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

4ኛ ክስ በ3ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሹ የወ/ህግ ቁጥር 37/1/ እና 256/ለ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ታህሳስ ወር 2001 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 2፡00 ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጉላ ኦዳ ወረዳ በዲዲሞቶ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ እራሱን የኦሮሚያ ነፃ አውጪ ግንባር /ኦነግ/ ብሎ በሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚለውን 3 ሳጥን ጥይት እና ብዛት ያለውን የወታደር የእስፖርት ልብስ 7ኛ ተከሣሽ ከሆነው ሲራጅ አህመድ በማቀበሉ በፈፀመው የአባሪነት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሳነዳት ወንጀል ተከሷል።

5ኛ ክስ - በ5ኛ እና በ14ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወ/ህግ ቁጥር አንቀፅ 32/1/ሀ/፣27/1/ እና 238/1/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ከጠዋቱ በግምት 12፡30 ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጉላ ኦዳ ወረዳ ጨካ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ እራሱን የኦሮሚያ ነፃ አውጪ ግንባር /ኦነግ/ ብሎ የሚጠራውን አሸባሪ እና ፀረ ሰላም ቡድን በመደገፍ ከ70 እስከ 120 የሚደርሱ የኦነግ ወታደሮችን በማስተባበር በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ ተኩስ በመክፈታቸው 1ኛ ኡስማን መሀመድ 2ኛ እቁብ አብዱልዋል 3ኛ መሀመድ አሊይ 4ኛ አልይ መሀመድ የተባሉት ግለሰቦች በመግደላቸው በተጨማሪም ቁጥራቸው የማይታወቅ ሰዎች በማቁሰላቸው በፈፀሙት በህገ መንግስቱ እና በህገመንግስታዊ ስርአት የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል።

6ኛ ክስ በ7ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሹ የወ/ህግ ቁጥር 256/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑን ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅበት ጥቅ ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ዳላ ኦዳ ወረዳ ጋው ጋው ቀበሌ ዱምቱ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ እራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሠላምና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውሉ 1ኛ ቁጥሩ 243865 የሆነ ማለሠደፍ ክላሽንኮቭ መሳሪያ

1137

ከሠላሳ አራት ጥይት ጋር፣ 2ኛ አንድ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት የቆዩ ጥይቶች፣ 3ኛ ለሠልጣኝ ወታደሮች የሚሆኑ 20 የስፖርት ልብሶች አዘጋጅቶ በማስቀመጡ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶች ግፍ በሆነ አይነት የማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

የተሻሻለው 7ኛ ክስ - በ7ኛ፣በ9ኛ እና በ61ኛ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሾች የወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 256/ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ሕገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ቀኑና ሠዓቱን በትክክል በማይታወቅበት ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ገራገፉ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመቀላቀል ለዚሁ ቡድን ወታደሮች ምግብ ውሃ በመስጠታቸው በፈፀሙት የተንኰል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት መሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

8ኛ ክስ - በ7ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 256/ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስቦ ከላይ በ7ኛ ክስ ላይ በተጠቀሠው ጊዜና ቦታ ፀረ ሠላምና ፀረ ህዝብ ለሆነው ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ቡድን የሚታገሉ ሰባ የተበታተኑ ወታደሮችን መልሶ በማደራጀት ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በማስረከቡ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

የተሻሻለው 9ኛ ክስ - በ9ኛ፣15ኛ፣22ኛ፣25ኛ፣29ኛ፣30ኛ፣34ኛ፣37ኛ፣ እና 54ኛ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሾች የወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 257/ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል ከማይታወቅበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ እጃቸው እስከተያዘበት ጥር ወር 2001 ዓ/ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ራሱን ኦነግ ብሎ ከሚጠራው ፀረ -ሰላምና አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤታቸው ድረስ በማምጣትና በመደበቅ እንዲሁም ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀሳቸው በፈፀሙት የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል።

10ኛ ክስ - በ11ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሹ የወ/ህግ ቁጥር 257/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ ምንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑና ወሩን በትክክል ከማይታወቅ 1997 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2001 ኣ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ቡርቃ ከተማ የሚኖሩትን የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ እንዲደራጁና እንዲቋቋሙ በመቀስቀሱ በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

1138

11ኛ [illegible] በ12ኛ፣በ17ኛ፣18ኛ፣19ኛ፣20ኛ፣ እና 21ኛ [illegible]ሾች ላይ

ተከሳሾቹ የወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 257/ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት በ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ካገያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ደንበል ወቤ በተባለው ከፍተኛ የኦነግ አመራር አማካኝነት ተደራጅተው የቡድኑን እኩይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሽፍቶችን ከጫካ ወደ ከተማ እንዲሁም ከከተማ ወደ ጫካ መንገድ እያሳዩ በመውሠዳቸው በፈፀሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል።

12ኛ ክስ በ13ኛ እኛ 16ኛ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሾች የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 256/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ ምንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነገያ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ደንበል ዋቢ በተባለው ከፍተኛ የኦነግ አመራር አማካኝነት ተደራጅተው የቡድኑን እኩይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ለምግብነት የሚውሉ እህሎችን በማስፈጨት እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለቡድኑ ሽፍቶች በማቅረባቸው በፈፀሙጽ የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ ዓይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

13ኛ ክስ - በ23ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 257/ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ- መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑና ወሩ ተለያቶ በማይታወቅበት 1997 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሀረሚያ ከተማ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ << የኦነግ ፖሊሲ ትክክለኛ ነው >> በማለት ህብረተሠቡን ለሽብር ተግባር እንዲነሳሳ በመቀስቀሱ በፈጠማ መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

14ኛ ክስ በ24ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሹ የወ/ህግ ቁጥር 257/መ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ-መንግስቱንና ህገ- መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑና ወሩ ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅበት በ1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ሚደጋ ከተማ አካባቢ በሚገኘው ጫካ ድረስ በመሄድ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሠላም እና አሸባሪ ቡድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲዋጉ ጉዳት የደረሠባቸውን ሽፍቶች የባህል ህክምና በማድረግ በመተባበሩ በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

1189

15ኛ ክስ -በ27ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 27/1/ እና 238/1/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላፍ ማንነታቸው ካልታወቀ ግብረአበሮች ጋር በመተባበር ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ በተለያየ ቀንና ወር 1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሜታ ወረዳ ጨለንቆ ከተማ ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለ3ኛ ጊዜ የተነሳውን አድማ በመምራቱና በማደራጀቱ በፈፀመው በህገ - መንግስትና በህገ - መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል።

16ኛ ክስ - በ27ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 244/2/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ማንነታቸው ካልታወቅ ግብር አበሮች ጋር በመተባበር ከላይ በ15ኛ ክስ ላይ በተጠቀሠው ጊዜና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በጨለንቆ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና በየራሬ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተሠቅለው የነበሩትን የፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማንና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሠንደቅ አላማን አውርዶ በአደባባይ በማቃጠሉ በፈፀመው የሀገሪቱን መንግስት እንዲሁም ያገሪቱን ምልክቶችና በመንግስት የታወቁ ሌሎች ምልክቶችን መድፈር ወንጀል ተከሷል።

17ኛ ክስ -በ35ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 37/1/ በ27/1/ እና 238/1/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን እና ህገ - መንግስቱን በሀይል ለመናድ አስባ ከላይ በ15ኛ ክስ ላይ በተጠሠው ጊዜና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ 15ኛ ተከሰሾችንና ማንነታቸው ያልታወቁ ሌሎች ግለሠቦችን በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር እንዲያመቻቸው በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ መጠለያ በመስጠት እንዲወያዩና እንዲደራጁ በማድረጓ በፈፀመችው በአባሪነት በህገ - መንግስትና በህገ - መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሳለች።

18ኛ ክስ - ተከሳሽ ላይ

ተከሳሽ የወ/ህግ ቁጥር 257/ሐ/ ላይ የተመለከተውን በምተላለፍ ህገ - መንግስቱንና ህገ- መንግስታዊ ስርዓቱን ህገወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስባ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልልምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሀሮሚያ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በሚገኘው መኖሪያ ቤቷ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የሚታገሉ ሽፍቶችን በማደራጀትና መጠለያ በመስጠቷ እንዲሁም የኦነግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በማሆን መረጃዎችን በማቀባበልዋ በፈፀመችው በማገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሳለች።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

1140

የተሻሻለው 19ኛ ክስ በ32ኛ እና 36ኛ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሾች የወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 256/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ቀኑንና ወሩን በትክክል_ከማይታወቅ 1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ድረስ በድሬዳዋ ከተማ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሠላም እና አሸባሪ ቡድን ውስጥ ባለው በመጀራጀት ለቡድኑ አላማ የሚውል መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብ በማሰብ ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠታቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ ዓይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

20ኛ ክስ -በ32ኛ እና በ36ኛ ተከሳሾች ላይ

ተከሳሾች የወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 257/ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ - መንግስቱንና ህገ- መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ከላይ በ19ኛ ክስ ላይ በተጠቀሠው ጊዜና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላም እና ፀረ - ህዝብ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮችና ሽፍቶች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በማሳደራቸው መጠለያ በመስጠታቸው በፈፀሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ግባር ተከሠዋል።

21ኛ ክስ -በ38ኛ ተከሳሽ ላይ

ተከሳሹ በወ/ህግ ቁጥር 256/ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሀሮማያ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድንን በመደገፍ ኢብሳ ሌንጮ ወይም አሊ አመድ በተባለው ከፍተኛ የኦ.ነግ አመራር አማካኝነት "001" በሚል የምልክት ሥም ተደራጅቶ ለሶስት ጊዜ 480.00 (አራት መቶ ሰማንያ/ ብር የወባ በሽታ መከላከያ የሚሆን 30 አጎበር እና የመሣሠሉትን ቁሳቀሶች ለቡድኑ እኩይ ዓላማ እንዲውሉ በመስጠቱ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት የማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

22ኛ ክስ -በ39 ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ። ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1996 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በድሬዳዋና በሀረር ከተሞች በሚገኙት መኖሪያ ቤቶች አሸባሪዎችን በማሣደሩና በማስጠለሉ፣ የታመሙ የኦ.ነ.ግ ወታደሮች ቤቱ ተቀምጠው እንዲታከሙ በማድረጉ እንዲሁም በእርሻው ውስጥ የጦር መሣሪያዎችን እንዲያስቀምጡ በመፍቀዱ በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

ሀዛ

23ኛ ክስ -በ40ኛ እና 70ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 257/ሀ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑና ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅ ሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ጭሮ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቻይና ሠፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ህዝቡ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በመንግስት ላይ እንዲነሣሣ በመቀስቀሳቸው በፈፀሙት መገፋፋት ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል።

24ኛ ክስ-በ41ኛ እና በ42ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 256/ሀ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑና ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅ ነሐሴ ወር 1997 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 2፡00 ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ደሮ ለቡ ወረዳ ሚጨታ ከተማ 42ኛ ተከሣሽ በሆነው መሐመድ ሀጂ ኢብራሂም መኖሪያ ቤት ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ መንግሥትን በኃይል ከሥልጣን ላይ ለማውረድ 1ኛ አዩብ አብዱሌን 2ኛ/ ገመቹ ወይም ብሩስ አረዳን 3ኛ/ ጉተማ መሀመድን እና ስማቸው የማይታወቅ ሌሎች ሁለት ሰዎችን ጂአ ደራራ$ በሚል መጠሪያ ስም በማደራጀታቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

25ኛ ክስ-በ43ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ በተለያየ ቀንና ወር 2000 ዓ.ም በኦሮምያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጎለ አዳ ወረዳ ብርቃ ነገያ ቀ/ገ/ማህበር ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር ለሆነው ቢራሣ ደዬ ስንቅ በማቀበል፣ በገንዘብ በመርዳትና የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች መሠረታዊ ቁሳቁሶችን በመስጠቱ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

26ኛ ክስ በ45ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 256 /ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ። ለጊዜው ካልተያዘው ግብረ አበሩ ጋር በመተባበር ህገ-መንግሥቱንና ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ በተለያዩ አራት ቀኖች ህዳር ወር 2000 ዓ.ም በኦርምያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቁኒ ወረዳ በዴሣ ከተማ በሚገኘው አዋሽ ባንክ በኩል የተላከለትን በአጠቃላይ 90,200 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ/ ብር አውጥቶ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ በሚጠራው ፀረ ሠላም አሸባሪ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራር ለሆነው መሀመድ ደራሣ በማስረከቡ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

1142

27ኛ ክስ -በ46ኛ እና በ56ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 256/ሀ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲንቱ ወረዳ ኩርፋ ሮቃ ቀ/ገ/ማህበር ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ከላይ በ26ኛ ክስ ላይ የተጠቀሠውን ገንዘብ መሀመድ ደራሣ ከተባለው ግለሠብ ተቀብለው የኦ.ነ.ግ ከፍተኛ አመራር ለሆነው ቢራሣ ዳዬ በማስረከባቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

የተሻሻለው 28ኛ ክስ-በ47ኛ እና በ48ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 257/ሐ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1998 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ሀረማያ ከተማ የቀበሌ 01 ውስጥ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን የኦነግ ከፍተኛ አመራር የሆነው መሀመድ አባድርንና ሌሎች ታጣቂዎችን በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በማስራቸውና በመሸሸጋቸው በፈፀሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል።

29ኛ ክስ -በ49ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 254/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ። ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1998 ዓ.ም በኦሮምያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ሀረማያ ከተማ ውስጥ የቀበሌ 01 የፀጥታና ፍትህ ዘፍር ኃላፊ ሆኖ ሲያገለግል ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ አባላት ወንጀል ለመፈፀም የሚያደርጉትን የመሠናዳት ተግባር እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ በፈፀመው በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት ወንጀል ተከሷል።

27ኛ ክስ-በ46ኛ እና በ56ኛ ተከሣሾች ላይ

የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 256/ለ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ።

ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ብርቃ ዲንቱ ወረዳ ኩርፋ ሮቃ ቀ/ገ/ማህበር ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ከላይ በ26ኛ ክስ ላይ የተጠቀሠውን ገንዘብ መሐመድ ደራሣ ከተባለው ግለሠብ ተቀብለው የኦ.ነ.ግ ከፍተኛ አመራር ለሆነው ቢራሣ ዶዬ በማስረከባቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

28ኛ ክስ -በ47ኛ እና በ48ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 257/ሐ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። ብዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ውስጥ የቀበሌ

የፌ.ደ.ራ.ል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1143

01 የፀጥታና ፍትህ ዘርፍ ኃላፊ ሆኖ ሲያገለግል እራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ አባላት ወንጀል ለመፈፀም የሚያደርጉትን የመሰናዳት ተግባር እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ በፈፀመው በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት ወንጀል ተከሷል።

29ኛ ክስ በ49ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 254 /1/ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐሮማያ ከተማ ውስጥ የቀበሌ 01 የፀጥታና ፍትህ ዘርፍ ኃላፊ ሆኖ ሲያገለግል እራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ አባላት ወንጀል ለመፈፀም የሚያደርጉትን የመሰናዳት ተግባር እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ በፈፀመው በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት ወንጀል ተከሷል።

30ኛ ክስ-በ50ኛ ፣በ51 እና በ52 ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1//ሀ/ እና 257 /ሐ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ።በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መሠረታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ እና በአገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1998 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ በሚጠራው ፀረ ሠላምና አሻባሪ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራር በሆነው መሐመድ አባድር አማካኝነት ተደራጅተው የቡድኑን ታጣቂዎች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በማሣደራቸውና በመሸሸጋቸው በፈፀሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል።

31ኛ ክስ- በ53ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 256 /ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1997 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ውስጥ በክሪ አብዱላሂ የተባለውን ግለሠብና ሌሎች ስማቸው የማይታወቅ ሰዎችን ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ በሚጠራው ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን ሥር በማደራጀቱ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል።

32ኛ ክስ -በ55ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 27 /1/ እና 238/1/ለ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ብርቃ ዲንቱ ወረዳ በዲምቱ ቡሬዳ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ - ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ማንነታቸው ካልታወቀ ታጣቂዎች ጋር በመሆን የቀበሌው ሚልሻዎች ላይ ተኩስ በመከፈቱ በፈፀመው በህገ- መንግሥትና በህገ-መንግሥት ሥርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል።

33ኛ ክስ-በ58ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ሠኔ ወር 2000 ዓ.ም በኦሮሚያ

ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ብርቃ ዲንቱ ወረዳ ቡርቃ ራሚስ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር /ኦ.ነ.ግ/ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የኦ.ነ.ግ ከፍተኛ አመራር በሆነው ቢረሣ ዶዬ አማካኝነት "ቡርቃ ዶዬ" በሚል መጠሪያ ስም ተደራጅቶ ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ጫማዎችን እና የመሣሠሉትን ነገሮች ለቡድኑ ታጣቂዎች በመስጠቱ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

34ኛ ክስ-በ61ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 27 /1/ እና 238 /1/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ሠአቱ በትክክል በማይታወቅ ታህሣስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጎለ ኦዳ ወረዳ ራምስ ወንዝ አካባቢ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር /ኦ.ነ.ግ/ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ተኩስ ከፍቶ አንድ ሠው በመግደሉና ሰባት ሰዎችን በማቁሰሉ በፈፀመው በህገ-መንግሥትና በህገ- መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል።

35ኛ ክስ-በ62ኛ፣63ኛ 65ኛ እና 66ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1/ ሀ እና 256 /ለ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ህዳር ወር 2000 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 2፡00 ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ልዩ ቦታው ቦረን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ በኃላፊነት ሲሰሩ ለህብረተሰቡ እንዲያከፋፍሉ ከተሰጣቸው የእርዳታ እህል ላይ አስር ሉቃ ስንዴና ስምንት ሉቃ በቆሎ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠታቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

36ኛ ክስ-በ62ኛ እና 68ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 27 /1/፣32/1/ ሀ እና 238/1/ለ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። ማንነታቸው ከማይታወቅ ግብረአበሮቻቸው ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ እና በሀገርና በመንግሥት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 2000 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር ተዋግተው በአጠቃላይ 11 ሠዎችን በመግደላቸውና አንድ የመንግስት ንብረት የሆነ መኪና በማቃጠላቸው በፈፀሙት በሕገ-መንግሥትና በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል።

37ኛ ክስ-በ64ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ። ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 2000 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ... ልዩ ዲ/ሬፐብሊክ

1145

ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ አዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን፣ ሲጋራ፣ ባትሪ ድንጋይና የመሣሠሉትን እቃዎችን ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠቱ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

38ኛ ክስ-በ67ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር የሆነው መሀመድ ሀጂ ዳዲን ወይም አሪያ ዳዲን ከመሥራቅ ሀረርጌ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ መንገድ እያሳየ በመውሰድ የቡድኑ እኩይ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ በመተባበር በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

39ኛ ክስ-በ67ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 256 /ለ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅ ጥር 23 ቀን 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ አዳ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ልዩ ቦታው አህመድ ኢብራሂም የተባለ ቦታ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን ዓላማ የሚውሉ ሁለት የጦር መሣሪያዎችን ከ34 ጥይት ጋር አዘጋጅቶ በማስቀመጡ በፈፀመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሷል።

40ኛ ክስ -በ12ኛ፣16ኛ፣18ኛ፣ እና 19ኛ ተከሣሾች ላይ

ተከሣሾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ ሀ/ እና 256 /ለ/ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስበው በተለያዩ ቀኖችና ወሮች 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነገያ ቀበሌ ውስጥ በሚገኝ መኖሪያ ቤታቸው ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን ዓላማ የሚውሉ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችን አዘጋጅተው በማስቀመጣቸው በፈፀሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሠናዳት ወንጀል ተከሰዋል።

የተሻሻለው 41ኛ ክስ በ71ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ሐ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ሠዓቱ በትክክል በማይታወቅ ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሀዊ ጉዲና ወረዳ ድሬ ገደራ የተባለ ቦታ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን የታጠቁ ወታደሮች መንገድ እያሳየና እየመራ በመውሰድ በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሠናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1148

42ኛ ክስ-በ72ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 27 /1/ እና 238 /1/ለ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል በማይታወቅ ህዳር ወር 2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ሀሮማያ ከተማ ውስጥ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ በማቀድ ኤፍ /AF/1 ቦምብ ለማፈንዳት በከተማው መስተዳድር ጽ/ቤት ላይ ወርውሮ ሳይፈነዳ ቢከሽፍም በፈፀመው በህገ መንግሥትና በሕገ- መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ የሚደረግ ሙከራ ወንጀል ተከሷል።

43ኛ ክስ-በ73ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 37 /1/ እና 238 /1/ለ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ከላይ በ42ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ 72ኛ ተከሣሽ የወረወረውን ኤፍ /AF/1 ቦምብ ገዝቶ በመስጠቱና ወንጀሉ የሚፈፀምበትን ሁኔታ በማመቻቸቱ በፈፀመው ተባባሪ በመሆን በህገ-መንግሥትና በህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ የሚደረግ ሙከራ ወንጀል ተከሷል።

44ኛ ክስ-በ26ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 27 /1/ እና 238 /1/ለ ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ። ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑና ወሩ በትክክል ከማይታወቅ 1999 ዓ.ም ጀምሮ ቀኑና ወሩ በትክክል እስከማይታወቅ 2000 ዓ.ም ድረስ ከሚኖርበት ኦሮምያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሣ ወረዳ ወተር ቀ/ገማህበር በመሄድ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር /ኦ.ነ.ግ/ ብሎ የሚጠራውን ፀረ- ሠላምና አሸባሪ ቡድን በመቀላቀል የዚህን ቡድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በወታደርነት ሲያገለግል በመቆየቱ በፈፀመው በህገ-መንግስቱና በህገ-መንግስት ሥርዓት ላይ ሥርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል።

45ኛ ክስ በ28ኛ ተከሣሽ ላይ

ተከሣሹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 /ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ።ህገ-መንግሥቱንና ህገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ህዳር ወር 1998 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 4፡00-6፡00 ድረስ በኦሮምያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ኮምቦልቻ ወረዳ ቀሬንሣ ቦርቴ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ ልዩ ቦታው ዩሱፍ መንደር አካባቢ 1ኛ አብዱ አዩብ 2ኛ አብዱላሂ አህመዴ እና ሌሎች ሁለት ሠዎችን ሰብስቦ ራሱን ኦ.ነ.ግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሠላምና የአሸባሪ ቡድንን አርማ በማሳየት ይህንኑ ቡድን በገንዘብና በጉልበት እንዲደገፉ በመቀስቀሱ በፈፀመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው ።

ሁሉም ተከሣሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ከ33ኛ ተከሣሽ ውጭ የተቀረበውን ተቋውም ውድቅ በማድረጉ በሰጡት እምነት ክህደት ቃል ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል።

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1147

33ኛ ተከሣሽ ከቀረበው ክስ የተሰናበተ ሲሆን በተቀሩት ተከሣሾች ላይ ዐቃቤ ህግ 89 የሰው ምስክር ለማቅረብ ዘርዝሮ 70 ምስክሮ አቅርቦ አሰምቷል።

በሰነድ ማስረጃነትም ከምስራቅ ሀረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ በቁጥር 4P6-HB/38/135/2001 በቀን 11/06/2001 በተፃፈ ደብዳቤ ሸኚነት ከ7ኛ፣12ኛ፣16ኛ፣18ኛ፣19ኛ፣20ኛ እና 60ኛ ተከሣሾች በኤግዚቢትነት የተያዘ የጦር መሣሪያና ጥይቶችና አይነትና ብዛት የሚገልጽ፣ 45ኛው ተከሣሽ ዩሱፍ ጩሎ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በደሳ ቅርንጫፍ ስለወጣው ገንዘብ የሚገለጽ 5 ገጽ እንዲሁም 1ኛ፣ 2ኛ 3ኛ 6ኛ፣ 8ኛ፣ 13ኛ፣ 16ኛ፣ 17ኛ፣ 20ኛ፣ 21ኛ፣ 43ኛ፣44ኛ፣46ኛ፣54ኛ፣55ኛ፣56ኛ፣ 58ኛ፣ 59ኛ እና 64ኛ ተከሣሽ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቀርበው በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሠረት የሰጡት ቃል 21 ገጽ ቀርቧል።

እንዲሁም ከ16ኛ ተከሣሽ መኖሪያ የተያዘ የተባለ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ ኦሮሞ /2 ገጽ/ ፣ በ20ኛው ተከሣሽ መኖሪያ ቤት የተያዘ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ አርማ 1 ገጽ በገላጭ ማስረጃነት ቀርቦዋል።

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ህግ ምስክሮች እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት ምስክሮቹ የሰጡት ቃል እንደሚከተለው ነው።

1ኛ--17ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር አህመድ ዑስማን ዱላ 46ኛ እና 56ኛ ፣ተከሣሾች በተመለከተ በቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ 46ኛ እና 56ኛ ተከሣሾች መጀመሪያው ዙሪያ 20.000/ሃያ ሺህ/ በሁለተኛ ዙር ላይ ደግሞ 29.900 በ1ኛ ዙር ደግሞ 40.000 ደራሶቸው ያስተላለፍ ስለመሆኑ ሰምቻለሁ ።ይህንን የሰማሁት በታዛቢነት ተቀመጡ ተብለን ሲሆን ዐ/ሕግ እና ፖሊስ ነበር ። ገንዘቡን ለአባዋ/ሸፍታ/ አስተላልፈውታል።ጀማል ሁሴ የተባለው ደግሞ በ2001 ዓ/ም በምስራቅ ሀረርጌ ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ዋቤ ቀ/ገ/ማህበር በመንግሥት ሚኒሻዎች ላይ ተኩስ ከፈቱብን። 46ኛ እና 56ኛ ተከሣሾች በጣቢያ ቃላቸውን ሲሰጡ የሚመታችሁ የሚነካችሁ የለም ተብለው ነበር። መማንም አለማመንም ተችላለችሁ ተብለዋል። ከተናገርኩት እንደሰማሁት ገንዘቡን ለአባዋ ወታደር አዛዥ ለሆነው ለቢራ ሳይዬ አስተላልፈውታል ቢራ ሳይዬ ደግሞ ሽፍታ ነው። የሽፍታውም መንግሥትን ለመናድ ነው።

2ኛ---18ኛየዐቃቤ ህግ ምስክር ኢብዱላከም መሀመድ በ32ኛ ክስ ላይ በ46ኛ ፣55 እና 56ኛ ተከሣሾች ላይ የሚመሰክር ሲሆን በጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም በፖሊስ ጣቢያ መርማሪ ባለበት በሰጡት ቃል 46ኛ ተከሣሽ ከመሀመድ ከሚባል ግለሰብ አንድ ጊዜ 20.000 ብር ለ1ኛ ጊዜ 20.000 ብር ለ3ኛ ጊዜ ደግሞ 40.000 ብር ተቀብሎ ለ56ኛ ተከሣሾች ሰጥቶታል። 56ኛ ተከሣሽ ደግሞ ለአባዎ ለተባለ መንግሥት ላይ ተቆውሞ ለሚነሳ ድርጅት ለሚመሩ ለቢና እና ለገመቺስ ሰጥቷል ሲባል ሰምቻለሁ። 55ኛ ተከሣሽ ደግሞ ለስራ ወደ ቦታው ማለትም ሀሮ ደምቱ የባለው ሄደን እየሰራ ከአበዎ ሰራዊቶች ጋር በመሆን ተኩስ ከፍቶብናል እኛ በወቅቱ የመንግሥት ሚኒሻዎች ነበር። በፖለስ ጣቢያ ቃላቸውን ከሰጡ ሳይገደድና ሃይል ሳይጣልባቸው ነው። አባዎ እና ኦነግ አንድ እና አንድ ናቸው ሁለቱም መንግሥትን ይቃወማሉ ፣ በመንግሥት ላይ ጥቃት ለማድረስ የተቋቋሙ ናቸው። 55ኛ ተከሣሾችን ከዚህም በፊት አውቃዋለሁ በኦነግ ውስጥ ነበር የሚታወቀው።

3ኛ--24ኛየዐቃቤ ህግ ምስክር አብዱላሃኪም አህመድ በ55ኛ ተከሣሽ ላይ በጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም ሁነን ሚነሻዎች ወጥተው እያለ 55ኛው ተከሣሽ በቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ዋቢ የሚባል ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ አበዋ

በመሆን ተኩስ ከፍቶብናል። በመሀከላችን በግምት 10 ሜትር ርቀት ነበር። 55ኛ ተከሣሽ የአበዎ አባል መሆኑን አውቃለሁ። አበዎ ማለት ኦነግ ሲሆን በመንግሥት ላይ ተቃውሞ ይነሳል።

4ኛ--22ኛየዐ/ሕግ ምስክር በ58ኛ ተከሣሽ ላይ ብቻ በሰኔ ወር 2000 ዓ/ም በቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ውስጥ ፖሊሶች ምርመራ ሲያደርጉለት 58ኛ ተከሣሽ ቃሉ በሚሰጥበት ወቅት ሊሊስ ይዬ የተባለ የኦነግ ሰራዊት ቡርቃ ይዬ በሚባል ስም እንዲረዳቸው አስመዝግቦል። በውስጡም 7 ሰዎች አባሎች አሉት ሲል ሰምቻለሁ።ተከሣሹ ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት የድብደባ ወይም የስቃይ ምልክት ባይታይበትም ቃሉን መስጠት ወይም ዝም የማለት መብት ያለው ስለመሆኑ ስለመናገሩ አለመነጋገሩ አላውቅም በማለት አስረድቷል።

5ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ብድር አህመድ በ40ኛ ተከሣሽ ላይ ሂርና እና ቱሉ የሚባሉ ቦታዎች በ1997 ዓ/ም ለአንድ ወር ያህል ቤት ተከራይቼ በምኖርበት ወቅት 40ኛ ተከሣሽ በአባዎ ስር እንዲረዱ ብሎ ሣሣብ አምጥቶ ከዛ በኋላ ሁለት ቀን ብር 50 እናውጣ ተብሎ በበኩሌ ብር አውጥቻለሁ።ብሩም ኦሮሞን ነፃ አወጣለሁ ለሚለው ለአባዎ ድጋፍ የሚል መሆኑን አውቃለሁ። ይህንን ሚስጥር እንዳናወጣ ቃለ መሀላ ቡመን ነበር። ያወጣሁትን ብር ለ40ኛ ተከሣሽ ነው የሰጠሁት በዛን ወቅት እኔ የግብርና ማሻሻያ ትምህርት እየወሰድኩ ነበር። ቃለመሀላ ያስፈፀመኝም 40ኛ ተከሣሽ ነው። ቃለ መሃላው የተፈፀመው እጅ ለእጅ ተያይዘን " የኦሮሞ ጀግኖች አጥንት እንደሆንን " ተባብለን ነው በዚህም ጊዜ 40ኛ ተከሣሽ አባል የሚሆኑ ሰዎችን እንድመለምል ነግሮኝ ነበር። ለኦነግ አባላት እርዳታ ተብሎ የተሰበሰው ገንዘብ የት እንደደረሰ አላውቅም በማለት አስረድቷል።

6ኛ--27የዐ/ሕግ ምስክር መሀመድ ሁሴን ሽሪፍ የ44ኛ እና 57ኛ ተከሣሾች ላይ በ2000 ዓ/ም ወሩን እና ቀኑን በማላስታውሰው ቡርቃ ዲምቱ ተብሎ የሚጠራ ቦታ በቀበሌው ውስጥ ተመራጭ እና ታጣቂ በነበርኩበት ወቅት አንድ አስሜሬ ለአባዎች እንዲሰጥ በሚል 71.000 ብር ለ44ኛ ተከሣሽ ሰጥቶታል ይህም ገንዘብ በቀጥታ በአደረግነው ክትትል ለአባዎች እንደደረሰ አውቀናል። ገንዘቡን በ44 ተከሣሽ እጅ አይቸው ነበር ከዛ 44 ና ተከሣሽ ለረሺድ አብዶ የሚባል ሲሰጠው ረሺድ ደግሞ ለፋርጋሱ የሚባል የአባዎ አባል ሰጥቶታል። በወቅቱ ገንዘቡ በ44ኛ ተከሣሽ እጅ እያለ ልረከብ ያልቻልኩት እነሱን ሃይል የታጠቁ በመሆናቸው ስለምፈራቸው ነው 44ኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ያስተላለፈ ስለመሆኑ ፋርጋሱ የሚባለው አረጋግጦል። 57ኛ ተከሣሽ ደግሞ 44ኛ ተከሣሽ ሰጥቶኛ ነው የሚለው ቶሪያ የሚባል ሞባይል ተገኝቶበታል። ይህ ሞባይል አባዎች ለመልከት ማስተላለፊያ የሚጠቀሙበት ነው። እንደመገናኛ ማለት ነው።የሞባይሉ አይነት የመንግሥት መከላከያዎች የሚይዙት አይነት ነው። 44ኛ ተከሣሹ በፋርጋሱ ጠቋሚት ሲያዝ በእራሱ ጊዜ 6000 ብር እና ሽጉጡን አውጥቶ ሰጠ ፋርጋስ በ2000 ዓ/ም ውስጡ አባዎች አዛዥ ነበር። ሁለት ተከሣሾች እዛው ነዋሪ ሲሆኑ አበዎ ወይም ሽፋታ ናቸው።

7ኛ--30ኛየዐ/ሕግ ምስክር ሰይፋ አብይ ዑመር በ44ኛ 57ኛ ተከሣሽ እና በ45ኛ ተከሣሾች ላይ ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ 44ኛ ተከሣሽ 71.000 ብር ለአባዎች እንደደረሰ እንዲሁም መኮሮኒ እና ስኳር ሌሎች 3 አባዎች በመኪና ጭኖ ሰንበቴ የሚባል ቦታ እንዳደረሰ፣ 6000 ብረ እና ሽጉጥ ለመከላከያዎች እንዳስረከብም አውቃለሁ፣ 57ኛ ተከሣሽ ደግሞ አባዎች በመከላከያ እንዳይገኙ መንገድ እንደሚያሳይ ... የሚሆን ነገር ለአባዎች እንደሚሰጥ አውቃለሁ ሲል 45ኛ ተከሣሽም ከሀረር አካባቢ ብርም ... ሰብስቦ በበዴሳ ... አድርሶ ለኦነግ እንደሚያደርስ ራሱ ሲናገር እንደሰማ አስረድቷል።መገናኛው ሶላር ... የሚባል ሲሆን በፀሀይ ብርሃን ሃይል ይሰራል ። 44ኛ ተከሣሽ 3 አባዎችን ከ57ኛ ተከሣሹ ጋር በመሆን ነው ወደ ውቤ የሚባል ቦታ የሸኛቸው 71.000 ብሩን

1149

44ኛ ተከሣሽ ራሱ እኔ ነኝ ለአባዎች ያደረስኩት ሲል ከመስማት ውጪ ገንዘብን አላየሁም የጠየቁትም በ2001 ዓ/ም ፖሊስ እና ዐ/ሕግ ናቸው ቦታውም ቡርቃ ዴንቱ ጨፊ ይባላል። ቃሉን ከመስጠቱ በፊት 44ኛ ተከሣሽ ፈቃደኛነቱ ተረጋግጦል። ቃሉም ከተፃፈ በኋላ ተከሣሹ ፈርሞበታል። 44ኛ ተከሣሹ 6000 ብር እና ሽጉጥ የአባዎች ነው ብሎ ሰጥቻለሁ ሲልም ሰምቻለሁ። 45ኛ ተከሣሽ በሙክታር አብዱልጀሊል እና አህመድ ደረስ በሚባሉ አማካኝነት 92.000 ብር ለኦነግ ተሰጠ ሲል ሰምቻለሁ ሽጉጡ ፈቃድ ያለው ሽጉጥ ነበር። ሲል 45ኛ ተከሣሽም የሰማሁት በጣቢያ ሳይገደድ ቃሉን ሲሰጥ ነው።

8ኛ--81ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ሬድዋን መሀመድ አብዱላጊ በ40ኛ ተከሣሽ ላይ አብዲ አደም እና መሀመድ ዳውድ ከሚባሉ ሰዎች ጋር በመሆን በ1997 ዓ/ም ሐምሌ ወር ውስጥ በአባዎ በሳሶዎች በመሆን ሕዝቡ ውስጥ በመንቀሣቀሱ ƀራሱ ቤትም በመሰብሰብ እንደሚንቀሣቀስ፣ መታወቂያም እንዳለው በስልጠና በሚልም ሌላ ቦታ ሌላ ሀገርም ሄዶ እንደሚመጣ አስረድቷል አባዋ ማለት መንግሥት ለመገልበጥ የሚፈልጉ ናቸው። እኔ እዛው አካባቢ ስለሆንኩ የ40ኛ ተከሣሽ ቤት ፖሊስ በሚፈተሽ ወቅት ገብቼ ተመልክቻለሁ መታወቂያውም ተገኝቷል። ወዲያውም ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጓል። ሌላው 70ኛ ተከሣሽ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አባዎነት ከላይ በሆነው አህመድ ቤት ይሰበሰብ ነበር። አህመድ የተባለው በሙያው አስተማሪ ሲሆን ውስጥ ለውስጥ ኦነግን የሚያደራጀው እሱ ነው በዛም አወጣ ወታደር ውስጥ ለውስጥ እናሰለጥናለን ይለን ነበር። 70ኛ ተከሣሽን በአህመድ ቤት ተሰብስቦ አይቻዋለሁ። እኔ አንድ አንድ ችግሮች ሲፈጠሩ ነው የሄድኩት ስብሰባ ላይ እያለን በሰው እንዲያዙ ተደርጓል።

9ኛ--1ኛየዐ/ሕግ ምስክር መሀዲ ኢሚን በ30ኛ እና 22ኛ ተከሣሽ ላይ ከ22ኛ ተከሣሽ ከ1998-2000 ድረስ እንተዋወቃለን ሰርዶ ወይም ኢብራሂም የሚባል ሰውዬ አንተን ይፈልግሃል እያለችን ሲነግረኝ ነበር። ስልኩም ሰጥታኛለች ኢብራሂም ኦነጎችን የሚያደራጀ በመሆኑ ለዛ ነው ሲፈልገኝ የነበረው በ1998 ዓ/ም እኔ እና ዩያ መሀመድ የምንባል ወደ 30ኛ ተከሣሽ ቤት ሄደን ነበር፣ ዑመር ፣ ሱፊያን እና አልያ ዳዲን አግኝተናል። እነዚህ 3ቱ ኦነግ ናቸው። 30ኛ ተከሣሽም በአባልነት ከእነሱ ጋር ገንዘብ በማሰባሰብ ሰውን ያደራጃሉ። ከተማሪም ከአስተማሪም ገንዘብ ይሰበስባሉ። ብሩን ሕዝቡን ለማነሳሳትና አባዋ ለማድረግ ይጠቀሙበታል። 22ኛ ተከሣሽ የኦነግ አባል እንጂ ካድሬ መሆኗን አላውቅም በ1998 ዓ/ም ከአገኘኋቸው መሀከል አብዲ አሊ አንዱ ሲሆን በዚህም መዝገብ 28ኛ ተከሣሽ ላይ ይገኛል። ከእሱ ጋር አብረን አበዋ ስለነበር እንተዋወቃለን። 28ኛ ተከሣሽ ከእነ መሀመድ አባድር ጋር እየኖር የኦነግ አባላትን ያደራጅ ነበር። 22ኛ 28ኛ እና 30ኛ ተከሣሽ የኦነግ አባሎች ነበሩ ። በወቅቱ ለሕዝብ መቀስቀሻ የሚሆን መውጫ ይሰበስቡ ነበር። ለዑመር ዳዲ ሲሰጡት ዑመር ደግሞ ለኦነግ ሃላፊ ለሆነው ለአርአያ ዳዲ ይሰጠዋል። 22ኛ ተከሣሽም በዚህ ሁሉ አብራ ነበረች ፣ ነገር ግን አበል አልነበረችም። እነዚህ 3ቱ ከኦነጎች ጋር በመሆን ገቢ ያሰባስባሉ፣ ሕዝብ ያቀሰቅሳሉ እንጂ ሌላ በግላቸው ያደረጉትን አላውቅም በማለት አስረድቷል።

10ኛ--59ኛ የዐ/ሕግ ምስክር አብዱራዛቅ ራቢራ በ11ኛ እና 1ኛ ተከሣሽ ላይ እንዲሁም በ5ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች ላይ 1ኛ ተከሣሽ በ1999 ዓ/ም ከትምህርት ቤት ወጥቶ የአባዎች የሆነ አመት በዓልነበራቸው ያንን አመት በዓል ለማክበር ሄዶ ነበር። የሚከበረውም በጫካ ውስጥ ነበር። በኦሮምኛ አባዋ ማለት የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ማለት ነው። ይህ የሆነውም 11ኛ ተከሣሽ ደግሞ በ1986 ዓ/ም አባዎች ተጠራርገው በሚጠፋባት ሰአት ኪሱ ወደ ሀገር ተመለሰ፣ ወደ ሕዝቡ ተቀላቅሎ ነበር ።ጀማል ከሚባል ሰው ጋር ስናገግረው ለአባዎች ብዙ ጊዜእንዳገለገለ ሰውነቱ ለእነሱ ሲል እንደተገዳ አሳውቆናል። ከ1997 ዓ/ም ምርጫ በኋላ ቁብ[illegible] የሚባል ሰውዬ ከገ[illegible]አድ የመጣ

ሀረር ከተማ አነጋገረኝ በግት የአባዎን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከእኛ ጋር እንቀሣቀሣለሀ እንዴት ነው ብሎ እንደጠየቀው የራሴ ችግር ስላለብኝ ትግል ባላደርግም ለትግሉ ግን ዕንቅፋት አልሆንም በማለት እንደመለስለት አስረድቶናል። በዛ ወቅትም 2 ሽጉጥ ሰጥቶት ለቱማስ ለሚባል አስተለፋ እንዳለውም አሳውቋል። ይሄንም ሽጉጥ ለቱማስ አድረሻለሁ አለን። 5ኛ እና 14ኛ ተከሣሽን በተመለከተ ደግሞ በአይኔ በላይም በ1998 ከተማሪዎች ጋር ሕገ ወጥ ሰለማዊ ሰልፍ ያደርጉ ነበር። በ1999 መጨረሻ ወደ 2000 መግቢያ ላይ መሣሪያ አስረከበዋል።

11ኛ--79ኛየዐ/ሕግ ምስክር አብዱራህማን አብዱላሂ በ1ኛ ተከሣሽ ላይ በ1997 ዓ/ም የቀበሌ ሊቀመንበር በነበርኩበት ወቅት በፖሊስ ተጋብዤ 1ኛ ተከሣሽ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ በዚህም ጊዜ ተከሣሽ የኦነግ አባል ነኝ ሲል እንደነበር የኦነግ ራዲዬ ጣቢያ እና ቪዲዮ እንደሚያደምጥ እና ቀይ እና አረንጓዴ ሻማ ይዞ ድልድይ ውስጥ የኦነግ አርበኞች ቀን በሚል ማክበሩን እንዳስረዳ ቃሉን ሰጥቷል። 1ኛ ተከሣሽ የኦነግ አርበኞች ቀን የሚለውን ያከበረው ከጓደኞች ጋር እንደሆነ በሰጠው ቃል አስገንዝቧል። ተከሣሹ ቃሉን ሲሰጥ ብትፈልግ መስጠት ትችላለህ ስለመባሉ አላውቅም።

12ኛ--8ኛየዐ/ሕግ ምስክር አብዲ አደም በ49ኛ ፣ 50ኛ ተከሣሾች እና ዩሱፍ ዳውድ በተመለከተ ከዚህ በፊት የምስክርነት ቃሉን አልሰጠሁም።

13ኛ--78ኛየዐ/ሕግ ምስክር አድማሱ አለሙ አያሌው በሰጠው የምስክርነት ቃል 1ኛ ተከሣሽ ላይ ብአለማያ ፖሊስ ጣቢያ በፍላጉት ቃሉን ሲሰጥ የቀበሌ ፀጥታ ሃላፊ ስለሆንኩ ተጠርቼ እንዳደምጥ ተደርጎ ነበር። ተከሣሹ የኦነግ አባል እንደሆነ ከጎሎአዳ ወደ አወዳይ በመምጣት ----------አባሎችን ይመለምሉ እንደነበር እንዲሁም የኦነግ ካሴት እንደተመለከተ እና አረንጓዴ እና ቢጫ የኦነግ ሻማ በመብራት የኦነግ ጀግኖች ቀን በማለት የኦነግ ድልድይ ስር እንዲከበሩ የኦነግ ራዲዬ እንደሚያደምጥ፣ ከዛሬ አምስት በፊት አባል እንደነበር ሲናገር እንደሰማ አስረድቷል።

14ኛ--71ኛየዐ/ሕግ ምስክር ግዛው ባሩዳ በ23ኛ ተከሣሽ ላይ ሲሆን 23ኛ ተከሣሽ የኦነግ አባል ነበር ከዛ በኃላ ግን ታድሶ ይግባ አይግባ አላውቅም። ኦነግ ከተበተነ በኋላም ከአለማያ ይኖር ነበር ከሰው ጋር ብዙ ጊዜ አላየውም ብቻውን ነው ብዙ ጊዜ የማየው ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ በኦነግ አባልነት ይንቀሣቀስ ነበር። ኦነግ ሕገ መንግስቱን አልቀበልም በማለት ረገጦ እስከወጣ ድረስ አባል ነበር የአነግ አላማ ሕዝብን መበጥበጥና አልባሌ ነገሮችን መስራት የልማት እንቅፋት መሆን ነው። ሌላ የማውቀው ነገር የለም።

15ኛ--13ኛዐ/ሕግ ምስክር አብዲ ሙመድ አብዱላሂ በ49 እና 47ኛ ተከሣሾች ላይ በ1998 ዓ/ም ዘር እየዘራን እያለ ሐረማያ አካባቢ ገንደ ቦዬ አካባቢ በ47ኛ ተከሣሽ እርሻ ውስጥ ለሁለትቀን ያህል የሆኑ ስራ የማይሰሩ እስከ 9፡00 እርሻ ከዛ በኋላ ከተማ ደርሰወው የሚመጡ ሰዎች አይቼ የ47ኛ ተከሣሽን እርሻ የሚጠብቀውን ልጅ ስጠይቀ የኦነግ ከድሬዎች ናቸው አለኝ ከዛ ከ49ኛ ተከሣሽ በጊዜው የቀበሌው ሊቀመንበር ለነበረው ነግረው ነበር የወሰደው እርምጃ የለም።

16ኛ--7ኛየዐ/ሕግ ምስክር አሊይ አብዱላሂ በ47ኛ፣48ኛ ፣49ኛ፣50ኛ እና 52ኛ ተከሣሾች ላይ ሲሆን 49ኛ ተከሣሽ የቀበሌ ሊቀመንበር ሆኖ በሚሰራበት ወቅት 15ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በ47ኛ ተከሣሽ እርሻ ውስጥ ያየውን ነገር አሳውቆት እያለ ይህንን መረጃ መደበቁ በግምገማ ወቅት ተነስቶባታል። 52ኛ ተከሣሽን በግምገማ ወቅት

የፌ.ዴ.ራ.ል ከፍተኛ ፍ/ቤት

1151

ተነስቶበታል። 52ኛ ተከሣሽን በተመለከተ በኦሮሞ የባህል ልብስ ለመንግሥት አላሳዩም ከማለቱ ውጪ ሌላ የሰራው ስራ አላውቅም 47ኛ እና 48ኛ ተከሣሾች ባልና ሚስት ሲሆኑ መሀመድ አባድር የተባለ የኦነግ አባል በቤታቸው መሸሸጋቸው ታውቋል። አበቃ ።

17ኛ-- 10ኛየዐ/ሕግ ምስክር ዩሱፍ አሜ በ47ኛ ፣48ኛ፣49ኛ፣52ኛ ተከሣሾች ላይ በወቅቱ የመንግሥት አባል በነበርኩበት እነዚህ ተከሣሾች የሚገመገሙበት ቦታ ተወስደን 47ኛ ተከሣሽ የኦነግ አባል የሆነው መሀመድ አባድር አንድ ልጅ እንደሚያኖረው ሌሎች ሁለት ሰዎችም ወደ ቤቱ እንደመጡ አንስቶ ተነግሯል ። መሀመድ አባድር ከእነቤተሰቦቼ አደራጅቶታል አለን። በወቅቱም በሃይስኩል ረብሻ ነበር ። 48ኛ ተከሣሽ በ47ኛ ተከሣሽ ባለቤት ነች። 52ኛ ተከሣሽ በግምገማ ወቅት የተነሳበት ነጥብ የኦሮሞ መረዳጃ ማህበር ጥኔኛ መደራጀት አለበት በሚለው ነው ይህ መረዳጃ ውስጥ የመሀመድ አባድር ሃሣብ ሳይኖር አይቀርም ተብሎ ይታሰባል። መሀመድ አባድር ከ52ኛ ተከሣሽ ጋር ነበር።በሰፈሩ ውስጥ መሀመድ አባድር ከሁሉም ጋር ነበር መሀመድ አባድርን መጀመሪያ ላይ የምናውቀው ሰርቶ የሚኖር አድርገን ነው። ግን በግምገማው ወቅት ኦነግ እንደሆነ በይፋ ታወቀ 49ኛ ተከሣሽ በግምገማ ወቅት የተነሳበት 15ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በ47ኛ ተከሣሽ እርሻ ውስጥ ሁለት ኦነጎች መኖራቸውን እሳውቆት እያለ መረጃውን ደብቋል ተብሎ ነው። 49ኛ ተከሣሽ በወቅቱ የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ሲሆን በግምገማው በተሰጠኝ መረጃ መሰረት ፍለጋ አድርጌ ስላጣሁኝ ነው ዝም ያልኩት ብሏል።

18ኛ-- 9ኛየዐ/ሕግ ምስክር ፋጡማ ዩሱፍ በ51ኛ ተከሣሽ ላይ 51ኛ ተከሣሽ ከመሀመድ አባድር ከተባለ ኦነግ ጋር ሆኖ እኔ ቤት መጥተው ጫት ቅመዋል። መሀመድ አባድር ነፃ አልወጣንም ይል ነበር። 55ኛ ተከሣሽ ላይ ከመሀመድ አባድር ጋር ሲሄድ ነው የማየው እንጂ ሌላ ምን እንደሚያደርግ አላውቅም።

19ኛ-- 77ኛየዐ/ሕግ ምስክር ማሾ አደም በ25ኛ ተከሣሽ ላይ 25ኛ ተከሣሽ አባዋ ነው የቀበሌ አስተዳደር በመሆኔ ነው ያወቅኩት ከ6 ወር በግምት በፊት አባዋ መሆኑ ታውቋል። ታስሮ ከወጣ በኋላም በእንደዚህ አይነት መንገድ እየተራመደ ነነበር። 23ኛ ተከሣሽ ከዚህ በፊት አወዳይ ከተማ ውስጥ ፈንጅ ያወጣው ሰው ናገር ፊንጠበስ ጓደኛ ነበር። በሌላ በኩል ምስክሩ በዐ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ለ27ኛ ተከሣሽ ላይ ለመመስከር የቆጠረ ቢሆንም ስለ 22ኛ ተከሣሽ በተመለከተ የሰጠው ቃል የለም። ከማለት አስመዝግቦል 25ኛ ተከሣሽ ከፊንጠባስ ጋር ሆኖ እኛ ከአባዋ ጋር ሆነን እናንተ ከጠላት ጋር እንዴት ትንቀሣቀሳላችሁ ብሎ ይቀሰቅስ ነበር 25ኛ ተከሣሽ ከፊንጠባስና ከእኛ ጋር በመሆን የሰፈሩን ሰው ይበጥብጡ ነበር። ጀማል አብዱልቃድር የተባለውን የፀጥታ ዘርይ በቢላዋ ሊድሉተ ሲሉ ሩጦ ነው ያመለጠው አሉ አስረድተዋል።

20ኛ-- 76ኛየዐ/ሕግ ምስክር አደም ዩሱፍ ኢብራሂም በ34ኛ 29ኛ ተከሣሾች እና ጃፋር መሀመድ በተባሉ ላይ ካለ በኋላ 34ኛ ተከሣሽን በተመለተ ልመስከር አልመጣሁም ብሏል። 29ኛ ተከሣሽ እኔ የማውቀው ቀን ሰፈር ውስጥ አይታየም ሸርጡን ተሸፋፍኖ የኦነግ ተጠርጣሪ መሆኑን ነው የምናውቀው ሰዎች ሰብስቦ ወደ ኦነግ ለመቀየር ያነጋግረን ነበር ተብሎ ነው የተጠረጠረው ቢያንስ ይህን ስራ ለአንድ አመት ፈፅሞታል እኔ የቀበሌ ፀጥታ ሰራተኛ በመሆኔ በተለያየ መልኩ መረጃ ይደርሰኛል የኦነግ ደጋፊ ነው ተጠንቀቁት ተብሎ ይደርሰናል።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1152

21ኛ-- 75ኛየዐ/ሕግ ምስክር ዑስማን አደም ብሎ 34ኛ ላይ በበአወዳይ ከተማ 34ኛ ተከሣሽ ከኦነግ ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ ፖሊስ ታዛቢ ትሆናላችሁ ብሎ ወደ ቤቱ ሄደን ሁለት ካርቶን ከኒን ያልተከፈተ እና መድሃኒት ተገኝቷል። ይህንን መገኘቱን አውቃለሁ እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር የለም።

22ኛ-- 66ኛየዐ/ሕግ ምስክር አህመድ ሀሩን ከሊፋ 34ኛ እና 29ኛ ተከሣሾች ላይ 29ኛ ተከሣሽ ብዙን ጊዜ ቀን ቀን አይታይም ማታ ብቻ ነው የሚንቀሳቀሰው ። ከዚህ በፊት ሕዝቡን ያደራጃል ተብሎ ተጠርጥሮ ነበር። የመንግሥት ስብሰባ ቢጠራም አይመጣም። በጽ/ቤት ትእዛዝ በ1998 ዓ/ም ቤቱ ሲፈተሽ ነበርኩ ፍተሻው ያስፈለገው አባዎችን ያደራጃል ተንሎ ስለማጠረጠር ነው። ሲፈተሽ ግን ምንም አልተገኘም 29ኛ ተከሣሽ መተዳደሪያ የሚሆን ሥራ ሲሰራ አይታይም። 34ኛ ተከሣሽ ቤት ሲፈተሽ 2 ካርቶን ከኒን እና መድሬዎች ሲወጡ አይቻለሁ። መድሃኒቶቹ እንደተገኙ ለአባዎች ይልካል ተብሎ ተጠርጥሯል። ሌላ ደግሞ የሆነ የሥም ዝርዝር ያለበት ሰነድ አግኝተናል። 29ኛ ተከሣሽ ሰፈር ውስጥ ሲያደራጅ አይቻልሁ ከዛ በተሰበሰቡት እኛ የመንግሥት አካላት ስንመጣ ይተተናሉ። 29ኛ ተከሣሽ ይህንን መንግሥት አትስሙት በማለት ሕዝቡን ሲቀሰቅስ እስማለሁ የተለያዩ መረጃም ይደርሰናል።

23ኛ-- 36ኛየዐ/ሕግ ምስክር ዩሱፍ መሀመድ የተባለው ምስክር በችሎት 1ኛ ተከሣሾች እና 4ኛ ተከሣሽን ለይቶ ያሳየ ቢሆንም በሰጠው ምስክርነት ቃል በስም አውቃቸዋለሁ ባላቸው በመሀመድ ኑር እና አህመድ ሁስማኤል ላይ ቃሉን ሰጥቷል። በ1989 ዓ/ም ይመስለኛል በጉሎዳ ወረዳ ሚኖ በሚባል ቦታ ለመርመሪ ፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ እንዳዳመጣቸው በቃላቸውም መሀመድ ኑር ኡስማኤል የተባለው መጀመሪያ ላይ የሕዝባዊ ሚኒሻ እንደነበር ከዛ በፊት ፈረጋስ ለሚባል የኦነግ መሪ እጅን መስጠቱን ለኦነጉች ረዳት ሆኖ ከሕዝቦች እህልና ወተት እያመላለሰ እንደቆየ አስረድቷል ያሉ ሲሆን አህመድ ዑስማን ደግሞ ከኦነጎች ጋር ግንኙነት እንዳለውና አምስት ኮንታል እህል እና ወተተ ከሕዝቡ እየሰበሰበ ለእነ ብራስ ዳዲ ለተባሉ ኦነጎች እንደሚያቀብል እና በመንግሥት መታደር ተመቶ የቆሰሉትን ኦነጎችን ሌት ቀን አስታሞ 500 ብር እንደታከሙበት እንደሰጠ ቃሉን መስጠቱን አስረድቷል በችሎት ለይቶቸው ያሳያቸውን በተመለከተ ግን ምንም እንደማያውቅ ምስክሩ አስረድቷል። ቃላቸውን በሚጡበትም ወቅት የመገደድ ነገር የለም ብለዋል።

24ኛ-- 38ኛየዐ/ሕግ ምስክር በድሬ አብዱልከሪም በ67ኛ ተከሣሽ ላይ በቁንቢ ወረዳ ሚኖ ከተማ በፖሊስ ጣቢያ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ በቃሉም ከ1998 ዓ/ም እጅ እስከተያዘበት 2001 ዓ/ም ድረስ በኦነግ አባልነት እንዳገለገል ሲያስረዳ ነበር። ከፖሊስ ጋር በመሆን ከመኖሪያ ቤቱ ተቆጥሮ አንድ ታጣፊ ክላሽ 30 ጥይት ጋር ፣ አንድ ኤስ ኬ.ኤስ ከ4 ጥይት ጋር ሲገኝ አይቻለሁ። ይህም ሂደት በቪዲዩ ተቀድቷል በማለት አስረድቷል።

25ኛ-- 51ኛየዐ/ሕግ ምስክር ሞኔ አብዱላሂ 1ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች ላይ 1ኛ ፣14ኛ ተከሣሾች እና ፍጥሽ /8ኛ/ የተባሉት በኦነግ ተደራጅተው ሕዝቡን ይቀሰቅሱ ነበር ። የሆነ ቀን በ1998 ዓ/ም 1ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች ልጆችንን ፈተሽን መተህ አትሄድም ሲሉት ነበር። ከተማሪዎች ጋር የነበረ የመንግሥት ሚኒሻ የሆነው መሁዲ መሀመድ አብዱላሃን ሲከተሉት ነበር። ከዛ ትንሽ ቆይቶ ጥይት ሁለት ጊዜ ወደ ሰማይ ተተኩሶ ተበተኑ የተወሰኑ ሰዎች በሕግ ጥላ ውስጥ ሆኑ ከ1998 ዓ/ም በኋላም 14ኛ ተከሣሽ የአባዋ ሰራዊት መሆኑን ሰምቻለሁ 1ኛ እና ፈጥሽ ደግሞ ከሕብረተሰቡ ገንዘብ እየሰበሰቡ ለአባዋ ሰራዊቶች እንደሚያደርሱ አውቃለሁ 1ኛ ተከሣሽ ኦነግ ስለመሆኑ ከሕብረተሰቡ እና ከሰው ሰምቻለሁ።

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1153

26ኛ-- 63ኛየዐ/ሕግ ምስክር ሀሰን አወል በሰጠው የምስክርነት ቃል በ1ኛ ፣8ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች ላይ 1ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች በ1998 ዓ/ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰአት ላይ ቡርቃ ከተማ የመንግሥት ሚኒሻ ዘርፍ ሃላፊ የሆነው መሀዲ መሀመድን 40-50 የሚሆኑ ልጆች ጋር ሆነው የወያኔ መለከተኛ በማለት በድንጋይ ሲያበሩት እንዳየ አስረድቷል መሀዲ ፈትሽን ልጆችን እና ሰዎች እየሰበሰብሽ በመግሥት ላይ የምታነሳቸው ነገር ጥሩ አይደለም በማለቱ ነው በ1ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች እና ልጆች በድንጋይ ሲባረር የነበረው ፈትሽ በመንግሥት ላይ ረብሻ እንዲነስ ታደርግ ነበር። ተማሪዎችን ኦነግ መንግሥት ይሁን ይሀ መንግሥት ይውርድ እያላት ትቀሰቅስ ነበር። መሀዲ ሁለት ጥይት ወደ ሰማይ ከተኮሰ በኋላ ነው የተመለሱለት ከዚህ በኋላ 14ኛ ተከሣሾች የኦነግ መታደር ሆነ ሲባል ሰምቻለሁ 1ኛ ተከሣሽን ግን አላየሁትም ፡፡

27ኛ-- 22ኛየዐ/ሕግ ምስክር አደም መሀመድ በሰጠው ቃል 1ኛ፡11ኛ፣5ኛ፡14ኛ ተከሣሾች ላይ ከ1998 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም የኦነግ አባል ሆነው ሲንቀሳቀሱ ነበር ። 1ኛ ተከሣሽ ተማሪዎች ይቀሰቅስ ነበርና ሌንጀስ ወይም 11ኛ ተከሣሽ ደግሞ የኦነግ ሰራዊት ነበር ፣ 1ኛ ተከሣሽ ተማዎች ይቀሰቅስ ነበርና ሌንጅስ ወይም 11ኛ የኦነግ ሰራዊት ነበር መንግሥት አስተምሮ ወደ እሱ ከመጣው በኋላ አሁንም ተመልሶ በዛው እንቀስቅሴ ቀጠለ መንግሥት ምህረት ካደረገለት በኃላ የኦነግ ሰራዊቶች ሰው እዲገድሉ ወደ ከተማ አስገብቶቸው የሽጉጥ ጋር ቤቱ ተገኝተዋል። 5ኛ ተከሣሽ ደግሞ በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች በመንግሥት ላይ ተቃውሞ እንዲያነሱ ይደግ ነበር። ለምሣሌ ልጆች በመቀስቀስ ይሰበስብና ተቃውሞ እንዲወጡ ይደርግ ነበር ከዛ በኋላ ሲታወቅበት ጠፍቶ ወደ ኦነግ ሰራዊት ተቀላቀለ። በ2001 ዓ/ም ደግሞ በቁጥጥር ስር ዋለ ። 14ኛ ተከሣሽ ለኦነግ ሰራዊት ስር የተደራጀ ሲሆን ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር በመሆን ሚኒሻውን ተከትለው በድንጋይ ሊመቱት ነበር። በወቅቱ ያከተማው አስተዳደር በመሆኔ ይህንን ላውቅ ችያለሁ።

28ኛ-- 58ኛየዐ/ሕግ ምስክር ኢብራሂም አሜ በ1ኛ ፣5ኛ 1ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች ላይ ሲሆን 11ኛው ተከሣሽ የኦነግ አባል ሲሆን ቀብሮት የነበረውን ሽጉጥ አውጥቶ ሰጥቷል።የኦነግ አባል የነበረው ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በጉሎዳ በተባለ ቦታ ነው። 1ኛ፣5ኛ እና 14ኛ ተከሣሾች በት/ቤቶች ላይ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። 14ኛ ተከሣሽ ከተማ ውስጥ ተይዞ ታስሮ እንደነበር ከዛ በኋላ ደግሞ እንደተለቀቀ አውቃለሁ። 5ኛ ተከሣሽም የኦነግ ሰራዊት ሆኖ ሲያገለግል መያዙ እና ተከሣሽም የኦነግ ሰራዊት ሆኖ ሲያለግል መያዙ እና 1ኛ ተከሣሽ ታስሮ ተፈትቶ ለሁለተኛ ጊዜ በምን ምክንያት እንደገባ አላውቅም።

29ኛ-- 70ኛየዐ/ሕግ ምስክር መሀመድ ኢብራሂም በ26ኛ ተከሣሽ ላይ በ1998 ዓ/ም 26ኛ ተከሣሽ የመንግሥት ተቃዋሚ የነበረ ሲሆን ከአካባቢው ተሰውሯል ብለን ለአስተዳደር አሳውቀን ነበር። ተከሣሹ ይህንን መንግሥት እንደገፍም ይነበር የኦነግ ሰራዊት ሃሣብን ይደግፍ ነበር። በየቦታው በቤት ውስጥ ሰዎችን ሰብስቦ ጫት ይቃወም መንግሥትን ይቃወም ነበር። ለአስተዳደር ያሳውቅነል ኦነግ ገባ ጠፋ ብለን ነው። ከዛ ከቆይታ በኋላ ወደ ቀድሞው የሚሰራበት ቦታ ሲመለስ ተይዞ ተሃድሶ የተደረገለት ግን ተመለሰ ወደ ኦነግ ገባ።

30ኛ-- 29ኛየዐ/ሕግ ምስክር ዑስማን አደም በሰጠው የምስክርነት ቃል በ9ኛ እና 29ኛ ተከሣሾች ላይ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ድረስ የኦነግ ደጋፊዎች እንደሆኑ አውቃለሁ ሕዝቡንም እኛን የእዚህ የኢፓዴዩ ጀሌዎች ናቸው በማለት ይቀሰቅሱ ነበር። 22ኛ ተከሣሽ እዚህ ፍ/ቤት ቃላችንን ለመስጠት በምንመላለስት ወቅበት እዛ ሄዳችሁ ብትናገሩ ምንም አታመጡም እስቲ አንድ ነገር ብትናገሩ በማለት እንደዛተባቸው አስረድቷል።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

1154

ጀሌ ማለት ተከታይ ማለት ነው። 22ኛ ተከሣሽ እኔን እስከ መሣሪያህ ወደ ኦነግ ተመለስ ትለኝ ነበር። ተማሪዎችንም የኦፒዲዩ እንትን አትሁኑ ሀገሪቱ ኦነግ ነች የኦነግ አባል ሁኑ እያሉ ይቀሰቅሱ ነበር። 29ኛ ተከሣሽ ተሀድሶ ከወሰዱ በኋላ ተመልሰው የኦገግ አባል ሆኑ እያሉ ይቀሰቅሱ ነበር። 15ኛ ተከሣሽ ባሏ ኦነግ ነበር 15ኛ ተከሣሽ ራሶም የኦነግ አባል ነበረች 9ኛ እና 29ኛ ተከሣሾች ቅስቀሣዎችን ሲያደርጉ የነበሩት በአወዳይ ከተማ ውስጥ ነው 9ኛ ተከሣሽ ተሃድሶ ከወሰደ በኋላ ሰዎች ቅስቀሳ አድርጓል ሲሉ ሰምቻለሁ እንጂ ያየሁት ነገር የለም። ከተማሪዎች ጋር ስንቀሳቀስ የነበረው እና ያየሁት ኀደኛ ተከሣሹ ነው። 15ኛ ተከሣሽ የኦነግ አባል ከመሆኗ ውጪ ሌላ ያደረገችሉም ንግድ አላውቅም ።

31ኛ-- 69ኛየዐ/ሕግ ምስክር አህመድ አሊዩ አህመድ በሰጠው የምስክርነት ቃል በ26ኛ ተከሣሽ ላይ በወተር አካባቢ የ26ኛ ተከሣሽ ልጅ የኦነግ ወታደር ሆኖ ሲንቀሣቀስ ነበር ወደ ጫካም ገብቷል። ከዛ በኋላ ተመለሰ ተሃድሶ ተደርጉለታል የተሃድሶ ወረቀት ተሰጥቷል።

32ኛ-- 48ኛየዐ/ሕግ ምስክር ዩሱፍ በያን በ12ኛ ተከሣሽ ላይ ተከሣሹ በኦነግ ውስጥ ሆኖ ሊያደራጅ መጣ እኔ የኦነግ አባል ነኝ ስራችሁ እንዲህ እንዲህ ነው ብሎ አለ በኦነግ ሥር ተደርጅ አለን።

33ኛ-- 47ኛየዐ/ሕግ ምስክር በድሪ ሼክ ዑመር በ20ኛ ተከሣሽ በዛን ሰአት በፀጥታና ይትህ ዘርፍ ሲሰራ ከዛን የመጡ ሰዎች ተከሣሹን ሲመረመሩት በኦነግ ስር ተደብቀን ነበር አለ። በማለት አስረዱቷል።

34ኛ-- 41ኛየዐ/ሀግ ምስክር ዑመር አብዱላሂ አብዱመሊክ በ12ኛ እና በ21ኛ ተከሣሾች ላይ፡- በ1998 ዓ.ም 12ኛው ተከሣሽ አባዎ አባል አድርግሀለሁ ብሎኝ ነበር። የአባዎ አባል አልሆንም አልኩት 21ኛው ተከሣሽ ደግሞ በሰፊው ህዝብ ፊት የአባዎ አባል ነኝ በማለት ይቅርታ እንዲሰጠው ጠይቋል።

35ኛ-- 40ኛየዐ/ሀግ ምስክር ሜላ ከማል ከድር፡- 12ኛ እና 21ኛ ተከሣሾች ላይ፡- በ1998 ዓ.ም 12ኛ ተከሣሽ አባዎን ለማጠናከር ወደ እኛ መጥቷል። የመጣውም ሚዳጋ የሚባል ከተማ ነው። 12ኛ ተከሣሽ እናንተን ማደራጀት እፈልጋለሁ። አለን በአባዎ አባልነት አድራጃችዋለሁ አለን 21ኛ ተከሣሽም በ1995 ዓ.ም ለአበዎ አባልነት አደራጃችሁለሁ በማለት ስብሰባ ከርቶን ተሰብስበናል። ገንዘብ አዋጡ በማለትም ብር 5.00 ተቀብሎናል። ሁለቱም ተከሣሾች ይቅርታ ጠይቀዋል።

36ኛ-- 46ኛየዐ/ሀግ ምስክር ዑመር አብዱላሂ በ12ኛ፣13ኛ 16ኛ፣17ኛ፣18ኛ ተከሣሾች እና 19ኛ ተከሣሾች ፡- 12ኛ ተከሣሽ አባዎ አባል ነበር ተመልሶ ቀበሌ ገብቷል፣ በ2002 ዓ.ም ተመልሶ ሚንሻ ሆኗል። ከተከሣሹ ጋር አንድ ሀገር ስለምንኖር ይህንን አውቃለሁ። ከዚህም በኋላ ወደ አባዎ አልመለስም ሲል ነበር። 13ኛ ተከሣሽ እና 16ኛ ተከሣሽ ከ12ኛ ተከሣሽ ጋር አብረው ነው በአባዎ ውስጥ የተደራጁት 13ኛ እና 16ኛ ተከሣሾች አባዎች ከከተማ ጫት ግዙን ብለዋቸው የ10 ብር ጫት እንድንገዛላቸው ጠይቀውን ነበር። ከ16ኛ ተከሣሽ አባት ቤት በመከላከያ ተፈትሾ ሁለት ፍሬ ትናንሽ የአባዎ ባንዲራ ተገኝቷል። እንዲሁም 53 ፍሬ ጥይት ተገኝቷል። 17ኛው እና 18ኛ ተከሣሽ ደግሞ በፌዴራል ፓሊስ መውሰዳቸውን እንጂ ምንም የማውቀው ነገር የለም። 19ኛ ተከሣሽ ለአባዎ ተደራጅ ተብሎ ሀገር ታስሮ ነበር። ከተፈታ በኋላ ቤቱ ሲፈተሽ አንድ ሲሞንጃ ተገኝቷል። ሚኒሻ ከሆነ በኋላ ነው በፌዴራል የተወሰደው። በመንግስት ጦር እና ለኦነግ መሀከል በተነሳ ግጭት የተወሰነ የመንግስት ወታደር ሲሞት 32ኛ ተከሣሽ በመንግስት ወገን በኩል ነበር።

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

1155

37ኛ-- 80ኛየዐ/ህግ ምስክር፡- አሚን ጣሂር በ71ኛ ተከሣሽ በ2001 ዓ.ም ሌንጮ የሚባል የኦነግ ወታደር እና 71ኛ ተከሣሽ ጫት ካልገዛህልን ህይወትህን ታጣለህ ስላሉ ጫት ገዝቼላቸዋለሁ። ቦታው ደደር ነው። 71ኛ ተከሣሽም የኦነግ አባል ነበር።

38ኛ-- 83ኛየዐ/ህግ ምስክር፡- አብዱልዋሂድ መሀመድ ሼክ አብዱረሀማን 71ኛ ተከሣሽ ላይ የሆነ ቀን በጠዋት የአባል ወደ ሰፈር መጥቶ አንድ ላይ ሆነው ቁርስ አምጡ አሉን። 71ኛ ተከሣሽም ከኦነጐች ጋር አብሮ ነበር። ሌሎችን በደንብ መለየት ባልችልም በወቅቱ 71ኛ ተከሣሽ አሳይቸዋለሁ። በ1982 ዓ.ም የአባዎ ወታደር ነበር። ምግብ እንድናመጣ የጠየቀን ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም ነው።

39ኛ-- 84ኛየዐ/ህግ ከሊፍ ሼክ ዑመር አሊን፡- 71ኛ ተከሣሽ ላይ በ2001 ዓ.ም ሊነጋጋ ሲል ኦነጐች ወደ እኛ ሰፈር መጥተው በፊት አባዎች 10 ነበሩ ከዛ በኋላ 10 ተጨመሩበት 71ኛ ተከሣሽ አለ። ከመጡት ኦነጐች መሀከል ሌንጮ ይገኙበታል። 71ኛ ተከሣሽ የኦነግ ቁጥር በተመለከተ ሲናገር አብሮት ሊንጮ የሚባለው ኦነግ አብሮት ነበር። በጧትምት ቁርስ አምጡ አሉን ቁርስ ስናመጣም 71ኛ ተከሣሽ አብሮ ነበር።

40ኛ-- 22ኛየዐ/ህግ አደም መሀመድ ሐረዌ በ58ኛ ተከሣሽ ብርቄ ዲምቱ የሚባል አካባቢ ውስጥ ተከሣሹ 7 ሰዎች አስገብቶ በአባዎ ተደራጅቶ ይንቀሳቀስ ነበር። አምስት ብር መዋጮ ለአባዎ ይሰባሰቡ ነበር። ይህንን ላውቅ የቻልኩት በሰኔ ወር በአካባቢው ወረዳ ፖሊስ መምሪያ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቼ ነበር ቃሉን የሰጠውም ሳይገደድ ነው። ቃሉን ሊሰጥም ቤሊሳ እና ቢረሳ አደራጅተውን ነው ሲል ነበር ብሏል።

41ኛ-- 25ኛየዐ/ህግ ምስክርም ሼክ ሀሰን ደርጋ ቦሩ በ55ኛ ተከሣሽ ላይ፡- በጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም ዲሞቱ በሬዳ የሚባል ወረዳ 55ኛ ተከሣሽ የኦነግ ፓርቲ አባል ሲል ከኦነግ ወታደር ጋር በመሆን ተኩስ ከፍቶብናል።ተከሣሹ በፖሊስ ሲያዝ ሸሽቶ ከኦነግ ወታደሮች ጋር ተቀላቅሏል። በተኩስ ልውውጥ ውስጥ በኦነግ ወገን ነበር። ተከሣሹ ከፖሊሶች አምልጦ ወደ ኦነግ በኩል ባለው ተኩስ ተቀለቅሏል።

42ኛ የዐ/ህግ ምስክር፡- በ40ኛ እና 70ኛ ተከሣሾች ላይ ተከሣሾቹ በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ በህዝቡ ፊት ተደራጅተን አባዎ ሆነናል፣ ይቅርታ ይደረግልን አሉ። ከመያዛቸው በፊት በ1997 ዓ.ም ከተማሪዎች ጋር በመሆን ረብሻ ለማስነሳት ሲሟከር እንደነበር መረጃ አለን። እንደዚህ የሚሉት በረብሻ ምክንያት በኦነግ ሴል ውስጥ ተደራጅተን ተማሪዎች ረብሻ እንዳነሱ አደርገናል። ብለው ህዝቡን ይቅርታ ጠይቀዋል። ተከሣሾች ተማሪዎችን አደራጅተናል በሚልም ተናጋግረዋል ይቅርታ ካደረጉ በኋላ በ3ኛው ቀን ተፈተዋል። ከዛ በኋላ በምን ጉዳይ እንደታሰሩ አላውቅም።

